# መግቢያ

የአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 ራሱን በራሱ እንደሚያስተዳድርና ዝርዝሩም በሕግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡

ይህን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የከተማ አስተዳደሩ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1996 እንዲቋቋም ተደርጓል በዚህ ቻርተር አዋጅና ማሻሻያዎቹ ነዋሪውን እያስተዳደረ ይገኛል፡፡

አስተዳደሩ በቻርተር አዋጅ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ የሕግ አውጭነት፣ የሕግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ሥልጣኖች ይገኙበታል፡፡ በሕግ አውጭነት ሥልጣኑ ያወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦችና እና መመሪያዎች ለነዋሪውና ለአገልግሎት ተጠቃሚው ተደራሽ ባለመሆናቸው ነዋሪው ወይም አገልግሎት ተጠቃሚው መብቱን ለማስከበርና ሕግና ሥርዓትን ለማስፈን የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዳያበረክት፣ የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዳያውቅና እንዳይወጣ አድርጎታል፡፡

በሕግ አስፈፃሚነቱ በከተማ አስተዳደሩና በፌዴራል መንግሥት የወጡ ሕጎችን ከማስፈፀም አንፃር ምሉዕ አላደረገውም፡፡ ከዳኝነት ጋር ተያይዞ ፍትሕን ለማረጋገጥ ሕጎቹ በቀላሉ የማይገኙ በመሆናቸው ፍርድ ቤቶች አገልግሎት ተጠቃሚው ሕጎቹን እንዲያቀርብ ሲጠይቅ ይስተዋላል፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የከተማ አስተዳደሩ በሥልጣን ወሰኑ አስተዳደራዊ፤ ፍትሕ፤ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ነክ መብቶቹን ለማልማት ያወጣውን አዋጅ፣ ደንብ እና በፌዴራል መንግሥት ወጥተው ዕለት ተዕለት የሚያስፈፅማቸውን በመፅሐፍ መልክ በማዘጋጀት አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ በድህረ-ገጽ በመጫን እንድትጠቀሙና በየጊዜው ወቅታዊ ስለምናደርጋቸው ድህረ-ገፁን እንድትጉበኙ እንጋብዛለን፡፡

በዚህም ቅጽ ሁለት የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ህጎችን ያካትታል፡፡ በህጎች ስብስብ ላይ ማንኛውም ቢካተቱ የሚሏቸው እንዲሁም ማንኛውንም ሃሳብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## ማውጫ


መግቢያ....................................................................................................................1

ቅፅ ሁለት .................................................................................................................4

ማህበራዊ እና ኢኮኖሚ ነክ ህጎች..................................................................................4

የከተማውን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ “ኢትዮጵያ ትቅድም ” ፺፯/፲፱፻’፺፯ ........5

የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፰/፪ሺ.ህ፪.................................................21

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የመዝናኛ ግብር ደንብ ፪፻፺፩/፲፱፻፶፯.....................29

የአዲስ አበባ የውሃ አቅርቦት እና የፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፬ ማሻሻያ ደንብ............31

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ፵፬/፪ሺ.፬...........................35

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩ ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፲፱/፲፻፺፯ .................................................................................................43

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት ደንብ ፲፪/፲፱፻፺፯ ..................................57

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሃላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ29/1999 .....................................................................60

የከተማው አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ኃላፊነታቸውን አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ) ፳፱/፲፱፻፺፱ ........................................................................61

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሃላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ 5/2000 ......................................................................63

የከተማው አስተዳዳር ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ለማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ ሺ ዓ.ም. ..................................................64

የአዲስ አበባ መዋቅራዊ ፕላን አዋጅ ቁጥር ፶፪/፪ሺ.፱.................................................................66

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ የወጣ ደንብ ፵፱/፪ሺ.፬......................83

የክልል 14 መስተዳድር የከተማ ቦታ በኪራይ ባለ ይዞታነት እና የኪራይ ተመንን ለመወሰን የወጣ ደንብ...........115

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሪል እስቴት ቦታ አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺፰ ዓ.ም...........................121

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገወጥ የመሬት ይዞታ መስፋፋትና ህጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታ ለመከላከል የወጣ ደንብ ፲፩/፲፱፻፻፺፯.................................................................124

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስተካከል እና ለመከላከል የወጣ ደንብ ፰፫/፪ሺ.፯ .........................................................................134

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፫/፪ሺ.፰ ..........................................................................................................151

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አንበሳ የከተማ አዉቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፻፬/፪ሺ.፲157

የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ፻፰/፪ሺ.፲፩............159

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 13/2001........................................163

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር 14/1991ዓ/ም.......................................................168

ደንብ ቁጥር ፳፬/፲፱፻፺፫ ዓ.ም ........................................................................................................182

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሕዝብ ት/ቤቶችን አመራር አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ....................182

የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ሥያሜና የአድራሻ ሥርዓት ደንብ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፯ ...........................................190

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የስጋ ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር ፺፮/፪ሺ፲ ዓ.ም ...........................................................................................................................197

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ፤አስተዳደርና አመራር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺህ፭ ዓ.ም. ...........................................................................................................................................204

የአዲስ አበባ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ዓ.ም ............................217

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፩/፲፱፻፺፰ .........................................................................................................................................229

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ፶፯/፪ሺ፮ .........246

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፳/፪ሺ፮ ..............................................................................................................................259

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ......................296

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፬ .......................313

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ፵፮/፪ሺ፬ ......................................................319

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ፵፮/፪ሺ፬ ......................................................326

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮርያ ዘማቾች መታሰቢያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞች የልህቀት ማዕከል ለማቋቋም፤ አደረጃጀትና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፪፩/፪ሺ፲ .................................330

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ትረስት ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ፪፮/፪ሺ፲፩ .................................335

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ፪፲/፪ሺ፲፪ ..........342

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፓሊታን ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ፪፲፬/፪ሺ፲፩ ...................................................................................................................346

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፳/፪ሺ፲፪ .....................349

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ የአሰራር ደንብ ፪፲፪/፪ሺ፲፪.................................355

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንደርን ማዕከል ያደረገ አሳታፊ አስተዳደር ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ፪፲፫/፪ሺ፲፪ ...................................................................................................................................363

## ቅፅ ሁለት

## ማህበራዊ እና ኢኮኖሚ ነክ ህጎች

# <u>የከተማውን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣ አዋጅ "ኢትዮጵያ ትቅድም " ፵፯/፲፱፻'፯</u>

በየከተማዎቹ ውስጥ የሚገኙት ፋብሪካዎች፣ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም በየከተሞች ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርቶ የሚገኘው የከተማው ወዝ አደርና ለፍቶ አዳሪው በኀብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው የኑሮ ደረጃ፣ ሰብአዋ መብቱ፣ ክበሩና ማዕረጉ የሚወሰነው የሚኖርባት ከተማ በምሰጠው የመኖርና የመስራት ዕድል በመሆኑ፣

በከተሞቻችን ውስጥ አብዛኛዎቹ ቦታዎችና ቤቶች በጥቂት መሳፍንት ፣መኳንንት ፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኞችና በከበርቴዎች በመያዛቸው፣ እነዚህም የሀብታም ክፍሎች ያላቸውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኃይል ያለአግባብ በመጠቀም ሰው ሠራሽ የከተማ ቦታ እጥረት በመፍጠር የከተማ ቦታ ዋጋን እንዲወደድ በማድረግ፣ በጠቅላላው የብዝበዛ ሥርዓት ጠንክሮ ለከተማው እድገትና ለብዙኃኑ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ የኑሮ መሻሻል ከፍተኛ እንቅፋት በመሆናቸው፣

ለመኖሪያ የሚያገለግልም ሆነ ለመሥሪያ የሚሆነው የከተማው ቤት በጥቂት ሰዎች እጅ መሆኑ የቤት ኪራይ ቁጥ ብለው ሳየለፉ በማግኘት ሰፊ ብዝበዛ እንዲፈጽሙ ከማስቻሉም በላይ ፣ ከእነዚህም መካከል ከሕግ በላይ ሆነው ለብዙ ዘመናት የግብር ክፍያ ግዴታቸውን እንዳያሟሉ ስላደረጋቸው፣

በከተማ የሚኖረው ወዝ አደርና ለፍቶ አዳሪው ለረጅም ዘመን ግፍና ጭቆና እየተፈጸመበት ለገዥ መደብ ቅንጦትና መንደላቀቅ መሣሪያ በመሆን ፣ የጭቆና አገዛዝ ተጭኖት የኢትዮጵያዊነቱን መብት ተገፍፎ ለብዙ ዘመን አጥቶት የነበረውን አገሩ በእኩልነት ልትሰጠው የሚገባውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሶሻል መብቱን እንዲገናጸፍ ለማድረግ፣ የሚኖርባት ከተማ የምትሰጠውን ማንኛውንም ዕድል በእኩልነት እንዲያገኝ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በቤት ኪራይ ላይ ቁጥጥር ባለመኖሩ ኪራይ በየጊዜው እየኖረ በመሄዱ፣ የሰፊው የከተማ ሕዝብ ኑሮ በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ በመውደቁ፣

ከተሞቻችን ለብዙኃኑ የከተማ ነዋሪ ህዝብ ለመኖሪያው ሆነ ለመሥሪያ እንዲመች አድርጎ በፕላን ለመቀየስ እንዲቻል፣

ከዚህ በፊት ከየባንኮችና ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች የመበደር ዕድል የነበረው ክፍል ቤትና ቦታ ዋስትና ለመስጠት የሚችል ብቻ በመሆኑ፣ በሲፊው የከተማ ሕዝብ ይህንን ጠቃሚ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ባለመቻሉና ይህንንም የመበደር መብት ሰፊው ሕዝብ እንዲያገኘው ለማድረግ፣

በከተማ የሚኖረው ሰፊ ሕዝብ ከከፍተኛ የኪራይ ሸክም በማዳን፣ አስፈላጊውን የብድር ዕርዳታና ለመኖሪያም ሆነ ለመሥሪ ቤት መሥሪያ የሚሆነውን ቦታ በመስጠት የኑሮውን ሁኔታ በማሻሻል ለአገሩ፣ ለወገኑ፣ ለቤተሰቡና ለራሱ በልበሙሉነት እንዲሰራ ለመድረግ፣

ከተሞቻችንን በዕቅድና በጥናት እንዲሰሩ ማድረግ የአገሪቱ ሀብት በሚገባ በቁጠባ ጥቅም ላይ እንዲውል ፣ የከተማን ሁኔታ ለማሻሻል ፣ ነዋሪውን ከበሽታ ለማዳንና በከተማ የሚፈጸሙትን ሕገ ወጥ ተግባሮች ለማጥፋት የሚያስችል መሆኑን በማመን፣

የከተሞቻችን ቦታና ቤት ይዞታ በፍርድ ቤቶች በኩል ያስከተለውን ማለቂያ የልለው ክርክር በማስቀረት ሀብትና ጉልበት እንዳይባክን ለማድረግ፣

በከተሞቻችን ውስጥ ማደሪያና መጠጊያ ሊያገኙ ላልቻሉት አስፈላጊ ዕርዳታዎች መስጠት ለመጀመር ፣

በከተማው ሕዝብ መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ ሀብትና ገቢ እንዲኑም አገልግሎት አጥጋቢ በሆነ ሄታ በማደላደል አሁን ያለውን ከፍተኛ የኑሮ መራራቅ ለማቅረብ ፣ ያንዱ ይወክላልፅግና በሌላው መቆርቆዝ ላይ እንዳይመሠረት ለማድረግ እንዲቻል የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ንብረት እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፷፮ ዓ.ም በአንቀጽ ፮ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጅዋል።

<u>ምዕራፍ ፩</u>

<u>መግቢያ</u>

፩፣ <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ አዋጅ "የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፷፮ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።"

፪፡ <u>ትርጓሜ፣</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "የከተማ ቦታ" ማለት በማዘጋጃ ቤት ወይም በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ነው።

፪/ "የከተማ ቤት" ማለት ተሠርቶ ያለቀ ወይም በጅመር ላይ ያለ ለመኖሪያ፣ ለሥራ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚውል ቤት ነው።

፫/ "ትርፍ ቤት" ማለት ፡-

ሀ) አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ከሚያስፈልገው ወይም ከያዘው ከአንድ መኖሪያ ቤት በላይ ወይም

ለ) አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹ ወይም በኃላፊነቱ ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች ለመኖሪያ ቤት ከሚያስፈልገው ወይም ከያዘው በላይ፣ ወይም

ሐ) አንድ ቤተሰብ፣ ከግለሰብ ወይም ድርጅት ለሥራው ከሚያስፈልገው መሥሪያ ቤት በላይ፣ የሆነ የኪራይ ገቢ ወይም ሌላ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ያለጥቅም የተያዘ የከተማ ቤት ነው፡፡

፬. "የመኖሪያ ቤት" ማለት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለራሱ ወይም አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹ ወይም በኃላፊነቱ ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች መኖሪያ የሚያውለው የከተማ ቤት ነው፡፡

፭. "የመሥሪያ ቤት" ማለት አንድ ቤተሰብ ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለሥራ የሚጠቀምበት የከተማ ቤት ወይም የከተማ ቦታ ነው፡፡

፮. "አከራይ" ማለት ከከተማ ቦታ ወይም ቤት ኪራይ የሚገኝ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፡፡

፯. "ተከራይ" ማለት ኪራይ እየከፈለ በሌላ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታ ወይም የከተማ ቤት የሚጠቀም ነው፡፡

፰. "ደባል" ማለት በአንድ የመኖሪያ ቤት ውስጥ አብሮ እየኖረ ለአከራዩ ወይም ለተከራዩ ኪራይ የሚከፍል ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ነው፡፡

፱. "ጭሰኛ" ማለት ኪራይ እየከፈለ ወይም አገልግሎት እየሰጠ በሌላ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታ ላይ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ቤት በመሥራት ወይም ሌላ አገልግሎት በማዋል የሚጠቀም ነው፡፡

፲. "ኪራይ" ማለት የከተማ ቦታን ወይም የከተማ ቤትን በማከራየት የሚገኝ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ነው፡፡

፲፩. "የወለድ አግድ ይዞታ " ማለት በዕዳ ዋስትና በአበዳሪ ወይም በውል በተጠቀሰው ሰው የተያዘ የከተማ ቤት ወይም የከተማ ቦታ ነው፡፡

፲፪. "የመጠቀም መብት" ማለት የከተማ ቦታን ማውረስን ፣ በስጦታ ማስተላለፍን ፣ በዕዳ ማስያዝን ወይም መሸጥን የማይጨምር በግል የመጠቀም መብት ነው፡፡

፲፫. "ድርጅት" ማለት በንግድ ሕግ ፣ በፍትሐ ብሔር ሕግ የተቋቋመ ድርጅትና እንዲሁም በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፺፰ የተመለከተው ድርጅት ነው፡፡

፲፬. "የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር" ማለት በዚሁ አዋጅ በምዕራብ ፰ መሠረት የሚቋቋም ማኅበር ነው፡፡

፲፭. "ሚኒስትር" ማለት የሥራና የቤቶች ሚኒስትር ነው፡፡

፲፮. "ሚኒስቴር" ማለት የሥራና የቤቶች ሚኒስቴር ነው፡፡

፲፯. "የከተማው ቦታና ቤት ነክ ክርክር" ማለት በከተማ ቤት ላይ የንብረትነት የማውረስን የይዞታን ፣ የኪራይን ወይም የመጠቀም መብት የሚመለከት ክርክር ነው፡፡ እንዲሁም የከተማ ቦታ ይዞታን ክርክርም ይጨምራል፡፡

<u>ምዕራፍ ፪</u>

<u>ስለ ከተማ ቦታ</u>

የከተማ ቦታ የመንግስት ስለማድረግ

ይህ አዋጅ ከጸናት ቀን ጀምሮ የከተማ ቦታ የመንግስት ንብረት ሆኗል፡፡

ማንኛውንም ቤተሰብ ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት የከተማ ቦታን በግል ባለሀብትነት ለመያዣ አይችልም፡፡

ለከተማ ቦታ ካሣ አይከፈልም፡፡

የከተማው ቦታ ማስተላለፍ ስለመከልከሉ፣

፩/ የከተማ ቦታ ሊሸጥ፣ በወለድ አግድ ሊሰጥ ወይም በዕዳ ሊያዝ ፣ በውርስ ወይም በሌላ መንገድ ሊተላለፍ አይችልም፡፡

፪/ ከታህሳስ ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ የከተማን ቦታ በስጦታ፣ በውርስ ፣ በጭሰኝነት ፣ በሽያች ወይም በሌላ መንገድ ለማስተላለፍ የተደረገ ተግባር ወይም ውል ተሽሯል፡፡

የይዞታ መጠን ስለመወሰን

፩/ አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ የሚያውለው እስከ አምስት መቶ (፭፻) ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማ ቦታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በይዞታ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ባለይዞታው ሲሞት የሚች ሚስት ወይም ባል ወይም ልጆች በይዞታው ተተክተው የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ እንደ ድርጅት ለመኖሪያ ቤት ወይም ለመሥሪያ ቤት መሥሪያ የከተማ ቦታ እንደሰጠው ሲያመለከት ሚኒስቴሩ አስፈላጊነቱን ሲያምንበት መጠኑን በሚወስነው መሰረት በይዞታ ሊሰጠው ይችላል

፫/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት፣ ለመሥሪያ ቤት ወይም ለሰራተኞች መኖሪያ ቤት መሥሪያ እንዲውል በግለሰብ፣ በቤተሰብ ወይም በድርጅት የተያዘ የከተማ ቦታ መጠን በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

፩. ስለከተማ ቦታ ጭሰኛ ይዞታ

፩/ በከተማ ባለርስትና በከተማ ጭሰኛ መካከል ያለው ግንኙነት ፈርሷል፡፡ ጭሰኛው ለከተማ ባለርስት ከሚከፍለው ኪራይና ሌላ ክፍያ እንዲሁም ከማንኛውም አገልግሎት ዕዳ ነፃ ሆኗል፡፡

፪/ በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ(፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፭ ንዑስ  አንቀጽ (፩) በተመለከተው የይዞታ መጠን ማንኛውንም ጭሰኛ በያዘው የከተማ ቦታ ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል፡፡

፯፣ የይዞታ ቅድሚያ ወይም መብት ስለመስጠት፣

፩/ የ/ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ ያለው ቤተሰብ፣ ወይም ግለሰብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ከሌላ በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፭ ንዑስ (፩) በተመለከተው የይዞታ መጠን በቦታው ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል፡፡

፪. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ ለመግዛት በቅድሚያ በሙሉም ሆነ በከፊል ገንዘብ የከፈለ ማንኛውንም ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ከልለው ከአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የይዞታ መጠን በዚሁ ቦታ ላይ የይዞታ ቅድሚያ ይኖረዋል።

፫. በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና በአንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ ያለ ድርጅት በቦታው ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል እንዲሁም ለመግዛት በቅድሚያ በሙሉም ሆነ በከፊል ገንዘብ የከፈለ ማንኛውንም ድርጅት የይዞታ ቅድሚያ ይኖረዋል።

፰፣ <u>የከተማ ቦታ መልሶ ስለመውሰድ ፣</u>

፩. የከተማ ቦታ የያዘ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሚኒስቴሩ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ ካላዋለው ሚኒስቴሩ ቦታው መልሶ በመውሰድ አስፈላጊ በመሰለው ጥቅም ላይ ያውለዋል።

፪. በቤተሰብ ፣ በግለሰብ ፣ ወይም በድርጅት የተያዘ የከተማ ቦታ መንግስት ለህዝብ አገልግሎት ለማዋል የሚያስፈልገው ሲሆን ሚኒስቴሩ ንጣፍ እየሰጠ ቦታውን ሊወስድ ይችላል።

፱. <u>ስለከተማ ቦታ ኪራይ ፣</u>

ማናቸውም ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት በያዘው የከተማ ቦታ መንግስት በሚወስነው መሠረት የከተማ ቦታ ኪራይ ይከፍላል።

፲. <u>በከተማ ክልል ውስጥ ስለተተከሉ ዛፎች ፣</u>

በከተማ ውስጠ በአንቀጽ ፫ ከተጠቀሰው የቦታ መጠን ውጪ የተተከሉ ዛፎች የመንግስት ንብረት ሆነዋል።

<u>ምዕራፍ ፫</u>

<u>ስለ ከተማ ቤት</u>

፲፩፣ <u>የመሥሪያ ቤትና የመኖሪያ ቤት ስለመያዝ፣</u>

፩. አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በሚመርጥበት አንድ ከተማ ብቻ አንድ የመኖሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

፪. መንግስት በሚወስነው መሠረት አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹ ወይም በኃላፊነት ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች ለመኖሪያ የሚሆን ቤት ሊኖረው ይችላል።

፫. አንድ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንደሥራው ሁኔታና ዓይነት መንግስት በሚወስነው መሰረት የመስሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

፬. መጠኑን መንግስት በሚወስነው መሠረት ፣ ማናቸውም መኖሪያ ቤት ወይም መሥሪያ ቤት ያለው ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ግብር ይከፍላል።

፲፪፣ <u>የከተማ ቤት ስለማስተላለፍ</u>

፩. አንድ ቤተሰብ ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት በከተማ ቤቱ የመጠቀም ወይም ይህንኑ ቤት የማውረስ ፣ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት አለው፡፡ ሆኖም ሽያጭ ከሆነ መንግሥት የግዥ ቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡

፪. ከታህሳስ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ የከተማን ቤት በንብረትነት የያዘ ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት መብቱ በሚኒስቴሩ ካልፀደቀለት በስተቀር ንብረትነቱ አይጸናለት፡፡ሚኒስቴሩም ንብረትነቱን የሚያጸድቀው የዚህ አዋጅ ዓላማ የማይቃረን ሆኖ ሲያገኘው ብቻ ነው፡

፲፫፣ የከተማን ትርፍ ቤት የመንግስት ስለማድረግ

በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፳) ፣ (፪) እና (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዘጋጃ ቤት ወይም በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ትርፍ ቤት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ የመንግስት ንብረት ሆኗል፡፡ ማንኛውም ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ያለውን ትርፍ የመኖሪያ ቤትና የመንግሥት ቤት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀን ውስጥ ለሚኒስቴሩ የማስታወቅ፣ የማስመዝገብና ፣ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

፲፬. ከመንግሥት ስለተወሰዱ ቤቶች ፣

የመንግስት ወይም ቀድሞ የጠላት ንብረት የነበሩ ወይም በህዝብ ወይም በመንግስት ገንዘብ የተሰሩ ቤቶች በግል ቤተሰቦች ወይም ግሰሰቦች ወይም ድርጅቶች በስጦታ ወይም በማይመጣጠን አነስተኛ ዋጋ የተሸጡ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጡ ቤቶች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የመንግስት ንብረት ሆነዋል፡፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ ለሶስተኛ ወገኖች ቢተላለፉም ቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተወሰደ ቤት ለሶስተኛ ወገን የተላለፈ ከሆነና ሶስተኛውም ወገን የከፈለው ገንዘብ ከቤቱ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ካልሆነ ትርፍ ቤት ከልለው ልዩነቱን ለመንግስት ከፍሎ የቤቱን ንብረትነት ሚኒስትሩ ሊያፀናበት ይችላል፡፡

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) መሠረት የተወሰደው ቤት ለሦስተኛ ወገን የተላለፈ ከሆነ፣ ሦስተኛውም ወገን የከፈለው ገንዘብ ከቤቱ ዋጋ ተመጣጣኝ ከሆነና ቤቱም ትርፍ ካልሆነ ሚኒስትሩ የቤቱን ንብረትነት ሊያጸናለት ይችላል፡፡

ማንኛውንም ሰው የከተማን ቤት ከመንግስት በስጦታ ወይም በማይመጣጠን አነስተኛ ዋጋ ወስዶ በመሸጥ የተጠቀመና ቤቱም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ከገዢው ያልተወረስ እንደሆነ ሻጩ ዋጋውን ለሚኒስቴሩ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፲፭፣ ለአካለ መጠን ባልደረሰ ሰው የተያዘ ቤት፣

ከወላጅ ፣ከአስተዳዳሪው ወይም ከአሳዳሪው ጋር የሚኖር ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው የሚያከራየው ወይም ሊያከራይ የሚችለው የከተማ ቤት የመንግስት ንብረት ሆኗል፡፡ ሆኖም ወላጅ የራሱ ከተማ ቤት ከልለው ለአካለ መጠን ያልደረሰው ሰው በአንቀጽ ፲፩ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው መብት መጠቀም ይችላል፡፡

፲፮. <u>ወደግል ቤት ስለመመለስ፣</u>

የራሱ የከተማ ቤት እያለው በማናቸውም ሁኔታ በሌላ ቤት የሚኖ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ወደ ግል ቤቱ ወይም ከአንድ የከተማ ቤት በላይ ያለው ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ወደ ሚመርጠው ቤት ለመመለስ መብት አለው። ሆኖም ቤቱ ለመሥሪያ ቤትነት አስፈላጊ መሆኑን ወይም ከአንድ ቤተሰብ በላይ በመኖሪያ ቤትነት ለማስፈር የሚችል መሆኑን ሚኒስቴር ሲያረጋግጥ ይህ ንዑስ አንቀጽ ተፈፃሚነት አይኖረውም። ቤቱንም መንግሥት ይወርሰዋል።

በወለድ እግድ በልለ ሰው የተያዘ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የመሥሪያ ቤት ያለው ሰው፣ ሌላ መሥሪያ ቤት የልለው ከሆነ የሚሠራው ሥራ ሕጋዊ ፈቃድ ይህ ወደ ሚመርጠው ቤቱ ለመግባት መብት አለው። ሆኖም ቤቱ በመሥሪያ ቤትነት ለማገልገል የማይችል መሆኑን ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ ይህ ንዑስ አንቀጽ ተፈፃሚነት አይኖረውም ቤቱንም መንግስት ይወርሰዋል።

በዚህ አንቀጽ ንዑስ  አንቀጽ(፬) የተወሰነውን ማስጠንቀቂያ በመስጠት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በደባልነት የሚያኖረውን ተከራይ የማስለቀቅ መብት አለው።

በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ(፫) ወይም (፪) መሠረት ወደ ከተማ ቤቱ ለመመለስ የሚፈልግ ማንኛውንም ሰው ቤቱን ለያዘው ሰው በጽሁፍ ከስድሰት ወር ጊዜ ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

በአንቀጽ ፫ ንዑስ  አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፫፩ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣(፫) እና (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራዩ ቤቱን እስካስረክብ ድረስ የቤቱን ኪራይ የሚከፍለው ለሚኒስቴሩ ወይም ለከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበር ነው።

አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በሥራ ምክንያት አዘወትሮ ከሚኖርበት ከተማ የለቀቀ ወይም የተዛወረ እንደሆነና ቀድሞ በሚኖርበት ከተማ የራሱ መኖሪያ ቤት ለው ከሆነ፣ በመልቀቁ ወይም በመዛወሩ ምክንያት ቤት ለመከራየት የሚያስከትልበትን ችግር ማስወገጃ እንዲሰጠው ሲያመለክት ሚኒስቴሩ ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የቤቱን አስተዳደር ተረክቦ እንደአካባቢው የኑሮ ሁኔታ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት ወይም ወጪ እየሰጠ በሚመለስበት ጊዜ ቤቱን መልሶ ያስረክበዋል።

፲፯. <u>በወለድ እግድ ስለተያዙ ቤቶች፣</u>

ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ቤትን በሚመለከት ረገድ የወለድ እግድ ውል ተሽሯል።

በወለድ እግድ የከተማን የመኖሪያ ቤት ፣ ወይም የመሥሪያ ቤት የያዘ አበዳሪ በቤቱ በመጠቀም ወይም በማከራየት ያገኘው ጥቅም ከአበደረው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ወይም የሚበልጥ ሆኖ ከተገኘ፣ ተበዳሪው ከዕዳ ነፃ ይሆናል።

በወለድ እግድ የተያዘ የመኖሪያ ወይም የመሥሪያ ቤት በአንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ለባለቤቱ የሚመለስ ወይም በትርፍ ቤትነት በመንግስት የሚወረስም ቢሆን አበዳሪው ላበደረው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ያላገኘ ከሆነ ቀሪውን ሂሳብ ከተበዳሪው የማስከፈል መብቱ የተጠበቀ ነው።

፲፰፣ <u>ለተወረሱ ትርፍ ቤቶች ካሣ ስለመክፈል</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት ለተወረሱ ቤቶች መንግስት ተገቢውን ካሣ ይከፍላል፡፡

ከነሀሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በኃላ ላለው ጊዜ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተከፈለ ኪራይ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተወረሱ ቤቶች የሚከፈል ካሣ ይቀነሳል፡፡

በአንቀጽ ፲፬ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለተወረሱ ቤቶች ካሣ ወይም ኪሣራ አይከፈልም፡፡

፲፱፣ <u>የከተማ ቤት ለሕዝብ አገልግሎት ስለማስለቀቅ</u>

በግለሰብ፣ በቤተሰብ ወይም በድርጅት የተያዘ የከተማ ቤት መንግሥት ለህዝብ አገልግሎት ለማዋል የሚያስፈልገው ሲሆን ካሣ ከፍሎ ቤቱን ሊወሰድ ይችላል፡፡

<u>ምዕራፍ ፬</u>

<u>ስለ ኪራይ</u>

፳፣ <u>ስለቤት ኪራይ፣</u>

ከነሀሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ካልሆኑ በስተቀር ማናቸውም ቤተሰብ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ከከተማ ቤትና ከከተማ ቦታ የኪራ ገቢ ሊያገኝ አይችልም፡፡

ከነሀሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ በአከራይና በተከራይ መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጧል፡፡ ሆኖም የተከራዩ ግንኙነት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ከሚኒስቴሩ ወይም ከከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ጋር ይቀጥላል፡፡

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረገ ማንኛውንም የኪራይ ውል ጊዜው ከታህሳስ ፳፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በፊት የሚያልቅ ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ከተከራዩ ጋር አዲስ ድርድር ለማድረግ ይችላል፡፡

ኪራይን የሚወሰን ደንብ እስከወጣ ድረስ ኪራያቸው ከ፫፻ ብር የማይበልጥ የከተማ መኖሪ ቤቶችና መሥሪያ ቤቶች ኪራይ ከነሀሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ በሚከተለው መጠን ተቀንሷል፡፡

ሀ/ በወር እስከ ፳፭ ብር ለሚከፍሉ ፶

ለ/ በወር ከ፳፭ ብር በላይ እስከ ፶ ብር ለሚከፍሉ ፵ በመቶ፡፡

ሐ/ በወር ከ፶ ብር በላይ እስከ ፶፻ ብር ለሚከፍሉ ፵ በመቶ፡፡

መ/ በወር ከ፳፻ ብር በላይ እስከ ፩፻፶ ብር ለሚከፍሉ ፳፭ በመቶ፡፡

ሠ/ በወር ከ፩፻፶ ብር በላይ እስከ ፪፻ ብር ለሚከፍሉ ፳ በመቶ፡፡

ረ/በወር ከ፪፻ ብር በላይ እስከ ፫፻ ብር ለሚከፍሉ ፫፭ በመቶ፡፡

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፬) በተመለከተው መሠረት በወር፣

ሀ/ እስከ ፩፻ ብር የሚከራዩ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ወይም መሥሪያ ቤቶች ኪራይ የሚሰበሰበውና ጠቅላላ የቤቶች አስተዳር የሚካሄደው በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ኃላፊነት ነው።

ለ/ ከ፩፻ ብር በላይ የሚከራዩ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ወይም መሥሪያ ቤቶች ኪራይ የሚሰበሰበውና ጠቅላላ የቤቶቹ አስተዳደር የሚካሄደው በሚኒስቴሩ ኃላፊነት ነው።

፮. በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚሰበሰበው ኪራይ የአካባቢውን ነዋሪዎች በሚጠቅም ተግባር ላይ ይውላል።

፯. ሚኒስቴሩ የሚሰበስበው ኪራይ ለጠቅላላ የከተማ ነዋሪዎች ኑሮ ማሻሻያና ለከተማ ዕድገት ይውላል።

፳፩. ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች፣

፩. የከተማ ቤት ለተወሰነበት የሃይማኖት፣ የትምህርት ፣ የጤና ጥበቃ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት መንግስት አስፈላጊነቱን እያጠና ለመተዳደሪያ የሚሆን በጀት ይመደብለታል።

፪. ትርፍ ቤት የተወረሰበት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ከቤት ኪራይ በስተቀር ለመኖሪያ የሚሆነው ሌላ ገቢ የልለው መሆኑን በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠ በመሥራት ገቢ እስኪያገኝ ድረስ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በየወሩ ለመተዳደሪያ እስከ ፪፻፶ (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ይከፍለዋል።

፫ የከተማ ቤት የተወረሰበት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ራሱ ወይም ወላጆቹ ከቤቱ ኪራይ በስተቀር ለመተዳደሪያ ሌላ ገቢ እንደሌላቸው ሚኒስቴሩ ካረጋገጠ በመሥራት ገቢ እስከሚያገኝ ወይም አካለ መጠን እስከ ደረሰ ድረስ ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በየወሩ ለመተዳደሪያ እስከ ፪፻፶ (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ድረስ ይከፍለዋል።

፬ ትርፍ ቤት የተወረሰበት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ በመሥራት ፣ በጡረታ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያገኘው የወር የተጣራ ገቢው ከ፪፻(አንድ መቶ) ብር ድረስ ይከፍላል።

፭ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፣(፪) ፣(፫) እና (፬) መሠረት ሚኒስቴሩ ወይም የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚያደረገው ክፍያ በኃላፊነቱ ከሚሰበሰበው ከኪራዩ ገቢ ሆኖ ለቤተሰብ ፣ ለግለሰብ ወይም ለድርጅት የሚከፈለውም ገንዘብ ከኪራይ ገቢ ከሚገኘው መሠረት ሊበልጥ አይችልም።

፮ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ ክፍያ ለከተማ ቤት ከሚከፈለው ካሣ ተቀናሽ ይሆናል። ጠቅላላ ክፍያው ለቤቱ ከሚሰጠው ካሣ ሊበልጥ አይችልም።

፯ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በቅድሚያ የተወሰደ ኪራይ ካለ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፣(፪) ፣ (፫) እና (፬) መሠረጽ ከሚደረገ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይሆናል።

ምዕራብ ፫

የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች

፳፪. የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ስለማቋቋም

ሚኒስቴሩ በሚወስነው የከተማ ክልል ውስጥ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ይቋቋማሉ።

፳፫. የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር አባሎች

ማንኛውንም የከተማ ነዋሪ የከተማ ነዋሪዎቸ የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን ይችላል። ሆኖም ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በአከራይ የነበረ ማንኛውንም ሰው በመጀመሪያው አንድ ዓመት ጊዜ ብቻ የማኅበሩን ሹማምንት የመምረጥ መብት ሊኖረው አይችልም። እንዲሁም የማኅበሩ የፍርድ ሸንጎ የማኅበሩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣ ወይም የህዝብ ደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ አባል ለመሆን አይችልም።

፳፯. የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ተግባር፣

የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል፣

ስለከተማ መሬት አጠቃቀምና ስለቤት አሠራር ሚኒስቴሩ የሚሰጠውን መመሪያ እየተከፈለ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

ሶስት አባላት ያሉተ የፍርድ ሸንጎ ያቋቁማል።

ከመንግስት ጋር በመተባበር ለአካባቢው የሚያስፈልጉትን የትምህርት፣ የጤና ፣ የገበያ ፣ የመንገድ ሥራና የመሳሳሉትን አገልግሎቶችን ያቋቁማል፡

ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጅለት ደረሰኞች መሠረት በወር እስከ ፩፻ ብር የሚከራይ የከተማ ቤትና ቦታ ኪራይ ይሰበስባል። የቤቶቹንም ጠቅላላ አስተዳደርና ጥገና ያካሂዳል።

ማኅበሩ የሰበሰበውን ኪራይ በህዝባዊ የመኖሪያ ቤቶችና የቁጠባ ባንክ ሚኒስቴሩ በሚከፍትለት ሂሳብ ውስጥ ያስቀምጣል።

የኅብረት ሥራው ማኅበር በተቋቋመበት የከተማ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ማናቸውንም የህዝብና የመንግስት ንብረት መጠበቅና በተለይም ከመንግስት ድርጅቶች ጋር በመተባበር የአካባቢውን ህዝብ ደኅንነትና ህይወት በተሟላ ሁኔታ እንዲያረጋግጥና እንዲከበር ያደርጋል። ማኅበሩ ይህንኑ ሥራ ለማስፈጸም የህዝብ የደኅንነት ጥበቃ ኮሚቴ ያቋቁማል።

ማኅበሩ በሚሰበስበው ኪራይና ከመንግስት የሚያገኘው ድጋፍ ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለአካባቢው ህዝብ የቁጠባ ቤት እንዲሰራለትና የኑሮውንም ሁኔታ የሚያሻሽሉ ተግባሮች እንዲደራጅ ያደርጋል።

ማኀበሩ ያዋጁን መንፈስ የተከተለ የራሱን የውስጥ ደንብ ያወጣል፡፡ በሚኒስትሩም ሲጸድቅ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፳፪. <u>የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ሥራ ማኀበር ስለማቋቋም ፣</u>

፩. እንደከተማው ስፋትና እንደህዝቡ ብዛት የከተማ ነዋሪዎች ማኀበር ተወካዮች የሚገኙበት ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ስራ ማኀበር ያቋቋማል፡፡

፪. ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ሥራ ማኀበር የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል፡-

ሀ/ በአንቀጽ ፳፩ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፣(፫)፣(፬) ፣(፮) ፣(፯፣፰) እና (፲) የተጠቀሱትን የከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ሥራ ማኀበር ተግባሮች ያስተባብራል፣

ለ/ በከፍተኛ የኀብረት ሥራ ማኀበር ክልል ውስጥ የሚገኙ ማኀበሮች በተቻለ መጠን የተመጣጠነ ይዞታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይዞታን በማሸጋሸግ ረገድ ሚኒስቴሩን ይረዳን፣

ሐ/ ማንኛውንም የከተማ ቦታ የልለው ቤተሰብ ፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለመኖሪያ ወይም ለመሥሪያ ቤት መሥሪያ የሚውለው ቦታ ሚኒስቴሩ እንዲሰጠው ሲያመለክት ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከርና በመተባበር በአስፈላጊው ሁሉ ይረዳል፣

መ/ ሦስት አባላት ያሉበት ከፍተኛ የፍርድ ሸንጎ ያቋቁማል፡፡

፳፫፣ <u>የአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ሥራ ማኀበር ስለማቋቋም፣</u>

፩/ እንደ ከተማው ስፋትና እንደህዝቡ ብዛት የያንዳንዱ ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኀበር ተወካዮች የሚገኙበት አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማኀበር ይቋቋማል፡፡

፪/ የአጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ሥራ ማኀበር የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል፡፡

ሀ/ የከፍተኛ ከተማ ነዋሪዎች የኀብረት ሥራ ማኀበር ተግባር ያስተባብራል፣

ለ/ ሦስት አባላት ያሉበት አጠቃላይ የፍርድ ሸንጎ ይቋቋማል ፡

፳፬፣ <u>ስለፍርድ ሸንጎዎች፣</u>

፩/ በአንቀጽ ፳፩ በንዑስ አንቀጽ (፪) የሚቋቋመው የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ ፣

ሀ / በነዋሪዎች መካከል የሚነሱትን የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን አለው ፡፡

ለ/ የወንጀል ክስ እንዲሁም በማኀበሩና በነዋሪዎች መካከል የሚነሣውን ክርክር ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡

፪/ በአንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) የሚቋቋመው ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ፣

ሀ/ በከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ የተወሰነውን ክርክር በይግባኝ አይቶ ይወስናል፡፡ በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ለ/ በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች መካከል እንዲሁም በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበርና በነዋሪዎች መካከል የሚነሣውን የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክረክር በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

ሐ/ የወንጀል ክስ ለማየት ሥልጣን የለውም ፡፡

፫/ በአንቀጽ ፳፯ በንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) የሚቋቋመው አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ ፣

ሀ/ በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎ በመጀመሪያ ደረጃ የተወሰነውን ክርክር በይግባኝ አይቶ ይወስናል፡፡ በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ለ/ በከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበሮች መካከል የሚነሣውን የከተማ ቦታና ቤት ነክ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ለመወሰን ሥልጣን አለው፡፡ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባን በሚኒስትሩ ይታያል፡፡ የሚኒስትሩ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ሐ/ የወንጀል ክስ ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡

፬/ በማንኛውም ከተማ ከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ከልለ የፍርድ ሸንጎ እስከተቋቋመ ድረስ ሚኒስትሩ የሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት እንደከፍተኛ ወይም አጠቃላይ የፍርድ ሸንጎ ሆኖ ለመሥራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

<u>፳፰፣ ስለፍርድ ሸንጎዎች ሥነ ሥርዓት</u>

፩. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋመው የፍርድ ሸንጎዎች ሚኒስትሩ የሚያወጣውን የሥነ ሥርዓት መመሪያ በመከተል ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡

፪. የፍርድ ሸንጎዎች የሚሰጡት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በይግባኝ ካልታገደ በስተቀር ከ፫፸ ቀን በኃላ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፫. የፍርድ ሸንጎዎች በሚሰጡት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው በ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

፬. የፍርድ ሸንጎዎች የሚሰጡት ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረጃው ባሉት ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አማካይነት በሥ ላይ ያውላል፡፡ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ከሥራ ላይ ለማጥል ያልቻለ እንደሆነ የፍርድ ሸንጎው ፖሊስን በቀጥታ በማዘዝ ውሳኔውን ወይም ትእዛዙን ያስፈጽማል፡፡

<u>፳፱፣ የፍርድ ሸንጎውን ስለመድፈር</u>

የፍርድ ሸንጎው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሥራውን ለማሰናከል፣ የስድብ ፣ የዛቻ ፣ የፌዝና ተመሳሳይ የሁከት አድራጎት በፈጸመ ማንም ሰው ላይ እስከ ሠላሳ ቀን የሚደርስ

እሥራት ወይም እስከ ፪፻፶( ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ለመድረስ በሚችል ገንዘብ መቀጮ በራሱ ሥልጣን ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ መቅጣት ይችላል፡፡

፴፣ ስለፍርድ ሸንጎዎች ሥልጣን ማጣራት፣

ማንኛውንም ሰው በፍርድ ሸንጎ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወሰንበት ጉዳይ የይግባኝ መብቱን በሸንጎዎቹ፣ በየደረጃው ከጨረሰ በኋላ ወይ መደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ አይችልም፡፡ ሆኖም በፍርድ ሸንጎ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ከፍርድ ሸንጎው ሥልጣን በላይ መሆኑን ሚኒስትሩ በሚቀርብለት ማመልከቻ መሠረት ካመነበት ጉዳዩን አጣርቶ በዚህ አዋጅ መሠረት ውሳኔ ሊሰጥበት ይችላል፡፡ የሚኒስትሩ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ፮

### የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

፴፩. አዋጁን የማስፈጸም ሥልጣን

ሚኒስቴሩ ይህ አዋጅ የሚደነግገውን ሁሉ ለማስፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፴፪፣ የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ስለማቋቋም

፩. ሚኒስቴሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴርና አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ለከተሞች ልማትና ለነዋሪዎቹ በሚስማማ ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በየደረጃው እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

፪. ሚኒስትሩ የከተማ ነዋሪዎችን የኅብረት ሥራ ማኅበር በምክርና በሌላም ልዩ ልዩ መንገድ የሚረዳ ቢያንስ በየከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር አንድ ወኪል ይመድባል፡፡

፴፫፣ አዋጁን ለህዝብ በይፋ ስለማሳወቅ

፩. ሚኒስትሩ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ዓላማ በማንኛውንም የመገናኛ ዘዴ ለከተማ ሕዝብ ያስረዳል፡፡

፪. በተለየም ሚኒስትሩ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ወዲያውኑ በከተማ ባለርስና ጭሰኛ ፣ በወለድ አግድ አያስኸና በወለድ አግድ ያኸ መካከል ያለውን ግንኙነት ከሚኒስቴሩ ወይም ከከተማ የኅብረት ሥራ ማኅበር ጋር መሆኑን ይገልጣል የተካመ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች የሚቋቋሙብትን ሁኔታ ያስረዳል፡፡

፫. የሚኒስትሩ ወኪል የከተማ ነዋሪዎችን በመሰብሰብና የዚህ አዋጅ መንፈስ ዓላማ በመግለፅ ማህበሩን እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

፴፬፣ ሚኒስቴሩ በፍርድ ሸንጎ ለመካፈል ያለ ጊዜያዊ ሥልጣን

፩. የሚኒስቴሩ ወኪሎች፣ የከተማ ነዋሪዎች የፍርድ ሸንጎዎች ተደራጅተው ሥራ ለማካሄድ እስከቻሉ ድረስ በሸንጉው ውስጥ በሊቀ መንበርነት ይሠራሉ፡፡

፪. የሚኒስቴሩ ወኪሎች የፍርድ ሸንጐ ጽሕፈት ቤቶች አቋቁመው በመዝገብ አያያዝ ረገድ ያለውን ሥራ በማደራጀት ይረዳሉ።

፴፫. መዝገብ ስለማቋቋምና ስለከተማ ክልሎች መወሰን

፩. ሚኒስቴሩ የከተማ ነዋሪዎች ዝርዝርና የቤቶችን ብዛትና ሁኔታ የሚያሳይ መዝገብ በየደረጃው አቋቁማል።

፪. ሚኒስትሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስትርና አግባብ ካላቸው ልሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የከተማ ክልል ወሰኖችን ለማስፋትና ለማጥበብ ወይም ለመለየት ሥልጣን አለው።

፴፯. የከተማ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታ ስለማሻሻል

፩. ሚኒስትሩ ከገንዘብ ሚኒስትር፣ ከፕላንና ልማት ኮሚሽን ፣ ከብሔራዊ ባንክና ከልሎችም አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የከተማ ነዋሪዎች ብድር አግኝተው የራሳቸውን የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ወይም ለመግዛት እንዲችሉ ይረዳል፡፡

፪. መንግስት በጠቅላላው ስለከተሞች ዕድገት በሚያወጣው ዕድቅና መመሪያ መሠረት ሚኒስቴሩ የሚሰበሰበው ኪራይ ለከተማ ነዋሪዎች አገልግሎት ይውላል፡፡

፫. ሚኒስቴሩ በከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር  የሚሰበሰበውን ኪራይ መንግስት በጠቅላላ ስለከተማዎች ዕድገት በሚያወጣው ዕቅድና መመሪያ መሠረት ለአካባቢው የኅብረት ሥራ ማኅበር ማስፋፊያ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል፡፡

፬. ሚኒስቴሩ የከተማ ቦታዎችንና የመንግስት የከተማ ቤቶች በበላይነት ያስተዳድራል፣

፭. ሚኒስቴሩ ለከተሞች ፕላን በማውጣት የቁጠባ ቤቶችን ይሠራል፣ ለከተማ ነዋሪዎች አስፈላጊ የሆኑትን አገልግሎቶችንም ይሰጣል፡፡

፮. ሚኒስቴሩ ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴርና ከከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች ጋር በመተባበር ቦታ የልለው የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

፯. ሚኒስቴሩ የከተማ ቤቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ደረጃ(እስታንዳርድ) እያወጣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፡፡

፰. ሚኒስትሩ ወይም የሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት ይህ አዋጅ በጸናበት ቀን ያልተከራዩ ቤቶችን ኪራይ ይወስናል፡፡

፰፮፣ መረጃ የመጠየቅ ሥልጣን

የሚኒስቴሩ ወኪል ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የውል ሰነዶችና ልሎችም መረጃዎች ከልሎች የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ፣ ከግል የንግድና የኅብረት ሥራ ድርጅቶችና ከግለሰቦች ጠይቆ ለማግኘት ሥልጣን አለው፡፡

## ምዕራፍ ፯

## ጠቅላላ ውሳኔዎች

**፴፰፡ ስለከተማ ማኅበሮች የህግ ሰውነት**

በዚህ አዋጅ መሠረት በየደረጃው የሚቋቋሙት የከተማ ነዋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበሮች የየራሳቸው የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል፡፡

**፴፱፡ ስለመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን**

በአንቀጽ ፲፯ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት እንዲሁም ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት ቀርቦ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚገኝ የከተማን ቤት የሚመለከት ክርክ በተባሉት ፍርድ ቤቶች ይታያል፡፡

**፵. ክስ ስለማገድ**

፩. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚገኝ የከተማን መሬት የሚመለከት ክርክር ተሰርዟል፡፡

፪. ይህ አዋጅ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚወሰደው እርምጃ ሕጋዊነት ለመቃወም ማናቸውንም ክስ ወይም ይግባን ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ አይቻልም፡፡

**፵፩. ወንጀሎች**

ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቤት ወይም ንብረት ያቃጠለ፣ ጉዳይ ያደረሰ፣ ያፈረስ፣ ያበላሸ፣ ወይም ከጥቅም ውጪ እንዲሆን ያደረገ ወይም የሞከረ፣ ፀጥታ ያደፈረሰ ወይም ለማደፍረስ የሞከረ ወይም በማንኛውም ሁኔታ አዋጁ በሥራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ፣ እንዲሁም ማንኛውንም ባለስልጣን ወይም መንግስት ሠራተኛ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በአዋጁ በተሰጠው ሥልጧን ወይም ኃላፊነት ያለአግባብ የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም የሞከረ ማንኛውንም ሰው በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፰/፲፱፻፷፯ ዓ.ም ከነማሻሻያ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል፡፡

**፵፪. ከልሎች ሕጎች ጋር ስላለው ቅራኔ**

ማንኛውንም ሕግ፣ ደንብ፣ የተለመደ አሠራር ወይም ሥርዓት የተፃፈም ቢሆን ሳይፃፍ በልማድ የሚሠራበት ሁሉ ይህ አዋጅ የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፵፫.፣ የዲፕሎማቲክ ይዞታዎች**

ይዞታው የዲፕሎማቲክ፣ የቆንሲላ፣ ወይም የኢንተርናሽናል ድርጅቶች የሆነ የከተማ ቦታ ወይም ንብረትነቱ የእነዚሁ የሆነ ቤት ሁኔታ ወደፊት ይወሰናል፡፡

**፵፬. አዋጅ የማይጸናባቸው ቤቶች**

የሃይማኖት ድርጅቶች ንብረት በሆኑ የጸሎት ቤቶች ላይ ይህ አዋጅ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣

**፵፭. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስትሩ የአዋጁን አንቀጾች ዓላማ በሚገባ ለማስፈፀም ደንቦችን ለማውጣት ይችላል፡፡

**፵፯. አዋጅ ስለሚፀናበት ቀን**

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ከሐምሌ ፰፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፡፡

## የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ፲፰/፪ሺ ህ፪ አጭር መግለጫ

ማውጫ

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. መቋቋም

፬. ዓላማዎች

፭. የማዕከሉ ተግባራትና ኃላፊነቶች

፮ ንብረት የመረከብ

ክፍል ሁለት

የማእከሉ አደረጃጀትና ስራ አመራር

፯ ድርጅታዊ መዋቅር

፰. የመማከር ካውንስል

፱. የማማከር ካውንስሉ አባልነት

፲. የቦርዱ አባልነት

፲፩. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

፲፪ የቦርዱ ስብሰባ

፲፫. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት

፲፬. የምክትል ዳይሬክተሮች ሥልጣን እና ተግባራት

ክፍል ሶስት

የፋይናንስ አቅርቦት

፲፭. የገንዘብ ምንጮች

፲፮. የፋይናንስ አስተዳደር

፲፯ ኦዲት

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፰. ከተማውን አስተዳደር እና ዩንቨርስቲውን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፳. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፳፩. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

አጭር መግለጫ

ይህ አዋጅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለተለያዩ ተግባራት የሚውል ዘመናዊ የእፅዋት እንክብካቤና የኢኮቱሪዝም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ዘመናዊ የዕፅዋት ማዕከል ለማቋቋም የሚያስችል ዓዋጅ ነው።

# <u>የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፰/፪ሺህ፪</u>

ተፈጥሯዊ መዝናኛ ቦታዎችን ጨምሮ ለተለያዩ ተግባራት የሚውል ዘመናዊ የእፅዋት እንክብካቤና የኢኮቱሪዝም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ማዕከል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም በጉለሌና ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ በሚገኘው መሬት ላይ ልዩ መልከዓ ምድርን ከፍተና ዋጋ ያላቸው የስነ ሕይወታዊ ሐብቶችና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን በዘላቂነት ለመንከበከብና ለልማት ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ዘመናዊ የዕፅዋት ማዕከል ለማቋቋም ያስፈለገ በመሆኑ፣

እንዲህ አይነት የእፅዋት ማዕከል መቋቋም በስነህይወት በተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝ እና በልሎች አካባቢዎች መስኮች ላይ ለሚካሄድ ትምህርታዊና ምርምር ስራዎች አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ፣

እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካትና የሕዝቡን የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ዘላቂታዊ የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት ጠቃሚ መሆኑን በማመን፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሸሻለ ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬ (፩) (ሀ) መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የጉለሌ የእጽዋት ማእከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፪ሺህ፪ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ የዋሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር

፩. ማዕከል ማለት የጉለሌ የእጽዋት ማእከል ነው፡፡

፪. የእጽዋት ማእከል ማለት በዚህ አዋጅ እና በልሎች የፌደራል ወይም የከተማ ሕጎች መሰረት በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት በጉለሌና በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተሞች ውስጥ በተሰጠው ፯፻፭ (ሰባት መቶ አምስት) ሄክታር መሬት ላይ ስራውን የሚያከናውን የጉለሌ የእጽዋት ማዕከል ነው፡፡

፫. ቦርድ ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የሚመሰረትና የእጽዋት ማእከሉን በበላይነት የሚያስተዳድር አካል ነው፡፡

፬. ከተማ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፭. የከተማ አስተዳደር ማለትየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፮. ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ማለት በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩ ተግባራትን የሚያከናውን የማእከሉ ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ነው፡፡

፯. ዩኒቨርሲቲ ማለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡

፰. ምክር ቤት ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው፡፡

፱. ካቢኔ ማለት በተሸሻለው  የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፷፩/፺፭ አንቀጽ ፳፫ የተዘረዘሩ ተግባራትን የሚያከናውን የከተማው አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

፲. የመማከር ካውንስል ማለት የጉለሌ የእጽዋት ማእከል መማከር ካውንስል ነው፡፡

፫. <u>መቋቋም</u>

፩. የጉለሌ የእጽዋት ማእከል ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪. ማእከሉ በቦርዱ በኩል ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ከንቲባ ይሆናል፡፡

፬. <u>ዓላማዎች</u>

ማእከሉ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

፩. በማእከሉ በአካባቢው ወይም በኢትዮጵያና በልሎች አካባቢዎች ለመጥፋት የተቃረቡ የዝርያዎች እንክብካቤ ተግባራትን ማከናወን፣

፪. በሥነ ሕይወት፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና በልሎች አካባቢነክ መስኮች ላይ ምርምር ማካሄድ፣

፫. በተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ የመዝናኛ የኢኮቱሪዝም አገልግሎት መስጠትና ማስፋፋት፣

፬. ከአካባቢ ጥበቃ ከተፈጥሮ ሀብትና ከሥነ ምህዳር አያያዝ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ግንዛቤ የመፍጠር ዓላማ ያላቸው የአካባቢ ትምህርት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ማመቻቸት መተግበር፣

፭. በአካባቢ ጥበቃ መስኮች የተሰማሩ ብሔራዊና አለም አቀፋዊ የሲልቫ ማህብረሰብ ድርጅቶችን መደገፍና ማበረታታት፣

፭. <u>የማዕከሉ ተግባራትና ኃላፊነቶች</u>

የዕፅዋት ማእከሉ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. የእጽዋት ማእከሉ የአጭር መካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ፕሮጀክቶችንና የድርጊት መርሐ ግብሮችን መቅረፍና በቦርዱ ይሁንታ መተግበር፣

፪. በአካባቢ እና በተፈጥሮ ሀብቶች ምህዳር እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ሥነ-ሕይወታዊ ሥነ0አካላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የምርምር ስራዎችን ማካሄድ

፫. ለእጽዋት ማእከሉ የተከለለው ቦታ የእጽዋት አይነትና የመሬት አጠቃቀም ዝርዝር ጥናት በጊዜው ማካሄድ እና መተግበር፣

፬. ለዘላቂ ምርቶችና አገልግሎቶች በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ በኢኮቱሪዝም ልማትና በታዳሽ የኃይል ምንጮች ምርምርና አቅርቦት ሰርቶ ማሳያዎችን ማከናወንና ማበረታታት

፭. በዕፅዋት ማእከሉ አካባቢ የሥነ ምህዳርጥናት ማመቻቸት ከብዙሃን ሕይወት እንክብካቤና ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎችን ማከናወን

፮. የዘመናዊ የእጽዋት ማእከል ተግባራትን ማከናወን፣

፯. ለአካባቢ ጥበቃ እና ምርምር እንክብካቤ የሚደርጉ የሲቪል ማህብረሰብ ድርጅቶች ማበረታታትና መደገፍ፣

፰ አግባብነት ያላቸው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኒኮች እና ውጤታማ የተፋሰስ አያያዝ ዘዴዎችን ማሰራጨት

፱. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት ከሚከተላቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም ከዩኒቨረሲቲ ጋር በቅርበት መስራት፣

፲. ለሰራተኞች እና ካላማዎቹጋር ተያያዥነት ባላቸው ስራዎች ውስጥ ለሚሳተፉ ግለሰቦች የስልጠናና የክህሎት ማሳደጊያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣

፲፩. ውሎችን መዋዋል፣ ንብረቶችን በባለቤትነት መያዥ እርዳታ እና ስጦታዎችን መቀበል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣

፲፪. የማእከሉ የሰው ኃይል ንብረትና ገንዘብ ማስተዳደር

፲፫. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ልሎች ተግባራት ማከናወን፣

፮ <u>ንብረት የመረከብ</u>

፩. የማእከሉ አስተዳደር በእጽዋት ማእከሉ ክልል ውስጥ በግለሰቦች እና በድርጅቶች በሕጋዊነት የተያዙ ንብረቶችን ስለመረከብ መመሪያ ያዘጋጃል በቦርዱና በከተማው አስተዳደር ይሁንታ ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪. ይህንን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እና በቦርዱ ይሩዊ ጥያቄ የከተማው አስተዳደር ለማእከሉ በተመደቡ ቦታዎች ላይ የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ለማእከሉ እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት ለሚከናወኑ ይዞታን የመውሰድ ወይም የማስተላለፍ እርምጃዎች የተነሳ ለሚከሰቱ አለመግባባቶች አግባብ ያላቸው የፌደራል እና የከተማዋ ሕጎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

## የማእከሉ አደረጃጀትና ስራ አመራር

፯ ድርጅታዊ መዋቅር

ማእከሉ የሚከተለው ድርጅታዊ መዋቅር ይኖረዋል፡፡

፩. የመማከር ካውንስል

፪. ቦርድ

፫. ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር

፬. የምርምርና ልማት እንዲሁም ትምህርትና መዝናኛ ዘርፎች ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች

፭. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች

፮. ቦርዱ በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ የሚያቋማቸው ልሎች ቋሚና ጊዜያዊ አማካሪ ኮሚቴዎች ወይም ኮሚሽኖች

፰. የመማከር ካውንስል

ማእከሉ የሚከተሉት ተግባራት ያለው የመማከር ካውንስል ይኖረዋል፡፡

፩ የማእከሉን እድገትና ልማት በሚያግዙ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ገንቢ ምክር ይሰጣል፡፡

፪. በማእከሉ ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርትና ልሎች መረጃዎች ላይ በመመስረት አስተያየቶችን ያቀርባል፡፡

፫. ካውንስሉ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፬. የቦርዱ ሰብሳቢ የካውንስሉ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፭. የማእከሉ ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር የካውንስሉ ጸሀፊ ይሆናል፡፡

፱. የማማከር ካውንስሉ አባልነት

፩. የመማከር ካውንስል በአካባቢ ጉዳዮች በአጠቃላይና በዕጽዋት ማእከል ልማት በተለይ ልምድና ፍላጎት ያላቸው የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሙያና ህዝባዊ ማህበራት የአለም አቀፍና ዲፕሎማቲክ ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦችን በአባልነት ያካትታል፡፡

፪. የአባላቱ ዝርዝር ለቦርዱ ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

፲. የቦርዱ አባልነት

፩. የቦርዱ አባላት በከተማው ከንቲባ የሚሰየሙ ሆነው የሚከተሉትን ይይዛል፡፡

ሀ/ የከተማው ከንቲባ-----------ሰብሳቢ

ለ/የዩኒቨርሲቲው ፕሬዘዴንት------ምክትል ሰብሳቢ

ሐ/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ዴታ---- አባል

መ/ የአዲስ አበባ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ---አባል

ሠ/ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲቱት ዋናዳሬክተር--------አባል

ረ/ የአዲስ አበባ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ-------አባል

ሰ/ የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ-------አባል

ሸ/ የዩኒቨርሲቲው የሳይንስ ፋኩሊቲ ዲን-------አባል

ቀ/ የኦሮሚያ ክሌላዊ መንግስት ተወካይ-------አባል

በ/ ታዋቂ ግለሰቦች እና/ወይም ሳይንቲስቶች ፪-----አባል

ተ/ የማእከሉ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር-----አባልና ጸሐፊ

፪. የከተማው ከንቲባ እንደሁኔታው ለምክትል ከንቲባው ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፲፩. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

፩. አግባብነት ያላቸው የፌደራል እና የከተማዋ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ማእከሉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

ሀ) የማእከሉ አጠቃላይ መመሪያ እና እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ፖሊሲዎቹን እና መርሀ ግብሮቹን በማመንጨት አፈጻጸማቸውን ለመወሰን እንዲሁም ከሶስተኛ ወገን ጋር ማእከሉ ሊመሰረት የሚችለው ግንኙነቶች መርምሮ ያጸድቃል፡፡

ለ) የማእከሉ ዓመታዊ የበጀት ጥያቄ እና ዋና ዋና መርሀ ግብሮች መርምሮ ያጸድቃሉ፡፡

ሐ) በስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር የሚቀርብለትን የማእከሉን አመታዊ ስራ አፈጻጸም እና የበጀት አጠቃቀምን መርምሮ ያጸድቃል፡፡

መ) የማእከሉን የፖሊሲ ጉዳዮች ይመረምራል፡፡ ያጸድቃል፣ ከስልጣኑ በላይ የሆኑትን ለከተማው አስተደደር እንዲቀርቡ ደርጋል፡፡

ሠ) የማእከሉን ኦዲተር ይሾማል ዓመታዊ ሪፖርቱንም ያጸድቃል፡፡

ረ) የስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተርን ይመድባል፣ ያነሳል

ሰ) ተጠሪነታቸውን በቀጥታ ለስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የሆኑትን የማእከሉን የስራ ሃላፊዎች በስራ አስፈጻሚው አቅራቢነት ይመድባል፣ ያነሳል፡፡

ሸ) የማእከሉን የውስጥ መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ተመልክቶምያጸድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፡፡

ቀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ልሎች ተግባራት ከናውናል፡፡

፲፪ <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

፩. ቦርዱ በዓመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪. የቦርዱ ልዩ ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም ከአባላቱ ፫/ኛው በጽሁፍ ሲጠይቁ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫. የቦርዱ አባላት ሀምሳ አንድ ከመቶና ከዚያ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፬. የቦርዱ ውሳኔዎች ምልዓተ ጉባኤ በሚኖርበት ጊዜ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይወስናል፡፡ እኩል-በእኩል ድምጽ በሚኖርበት ጊዜ የሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ድምጽ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፭. ቦርዱ የራሱ የስነ ስርዓት መርሆች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፫. <u>የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

፩. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን ለፖሊሶች፣ ለቦርዱ ውሳኑዎች አፈፃፀም እና የማዕከሉን የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች በመምራት፣ በማቀድ፣ በማደራጀት እና በመቆጣጠር ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተገለፀው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ….. ሥር የተገለጹትን የማዕከሉ ተግባራት እና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡፡

ለ) የማዕከሉን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅዶች እና መርሀ ግብሮችን ይቀርጻል፣ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በቦርዱ ሲፀድቅ ይፈጽማል፡፡

ሐ) ማዕከሉ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚኖሩት ጉዳዮች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፣ ወይም ልሎች እንዲወክሉት ያደርጋል፡፡
መ) የማዕከሉን በጀት ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ቦርዱ ሲፀድቅም ያስፈፅማል፡፡
ሠ) የማዕከሉ የውስጥ መመሪያዎች እና የሥራ መርሀ ግብሮች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡
ረ) በማዕከሉ የሚከናወኑ ሥራዎች ይቆጣጠራል፡፡
ሰ) የማዕከሉ የሰው ኃይል ንብረትና ሀብት ያስተዳድራል፡፡
ሸ) በዚህ አዋጅ ያለው ድንጋጌ እና የሀገሪቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ያሰናብታል፡፡
ቀ) በቦርዱ አመራር መሠረት የማዕከሉን የባንክ ሂሳቦች ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፡፡
በ) የማዕከሉን አግባብ ያላቸው የሂሳብ ደብተሮች ይይዛል ወይም እንዲያዙ ያደርጋል፡፡ ከማዕከሉ በፀደቀ በጀት እና የፋይናንስ መመሪያ መሠረት ወጪዎችን ይፈጽማል፡፡
ተ) በየጊዜው የስራ አፈፃፀም እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
ቸ) በማዕከሉ ለሚሰጡት የተለያዩ አገልግሎቶች የሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች በቦርዱ ያስወስናል፤ ያስፈፅማል፡፡
ነ) የማዕከሉን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ፣ ግዥ እና ግንባታን በተመለከተ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውሎችን ይዋዋላል፤ የማዕከሉን ንብረት በመያዣነት በማስያዝ የብድር ውል ይዋዋላል፣ ከውጭና ከሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር ያሉ የምርመራና ልሎች ውሎችን ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያስፈፅማል፡፡
ኘ) በማዕከሉ እና በዩኒቨርስቲው በጣምራ የሚከናወኑ የምርመራ ፕሮጀክቶችን እና ሳይንሳዊ ጆርናሎችን በመመስረተ ያፀድቃል፡፡
አ) በቦርድ የሚሰጡት ልሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡
፫ የማዕከሉን ተግባራት እና ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆኑ ድረስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የተወሰኑ ኃላፊነቱን ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለእርሱ ለሆኑ የማዕከሉ የስራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
፬. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡፡
፲፬. <u>የምክትል ዳይሬክተሮች ሥልጣን እና ተግባራት</u>
፩. የምርመራና ልማት ምክትል ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶችን ያከናውናል፡፡
ሀ) የምርምርና ልማት ሥራዎችን ያቅዳል፤ ይፈፅማል፡፡
ለ) ልሎች በስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡
ሐ) እንደሁኔታው ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክከተሩ በማይኖርበት ጊዜ ወክሎ ይሰራል፡፡
፪. የትምህርትና መዝናኛ ምክትል ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
ሀ) የማዕከሉ የትምህርት፣ የመዝናኛ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ያቅዳል ይተገብራል፡፡
ለ) እንደሁኔታው ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ወክሎ ይሰራል፡፡
ሐ) ልሎች በስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተሩ የሚሰጡት ተግባራት ያከናውናውናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የፋይናንስ አቅርቦት</u>

፲፭. <u>የገንዘብ ምንጮች</u>
፩. የማዕከሉ የገንዘብ ምንጮች የሚያካትቱት በከተማው አስተዳደር በሚመደብ ጥልቅ የበጀት፣ በዩንቨርስቲው የሚገኝ ጥልቅ የበጀት ድጋፍ፣ ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎት ሊሰበሰቡ የሚችሉ የአገልግሎቶች ክፍያዎች፣ የማዕከሉን የምርምር ሥራዎች እና ልሎች ፕሮጀክቶች ስፖንሰር በማድረግ ከድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚገኝ ገንዘብ፣ እርዳታዎች እና ከካፒታል የሚገኝ ገንዘብ ቦርዱ በየጊዜው ወስኖ ከሚዘጋጂት ዝግጅቶች እና ልሎች የገቢ ምንጮች ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት ማዕከሉ ከማንኛውም ምንጭ የሚያገኘውን ገንዘብ ሁሉ በማዕከሉ ስም የተከፈተ የባንክ ሂሳብ የሚጠራቀም ሲሆን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለማዕከሉ ሥራ ውጪ ይሆናል፡፡

፲፯. የፋይናንስ አስተዳደር

፩. የማዕከሉ ንብረት እና ፋይናንስ በሀገሪቱና በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህጎች መሠረት ይተዳደራል፡፡

፪. ማዕከሉ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ ማግበት ይይዛል፡፡

፫. የማዕከሉ የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ሐምል ፩ ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው አመት ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል፡፡

፬. ማዕከሉ ሂሳቡን ቢያንስ በአመት አንዴ ይዘጋል፡፡

፲፯ ኦዲት

፩. የማዕከሉ ኦዲተሮች በቦርዱ የሚሾሙ ሲሆን የማዕከሉን ሂሳቦች፣ መዛግብቶች፣ ሰነዶች እና ወረቀቶች ባልተገደበ ሁኔታ ማግኘት ይችላሉ፡፡

፪. ኦዲተሮች የኦዲት ተግባራቸውን በሀገሪቱ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባላቸው የሂሳብ ማጣራት ህጎች መሠረት የሚያከናውኑ ሲሆን ሪፖርታቸውን በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፰. ከተማውን አስተዳደር እና ዩንቨርስቲውን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች

፩. የከተማው ነዋሪዎችን ሁለንተናዊና ይወክላልጽግና ለማራመድ ካለበት ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነትና ለዚሁ አላማ በከተማው ቻርተር በተደነገገው ልዩ ተልዕኮው መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማዕከሉን ሁሉን አቀፍ ተግባራት እና እንቅስቃሴዎች የመደገፍና የመቆጣር ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. በመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራ ካለው የረጅም ጊዜ ልምድ እንዲሁም በሰው ኃይል እና በቁሳዊ ሐብቶቹ በአንፃራዊነት ካጎለበተው የምርምር አቅምሙ በመነሳት ዩንቨርስቲው የምርምር ፕሮጀክቶች መቅረጽን፣ ማጎልበትን እና ማካሄድን በተመለከተ በአጠቃላይ የማዕከሉ የሥራ አመራርና እንቅስቃሴ ላይ እንደከተማው አስተዳደር ሙሉ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

፲፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩. ካቢኔው ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪. ቦርዱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ልምዳዊ አሰራሮች በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ ለተደነገጉ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

፳፩. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የሚፀና ይሆናል፡

አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፱፪ ዓ.ም

ኩማ ደመቅሳ

## የሕግ ክፍል ማስታወቂያ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የመዝናኛ ግብር ደንብ አጭር መግለጫ

## ፪፻፺፩/፲፱፻፺፯

ማውጫ

አንቀጽ ፩ የሕግ ማውጣት ሥልጣን

አንቀጽ ፪ የሕጉ ሥያሜ

አንቀጽ ፫ ተርጉም

አንቀጽ ፬ አከፋፈል

አንቀጽ ፭ የግብሩ ጠቀሜታ

አንቀጽ ፮ የመሰብሰብ ሥልጣንና የመክፈል ግዴታ

አንቀጽ ፯ የግብር አሰባሰብ

አንቀጽ ፰ አስተዳደራዊ መቀጮ

አንቀጽ ፱ የማዘጋጃ ቤት ሥልጣን

<u>አጭር መግለጫ</u>

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የሕዝብ መዝናኛ ቦታ ለመግባት ባለቤቱ የሚያስከፍለውን ዋጋና በከፊል ወይም በሙሉ ለመግቢያ ዋጋ ምትክ እንደ ተጠየቀ አድርጎ ማዘጋጃ ቤት የሚወስነውን ማናቸውንም መሸፈኛና ይህን የመሳሰለ ከዋጋ በላይ የሚከፈል ገንዘብን በሕግ ለመወሰን የወጣ ደንብ ነው፡፡

## የሕግ ክፍል ማስታወቂያ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የመዝናኛ ግብር ደንብ ፪፻፺፩/፲፱፻፶፯

፩፣ ለአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በቁጥር ፩፻፸፪/፵፯ በተሰጠው ቻርተር በአንቀጽ ፲፰ ለምክር ቤቱ በተሰጠው ሥልጣንና በአንቀጽ ፳፩ ለከንቲባው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወጣ የሕግ ክፍል ማስተሰወቂያ፡፡

፪፣ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የመዝናኛ ግብር ደንብ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

፫፣ ትርጉም ፣ ለዚህ ደንብ እንዲያገለግል፣

፩/ ‹‹ የመግቢያ ዋጋ›› ማለት፣

ሀ) በአዲስ አበባ ከተማ የሚገበኙ የሕዝብ መዝናኛ ቦታ ለመግባት ባለቤቱ የሚያስከፍለውን ዋጋና

ለ) በከፊል ወይም በሙሉ ለመግቢያ ዋጋ ምትክ እንደ ተጠየቀ አድርጎ ማዘጋጃ ቤት የሚወስነውን ማናቸውንም መሸፈኛና ይህን የመሳሰለ ከዋጋ በላይ የሚከፈል ገንዘብንይጨምራል፡፡

ሐ) ስለሆነ ግን በመዝናኛ ዋጋ ላይ ቀጥታ በመመሥረት የሚከፈለውን ልዩ ቀረጥ አይጨምርም፡፡

፪) ‹‹ወር›› ማለት በኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ለወር የተደለደለውን ጊዜ ያመለክታል፡፡

፫) ‹‹ባለቤት›› ማለት ማናቸውንም የመዝናኛ ቦታ ባለጥቅም (ባለንግድ) ሰውና የሕግ አካል ያለውን ድርጅት ይጨምራል፡፡

፬) ‹‹የሕዝብ መዝናኛ›› ማለት ማናቸውም ቲያትር፣ ሲኒም፣ ካባሬ (ናይት ክለብ) ፣ የስፖርት ቦታና ይህን የመሳሰለ የመግቢያ ዋጋ በማስከፈል የሚቀርበን ትርኢትና የጨዋታ ቤቶችን ይጨምራል፡፡

፬፣ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫/፩ በተመለከተው መሠረት የሕዝብ መዝናኛ በሆነ ስፍራ ለመግባት በሚከፈል በማናቸውም የመግቢያ ዋጋ ላይ በመቶ ዐሥር (10%) የመዝናኛ ግብር ተመድቦ ይከፈልበታል፡፡

፭፣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት በሚሰጣቸው ቋሚ ውሳኔዎችና ሥልጣን መሠረት ከሕዝብ መዝናኛ መግቢያ የሚገኘውን ገንዘብ በሙሉ ለበጎ አድራጎት ወይም ለትምህርት ጉዳይ የሚውል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ፕሬዝዴንት በዚህ ደንብ በሠረት ሊከፈል የሚገባውን የሕዝብ መዝናኛ መግቢያ ግብር ነጻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፮፣ ባለቤቱ የመዝናኛውን ግብር በመግቢያው ዋጋ ላይ ጨምሮ ይሰበስባል፡፡ ግብሩን ሳይሰበስብ ቢቀር ግን ፣ባለቤቱ ራሱ ግብሩን ይከፍላል፡፡

፯፤ባለቤቱ ፤ ለማናቸውም መግቢያ ዋጋ ካርኔ (ቲኬት) መቁረጥ አለበት፡፡ ካርኔዎች ከመሸጣቸው በፊት ባለቤቱ ለማዘጋጃ ቤት የገቢ ክፍል አቅርቦ ተፈላጊውን ግብር አስቀድሞ በመክፈል፤ ማስመዝገብና ማኅተም ማስደረግ አለበት፡፡ ያልተሸጡ ካርኔዎችን በማናቸውም ጊዜ ለማዘጋጃ ቤት ሲያስለክብ በነዚሁ ትኬቶች ላይ በግብር ስም የተከፈለው ገንዘብ ለባለቤቱ መመለስ አለበት፡፡

፰፤ማናቸውም የሕዝብ መዝናኛ ባለቤት ግብሩን ሳይከፍል ቢዘገይ ፤ ግብሩን ሊከፍልበት ከሚገባው ቀን ጀምሮ በውዝፍ ለሚፈለግበት ግብር በየወሩ ፫% ሒሳብ ወለዱን ጭምር መክፈል አለበት፡፡ ስለሆነም በዚህ አኳኋን በተጨማሪ የሚከፈለው ወለድ ሊከፈል ከሚገባው ከዋናው ዕዳ መጠን መብለጥ የለበትም፡፡

፱፤የመዝናኛን ግብር ለማስገባት እንዲቻል የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ደንቦች ለማውጣት ፤ የማስፈፀሚያ ሥነ ሥርዓት ለመስጠትና አፈጻጸሙንም ለመመርመር ስልጣን አለው፡፡

፲፤ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ.ም.

ዘውዴ ገብረ ሕይወት

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ፡፡

# የአዲስ አበባ የውሃ አቅርቦት እና የፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፩ ማሻሻያ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ከመጠጥ ውሀ አቅርቦትና ከፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት የሚሰበስበው ገቢ ለአገልግሎት ከሚወጣው ወጭ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ በመሆኑ፤

የፌደራሉ የውሃ ሃብት አስተዳደር ፖሊሲ የከተሞች የውሃ ታሪፍ ሙሉ ወጪን ሊሸፍን እንደሚገባ በተመለከተው መሠረት ባለስልጣኑ የሚሰበስበው ገቢ ከሚሠጠው አገልግሎትና ከወጭው ጋር ተመጣጣኝ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በስራ ላይ በነበረው የአዲስ አበባ የውሃ አቅርቦትና የፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፩ የተመለከተውን የውሃ አቅርቦት ታሪፍ ማሻሻልበ ማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፲፯/፩ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷ ፡፡

፩.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ የውሃ አቅርቦትና የፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት ደንብ ቁጥር ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፩ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፴፮/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.<u>ማሻሻያ</u>

የአዲስ አበባ የውሀ አቅርቦትና የፍሳሽ ማስወገድ ደንብ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፩እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. ከደንቡ ጋር አባሪ የሆነው ሠንጠረዥ ፩ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በሆነው አዲስ ሠንጠረዥ ፩ ተተክቷል፡፡

፫. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ፴፱/፪ሺህ፫

ማውጫ


ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

ክፍል ሁለት

በጀት

፫. መርህ

፬. የክፍለ-ከተሞችን ጥቅል በጀት ስለመወሰን

፭. የበጀት ዝግጅት እና አቀራረብ

፮. የበጀት ግምትን ስለማፅደቅ

፯. የበጀት የጊዜ ሰሌዳ

፰. ልዩ ስልጣን

፱. የበጀት ዝውውር

፲. የበጀት ዝውውር አፈፃፀም

፲፩. የበጀት ቁጥጥር

፲፪. ተጨማሪ በጀት

ክፍል ሶስት

የመንግስት ገንዘብ ክፍያ

፲፫. ክፍያና ወጪ

፲፬. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ማዘዣ

፲፭. ውክልና ስለተሰጣቸው ሰዎች ዝርዝር

፲፮. የጥሬ ገንዘብ ዝውውር

፲፯. የመንግስትን ገንዘብ ስለመክፈልና ወጪ ስለማድረግ

፲፰. ገንዘብ ያዥ እጅ ስለሚቀመጥ የመንግስት ገንዘብ ደህንነት

ክፍል አራት

የዕቃና አገልግሎት ዋጋ

፲፱. መርህ

፳. የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦትን ስለማስጠናት

፳፩. የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ልክ የመወሰኛ መመዘኛዎች

፳፪. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ክፍያ ስሌት ዘዴ

፳፫. ማፅደቅ

፳፬. ስለማሳወቅ

፳፭. መመርመር

ክፍል አምስት

የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብና ገቢ ማድረግ

፳፮. የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ

፳፯. የመንግስት ገንዘብ ስለመቀበል

፳፰. የአደራ ወይም የመያዣ ገንዘብ

፳፱. በቼክ ስለሚሰበሰብ ገንዘብ

፴. ከመንግስት ንብረት ስለሚገኝ ገቢ

፴፩. ገቢ ስለማድረግ

፷፪. ምዝገባ
፷፫. መመሪያዎች
ክፍል ስድስት
የቅድሚያ ክፍያዎች
፷፬. ለግዝ ሰራተኞች ስለሚሰጡ የቅድሚያ ክፍያዎች
፷፭. ለውሎ አበልማ ለመጓጓዛ ስለሚደረግ የቅድሚያ ክፍያ
፷፮. የቅድሚያ ክፍያ ገደብ
፷፯. የቅድሚያ ክፍያዎችን ስለማስመለስ
፷፰. መዛግብት
፷፱. ሪፖርት ስለማቅረብ
ክፍል ሰባት
ተሰብሳቢ ሂሳቦችን፣ ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን ከመዝገብ ስለመሰረዝ
፸. ከመዝገብ የመሰረዝ ስልጣን
፸፩. የሰራተኞች እና የቀድሞ ሰራተኞች የዕዳ ስረዛ
፸፪. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ
፸፫. መመሪያዎች
ክፍል ስምንት
የከተማ አስተዳደሩ ብድር እና የመንግስትን ገንዘብ ለመዋለ-ንዋይ ስለማድረግ
፸፬. የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ
፸፭. መንግስት የወሰደው ብድር
፸፮. የቢሮው የመቆጣጠር ስልጣን
፸፯. ዋስትና
፸፰. መዋለ-ንዋይ
፸፱. የጥሪት ፈንድ
፹. ዕዳን ስለማስተላለፍ
፹፩. የከተማ አስተዳደሩ ባንክ እና የፋይናንስ ወኪል
፹፪. መዝገቦች እና ሂሳቦች
ክፍል ዘጠኝ
የከተማ አስተዳደር እና የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግንኙነት
፹፫. የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ስርዐት
፹፬. የአገር ውስጥ ብድር
፹፭. የፋይናንስ ድጋፍ
፹፮. ቅፆችና የጊዜ ገደብ
፹፯. የከተማው አስተዳደር የሂሳብ ሪፖርት
፹፰. ኦዲት
ክፍል አስር
የመንግስት ሂሳብ
፹፱. የመንግስት ሂሳብ አቀራረብ
ክፍል አስራ አንድ
የውስጥ ኦዲት
፺. የውስጥ ኦዲት ስልጣን
፺፩. የውስጥ ኦዲት ተግባርና ኃላፊነት
ክፍል አስራ ሁለት
የመንግስት ገንዘብና ንብረት ስለመጥፋት
፺፪. ምርመራ ስለማካሄድ
፺፫. ሪፖርት ስለማቅረብ
፺፬. የፍትሐ-ብሄር እርምጃ
፺፭. የዲሲፕሊን እርምጃ
፺፮. ስለመተካት
፺፯. የመንግስት ካዝናዎች
፺፰. ጉድለትን ሪፖርት ስለማድረግ
ክፍል አስራ ሶስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
፺፱. መዛግብት የሚቆበት የጊዜ ገደብ
፻. መቆየት ያለባቸው የመዛግብት አይነቶች
፻፩. በኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ስለመጠቀም
፻፪. የማቆየት ዘዴዎች

፸፫. የተሻረ ህግ ፸፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ የአዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፫መሻሻሉን ተከትሎ የወጣ ደንብ ነው፡፡ ይህም ደንብቀደም ሲል በስራ ላይ ያጋጠሙ የአፈጻጸም ችግሮች ለመቅረፍ ታስቦ የተደነገገ ነው፡፡ደንቡ የመንግሰት በጀት አዘገጃጀት፣ የመንግስት ገንዘብ አሰባሰብ፣ የክፍያ፣ የሂሳብ አያያዝ እና የውስጥ ቁጥጥር እንዲሁም የሀብትና የዕዳ አስተዳደር እና አጠቃላይ የፋንናንስ አስተዳደርን በተመለከተ ያሉ ጉዳዮችን ይደነግጋል

## የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ፵፬/፪ሺ፬

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸውና ድህነትን ከመቅረፍ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆናቸው ብድር ለመበደር የሚጋጥማቸውን የዋስትና ችግር መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፵፬/፪ሺ.፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ከንቲባ" ማለት የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ነው፤

፬. "የብድር ዋስትና ፈንድ" ማለት በጥቃቅን ወይም አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ የተወሰደ ብድር ባይከፈል ለአበዳሪ ሊከፈል የሚችል የተያዘ ወይም ተቀማጭ ገንዘብ ነው፤

፭. "የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ" ማለት ባለቤቱን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ሀብቱ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር ፶ሺ. ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር ፺ሺ. ያልበለጠ ኢንተርኘራይዝ ነው፤

፮."አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ" ማለት ባለቤቱን ጨምሮ እስ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ሀብቱ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር ፶ሺ.፩ እስከ ፭፻ሺ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር ፺ሺ.፩ እስከ ፩ ሚሊዮን ፭፻ ሺ. ያልበለጠ ኢንተርኘራይዝ ነው፤

፯. "የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም" ማለት አዲስ የብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማህበርን ጨምሮ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በዘርፉ

ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በፋይናንስ አገልግሎት ለመደገፍ ከብሄራዊ ባንክ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ አበዳሪ ተቋም ነው፡፡

፫. ዓላማ

፩. የብድር ዋስትና የሚሆን ንብረት ለሌላቸው ነገር ግን ብድር ቢያገኙ ሠርተው ብድራቸውን ከመመለስ አልፈው ራሳቸውን ማሳደግና ትርፋማ መሆን የሚችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር እንዲያገኙ ዋስትና ለመስጠት፤

፪. በኤክስፖርት ምርት ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች ለመተካትና በሌሎች ትኩረት በሚሰጣቸው የስራ ዘርፎች የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለመበደር የሚጋጥማቸውን የዋስትና ችግር በመቅረፍ በዚህ ዘርፍ የሚሰማሩትን ለማበረታታት፤

፫. የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማገዝ ፡፡

፬. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስራዎች ላይ ተሰማርተው የብድር ዋስትና ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፭. መርሆዎች

፩.የብድር ዋስትና ፈንድ የብድር ዋስትናን ለማጠናከር በድጋፍ ማዕቀፍ ውስጥ የተካተተና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ፣ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና ከተማው አስተዳደር የሚቋቋምና የሚተዳደር ፈንድ ነው፤

፪.የዋስትና ፈንድ አጠቃቀም በብድር ስርዓቱ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የስራ ዘርፎች ብቻ ይሆናል፤

፫.የዋስትና ፈንዱ ዋስትና ማቅረብ ለማይችሉና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት መደብር ወይም በሌሎች የዋስትና አማራጮች መስተናገድ ያልቻሉት ብቻ የሚስተናገዱበት የድጋፍ ስርዓት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## አወቃቀር፣ ኃላፊነትና ተግባር

፮. የፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ

፩.የከተማ አስተዳደሩ የብድር ዋስትና ፈንድ ከአስተዳደሩ አካላት ተውጣጥቶ በተደራጀ የአስተዳደር ኮሚቴ የሚመራ ይሆናል፤

፪.የአስተዳደር ኮሚቴ ተጠሪነት ለከንቲባው ሆኖ  የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ……..……ሰብሳቢ፣

ለ. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ኃላፊ ……………….……….አባል፣

ሐ. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ……………………………..…….አባል፣

መ. የአዲስ ብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማህበር ተቋም ማኔጂንግ ዳይሬክተር…...……....አባል፣

ሠ. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዳይሬክተር…………………...…..አባል፣

ረ. ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚመደብ የዋስትና ፈንድ አስተባባሪ…..አባልና ፀሐፊ፡፡

፯.የፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የአስተዳደር ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የብድር ዋስትና ፈንድ ምንጮችን በማፈላለግ የዋስትና ፈንዱን ያቋቁማል፣ ፈንዱን ከልዩ ልዩ ምንጮች በሚያገኘው ገቢ ያጠናክራል፤

፪. የዋስትና ፈንዱን በሚመለከት ሪፖርቶችን ያዳምጣል፤

፫.በዋስትና ፈንዱ አፈፃፀም ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፰.የፈንዱ ምንጭ

ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች ይሰበሰባል፡-

፩. ፸ በመቶ ከከተማው አስተዳደር ከሚመደብ በጀት፣

፪. ፳ በመቶ  በዘርፉ ከተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚደረግ ቁጠባ፣

፫. ፲ በመቶ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ከሚደረግ መዋጮ ፣ እና

፬. ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎችና መመልመያ መስፈርት

፱.የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች

የሚከተሉት የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች ናቸው፡-

፩.ለኤክስፖርትና ለገበያ የሚያመርቱ ኢንተርፕራይዞች፤

፪. ከውጭ ሀገር የሚገቡትን በሚተኩ ምርቶችና በኮንስትራክሽን ስራ ለተሰማሩ፤

፫. በክላስተር ማዕከላት በመሰባሰብ በሞዴልነት ተመርጠው የሚያመርቱና አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ፤

፬. የራሳቸው ቁጠባና የመልካም ተበዳሪነት ታሪክ ያላቸው ሆነው በማምረትና በኤክስፖርት ምርት ላይ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሲሆን እንደተጠቃሚው

ብዛት በሌሎች የተመረጡ የስራ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችም የቁጠባ ፈንዱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

፲.<u>መመልመያ መስፈርቶች</u>

፩.ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች

ሀ/ ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለማግኘትና ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ፳ በመቶ ቢያንስ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በየወሩ እኩል ክፍያ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፣

ለ/ የኤክስፖርት ምርት ከሚያመርቱና በእድገት ተኮር የስራ ዘርፍ ከተሰማሩ ውጭ ያሉ ጀማሪ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ለመበደር ያቀዱትን ፳፭ በመቶ ቢያንስ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በየወሩ እኩል ክፍያ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>፪.ታዳጊ ኢንተርፕራይዞች</u>

ሀ/ ኤክስፖርት ምርት የሚያመርቱና በእድገት ተኮር ዘርፍ የሚሰማሩ ታዳጊ ኢንተርፕራይዞች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ለመበደር ያቀዱትን ፲፭ በመቶ ቢያንስ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በየወሩ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፣

ለ/ በስትራቴጂው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የሥራ ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ኢንተርፕራዞች ብድር ለማግኘትና ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ፳ በመቶ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፣

ሐ/ የዕድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት በማስፈፀሚያ መመሪያው መሠረት የያዙ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

<u>፫.የበቃ ኢንተርፕራዝ</u>

ሀ. ኤክስፖርት ምርት የሚያመርቱና በእድገት ተኮር ዘርፍ የሚሰማሩ የበቁ ኢንተርፕራይዞች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ለመበደር ያቀዱትን ፲፭ በመቶ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፣

ለ. በስትራቴጂው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የሥራ ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለማግኘትና ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ፳ በመቶ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፣

ሐ. የዕድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት በማስፈፀሚያ መመሪያው መሠረት የያዙ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስልጣንና ተግባር</u>

፲፩. <u>የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስልጣንና ተግባር</u>

ሀ. ለዋስትና ፈንድ የሚሆን የገንዘብ ምንጭ ያፈላልጋል፤ በከተማው የሚንቀሳቀሱ ግብረሰናይ ድርጅቶች እንዲሳተፉ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

ለ. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ቢሮ በሚቀርበው የዋስትና ፈንድ የበጀት ጥያቄ መሠረት በጀት ይመድባል፣ በዋስትና ፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ውሳኔ ሲሰጥም አግባብነት ወዳለው አነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ የባንክ ሂሳብ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

ሐ. የዋስትና ፈንድ አስተዳደር መረጃ ያደራጃል፤ ወቅታዊ ሪፖርት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ያዘጋጃል ሪፖርት ያደርጋል፤

መ. የዋስትና ፈንድን አፈፃፀም ኦዲት ያደርጋል፤ የውጤት ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤

ሠ. ሌሎች ከፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡

፲፪.<u>የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩.ለኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጣል፤

፪.የዋስትና ፈንድ የሚያስፈልጋቸውን ኢንተርፕራይዞች ይለያል፤ ለአበዳሪ ተቋሙ ያስተላልፋል፤

፫.ብድር ሳይመልሱ በመቅረታቸው ዋስትና ፈንዱ የሚተካላቸውን ኢንተርፕራይዞች ከአበዳሪ ተቋሙ ጋር በመቀናጀት ይለያል፤ ለፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

፲፫.<u>የአበዳሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. የተበዳሪዎችን የንግድ እቅድ በመገምገም አዋጭነቱን ያረጋግጣል፤

፪. የተበዳሪዎችን የብድር አጠቃቀምና የፕሮጀክት አፈፃፀም ይከታተላል፤

፫. በስድስት ወር አንድ ጊዜ ስለፈንዱ አጠቃቀምና አፈፃፀም ለፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፤

፬. የሚጠየቀው የዋስትና ክፍያ ጥያቄ ወቅቱን የጠበቀና በስምምነቱ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፤

፭. ከዋስትና ፈንድ በቀጥታ ላልተመለሰ የብድር ገንዘብ እንዲተካ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት በሚቻለው መንገድ ሁሉ አበዳሪው ብድሩን እንዲመልስ ጥረት ያደርጋል፡፡ ይህንንም የሚያረጋግጥ የማስረጃ ሪፖርት ለፈንድ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

፮.ከብድር ጋር በተያያዘ ዋስትና ሰጭው ወይም የፈንድ አስፈፃሚ ኮሚቴ በየጊዜው የሚሰጣቸውን መመሪያዎች ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፡፡

፲፬.<u>የዋስትና ሽፋን አፈፃፀም</u>

፩. ከዋስትና መያዣ ወይም ከብድር ዋስትና ፈንድ የሚተካ ብድር የመጨረሻው አማራጭ ሆኖ ከብድር ዋስትና ፈንድ እንዲተካ የሚደረገው ብድር በየስድስት ወሩ የሚከናወን ይሆናል፤

፪. በንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዋስትና ፈንድ የተሸፈነ የብድር ገንዘብ ክትትልና የማስመለሱ ተግባር በአበዳሪ ተቋማቱም ሆነ በሚመለከታቸው አካላት የሚቀጥል ይሆናል፤

፫. የሚመለሰው ገንዘብ በቀጣይነት በተዘዋዋሪ ፈንድነት የሚያገለግል ወይም የሀብት ማጠናከሪያ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲፭.<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረም፡፡

፲፮.<u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

በዚህ ደንብ ዋስትና የፈንዱ አስተዳደር ኮሚቴ ለዚህ ደንብ አፈፃጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፯. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፰. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህደንብ  የካቲት ፳፪ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

አዲስ አበባ

የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፲፱/፲፱፻፺፺ አጭር መግለጫ

አጭር መግለጫ

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማ አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሀላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን ፍትሐዊ፣ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጣ ውረድ በለሌላው ቀላል በሆነ ሥነ-ሥርዓት፣ እንዲሁም የተጠቃሚዎችን የፆታ ተዋፅኦ በሚያረጋግጥና የገበያ አቅምን ግምት ውስጥ በሚያስገባ የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶች ለከተማው ነዋሪዎች የሚተላለፉበትና የቤት ባለቤት የሚሆኑበት አፈፃፀም ለመደንገግ የወጣ ዓዋጅ ነው፡፡

ማውጫ

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት

ቤት ፈላጊዎችን መመዝገብና የከተማው አስተዳደር ቤቶችን የማስተላለፍ አፈፃፀም

፬. የቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ ይዘትና አቀራረብ

፭. ቤት ፈላጊዎችን ማጣራትና መመዝገብ

፮. የቅድሚያ አወሳሰን

፯. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

፰. የክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

ክፍል ሦስት

የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ፣እንዲሁም የግንባታ ወጪ ስለልትና አሸፋፈን

፱.የቅድሚያ ክፍያ መጠን፣እንዲሁም የቀሪ ክፍያና የችረሬታ ጊዜ

፲. ስለ ክፍያ አፈፃፀም

፲፩.የወለድ መጠንና አከፋፈል

፲፪. የወጪ ስለልትና አሸፋፈን

ክፍል አራት

የገዢዎች መብትና ግዴታ፣ልሎችም ተዛማች ጉዳዮች

፲፫. በመንግስት ቤት የሚኖር ገገር ግዴታ
፲፬. ክፍያ ያጠናቀቀ ገገር መብትና ግዴታ
፲፭. የወራሾች መብት
፲፮. ውል ስለማቋረጥ
፲፯. የለላዝ ክፍያ
፲፰. አቤቱታ የማቅረብ መብትና አወሳሰን
ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
፲፱. የመተባበር ግዴታ
፳.ቅጣት
፳፩. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች
፳፪. ደንብ የማውጣት ሥልጣን
፳፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

<u>**የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩ ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን**</u>

<u>**ለመወሰን የወጣ አዋጅ፲፱/፲፱፻፺፯**</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚስተዋለውን ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት እጥረት መንግስት አቅም ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ የግል ባለሃብቱና መሬት ወስደው በማህበር ማልማት ለሚችሉ ዜጎች በዚህም ትርጉም ባለው መልኩ በከተማዋ የሚስተዋለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት መቅረፍ የሚያስችል አዋጅ ነው፡፡

የከተማው አስተዳደር በግል ባለሀብቶችና አቅም ባላቸው ልሎች ሰዎች በማህበርም ሆነ በተናጥል መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ ቦታ አዘጋጅቶ በማቅረብና አስፈላጊ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የከተማው ነዋሪዎች ከፍተኛ የመጠለያ ችግር ለመቅረፍ እየሠራ ያለ በመሆኑ፣

ከዚህም ጎን ለጎን የመንግሥትም ሆነ የግል ንብረት የሆኑና የመሠረት ልማት አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ የማያገኙ ቤቶችን ተክቶ ከተማውን መልሶ በማልማትና በከተማው ውስጥ ከድህነት መግለጫዎች መካከል አንዱ የሆነውን የአብዛኛዎቹን የከተማውን ነዋሪዎች ከፍተኛ የመጠለያ ችግር ትርጉም ባለው መልኩ በመቅረፍ ከተማውን ተስማሚ የመኖሪያና የሥራ ከባቢ እንዲሆን ለማድረግ የከተማው አስተዳደር የከተማው ነዋሪዎች ያኗኗር ደረጃና ፍላጎት ግምት ውስጥ አስገብቶ ባወጣው የቤት ልማት ፕሮግራም መሠረት ቤቶችን በመገንባት ላይ ያለ በመሆኑ፤

ፍትሐዊ፣ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጣ ውረድ በሌለው ቀላል በሆነ ሥነ-ሥርዓት፣ እንዲሁም የተጠቃሚዎችን የፆታ ተዋፅኦ በሚያረጋግጥና የገበያ አቅምን ግምት ውስጥ በሚያስገባ የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶች ለከተማው ነዋሪዎች የሚተላለፉበትና የቤት ባለቤት የሚሆኑበት አፈፃፀም መደንገግ አስፈላጊ ሆነ በመገኘቱ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬/፮/ሀ እና ፷፮/፪ መሠረት ጊዜያዊ አስተዳደሩ ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የከተማው አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩. "ቤት ፈላጊ " ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በከተማው አስተዳደር ቤት ያልተላለፈለት ሰው ሆኖ፣

ሀ) በዘህ አዋጅ አንቀጽ ፬ በተመለከተው መሰረት ማመልከቻ እስካቀረበበት ቀን ድረስ በአዲስአበባ ከተማ ውስጥ ቢያንስ ለ፪ ዓመት በተከታታይ የኖረና በከተማው ውስጥ የእራሱ የግል ቤት ወይም ቤት መሥሪያ ቦታ የለለለው ወይም

ለ) የግል መኖሪያ ቤቱ፣ የቤት መስሪያ ቦታው ወይም የተከራየው የመንግሥት ቤት በከተማው አስተዳዳደር የቤት ልማት ፕሮግራም ወይም በለሌላ የልማት ስራ ምክንያት የሚነሣበትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት ቤት ለመግዛት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውንም ሰው ሲሆን፣ በስራ ወይም በትምህርት ምክንያት ለጊዜው ከአዲስ አበባ ውጪ የሚኖር ሰውን ይጨምራል፡፡

፪. "ቤት"፣"የጋራ ህንፃ" እና "የጋራ መጠቀሚያ " በአዋጅ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

፫. "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጋራ ህንፃ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸/፲፱፻፺፭ ነው፡፡

፬. "ስቱድዮ" ማለት የግል መጸዳጃ ክፍልና ማዕድ ቤት በውስጡ ወይም ከውጪ እንስኖረው ተደርጎ የተሠራ እና የጋራ ሕንፃ አካል የሆነ ባለአንድ ክፍል የመኖሪያ ቤት ነው፡፡

፭.የመንግሥት ቤት ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማንኛውንም አካል ወይም በፌደራል መንግስት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ለቤት ፈላጊ የተከራየ በከተማው ውስጥ የሚገኝ ቤት ነው፡፡

፮. "የግንባታ ወጪ" ማለት የከተማው አስተዳደር ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚያገለግለውን ቤት ለመገንባት ብቻ ያወጣው ወይም የሚያወጣ ቀጥተኛ ወጪ ነው፡፡

፯. "ኤጀንሲ" ማለት የከተማው አስተዳደር የቤቶች ኤጀንሲ ነው፡፡

፰. "ጽሕፈት ቤት" ማለት የክፍለ ከተማ የመሠረተ ልማትና የቤቶች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ወይም በከተማው አስተዳደር የቤት ልማት ፕሮግራም የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶች አስተዳደርና የባለቤትነት ዝውውር ሥራዎችን ለማከናወን የተደራጅ የክፍለ ከተማም ሆነ የቀበሌው አስተዳደር አካል ነው፡፡

፱. "ማኅበር" ማለት በከተማ አቀፍ ደረጃ የተመሰረተ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ህብረት ወይም መሠረታዊ የብድርና ቁጠባ ኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም በክፍለ ከተማ አቀፍ ደረጃ የተመሰረተ የዕድሮች ኅብረት ወይም ማናቸውም ዕድር ነው፡፡

፲. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በቤት ልማት ፕሮግራም በሚገነቡ ቤቶች ተጠቃሚዎችና ከቤቶች አስተዳደር ጋር ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ቤት ፈላጊዎችን መመዝገብና የከተማው አስተዳደር ቤቶችን የማስተላለፍ አፈፃፀም

፬. የቤት ፈላጊዎችን ማመልከቻ ቅጽ ይዘትና አቀራረብ፣

፩. ማንኛውንም ቤት ፈላጊ

ሀ) አባል ከሆነበት ማህበር፣ ከጽህፈት ቤቱ፣ ከክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር ልማት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ወይም ከኤጀንሲው የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ ወስዶ በመሙላት የመኖሪያ ቤት በተከፋፈለ የረጅም ጊዜ ክፍያ ወይም በአንድ ጊዜ ክፍያ ወይም በአንድ ጊዜ ክፍያ ከከተማው አስተዳደር ለመግዛት እንደሚፈልግ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

ለ) ንግድ ቤት ለመግዛት ወይም ለመከራየት የሚፈልግ ከሆነ ደግሞ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ እንደተደነገገው በጨረታ ማስታወቂያ በሚገለፀው መሰረት አግባብነት ያለው የንግድ ቤት ግዢ ወይም የኪራይ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡

፪. ቤት ፈላጊ በመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መሙላት አለበት፡-

ሀ) ሙሉ ስሙን ከነአያቱና ፣ የመኖሪያና የሥራ አድራሻው፣

ለ) ያገባ ከሆነ የትዳር ጓደኛውን ሙል ስም ከነአያት፣

ሐ) በዚህ አዋጅ መሰረት ቀደም ብሎ በከተማው አስተዳደር ቤት ያልተላለፈለት መሆኑን፣

መ) በከተማው ውስጥ የግል መኖሪያ ቤት ወይም የቤት መሥሪያ ቦታ የሌለው መሆኑን፣

ሠ) በቤቶች ልማት ፕሮግራም ወይም በሌላ የልማት ሥራ ምክንያት በከተማው ውስጥ የሚገኝ በግል ቤቱን ወይም ቤት መስሪያ ቦታውን የሚለቅ መሆኑን፣

ረ) ማመልከቻ እስካቀረበበት ቀን ድረስ በተከታታይ በከተማው ውስጥ ቢያንስ ፪ ዓመት የኖረ መሆኑ፣ ካልኖረ ደግሞ ከከተማው ውጪ የኖረበትን የሥራ ወይም የትምህርት ሁኔታ እና የትና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ወይም እንደሚቆይ፣

ሰ) ለመግዛት የሚፈልገውን ቤት ዓይነትና የክፍል ብዛት፣ እንዲሁም ቤቱ የሚገኝበትን ክፍለ ከተማና ቀበሌ፣

ሸ) የገቢውን መጠንና ምንጭ፣

ቀ) የቤቱን ዋጋ በአንድ ጊዜ ወይም በተከፋፈለ የረጅም ጊዜ ክፍያ የሚከፍል መሆኑን፣ እንዲሁም የተከፋፈለ የረጅም ጊዜ ክፍያ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚህ አዋጅ መሰረት ቅድሚያ ክፍያ ለመክፈልና የተከፋፈለውን ክፍያ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ መሆኑን፣

በ) የገዛውን የመኖሪያ ቤት ከገዛበት ቀን አንስቶ በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት ውስጠ በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን የማያስተላልፍ መሆኑን፣

ተ) በአዋጅ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኑን፣

ቸ) የሚኖረው በመንግስት ቤት ከሆነ ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል የገዛውን ቤት በተረከበ በ ፴ ቀን ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኑን ፣ እና

ኀ) በማመልከቻው ቅጽ የሞላው ዝርዝር ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ ውል ተቋርጦ የገዛውን ቤት በመልቀቅ ለሻጬ ለማስረከብና ከከፈለው ገንዘብ ላይ ለቤቱ ዕድሳት የሚያስፈልገው ወጪና ለቆየበት ጊዜ በኤጀንሲው በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የኪራይ ተመን መሠረት በየወሩ የሚሰላ የኪራይ ዋጋ ተቀንሶ ቀሪው ብቻ እንዲመለስለት የሚፈቅድ መሆኑን

፫. ቤት ፈላጊው በማመልከቻ ቅጽ ላይ የሞላው ዝርዝር ዕውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

<u>፫. ቤት ፈላጊዎችን ማጣራትና መመዝገብ</u>

፩. በማንኛውንም ቤት ፈላጊ በማመልከቻ ቅጽ የሞላው ዝርዝር በከተማው አስተዳደር የመረጃ ማዕከል ካለው መረጃ ጋር እንዲገናዘብ በማድረግ፣ የግል መኖሪያ ቤት ወይም ቤት መስሪያ ቦታ እንደሌለው ፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት በእራሱ ስም ወይም በጋብቻ ውስጥ ያለ በትዳር ጓደኛው ስም የተገዛ የመኖሪያ ቤት እንደሌላው ይጣራል።

፪. በዚህ መሠረት በሚደረገው ማጣራት በከተማው ውስጥ የግል ቤት ወይም ቤት መሥሪያ ቦታ የሌላቸው፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሰረት የመኖሪያ ቤት ወይም ቤት መስሪያ ቦታ የሌላቸው፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሰረት የመኖሪያ ቤት ገዝተው የማያውቁ ቤት ፈላጊዎች ከተለዩ በኃላ እያንዳንዱ ቤት ፈላጊ በከተማው ውስጥ የግል ቤት ወይም ቤት መሥሪያ ቦታ የለኝም፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የመኖሪያ ቤት ገዝቼ አላውቅም ብሎ ቤት እንዲሸጥለት ማመልከቱን በመግለፅ በሚከተለው መሠረት ተጨማሪ ማጣሪያ ያደርጋል፡-

ሀ) ቤት ፈላጊው በሚኖርበትና ማመልከቻ ቅጽ በሞላበት ቀበሌ ነዋሪዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ለ፲ ቀናት በማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ ለጥፎ ከሚገኘው መረጃ ጋር በማገናዘብ።

ለ) ቤት ፈላጊው ማመልከቻ ቅጽ በሞላበትና አባል በሆነበት ማኅበር ሌሎች አባላት አስተያየት/ጥቆማ/ ካላቸው እንዲያቀርቡ፣ ስሙ በማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረግና ለ፲ ቀን ለጥፎ በማቆየት የሚገኘውን መረጃ በማገናዘብ፡፡

፫. ቤት ፈላጊው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፩/ እና/፪/ በተመለከተው መሰረት በሚደረገው ማጣራት በማመልከቻው ቅጽ የሞላው ዝርዝር ትክክለኛ መሆኑ ሲረጋገጥ

ሀ) በኤጀንሲው በሚወሰነው መሠረት ከከተማው አስተዳደር ቤት ለመግዛት ባመለከቱ ቤት ፈላጊዎች መዝገብ በጽሕፈት ቤቱ ይመዘገባል።

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ/፯/ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት የመኖሪያ ቤት የመግዛት መብት ያገኛል፣ ይኸው ተገልፆ በጽህፈት ቤቱ የማስታወቂያ ሠሌዳ ስሙ ይፋ ይሆናል፡፡

፯. የቅድሚያ አወሳሰን

ኤጀንሲው ከከተማው አስተዳደር የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሚረከባቸውንና ቀደም ሲል የተረከባቸውን የከተማውን አሰደተዳደር ቤቶች ብዛት መሰረት በማድረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ/፫/ መሠረት ከተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች መካከል።

፩. ከክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት በሚገኝ መረጃ መነሻ በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው መሰረት በልማት ምክንያት ለሚነሱ ቤት ፈላጊዎች የተወሰነ የቤቶች ድርሻ በልዩ ሁኔታ ተይዞላቸው ቤቶችን የመግዛት ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቤት ፈላጊዎች ብዛት ለሽያጭ ከቀረቡት ቤቶች የሚያንስበት ጊዜ በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ/፫/ መሠረት የተመዘገቡ ሌሎች ቤት ፈላጊዎች የመግዛት መብት ያገኛል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ የተመለከተው ቢኖርም፣ የከተማው ካቢኔ ወይም የከተማው ከንቲባ የሚወስናቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ ቤት ፈላጊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተመለከተውን ሥነ - ሥርዓት መከተል ሳያስፈልግ ቤት የመግዛት ልዩ ቅድሚያ ያገኛል፣

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፤/ ከተመለከቱት ቤት ፈላጊዎች መካከል፡-

ሀ) እስከ ፫፻ ብር ገቢ ያላቸው ቤት ፈላጊዎች ለስቱዲዮ።

ለ) ከ፫0፩ እስከ ፮፻ ብር ገቢ ያላቸው ቤት ፈላጊዎች ደግሞ ከ፴ ካ.ሜ በታች የቆዳ ስፋት ላለው ባለአንድ መኝታ የመኖሪያ ቤት፣ የቅድሚያ ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፬/ መሠረት በቅድሚያ ቅድሚያ መብት ተጠቃሚ ከሚሆኑ ቤት ፈላጊዎች መካከል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሰረት የተመዘገቡ እስከ ሆኑ ድረስ ቢያንስ ፴% እማወራዎች ይሆናል፣

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፬/ መሠረት በቅድሚያ ቅድሚያ መብት ተጠቃሚ ከመሆኑ ቤት ፈላጊዎች መካከል በዚህ አወጅ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ/፫/ መሰረት የተመዘገቡ እስከ ሆኑ ድረስ ቢያንስ ፴% እማወራዎች ይሆናል፣

፯. የእንቅስቃሴ አካል ጉዳተኛ የሆነ ቤት ፈላጊ እንደ የአግባቡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፩/ እስከ /፮/ የተደነገገው እስካሟላ ድረስ ምርጫው እንደተጠበቀ ሆኖ ተደራሽ በሆነው የህንፃው ወለል ላይ የሚገኝ ቤት የመግዛት የቅድሚያ ቅድሚያ መብት ያገኛል፡፡

፰. ማናቸውንም ማኀበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ/፩/ እንደተመለከተው ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ በአንድ ጊዜ ከፍሎ የሚገዛቸውና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፬/ እስከ /፯/ በተደነገገው መሰረት ለቤት ፈላጊ አባላቱ የሚያከፋፍላቸው የተወሰኑ ቤቶች ለላመደቡለት ይችላል፡፡

<u>፯. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር</u>

ኤጀንሲው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፰ /እንደተሻሻለ/ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ።

፩. ኤጀንሲው የተገነቡ ወይም በግንባታ ላይ ያሉ ቤቶች አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ከከተማው አስተዳደር የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት በመረከብ

ሀ) ቀደም ሲል ከሚያስተዳድራቸው የከተማው አስተዳደር ቤቶች ጋር አዳምሮ በዝርዝር ይመዘግባል፣ ወይም ጽሕፈት ቤቱ ተረክቦ እንዲመዘግብ ያደርጋል፣

ለ) ዓይነታቸውን በስቱዲዮ፣ ከ፴ ካ.ሜ በታች የቆዳ ስፋት ባለው በባለአንድ መኝታ ክፍል ከ፴ ካ.ሜ በላይ የቆዳ ስፋት ባለው በባለአንድ መኝታ ክፍል ፣ በባለሁለት መኝታ ክፍል፣ በባለሶስተኛና በባለአራት መኝታ ክፍል፣ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ክፍል መኖሪያ ቤቶችና በንግድ ቤቶች ለያይቶ በመመዘገብ ለሽያጭ ያዘጋጃል፣ ወይም በጽሕፈት ቤቱ እንስዘጋጅ ያደርጋል፣ ያስተዋውቃል።

፪. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) መሰረት የተረከባቸውን ቤቶች ከመሸጡ በፊት በአዋጅ መሰረት በባለቤቶች ማሕበር እንስተዳደር አስፈላጊውን አሟልቶ ያስመዘግባል. በጽሐፈት ቤቱ ወይም ውክልና በሰጠው ለልላ አካል አማካኝነት አስፈላጊውን ተሟልቶ እንስመዘገቡ ያደርጋል፡፡

<u>፫. ኤጀንሲው</u>

ሀ) በተለያዩ የገቢ ደረጃዎች የሚገኙ ቤት ፈላጊዎች በብዛት ጥንቀር ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ያደራጃል፣ ወይም በየክፍለ ከተማው እንዲደራጅ ያደርጋል፣

ለ) ለመረጃው አሰባሰብ እንስረዳም የቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅፅ በማዘጋጀት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፩ / ለተመለከቱት አካላት ያስተላልፋል፡፡

፬. ኤጀንሲው ከተለያዩ አካላት ያሰባሰበውን የቤት ፈላጊዎችን ብዛትና ጥንቅር እንዲሁም የተገነቡና በመገንባት ላይ ያሉ ቤቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ለቤት ፈላጊዎች ለላከፋፈል ስለሚገባው ድርሻና የመምረጫ መስፈርቶችን አስመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ በየጊዜው እያዘጋጀ ለከተማው ከንቲባ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ወይም እንደየግባቡ ለጽሕፈት ቤቱ በማስተላለፍ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፣

፭. ኤጀንሲውን ቤት ፈላጊዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት በአግባቡ መመዝገባቸውን ያረጋግጣል፣

፮. ኤጀንሲው

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ አንቀጽ/፪/ እና /፫/ የተመለከቱትን ሁኔታዎች አካትቶ መኖሪያ ቤት ለቤት ፈላጊ የሚተላለፍበት ናሙና ውል ያዘጋጃል፣

ለ) ዕጣ አውጥቶ የሚገዛውን ቤት ከለየ ቤት ፈላጊ ጋር ባዘጋጀው ውል መሰረት እንስፈራረም ለጽሕፈት ቤቱ ወይም በሚፈረም መሰረታዊ ውል መሰረት ለለልላ አግባብ ላለው አካል ውክልና ይሰጣል፣

ሐ) በሚሰጠው ውክልናም ውል ባፈረሰ ቤት ገገር ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ በተመለከተው መሠረት ተወካዩ ተገቢውን እርምጃ እንስወስድ መፍቀድ ይችላል፣ ተወካዩን ውልን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋልን ያረጋግጣል፣

መ) ቤት ገዥዎች በፈረሙት ውል መሠረት እንደየአግባቡ ቅድሚያ ክፍያ ወይም ጠቅላላ ዋጋ በአንድ ጊዜ እንዲከፍልና የገዙትን ቤት እንዲረከቡ ያደርጋል፣

ሠ) የንግድ ቤት ለመግዛት ወይም ለመከራየት በጨረታ ተወዳድሮ ካሸነፈ ማንኛውንም ቤት ፈላጊ ጋር እንደየ አግባቡ ናሙና የቤት ሽያጭ ወይም የኪራይ ውል በማዘጋጀት ቤቱ የሚገኝበት ጽሕፈት ቤት እንዲፈረም ውክልና ይሰጣል፣ የተከራዩ ንግድ ቤቶችንም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፮ በተደነገገው መሠረት መተዳደራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፯. ማናቸውም ቤት ገዢ በውል መሰረት ክፍያውን ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ ስገዛው በታች ባለሀብትነት ምስክር ወረቀት እንደየአግባቡ በክፍለ ከተማ |የመሬት ልማትና አሰተዳደር ጽህፈት ቤት ወይም በሚመለከተው ጽ\ህፈትቤት እንዲሰጠው ያደርጋል መስጠቱንም ይከታተላል

፰. በጋራ መጠቀሚያ በአዋጁ መሰረት ለተመዘገበ የባለቤቶች ማህበር ወይም ለንግድ ማህበር በሽያጭ መተላለፉንና አገልግሎቱን ሳይለውጥ ስራ ላይ መዋልን ያረጋግጣል፡፡

፱. ቅድሚያ ክፍያና ቀሪ ክፍያ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሠረት በደረሰኝ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፣ ይህንንም እንደአግባቡ እራሱ ተዋውሎ የሸጠውን ወይም ያከራየውን ቤት ክፍያ በመቀበል ወይም ገገሮች ክፍያ የሚፈፅሙበት አበዳሪ ተቋም ወይም ለሌላ አግባብ ያለው አካል በመወከል ያስፈጽማል፣

፲. በማናቸውም ቤት ገገር በዘህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ በተደነገገው መሠረት ውል ማፍረሱን ሲያረጋግጥ፣

ሀ) ውልን በማቋረጥ ከተረከበው ቤት እንዲለቅ ያደርጋል፣ ወይም ውክልና በመስጠት እንዲፈፅም ያደርጋል፣ ይህንኑ ለማስፈጸም እንደአስፈላጊነቱ ፖሊስን ማዘዝ ይችላል፣

ለ) ከከፈለው ገንዘብ ላይ ለቤቱ ዕድሳት የሚደስፈልገው ወጪ ለማቆየት ጊዜ በኤጀንሲው በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የኪራይ ተመን መሠረት በየወሩ የሚሰላ የኪራይ ዋጋ ተቀንሶ ቀሪውን ብቻ እንዲመለስለት ያደርጋል፣ ወይም መደረጉን ያረጋግጣል፣

ሐ) ቤቱ እንደተለቀቀ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ በተደነገገው የቅድሚያ አወሳሰን መሠረት ለሌላ ቤት ፈላጊ ውል ፈርሞ እንዲተካ ያደርጋል፣ ወይም መተካቱን ያረጋግጣል፣

፲፩. ቤት ገገር ቅድሚያ ክፍያ ፈጽሞ የቤት ሽያጭ ውል ከተፈራረመ በኃላ ለአበዳሪ ተቋም በዋስትና በማስያዝ ቤት ለመግዛት እንደሚፈልግና ኤጀንሲው ለተቋሙ የቤቱን ግምት እንስያሳቅቅለት በማመልከቻ ሲጠይቅ፣ የተጠየቀው አካል ተቋሙ ቤቱን በዋስትና ይዞ ለገገሩ የቤቱን ቀሪ ገንዘብ የሚያበድረው ከሆነ የቤቱ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት በዋስትና መያዣ ውል መሰረት እንስያዝ እንደሚያስተላልፍ ወይም እንዲተላለፍ እንደሚያደርግ ገልፆ ለተቋሙና ለገገሩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

## <u>፳. የክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር</u>

የክፍለ ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት

፩. በከተማው አስተዳደር የቤት ልማት ፕሮግራም ከመኖሪያ ቦታቸው የሚነሱ የከተማውን ነዋሪዎች ማኀበራዊና ኤኮኖሚያዊ አቋም የሚያመለክቱ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፣

፪. ምትክ ቦታና የገንዘብ ካሳ ፣ ወይም ምትክ ቤት ወይም የገንዘብ ካሣ ብቻ እንስከፈላቸው የሚፈልጉ፣ ቤት መግዛት የማይፈልጉ ተነሺ ከመኖሪያ ቦታቸው የሚነሱ ሰዎች ማመልከቻ ቅጽ በማስሞላትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ መሠረት በማጣራት መዝግቦ ዝርዝራቸውን ለኤጀንሲው ያስተላልፋል፡፡

፫. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኤጀንሲው ወይም እንደሁኔታው በጽሕፈት ቤቱ ሲጠየቅ በዚህ አዋጅ መሠረት ቤት ለገዛ ሰው የቤት ባለሃብትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ይሰጣል፣

፬. ኤጀንሲው ወይም እንደሁኔታው ጽሕፈት ቤቱ ከቤት ፈላጊ ጋር በሚፈራረሙ የቤት መሸጫ ውል መነሻ የቤት ባለሃብነት ምዝገብ ምስክር ወረቀት ለአበዳሪ ተቋም እንዲተላለፍና በዋስትና እንዲያዝ ሲጠይቀው ምስክር ወረቀቱን አዘጋጅቶ ለተቋሙ ያስተላልፋል፣ ለፈላጊውን ከተቋሙ ሲበደርም ከተቋሙ ጋር በተፈራረሙት ውል መሰረት የዋስትና መያዣ ውል ሲተላለፍለት ተቀብሎ ይመዘግባል።

፭. ለገዢ በሚሰጠው የቤት ባለሃብነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ላይ "እስከ አምስት ዓመት በሽያጭ ወይም በስጦታ አይተላለፍም፡፡" የሚል መግለጫ ይፃፍበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ፣ እንዲሁም የግንባታ ወጪ ስለልትና አሸፋፈን

፱. ቅድሚያ ክፍያ መጠን፣ እንዲሁም የቀሪ ክፍያና የችረሬታ ጊዜ

፩.ቅድሚያ ክፍያ ቤት ገዢ ውል ከመፈረሙ በፊት የሚከፍለው የቤቱ ጠቅላላ ዋጋ አካል የሆነ የተወሰነ መቶኛ የመጀመሪያ ክፍያ ሆኖ፣

ሀ) እንደየቤቱ ዓይነትና መጠን ከዚህ በታች ባለው መሠረት ቅድሚያ ክፍያ ይከፈላል፦

፩. ለስቱድዮ ፡- ፯.፭%።

፪. ለባለአንድ መኝታ ቤት ፡-10%

፫. ለባለ ሁለት መኝታ ቤት ፡-20% እና

፬. ከሁለት በላይ መኝታ ክፍሎች ላት ቤት፡-30%፡፡

ለ) በየጊዜው ለሚገነቡና በዚህ አዋጅ መሰረት ለቤት ፈላጊዎች ለሚሸጡ ቤቶች በቤቶች ኤጀንሲ በሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በከተማው ካቢኒ በሚወጣ ደንብ ለየቤቱ ዓይነት የሚከፈለው የቅድሚያ ክፍያ መጠን ለላለወጥ ይችላል፡፡

፪. ቅድሚያ ክፍያ ከተከፈለ በኃላ ቀሪው የቤቱ ዋጋ እንደቤቱ ዓይነትና መጠን በማንኛውም ቤት ገዢ በየወሩ መከፈል እንደተጠናቀ ሆኖ የስቱድዮ ወይም የአንድ መኝታ ክፍለ ቤት ገዢ ቤቱን ከተረከበበት ቀን በኋላ የተሰጠውን የችረሬታ ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን የሚቀጥለውን የስራ ቀን መነሻ በማድረግ በሚከተለው የጊዜ ወሠን መሠረት ይከፈላል፦

ሀ) ለስቱድዮ እስከ ፳ ዓመት፣

ለ) ለባለአንድ መኝታ ቤት እስከ ፳ ዓመት፣

ሐ) ለባለ ሁለት መኝታ ቤት እስከ ፲፭ ዓመት

መ) ከሁለት በላይ መኝታ ክፍሎች ላልት ቤት እስከ ፲ ዓመት፡፡

፫. የቤቱን ዋጋ በተከፋፈለ ተከታታይ የረጅም ጊዜ ክፍያ ለመክፈል የተዋዋለ የስቱድዮና የባለአንድ መኝታ ቤት ገዢ እንደቤቱ ዓይነትና መጠን ቤቱን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ክፍያ መጀመሪያ የችረሬታ ጊዜ በሚከተለው መሠረት ይሰጠዋል፡-

ሀ) ለስቱድዮ እስከ ፯ ወር፣

ለ) ለማናቸውንም ባለ አንድ መኝታ ቤት እስከ ፫ ወር፡፡

<u>፤. ስለ ክፍያ አፈፃፀም</u>

፩. የቤቱን ጠቅላላ ዋጋ በአንድ ጊዜ በመክፈል ቤት ለመግዛት የተዋዋለ ገዢ ክፍያውን እንደፈፀመ በውል የተመለከተውን ቤት ከተዋዋለው አካል ይረከባል፣ ገዢው ማኅበር በሚሆንበት ጊዜም ማኅበሩ 100% ክፍያ ፈፅሞ ለአባላቱ እንዲያከፋፈል ውል የሚፈርም ሲሆን ማኅበሩ ለዚህ ግልጋሎቱ በቤቶች ኤጀንሲ በሚቀርብ የውሳኔ ሀሣብ መሠረት በከንቲባው የሚወሰን የአገልግሎት ክፍያ ሊያስብ ይችላል፡፡

፪. በተከፋፈለ ተከታታይ የረጅም ጊዜ ክፍያ ቤት የገዛ ሰው፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፩/ እንደተመለከተው ለኤጀንሲው ወይም ኤጀንሲው ለሚወክለው አካል ቅድሚያ ክፍያ መክፈል ሲታወቅ የገዛውን ቤት እንዲረከብ ይደረጋል፣ ይረከባል

ለ) ወርሃዊ ክፍያውን በውል መሠረት ለኤጀንሲው ወይም ኤጀንሲው ለሚወክለው ለሌላ አካል ይፈፀማል፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተመለከተው ቢኖርም፣ ገዢው ግንባታ ከመጀመሪ ወይም ግንባታው ከመጠናቀቁ በፊት ውል ተዋውሎ ለገዛው ቤት ጠቅላላ ዋጋ ወይም ቅድሚያ ክፍያ ሊከፍል ይችላል፣

መ) ለሚገዛው ቤት ጠቅላላ ዋጋ ወይም በአንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከተወሰነው የተሻለ ቅድሚያ ክፍያ የሚፈጽም ገዢ እንደ አስፈላጊነቱ የግገር ቅድሚያ ሰጠው ወይም በመረጠው ሕንፃና/ወይም ወለል ላይ ቤት የመግዛት ቅድሚያ ለላያገኝ ይችላል፡፡

፫. ገዢው የተላለፈለት መኖሪያ ቤት ወይም ንግድ ቤት የሚገኝበት ሕንፃና የጋራ መጠቀሚያ ህንፃ ለቤት ባለቤቶች ማኅበር የተሸጠ እንደሆነ የግዢ ዋጋና የመድህን ዋስትና በቤቱ ድርሻ መጠን ይከፍላል፡፡ እንደዚሁም የጋራ መጠቀሚያ ሕንፃውን የቤት ባለቤቶች ማኅበር ከኤጀንሲው ወይም ከጽ/ቤቱ ከገዛ የንግድ ማኅበር በሚከራይበት ጊዜ በገዛው ቤት ድርሻ መጠን ወርሃዊ የኪራይ ዋጋ ለባለንብረቱ ይከፍላል፡፡

፬. ገዢው ከአበዳሪ ተቋም ተበድሮ ቤት በሚገባበት ጊዜ የቤት ባለሃብትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት በተቋሙ ለዋስትና እንስያዝ ፈቃደኛ እንደሆነ መግለጽ የቤቱ ግምት ተገልፆ ለተቋሙ እንስተላለፍለት በማመልከቻ ኤጀንሲውን መጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ገዢው

በማንኛውም መንገድ ዕዳውን መክፈል ቢያቋርጥ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፯/፩፱፺ /እንደተሻሻለ/ የተደነገገውን በመጠቀም ተቋሙ በሚያሳውቀው መሰረት እንደየአግባቡ ኤጀንሲው ወይም ጽ/ቤቱ ለልላ ገዢ እንስተካና የተቋሙ መብት እንስጠበቅ ያደርጋል፡፡

<u>፲፩. የወለድ መጠንና አከፋፈል</u>

፩. ስቱድዮ የገዛ ከወለድ ነፃ ሆኖ፣ ለልላ ዓይነት መኖሪያ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት በተከፋፈለ ተከታታይ የረጅም ጊዜ ክፍያ የገዛ ሰው ግን በሚከተለው ተመን መሠረት ወለድ ይከፍላል፡

ሀ) ለባለአንድ መኝታ ቤት፡-፪%፣

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ/ሀ/ ከተጠቀሰው በላይ መኝታ ክፍል ያላቸው ሌሎች ቤቶች - ፰.፺፭%፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ለ/ የተመለከተው ቢኖርም፣ የከተማው ካቢኔ ባለአንድ መኝታ ክፍል የመኖሪያ ቤትን የተወሰነ ካሬ ሜትር ስፋት መነሻ በማድረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩/ሐ/ መሠረት ለያይቶ በሚወስንበት ጊዜ የወለድ መጠኑን በተመሳሳይ መልኩ መወሰን ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም፣ በተከፋፈለ ተከታታይ የረጅም ጊዜ ክፍያ መኖሪያ ቤት የሚገዛ ሰው የሚከፍለው የወለድ መጠን አስቀድሞ የገዙ ሰዎችን ሳይጨምር በባንክ የወለድ መጣኔ መሠረት በየጊዜው እንዲስተካከል በከተማው ካቢኔ እንደየአግባቡ ሊወሰን ይችላል፡፡

<u>፲፪. የውጪ ስልትና አሸፋፈን</u>

፩. ቤቶች ከፎቅ ወደ ፎቅ የተለያዩ የሽያጭ ዋጋ ሊኖራቸው መቻል እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ቤት የሚሸጥበት ዋጋ የሚወሰነው የግንባታ ወጪና የቤቱና የቤቱ አካባቢ የውስጥ ለውስጥ መሠረት ልማት ወጪዎች፣ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡ ሆኖም የአካባቢውን ዋና ዋና የመሠረተ ልማት መስመሮችን ከቤቱና ከህንፃው የውስጥ ለውስጥ መስመሮች ጋር ለማገናኘት የሚያስፈልጉት የመሠረተ ልማት ወጪዎች በከተማው አስተዳደር ይሸፈናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፩/ የተደነገገው ቢኖርም፣ እንደአስፈላጊነቱ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ገዥዎች የተሻለ ገቢ ባላቸው ገዥዎች ለማደጓጎም በሚያስችል መልኩ የግንባታ ወጪ እየሠላ በከተማው ካቢኔ ሊወሰን ይችላል፡፡

፫. ንግድ ቤቶች በሚቀመጥላቸው መነሻ ዋጋ መሠረት በጨረታ የሚሸጡ ወይም የሚከራዩ ሆነው የሚቀመጥላቸው የመነሻ ዋጋ የግንባታ ወጪያቸውን ለመሸፈንና የመኖሪያ ቤቶችን የግንባታ ወጪ ለመደጎም በሚያስችል መልኩ እየተሰላ በከተማው ካቢኔ ይወሰናል፡፡

፬.በአዋጅ፣ በጋራ ህንጻ ደንብና መመሪያ የተደነገጉት የጋራ ወጪዎች በሙል በገዥዎች ይሸፈናል፡፡

## ክፍል አራት

## የገዢዎች መብትና ግዴታ ፣ለሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዮች

**፲፫. በመንግስት ቤት የሚኖር ገዢ ግዴታ**

ገዢው በመንግስት ቤት የሚኖር ከሆነ፣ የገዛውን ቤት በተረከበ በ ፴ ቀን ውስጥ የመንግሥት ቤቱን ለባለንብረቱ ማስረከብ አለበት፣

**፲፬. ክፍያ ያጠናቀቀ ገዢ የመብትና ግዴታ**

፩. በተከፋፈለ ተከታታይ ክፍያ ቤት ገዝቶ ዋጋውን ከፍሎ ያጠናቀቀ ገዥ የቤቱን የባለሀብትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ከኤጀንሲው ወይም ውክልና የሚሰጠው አካል ወይም ምሰክር ወረቀቱን በዋስትና ከያዘው አካል መውሰድ የሚችልበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

፪. ገዢው ጠቅላላ ዋጋውን ከፍሎ ቢያጠናቅቅም፣ ቤቱን ለሦስተኛ ወገን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ የሚችለው ቤቱን ከገዛ ፭ ዓመት ሲሞላው ብቻ ይሆናል። ፭ ዓመት የሞላው የቤት ባለሀብትነት የምስክር ወረቀት መያዝ የቤቱ ዋጋ ተከፍሎ ስለመጠናቀቁ አስረጂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ገዢው ፭ ዓመት መሙላቱን እና ክፍያ ማጠናቀቁን በኤጀንሲው ወይም በጽ/ቤቱ የሚሰጠውን ማስረጃ የሚመለከተው ሁል በማቅረብ ማረጋገጥ ይችላል፡፡

**፲፭. የወራሾች መብት**

ገዢ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ፡-

፩. መብቶቹን ግዴታዎቹ ለወራሹ/ሾቹ በህግ መሠረት ይተላለፋል፣

፪. ገዢው በሞተበት ጊዜ በቤቱ ውስጥ ያልተ የቤተሰቡ አባላት የወራሽነት ማስረጃ እስኪያመጡ ድረስ ለ፮ ተከታታይ ወራት ወርሃዊ ክፍያ በገዢው ስም እየከፈሉ መቆየት ይችላል፡፡

**፲፮. ውል ስለማቋረጥ**

፩. ከዘሀ አዋጅ መሰረት ቤት የሸጠ ማንኛውንም አካል ገዢው ከሚከተልት ሁኔታዎች አንዱ መፈጸሙን ሲያረጋግጥ የቤት ሽያጭ ውልን ያቋርጣል፡፡

ሀ) ወርሃዊ ክፍያ ለ፫ ተከታታይ ወራት ካልፈፀመ፣ ወይም

ለ) በአንድ ዓመት ውስጥ በድምሩ ለ፮ ጊዜ ወርሃዊ ክፍያ ካልፈፀመ፣ ወይም

ሐ) የገባውን መኖሪያ ቤት ፫ ዓመት ሣይሞላው በሽያጭ ወይም በስጦታ ካስተላለፈ ፣ ወይም

መ) የገዛውን መኖሪያ ቤት በተረከበ በ፴ ቀን ውስጥ የተከራየውን የመንግሥት ቤት ለሚያስተዳድረው አካል ካለስረከበ፣ ወይም

ሠ) የግል መኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እያለው የለኝም ፣ ወይም ደግሞ ቀደም ሲል በዚህ አዋጅ መሠረት ቤት ከኤጀንሲው ወይም ከጽ/ቤቱ በእራሱ ስምም ሆነ በጋብቻ ውስጥ እያል በትዳር ጓደኛው ስም አልገዛሁም ብሎ የቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽ የሞላው ሀሰት ሆኖ ሲገኝ ወይም

ረ) በከተማው ውስጠ ቢያንስ ለ፪ ዓመት ኖሬአለሁ ብሎ በማመልከቻ ቅጽ የሞለው ቃል ሀሰተኛው ሆኖ ሲገኝ፡፡

፪. ቤቱን የሸጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው ምክንያት ውል እንዳቋረጠ በመግለፅ ቤቱን የሚለቅበትን ጊዜ በጽሁፍ በሚያስታውቀው መሠረት ገዢው።

ሀ) የገዛው ቤት ለኤጀንሲው ወይም ኤጀንሲው ለወከለው አካል ያስረክባል፣ በተወሰነው ጊዜ ካላስረከበም በፓለላስ ተገድዶ ቤተን እንስያስረክብ ያደረጋል፣

ለ) ከከፈለው ገንዘብ ላይ ለቤቱ ዕድሣት የሚያስፈልገው ወጪና ለቆየበት ጊዜ በኤጀንሲው በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የኪራይ ተምን መሠረት በየወሩ የሚሰላ የኪራይ ዋጋ ተቀንሶ ቀሪውን ያለወለድ ይመለስለታል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/፩/ /ሐ/ እስከ /ረ/ የተመለከተውን ማናቸውንም ሁኔታ የፈጸመ ቤት ገደገር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፲፯. የሊዝ ክፍያ

፩. በቤት ልማት ፕሮግራም አማካኝነት የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ቤቶች ገገርዎች በጋራ ይዞታነት የሚጠቀሙበት መሬት በለላዝ ህግ መሠረት ተዳደራል፡፡

፪. ገገርዎቹ በህግ መሠረት ዓመታዊ የመኖሪያ ቤት የመሬት ለላዝ ክፍያ እና የህንፃ ታክስ ይከፍላል፡፡

## ፲፰. አቤቱታ የማቅረብ መብትና አወሳሰን

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሠረት በተደረገው ማጣራት በቤት ፈላጊነት እንዳልመዘገብ ተደርጌአለሁ የሚል፣ ወይም በአንቀጽ ፮ የተደነገገው የቅድሚያ መብት አልተጠበቀልኝመ የሚል ወይም ውል ያለአግባብ ፈረሰብኝ የሚል አቤቱታ አቅራቢ ለመግዛት ያመለከተው ወይም የገዛው ቤት በሚገኝበት ክፍል ከተማ ለሚሠየም ቅሬት አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ማቅረብና የመጨረሻ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

፪.ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ የሚሰየም ሆኖ ሦስት አባላት ይኖሩታል፡፡

፫.ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው አቤቱታ በቀረበለት ከ፩ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬.ከሚቴው የቀረበለትን አቤቱታ ለማጣራት ማናቸውንም ሰነድ ወይም ምስክር በትዕዛዝ ማስቀረብና መመርመር ይችላል፡፡

፭. ኮሚቴው ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ መሠረት ያሳውቃል፡፡

፮.በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኮሚቴው ስብሰባ ሥነ-ስርዓትና ዝርዝር አሠራር በከተማው ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሠናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፱. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውንም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፳. ቅጣት

ይህን አዋጅ የጣሰ ማንኛውም ሰው በሀገሪቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል

### ፳፩. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውንም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### ፳፪. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የከተማው ካቢኔ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

### ፳፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአዲስነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምረሬ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት ደንብ ፲፪/፲፱፻፺፰አጭር መግለጫ

በከተሞች ያለውን የቤት አቅርቦትና የቤት ፍላጎት አለመጣጣም ለመቀነስ የከተማ ቦታን በግል ከመሸንሸን በተ ጨማሪ ሌሎች የከተማ ቦታ አማራች አጠቃቀሞችን ጎን ለጎን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጲያ ፌድራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥ ር ፫፻፸/፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ያወጣ በመሆኑ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ እንዲያወጣ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ለ ከተማ አስተዳደር ስልጣን የተሰጠ በመሆኑ የወጣ ህግ ነው፡፡

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የጋራ ህንጻ ምዝገባ

# <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት ደንብ ፲፪/፲፱፻፺፯</u>

በከተሞች ያለውን የቤት አቅርቦትና የቤት ፍላጎት አለመጣጣም ለመቀነስ የከተማ ቦታን በግል ከመሸንሸን በተ ጨማሪ ሌሎች የከተማ ቦታ አማራች አጠቃቀሞችን ጎን ለጎን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጲያ ፌድራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥ ር ፫፻፸/፲፱፻፺፮ ዓ.ም. ያወጣ በመሆኑ፣

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ እንዲያወጣ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ለከተማ አስተዳደር ስልጣን የተሰጠ በመሆኑ፣

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ቁጥ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬ /፪/ለ እና በጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት አ ዋጅ ቁጥር ፫፻፸/፲፱፻፺፮ ዓ.ም. አንቀጽ ፵፪ መሰረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርየጋራ ህንጻቤት ባለቤትነት ደንብቁጥር ፲፪/፲፱፻፺፯ (፺ዓ.ም.›› ተ ብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. “የጋራ ህንጻ” ማለት በግል ባለቤትነት የሚያዙ አምስትነሰ ከአምስት በላይ ቤቶች እና በጋራ ባለቤትነት የ ሚያዙ የጋራመጠቀሚያዎች ያሉት ከመሬት ወደ ላይ ወይም ወደ ጎን ለጎን የተሠራ ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎትየሚውልግንባታ ሲሆን ሕንጻውያረፈበትን የቦታ ይዞታ ይጨምራል፤

፪. “የጋራ መጠቀሚያ” ማት በተናጠል ከተያዙት ቤቶች ውጭ ያለ ማናቸውም የሕንፃው አካል ነው፤

፫. “የጋራ ወጪ” ማለት የባለቤቶች ማህበርን ዓላማ እና ግዴታ ለማስፈጸም የሚደረግ ማናቸውም ወጪ እ ንደዚሁም በሕንጻ ማስታወቂያ የጋራ ወጪ ተብሎ የተጠቀሰው ወጪ ነው፡፡

፬. “የጋራ ትርፍ” ማለት የባለቤቶች ማበር ከሚሰበስበው ገቢ ላይ ወጪው ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት ነው፤

፭. “የጋራ ባለቤቶች ማህበር” ማለት በአዋጁ መሰረት የተቋቋመ የጋራ የሕንጻ ቤቶች ባለቤቶች ማህበር ነው ፤

፮. “የሕንጻ ማስታወቂያ” ማለት የቤት ባለቤቶች ማህበርን እናየእያንዳንዱን የቤት ባለቤት መብትና ግዴታ የሚወስን ሠነድ ሲሆን ማንቸውም የሕንጻ ማሻሻያን ይጨምራል፤

፯. “የሕንጻ መግለጫ” ማለት የጋራ ሕንጻውን አድራሻ፣ የቤቶችንና የጋራ መጠቀሚያ ወሰኖች እንደዚሁም ከጋራ ሕንጻው አንጻር

የጋራ መጠቀመ፣ያዎችና እያንዳንዱ ቤት የሚገኝበትን

ትክክለኛ ቦታ የሚያሳይ ሠነድ ሲሆን ማናቸውም የሕንጻ መግለጫ ማሻሻያን ይጨምራል፤

፰. “ቤት” ማት በሕንጻ ማሳወቂያ እና መግለጫ ለአንድ የተወሰነ

አገልግሎት የተመደበ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች

ያሉት የሕንጻው አካል ነው፡፡

፱. “ባለሥልጣን” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ነው፤

፲. “ለተወሰነ ቤት የተመደበ የጋራ መጠቀሚያ” ማለት ከጋራመጠቀሚያ ውስጥ ለተወሰነ ወይም ለተወሰኑ ቤቶች አገልግሎት የተመደበ የሕንጻው አካል ነው፤

፲፩.“አስመዝጋቢ” ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፬ ሕንጻ ያስመዘገበ ሰው ነው፤

፲፪. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው

፲፫. “አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፲፬. “አዋጅ” ማለት የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸/፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ነው፤

፲፭. “ማኅበር” ማለት በአዋጁ መሰረት የሚቋቋም የቤት ባለቤቶች ማኅበር ነው፤

፲፮. “መዝጋቢ አካል” ማለት በአዋጁ መሠረት የምዝገባ ተግባር ለማከናወን የሚሰየም አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

፫. <u>የጋራ ህንጻ ምዝገባ</u>

፩. በአዋጁ መሠረት ለማስመዝገብ የሚፈልግ አስመዝጋቢ ሕንጻው እንዲመዘገብ የሚጠይቅ የጽሁፍ ለመዝጋቢው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

፪. ሕንጻ ለማስመዝገብ የሚችለው ከሚከተሉት አንዱ መሆን አለበት፡-

ሀ)ሕንጻውን በባለቤትነት የያዘ ሰው ወይምሕንጻውን ለማስመዝገብ ልዩ ውክልና የተሰጠው ሰው፤

ለ) በአዋጁ መሠረት የጋራ ህንጻ ለመስራት በተቋቋመ የኅብረት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤

፫. በአዋጁአንቀጽ ፬ እና አንቀጽ ፭ የተመለከተውን የጋራሕንጻ ምዝገባ የሚያከናውነውና የምስክር ወረቀት የሚሰጠው የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ይሆናል፡፡

፬. በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ መሠረትሕንጻ የሚየስመዘግብ ሰው የሚከተሉትን አሟልቶ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) ሕንጻው ላረፈበት ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ፣

ለ) ለሕንጻ ው የተሰጠ የግንባታ ፍቃድ፣

ሐ) የጋራ ሕንጻ ኅብረት ሥራ ማኅበር ከኖነ ማኅበሩ ህጋዊ ሰውነት ያገኘበት ሠነድ፤

መ) የጋራ ህንጻው ያልተገነባ ከሆነ በአዋጁ መሠረት ሲመዘገብ ሥራ ላ የሚውሉና በቤት ባለቤቶች የጸደቀወይም በአስመዝጋቢው በጊዜያዊነት የተዘጋጁ የሕንጻማሳወቂያ እና መግለጫ፣የመተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ ሠነዶች፤

ሠ) አስመዝጋቢው በአዋጅ እና በዚህ ደንብ መሠረትሕንጻውን ለማስመዝገብ የሚያስችለውን መብት ወይ ሥልጣን ወይም ሕጋዊ ውክልና የሚያረጋግጥ ሠነድ፣እና

ረ) በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የቤት ባለቤቶሕንጻው እንዲመዘገብ ፍቃዳቸውን የሰጡበትን እደዚሁ ም የሕንጻ ማሳወቂያ መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ ያጸደቁበትትን ቃለ ጉባኤ፡፡

**፬. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ ይዘት**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚቀርብየሕንጻ ማሳወቂያ የሚከተሉት ዝርዝር መረጃ ዎች መግለጽ ወይም መያዝ አለበት፡

ሀ) ሕንጻው የተሰራበት ቦታና የአከባቢ መግለጫ፣

ለ) ቦታው የተያዘበት ሁኔታ /ሊዝ ወይም ምሪት/፣

ሐ) በሊዝ የተያዘ ከሆነ የሊዝ ውል ዘመኑ፣

መ)ባለፎቅ ሕንጻ ሲሆን የፎቁን የቤዝመንቶች ብዛት፣

ሠ) የሕንጻው ስም/ኮድ ወይም ቁጥር/፣ የሕንጻው ይዘት መጠን፣

ረ) የጋራ መጠቀሚያዎች ዝርዝር፣

ሰ) የመውጫ መግቢያ አከባቢዎች መግለጫ፣

ሸ) ለተወሰኑ ቤቶች መጠቀሚያዎች ብቻ የተመደቡ የጋራ መጠቀሚያዎች ዝርዝር፣

ቀ) የቤቶችን ዝርዝር፣ ደራጃቸውንና የወለል ስፋታቸውን፣ለእያንዳንዱ ቤት የተሰጠውን መለያ ቁጥርና የቤቱን ባለቤት ስም፣

በ) ሕንጻውና እያንዳንዱ ቤት ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ መግለጫ፣

ተ) በጋራ መጠቀሚያዎች አንጻር በሕንጻው መዋቅራዊፕላን የአንድ ቤተ አካላት ተብለው የሚወሰዱ የ ሕንጻውን አካላት ዝርዝር፣

ቸ) በጋራ መጠቀሚያዎች ላይ እያንዳንዱ ቤት የሚኖረው የማከፋፈል የመቶኛ ጥቅም መጠን፣

ኀ) በአዋጁ መሠረት የሚቋቋመው የቤት ባለቤቶች ማኅበር የሥራ አድራሻ፣

ነ) የጋራ ወጪዎች ዝርዝር

ኘ) ቤቶችንና የጋራ መጠቀሚያዎችን ስለመያዝና መጠቀም ያሉ ሁኔታዎችና ገደቦች

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሃላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ29/1999</u>

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማ አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሀላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/1993 የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 29/1999 ሲሆን ይህም አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 19/1993 አፈጻጸም ሂደት ላይ የታዩትን መልካም ልምዶች ባካተተ መልኩ ተሻሽሎ ወጥቷል::

1. አጭር ርዕስ

2. መሻሻያ

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ 2/መ/ ስለ ማሻሻል

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ ፫ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፬ እና ፫ ስለመጨመር ።

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ ፮ ንኡስ አንቀጽ ፫ - ፰ ተሰርዘው በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ ተተክቷል።

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 3 ውስጥ ንኡስ አንቀጽ 10 ውስጥ 1፫ የሚለው ቁጥር ተሰርዞ 1፮ የሚል ቁጥር ስለመተካት

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ ፫ ተከትሎ አዲስ ንኡስ አንቀጽ ፬ ስለመጨመር

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል 1 ሀ እና ለ ስለማሻሻል

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል ሐ ተሰርዟል።

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫ ስለመጨመር

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 1፬ንዑስ አንቀጽ 2 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫ ስለመጨመር

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ 1፮ ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል ረ ቀጥሎ ተራ ፊደል ሰ ስለመጨመር

## የከተማው አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ኃላፊነታቸውን አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ) ፷፱/፲፱፻፺፱

አጭር መግለጫ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚስተዋለውን ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጥረት መኖሪያ ቤቶችን ከመገንባትም ባለፈ ያሉት መኖሪያ ቤቶች በፍትሃዊነት እና በሃላፊነት ማስተዳደር እንደሚገባ ለዚህም የህግ ማዕቀፍ ሊኖረው እንደሚገባ እሙን ነው ። በዚህም የአዲስ አበባ አስተዳደር የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ በአፈጻጸሙ ሂደት የታዩትን መልካም ልምዶች ባካተተ መልኩ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፩(፩) (ረ) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ባለአደራ ጊዜያዊ አስተዳደር ይህን አዋጅ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የከተማው አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውን አፈጻፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፷፱/ ፲፱፻፺፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ማሻሻያ

የከተማው አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈጻፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

፩. የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

“መ. በከተማተማው ውስጥ በራሱ ስም ወይም በትዳር ጓደኛው ስም የግል መኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለው መሆኑን እና በራሱ ስም ወይም በትዳር ጓደኛው ስም በዚህ አዋጅ መሰረት በቤት ፈላጊነት ለሌላ ምዝገባ ያላከናወነ መሆኑን እንዲሁም የቤቱን ቀሪ እዳም ክፍያ ከሚከፍልለት ባንክ ጋር የብድር ውል የሚፈርም መሆኑን”

፪. በአዋጅ አንቀጽ ፬ ከንዑስ አንቀጽ ፫ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፬ እና ፭ ተጨምሯል።

“፬. የቤት ፈላጊዎች ማመልከቻ ቅጽን በውክልና መሙላት አይቻልም።”

“፭. የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ለላሻሻል ወይም ለላለወጥ ይችላል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

፫. የአዋጁ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ ፫-፰ ተሰርዘው በሚከተልት ንዑስ አንቀፆች ፫ እና ፬ ተተክተዋል።

“፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሽያጭ የቀረቡት መኖሪያ ቤቶች በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት ለተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች በሽያጭ የሚተላለፉት በዕጣ ብቻ ይሆናል”፡፡

“፬. የእንቅስቃሴ አካል ጉዳተኛ የሆነ ቤት ፈላጊ ቤት ለመግዛት ዕጣ እስከወጣለት ድረስ ምርጫው እንደተጠበቀ ሆኖ ተደራሽ በሆነው የሕንፃ ወለል ላይ የሚገኝ ቤት የመግዛት ቅድሚያ ያገኛል፡፡ ይህ መብት ለቤተሰብ አባላት አይተላለፍም፡፡ ማንኛውም ቤት ፈላጊ ይህንን የቅድሚያ መብት መቃወም አይችልም”፡፡ በአዋጅ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፲ ውስጥ “፲፰” የሚለው ቁጥር ተሰርዞ “፲፯” በሚል ቁጥር ተተክቷል፡፡

፰. ከአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ
አንቀጽ ፬ ተጨምሯል፡፡

“፬. የሚሸጡ ቤቶች ዋጋ ልክ በየዓመቱ በከተማው ካቢኔ በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት ይሆናል፡፡

፮. የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተራ ፊደል (ሀ)
እና (ለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

“ለ ከአንድ መኝታ ክፍል በላይ ያላቸው ቤቶች ገዢው ከባንክ ጋር በሚፈርመው የብድር ውል ውስጥ የሚጠቀስ የወለድ መጠን ይሆናል፡፡”

፯. የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ኸ ተሰርዟል፡፡

፰. ከአዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫ ተጨምሯል፡፡

“፫ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖር አስቀድሞ ስቱድዮ ቤት የገዙ ሰዎችን ሳይጨምር በረጅም ጊዜ ክፍያ ስቱድዮ ቤት የሚገዛ ሰው ወለድ እንዲከፍል እና የወለዱን መጠን የከተማው ካቢኔ ለላወስን ይችላል፡፡

፱. ከአዋጅ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ-አንቀፅ ፫ ተጨምሯል፡፡

“፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው የአምስት ዓመት ጊዜ ገደብ ቤቱን በዋስትና በመያዝ ለገዢው ብድር የሰጠውን አበዳሪ ተቋም እና ውል ክፍያ ከፍሎ የንግድ ቤት የገዛውን ሰው አይመለከትም፡፡”

፲. ከአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ ፩ ተራ ፊደል (ረ) ቀጥሎ የሚከተለው ተራ ፊደል “ሰ” ተጨምሯል፡፡ “

“ሰ በማመልከቻው ቅፅ ላይ የሞላቸው ማናቸውም ሌሎች ዝርዝሮች በማናቸውም ጊዜ ሐሰተኛ ሆነው ሲገኙ፣”

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዚያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ባለአደራ ጊዜያዊ አስተዳደር

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማውን አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሃላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ 5/2000</u>

አጭር ርዕስ

ማሻሻያ

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ ፯ ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀጽ ፯ ስለመተካት

የአዋጁ ቁጥር 19/1993 አንቀጽ ፱ ስር በአዋጅ ቁጥር 29/1999 ከተጨመረው ንኡስ አንቀጽ ፬ ቀጥሎ ንኡስ አንቀጽ ፭ ስለመጨመር፡፡

የአዋጁ ቁጥር19/1993 አንቀጽ 11 ተሰርዞ አዲስ አንቀጽ 11 ስለመተካት

አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካላት የከተማ አስተዳደር ቤቶች የማስተዳደር ሀላፊነታቸውንና አፈጻጸሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/1993 እንደተሻሻለ እንደገና የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 5/2000 ሲሆን ይህም አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 19/1993 አፈጻጸም ሂደት የጋራ ቤቶችን በማስተላፍ ሂደት ውስጥ የታዩትን ክፍተቶችን በማየት የተሻለ አሰራር እና አፈጻጸም እንዲኖር ለማድረግ እንዲቻል የተወሰኑ አንቀጾችን ተሻሽሏል፡፡

## የከተማው አስተዳዳር ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ለማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፰/፪ ሺ ዓ.ም.

የአስተዳደሩን የጋራ የሕንፃ ቤቶች በማስተላለፍ ሂደት የተገኙ ጠቃሚ ተሞክሮዎችንና ያጋጠሙ ችግሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለ የቤት ማስተላለፍ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣

ይህንኑ ለመፈፀም የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ /እንደተሻሻለ/ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ/ በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል ፡፡

፩. አጭር ርዕስ

‹‹ይህ አዋጅ የከተማው አስተዳዳር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፰/፪ ሺ ዓ.ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

የከተማው አሰተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡፡

፩. የአዋጅ አንቀጽ ፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል፡-

፯ የቅድሚያ አወሳሰን

፩. ከክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት በሚገኘው መረጃ መነሻ በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው መሠረት እስካሁን በቤት ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም ተነስተው በመጠለያ ውስጥ ላልና በቀጣይ በቤት ልማት ምክንያት ሆነ በከተማው የመሃል አካባቢ በሚከናወኑ የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች ምክንያት በፈቃዳቸው ለሚነሱ የከተማው ነዋሪዎች የተወሰነ የቤት ድርሻ በልዩ ሁኔታ ተይዞላቸው ቤቶችን የመግዛት የቅድሚያ መብት ላያገኙ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ የቅድሚያ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት የመጠለያ ነዋሪዎችና ሌሎች ተነሺዎች በተነሱበት ቀበሌ የግል ቤት ባለቤቶች፣ የግል ቦታ ባለይዞታዎች ወይም የመንግሥት ቤት ከአከራዩ መስሪያ ቤት የተከራዩ የከተማው ነዎሪዎች ወይም አብረዋቸው የሚኖሩ ሕጋዊ ወራሾቻቸው ብቻ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሽያጭ የቀረቡት መኖሪያ ቤቶች በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ለተመዘገቡት ቤት ፈላጊዎች በሽያጭ የሚተላለፉት በዕጣ ብቻ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት በቤት ፈላጊነት የተመዘገቡ አስከሆኑ ድረስ ቢያንስ ፴ ፐርሰንት ሴቶች በእያንዳንዱ የዕጣ ማውጣት ሥርዓት ተካትተው ቤት የመግዛት የቅድሚያ መብት ተጠቃሚዎች ይሆናል፡፡

፬. የእንቅስቃሴ አካል ጉዳተኛ የሆነ ቤት ፈላጊ ቤት ለመግዛት ዕጣ እስከወጣለት ድረስ ምርጫው እንደተጠበቀ ሆኖ ተደራሽ በሆነው የሕንፃው ወለል ላይ የሚገኝ ቤት የመግዛት ቅድሚያ ያገኛል፡፡ ይህ መብት ለቤተሰብ አባላት አይተላለፍም፡፡ ማንኛውም ቤት ፈላጊ ይህንን የቅድሚያ መብት መቃወም አይችልም፡፡

፪. በአዋጅ አንቀጽ ፱ ሥር በአዋጅ ቁጥር ፳፱/፲፱፻፺ ከተጨመረው ንዑስ አንቀጽ ፬ ቀጥሎ አንቀጽ ፭ ተጨምሯል፡-

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እስከ /፫/ የተደነገገው ቢኖርም የከተማው ካቢኔ ከባንክ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በሌላ መልክ እንዲፈጸም ሊወስን ይችላል፡፡

፫. የአዋጅ አንቀጽ ፲፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፩ ተተክቷል፡-

<u>፲፩ የወለድ መጠንና አከፋፈል</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት በተከፋፈለ ተከታታይ የረጅም ጊዜ ክፍያ ቤት የገዛ ሰው በሁልም የቤት አይነቶች በባንክ ወለድ መጣኔ መሠረት ወለድ ይከፍላል፣

፬. <u>አዋጁ የሚፀናውበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፺ ቀን ፪ ሺህ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፺ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

ኩማ ደመቅሳ

# <u>የአዲስ አበባ መዋቅራዊ ፕላን አዋጅ ቁጥር ፺፪/፪ሺ፱</u>

የአዲስ አበባ ዕድገትና ልማት ወቅታዊና ቀጣይ የሀገሪቱን የልማት ዕቅድ አቅጣጫዎችን በመከተል የሚገለጽበትና የሚመራበት እንዲሁም የተፈፃሚነት ዘመኑ ያበቃው የአዲስ አበባ ከተማ መዋቅራዊ ፕላን በፌደራል መንግስት በወጣው የከተማ ፕላን አዋጅ ስለፕላን ዝግጅት ከተደነገጉት መርሆች ጋር በተጣጣመ መልኩ የሚተካበት ሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የልማት ኃይልች በአዲስ አበባ ቀጣይ እድገትና  የለውጥ እንቅስቃሴዎች በተሟላና ውጤታማ በሆነ መልኩ መሳተፍና በጎ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችለበት ሁኔታ ማመቻቸትና ፕላን የሚፈጸምበት አደረጃጀት የሚሟላበት ሁኔታም ሆነ በቀጣይ የሚሻሻልበትና የሚተካበት ስነስርዓት መደንገግ በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፻፺፭ አንቀጽ (፩)(ሐ)እና በፌዳራል የከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፬ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

<u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “የአዲስ አበባ መዋቅራዊ ፕላን አዋጅ  ተበሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

<u>፪. ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣የቃለ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

<u>፩</u>) “ከተማ ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪) “የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ  አስተዳደር ነው፤

፫) “ከተማ ምክር ቤት” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው፤

፬) “ከተማ ካቢኔ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ  ነው፤

፭) “ክንቲባ” ማለት የአዲስ አበበ ከተማ ክንቲባ ነው፤

፮) “ኮሚሽን” ማለት የከተማው አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ነው፤

“ፕላን” ማለት መዋቅራዊ ፕላንና የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲሁም በሕግ የተደነገጉ ሌሎች ፕላኖችን ያጠቃልላል፤

፰) “መዋቅራዊ ፕላን” ማለት በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊ እና በአካባቢያዊ ዘርፎች የተመጣጠነ የከተማ ልማት ለማስገኘት በሚያስችል መልኩ የከተማውን ፊዚካሊዊ እድገትና ልማት በተመለከተ መሟሊት የሚገባቸው ጉዳዮችን የሚዘረዝርና ሕጋዊ ተፈፃሚነት ያለው አብይ የከተማ ፕላን ነው፤

“የአካባቢ ልማት ፕላን” ማለት በስልታዊ ባህሪያቸው ምክንያት በተመረጡ አካባቢዎች ላይ በማተኮር የከተማውን አንድ አካባቢ ለማሻሻል፣ለማደስና ለማስፋፋት በመካከለኛ የዕቅድ ዘመን በጊዜ እየተከፋፈለና እየተቀናጁ የሚከናወኑ የልማት ስራዎችን የሚያሳይና መዋቅራዊ ፕላኑን በተመረጡ አካባቢዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለ የልማት ግቦችን፣ አበይት ተግባራትን፣ የአፈጻጸም ስልቶችን፣ የፈጻሚ አካላትን ሚና እና ተፈሊጊ ተቋሞችን፣ የአካባቢ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴን፣ የከተማ ዲዛይን መርሆዎችን፣ ተጨባጭ መስፈርቶችን፣ የአካባቢ ማዕቀፉን፣ በጀትንና ጊዜን በዝርዝር የሚያሳይ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለውና መዋቅራዊ ፕላኑ ተግባራዊ የሚደረግበት ፕላን ነው፤

“ማጠቃለያ ሰነድ” ማለት የመዋቅራዊ ፕላኑን የጥናት ውጤቶችና ልዩ ልዩ ክፍልች እንዲሁም የፕላኑን የመሬት አጠቃቀም አመዳደብ መፍቻ የያዘ የፕላን ማጠቃለያ ይወክላል ነው፤

፩) “ልማት” ማለት በፕላን በመመራት በከተማው መሬት ውስጥ፣ ላይ እና/ወይም በላይ የሆነ የግንባታና የሰውን ልጅ የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ የሚካሄድ ማናቸውም ማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ ተግባር ነው፤

“መልሶ ማልማት” ማለት አስቀድሞ የግንባታ ልማት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ከተማ ነክ ችግሮችን ለማቃለል፣ የኑሮ ደረጃን ለማሻሻልና የተፋጠነ የከተማ ለውጥና የተሳለጠ የመሬት አጠቃቀም ለማስገኘት ታቅዶ የሚፈጸም የልማት ተግባር ነው፤

“ግንባታ” ማለት የመሬትን ገፅታ በመለወጥ ወይም በማሻሻል በመሬት ላይም ሆነ ከመሬት በላይ እንዲሁም በመሬት ውስጥ የተካሄደ ወይም የሚካሄድ የግንባታ ተግባር ነው፤

“ቅይጥ መኖሪያ” ማለት በአንድ ቦታ ላይ መኖሪያ ቤትን የቀላቀለ ወይም የሚቀላቅለ ግንባታዎች ማለት ሲሆን፣ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ለመኖሪያ ግንባታ ይወክላል በተመደቡት ቦታዎች ላይ መኖሪያ ቤትንና ከመኖሪያ ጋር የሚጣጣሙ እና የሚቀናጁ ሌሎች አገልግልቶችን ያካትታል፤

፲፰) “ፕላን ማሻሻል ወይም ማሻሻያ” ማለት መዋቅራዊ ፕላኑ ጸንቶ በሚቆይበት ዘመን በመዋቅራዊ ፕላኑ አንድ ክፍል ወይም ክፍልች ላይ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሚከናወን ፕላን የማስተካከያ ወይም የማጣጣም ሥራ ነው፤

"የፌዳራል አዋጅ" ማለት ስለ ከተሞች ፕላን ዝግጅት በፌደራል መንግስት የወጣው የከተማ ፕላን አዋጅ ወይም እሱን የሚተካ አዋጅ ነው፤

፲፯) "የወንጀል ሕግ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዳራሊዊ ዱሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ የወንጀል ሕግ ነው፤ አመዳደብ

፳) "የሕንፃ አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩ ነው፤

፲፱ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት የመዋቅራዊ ፕላን መጽደቅ፣ ክፍሎችና መሠረታዊ ድንጋጌዎች</u>

## ምዕራፍ አንድ የመዋቅራዊ ፕላን መጽደቅ፣ ማስተዋወቅና የተፈጻሚነት ወሰን

### <u>፫. የመዋቅራዊ ፕላን መጽደቅና ማስተዋወቅ</u>

፩) መዋቅራዊ ፕላኑ በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

፪) በዚህ አዋጅ በኮሚሽኑ እንደሚታተሙ ተለይተው ከተመለከቱት ክፍሎች በስተቀር የጸደቀው መዋቅራዊ ፕላንና ክፍሎቹ ከዚህ አዋጅ ጋር በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትመው ይወጣሉ፤ እንዲሁም በኤላክትሮኒክ ዘዴ ታትመው እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

፫) መዋቅራዊ ፕላኑና ክፍሎቹ፡-

ሀ) ልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለከተማው ነዋሪዎችና ለተጠቃሚዎች በስፋት እንዲታወቁ ይደረጋል፤

ለ) ፕላን የመፈጸምና የማስፈጸም ሓላፊነት ላለባቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለሚመለከታቸው ሌሎች ሰዎች በሙሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### <u>፬. መዋቅራዊ ፕላኑ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

መዋቅራዊ ፕላኑ በዚህ አዋጅ ከተወሰነው ቀን ጀምሮ ለ10 ዓመት የጸና ይሆናል፡፡

### <u>፭. የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅም ሆነ በዚህ አዋጅ የጸደቀው መዋቅራዊ ፕላን በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፻፺፭ በተደነገገው መሰረት እውቅና በተሰጠው የከተማው ሕጋዊ የአስተዳደር ወሰንና በውስጡ በሚገኝ በማናቸውም ስፍራ ወይም በማናቸውም ሰው በሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ነክ ተግባርና ልማት እንቅስቃሴ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የአዋጁ ዓላማዎች እና የመዋቅራዊ ፕላን ክፍሎች</u>

### <u>፮. የአዋጁ ዓላማዎች</u>

አዋጁ የሚከተለት አላማዎች ይኖሩታል፡-

፩) ከተማው በፕላን ሕግ እንዲመራ የማስቻል፤

፪) በከተማው ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎችን በፕላን በመምራትና በመቆጣጠር የከተማውን እድገት እና ልማት የማሻሻል፤ እና

፫) በከተማው ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመዘገበ ያለውን እድገት እና ልማት በፕላን በመደገፍ ቀጣይነቱን የበለጠ የማረጋገጥ፡፡

<u>፯. የመዋቅራዊ ፕላን ክፍሎች</u>

፩) መዋቅራዊ ፕላኑ የሚከተሉት ክፍልች ይኖሩታል፡-

ሀ) የመሬት አጠቃቀም ፕላን፤

ለ) የመንገድና መጓጓዣ መረብ ፕላን፤

ሐ) የሕንፃ ከፍታ ፕላን፤

መ) በኮሚሽኑ ታትሞ የሚሰራጭ የፕላን ማጠቃለያ ሰነድ፤ እና

ሠ) በኮሚሽኑ ታትሞ የሚሰራጭ የከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምድች እና ደረጃዎች መመሪያ፡፡

የመዋቅራዊ ፕላኑ ክፍሎች አበይት እና ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ምድቦችና መሠረታዊ የፕላን አተገባበር ድንጋጌዎችን በካርታ ንድፍና በመሬት አጠቃቀም እንዲሁም በግንባታ ከፍታ ደንብ አገላለጾች በአመዛኙ በተደነገገው መሠረት ያመላክታል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የመሬት አጠቃቀም ፕላን አበይትና ዝርዝር ምድቦች</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ የመሬት አጠቃቀም አበይት ምድቦችና ፈቃጅ ድንጋጌዎች</u>

### <u>፩. የመሬት አጠቃቀም ፕላን አበይት ምድቦች</u>

የመሬት አጠቃቀም የሚከተለትን አስራ አራት አበይት የመሬት አጠቃቀም ምድቦችን ያመለክታል፡-

፩) ቅይጥ መኖሪያ፤

፪) ንግድ ሥራ፤

፫) አስተዳደራዊ አገልግሎት፤

፬) ማህበራዊ አገልግሎት፤

፭) ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት፤

፮) የመጓጓዣ አገልግሎት፤

፯) የመሠረተ ልማት አገልግሎት፤

፰) የመንገድ መረብ፤

፱) የአካባቢ ጥበቃ፤

) የከተማ ግብርና፤

፲፩) ማምረቻና ማከማቻ፤

፲፪) ልዩ ፕሮጀክቶች፤

፲፫) ታሪካዊ ግንባታዎችና ስፍራዎች፤ እና

፲፬) ጥብቅ አካባቢዎች፡፡

## የመሬት አጠቃቀም ፈቃጅ ድንጋጌዎች

፩) በተከታዮቹ አንቀጾች ከተመለከቱት አበይትና ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ምድቦች አኳያ ከተከለከለ አገልግሎቶች ወይም ተግባራት ውጪ የሆነ ማናቸውም አገልግሎት ወይም ተግባር በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተፈቅዶል፡፡

፪) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የፕላን ማሻሻያ ተደርጎ ካልጸደቀ እና በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ፈቃጅ ድንጋጌ ከአንድ የመሬት አጠቃቀም ምድብ ወደ ሌላ ምድብ ወይም አገልግሎት መለወጥን አያካትትም፡፡

፫) በእያንዳንዱ የመሬት አጠቃቀም ምድብ የሚፈቀድ ግንባታዎች ከዚህ አዋጅ ጋር አባሪ በተደረገው የሕንፃ ከፍታ ፕላን ድንጋጌ እና እንደየአግባቡ መዋቅራዊ ፕላኑን ለማስፈጸም በሚወጣ ሕግ መሰረት ይፈጸማሉ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የቅይጥ መኖሪያና የንግድ ሥራ መሬት አጠቃቀም ምድቦች እና መሰረታዊ ድንጋጌዎች

፩. የቅይጥ መኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) ቅይጥ የመኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት አራት ንዑስ ምድቦች ተከፋፍልና በመለያ ኮድ R ተለያይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) አነስተኛ ጥግግት ያለው ቅይጥ የመኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ፡- R-፩፤

ለ) መካከለኛ ጥግግት ያለው ቅይጥ የመኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ፡- R-፪፤

ሐ) ከፍተኛ ጥግግት ያለው ቅይጥ የመኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ፡- R-፫፤

መ) ከአካባቢ ጥበቃና ከአረንጓዳ የደን ክልል ቦታ ተነስተው ለሚሰፍሩ ነዋሪዎች የተከለለ መሬት አጠቃቀም ምድብ R- ፬፡፡

፪) ከወንዝ ዳርቻ ክልልና ከተለያዩ አነስተኛ የአረንጓዴ መናፈሻ ቦታዎች የሚነሱ ነዋሪዎች በወንዝ ዳርቻና መናፈሻ ፕሮጀክቶች መሰረት በልማቱ ይታቀፋሉ፡፡

፩. የንግድ ሥራ መሬት አጠቃቀም ምድብ

የንግድ ሥራ መሬት አጠቃቀም ምድብ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ በተመለከተው መሠረት CB በሚለው ኮድ ተለይቶ በንግድ ሥራ ቦታ ምድብ እና በገበያ ቦታ ምድብ ተከፋፍሎ እንደሚከተለው በአንቀጽ ፲፪ እና ፲፫ ተወስኗል፡፡

ቅይጥ የንግድ ሥራ የመሬት አጠቃቀም ምድብ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ከተወሰነው የንግድ ሥራ ቦታ ምድብ CB-፩ ከሚፈቀደው ግንባታ የመሬት አጠቃቀም ፕላኑና የሕንጻ ከፍታ ፕላኑ በሚያመለክቱት መጠን ለመኖሪያ አገልግሎት መዋል አለበት፡፡

የገበያ መሬት አጠቃቀም ምድብ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሰረት የገበያ ቦታ CB-፪ በሚከተለት ሦስት ንዑስ ምድቦች ተከፋፍሎ ተወስኗል፡-

፩) አነስተኛ ገበያ CB- ፪፩፣

፪መካከለኛ ገበያ CB-፪፪፣ እና

፫) ከፍተኛ ገበያ CB-፪፫፡፡

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

<u>አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ እና ማዘጋጃ ቤታዊ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች እና መሰረታዊ ድንጋጌዎች</u>

. የአስተዳደራዊ ተቋማት የመሬት አጠቃቀም
ምድብ

፩) የአስተዳደራዊ ተቋማት መሬት አጠቃቀም በሚከተለት ሁለት ንዑስ ምድቦች ተከፋፍሎና በመለያ ኮድ AD ተለያይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) የመንግስታዊ ተቋማት ቦታ AD-፩፣

ለ) የበይነ መንግስታዊ ተቋማት ቦታ AD-፪፡፡

፪) የመንግስታዊ ተቋማት ቦታ በሚከተለት ፬ ዝርዝር አገልግልቶችና መለያ ኮዶች ተከፋፍል በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኖል፡-

ሀ) የከተማ አስተዳደር AD-፩፩፣

ለ) የክፍለ ከተማ አስተዳደር AD-፩፪፣

ሐ) የወረዳ አስተዳደር AD-፩፫፣እና

መ) ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት AD-፩፬፡፡

፫) ለአስተዳደራዊ ተቋማት አገልግሎት የሚሰራ ግንባታ፣ አጥርና አረንጓዳ ስፍራዎች በግንባታ ፈቃድ ደረጃዎች መሰረት መገንባት አለባቸው፡፡

፬) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ

፪(ሐ) የተመለከተው የወረዳ ማዕከል የወረዳውን አስተዳደር ተቋማት እንዲያካትት ተደርጎ መልማት አለበት፡፡

፫) በማናቸውም የአስተዳደራዊ ተቋም ቦታ ምድብ የማምረቻና ማከማቻ መጋዘን፣ የቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ እና ቆሻሻ ማጎሪያ ቦታ፣ መካነ-መቃብር፣ የሃይማኖት ድርጅት የአምልኮ ተቋም፣ ካባና ማዕድን ማውጫ ፣ ስታድየም፣ ማረሚያ ቤት እና ወታደራዊ ተቋም መገንባት ክልክል ነው፡፡

፲. የማህበራዊ አገልግሎት መሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የማህበራዊ አገልግሎት መሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት አራት ንዑስ ምድቦች ተከፋፍሎና በመለያ ኮድ S ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል:-

የማህበራዊ አገልግሎት የመሬት አጠቃቀም ዝርዝር ምድቦች

የትምህርት፣ የጤናና የስፖርት የሚውለ የመሬት አጠቃቀም ዝርዝር ምድቦች በሚከተለው መልኩ ተለያይተው በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስነዋል፡-

፩) የትምህርት አገልግሎት S-፩ የመሬት አጠቃቀም ምድብ የሚከተለት አምስት ንዑስ ምድቦች በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስነውለታል፡-

ሀ) ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት S-፩፩፤

ለ) የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤት S-፩፪፤

ሐ) ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ተቋማት S-፩፫፤

መ) ዩኒቨርስቲ/ ኮላጅ S-፩፬፤እና ሠ) የምርምር ማዕከላት S-፩፭፡፡

የጤና አገልግሎት መሬት አጠቃቀም S-፪ የሚከተለት ሶስት ንዑስ ምድቦች በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስነውለታል፡-

ሀ) ጤና ጣቢያ S-፪፩፤

ለ) ሆስፒታል S-፪፪፤ እና

ሐ) ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል S-፪፫፡፡

መ) የስፖርት ማዘውተሪያ መሬት አጠቃቀም S-፫ የሚከተለት አምስት ንዑስ ምድቦች በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስነውለታል፡-

ሀ) ብሔራዊ ስታድየም S-፫፩፤

ለ) ከተማ ደረጃ ስታድየም S-፫፪፤

ሐ) ክፍለ ከተማ ስታድየም S-፫፫፤

መ) የወረዳ ስፖርት ሜዳ S-፫፬፤ እና

ሠ) ስፖርት ማዕከል S-፫፭፡፡

የአምልኮ ቦታዎች በሚወጣ የሀይማኖት ድርጅቶች ቦታ አመዳደብ ደንብ መሰረት በቅይጥ መኖሪያ የመሬት አጠቃቀም ውስጥ ይስተናገዳሉ፡፡

፭) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ በተመለከተው መሠረት የቦታ ምድባቸው ተለይቶ ከተመላከቱት ውጪ የሆኑ አግባብነት ያላቸው ማህበራዊ አገልግልቶች በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምድችና ደረጃዎች መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በቅይጥ መኖሪያ የመሬት አጠቃቀም ተካትተው ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት የመሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት መሬት አጠቃቀም ምድብ S-፭ በሚከተለት አምስት ንዑስ ምድቦች ተከፋፍልና በመለያ ኮድ ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት S-፭፩፤

ለ) የቄራ አገልግሎት S-፭፪፤

ሐ) አረንጓዴ መካነ መቃብር S-፭፫፤

መ) የክብረ በዓል እና ክፍት የሕዝብ መናኸሪያ ቦታዎች S-፭፬፤እና

ሠ) ባህላዊና ማህበረሰብ አቀፍ ማዕከል S-፭፭፡፡

ሌሎች ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በቅይጥ መኖሪያ የመሬት አጠቃቀም ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ በእያንዳንዱ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቦታ ንዑስ ምድብ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ከተመደበለት አገልግሎት የተለየ አላማ ያለው ግንባታ ማካሄድ ክልክል ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በህዝብ መናኸሪያ ቦታ የመሬት አጠቃቀም ምድብ ውስጥ አረንጓዴ ስፍራ፣ ፏፏቴ እንዲሁም የሚለሰልስም ሆነ የሚሻከር መተሊለፊያ መንገድ መገንባት ተፈቅዶል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የመሰረተ ልማት አገልግሎት፣ የመጓጓዣ አገልግሎት እና የመንገድ መረብ መሬት አጠቃቀም ምድቦች እና መሰረታዊ ድንጋጌዎች

### ፰. የመሰረተ ልማት አገልግሎት የመሬት አጠቃቀም ምድብ

የመሰረተ ልማት አገልግሎት የመሬት አጠቃቀም ምድብ IS ፩ በሚከተለት አምስት ንዑስ ምድቦች እና በመለያ ኮድች ተለያይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

፩) ውሃ ማከማቻ IS-0፩፤

፪) ኤሌክትሪክ ኃይል ጣቢያ IS-0፪፤

፫) ከፍተኛ የኤሌክትሪክ መስመር ክልል IS-0፫፤

፬) ቀላል ባቡር ኃይል ጣቢያ IS-0፬፤እና ፭) ቴሌኮሙኒኬሽን ጣቢያ IS-0፭፡፡

ሀ) የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት S-፳፩፤

ለ) የቄራ አገልግሎት S-፳፪፤

ሐ) አረንጓዴ መካነ መቃብር S-፳፫፤

መ) የክብረ በዓል እና ክፍት የሕዝብ መናኸሪያ ቦታዎች S-፳፬፤እና

ሠ) ባህላዊና ማህበረሰብ አቀፍ ማዕከል S-፳፭፡፡

ሌሎች ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በቅይጥ መኖሪያ የመሬት አጠቃቀም ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ በእያንዳንዱ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቦታ ንዑስ ምድብ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ከተመደበለት አገልግሎት የተለየ አላማ ያለው ግንባታ ማካሄድ ክልክል ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በህዝብ መናኸሪያ ቦታ የመሬት አጠቃቀም ምድብ ውስጥ አረንጓዴ ስፍራ፣ ፏፏቴ እንዲሁም የሚለሰልስም ሆነ የሚሻክር መተላለፊያ መንገድ መገንባት ተፈቅዷል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የአካባቢ ጥበቃ እና የከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም ምድቦች እና መሠረታዊ ድንጋጌዎች

### ፭፫. የአካባቢ ጥበቃ የመሬት አጠቃቀም ምድብ

የአካባቢ ጥበቃ የመሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት ሦስት ንዑስ ምድቦችና በመለያ ኮድ EA ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

፩) አረንጓዴ መሰረተ ልማት EA-፩፤

፪) የቆሻሻ ማጎሪያ ቦታና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ EA-፪፤ እና

፫) ካባ እና የውሃ አካላት EA-፫፡፡

፭. የአረንጓድ መሠረተ ልማት የመሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የአረንጓዳ መሰረተ ልማት መሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት አምስት ንዑስ ምድቦች እና በመለያ ኮድ EA-፩ ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) ተግባረ ብዙ የደን ክልል EA-፩፩፤

ለ) የወንዝ ዳርቻ ክልል EA-፩፪፤

ሐ) ክልላዊ መናፈሻ EA-፩፫፤

መ) የከተማ መናፈሻ EA-፩፬፤እና

ሠ) ልዩ መናፈሻዎች EA-፩፭፡፡

፪) የከተማ መናፈሻ በከተማ አቀፍ፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳ እና በሰፈር መናፈሻዎች ተዋረድ በአካባቢ ጥበቃ የመሬት አጠቃቀም ምድብ በተመለከተው እና ኮሚሽኑ በቀጣይ በሚያዘጋጀው ዝርዝር ፕላን መሰረት ይወሰናል፡፡

፫) በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፩)(ሐ) እንደተመለከተው መካነ መቃብሮች በከተማ የህዝብ መናፈሻነት ይለማል፤ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

<u>፲፰. የቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ መሬት አጠቃቀም ምድብ</u>

የቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ መሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት ሁለት ንዑስ ምድቦች  እና በመለያ ኮድች ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

፩) የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ EA- ፪፩፤እና

፪) የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ EA- ፪፪፡፡

፳. የካባና የውሀ አካላት የመሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የካባ እና የውሃ አካላት የመሬት አጠቃቀም  በሚከተለት ሶስት ዝርዝር ንዑስ ምድቦች እና በመለያ ኮድ EA-፫ ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡፡

ሀ) ካባ EA-፫፩፤

ለ) የከርሰ ምድር ውሃ መከላከያ ቀጠና EA-፫፪፤ እና

ሐ) የገጸ ምድር ውሃ አካላት EA-፫፫፡፡

፩) ለካባ አገልግሎት የዋለ ቦታ አገልግልቱ ሲያበቃ፣ ለሕዝብ ተደራሽ ለሆነ አረንጓዴ ልማት እንዲውል ተደርጎ መደልደል፣ መስተካከል እና መልማት አለበት፡፡

፪) በከርሰ ምድር እና በገጸ ምድራዊ ውሃ አካላት መከሊከያ ቀጠና ቦታ ምድብ ግንባታ ለማካሄድ አግባብ ባለው የአካባቢ ጥበቃ ሕግ መሰረት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ በቅድሚያ በማካሄድ ችግር የማያስከትል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ መከላከያ

<u>፳፩. የከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም ምድብ</u>

፩) የከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም በመለያ ኮድ UA ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተመላክቷል፡፡

፩) በከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም ምድብ ውስጥ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዛፎች ማልማት እንዲሁም የእንሰሳት እርባታና ተዋጽኦ ልማት ለንግድ አላማ ማካሄድ ይቻላል፡፡

፪) በከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም ውስጥ ፀረተባይና ኬሚካላዊ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ መጠቀም እና ከከተማ ግብርና ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ካላቸው ተግባራት ውጭ የሆነ ሥራ ማካሄድ ክልክል ነው፡፡

<u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## የማምረቻና የማከማቻ እንዲሁም የልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች የመሬት አጠቃቀም ምድቦች እና መሰረታዊ ድንጋጌዎች

### ፳፱. የማምረቻና ማከማቻ የመሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የማምረቻና ማከማቻ የመሬት አጠቃቀም በሚከተለት አራት ንዑስ ምድቦች እና በመለያ ኮድ MS ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) ማምረቻና ማከማቻ MS-፩፤

ለ) ነዳጅ ዴፖ MS-፪፤

ሐ) እህል ጎተራ MS-፫፤እና

መ)ከግብርና ቦታዎች ለሚነሱ ለመኖሪያና ለአነስተኛና ጥቃቅን ሥራዎች የሚውሉ ቦታዎች MS-፬፡፡

፪) በእነዚህ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ውስጥ ከማምረቻና ከማከማቻ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ካላቸው ተግባራት ውጪ የሆነ መሬት አጠቃቀም ክልክል ነው፡፡

### ፴. የልዩ ፕሮጀክት የመሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የልዩ ፕሮጀክት የመሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት ስድስት ንዑስ ምድቦች እና በመለያ ኮድ SP ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) ባለ፫ እና ከ፫ በላይ ኮከብ ሆቴል SP-፩፤

ለ) አለማቀፍ ደረጃ ያላቸው ልዩ ሆስፒታልች SP-፪፤

ሐ) ልዩ የመዝናኛ አገልግሎቶች (የጎልፍ ሜዳዎች፣የፈረስ መጋለቢያ ሜዳዎች፣ ወዘተ) SP-፫፤

መ) መጠነ ሰፊ ቤተ ገበያዎች SP-፬፤

ሠ) መዝናኛ ማማ SP-፭፤እና

ረ) ልዩ ልማቶች SP-፮፡፡

፭) በእነዚህ የመሬት አጠቃቀሞች ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ከልዩ ፕሮጀክቶች ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ካሊቸው ተግባራት ውጪ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ክልክል ነው፡፡

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>ታሪካዊ ግንባታዎችና ሥፍራዎች እንዲሁም የጥብቅ መሬት አጠቃቀም ምድቦች እና መሰረታዊ ድንጋጌዎች</u>

፴. የታሪካዊ ግንባታዎችና ሥፍራዎች መሬት አጠቃቀም ምድብ

፩) የታሪካዊ ግንባታዎችና ሥፍራዎች የመሬት አጠቃቀም ምድብ በሚከተለት ሁለት ንዑስ ምድቦች እና በመለያ ኮድ HB ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡-

ሀ) ታሪካዊ ሕንፃዎችና መዋቅሮች HB-፩፤ እና

ለ) ታሪካዊ ስፍራዎች HB-፪፡፡

፩) በታሪካዊ ግንባታዎችና ስፍራዎች የመሬት አጠቃቀም ውስጥ ያለትን ከማደስና ከመንከባከብ ውጪ ግንባታውን የሚመለከት ሌላ ተግባር መፈፀም ክልክል ነው፡፡

፪) በታሪካዊ ግንባታዎች እና ሥፍራዎች የሚከናወን የእድሳት ወይም የጥገና ሥራ በሕግ ግልጽ ስልጣን በተሰጠው የፌዳራል ወይም የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤት ፈቃድ መሰረት መፈጸም አለበት፡፡

<u>፴፩. የጥብቅ አካባቢ መሬት አጠቃቀም ምድብ</u>

፩) የጥብቅ አካባቢ የመሬት አጠቃቀም ምድብ የበረራ ክልል ሲሆን፣ PA በሚል መለያ ኮድ ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ተወስኗል፡፡

፪) በጥብቅ አካባቢ ወይም በበረራ ክልል ውስጥ ጪስ የሚያመነጭና አእዋፍን የሚስብ ሥራ እንዲሁም በሕንፃ ከፍታ ፕላን ድንጋጌዎች ከሚፈቀደው በላይ ከፍታ ያለው የማናቸውም ሕንፃ ወይም መዋቅር ግንባታ ክልክል ነው፡፡

<u>**ክፍል አራት**</u>

<u>**መዋቅራዊ ፕላን ማስፈጸምና ማሻሻል**</u>

<u>**ምዕራፍ አንድ**</u>

<u>**የፕላን አፈፃፀም መርሆዎችና ስልቶች**</u>

**፴፪. የፕላን አፈጻጸም መርሆዎች**

፩) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የመዋቅራዊ ፕላን ክፍሎች የሆኑትን ፖሊሲዎች ለማስፈጸም በአንድነትና በተደጋጋፊነት በሥራ ላይ ይውሊለ፡፡

፪) ፕላን የሚያስፈጽም ማናቸውም የከተማው አስተዳደር ተቋም ፕላኑን ሲያስፈጽም፣ የመዋቅራዊ ኘሊኑን ማጠቃለያ ሰነድ ማገናዘብ አለበት፡፡

፫) በመዋቅራዊ ፕላን እና በአካባቢ ልማት ፕላን መካከል ልዩነት ሲያጋጥም፣መዋቅራዊ ፕላኑ የበላይነት ይኖረዋል፡፡

**፴፫ . የመዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም ስልቶች**

መዋቅራዊ ፕላኑ በሚከተለት የአፈጻጸም ስልቶች መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡-

፩) የከተማ አስተዳደሩን የአስር ዓመት የዕቅድ ማእቀፍና የአምስት ዓመት ስልታዊ ዕቅድ በማዘጋጀትና በማጽደቅ፣

፪) ማናቸውም የከተማው አስተዳደር ተቋም በጸደቀ የከተማው አስተዳደር የአስር ዓመት የዕቅድ ማእቀፍና የአምስት ዓመት ስልታዊ ዕቅድ በተመለከተው መሰረት የየበኩለን ዕቅድ እንዱያወጣና እንዱተገብር በማድረግ፣

፫) በተመረጡ አካባቢዎች የአካባቢ ልማት ፕላን አዘጋጅቶና አጽድቆ ተፈጻሚ በማድረግ፣

፬) የአካባቢ ልማት ፕላን ባልተዘጋጀሊቸው ወይም ማዘጋጀት በማያስፈልጋቸው አካባቢዎች መዋቅራዊ ፕላኑን በቀጥታ በመጠቀም፣

፭) በመዋቅራዊ ፕላኑ የመሬት አጠቃቀም ምድቦች ያልተመሊከቱ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀሞች በአካባቢ ልማት ፕላንና በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ሙያዊ ልምድችና ደረጃዎች መመሪያ መሰረት እንዱወሰኑ በማድረግ፣

፮) ፕላን ለመፈጸም እና ለማስፈጸም የሚያስፈልጉና አግባብነት ያላቸው የከተማውን አስተዳደር ተቋማት አጥንቶና ስልጣንና ተግባራቸውን ወስኖ በሕግ በማቋቋም እንዲሁም አደራጅቶ ወደ ሥራ እንዱገቡ በማድረግ፣

፯) ፕላኑን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዲሁም ሥልቶች በማዘጋጀትና አጽድቆ በመተግበር፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**መዋቅራዊ ፕላን ማሻሻልና ማጽደቅ**

**፴፬. መዋቅራዊ ፕላን ማሻሻል**

፩) የመዋቅራዊ ፕላን ማሻሻያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት መዋቅራዊ ፕላኑን በሚከተለው መነሻ ማሻሻል ይቻላል፡-

ሀ) በመንገድ ወይም በሌላ የመሰረተ ልማት አገልግሎት መስመር ግንባታ ዲዛይን ወይም ሀገራዊ ወይም ከተማ አቀፍ ፋይዳ ባለው ፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ሲቀርብ፤ ወይም

ለ) ኮሚሽኑ በሚያካሂደው ጥናትና ምርምር ፕላኑ መስተካከል እንዳለበት ሲያምን፡፡

ሐ) ፕላን ማሻሻል ጥያቄው መንገድን ወይም ሌላ የመሰረተ ልማት አገልግሎት መስመርን የሚመለከት ከሆነ፣የፕላን ማሻሻል ስራ ያስፈልጋል የሚለው የግንባታው ባለቤት ጥያቄውን በፕላን አስተያየት መረጃ አስደግፎ ለኮሚሽኑ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል ፡፡

በተመለከተው መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት ኮሚሽኑ፡-

ሀ) የቀረበውን ጥያቄ ከጸደቀው ፕላን ጋር በማገናዘብ መርምሮና አጥንቶ ፕላኑን ያሻሽሊል፤ ወይም

ለ) ፕላኑን ለማሻሻል የሚያበቃ አጥጋቢ ምክንያት ካሊገኘ፣ ፕላኑ የማይሻሻልበትን ምክንያት ለጠያቂው በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡

ሐ) ፕላን ማሻሻል የሚያስፈልገው ሀገራዊ ወይም ከተማ አቀፍ ፋይዳ ባለው ፕሮጀክት ምክንያት ከሆነ፣

ሀ) የፕላን ማሻሻል ስራ ያስፈልጋል የሚለው የስራው ባለቤት ጥያቄውን ባስፈሊጊው የፕላን ስምምነት መረጃ አስደግፎ በጽሑፍ ለከንቲባው ያቀርባል፤

ለ) የፕላን ማሻሻል ጥያቄው በከንቲባው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ኮሚሽኑ ሲመራ፣ ኮሚሽኑ የቀረበውን ጥያቄ ከጸደቀው ፕላን ጋር በማገናዘብ መርምሮና አጥንቶ ለኮሚሽኑ ቦርድ በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ የውሳኔ ሐሳቡን ለከንቲባው ያቀርባል፤

ሐ) ከንቲባውም ፕላን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ሲያምንበት፣ ፕላኑ ተሻሽሎ የተጠየቀው ስራ በተሻሻለው ፕላን መሰረት እንዲስተናገድ በመወሰን ውሳኔውን ለኮሚሽኑ በጽሁፍ ያስታውቃል፤ ለሚቀጥለው የከተማው ምክር ቤት ስብሰባም በሚያቀርበው ዘገባ በማሳወቅ ያፀድቃል፤

መ) ኮሚሽኑም በከንቲባው ውሳኔ መሰረት ፕላኑን በ ማ ሻ ሻ ል ከ ን ቲ ባ ው ን ጨ ም ሮ ለሚመለከታቸው ተቋማት በጽሁፍ ያስታውቃል፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)-(፬) የተደነገገው ቢኖርም፣ኮሚሽኑ በመደበኛነት በሚያካሂደው ጥናትና ምርምር ግኝቶች ላይ ተመስርቶ መዋቅራዊ ፕላኑን በየሁለት ዓመት ተኩል ጊዜው ማሻሻል ይችላል ፡፡

፴፫. ግንባታን ለተወሰነ ጊዜ ስለማስቆም

፩) ኮሚሽኑ ፕላን በማዘጋጀት ወይም በማሻሻል ላይ በሚገኝበት በማንኛውም ጊዜ የማልማት ተግባር በዝግጅት ወይም በመሻሻል ላይ የሚገኝ ማናቸውም የከተማው ፕላን በሥራ ላይ እንዳይውል የማሰናከል ውጤት ይኖረዋል ተይወክላል ሲገመት፣ አዲስ የሚቀርብ የልማት ሥራን ለጊዜው ሊያስቆም ይችላል ፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ መሠረት የልማት ሥራ ለጊዜው እንዲቆም በተደረገበት አካባቢ የማልማት ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም፣ ለጊዜው እንዲቆም የተደረገ የልማት እንቅስቃሴ በዝግጅት ወይም በመሻሻል ላይ ያለን ፕላን ተፈጻሚነት በከፍተኛ ደረጃ ለዘለቄታው የማያውክ ሆኖ ሲገኝና በጣም ያስተዳድራል መሆኑ በከንቲባው በኩል ታምኖበት ሲቀርብ፣ የልማት ፈቃድ ተፈጻሚነቱ እንዲቀጥል በኮሚሽኑ ሊፈቀድ ይችላል ፡፡

፬) በዝርዝር ሕግ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም የልማት ሥራ ለጊዜው የማስቆም እርምጃ ተፈጻሚ የሚሆነው የፕላን ዝግጅት ወይም ማሻሻል ሥራ ተጠናቅቆ በልማት ስራው ላይ አለታዊ ውጤት እንደማይኖር እስከሚታወቅ ድረስ ይሆናል፡፡

፭) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ ልማትን ለጊዜው ማስቆሚያ የጊዜ ርዝመት ከአንድ ዓመት አይበልጥም፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፮. አዋጁን የማክበር ግድታ

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ በሕግ መሰረት አክብሮ የመፈጸምና ለአፈጻጸሙም የመተባበር ግድታ አለበት፡፡

፴፯. ቅጣት

፩) የወንጀል አፈፃፀም ክብደት እና መደራረብ በአጥፊው ላይ ስለሚያስከትለው ተጠያቂነት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር ፮፩/፪ሺ፯ አንቀጽ ፱ (፪) እና (፫) የተደነገጉት እንደየአግባቡ ተፈጻሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና ወይም መመሪያዎችን ለማስፈፀም የተመደበ የከተማው አስተዳደር ሓላፊ ወይም ሠራተኛ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ የተደነገገውን በመጣስ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ የተሰጠውን

ሹመት ስልጣን ወይም ሓላፊነት በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ወይም ስልጣኑን ወይም ሓላፊነቱን በመተላለፍ ወይም የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ በሙስና ወንጀልች አዋጁ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ህግ መሠረት እንደነገሩ ሁኔታ ይቀጣል!

ለ) ጉቦ ስለመቀበል፣ የማይገባ ጥቅም ስለማግኘት፣ ሥራን በማይመች አኳኋን ስለመምራት በሥራው ተግባር ስለሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ተግባር # በስልጣን ወይም በሓላፊነት ስለመነገድ፣ ያለአግባብ ጉዲይን ስለማጓተት፣ ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ስለማግኘት፣ ያለአግባብ ፈቃድ ስለመስጠት ወይም ስለማጽደቅ፣ የሥራ ሚስጢርን ስለመግለጽ እና ስለሌሎችም ሕገወጥ ተግባሮች በሙስና ወንጀልች አዋጁ የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ወንጀል የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀሎችን አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሐ) ማንኛውም ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ለማስፈጸም የተመደበ የከተማው አስተዳደር ሓላፊ ወይም ሠራተኛ ለፕላን ስምምነት የቀረበን ማመልከቻ ይወክላል ከከተማው ፕላን ጋር ለማይጣጣም የግንባታ ጥያቄ የግንባታ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣ በሕንፃ አዋጅ አንቀጽ ፴ በተደነገገው መሰረት እንደነገሩ ሁኔታ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አስርሺ በማያንስ ከብር ሀምሳ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ) ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ የቦታ አጠቃቀምና ይዞታን እንዲሁም ከግንባታ ሥራ አፈጻጸም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች የማስፈር፣ሰነድችን የመያዝ ወይም የመጠበቅ፣ የሰነድችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ወይም የመስጠት ሓላፊነት የተሰጠው የከተማው አስተዳደር ሓላፊ ወይም ሠራተኛ በጉዳዩ ጥቅም ያለውን ሰው ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌሎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ በሰነድ ያልተረጋገጠ መረጃ ወይም ሰነድ ከሚያስረዳው የተለየ መረጃ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም በትክክል መግለጽ ያለበትን ሁኔታ የሚያስገኘውን ውጤት ለማስቀረት ወሳኝነት ያለውን ፍሬ ነገር ያስቀረ እንደሆነ፣ በሕንፃ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አስር ሺህ እስከ ብር ሃያ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬) በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም፣ የተሳሳተው መረጃ የተሰጠው መረጃው የሚያስከትለውን ጉዳት ለመረዳት ሙያዊ ዕውቀቱ ወይም የሥራው ሓላፊነቱ በሚፈቅድለት ሠራተኛ

ወይም ሓላፊ የሆነ እንደሆነ፣ በሕንፃ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አስር ሺህ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተመለከቱ ሌሎች ድርጊቶችን የፈጸመ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ይቀጣል፡፡

**፴፰. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በአዋጁ የተሸፈኑ ጉዳዩችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፴፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩) የከተማው ካቢኔ የዚህን አዋጅ ዝርዝር አፈፃፀም የሚደነግጉ ደንቦችን እንደየአግባቡ ማውጣት ይችላል ፡፡

፪) የከተማው ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ዝርዝር የአፈጻጸም ስነ-ስርዓቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን እንዲያወጡ አግባብ ላላቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ስልጣን መስጠት ይችላል ፡፡

፫) በዚህ አንቀፅ የተደነገገው ቢኖርም፣ ኮሚሽኑ የከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ሙያዊ ልምድችና ደረጃዎች መመሪያ በዚህ አዋጅ መሰረት ያወጣል፡፡

**፵. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከዛሬ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡ ድ

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ የወጣ ደንብ

## ፵፱/፪ሺ፬

የመሬት ባለቤትነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በግልፅ እንደሰፈረው የሕዝብና የመንግስት ሀብት ሲሆን መሸጥ መለወጥ እንደማይቻል የተደነገገ በመሆኑ፤ ሀገሪቱ ከምትከተለው የነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር ለማጣጣም የመሬት አሰጣጥ ሥርዓት፣ የመጠቀም መብትና የመጠቀም መብትን በሊዝ የማስተላለፍ መብት በግልፅ እንዲለይ በማስፈለጉ እና በነበሩት አዋጆችና መመሪያዎች አፈፃፀም ላይ በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት በሊዝ የተሰጡ ቦታዎች ምንም ግንባታ ሳይካሄድባቸው ወይም ከተፈቀደው የግንባታ ደረጃ በታች እየተገነባባቸው ወደ ሦስተኛ ወገን የሚተላለፍበት ሁኔታ በስፋት መኖሩና ይህም ለኪራይ ሰብሳቢነት ዓይነተኛ ስልት እንደነበረ እንዲሁም የከተማ ቦታ በሊዝ የሚፈቀድባቸው ስልቶች በዓይነትም ሆነ በብዛት የተለያዩ መሆን ለብልሹ አሰራር ሰፊ በር የሚከፍቱ ሆነው በመመገኘታቸው፤

የከተማ መሬቶች በምሪት እና በሊዝ ስሪቶች የሚተዳደሩ በመሆኑ የከተማችን የመሬት ነክ ግብይት ከፍተኛ ልዩነት እንዲኖረው ማድረጉ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም ደንቦችንና መመሪያዎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ተግባራትን ለመቅጣት የሚያስችል ግልጽ የሆነ የቅጣት ድንጋጌ በአዋጁ ያልተደነገገ በመሆኑ እነዚህን ክፍተቶች ለመዝጋት እና አሰራሩን ወጥ ማድረግ በማስፈለጉ የአዋጅ ቁጥር ፯፩/፪ሺ፬ መውጣት ተከትሎ አዋጁን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ደንብ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፩/፪ሺ፬ ዓ.ም አንቀጽ ፴፫ ንኡስ አንቀጽ ፪ እና በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፩/፩[ü-፰ ዓ.ም አንቀጽ ፫(፩)ረ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት በሊዝ ስለመያዝ የወጣ ደንብ ቁጥር ፵፱/፪ሺ፬ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. “አዋጅ” ማለት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ነው፤

፪. “ሊዝ” ማለት በጊዜ በተገደበ ውል መሠረት የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት የሚገኝበት የመሬት ይዞታ ስሪት ዓይነት ነው፤

፫. “ከተማ” የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፬. “አግባብ ያለው ባለሥልጣን” ማለት በከተሞች መሬትን ለማስተዳደር እና ለማልማት በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

፭.“የከተማ ቦታ” ማለት በከተማ አስተዳደራዊ ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ነው፤

፮.“የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፯.“ካቢኔ” ማለት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፩/፲፭ አንቀጽ ፳፫ የተዘረዘሩት ተግባራትን የሚያከናውን የከተማው አስፈፃሚ አካል ነው፤

፰.“ነባር ይዞታ” ማለት ከተማው በሊዝ ስርዓት መተዳደር ከመጀመሩ በፊት በሕጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም ሊዝ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ለነባር ይዞታ ተነሺ በምትክ የተሰጠ ወይም ሊዝ ከመተግበሩ በፊት የተያዘ ሆኖ በአስተዳደሩ ከሊዝ ስሪት ውጭ እንዲቀጥል በህግ እውቅና የተሰጠው ቦታ ነው፤

፱.“በሕጋዊ መንገድ የተያዘ ወይንም አግባብ ባለው አካል ተፈቅዶ የተያዘ” ማለት መጀመሪያ አግባብ ባለው አካል ውሳኔ የተገኘና የተያዘ ቦታ ወይንም በህጋዊ መንገድ ባይያዝም ህጋዊ እውቅና ተሰጥቶት የይዞታ ማስረጃ የተሰጠው ወይም ከሺ፱፻፹፯ በፊት ተይዞ እንደሕጋዊ ይዞታ እንዲቆጠር አግባብ ባለው አካል በህግ እውቅና ተሰጥቶት የተያዘ ነባር ይዞታ ነው፤

፲.“የሕዝብ ጥቅም” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ወይም በልማት ዕቅድ መሠረት የህዝብ ጥቅም እንዲውል ብሎ የሚወስነው ቦታ ነው፤

፲፩.“የከተማ ፕላን” ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፤

፲፪.“ጨረታ” ማለት የከተማ የመሬት ይዞታ በገበያ የውድድር ሥርዓት በሚወጡ የውድድር መስፈርቶች መሠረት ለተጠቃሚው ወይም ለአልሚው መሬት በሊዝ የሚተላለፍበት አግባብ ዘዴ ነው፤

፲፫ “ልዩ ጨረታ” ማለት በአዋጁ ልዩ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች በጨረታ አግባብ የሚሰጥበት የጨረታ ዓይነት ነው፤

፲፬ “የጨረታ አስፈጻሚ ቡድን” ማለት አግባብ ባለው አካል የጨረታ ሂደቱን እንዲያስፈጽሙ በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት የቋሚ ቅጥር ምዝገባ የተሰጣቸው እና ተገቢ ባለሙያዎች

ያሉት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ የተዘረዘሩትን የመሬት ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚሰየሙ አባላት ያሉት ቡድን ነው፤

፲፭. "ምደባ" ማለት የከተማ መሬት ከውድድር ውጪ ባላቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ እየተመዘኑ በነፃ ወይም በሊዝ አግባብ መሬት ለልማት የሚፈቀድበት ሥልት ነው፤

፲፮. "የሊዝ መነሻ ዋጋ" ማለት የመሠረተ ልማት ዋጋን፣ የመሬት የዝግጅት ወጪን እና እንዲሁም ሌሎች ተጨባጭነት ያላቸው ታሳቢዎችን መሠረት በማድረግ የሚሠላ የመሬት ሊዝ ዋጋ ወለል ነው፤

፲፯. "ወቅታዊ የሊዝ ጨረታ ዋጋ" ማለትበአከባቢዉ ለተመሳሳይ የቦታ ደረጃና አገልግሎት በጨረታ ለቀረቡት ቦታዎች የተወዳደሩት ተጫራቾች የሰጡት ዋጋ አማካይ ስሌት ነዉ፤

፲፰. "የሊዝ መብት ማስተላለፊያ ዋጋ" ማለት ግንባታ ያልተከናወነበት ወይም ከግማሽ በታች የተገነባ ግንባታ ያረፈበትን የሊዝ መሬት መብት በህጉ መሰረት ሲተላለፍ አግባብ ባለው አካል የአካባቢውን የሊዝ መሬት ወቅታዊ የጨረታ ዋጋ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ዋጋ ነው፤

፲፱. "የችሮታ ጊዜ" ማለት መሬት በሊዝ የተፈቀደለት ሰው ወይም ነባር ስሪት ከውርስ በስተቀር የተላለፈለት ሶስተኛ አካል ከጠቅላላ የመሬቱ የሊዝ ዋጋ ውስጥ በየአመቱ መክፈል ያለበትን መክፈል ከመጀመሩ በፊት ከአመታዊ ክፍያ ነጻ ሆኖ እንዲቆይ የሚፈቀድለት የእፎይታ ጊዜ ነው፤

፳. "ግንባታ መጀመር" ማለት በቦታው ላይ  ለመስራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ሕንፃ ቢያንስ የመሠረት ሥራ፣ መጨረስና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችሉ የኮለን ብረቶች የማቆም ሥራ ማጠናቀቅ ነው፤

<u>፳፩ "ግንባታን በግማሽ ማጠናቀቅ" ማለት፡-</u>

ሀ. ቪላ ሲሆን የመሠረቱን፣ የኮለኖችና ለጣሪያ ውቅር የሚያስፈልጉ ቢሞችን ሥራ ማጠናቀቅ፤

ለ. ፎቅ ሲሆን የመሠረቱንና ከጠቅላላው ወለሎች ውስጥ፶በመቶ የሚሆኑትን የሶሌታ ሥራ ማጠናቀቅ፤ ወይም

ሐ. ሪል ስቴት ሲሆን የሁሉንም ብሎኮች ግንባታ እንደአግባቡ  በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) በተመለከተው ደረጃ ማጠናቀቅ ማለት ነው፤

፳፪. "ግንባታ ማጠናቀቅ" ማለት በሊዝ የተፈቀደ ቦታ ላይ እንዲገነባ የተፈቀደን ግንባታ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሰረት ሙሉ በሙሉ መሥራትና ዋና ዋና አገልግሎቶች ተሟልተውለት ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ነው፤

፳፫. "ቤት" ማለት በከተማ ለመኖሪያ፣ ለንግድ፣ ለማህበራዊ ወይም ለማንኛውም ሌላ አገልግሎት የተሠራ ወይም በመሰራት ላይ ያለ ማንኛውም ህጋዊ ግንባታ ነው፤

፳፬. “ልዩ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች” ማለት ለኢትዮጵያ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጡ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ወይም የትብብር መስኮች ለማስፋት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ለሚኖራት የተሻለ ግንኙነት መሠረት እንዲጥሉ በመንግሥት የታቀዱ እና የተወሰኑ ፕሮጀክቶች ናቸው፤

፳፭.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፮. የቃሉ አግባብ ሌላ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

__፫. የተፈፃሚነት ወሰን__

__፩ ይህ ደንብ፡-__

ሀ. በሚወጣበት ጊዜ በማንም ሰው ባልተያዘ የከተማ ቦታ ላይ፤

ለ. በከተማው መዋቅራዊ ኘላንና የአካባቢ ልማት ፕላን መሰረት አስተዳደሩ የመልሶ ማልማት ፕሮግራም ፈርሶ መልሶ እንዲለማ በሚደረግ የከተማው አካባቢዎች ላይ፤

ሐ. በሊዝ ለመያዝ በተጠየቀ ማንኛውም ነባር ይዞታ ላይ፤

መ. የሊዝ ስሪት ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት የተያዙና አስተዳደሩ ከሊዝ ስሪት ውጭ እንዲቀጥሉ በህግ እውቅና የሰጣቸው ይዞታዎች በነዚሁ እዉቅና በሰጡት ህጎች በነባር ስሪት እንዲቀጥሉ ከሚፈቀድላቸው ከፍተኛው የቦታ ስፋት በላይ ባላቸው ይዞታዎች/ቦታዎች ላይ፤

ሠ. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቅድ የተያዙና ህጋዊ እውቅና የሌላቸውን ይዞታዎች ስርዓት ለማስያዝ ሲሰራ ተቀባይነት የሚያገኙ ይዞታዎች፤

፪. በሌሎች ነባር ይዞታዎች ላይ ደንቡ ተፈጻሚ የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ ፮ መሰረት ይሆናል፡፡

## __ክፍል ሁለት__

## __መሬትን በሊዝ ስለማስተዳደር__

__፬. መሬት በሊዝ አግባብ ስለሚሰጥበት ስልት__

፩. ይህ ደንብ ከወጣ በኋላ የሚተላለፍ ማንኛውም የከተማ ቦታ የሚያዘው በሊዝ ስሪት ብቻ ነው፡፡

፪. በከተማ አስተዳደሩ ቦታ በሊዝ የሚፈቀደው፡-

ሀ. በዋናነት በጨረታ እና፤

ለ. እንደአስፈላጊነቱም በምደባ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ መሰረት በሊዝ የሚፈቀደው ቦታ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን እና ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲሁም ሌሎች ተገቢ የሆኑ የመሬት አጠቃቀም ፕላኖችን መሠረት በማድረግ ይሆናል፤ ይህም ለህዝቡ ይፋ መደረግ ይኖርበታል፡፡

፳.የነባር ይዞታ አስተዳደርን በተመለከተ

በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሰረት ከሕዝቡ ጋር ተወያይቶ እና ዝርዝር ጥናት ተከናውኖ እስከሚወሰን ድረስ ነባር ይዞታዎች በነባር ይዞታነት የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

፯.ነባር ይዞታን በሊዝ ስሪት ስለማስተዳደር

፩. ወደ ሦስተኛ ወገን የሚተላለፉ ነባር ይዞታዎች

በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንኡስ አንቀጽ ፫ መሰረት ከውርስ በስተቀር በማናቸውም መንገድ ወደ ሦስተኛ ወገን የሚተላለፍ ነባር ይዞታ ወደሊዝ ስሪት ሲሸጋገር በሊዝ መነሻ ዋጋ ክፍያ የሚፈጸም ሆኖ፡-

ሀ. ይዞታ የተላለፈለት ሰው የይዞታው አገልግሎት በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ወይም በአካባቢው የልማት ፕላን መሰረት የሚወሰን ሆኖ፣ የውል ዘመኑም በአዋጁ ለአገልግሎቱ በተወሰነው የሊዝ ዘመን ይሆናል፡፡ ሆኖም የቦታዉ ስፋትና ቅርጽ በፕላኑ የተቀመጠዉን የግንባታ ደረጃ ማከናወን የማይቻል ከሆነ አገልግሎቱ በሰነዱ ላይ በተጠቀሰዉ መሰረት ይሆናል፡፡

ለ. ወደ ሊዝ የሚገባው የቦታ ስፋት በሰነዱ ላይ ካለው የበለጠ ከሆነ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ዝርዝሩ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የይዞታው ስፋት ከሰነዱ ካነሰ ወይም ተመጣጣኝነት ካለው ግን በመስክ በልኬት በሚገኘው የቦታ ስፋት መሰረት ይሆናል፡፡

ሐ. ይዞታው ወደሊዝ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ቀደም ሲል ሲከፈል የነበረው ዓመታዊ የቦታ ኪራይ ቀሪ ሆኖ ቦታው ላይ ላረፈ ግንባታ ብቻ ግብር ይከፈላል፡፡

መ. የሊዝ ቅድሚያ ክፍያ የማይጠየቅ ሆኖ የሊዝ ክፍያው እንደቦታው አገልግሎት በዚህ ደንብ በተቀመጠው የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ ይሆናል፡፡

ሠ. ይዞታዉ የተላለፈለት ሰዉ ቦታዉን የፈለገዉ በቦታዉ ያለዉን ግንባታ ባለበት ሁኔታ ለመጠቀም ሳይሆን አዲስ በፕላኑ ሚፈቅደዉን ግንባታ ለማከናወን ከሆነ ጥያቄውን በጽሁፍ ሲያቀርብ የሁለት ዓመት የችሮታ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

ረ. የውል ዘመን መቆጠር የሚጀምረው የሊዝ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

ሰ. ይዞታዉ የጋራ ግቢ በመሆኑ የቤቱ ስፋት ከቦታው ስፋት ምጣኔ የክፍፍል ድርሻ ተሰልቶ በሚሰጥ የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የተያዘ ንብረት ከውርስ በስተቀር ወደ ሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ ከጋራ ግቢው የክፍፍል ምጣኔ ድርሻዉ ከ፶ በመቶ በላይ ከሆነ በሊዝ መነሻ ዋጋ ሆኖ ቀሪዉ የመንግስት ይዞታ ከሆነ በወቅታዊ የአከባቢዉ የሊዝ ጨረታ ዋጋ በሊዝ ይተላለፋል፡፡

፪. ህገወጥ ይዞታዎች ህጋዊ ሲደረጉ የአካባቢ ልማት ፕላን እና የሽንሻኖ ፕላንን መሰረት በማድረግ ህጋዊ ተደርገው ወደ ሊዝ ሲሸጋገሩ፤ የሊዝ መነሻ ዋጋን መሠረት በማድረግ፡-

ሀ) መዋቅራዊ ፕላኑ ወይም የአካባቢው የልማት ፕላን ባስቀመጠው የቦታ የአገልግሎት ዓይነት መሠረት አስተዳደሩ በሚወስነው የሊዝ ዋጋ የሊዝ ውል የሚገቡ ሆኖ የሊዝ ዋጋው ግን በልዩ ሁኔታ እስካልተወሰነ ድረስ ከአካባቢው የሊዝ መነሻ ዋጋ ማነስ የለበትም፤ የውል ዘመኑም ለአገልግሎቱ በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ወሰን መሰረት ይሆናል፡፡

ለ) የውል ዘመኑ መቆጠር የሚጀምረው ውል ከተዋዋለበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ ፳ ንኡስ አንቀጽ ፪ ከተመለከተዉ ቅድመክፍያ ያላነሰ እዉቅና ለተሰጠዉ ይዞታ በቅድሚያ መከፈል ይኖርበታል፡፡

መ) በይዞታዉ ላይ ተገንብቶ የሚገኘዉ ግንባታ የአከባቢዉ ፕላን ከሚፈቅደዉ ደረጃ በታችም ቢሆን ህጋዊ እዉቅና ሊሰጠዉ ይችላል፡፡ ሆኖም ባለይዞታዉ አስተዳደሩ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት በፕላኑ በተቀመጠዉ የግንባታ ደረጃ ቦታዉን እንዲያለማ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፫. በነባር እና በሊዝ ስሪት የሚተዳደሩ ይዞታዎች ለማቀላቀል በፕላን የሚፈቀድ ከሆነ እና የይዞታዎቹ መቀላቀል የሽንሻኖ ስታንዳርድን የጠበቀ ሆኖ ነባሩ ወደሊዝ ሲሸጋገር ባለመብቱ፡-

ሀ) የቦታው አገልግሎት የከተማው ፕላን በሚፈቅደው መሰረት ይሆናል፤

ለ) ነባሩ ይዞታ በሊዝ መነሻ ዋጋ የሚተላለፍ ሲሆን፣ ቀድሞ በሊዝ የተገኘው ይዞታ ግን ቀድሞ በተዋዋለው ውል ላይ በሰፈረው የሊዝ ውል ላይ የሰፈረዉ ዋጋ ይቀጥላል፤

ሐ) የሊዝ ዘመኑ የመወሰነዉ በሊዝ ቀድሞ ለተገኘው ቦታ የተፈቀደለትና የተጠቀመበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግና አዲስ ወደ ሊዝ ለሚገባው ነበሩ ይዞታ የሚፈቀደውን የሊዝ ዘመን አማካይ በማስላት ይወሰናል፤

መ) አመታዊ የሊዝ ክፍያ የሁለቱ ይዞታዎች ቀሪ ክፍያ ተደምሮ ለአማካዩ የሊዝ ዘመን በማካፈል በሚገኘው ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡

<u>፯.ወደ ሊዝ ስሪት ስለማይገቡ ነባር ይዞታዎች</u>

በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ነባር ይዞታዎች ወደ ሊዝ ስሪት የሚገቡ አይሆንም፡-

፩. በውርስ አግባብ የተገኘ ነባር ይዞታ ባለመብቶች ለመከፋፈል ጥያቄ አቅርበው ሽንሻኖው በፕላን ተቀባይነት አግኝቶ ክፍፍሉ ሲፈቀድላቸው፤

፪. በፍቺ የተለያዩ ነባር ይዞታ ያላቸው ባልና ሚስት በህግ በተወሰነው አግባብ ይዞታቸውን ሲከፋፈሉ ሽንሻኖው በፕላን ተቀባይነት ሲያገኝ፤

፫. በፍቺ የተለያዩ ባልና ሚስት ወይም የውርስ ባለመብቶች በይዞታው ላይ የክፍፍል ውሳኔ የተላለፈበት እና ከሁለቱ አንደኛው ወይም ከውርስ ባለመብቶቹ ከፊሎቹ ግምቱን ከፍለው ወይንም በባለድርሻዎች ስምምነት መሰረት ይዞታውን ያጠቃለሉት እንደሆነ፤

፬. ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከነባር ይዞታቸው ተነሺ የሆኑ ባለመብቶች በምትክነት በሚያገኙት ቦታ፤

፭.የሊዝ ስሪት ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት የተያዙና አስተዳደሩ ከሊዝ ስሪት ውጭ እንዲቀጥሉ በህግ እውቅና የሰጣቸው ይዞታዎች፤

፮.ከአዋጅ ፵፯/፷፯ ዓ.ም አግባብ ውጪ የተወረሱና አሁንበሚመለከተው መንግስታዊ አካል ለቀድሞ ባለመብቶች እንዲመለሱ በሚወሰኑ ይዞታዎች፤

፯.አዋጁ ጸድቆ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ነባር ይዞታ ላይ የሰፈረ ቤትን ተላልፎላቸው ወይም በነባር ይዞታነት በተገኙት የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ይዞታ ላይ የአባላት መተካካት ፈጽመዉ ዉላቸዉን ወይም ሰነዳቸዉን በፌዴራል የዉልና ማስረጃ ምዝገባ ኤጀንሲ ወይም በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳደሩ እጅ ገቢ ያደረጉና ያስመዘገቡ ሆነዉ በሂደት ላይ የነበሩ ወይም በባንኮች ተመላሽ ላልተደረገ ብድር ማስከፈያ በሀራጅ የተሸጡ ወይም በባንኮቹ የተወረሱና በዕጃቸዉ የሚገኙ ወይም በግዥ ወይም በስጦታ አግኝተዉ ስም ሳያዛዉሩ ቦታዉን ይዘዉ ቆይተዉ የነበሩና በልማት ሲነሱ እንዲያዛዉሩ የሚገደዱ ባለይዞታዎች ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅት ገዝተዉ ከተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር ዉል ያለዉ ይህ ደንብ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ስም ዝዉዉሩን ቀርበዉ ከፈጸሙ በነባር ስሪት ይቀጥላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዉስጥ ቀርበዉ ስም ዝዉዉሩን ካልፈጸሙ ወደ ሊዝ ስሪት የሚገቡ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የከተማ ቦታን በሊዝ ጨረታ ስለመስጠት</u>

### <u>፰.ለጨረታ የሚቀርብ መሬት መረጃን ለህዝብ ይፋ ስለማድረግ</u>

በአዋጁ አንቀፅ ፰ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መሬት ለጨረታ የሚቀርበው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-

፩. ከተማ አስተዳደሩ የመሬት ልማት ፍላጎትን መሰረት በማድረግ በየዓመቱ ለጨረታ የሚወጣውን የመሬት መጠን እና ጨረታው ትኩረት የሚያደርግባቸውን የልማት መስኮች በመለየትና አመታዊ እቅድ በማውጣት፡

ሀ) ለመኖሪያ፤

ለ) ለንግድ፤

ሐ) ለኢንዱስትሪ፤

መ) ለማህበራዊ አገልግሎት (ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለባህል፣ ለስፖርት እና ለመሳሰሉት)፤

ሠ) ለሌሎችም በሚል በዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዕቅዱ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

፪.ከተማ አስተዳደሩ ጨረታ ለማውጣት እቅዱን ለህዝብ ይፋ ባደረገው መሰረት አግባብ ያለው አካል የመፈጸም ግዴታ እና ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወጣል፡፡

፫.የጨረታ መነሻ ዋጋ፣ የቀድሞ የአካባቢው የጨረታ ዋጋ፣ የአካባቢዉ የልማት ዕቅድ እና ተዛማጅ መረጃዎች ህዝቡ በግልጽ እና በቀላሉ ሊያገኘው በሚችልበት አግባብ በስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ይህንን አለመፈጸምም ተጠያቂነትን የሚያስከትል ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወጣል፡፡

፬.የከተማ አስተዳደሩ የወደፊት ቀጣይ የጨረታ ቦታ ዝግጅት እና ያለፉ ጨረታዎች ዝርዝር መረጃ ለህዝብ ይፋ መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>፱.የጨረታ አቀራረብ</u>

፩. ጨረታ እንደፕሮጀክቱ ባህሪ መደበኛ ጨረታ ወይም ልዩ ጨረታ በመባል በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወጣ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩የተመለከተው መደበኛ ጨረታ በመደበኛ መርህ ግብር የሚወጣ እና በመጀመሪያው ዙር ቢያንስ ሶስት ተጫራቾች ካልቀረቡ የሚሰረዝ ነው፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወጣል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ በልዩ ጨረታ የሚካተቱት በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንኡስ አንቀጽ ፯ እና ፰ መሰረት ተለይተው በጨረታ አግባብ የሚስተናገዱ እና በመጀመሪያው ዙር አንድ ተጫራች ቢቀርብም እንዲስተናገድ የሚደረግበት ነው፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬. በዚህ ደንብና ይህንን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የማይሸፈኑ ጨረታን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሌሎች አግባብነት ባላቸዉ የሀገሪቷ ህጎች ይሸፈናሉ፡፡

<u>፲.ስለጨረታ ማስታወቂያ</u>

፩. የጨረታ ማስታወቂያ በጨረታው ስለሚወጣው መሬት ዝርዝር መረጃን በሚሰጥ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወጣ ይሆናል፡፡

፪. የጨረታ ማስታወቂያው በአማርኛ እንዲሁም ልዩ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጭምር የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

፫. የጨረታ ማስታወቂያ ጨረታው ከመውጣቱ ከአስር የስራ ቀናት በፊት አመቺ በሆኑ የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች የሚተላለፍ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወጣል፡፡

<u>፲፩.የመሬት ሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

በአዋጁ አንቀፅ ፱የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም በኤፍ.ም ሬዲዮዎች፣ በማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ በከተማ አስተዳደሩ

ድህረ ገጽ እና በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን አግባብ ባለው አካል አማካይነት ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

<u>፲፪. የጨረታ ሰነድ ይዘት እና አቅርቦት</u>

፩.የጨረታ ሰነድ የጨረታውን ዝርዝር መረጃ የጨረታ ዋጋ እና መወዳደሪያ መስፈርት ማቅረቢያ እንዲሁም ለተጫራች ዝርዝር መረጃን በሚሰጥ አግባብ የሚዘጋጅ ሆኖ ይዘቱ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. ማንኛውም ተጫራች በወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የጨረታዉን ሰነድ በግዥብቻ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

፫. የጨረታ ሰነዶችን ይዘት የሚለውጥ ማናቸውም ማሻሻያ ከተደረገ ማሻሻያውን በተጨማሪ የጨረታ ሰነድነት የጨረታውን ሰነድ ለገዙ ሁሉ በማስታወቂያ ሰሌዳ ተገልጾ እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

፬. የጨረታ ሰነድ ዋጋ ለጨረታው ማስፈጸሚያ የሚወጣውን ወጪ የሚተካ መሆን ይኖርበታል፡፡

፭. በጨረታ ሰነድ ግዢ መጠን ላይ የሚጣል ገደብ አይኖርም፡፡ ሆኖም አንድ ተጫራች ለአንድ ቦታ ከአንድ የጨረታ ሰነድ በላይ መግዛት አይችልም፡፡

፮. የጨረታ ሰነድ በሳጥን በማይገባበት ሁኔታ የጨረታ ሰነድ የተቀበለ ሰው መተማመኛ ደረሰኝ ለተጫራች ሊሰጥ ይገባል፡፡

<u>፲፫.የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና</u>

፩. ማንኛውም በጨረታው ለመሳተፍ የፈለገ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማስያዝ አለበት፤ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናው መጠን፣ የጠቅላላ የቦታው ስፋት በመነሻ ዋጋው ተባዝቶ ከሚገኘው ውጤት ፭ በመቶ ያነሰ መሆን የለበትም ፡፡ መጠኑና ሌሎች ተጫራቹ ሊያሟሉቸው የሚገቡት ቅድመ ሁኔታዎችን በሚመለከት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለተሸናፊ ተጫራቾች በዚህ ደንብ በተወሰነው ጊዜ እና ሁኔታ መሰረት ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አሸናፊ የሆነው ተጫራች የውል ግዴታውን ለመፈጸም የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ በዝግ ሂሳብ ያስያዘው ገንዘብ የሚታሰብለት ይሆናል፡፡ ሆኖም አሸናፊው ተጫራች በዚህ ደንብ በተወሰነው ቀነ ገደብ ውስጥ ቀርቦ ካልተዋዋለ አሸናፊነቱ ይሰረዛል፡፡ ያስያዘውም የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለአስተዳደሩ ገቢ ይደረጋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ መሰረት በአንድ ዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ አሸናፊነቱ ተገልፆ ቀርቦ ያልተዋዋለ እና ጨረታው የተሰረዘበት ተጫራች ለሁለት ዓመት በከተማው ውስጥ ከሚካሄድ ጨረታ ይታገዳል፡፡

## ፲፬. ተጫራቾችን የማወዳደርና አሸናፊዎችን የመለየት ሂደት

፩.የጨረታ አሸናፊዎችን ለመለየት የሚከተሉትን የማወዳደሪያ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ግልፅ በሆነ አግባብ ተገምግሞ ይወሰናል፡-

ሀ. ተጫራቾች ለቦታው ያቀረቡት ከፍተኛ የጨረታ ዋጋ ፹፭ በመቶ፤

ለ. የሊዝ ቅድሚያ ክፍያ መጠን ፲፶፭ በመቶ ይሆናል፡፡

፪.በጨረታ ውጤቱ ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋና የገቧቸው ግዴታዎች ተመሳሳይ ሆነው ከመቶ እኩል ነጥብ ካገኙና ከውድድሩ ተካፋዮች ውስጥ ብቸኛ ሴት ተወዳዳሪ ካለች የጨረታው አሸናፊ እንድትሆን ይደረጋል፡፡ ከዚህ ውጭ ከሆነ አጠቃላይ አሸናፊው በእጣ እንዲለይ ይደረጋል፡፡

፫. ለተጫረተበት ቦታ በሁሉም መስፈርቶች በሚያገኘው ድምር ውጤት ከፍተኛውን ነጥብ ከመቶ ያገኘ ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ይሆናል፤ አንደኛ የወጣው ተጫራች ካልቀረበና ሁለተኛ የወጣው ተጫራች አንደኛ የወጣዉ ተጫራች የሰጠውን ዋጋ ከፍሎ ቦታውን ለመረከብ ከፈለገ መብቱ ይጠበቅለታል፡፡ ሁለተኛ የወጣው ለመረከብ ፍቃደኛ ካልሆነ ጨረታው ይሰረዛል፡፡

፬. የጨረታ አሸናፊዎች ያሸነፉበት መስፈርት፤ ለቦታው የሰጡት ዋጋ፤ የሊዝ ቅድሚያ ክፍያ መጠኑ፤ ያሸነፈበት የቦታ አድራሻ፤ የአሸናፊው ሰው ሙሉ ስም በዝርዝር በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በግልፅ ለህዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡

፭. የጨረታ አሸናፊ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ መሰረት በሚመለከተው አካል የጨረታ ሂደቱ እና የተጫራቹ ሰነድ ትክክለኛነት እንዲሁም የአሰራር ጥራት ኦዲቱ ተረጋግጦ በማስታወቂያና በጽሁፍ ጥሪ ከቀረበለትና ከተገለጸለት ጀምሮ ባሉት ፲የስራ  ቀናት ውስጥ ቀርቦ አግባብ ካለው አካል ጋር  የሊዝ ውል መዋዋል አለበት፡፡ የከተማ ቦታ ሊዝ ውል እስኪፈረም ድረስ ባለመብትነት የሚረጋገጥ አይሆንም፡፡

፮.  የጨረታ አሸናፊ የሆነ ሰው አሸናፊነቱና የሚፈጽማቸው ቀጣይ ተግባራት አግባብ ባለው አካል ከማስጠንቀቂያው ጭምር በጽሑፍ ተገልጾለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭እና በአንቀጽ ፲፭ንዑስ አንቀጽ ፬ በተጠቀሰው ቀነ-ገደብ ውስጥ ቀርቦ ውል ካልተዋዋለ አሸናፊነቱ ተሰርዞ ያስያዘውም የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለከተማው ገቢ ይደረጋል፡፡

፯. የጨረታውም ውጤት ጨረታው በተከፈተ በሚቀጥለው የስራ ቀን ለሕዝቡ በማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

፰.  በአዋጁ አንቀፅ ፲፩ ንኡስ አንቀጽ ፯ ከተጠቀሰው ውጪ ለአንድ የቦታ ጨረታ ቦታው ለመጀመርያ ጊዜ የወጣ ከሆነ ቢያንስ ሦስት ተጫራቾች መቅረብ አለባቸው፡፡ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ በቂ ተወዳዳሪ ካልቀረበ ጨረታው ተሰርዞ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## ፲፭.ጨረታን ስለመመርመር

፩. የመሬት ሊዝ ጨረታ አስፈጻሚ ቡድን ጨረታውን ሊቀበል የሚችለው በጨረታ ሰነድ ላይ የተዘረዘሩት ተፈላጊ ነጥቦች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

፪. በጨረታው የቀረበው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪዎች፣ የውሉ ቃላትና ሁኔታዎች እንዲሁም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢታይበትና ይሄው ልዩነት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ የማያስከትልና የጨረታውን ቁምነገር ሳይለውጥ በቀላሉ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ያዘለ መሆኑ በፈፃሚ አካሉ ሲታመን ጨረታውን እንደተሟላ አድርጐ ሊቀበለው ይችላል፡፡

፫. አግባብ ያለው አካል ጨረታን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

፬. አግባብ ያለው አካል ተጫራችን አሳማኝ በሆነ ምክንያት ከጨረታው የማገድ ስልጣን ያለው ሲሆን ተጫራቹን ወይም ከጨረታ ሂደት ለማገድ የሚያበቁ መሰረታዊ ጉዳዮች እና ዝርዝር ምክንያቶች በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲፮.<u>የጨረታ ውጤት ስለማጽደቅ</u>

፩. የመሬት ሊዝ ጨረታ አስፈጻሚ የስራ ቡድን የጨረታ ውጤቱን በመገምገም አሸናፊውን እንዲሁም ሁለተኛ የወጣውን በመለየት ጨረታው በተከፈተ በሚቀጥለው የሥራ ቀን የጨረታ ውጤቱን  ይገልጻል፡፡ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሬትን ለማስተላለፍ ስልጣን የተሰጠዉ መስሪያ ቤት ዉስጥ የተቋቋመ የማኔጅመንት ኮሚቴ የጨረታ ዉጤቱን የማጽደቅ ስልጣን ይኖረዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩የተጠቀሰውን ውጤት እንዲያጸድቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ውጤቱ በቀረበለት በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ በማጽደቅ አግባብ ባለው ማስታወቂያ እና በከተማው ድህረ ገጽ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡ዝርዝሩ በመመሪያ ይገለፃል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሰረት የተገለጸው አሸናፊ ተጫራች ውጤቱ አግባብ ባለው መንገድከተገለጸለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት፲የስራ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ቅድመ ክፍያ በመፈጸም እና ተገቢውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ውል እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ መሰረት አሸናፊው ተጫራች ግዴታውን አሟልቶ ውል ካልፈረመ በሦስት ተጨማሪ የስራ ቀናት ቀርቦ ቅድመ ሁኔታዉን አሟልቶ ውል እንዲፈርም በጽ/ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ማስጠንቀቂያ እንዲለጠፍለት ይደረጋል፡፡

፭.የጨረታው አሸናፊ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ መሰረት በተሰጠው ሦስት ተጨማሪ የስራ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ቅድመ ክፍያ ያልፈጸመ ከሆነ ቦታውን እንደማይፈልገው ተቆጥሮ በሲፒኦ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበርያ ገንዘብ ለከተማው ገቢ ይደረጋል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ፭መሰረት ውል ላልተፈጸመበት ቦታ የጨረታ አስፈጻሚ ቡድኑ ሁለተኛ ለወጣው ተጫራች አንደኛ የወጣዉ ተጫራች በሰጠዉ ዋጋ መሠረት

ተመሳሳይ ጥሪ በማድረግ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ እና ፬ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን ቅድመ ሁኔታ እንዲያሟላ እና ውል እንዲፈጽም ያደርጋል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፮ መሰረት በተሠጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ካልቀረበ ጨረታው እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

፲፮.<u>የጨረታ ማስከበሪያ ዋጋ ሲፒኦን ተመላሽ ስለማድረግ</u>

፩.በቂ ተጫራቾች ባለመቅረባቸው ምክንያት ከጨረታው የተሰረዙ ተጫራቾች ለማስከበርያ ያስያዙት ሲፒኦ ተመላሽ የሚደረግላቸው ይሆናል፡፡

፪. የጨረታው አሸናፊዎች ውጤት ከተገለጸ ጊዜ ጀምሮ ቀሪዎቹ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዙት ሲፒኦ ከሚቀጥለው የሥራ ቀን ጀምሮ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

፫. በጨረታው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች አሸናፊው ቀርቦ ውል መዋዋሉ እስኪረጋገጥ ድረስ ለመቆየት እና አሸናፊው ካልቀረበ ወይም ውጤቱ ካልጸደቀለት ለጨረታ ባቀረበው ዋጋ ቦታውን ለመቀበል ፍላጎት ካለው እና ይህንንም በማመልከቻ ለጨረታ አስፈጻሚ ቡድን ከገለጸ ያስያዘው ሲፒኦ ሳይመለስ ተመዝግቦ ሊቆይ ይችላል፡፡

፲፯.<u>የሊዝ ጨረታ አስፈጻሚ ስለማደራጀት</u>

፩. የሊዝ ጨረታ አስፈጻሚው መሥሪያ ቤት የሊዝ ጨረታ አስፈጻሚ ቡድን ሲያደራጅ ቋሚ ቅጥር ሠራተኞች መሆን አለባቸው፡፡

፪. የጨረታ አስፈጻሚ የሙያ ስብጥር፣ ተግባር እና ኃላፊነት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፱.<u>የሊዝ ጨረታ አስፈጻሚ ኃላፊነት</u>

፩. ለሊዝ ጨረታ የተዘጋጁትን ቦታዎች ከምንም ዓይነት ይዞታ ነፃ መሆናቸውን፣ ሽንሻኖ ያላቸው መሆኑንና መሠረተ ልማት የቀረበላቸው መሆናቸውን በመስክ በማረጋገጥ ርክክብ ያደርጋል፡፡

፪. ዝርዝር የጨረታ ጥሪ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

፫. የጨረታ ማስታወቂያ ጥሪ ያደርጋል፡፡

፬. የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ ግምት ያወጣል፣ ሽያጭ ያከናውናል፡፡

፭. የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ያዘጋጃል፣ ያሽጋል፡፡

፮. የጨረታዉን ሂደት ይመራል፡፡

፯. የጨረታ አሸናፊን በተቀመጠው የግምገማ መስፈርት ይለያል፤ የውሳኔ ሃሳብ አደራጅቶና ውሳኔ እንዲሰጥ ስልጣን ለተሰጠው አካል አቅርቦ ያጸድቃል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፰. በእያንዳንዱ የሊዝ ጨረታ የጨረታውን አጠቃላይ ሂደት የሚያሳይ በተለይም የጨረታውን አፈፃፀም ሥርዓት፣ እያንዳንዱ ተጫራች ለመስፈርቱ ያቀረበውን ኃሳብና

የገባቸውን ግዴታዎች፣ ያቀረባቸውን ልዩ ልዩ ሰነዶች፣ በተለየ ሁኔታ የቀረበ ማመልከቻ ካለ የጨረታውን አሸናፊ፣ አሸናፊ የሆነበትን ምክንያት እንዲሁም ሌሎች ተጫራቾች ያላሸነፉበትን ምክንያት የያዘ ቃለ ጉባዔ ያዘጋጃል፡፡

፱. ለዉዝፍ ዕዳ መክፈያ የተያዘን መሬትና መሬት ነክ ንብረት በተቻለ መጠን ሽያጩን የሚፈጽመዉ በዕዳው ልክ ብቻ ይሆናል፡፡ ለሥራውም የተለያዩ አግባብነት ያላቸው አጋዥ ሙያተኞችን ያስተባብራል ይመራል፡

## ክፍል አራት

## የከተማ ቦታን በሊዝ ምደባ ስለመስጠት

### ኟ.መሬት በሊዝ ምደባ የሚሰጥበት አግባብ

፩. መሬት በሊዝ ምደባ የሚሰጠው በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ መሰረት ለተፈቀደላቸው ፕሮጀክቶች እና ዘርፎች በከተማው ካቢኔ በኩል በየዓመቱ ዕቅድ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ ይተገበራል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንኡስ አንቀጽ ፩ በፊደል ተራ "ሰ" መሰረት በከተማ ከንቲባ እየተመሩ በካቢኔ የሚወሰኑ ሌሎች ፕሮጀክቶች ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### ኟ፩. በሊዝ ምደባ ስለሚሰጡ ቦታዎች የጥያቄ አቀራረብና አወሳሰን ስርአት

፩. ጥያቄዉ የባለ በጀት መስሪያ ቤት ከሆነ ቀጥሎ በተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) የባለበጀት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማረጋገጫ፣

ለ) ቦታው የሚጠየቀው በበጀት ዓመቱ ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች መሆኑ ማረጋገጫ፣

ሐ) ለፕሮጀክቱ የተፈቀደ በጀት መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

፪. ጥያቄው በበጎ አድራጎት ድርጅት ለማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋም ለመገንባት የቀረበ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ፡-

ሀ) የዘመኑ የታደሰ የምዝገባ ፍቃድ፣

ለ) ስራውን ለመስራት ከከተማ አስተዳደሩ የተሰጠው ፍቃድ፣

ሐ) ለመስራት የታሰበው ፕሮጀክት ተቀባይነት ከከተማ አስተዳደሩ ማረጋገጫ፣

መ) ለፕሮጀክቱ የተያዘ በጀት ስለመኖሩ ማረጋገጫ ሊያሟሉ ይገባል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸው ሲረጋገጥ እና ሲፈቀድ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነዱ በአስተዳደሩ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስም ተዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡

፫. ጥያቄው ለእምነት ተቋማት ማምለኪያ ቦታዎች ከሆነ በዚህ ደንብ የከተማ አስተዳደሩ በሚያጸድቀው አግባብ ተወስኖ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬.ጥያቄው በመንግስት የከተማ የመኖሪያ ቤት ፖሊሲ መሠረት ለሚቀርብ መሬት ከሆነ በወጣው ፖሊሲና ተከትለው በሚወጡ ዝርዝር መመሪያ መሠረት ይተገበራል፡፡

፭. ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እና ሌሎች በአዋጁ ለተመለከቱ ምደባዎች የፕሮጀክቱ ዝርዝር ጥናት በመሰረታዊነት መሟላት አለበት፡፡

፮.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ከ፩ እስከ ፫ መሰረት ተገቢው ቅድመ ሁኔታ የተጠናቀቀ እና የማጣራት ሂደቱን በአግባቡ የፈጸመ ፕሮጀክት ወይም ዘርፍ በስታንዳርድ መሰረት ተገቢ የሆነ የቦታ ስፋት በምደባ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

፯. በልማት ምክንያት ለሚነሱ የመንግስት የንግድ ቤት ተከራዮች በአዋጅና በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት የልማት ቦታ ሲሰጥ በምደባ ይሆናል፡፡

፳፪.<u>በልማት ምክንያት የሚነሱ ነዋሪዎችን መልሶ ለማስፈር ስለሚሰጥ ቦታ</u>

ይዞታቸው በልማት ምክንያት ወይም በመልሶ ማልማት ምክንያት ለሚለሱ ነዋሪዎች የሚደረገው የካሳ አከፋፈል ስርዓት አግባብ ባለው ሕግ የሚመራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ህጋዊ የነባር ባለይዞታ ምትክ ቦታ በነባሩ ስሪት ይሰጠዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. የሊዝ ይዞታ ባለመብት የውል ዘመኑ ከመድረሱ በፊት ቦታውን እንዲለቅ አይደረግም፡፡ ሆኖም ይዞታው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚፈለግ ሲሆን የሊዝ ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ህጋዊ ባለመብት ለቀሪው የሊዝ ዘመን ተመሳሳይ ስፋት እና ደረጃ ያለው ምትክ ቦታ በነባሩ ሊዝ አግባብ ይሰጠዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. በሬጉላራይዜሽን ስራ እውቅና ከሚሰጣቸው ይዞታዎች ውጪ በህገ-ወጥ መንገድ በተያዘ ቦታ ላይ ለሰፈረ ንብረት በተለያየ ምክንያት እንዲነሳ ሲወሰን ምንም ዓይነት ካሣ እና ምትክ ቦታ አይሰጥም፡፡

፬. በከተማው ውስጥ የመንግስት ቤት ወይም የቀበሌ መኖሪያ ቤት ህጋዊ ተከራይ ሆነው በከተማው መልሶ ማልማት ፕሮግራም ምክንያት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ የጋራ መኖሪያ ቤት በግዥ የሚያገኝበት ሁኔታ ይመቻችለታል ፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፭. የመንግስት ወይም የቀበሌ የንግድ ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆኑ ሰዎች በከተማ መልሶ ማልማት ፕሮግራም ምክንያት ተነሺ በሚሆኑበት ጊዜ ፕላኑ የሚፈቅደውን ግንባታ በጋራ ለማከናወን ፍላጎት ሲኖራቸዉ ለዚሁ ግንባታ የሚሆን ተመጣጣኝ ቦታ የከተማ አስተዳደሩበሚወስነው መሠረት ማጣራት ተደርጎ በፕላኑ ለህንጻ ግንባታው ከተፈቀደው ቦታ፡-

ሀ) በነፍስ ወከፍ ፳፭ ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ መነሻ ዋጋ የሚስተናገዱ ሆኖ በፕላን የተመለከተው ሽንሻኖ ለአባላቱ በነፍስ ወከፍ ከተፈቀደው ጠቅላላ ስፋት በላይ ከሆነ

ቀሪው አስተዳደሩ ወቅታዊ የአከባቢዉ የጨረታ ዋጋን መሰረት በማድረግ በሚወስነዉ ዋጋ ይሆናል፤

ለ) ሆኖም አስተዳደሩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቦታ ማቅረብ የማይችል ከሆነ ወይም የልማት ተነሺዎቹ ቁጥራቸዉ አነስተኛ በመሆኑ ቦታ መመደብ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም ተነሽዎቹ በሚፈለገዉ እስታንዳርድ ለማልማት አቅም ሳኖራቸዉ ሲቀር የኮንዶሚንየም ንግድ ቤቶች ወይም ሌሎች በአስተዳደሩ ለተመሳሳይ አላማ ከተገነቡ ቤቶች በገበያ ዋጋ ቅድሚያ ግዥ መብት ይኖራቸዋል፡፡

፮. በከተማው ክልል ውስጥ በልማት ምክንያት የመኖሪያ ቤትና ቦታቸውን እንዲለቁ የተደረጉ አርሶ አደሮች አግባብ ባለው ሕግ ተወስኖ ለንብረቱ ከሚከፈለው ካሳ በተጨማሪ በከተማ አስተዳደር ካቢኔ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ምትክ ቦታ በነባር ስሪት ይሰጣቸዋል፡፡

፳፫.<u>በአጭር ጊዜ በሊዝ ስለሚሰጡ ቦታዎች</u>

፩. በአዋጁ አንቀፅ ፲፰ ንዑስ አንቀፅ ፪ ፊደል ተራ ለ በተጠቀሰው መሰረት በአጭር ጊዜ ጥቅም ላይ የማይውሉ የከተማ ቦታዎች ለሚከተሉት አገልግሎቶች ማለትም፡-

ሀ) ከከተማ ግብርና ሥራ ጋር የተያያዙ /አትክልት፣ አበባ፣ ዶሮ እርባታ ወዘተ፤

ለ) ለግንባታ ዕቃዎች ማምረቻ ወይም መሸጫ ወይም ማሳያ፤

ሐ) ለግንባታ ጊዜ ማሽነሪና ቁሳቁስ ማስቀመጫ፤

መ) ለግንባታ ድንጋይ ማውጫ እና ለዚሁ ተግባር የሚሆን ማሽነሪ መትከያ፤

ሠ) ለማስታወቂያ ሰሌዳ መትከያ፤

ረ) ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለተለያዩ አገልግሎቶች ማቅረቢያ እና ማምረቻ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

፪. በአጭር ጊዜ ሊዝ ይዞታ የተሰጠ ቦታ አጠቃቀምና ውል አያያዝ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) የአጭር ጊዜ ለሊዝ ይዞታ ውል ለግብርና ስራ ፲፭ ዓመት ሲሆን ለሌሎች እስከ ፭ ዓመት ጊዜያት ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

ለ) ለአጭር ጊዜ የተሰጠ ቦታ ለልማት ሲፈለግ አስፈላጊነቱ እየታየ ለቀሪው የውል ጊዜ ብቻ መጠቀሚያ የሚሆን ምትክ ቦታ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫. በጊዜያዊ ሊዝ የሚሰጥ ቦታ የከተማ አስተዳደሩ የሊዝ መነሻ ዋጋንና የጨረታ ዋጋን መሰረት በማድረግ በሚወስነዉ አመታዊ ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለሊዝ ውል እና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

፳፬.<u>የሊዝ ውል የሚመራባቸው መርሆዎች</u>

የአዋጁ እና የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሊዝ ውል በፍትህብሔር ህግ አስተዳደር ክፍል መስሪያ ቤቶች ስለሚያደርጓቸው ውሎች በተደነገገው መሰረት ይመራል፡፡

፳፫.የሊዝ ውል ስለመፈረም

፩. ቦታ በሊዝ ጨረታ ባሸነፈ ወይም በምደባ በተሰጠው ወይም በአዋጁና በዚህ ደንብ ወደ ሊዝ ሥሪት እንዲገባ በሚደረግ የከተማ ቦታ ሊዝ ባለመብትና በውል ሰጪው መካከል ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት የከተማ ቦታዎች በሊዝ ሲተላለፍ በውሉ ሰነድ ላይ የዉል ተቀባይ መብትና ግዴታ፣ የውል ሰጪን ተግባርና ኃላፊነት፣ ጠቅላላ የሊዝ ይዞታ አስተዳደር ሁኔታዎችን፣ የግንባታ መጀመሪያና ማጠናቀቂያ የጊዜ ገደብ፣ በተጨማሪ ከቦታው የተለየ ባህሪ ጋር የሚሄዱ ልዩ ሁኔታዎችን የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡ ዝርዝሩ በመመርያ ይወሰናል፡፡

፫. የውሉ ቃሎችና ሁኔታዎች ረቂቅ ከጨረታው ሰነድ ጋር እንደ አንድ ክፍል ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፬. በሊዝ ውሉ ላይ የተገለፁና የውሉ ሰነድ አካል ሆነው የተፈረሙ ጉዳዮች በሊዝ ተቀባዩም ሆነ በሊዝ ውል ሰጪው በኩል ሕግ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

፭. በጨረታ የተሰጡ ቦታዎችን በመስሪያ ቤቱ ወይንም ሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት በውሉ በተጠቀሰው ቀን መሠረት ማስረከብ ካልተቻለ ውሉ እንደገና ይታደሳል፤ የችሮታ ጊዜ፣የግንባታ መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ ጊዜ እንዲሁም የሊዝ ክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ እንደገና እንደ አዲስ ይወሰናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፮. አስፈላጊውን ክፍያ አጠናቅቆ የሊዝ ውል የተዋዋለ ሰው በግንባታው ዓይነትና ደረጃ ተለይቶ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ መጀመርና ማጠናቀቅ አለበት፡፡

፳፮. የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት

፩. የከተማ ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው የሊዝ ይዞታ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪. የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መግለጫዎች፦

ሀ) ቦታ በሊዝ የተፈቀደለትን ሰው ሙሉ ስም ከነአያት ወይም የድርጅቱ ስም፤

ለ) የቦታውን ስፋትና አድራሻ፤

ሐ) የቦታውን የአገልግሎት ዓይነት፣ ደረጃና የፕሎት ቁጥር፤

መ) የሊዝ ይዞታው ፀንቶ የሚቆይበትን ዘመን፤

ሠ) የይዞታ የምስክር ወረቀት ቁጥር፤

ረ) ኤክስ ዋይ ኮኦርድኔት አካቶ መያዝ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## የከተማ ቦታ ሊዝ ዋጋ እና የክፍያ አፈፃፀም

## ፳፮. የከተማ ቦታ የሊዝ መነሻ ዋጋ

፩. የከተማ የቦታ ሊዝ መነሻ ዋጋ ትመና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ስልቶች በማገናዘብ ይዘጋጃል፡-

ሀ) የከተማ ቦታ የሊዝ መነሻ ዋጋ የቅመራ ስልቱ በርካታ መሬትና መሬት ነክ ግብይቶች፣ የጊዜ ልዩነት ማስተካከያን፣ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን፤ ወቅታዊና የወደፊት የእድገት እንድምታ ጥናቶችን በማካሄድና የመሬት አጠቃቀም እና የቦታ ደረጃን ታሳቢ በማድረግ መዘጋጀት አለበት፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ (ሀ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦታውን ለማዘጋጀት ለተነሺዎች የተፈጸመ የካሳ ክፍያ፣ የቦታ ዝግጅት፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የስራ ማስኬጃ እና ሌሎች ተጨባጭነት ያላቸው ተጓዳኝ ወጪዎችን የሚያገናዝብ ይሆናል፡፡

፪. የከተማ ቦታን በዋጋ ቀጠና ስለ መከፋፈል እና አተገባበሩ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሰረት የተሰላውን የከተማ ቦታዎች ዝርዝር የሊዝ መነሻ ዋጋ መሰረት በማድረግ የዋጋ ቀጠና ካርታ መዘጋጀት አለበት፤

ለ) የሊዝ መነሻ ዋጋ ወቅታዊነቱ ተጠብቆ እንዲካሄድ በየሁለት ዓመቱ የሚካሄዱትን የመሬት ሊዝ ጨረታዎች ሁሉንም የቦታ ቀጠና እና የአገልግሎት ዓይነት ታሳቢ በማድረግ መዘጋጀት አለበት፤

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ፪ (ሀ) የተዘጋጀ የዋጋ ቀጠና ካርታ በወቅቱ አግባብ ባለው አካል በማስጸደቅ በከተማው መሠረታዊ ካርታ እና በጽሑፍ ተዘጋጅቶ በማንኛውም ተደራሽ የመረጃ መረብና ለእይታ በሚመች የማስታወቂያ ሰሌዳ ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ በተዘጋጀው መሠረት የተዘጋጀ የመነሻ ዋጋ በጨረታ ለሚቀርቡና በምደባ በሚሰጡ ቦታዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል ፡፡

፬. ለጨረታ የቀረበ ማንኛውም ቦታ ለቦታው ደረጃ ከተቀመጠው የመነሻ ዋጋ በታች ሊተላለፍ አይችልም፡፡

፭. አነስተኛ ገቢ ላላቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለመኖሪያ አገልግሎት፣ ለማኑፋክቸሪንግ፣ ለከተማ ግብርና እና ለቢዚነስ አገልግሎት የሚዉሉ ቦታዎች እንደየአገልግሎቱ የተለየ መነሻ ዋጋ በማጥናት ሊደረግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፯.የመሬት የሊዝ ዋጋ

፩. የከተማ መሬት የጨረታ ዋጋ ለእያንዳንዱ ቦታ ወይም የጨረታ ቁጥር አሸናፊ ተጫራች የሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ነው፡፡

፪. በምደባ የተላለፈ ቦታ የሊዝ ዋጋ በየአገልግሎቱ ዓይነት በተናጠል ተለያይቶ ሊተመን ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለዲኘሎማቲክና ለዓለም አቀፍ ተቋማት በመንግስት ስምምነት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በመንግስት በኩል ግልጽ ስምምነት በማይኖርበት ጊዜ በአከባቢዉ ወቅታዊ የጨረታ ዋጋ መሰረት ይሆናል፡፡

፬. ለሀይማኖት ተቋማት የአምልኮ ማከናወኛ እና ለባለበጀት የመንግስታዊ ተቋማት የመስሪያ ቦታ የሚመደበው በቦታው ላይ ለነበረው ንብረት እና ቦታው የአርሶ አደር ከሆነም ለዚሁ አግባብ የተከፈለውን ካሳ ክፍያ የሚተካ ክፍያ  በአንድ ጊዜ ሲፈጽሙ ነው፡፡ መሬቱ ግን ከሊዝ ክፍያ ነፃ ይሰጣል፡፡ ዝርዝር የክፍያ አወሳሰኑ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፱.የሊዝ ክፍያ አፈፃፀም

በሊዝ ቦታ የተፈቀደለት ሰው፡-

፩. ከሊዝ ዋጋ የቅድሚያ ክፍያ መጠን በልማት ሥራው ወይም በአገልግሎቱ ዓይነት ተለይቶ የሚወሰን ሆኖውል ተቀባይ የሚፈጽመው የሊዝ ቅድሚያ ክፍያ ከጠቅላላው የሊዝ ዋጋ ፲ በመቶ ያነሰ አይሆንም፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከተው ቢኖርም፣ ጠቅላላ የቦታውን የሊዝ ዋጋ ክፍያ በአንድ ጊዜ የመክፈል መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

፫. ቅድሚያ ክፍያ ከፈፀመ በኋላ እንደ ልማት ወይም አገልግሎት ዓይነት የሚለያይ ሆኖ ለመኖሪያ አገልግሎት እስከ ፳ ዓመት ለሌሎች አገልግሎቶች እስከ ፴ ዓመት እንዲሁም ለከተማ ግብርና እስከ ፭ ዓመት የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ ይሰጠዋል፤ ዝርዝሩ ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ ላይ ይወጣል፡፡

፬. በየዓመቱ የሊዝ ክፍያ መፈጸም ያለበት ሆኖ ከጠቅላላ የቦታው የሊዝ ዋጋ የከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ተቀንሶና ቀሪው ክፍያ ለተሰጠው የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ ተካፍሎ የሚገኘውን አማካይ ዋጋ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ እስከ ማጠናቀቂያ ጊዜው በየዓመቱ ይከፍላል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ውል ተቀባይ ዓመታዊ ክፍያውን በዓመቱም ውስጥ ከፋፍሎ ለመክፈል ጥያቄ ካቀረበ የሚመለከተው አካል ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ሆኖም የክፍያ አፈጻጸሙ ከሶስት ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

፮. በየዓመቱ በሚከፈለው ቀሪ የሊዝ ክፍያ ላይ የዓመቱ ወለድ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማበደሪያ ተመን መሠረት ይከፍላል፡፡ የወለድ ምጣኔውም የባንክ የማበደሪያ ተመን ሲለወጥ አብሮ ይለወጣል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ ፩ እስከ ፮ የተደነገጉት ቢኖሩም አነስተኛ ገቢ ላለቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለመኖሪያ አገልግሎት በሊዝ የሚመደቡት ቦታዎች የሊዝ

ክፍያዉ እስከ ሊዝ ዘመኑ ማብቂያ ድረስ በየአመቱ የሚከፈል ሆኖ ወለድ አይታሰብም፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፰. የሊዝ ክፍያዉን ከመክፈያ ጊዜዉ ቀድሞ ላጠናቀቀ ሰዉ ከጠቅላላዉ የሊዝ ዋጋ እስከ ፭ በመቶ የሚደርስ የሊዝ ዋጋ ቅናሽ ማበረታቻ ሊደረግለት ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፴.<u>የሊዝ ውዝፍ ክፍያን ስለመሰብሰብ</u>

፩. መሬት በሊዝ አግባብ የተፈቀደለት ሰው አግባብ ካለው አካል ጋር በገባው ውል መሰረት ክፍያውን በወቅቱ መፈጸም አለበት፡፡

፪. በአዋጁ አንቀጽ ፳ ንኡስ አንቀጽ ፯ መሰረት የሊዝ ባለይዞታው የሊዝ ክፍያውን ለመክፈል በሚገባው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልከፈለ በየአመቱ ክፍያውን ባለመክፈሉ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በየደረጃው የሚሰጠው ሆኖ የሦስት ዓመት ውዝፍ ካለበት ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ አግባብ ያለው አካል ንብረቱን ይዞ በመሸጥ ለውዝፍ ዕዳው መክፈያ የማዋል ስልጣን አለው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚሸጠው ንብረት በጨረታ አግባብ ሆኖ በሊዝ የተያዘው መሬት እና በመሬቱ ላይ የሠፈረውን ንብረት ብቻ የሚመለከት ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፰ መሰረት የሚመለከተው አካል ውዝፍ ዕዳውን ለማስመለስ የሚያከናውነው ሽያጭ የንብረት አስተዳደሩን በህግ አግባብ የሚያውክ አለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ያልተከፈለውን የሊዝ ዕዳ ለማስከፈል የሚበቃውን ንብረት ብቻ ይሆናል፡፡

፭. የሊዝ ባለይዞታ ሃብት መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት ብቻ ላይ ነው፡፡

፮. ውዝፍ የሊዝ ክፍያ የሚሰበሰበው ተቋም የሊዝ ባለይዞታውን ሃብት በሚይዝበት ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፖሊስ ሃይል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል፡

፯. ሃብቱን የያዘው ተቋም ሃብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከአሥር የሥራ ቀናት በኋላ በሃራጅ እስከቻለው ድረስ በዕዳው ገደብ ንብረቱን መሸጥ ይችላል፡፡

፰. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ባልተከፈለ የሊዝ ክፍያ ምክንያት የሚገኝን ገቢ ወይም ሌላ ንብረት መያዝ የሚቻለው የሊዝ ክፍያ ለመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም ሃብቱን በመያዝ ውዝፍ የሊዝ ክፍያ እንደሚሰበስብ አስቀድሞ ለሊዝ ባለይዞታው በፅሁፍ ካስታወቀ በኃላ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሃብቱ ከመያዙ ሠላሳ (፴) ቀናት በፊት ለሊዝ ክፍያ ባለዕዳው ሊደርሰው ይገባል፡፡

፱.በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በሕግ አግባብ በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በውዝፍ የሊዝ ክፍያ ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ

ወይም ለውዝፍ ሊዝ ባለዕዳው ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው ውዝፍ የሊዝ ክፍያ የሚሰበስብ ተቋም ሲጠይቀው የያዘውን ሃብት የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

፲.ማንኛውም ሰው የውዝፍ ሊዝ ክፍያ የሚሰበስብ ተቋም ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው ውዝፍ የሊዝ ክፍያ መጠን (በውዝፍ ሊዝ ክፍያ ላይ የሚታሰበውን ወጪ ጨምሮ) ሊበልጥ አይችልም፡፡

፲፩.በዚህ አንቀጽ መሰረት ንብረቱ ለውዝፍ ዕዳው መክፈያ የተያዘበት ሰው በአፈጻጸሙ ላይ ቅሬታ ካለው ጉዳዩን ለከተማው ከንቲባ ኮሚቴ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

፲፪.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፲፪ መሰረት አቤቱታው የቀረበለት አካል ጉዳዩን መርምሮ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

<u>፵፩.የችሮታ ጊዜን ስለመወሰን</u>

፩. የከተማ ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው እንደ ልማቱ ወይም አገልግሎቱ ዓይነት ከሁለት እስከ አራት ዓመት የሚደርስ ሆኖ፡-

ሀ) ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ዘርፎች ፬ ዓመት ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

ለ) ለግዙፍ ሪል እስቴት ፬ ዓመት ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

ሐ) ለትምህርት ዘርፍ በየደረጃዉ እስከ ፬ ዓመት ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

መ) ለጤና ዘርፍ እስከ ፫ ዓመት ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

ሠ) ለሆቴሎች እስከ ፬ ዓመት ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

ረ) ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ፬ ዓመት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ ፩ ከ ሀ እስከ ረ የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆኖ የችሮታ ጊዜን ላልተወሰነላቸው ዘርፎች የከተማ አስተዳደሩ ከተጨባጭ ሁኔታው በመነሳት እስከ አራት ዓመት ጊዜ ድረስ መወሰን ይችላል፡፡

፫.የችሮታ ጊዜ የተወሰነለት አካል የችሮታ ጊዜ መነሻ የሊዝ ውል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ይሆናል፡፡ የሚፈቀደው የችሮታ ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ከግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

፬.ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የከተማ ቦታ በሊዝ ተፈቅዶለት በቦታ አስረካቢው አካል ምክንያት ቦታ ያልተረከበ ወይም ቦታ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ደንቡ እስከፀናበት ቀን ድረስ ከ ፪ ዓመት በላይ ያልሆነው ወይም የቅድሚያ ክፍያ መጠን ይቀነስልኝ ወይም የክፍያ ማጠናቀቂያ ጊዜ ይራዘምልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የችሮታ ጊዜ እንደአግባብነቱ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

## ስለቦታ አጠቃቀም፣ የግንባታ መጀመር እና ማጠናቀቅ

## የግንባታ ደረጃዎች

፴፪.የግንባታ ደረጃዎች

፩. አነስተኛ ደረጃ ያላቸው ግንባታዎች፡-

ሀ) እስከ ፫ ወለል ያላቸዉ የተናጠል መኖሪያ ቤት፣ ወይም፤

ለ)እስከ ሶስት ወለል ያላቸዉ የሕዝብ መጠቀሚያ ያልሆኑ ሌሎች ግንባታዎች ወይም፤

ሐ)የይዞታ ስፋቱ እስከ ፪፻፶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚገነቡ ግንባታዎች ናቸው፡፡

፪.መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ግንባታዎች፡-

ሀ) ፩ ወለልና ከዚያ በታች ለሆኑ የሕዝብ መጠቀሚያ ህንፃዎች፤ወይም

ለ) የይዞታ ስፋቱ ከ ፪፻፶፩ እስከ ፭ ሺ ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገነባ ግንባታዎች፤ወይም

ሐ) የመኖሪያ ቤት ፬ እና ፭ ወለል የሆኑ ግንባታዎች፤ወይም

መ) የመኖሪያ ቤት በአንድ ጊዜ እስከ ፹ ነጠላ ቤቶች የያዙ፤ወይም

ሠ) የሕዝብ መጠቀሚያ ያልሆኑ ሌሎች ወለላቸው ፬ እና ፭ ለሆኑ ግንባታዎች፤ወይም

ረ) ለትምህርት ተቋማት እስከ ፪ኛ ከፍተኛ ደረጃ የሚያጠቃልሉ ግንባታዎች፤ወይም

ሰ) ለጤና ማዕከል እስከ ከፍተኛ ልዩ ክሊኒክ የሚያጠቃልሉ ግንባታዎች፤ ወይም

ሸ) ለቤተ መፃሕፍትና ለሁለገብ አዳራሾች እስከ ፭፻ ሰው የሚይዙ ግንባታዎች፤ወይም

ቀ) ለስፖርት ሜዳዎችና ለስፖርት ማዘውተሪያ ማዕከላት እስከ ፭፻ ሰው የሚይዙ ግንባታዎች፤ወይም

በ) አጠቃላይ የወጪ ግምታቸው እስከ ብር ፭ሚሊዮን (አምስት ሚሊዮን) የሆኑ መካከለኛና አነስተኛ የማምረቻ እና ማከማቻ ተቋማቶችን ያጠቃልላል፡፡

፫.ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ግንባታዎች

ሀ) ፮ ወለልና ከዚያ በላይ ለሆነ ማንኛውም ግንባታ፤ ወይም

ለ) ስፋቱ ከ፭ሺ ካሬ ሜትር ቦታ በላይ በሆነ ይዞታ ላይ ለሚገነቡ፤ወይም

ሐ) በዓለም፣ በአገር እንዲሁም በከተማ አቀፍ ደረጃ ለሚገነቡ የትራንስፖርት የመናኸሪያ ተቋማቶች፤ ወይም

መ) ትላልቅ የዲፕሎማቲክ ተቋማት የሚገነቧቸው ግንባታዎች፤

ሠ) ከላይ በአነስተኛና በመካከለኛ ግንባታ ደረጃ ከተጠቀሱት ዉጭ ያሉትን ግንባታዎች ያጠቃልላል፡፡

፴፫.ግንባታን መጀመር

፩.ማንኛውም ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው የሊዝ ዉል ከፈረመበት ቀን ጀምሮ ለግንባታ ደረጃው በተቀመጠው የግንባታ መጀመሪያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ መጀመር አለበት፡፡

፪.የግንባታ መጀመሪያ የጊዜ ጣሪያ ለአነስተኛ ደረጃ ግንባታዎች እስከ ፮ ወር፣ ለመካከለኛ ደረጃ ግንባታዎች እስከ ፱ ወር እና ለከፍተኛ ግንባታዎች እስከ ፲፰ ወር ይሆናል፡፡

፫.በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከ ሀ-ሐ የተመለከተው ጣሪያ ቢኖርም በዚህ የጊዜ ጣሪያ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታ ሳይጀምር ቢቀር ለአንድ ጊዜ ብቻ ከማስጠንቀቂያ ጋር ለአነሰተኛ ግንባታዎች ፮ ወር፣ ለመካከለኛ ግንባታዎች ፱ ወር እና ለከፍተኛ ግንባታዎች ፩ ዓመት ተጨማሪ የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ በግንባታ ፈቃድ ሰጪው አካል ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ የሚፈቀዱት የግንባታ መጀመሪያ የጊዜ ዕርዝማኔ በማንኛውም ሁኔታ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ዕርዝማኔን ለመጠየቅ ወይም ለመፍቀድ በምክንያትነት ሊቀርቡ አይችሉም፡፡

፭.ከላይ በዚህ አንቀጽ ስር የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ በመልሶ ማልማትና ሌሎች ፈጣን ልማት በሚጠይቁ ሁኔታዎች ላይ አስተዳደሩ ከዚህ ያጠረ ጊዜ ሊደነግግ ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

<u>፴፬.ግንባታን ስለማጠናቀቅ፣</u>

፩. ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው የሊዝ ውል ከሚመለከተው አካል ጋር በተፈራረመው መሠረት የግንባታ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን አንስቶ በግንባታው ደረጃ ወይም ዓይነት በተወሰነው የጊዜ ጣሪያ ውስጥ ግንባታውን በማጠናቀቅ በቦታው ላይ አገልግሎት መስጠት መጀመር አለበት፡፡

፪. አነስተኛ ደረጃ ግንባታዎች እስከ ፳፬ ወራት፣ መካከለኛ ደረጃ ግንባታዎች እስከ ፴፮ ወራት እና ከፍተኛ ደረጃ ግንባታዎች እስከ ፶፰ ወራት የሚደርስ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ይኖራቸዋል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአነስተኛ የግንባታ ደረጃ ለአንድ ጊዜ ከማስጠንቀቂያ ጋር ተጨማሪ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ፮ ወራት ሊፈቀድ ይችላል፡፡ ለመካከለኛ ለአንድ ዓመት እና ለከፍተኛ ደረጃ ግንባታዎች አንድ ዓመት ከማስጠንቀቂያ ጋር ተጨማሪ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፫/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ  በአዋጁ አንቀፅ ፳፫ ንዑስ አንቀፅ /፫/ በተደነገገው መሠረት በማንኛውም ሁኔታ የአነስተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ደረጃ ግንባታዎች እንደቅደም ተከተላቸው ፪ ዓመት ተኩል፣ ፬ ዓመትና ከ፭ ዓመት በላይ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ሊፈቀድላቸው አይችልም፡፡ ሆኖም ግዙፍ እና የተቀናጀ ልማትን የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች በከተማው አስተዳደር በኩል ተጨባጭ እና ልዩ መርሀ ግብር ወጥቶላቸው ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፯. ከላይ በዚህ አንቀጽ ስር የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ በመልሶ ማልማትና ሌሎች ፈጣን ልማት በሚጠይቁ ሁኔታዎች ላይ አስተዳደሩ ከዚህ ያጠረ ጊዜ ሊደነግግ ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፴፯.<u>የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ ስላለፈባቸው ይዞታዎች</u>

፩. አግባብ ባለው አካል በሊዝ መሬት የተፈቀደላቸውን ሰዎች መረጃ በመያዝ የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ ከማለቁ ቢያንስ ከሁለት ወር ቀደም ብሎ እንደአመቺነቱ በደብዳቤ በአድራሻቸው ወይም ማስታወቂያ በቦታው ላይ በመለጠፍ ወይም በአካባቢው በሚገኝ የህዝብ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

፪. የግንባታ መጀመሪያ የጊዜ ገደብ ያለፈበት ሰው ቦታው በተፈቀደበት የአስተዳደር ዕርከን ለሚገኘው አግባብ ያለው አካል ቀርቦ ግንባታ ያልጀመረበትን ምክንያትና በቀጣይ ግንባታውን ለመጀመር ያለውን ዝግጁነትና አቅም የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ወይም ካለፈ በኃላ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

፫. ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ በዚህ ደንብ የተቀመጠው ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ የጊዜ ይራዘምልኝ ጥያቄ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር እንዳጋጠመው በማስረጃ ማረጋገጥ እስካልተቻለ ድረስ ተቀባይነት የለውም፤ የጥያቄዉ ዝርዝር መገምገሚያ መስፈርት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬. ተጨማሪ የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ ተፈቅዶለት በተጨማሪው ጊዜ ውስጥ ግንባታ ያልጀመረ ወይም ተጨማሪ የጊዜ ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ ወይም ቀርቦ ያልጠየቀን ሰው ውል በማቋረጥ አግባብ ያለው አካል ቦታውን መልሶ መረከብ ይችላል፡፡

፭. የሊዝ ውል የተቋረጠበት ሰው በዚህ ደንብና በሊዝ አዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከፊደል ተራ ሀ-ሐ የተደነገገው ቅጣት እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

፴፰.<u>የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ስላለፈባቸው</u>

፩. አግባብ ያለው አካል እንደግንባታው ደረጃ በዚህ ደንብ የተቀመጠው የጊዜ ጣሪያ ካለፈ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ያላጠናቀቀበትን ምክንያት በአሥር የስራ ቀናት ውስጥ የሊዝ ባለመብቱ ቀርቦ በማስረጃ እንዲያስረዳ  በጽሁፍ ጥሪ ማድረግ አለበት፡፡

፪. ባለመብቱ ጥሪው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ካላስረዳ ወይም አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ ካልቻለ የግንባታው ማጠናቀቂያ የጊዜ ገደብ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ለሚፈቀድለት ተጨማሪ ጊዜ ከጠቅላላው የሊዝ ዋጋ የሚታሰብ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ወር የ፩ በመቶ የገንዘብ ቅጣት በአንድ ጊዜ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፫. የሊዝ ባለመብቱ በተሰጠው ፲ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ካመለከተና ግንባታውን ያላጠናቀቀው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በማስረጃ ካረጋገጠ ያለቅጣት ተጨማሪው ጊዜ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

፬. የሊዝ ባለመብቱ በተጨማሪ የጊዜ ገደብ ውሰጥ ግንባታውን ካላጠናቀቀና በቦታው ላይ የተገነባው ግንባታ ከተፈቀደዉ ጠቅላላ ግንባታ ከ፴ በመቶኛ ያነሰ ከሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሊዝ ውሉን በማቋረጥ ቦታውን መረከብ ይችላል፡፡ ሆኖም በቦታው ላይ የተገነባው ከተፈቀደው ጠቅላላ ግንባታ ፴ በመቶኛ እና ከዚያ በላይ ከሆነ በሊዝ አዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ ፯ የተደነገገው እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

፭. የሊዝ ባለመብቱ ተጨማሪ የጊዜ ገድብ ውስጥ ግንባታውን ማጠናቀቅ ባለመቻሉ አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀፅ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ ፬ ከፊደል ተራ ሀ-ሐ መሠረት የሚሰጠው ጊዜ ገደብ እንደ ግንባታ ማጠናቀቅያ ተጨማሪ ጊዜ የሚታሰብ ይሆናል፡፡

፮. በአዋጁ አንቀፅ ፳፫ ንዑስ አንቀፅ ፯ መሠረት በወጣው ጨረታ ተወዳደሮ ያሸነፈ ባለሀብት በስሙ ይዛወርለታል፡፡ አግባብ ካለው አካል ጋርም አዲስ ውል ይዋዋላል፡፡ ግንባታ ማጠናቀቅያ ጊዜን በተመለከተ ግንባታው ያለበት ደረጃ ታይቶ ለቀሪው ሥራ የሚያስፈልገው ጊዜ በባለሙያ ተረጋግጦ ይሰጠዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፴፯.<u>በሊዝ የተሰጡ ቦታዎች የአገልግሎት ለውጥ ስለመፍቀድ</u>

፩. በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሰረት አንድ የአገልግሎት ለውጥ ሲፈቀድ አስቀድሞ በተገባው ውል መሰረት ሊዝ ውሉ ይፈረማል፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል የተፈረመው ውል የአገልግሎት ለውጥ እንዲደረግ ከተጠየቀበት የሊዝ ዘመን ጣርያ ከበለጠና የዋጋ ለዉጥ ካለ ለአገልግሎቱ በተሰጠው የሊዝ ዘመን ጣርያና በአዲሱ ዋጋ ይሆናል፡፡

፪. የቀረበው የአገልግሎት ለውጥ ጥያቄ የፕላን ምደባ ለውጥ (የዞኒንግ ለውጥ) የሚያስፈልገው ከሆነ መጀመሪያ የፕላን ለውጥ ጥያቄው በፕላን አፈጻጸም ክትትል አግባብነት ላለዉ አካል ቀርቦ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል ፡፡

፫. የአገልግሎት ለውጥ ሲፈቀድ አስቀድሞ በተገባው ውል መሰረት ሊዝ ውሉ ይፈረማል፡፡ሆኖም ቀደም ሲል የተፈረመው ውል የአገልግሎት ለውጥ እንዲደረግ ከተጠየቀበት የሊዝ ዘመን ጣርያ ከበለጠ ለአገልግሎቱ በተሰጠው የዘመን ጣርያ መሰረት የሊዝ ዘመኑ ይለወጣል፡፡

፬. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት አግባብነት ያለው አካል ሳያውቀው ወይም ሳያፀድቀው የተፈፀመ ማናቸውም የአገልግሎት ለውጥ ፕላኑ የሚቀበለው ከሆነ ብቻ የግንባታውን ዝርዝር ዋጋ .፩ በመቶ በማስከፈል ለውጡ በዚህ ደንብ ድንጋጌ መሰረት እንዲስተካከል ይደረጋል ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ስር ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም ሁኔታ የአገልግሎት ለውጥ ተፈጽሞ ከተገኘ የአካባቢው ከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ፫ በመቶ ቅጣት ተከፍሎ መዋቅራዊ ፕላኑ የሚፈቅድ ወይም ሊስተካከል የሚችል ከሆነ ለውጡ ሊፈቀድ ይችላል፤ የሊዝ ዋጋውም አዲስ በተቀየረው የአገልግሎት ዓይነት  መሰረት ተስተካክሎ በቀሪው የሊዝ የመክፈያ ዘመን እንዲጠናቀቅ ይደረጋል፡፡

፬. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለአገልግሎት ለውጡ የሚከፈለው የሊዝ ዋጋ ቀድሞ ከነበረው አገልግሎት ዓይነት የሊዝ ዋጋ የሚያንስ ሆኖ ከተገኘ ከነበረው የሊዝ ዋጋ አይቀነስም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ስር ከላይ የተዘረዘሩት ቢኖሩም የአገልግሎት ለዉጥ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረዉ የሚችለዉ ጥያቄዉ በከተማዉ መዋቅራዊ ፕላንና የአከባቢ ልማት ፕላን መሰረት ተቀባይነት ካለዉ ብቻ ነዉ፡፡

## ክፍል ስምንት

## የሊዝ መብትን ስለማስተላለፍ

### ፴፰. ግንባታ ያልተጀመረበትን ቦታ የሊዝ መብት ስለማስተላለፍ

የሊዝ መብትን የማስተላለፍና በዋስትና የማስያዝ አፈፃፀም በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ፡-

፩. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ ግንባታ ለመጀመር በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፬ የተቀመጠው ጊዜ ከማለፉ በፊት የሊዝ መብቱን ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

፪. ማንኛውም የሊዝ ባለመብት ግንባታ ለመጀመር የተመለከተዉ ጊዜ ከማለፉ በፊት የሊዝ መብቱን ሲያስተላልፍ ከውርስ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንኡስ አንቀጽ ፫ (ሐ) የተመለከተው የሚፈጸመው አግባብ ባለው አካል በሚወስነው ወቅታዊ የመሬት ሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ መሰረት ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መብቱን ለመሸጥ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን አግባብ ላለው አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ አግባብ ያለው አካልም በአስራ አምስት የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ መሬቱን ለጨረታ በማቅረብ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንኡስ አንቀጽ ፫ (ሀ) እና (ሐ) በተመለከተው መሰረት መብቱን የሚያስጠብቅለት ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለመብቱ በመሸጫ ዋጋው ካልተስማማ እና መሬቱም ለጨረታ እንዲወጣ ፈቃደኛ ካልሆነ አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንኡስ አንቀጽ ፫ (ሀ) የተመለከተውን ክፍያ በመፈጸም ቦታውን መልሶ ይረከበዋል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ መሰረት የሚመለከተው አካል ቦታውን በህጉ የተቀመጠው ጊዜ ገደብ ከመድረሱ በፊት መልሶ ለመረከብ የሚችለው ባለመብቱ በጽሁፍ ስምምነቱን ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

፴፱. <u>ግማሽ ግንባታ ያረፈበትን ቦታ የሊዝ መብት ማስተላለፍ</u>

፩. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ከግማሽ በታች ግንባታ ያረፈበትን ቦታ የሊዝ መብት ለሶስተኛ አካል ማስተላለፍ ይችላል፡፡

፪. የሪል ስቴት ልማትን በተመለከተ በተናጠል በተጠናቀቀ ግንባታ ላይ የሪል ስቴት ባለሀብቱ በገባው ውል መሰረት ለተጠቃሚው ማስተላለፍ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ሪል ስቴቱን ወደሶስተኛ አካል ከውርስ በስተቀር ለማስተላለፍ ሲፈልግ በሁሉም ብሎኮች ላይ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪ ንኡስ አንቀጽ ፳፩ መሰረት ግንባታውን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሰረት የተላለፈ የሊዝ መብት ዋጋ አግባብ ላለው አካል የሚቀርበው የመሬት ሊዝ መብት ዋጋ እና የግንባታ ዋጋ በሚል ተለይቶ ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀፅ መሰረት ከግማሽ በታች ግንባታ የተፈጸመበት ቦታ ዝውውር የሚፈጸመው ባለመብቱ በቅድሚያ አግባብ ባለው አካል በቀረበው የመሬት ሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ ከተስማማ ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ መሰረት ከውርስ በስተቀር ወደ ሶስተኛ አካል የተላለፈ የሊዝ መብት የስም ዝውውር የሚፈጸመው መብቱ የሚተላለፍለት ሰው አግባብ ላለው አካል የመሬት ሊዝ መብት ዋጋውን ገቢ አድርጎ የሊዝ ዉል ሲዋዋልና የሊዝ ቅድመ ክፍያ ሲፈጽም ብቻ ነው፡፡

፮. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ መሰረት ገቢ ከተደረገለት ገንዘብ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንኡስ አንቀጽ ፫ (ሀ) እና (ሐ) የተመለከተውን ክፍያ ገንዘቡ ገቢ በተደረገ በሶስት የስራ ቀናት ዉስጥ ለሻጭ የሚከፍለው ይሆናል፡፡

፯.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፬ በተመለከተው መሰረት የሊዝ መብቱን ለማስተላለፍ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን አግባብ ላለው አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ አግባብ ያለው አካልም በአስራ አምስት የስራ ቀን ጊዜ ውስጥ ቦታውን ለጨረታ በማቅረብ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንኡስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሰረት መብቱን የሚያስጠብቅለት ይሆናል፡፡

፰.በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ፯ መሰረት የጨረታ መነሻ ዋጋ የመሬት ሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ ከግንባታው ዋጋ ጋር ተደምሮ ይሆናል፡፡

፱. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፰ የተመለከተውን የግንባታ ግምት አግባብ ያለው አካል ግልጽ በሆነ አግባብ የሚገምተው ይሆናል፡፡ ግንባታን ለመገመት የወጡ ወጪዎች ካሉ ከሽያጩ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፵. ግማሽና በታች ግንባታ የተከናወነበትን ቦታ ከዉርስና ካፒታል መዋጮ ዉጭ የሊዝ መብት ማስተላለፍ ላይ የተቀመጡ ክልከላዎች

፩.በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንኡስ አንቀጽ ፺ በተመለከተው መሰረት በመሬት የወቅት ጥበቃ የሚመጣን ጥቅም ለማግኘት ሲባል ግንባታ ከመጀመሩ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪ ንኡስ አንቀጽ ፳፩ መሰረት ግንባታውን ከግማሽ በላይ ከመገንባቱ በፊት በሦስት ዓመት ውስጥ ለሦስት ጊዜ የሊዝ መብቱን ያስተላለፈ ከሆነ ለሁለት ዓመት ከማንኛውም የመሬት ሊዝ ጨረታ እንዳይሳተፍ ይደረጋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መሰረት የእግድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው በእግዱ ጊዜ ውስጥ በጨረታ ሂደት የተሳተፈ ከሆነ ከጨረታው ተሰርዞ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ ሆኖ በሊዝ ጨረታ እንዳይሳተፍ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እግዱ ይራዘማል፡፡

፵፩.የሊዝ መብት መሸጫ ወይም ማስተላለፊያ ዋጋ

፩.ማንኛውም የሊዝ ባለመብት ግንባታ ያልተከናወነበትን መሬት ወይም ከግማሽ በታች ግንባታ ያረፈበትን መሬት የሊዝ መብት ወደሶስተኛ ወገን ሲያስተላልፍ አግባብ ያለው አካል መብቱ የተላለፈበትን ዋጋ የሚወስነው በሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ መሰረት ይሆናል፣በሚኖረው አማካይ ውጤት ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. የሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ የሚወሰነው ቦታው በተላለፈበት አካባቢ ያለው የወቅቱ ከፍተኛ ጨረታ ዋጋ እና መሬቱ ቀደም ሲል ለባለመብቱ የተላለፈበት ዋጋ ተደምሮ ለሁለት በማካፈል ነው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሰረት የተገኘው ውጤት ገዥ ለመሬቱ ካቀረበው ዋጋ እኩል ወይም የሚያንስ ከሆነ ማስተላለፉ አግባብ ባለው አካል ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፬. ገዥ ዋጋ ባልሰጠበት ሁኔታ የሊዝ መብት መሸጫ ዋጋው (አማካይ ውጤቱ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ መሰረት አማካይ ውጤቱ ለባለመብቱ መሬቱ ቀደም ሲል ከተላለፈበት ዋጋ በታች ከሆነ አግባብ ያለው አካል ከሁለቱ ተደማሪዎች በተሻለው የመሸጫ ዋጋውን ሊወስን ይችላል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ገዢው ከተገኘው አማካይ የሰጠው ዋጋ ውጤት ከ፭ በመቶ በታች ከሆነ አግባብ ያለው አካል አማካይ ውጤቱን መነሻ በማድረግ ቦታውን ለጨረታ የሚያቀርበው ይሆናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የሊዝ መብትን በዋስትና ስለማስያዝ

፵፪.<u>ግንባታ ያልተከናወነበትን ቦታ በዋስትና ስለማስያዝ ወይም በካፒታል አስተዋጽኦነት ስለመጠቀም</u>

፩. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬መሰረት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የሊዝ መብቱን በዋስትና ለማስያዝ ወይም የከፈለውን ቅድመ ክፍያ በካፒታል አስተዋጽኦነት መጠቀም ይችላል፤

፪. ማንኛውም ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሰረት በዋስትና ማስያዝ የሚችለው ከሊዝ የቅድሚያ ክፍያው ወይም ከቅድሚያ ክፍያው ተጨማሪ የከፈለም ከሆነ ከክፍያ መጠኑ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ሊደረጉ የሚችሉ ተቀናሾች ታስበው በሚቀረው የገንዘብ መጠን ላይ ብቻ ይሆናል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሊዝ መብቱን በዋስትና ያስያዘ ሰው የዋስትና ግዴታውን ባለመወጣቱ በህጉ መሰረት የተመለከተው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

፵፫. <u>ግንባታ ያረፈበትን ቦታ በዋስትና ስለማስያዝ ወይም በካፒታል አስተዋጽኦነት ስለመጠቀም</u>

፩. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ በማንኛውም ደረጃ ላይ ግንባታ ያረፈበትን ይዞታ የሊዝ መብቱን በዋስትና ለማስያዝ ወይም በካፒታል አስተዋጽኦነት ለመጠቀም ይችላል፡፡

፪.ማንኛውም ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሰረት በዋስትና ማስያዝ የሚችለው ከሊዝ የቅድሚያ ክፍያው ወይም ሌላ በተጨማሪነት የተፈጸመ ክፍያ ካለም በተከፈለው መጠን ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሊደረጉ የሚችሉ ተቀናሾች ታስበው በሚቀረው የገንዘብ መጠን እና የግንባታ ዋጋው ተሰልቶ ብቻ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሰረት በመሬቱ ላይ ያለውን የሊዝ መብት መጠን መረጃ አግባብ ያለው አካል የሚሰጥ ሲሆን የግንባታ ዋጋ ግምቱ በዋስትና የሚይዘው አካል ሀላፊነት ይሆናል፡፡

፬. ይዞታውን በዋስትና የሚይዘው አካል የንብረቱን ግምት እና ያበደረውን የገንዘብ መጠን ዕዳውን ለሚመዘግበው አካል በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፭. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በዋስትና የተያዙ የሊዝ መብቶች በነባር ዉላቸዉ መሠረት በቀድሞው አሰራር የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፭ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በመያዣነት የተያዘ የሊዝ ዕዳ ያለበት ይዞታ በተለይ ግንባታው በጅምር ወይም ከግማሽ በታች ሆኖ ዕዳው ሳይጠናቀቅ እና ተበዳሪ ግዴታውን ባለመወጣቱ ንብረቱ በሊዝ ሰጭዉ አስተዳደር ስር የሚሸጥ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ያለው አካል ቀሪ የሊዝ ዕዳው ቅድሚያ ከሽያጩ ላይ የሚከፈለው ይሆናል፡፡ መብትና ግደታዎቹን በተመለከተ በአዋጁ መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፮ መሰረት ቀሪ የሊዝ ዕዳ ያልተፈጸመ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ያለው አካል የስም ዝውውሩን የሚፈጽም አይሆንም፡፡

፰. የሊዝ ይዞታና ንብረቱ በዋስትና ያስያዘ ሰዉ የዋስትና ያዥዉን ግዴታ ባለመወጣቱ በህግ አግባብ ንብረቱን የሚሸጥ ወይንም የሚወርስ ከሆነ የሊዝ ሰጭዉ ስምምነትና መብት ባከበረ መልኩ መከናወን ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አስር

## የሊዝ ዘመን አወሳሰን የሊዝ ውል እድሳት እና የሊዝ ውል ማቋረጥ

### ፵፬.የሊዝ ዘመን አወሳሰን

የከተማ ቦታ የሊዝ ዘመን በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ የተመለከተው ይሆናል፡፡ ሆኖም በአዋጁ በግልጽ ባልተደነገጉ የልማት ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች የሊዝ ዘመንን በተመለከተ በከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይወሰናል፡፡

### ፵፭.የሊዝ ውል እድሳት

፩. የሊዝ ዘመን እድሳትና የእድሳት አፈፃፀም ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት መሠረታዊ ምክንያቶች፡-

ሀ. በመዋቅራዊ ፕላን ለውጥ፣

ለ. ቦታው ለህዝብ ጥቅም ሲፈለግ፣

ሐ. ነባሩን ልማት ቦታው ወደሚጠይቀው የልማት ደረጃ እና አግባብ ለመቀየር የማይቻል ሲሆን የሊዝ ውሉ ዳግም ላይታደስ ይችላል፡፡

### ፵፮.የአጭር ጊዜ የሊዝ ዉል ዕድሳት

፩. የአጭር ጊዜ ሊዝ ውል ቦታው ለሌላ ልማት የማይፈለግ መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሊታደስ ይችላል፣ ሆኖም የውል እድሳቱ ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. ለማስታወቂያ ሰሌዳ መትከያ የተፈቀዱ ቦታዎች ቦታው የማይፈለግና የትራፊክ እንቅስቃሴን የማያውክ መሆኑ እየተረጋገጠ በየጊዜው ሊታደስ ይችላል፡፡

### ፵፯.የሊዝ ውል ስለማቋረጥ እና ካሳ አከፋፈል

፩. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) መሠረት ሲቋረጥ ተገቢው ወጪና መቀጫ ተቀንሶ የሊዝ ክፍያው ለባለመብቱ ተመላሽ ይሆናል፡፡

፪. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ለ) መሠረት ሲቋረጥ ባለይዞታው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

፫. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በአዋጁ አንቀጽ ፭፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሐ) መሠረት ሲቋረጥ ባለይዞታው እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በቦታው ላይ ያሰፈረውን ንብረት የማንሳት መብቱን በመጠቀም ንብረቱን በማንሳት ቦታውን አግባብ ላለው አካል መልሶ ማስረከብ አለበት፡፡

፬. ባለይዞታው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በተሰጠዉ መብት ተጠቅሞ ንብረቱን ካላነሳ አግባብ ያለው አካል ለንብረቱ ክፍያ ሳይፈጽም ቦታውን ሊወስደው ይችላል፡፡ ለአፈፃፀሙም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፖሊስን ማዘዝ ይችላል፡፡

፵፰.<u>አቤቱታ ማቅረብና ውጤቱ</u>

የከተማን ቦታን ከማስለቀቂያ ጋር ተያይዘው የሚቀርብ አቤቱታዎች እና በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞች በተመለከተ በአዋጁ ፭፰ ፣፭፱ እና ፷ መሰረት የሚፈጸም ሆኖ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፵፱.<u>የከተማ ቦታ የማስለቀቅ ትእዛዝ አሰጣጥ</u>

፩. ይህንን ተግባር ለመፈጸም አግባብ ያለው አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ለባለይዞታው ይሰጣል፤ሆኖም ጊዜው ከ፺ ቀን ማነስ የለበትም፡፡ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የሚሰጠው ትእዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ አግባብ ላለው ባለይዞታ እንዲደርሰው ይደረጋል፡-

ሀ. በአድራሻው በጽሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፤

ለ. በአድራሻው ያልተገኘ ከሆነ በሚለቀቀው ይዞታ ላይ እንዲሁም አግባብ ባለው አካል የማስታወቂያ ሰሌዳ እና ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ላይ እንዲለጠፍ ይደረጋል፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ (ለ) መሰረት የተለጠፈ ማስጠንቀቂያ ለባለይዞታው እንደደረሰው ይቆጠራል፡፡

፫. በትእዛዝ የሚለቀቀው ይዞታ የመንግስት ንብረት የሰፈረበት ከሆነ የማስለቀቂያ ትእዛዙ የሚደርሰው ንብረቶቹን ለሚያስተዳድረው መንግስታዊ ተቋም ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የተላለፈበት ንብረት የተከራየ ከሆነ ትዕዛዙ የደረሰው አካል የማስጠንቀቂያ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

፭. የከተማ ቦታ ከማስለቀቅ ጋር ተያይዞ መከናወን የሚገባቸው ጉዳዮች በአዋጁ አንቀጽ ፭፮ እና ፭፰ መሰረት የሚፈጸም ሆኖ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡

## <u>ክፍል አስራ አንድ</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## ፶.ከዚህ በፊት ስለተሰጡት ዉሳኔዎችና የሊዝ ውሎች

፩. ከዚህ በፊት በነበሩት የሊዝ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት የተሰጡት ዉሳኔዎችና የተፈረሙት የሊዝ ዉሎች ተፈጻሚነታቸዉ ይቀጥላል፡፡

፪.ከዚህ በፊት በነበረዉ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ በተሰጡት ዉሳኔዎች እና በተገቡት ዉሎች ላይ የሚነሱት ቅሬታዎችና አቤቱታዎች የሚታዩት እንደጥያቄዎቹ ይዘት አግባብ ባለዉ አካል ወይም በካቢኔ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫.አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከ ፶ ከመቶ በታች ግንባታ ያረፈበት የሊዝ ይዞታ የተላለፈላቸው መሆኑ በሚመለከተው አካል የታወቀ /የተመዘገበ/ ገቢ ለመሆኑ ማህተም ያረፈበት ሰነድ ኖሮአቸው የስም/የባለይዞታነት ዝውውር ያላጠናቀቁ ባለይዞታዎች ዝውውርን በነባሩ ህግ መመሪያ መሰረት ይህ ደንብ ከፀናበት በ ፩ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ዝውውሩን ያላጠናቀቁ ሰዎች የአዋጁ እና የዚህ ደንብ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆንባቸዋል፡፡

## ፶፩.ከዚህ በፊት በሊዝ ተይዘው ግንባታ ያላጠናቀቁትን በተመለከተ

፩.ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የግል መኖሪያ ቤት ቦታ በሊዝ አግባብ ወስደው ሰርቪስ ቤት በመስራት የሚኖሩ የዋናውን ቤት ግንባታ ባያጠናቅቁም ሊገለገሉበት ይችላሉ ፡፡ ነገር ግን ከውርስ በስተቀር ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ከፈለጉ የዋናውን ቤት ግንባታ እንዲያጠናቅቁ ወይንም በዚህ ደንብ አግባብ፶ በመቶ ግንባታ ሳይጠናቀቅ በሚከናወን ዝውውር አግባብ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩ ከተጠቀሰው ውጭ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት በሊዝ አግባብ ቦታ ወስደው ግንባታ ጀምረው ያላጠናቀቁ ይዞታዎች እንደ ግንባታቸው ደረጃ ከሁለት እስከ አራት አመት የሚደርስ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይችላል ፡፡ ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ ፶ በመቶ ግንባታው ሳይጠናቀቅ  ከውርስ በስተቀር ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ከፈለጉ በዚህ ደንብ አግባብ ፶ በመቶ ግንባታ ሳይጠናቀቅ በሚከናወን ዝውውር አግባብ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፶፪. መመሪያ የማዉጣት ስልጣን

የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፶፫. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚደረግ ማናቸውም እንቅስቃሴ ትብብር እንዲያደርግ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፶፬.የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

፩. የከተማው አስተዳደር የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝን እደገና ለመደንገግ የወጣውን ደንብ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፪ ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያና አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፶፭.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደር ካቢኔ ከፀደቀበት ከግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ ሺ፬ዓ.ም
ኩማ ደመቅሳ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ

## የክልል 14 መስተዳድር የከተማ ቦታ በኪራይባለይዞታነት እና የኪራይ ተመንን ለመወሰን የወጣደንብ አጭር መግለጫ

አጭር መግለጫ

የሊዝ ፖሊሲ የመሬትን የመጠቀም መብት የገበያ ዋጋ እንዲኖረው የሚያደርግ ቢሆንም የሊዙን ደንብ በነባር ይዞታዎች ከሙሉ ላይ በአንድ ወቅት ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል ሆኖ በመገኘቱ ነባር ይዞታዎች እንደምር ጫቸው ደንብ እንዲተዳደሩ ለማድረግ የወጣ ህግ ነው፡፡

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. ነባር የከተማ ቦታ ይዞታ

፬. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

፭. የቦታ ደረጃ

፮. ስለኪራይ ክፍያና አከፋፈል

፯. የኪራይ ይዞታ መቋረጥ

፱. ስለ ካሣ አከፋፈል

፩0. ከኪራይ ይዞታ ወደ ሊዝ ይዞታ ስለመተላለፍ

፩፩. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩፪. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

፩፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

## የክልል 14 መስተዳድር የከተማ ቦታ በኪራይ ባለ ይዞታነት እና የኪራይ ተመንን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የሽግግሩን ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲና ተዛማጅ ሕጐችን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ስለከተማ ቦታ በሊዝ ባለይዞታነት አዋጅ ያወጣ በመሆኑና ዝርዝር የአፈፃፀም ደንብ የማ ውጣት ሥልጣን ለብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች የሰጠ ስለሆነ፣

የሊዝ ፖሊሲ የመሬትን የመጠቀም መብት የገበያ ዋጋ እንዲኖረው የሚያደርግ ቢሆንም የሊዙን ደንብ በነባር ይዞታዎች ከሙሉ ላይ በአንድ ወቅት ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል ሆኖ በመገኘቱ ነባር ይዞታዎች እንደ ምርጫቸው ደንብ እንዲተዳደሩ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፡-

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ ‹‹የከተማ ቦታን በኪራይ ስለመያዝና የኪራይ ተመንን ለመወሰን የወጣ ደንብ › ተብሎ ሊጠቀስ ይችላ ል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

1‹‹አዋጅ›› ማለት የከተማ ቦታ በሊዝ ባለይዞታነት አዋጅ . ነው፡፡

2‹‹የክልል መስተዳድር››ማለት በአዋጅ መሠረት የተቋቋመ የክልል 14 መስተዳድር ነው፡፡

3. ‹‹ሚኒስቴር›› ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡

4. ‹‹ቢሮ›› ማለት የክልል 14 መስተዳድር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ነው፡፡

5.‹‹ከተማ›› ማለት አዲስ አበባ ተብሎ የሚታወቀው የክልል 14 መስተዳድር ክልል ነው፡፡

6.‹‹የከተማ ቦታ›› ማለት የገበሬ ማኅበራት የተቋቋመባቸውን ክልል ሳይጨምር በክልል መስተዳድሩ የሚገኝ ማናቸውም ቦታ ነው፡፡

7.‹‹የንግድ ሥራ›› ማለት የልውውጥ፣ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ሥራ ነው

8.‹‹ነባር ይዞታ›› ማለት አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ይሠራባቸው በነበሩ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሕጋዊ መንገድ የተያዙና በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን ይጨምራል፡

9. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

10.. ‹‹ግንባታ›› ማለት ቤት ወይም ሕንፃ ማለት ነው፡፡

11.‹‹የግል መኖሪያ ቤት ይዞታ›› ማለት በግል ወይም በማኅበር የተሠራና ለባለቤቱ ለመኖሪያነት የሚ ያገለግል የቤት ይዞታ ነው፡፡

12.‹‹የቦታ ደረጃ›› ማለት በአዲስ አበባ መሪ ፕላን አዋጅ መሠረት በልማትና በጠቀሜታቸው ዋጋ መ ሠረት ለቦታው የተሰጠ ደረጃ ነው፡፡

13. ‹‹ጸሎት ቤቶች›› ማለት ለሕዝብ ለጸሎት ማድረስ ብቻ የሚውሉ ይዞታዎች ናቸው፡፡

14.‹‹የሕዝብ ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት›› ማለት ዓላማቸው ለትርፍ ሳይሆን አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ የሕዝብ ንብረት የሆኑ ተቋማት ናቸው፡፡

### 3. ነባር የከተማ ቦታ ይዞታ

በነባር የሚታወቅ የከተማ ቦታ ይዞታ ለአዋጁ አፈጻጸም የሚከተሉትን ይዞታዎች ያጠቃልላል፡፡

1. አዋጅ ከመውጣቱ በፊት
   ሀ) ካርታ ያላቸውና ያልተወረሱ ይዞታዎች
   ለ) በጭሰኝነት የተያዙ በመሆናቸው በአዋጅ ሕጋዊ የሆነ ይዞታዎች፣
   ሐ) ለረዥም ጊዜ በቦታው ላይ ቤት ሠርተው ሲኖሩ በሕጋዊ መንገድ ባለቤት የሆኑበት መሆኑን ማስረጃ ሊቀርብበት የሚችል ይዞታ
2. ከአዋጅ  በኂላ ቦታ ተመርተው ከማዘጋጃ ቤት ካርታ የተሰጣቸው፡፡
3. በሚኒስቴሩ የባለቤትነት ደብተር የተሰጣቸው ቤቶች የተሠሩባቸውና
   ሀ/ ቦታው የግላቸው ስለነበረ፣
   ለ/ ቦታውን በጭሰኝነት ይዘው  ባለይዞታ ስላደረጋቸው
   ሐ) በተለያየ ምክንያት የግላቸው በነበረ ቦታ ላይ የሠሩት ቤት ተወስዶባቸው በልዋጭ ቤት በባለቤትነት ተሰጥቷቸው ደብተር ስለያዙ፡፡

   የይዞታ ምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ይዞታዎች
4. ከአዋጅ በፊት በባለቤትነት በያዙት ቦታ ላይ ያሠፈሩት ንብረት እንዲመዘገብላቸው በሚኒስቴሩ የተ ወሰነላቸው
5. በሚኒስቴሩ ፈቃድ ተከልለው የራስ አገዝ ቤት የተሠራባቸው፣
6. በሽያጭ በውርስ ወይም በስጦታ የይዞታ ባለመብት የሆኑና የስም ዝውውር ተከናውኖ በአዲስ አበባ ና በአቃቂ ማዘጋጃ ቤት እንዲሁም በሸዋ ከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃ የተሰጣቸው፣
7. በቀበሌ ማኅበራት በምሪት ተሰጥተው የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሕጋዊ ይዞታ መሆናቸውን አውቆ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው የተወሰነላቸው

### 4. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

1. በሊዝ ደንብ መሠረት የሊዝ ውል ያልፈረሙ የንግድ ሥራ የሚካሄድባቸው ነባር ይዞታዎች
2. የሊዝ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ለግል መኖሪያ ቤት የተያዘ የቦታ ይዞታ፣
3. ለመኖሪያነት የተከራየ ቤት ነባር ይዞታ፡፡

### 5. የቦታ ደረጃ

1. በአዲስ አበባ መሪ ፕላን መሠረት የልማትና የጠቀሜታ ዋጋቸውን መሠረት በማድረግ የከተማ ቦታዎች
:

ሀ/ በአምስት ዞኖች

ለ/ እያንዳንዱን ዞን በሦስት የቦታ ደረጃዎች ተመድቧል፡፡

2. በዚህ ደንብ መሠረት በኪራይ ለተያዘ የከተማ ቦታ የሚከፈለው የኪራይ ተመን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን የቦታ ደረጃ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

6. ስለኪራይ ክፍያና አከፋፈል

1. ማናቸውም የከተማ ቦታን ለንግድ በኪራይ የያዘ ሰው ከዚህ በታች የተመለከተውን የኪራይ ተመን በካሬ ሜትር በዓመት ይከፍላል፣

| ዞን | ንዑስ ዞን | የንግድ ሥራ | |
|---|---|---|---|
| | | ንግድ | ኢንዱስትሪ |
| | 1 | 4.00 | 2.00 |
| 1 | 2 | 2.66 | 1.33 |
| | 3 | 1.33 | 0.66 |
| | 1 | 3.50 | 1.75 |
| 2 | 2 | 2.33 | 1.17 |
| | 3 | 1.16 | 0.58 |
| | 1 | 3.00 | 1.50 |
| 3 | 2 | 2.00 | 1.00 |
| | 3 | 1.00 | 0.50 |
| | 1 | 2.80 | 1.40 |
| 4 | 2 | 1.85 | 0.93 |
| | 3 | 0.80 | 0.40 |

2. ከ73 ካሬ ሜትር በታች የተያዙ ነባር የግል መኖሪያ ቤት ይዞታዎች ከክፍያ ነፃ ናቸው፡፡

3. ከ75 ካሬ ሜትር በላይ የተያዙ ነባር የግል መኖሪያ ቤት ባለይዞታዎች ከዚህ በታች የተመለከተውን ይከፍላሉ፡፡

| ስፋት ካሬ ሜትር | ዞን 1 ብር/ካ.ሜ | ዞን2 ብር/ካ.ሜ | ዞን 3 ብር/ካ.ሜ | ዞን 4 ብር/ካ.ሜ |
|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 73 እስከ | 175.00 | 0.15 | 0.13 | 0.11 | 0.09 |
| እስከ | 275 | 0.17 | 0.15 | 0.12 | 0.10 |
| እስከ | 375 | 0.19 | 0.16 | 0.14 | 0.11 |
| እስከ | 475 | 0.21 | 0.18 | 0.16 | 0.13 |
| እስከ | 575 | 0.24 | 0.21 | 0.17 | 0.14 |
| እስከ | 675 | 0.31 | 0.26 | 0.22 | 0.18 |
| እስከ | 775 | 0.37 | 0.32 | 0.27 | 0.22 |
| እስከ | 875 | 0.43 | 0.37 | 0.32 | 0.26 |
| እስከ | 1000.00 | 0.50 | 0.43 | 0.37 | 0.30 |
| እስከ | 1100.00 | 0.64 | 0.55 | 0.47 | 0.38 |
| እስከ | 1200.00 | 0.79 | 0.69 | 0.58 | 0.48 |
| እስከ | 1300.00 | 0.96 | 0.83 | 0.71 | 0.58 |
| እስከ | 1400.00 | 1.14 | 0.99 | 0.84 | 0.69 |
| እስከ | 1500.00 | 1.33 | 1.16 | 0.98 | 0.80 |
| እስከ | 1600.00 | 1.53 | 1.33 | 1.12 | 0.92 |
| እስከ | 1700.00 | 1.74 | 1.50 | 1.27 | 1.04 |
| እስከ | 1800.00 | 1.95 | 1.69 | 1.43 | 1.17 |
| እስከ | 1900.00 | 2.16 | 1.87 | 1.58 | 1.30 |
| እስከ | 2000.00 | 2.38 | 2.06 | 1.74 | 1.43 |

4. አንድ የግል መኖሪያ ቤት የቦታ ይዞታ ብቻ ያላቸው ቤታቸውን በጊዜያዊነት ለመኖሪያነት ቢያከራዩ የኪራይ ክፍያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው ይሆናል፡፡
5. ለመኖሪያ ቤትና ሕጋዊ ፈቃድ ላለው የንግድ ሥራ ለዋለው ምድርና ፎቅ ሕንፃ የሰፈረበት ነባር ይዞታ ለ ንግድ ሥራ የተመደበውን ይከፈልበታል፡፡
6. በነባር የቦታ ይዞታ ላይ የሠፈረ ግንባታ ጣራና ግድግዳው ተያይዞ ወደ ጐን በመደዳ የተሠራና የተወሰነው ለንግድ ሥራ የዋለ የተወሰነው ደግሞ ለመኖሪያነት የሚያገለግል ሲሆን እንዲሁም በአንድ ግቢ ውስጥ ተነጣጥሎ ለንግድና ለመኖሪያነት የሚያገለግል ግንባታ ሲኖር ለንግድ ሥራ የተተመነውን የኪራይ ተመን ይከፈልበታል፡፡
7. ጸሎት ቤቶችና የሕዝብ ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ከኪራይ ክፍያ ነፃ ናቸው፡፡

<u>7. ስለአጠቃቀም ለውጥ</u>

1. አግባብ ያለው አካል ከመሪ ፕላኑ ጋር በማገናዘብ በጽሑፍ ሲፈቅድ ባለይዞታው ቦታው መጀመሪያ ይሰጥ የነበረውን አጠቃቀም ሊቀይር ይችላል፡፡

2. የአጠቃቀም ለውጥ ሲፈቀድ የኪራይ ዋጋው ለተለወጠው ተግባር የተወሰነው ይሆናል፡፡

**8. የኪራይ ይዞታ መቋረጥ**

የከተማ ቦታ ይዞታ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡፡

1. ቦታው ለሕዝብ አገልግሎት የሚፈልግ ከሆነ
2. በከተማው ማስተር ፕላን መሠረት መሬቱን ጥቅም ላይ ማዋል ካስፈለገ፡፡

9. ስለ ካሣ አከፋፈል

በኪራይ የተያዘ ቦታ ለሕዝብ አገልግሎት የሚፈለግ ወይም በከተማው መሪ ፕላን መሠረት መሬቱን ጥቅም ላይ ማዋል ካስፈለገ ተከፋይ የሚሆነው የካሣ መጠን ባለይዞታው ላሰፈረው ንብረት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ነው፡፡

**10. ከኪራይ ይዞታ ወደ ሊዝ ይዞታ ስለመተላለፍ**

1. በዚህ ደንብ መሠረት በኪራይ የተያዘን የከተማ ቦታ በሊዝ ይዞታ ደንብ መሠረት እንዲተዳደር ለማዛወር ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለመፈጸም ቢሮው በጽሁፍ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ዝውውሩ ሲፈጸም ያለጨረታ በቀጥታ ይሆናል፡፡
4. ዝውውሩ ሲፈጸም የሊዝ ተመኑ በአካባቢው የወቅቱ ጨረታ ባስገኘው አማካይ የሊዝ ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

**11. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ይህን ደንብ ለማስፈጸም ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

**12. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጐች**

1. በአዲስ አበባ የከተማ ቦታ ኪራይና የከተማ ቤት ግብር ደንብ ላይ ስለ ከተማ ቦታ ኪራይ የተመለከቱት አንቀጾች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡
2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**13. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህን ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የክልል 14 ምክር ቤት

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሪል እስቴት ቦታ አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺፰ ዓ.ም አጭር መግለጫ

በሪል እስቴቱ አሰጣጥ እስካሁን በተደረገው እንቅስቃሴ በዘርፉ በርካታ አልሚዎች በመግባታቸው ማበረታቻ መቀጠሉ አስፈላጊ ባለመሆኑእናለሪል እስቴት ከተከለለው ውጭ በሚሰጥበት አጋጣሚ በዋጋ ረገድ ችግር በመፍጠሩ ከተከለለው ውጪ በሚሰጥበት አጋጣሚ በአካባቢው ከፍተና የጨረታ ዋጋ ለመስጠት የወጣ ህግ ነው፡፡

፩. አጭር ርዕስ

፪.ትርጉም

፫. ሪል እስቴት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

፬. የቦታ ስፋት

፭. ቦ ታ ዋጋ

፮. ከማስፋፊያና ለሪል እስቴት ከተከለለው ቦታ ውጭ የሊዝ ዋጋ

፯. ስለቦታ አሰጣጥ

፰. ማስፋፊያ

፱ መንገድ ቦታ

፲. አስፈፃሚ ዴስክ ስለማቋቋም

፲፩. መመሪያ ስለማውጣት

፲፪. ደንብ የሚፀናበት ጊዜ

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሪል እስቴት ቦታ አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺፰ ዓ.ም</u>

በሪል እስቴቱ አሰጣጥ እስካሁን በተደረገው እንቅስቃሴ በዘርፉ በርካታ አልሚዎች በመግባታቸው ማበረታቻ መቀጠሉ አስፈላጊ ባለመሆኑ፣

ለሪል እስቴት ከተከለለው ውጭ በሚሰጥበት አጋጣሚ በዋጋ ረገድ ችግር በመፍጠሩ ከተከለለው ውጪ በሚሰጥበት አጋጣሚ በአካባቢው ከፍተኛየጨረታ ዋጋ መስጠቱት አግባብ በመሆኑ፣

ለፕሮጀክቱ ከሚፈቀደው መሬት በኮንዶሚኒየም ፸ ፐርሰንት እና ቪላ ፴ ፐርሰንት መመዘኛ የሚያሟሉ በድርድር ዋጋ የሚሰጥሲሆን ከዚሁ በታች ወይምሙሉ በሙሉ ቪላ ለሚገነቡ ግን በአካባቢው ከፍተኛ የጨረታ አማካይ ዋጋ መውሰድ እንዳለባቸው በደንቡ ማካተቱ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአረንጓዴ አካባቢ ደረጃ መቶኛ መውጣት እንዳለበት በመታመኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፬/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፷፮ (፪) እና ፲፬/፪/ለ እንዲሁም የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝን እንደገና ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፪/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፲፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡
፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሪል እስቴት ቦታ አሰታጥ ለመደንገግ የወጣ ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺፰ ዓ.ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.<u>ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. አስተዳደር ማለት  የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. ባለስልጣን ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ባለስልጣን ነው፡፡

፫.“መኖሪያ ህንፃ ማለት የተሰራው ሕንፃ ፸% በላይ ከንግድ   እና ምርት አገልግሎት ውጪ ለመኖሪያነት ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ነው፡፤

፬.“የሊዝ መደራደሪያ ዋጋ ማለት የመነሻና የገበያ ዋጋን መሰረት አድርጎ የሚወስን የመሬት ዋጋ ማለት ነው፤

፭. ሪል እስቴት አልሚ ማለት ፶ ቤትና ከዚያ በላይ የሚገነባ ነው፡፡

፮.“ቪላ ማለት በሪል እስቴት አልሚ በጋራ ሳይሆን በግል ገቢ ውስጥ የሚሰራ ቤት ነው፡፡

፯..“ኮንዶሚኒየም ማለት በጋራ ሕንፃ ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸/፲፱፻፺፭ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

## ፫. ሪል እስቴት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው

፩. ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፡፡

፪. የመኖሪያ ቤት ችግርን መቅረፍ፡፡

፫. ቦታን በቁጠባ እና በፕላን መጠቀም፡፡

## ፬. የቦታ ስፋት

ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የቪላ ቤት እና የኮንዶሚኒየም ግንባታ የሚያርፍበት የቦታ ምጣኔ ፴ ፐርሰንት ለቪላ ፸ ፐርሰንት ለጋራ ቤት ይሆናል፡፡

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንዶሚኒየም ያንዱ ቤት ድርሻ የጋራ መገልገያውን ጨምሮ ከ፻ ካሬ ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡

## ፭. ቦ ታ ዋጋ

ቁጠባዊ የቦታ  አጠቃቀምን ለማበረታታት በማስፋፋት እና     ለሪል እስቴት በተከለለ አካባቢ፸ ፐርሰንት እና ፐርሰንት የኮንዶሚኒየም እና ቪላ ምጣኔ መሰረት የሚሰጥ ቦታ ዋጋ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ. ከ፪፻፶--፫፻ ሜትር ካሬ የአካባቢው የመንደራደሪያ ዋጋ ይሆናል፡፡

ለ. ከ፪፻፶እስከ፫፻ ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) ከተደነገገው ዋጋ በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መንደራደሪያ ዋጋ በ፲ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

ሐ. ከ፫፻፩-

፩ሺ. ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ለ) ከተደነገገው ዋጋ በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መንደራደሪያ ዋጋ በ፲ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

መ ከ፩ሺ.፩፻፩እስከ፩ሺ.፫፻ ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሐ) ከተደነገገው ዋጋ በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መንደርደሪያ ዋጋ በ፳ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

ሠ) ከ፩ሺ.፫፻፩እስከ፪ሺ.፫፻ ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (መ) በተደነገገው በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መንደርደሪ ዋጋ ፴ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

፮. የሪል ስቴት በፐርሰንት ይሆናል፡፡

፯. የማስፋፊያ አካባቢ የሪል እስቴት የሊዝ ዋጋ በድርድር ዋጋ ይሆናል፡፡

፰. የማበረታቻ ቀሪ መሆን

ሀ. ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው ፶ ካ.ሜ ከሊዝ ክፍያ ነፃ የመሆን መብት ቀሪ ይሆናል፡፡

ለ. ለሪል እስቴት ከተከለለው ውጪ የሚሰጡ ቦወታዎች በጨረታ መንገድ የሚስነታገድ ይሆናል፡፡

## ፱. ከማስፋፊያና ለሪል እስቴት ከተከለለው ቦታ ውጭ  የሊዝ ዋጋ

፩. ከማስፋፊያ እና ለሪል እስቴት ከተከለከለ አካባቢ ውጭ ያለ የሪል እስቴት ቦታ የሊዝ ዋጋ በጨረታ ከፍተኛ ዋጋ ይሆናል፡፡

ሀ) እስከ ፪፻፶ሜትር ካሬ የአካባቢው የመደራደሪያ ዋጋ ይሆናል፡፡

ለ) ከ፪፻፶፭፻ ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) ከተደነገገው ዋጋ ተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መደራደሪያ ዋጋ በ፩.፭ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

ሐ) ከ፭፻፩--

፩ ሺ. ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ለ) ከተደነገው ዋጋ በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መደራደሪያ ዋጋ በ፫ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

መ) ከ፩ሺ.፩፩ሺ.፭፻ ሜትር ካሬ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሐ) ከተደነገገው ዋጋ በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መደራደሪያ ዋጋ በ፬ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

ሠ) ከ፩ሺ.ህ፭፻፩፪ሺ.፭፻ ሜትር ካሬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (መ) ከተደነገገው በተጨማሪ ለልዩነት የስፋት መጠን የሊዝ መደራደሪያ ዋጋ በ፭ ተባዝቶ የሚደመር ይሆናል፡፡

**፯. ስለቦታ አሰጣጥ**

፩. አልሚው ለመጀመሪያ ጊዜ ቦታ በሊዝ ለመውሰድ ሲጠይቅ የሚሰጠው የመሬት ስፋት መጠን እስከ ፳፭ሺ. ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

፪. አልሚው በድጋሚ ቦታ በሊዝ ለመውሰድ ሲጠይቅ የሚሰጠው የመሬት ስፋት መጠን ፳፭ሺ. ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

**፰. ማስፋፊያ**

አለሚው በእጁ ከሚገኘው ቦታ ተጨማሪ ማስፋፊያ ሲጠይቅ የነባሩ ፕሮጀክት ፸፭ ፐርሰንት ስለመጠናቀቁ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**፱ መንገድ ቦታ**

ለሪል ስቴት የሚሰጡ ቦታዎች ላይ ለአረንጓዴ ሥፍራና መንገድ የሚሰጥ የቦታው መጠን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲. አስፈፃሚ ዴስክ ስለማቋቋም**

እድሩ ወይም በመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ከሚወጣው መሰረት የሪል እስቴት አስፈፃሚ ዴስክ ይቋቋማል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲፩. መመሪያ ስለማውጣት**

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም አስተዳደሩ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**፲፪. ደንብ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሕዳር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

# <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገወጥ የመሬት ይዞታ መስፋፋትና ህጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታ ለመከላከል የወጣ ደንብ ፲፩/፲፱፻፻፺፮</u>

ሕገወጥ የመሬት የይዞታ መስፋፋትና ሕጋዊ ባልሆነ የመሬት ይዞታ ግንባታ ማከናወን ከተማን በዕቅድና በሥርዓት ለማሳደግ የሚደረግ ጥረትን የሚያደናቅፍና ጤናማ የከተማ ሕይወትን የሚያደክም በመሆኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ ሕገወጥ የይዞታ ማስፋፋት ከሚያከናውኑና ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የግንባታ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰቦች የአብዛኞቹ መነሻ የመጠለያ ችግር ሳይሆን የሕዝብ ሀብት በሆነው የከተማ መሬት ያለአግባብ መበልጸግ በመሆኑና ይህም በሕግ መገታት ያለበት ሆኖ በመሆኑ፡፡ የከተማው አስተዳደር እስከ አሁን ድረስ ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታን የሚከላከልበት ጠንካራ ሕግ ስላልነበረው ይህንን የሕግ ክፍተቱን በመሙላት ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ የመከላከል ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጡ ዘንድ፣ የሕግ መሰረት እንዲኖራቸው ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እስከ አሁን በሕገወጥ ይዞታ ላይ የተሰሩ ግንባታዎች ላይ አስተማሪ እርምህጃ መውሰድ ለመከላከሉተግባር አንድ ወሳኝ መነሻ መሆኑ ስለታመነበት፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፷፫ (፩) (ረ) እና ፷፮ (፪) መሠረት እንዲሁም በመሪ ፕላን አዘገጃጀት አወጣጥና አፈፃፀም አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፮ ዓ.ም አንቀጽ ፷፱ (፪) (ሀ) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገወጥ የይዞታ መስፋፋትንና ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታን ለመከላከል የወጣ ደንብ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. "የከተማ ክልል" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ነው፣

፪. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ሕገወጥ የይዞታ መስፋፋት" ማለት በሕጋዊ መንገድ የከተማው አስተዳደር ቦታን በይዞታነት እንዲያስተላልፍ ሥልጣን ከተሰጠው አካል በተገነ ይዞታ በተጨማሪነት ከጎን ያለን ቦታ መከለልላ መያዝ ማለት ነው፡፡

፬. “ሕጋዊ ያልሆነ ይዞታ” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ክልል የከተማ ቦታ ለተለያዩ አገልግሎት እንዲመደብ በሕግ ኃላፊነት ከተሰጠው አካል እውቅና ውጭ የተገዛና በእጅ መናኛ የተያዘ ቦታ ነው፣

፭. “በሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተደረገ ግንባታ” ማለት ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ በተጠቀሰው በተስፋፋ ሕገወጥ ይዞ ወይም ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተካሄደ ግንባታ ነው፤

፮. “መሪ ፕላን” ማለት የተከለሰውና በከተማው አስተዳደር የጸደቀው የአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን ነው፤

፯. “ባለስልጣን” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ነው፤

፰ “ድርጅት” ማለት ከመኖሪያ ውጭ ለማምረቻ ለማከማቻ፣ ለኢንዱስትር፣ ለምግድና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የዋለ ቦታና ሕንፃ ነው፤

፱. “የማስተካከያ እርምጃ” ማለት ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ ከተካሄዱ ግንባታዎች መካከል ከከተማው መዋቅራዊ ፕላን የመሬት አጠቃቀም ጋር የማይጋጩትን ለይቶ በዚህ ደንብ መሠረት ሕጋዊ እውቅና የመስጠትና የሚጋጩትን የማፍረስ እርምጃ ነው፤

፲. “የመከላከል እርምጃ” ማለት ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታ መንሥኤዎችን ማስወገድ፣ ግንባታዎችን ከጅመሩ ማስቆምና ማፍረስ፣ ገንቢዎችንም ወደ ሕግ ማቅረብ እና ማንኛውንም ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ መከላከል ነው፤

፲፩. “የደንብ ማስከበር አገልግሎት” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር አገልግሎት ነው፣

፲፪. “ሰው” ማለት ማንኛውም በተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

፲፫. “የሊዝ ገበያ ዋጋ” ማለት ባለስልጣኑ በየስድስት ወሩ በሊዝ መነሻ ዋጋና መካከል ባለው ልዩነት ላይ ተመስርቶ የሚያወጣው የዋጋ ማስተካከያ ምጣኔ በአካባቢው የሊዝ መነሻ ዋጋ ተባዝቶ የሚገኘው ውጤት ነው፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩. በዚህ ደንብ የተጠቀሰው የማስተካከያ እርምጃ በመመሪያ ቁጥር ፩ ከሚስተናገዱ ውጭ በ፲፱፻፺፰ እና በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም በተነሱት የአየር ፎቶዎች በሚታየው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሕገወጥ በተስፋፋና በተያዙ ይዞታዎች እንዲሁም በነዚህ ላይ በተገነቡ ግንባታዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

፪. ከ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ወዲህ በሕገ ወጥ መንገድ ተስፋፋ ወይም የተያዘ ይዞታ መስፋፋቱ በኪራይ ከተያዘ የመንግሥት ቤት ጋር የተያያዘ እስካልሆነና ግንባታው በፕላን ተቀባይነት እስካለው ድረስ በዚህ ደንብ መሰረት ይስተናገዳል፡፡

፫. የመከላከሉ እርምጃ ድንጋጌዎች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ ባለ ቦታ ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተደረጉ ግንባታዎችን በመለየት የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች እና የይዞታ ማረጋገጫ ስለመስጠት

፩. ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ ተደረጉ ግንባታዎችን መለየት

፩. በዚህ ደንብ ሕጋዊ መሬት ባለይዞታ ሆኖ የሚቆጠረው አግባብ ባለው ባለስልጣን የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሚቀርብ ማስረጃ በማንኛውም አካል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፪. በሕገወጥ የተስፋፋና ሕጋዊ ያልሆነ ይዞ የከለሉ እንዲሁም በነዚህ ይዞታዎች ግንባታዎች ያካሄዱ ሰዎች ዝርዝር በ፲፱፻፹፰ እና በ፰፱፻፺፩ ዓ.ም በተነሱት የአየር ካርታዎች ላይ በመመስረት እንዲለዩ ይደረጋል፡፡

፫. በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም በተነሳው የአየር ካርታ ላይ የማይታዩ በሕገወጥ በተስፋፋና ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተደረጉ ግንባታዎች ያለምንም ተጨማሪ የማስተካከያ እርምጃ የሚፈርሱ ይሆናሉ ቦታዎቹ ግንባታ የሌለባቸው ከሆነው እንዲለቀቁ ይደረጋል፡፡

፬. ሕገወጥ ማስፋፋቱ፣ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዙት ይዞታዎች እንዲሁም በነዚህ ላይ የተደረጉት ግንባታዎች ያለባቸው አካባቢዎች የመንገዶች አውታር፣ የማህበራዊ ተቋማትን ሥርጭት፣ የመናፈሻና አረንጓዴ ሥፍራ ክልሎችን፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችን የመሬት አጠቃቀም ሽንሻኖ ለይቶ የሚያሳይ የአካባቢ ልማት ፕላን በቅድሚያ መዘጋጀት አለበት፡፡

፭. በሚዘጋጀው የአካባቢ ልማት ፕላን መሠረት ለመንገዶች አውታር፣ ለማህበራዊ ተቋማትና ለአረንጓዴ ሥፍራዎች አገልግሎት እንዲውሉ በተከለሉ ቦታዎች ላይ ያሉ በሕገ ወጥነት የተያዙና የተከለሉ ይዞታዎች ግንባታቸው የሚያርፍባቸው ሰዎች ማንነት በዝርዝር መለየት አለበት፡፡

፭. <u>የማስተካከያ እርምጃዎች</u>

፩. ዝርዝር ፕላኑ ለሚቀበለው ይዞታ ብቻ ሕጋዊ እውቅና ይሰጣል፡፡ ፕላኑ የማይቀበላቸው ግን የሚፈርሱ ይሆናል፡፡

፪. ሕጋዊ ባልሆነ መስፋፋት የተያዘ ወይም የተከለለ ቦታ ወይም በነዚህ ይታዎች ላይ ግንባታ የተካሄደበትን ቦታ መቁረጥ ከተቻለ ካለበት ቦታ ተቀንሶ ይወሰዳል፤ ተራፊው ቦታ ከሌላ አገልግሎት መዋል የማይቻል ከሆነ ግን እንደ ስፋቱ ቅጣት በማስከፈል ለባለይዞታው ተራፊውን ቦታ ጨምሮ መስጠት ይቻላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተጠቀሰው አግባብ የማይቆረጥ ይዞታ ማለት

ሀ) መኖሪያ ከሆነ የሚቆረጠውም ቦታ፣

፩. ስፋቱ ከ፩፻፶ ሜ/ካሬ ያነሰ ከሆነ፣

፪. ስፋቱ ፩፻፶ ሜ/ካሬ በላይ ሆኖ ፬ ሜትር ስፋት መንገድ የሌለው ከሆነ፣

፫. ስፋቱ ከ፩፻፺ ሜ/ካሬ በላይ ሆኖ ፬ ሜትር ስፋት መዳረሻ መንገድ ቢኖረውም በአራት ማዕዘን ሲታይ ለንዱ ከ፺ ሜትር ካሬ በታች የሆነ፣

፬. ስፋቱ ከ፩፻፺ ሜ/ካሬ በላይ ሆኖ ፬ ሜትር ስፋት መዳረሻ መንገድ ያለውና ስፋቱ በሁሉም ጎኑ ከ፺ ሜትር በላይ የሆነ ነገር ግን ግንባታ ኖሮበት ያለው ግንባታ ከመሬቱ ዋጋ ፳% እና በላይ የሆነ፣

፭. ከላይ ተዘረዘሩትን የስፋት፣ መዳረሻና የጎን ስፋት ለብቻው ሲታይ የሚያሟላ ቢሆንም የሚቆረጠው ቦታ የፕሎት ሽንሻኖ ከአጎራባቹ ጋር ሲታይ ለሌላ ግልጋሎት የማይውሉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ለ) ድርጅቱ ከሆነ የሚቆረጠውም ሆነ የሚቀረው ቦታ

፩. ለአካባቢው በተቀመጠው የሕንጻ ከፍታ ዝቅተኛውንም የማያሰራ ከሆነ፣

፪. የቦታው ስፋት በፕላን በተያዘው ሴክተር ልማት ለማካሄድ፤ ዝቅተኛ እስታንዳርድ የማያሟላ ከሆነ፤

፫. ስፋቱ ለቦታው የተቀመተውን ሕንፃ ከፍታና የሴክተር ልማት ለማረጋገጥ ቢችልም ፯ ሜትር ስፋት መዳረሻ መንገድ የሌለው ከሆነ፤

፬. ስፋቱ በቂና መዳረሻ መንገድ ፯ ሜትር ካሬ በላይ ቢሆንም ቦታው በአራት ማዕዘን ሲታይ አንዱ ከ፺ ሜትር ካሬ በታች ከሆነ፤

፭. ስፋቱ በቂ ቢሆንና መዳረሻ መንገድ ፯ ሜትር በላይ ስፋት ያለው የመዳረሻ መንገድ ቢኖረውም ቦታው በአራት ማዕዘን ሲታይ አንዱ ከ፺ ሜትር በታች ባይሆንም የሚቆጠረው ቦታ ፕሎት ሽንሻኖ ከአጎራባች ጋር ሲታይ ለሌላ ግልጋሎት የማይውል ከሆነ ብቻ፡፡

፯. የማይቆረጠው ድርጅት ይዞታ ስፋት ለመወሰን በቦታው ሊሰራ የሚችለው የሴክተር ልማትና የሕንፃ ከፍታ መሠረት ዝቅተኛውን የቦታ ስፋት የሚጠይቀውን ማሟላት አለበት፡፡

ሐ) ለኢንዱስትሪ

፩. በመኖሪያ አካባቢ ለሚደረግ አነስተኛ የይዞታ ስፋት ከ፩፻፺ እስከ ፭፻ ሜ/ካሬ

፪. መካከለኛና ከፍተኛ (ለኢንዱስትሪ በተከለሉ ቦታዎች) ከ፩ሺ ሜትር ካሬ በታች ከሆነ፣

መ) ለትምህርት ተቋም

፩. አፀደ ሕፃናት ከሺ፭፻ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፣

፪. ፩ኛ ደረጃ ከ፰ሺ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፣

፫. ፪ኛ ደረጃ ከ፰ሺ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፤

ሠ) ለጤና ተቋም

፩. ጤና ኬላ ከ፭፻ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፣

፪. ክሊኒክ ከ፮ሺ፭፻ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፣

፫. ጤና ጣቢያ ከ፪ሺ፭፻ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፣

ረ) ለቢዝነስና ልዩ ልዩ

፩. G+0 — G+፬ ከ፩፻፶ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፤

፪. G+፭ — G+፯ ከ፫፻ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፤

፫. G+፯ — G+፰ ከ፯፻ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ

፬. G+፱ — G+፲ ከ፰፻፩ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፤

፭. G+፲ በላይ ከ፩ ሜ/ካሬ በታች ከሆነ፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ለሌላ አገልግሎት ማዋልና ተራፊ ቦታ ጠቅልሎ ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በሕገወጥነት ያስፋፋ ወይም በሕገ ወጥነት ይዞታ የከለለ እንዲሁም በነዚህ ይዞታዎች ላይ ግንባታ ያካሄደ ሰው ይዞታውን ሙሉ በሙሉ እንዲለቅ ይገደዳል፡፡

፭. ለአንድ ሕጋዊ ያልሆነ ይዞታ መብት አለኝ ብሎ መቅረብ የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡

፯. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለመንገድ፣ ማህበራዊ አገልግሎትና ለአረንጓዴ ሥፍራዎች በተከለሉ ቦታዎች ላይ የሚያርፉ ግንባታዎችን በሚመለከት ለገንቢዎቹ ማስታወቂያ በደረሳቸው በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ግንባታውን እንዲያፈርሱና ቦታውን እንዲለቁ ይደረጋል፡፡

፯. ግንባታው በዝርዝር ፕላኑ መሠረት የሚፈርስባቸው ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ መኖሪያ ቤት ግንባታ ያካሄዱ ሕገወጥ ገንቢዎች በጋራ ሕንጻ ቤት ባለቤትነት ሕግ መሠረት በማህበር ተደራጅተው ሲቀርቡ በመኖሪያ ቤት መምሪያ ቦታ አሰጣጥ መመሪያ መሠረት የመልሶ መስፈሪያ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡

፰. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት ወደ ሌላ አካባቢ የሚዛወሩት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ማፍረስ የሚገባቸውን ግንባታዎች በማፍረስ ቦታውን ለቀው በጋራ ሕንፃ ቤት ባለቤትነት ሕግ መሰረት በማህበር ተደራጅተው የሚቀርቡ ገንቢዎች ብቻ ናቸው፡፡

፯. <u>የማስተካከያ እርምጃ ስለሚኖረው ውጤት</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተለውን ግዴታ እንዲወጡ በማድረግ ይሆናል፡፡

፩. ለመኖሪያ የተያዘ ቦታ በሕገወጥነት በያዙት የቦታ ስፋት መጠን

ሀ) እስከ ፪፻፶ ሜትር ካሬ የቦታ ስፋት ያኸው ፶ ሜ/ካሬ ነፃ ሆኖ ሌላው ሙሉ የአካባቢውን ሊዝ የመደረደሪያ ዋጋና ቅጣት ፲% እንዲከፍሉ ይደረጋል፤

ለ) ከ፩፻፶ እስከ ፭፻ ሜትር ካሬ የቦታ ስፋት ላላቸው ለተጨማሪው ቦታ የሊዝ የመደራድያ ዋጋ ሲበዛ በ፩.፭ እና ቅጣት ፳%

ሐ) ከ፭፻፩ እስከ ፩ሺ ሜትር ካሬ የቦታ ስፋት ላላቸው ለተጨማሪ ፭፻ ሜትር ካሬ የቦታ የሊዝ የመደራደሪያ ዋጋው ሲበዛ በ፪ እና ቅጣት ፴%

መ) ከ፩ሺ.፩ እስከ ፩ሺ.፳፱ ሜትር ካሬ የቦታ ስፋት ላላቸው ለተጨማሪ የቦታ የሊዝ የመደራደሪያ ዋጋ ሲበዛ በ፪ እና ቅጣት ፵%

ሠ. ከሺ.፳፱፩ እስከ ፪ሺ.፳፱ ሜትር ካሬ የቦታ ስፋት ላላቸው ለተጨማሪው ቦታ የሊዝ የመደራደሪያ ዋጋ ሲበዛ በ፫ እና ቅጣት ፶%

ረ. ከ፪ሺ.፳፱፩ ሜትር ካሬ በላይ የቦታ ስፋት ላላቸው ለተጨማሪ ቦታ የሊዝ የመደራደሪያ ዋጋ ሲበዛ በ፬ እና ቅጣት ፷%:: እንዲከፈል ለማድረግ ነው::

፪. <u>የይዞታ ማረጋገጫ ስለመስጠት</u>

፩. ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ ግበንባታ ያካሄደ ሰው ለይዞታ ሕጋዊ እውቅና ለማግኘት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሠረት ከሚፈለግበት ጠቅላላ ክፍያ ውስጥ ፳% ቅድሚያ ክፍያ ማጠናቀቅ አለበት::

. ፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚፈለግበትን ቅድሚያ ክፍያ በ፮ ወር ጊዜ ውስጥ ያጠናቀቀ ባለይዞታ ለሚፈቀድለት ይዞታ የሽግግር የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጠዋል::

፫. የጠቅላላ ክፍያን ፶% ያጠናቀቀና በቦታው ፕላን የሚጠይቀውን ደረጃ የጠበቀ ግንባታ ያካሄደ ባለይዞታ በሌሎች ሕጎች ያሉበት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው መደበኛ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጠዋል::

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰው ሁኔታ ተሟልቶ መደበኛ ካርታ ያልተሰጠው ሰው ከውርስ በስተቀር ይዞታውን ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ እና ይዞታውን አስይዞ መበደር አይችልም::

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የመከላከል እርምጃዎች</u>

<u>፳. ሕገወጥ ግንባታን ስለማስቀም</u>

፩. ሕገወጥ የይዞታ መስፋፋትና በሕገወጥ ቦታ መከለል ንብረት ማስፈርና ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ የግንባታ እንቅስቃሴ ከጅምሩ የማስቆም ኃላፊነት የቀበሌ ደንብ ማስከበር አገልግሎት ት/ቤት ይሆናል፡

፪. የቀበሌ ደንብ አስከባሪዎች በሂደት ላይ የሚገኝ ሕገወጥ የይዞታ ማስፋፋትና ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታ ወዲያውኑ የማስቆምና ገንቢውን በቁጥጥር ሥር አውለው ፖሊስ ጣቢያ በማቅረብ በሕግ እንዲጠየቅ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው::

፫. የቀበሌው ደንብ ማስከበር ጽሕፈት ቤት ተገቢውን የመከላከልና የማፍረስ ሥራ ሲከናውን የመቆጣርና የመከታተል ኃላፊነት የቀበሌው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ነው:: የቀበሌው አስተዳር ተገቢውን ድጋፍና ቁጥጥር ባለማድረጉ ለሚፈጠረው የሕገ ወጥ ይዞታ መስፋፋትና ግንባታ ተጠያቂ ነው::

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የግንባታ ሂደቱ እንዲቆም የተደረገ ግንባታ ሕገወጥነቱ አጠራጣሪ ካልሆነ የቀበሌው ደንብ አስከባሪ ግንባታው ወዲያዉኑ እንዲፈርስ

ያደርጋል/ ያስደርጋል፡፡ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳር ጽሕፈት ቤት ጉዳዩ እንዲጣራ ወዲያውኑ ያስተላልፋል፡፡ የክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር ጽህፈት ቤትም ጥያቄው በደረሰው ቢበዛ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ውስጥ ተገቢውን በመጣራት መልስ ይሰጣል፤ ሕገወጥነቱ ተጣርቶ እንደደረሰ የቀበሌው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ግንባታውን ያፈርሳል/ ያስፈርሳል ገቢውን ለፍርድ ያቀርባል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተጠቀሰው ሕገወጥ የይዞታ ማስፋፋትና ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ ላይ ግንባታ ሲያካሄድ በቁጥር ሥር የዋለ ሰው ይህንን ደንብ በመተላለፍ በወንጀለኛ መቅጫ በተመለከተው መሠረት ይቀጣል፡

፬. ይህ ደንብ ከወጣ በኋላ የቀበሌው ደንብ አስከባሪ ከአቅሙ በላይ ሆኖ የበላይ እርዳታ ያልጠየቀበት ወይም አጠራጣሪ ሆኖ እንዲጣራ ለክፍለ ከተማው መሬት አስተዳር ጽሕፈት ቤት ያላሳወቀው ህጋዊ ባልሆነ ይዞታ ግንባታ ተገንብቶ ከተገኘ ይዞታው ሲከለልና ግንባታ ሲደረግ ሳያውቅ እንደሆነ በቂ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ሕገወጥ ግንባታ የተካሄደበት ቀበሌ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፭. ህገወጥ የይዞታ ማስፋፋትና ህጋዊ ባልሆነ ይዞታ ላይ የሚካሄደውን ግንባታ በማስቆም ሆነ ገንቢውን ለህግ ለማቅረብ በሚደረ ገው እንቅስቃሴ በአቅራቢው የሚገነው የከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጣቢያ ወይም በግዳጅ ላይ የሚገኝ ፖሊስ አባል ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የትብብር ጥያቄ የቀረበለት የከተማው አስተዳደር ፖሊስ ጣቢያ ወይም የፖሊስ አባል ፈጣን ምላሽ ባለመሰጠቱ ምክንያት የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፱. <u>የእርሻ መሬትን ለህገወጥ ገንቢዎች ማስተላለፍ የተከለከለ ስለመሆኑ</u>**

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ክልል ለሚገኙ ገበሬዎች ለእርሻና ተጓዳኝ አገልግሎት የሚጠቀሙበትን ይዞታ ለይቶ የሚየመለክት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጣቸዋል፡፡

፪. ለእርሻና ተጓዳኝ አገልግሎት የተሰጠን መሬት በማንኛውም መንገድ ህገወጥ ግንባታ ለሚገነባ ሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

፫. በህገወጥ ገንቢው ላይ በዚህ ደንብ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገውን በመተላለፍ የእርሻ መሬቱን ለህገወጥ ገንቢ አካል የሰጠ ገበሬ ይህንን ደንብ በመተላለፍ በወንጀለኛ መቅጫ በተመለከተው ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ህገ ወጥ ግንባታ ተካሄደበት በተገኘ መሬት ላይ የሚገኘው ግንባታ ከፈረሰ በኋላ ገበሬው የይገባኛል ጥያቄ ማንሳት አይችልም፣ መሬቱን የከተማ አስተዳደር ለፈለገው አገልግሎት ሊያውለው ይችላል፡፡

**፲. <u>ለህገወጥ ይዞታ ማስፋፋትና ህገወጥ ግንባታ ለሚጋለጡ ቦታዎች ጥበቃ ስለማድረግ</u>**

፩. የክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለልማት የማይፈለጉና ለሕገወጥ ይዞታ መስፋፋትና ግንባታ የተጋለጡ ቦታዎችን ለይቶ በፕላን ላይ በማስፈር ለተገቢው ክትትል ለቀበሌው አስተዳርና ለደንብ ማስከበር አገልግሎት ማሳወቅ አለበት፡፡

፪. የክፍለ ከተማና የቀበሌ አስተዳር አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተለያዩ ቦታዎች ከክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን በጊዜያዊነት ጥቅም እንዲሰጡና እንዲጠበቁ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**<u>፲፩. የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማክበርና በማስከበር ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

<u>፲፪. መመሪያ ስለማውጣት</u>

ይህ ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን እንደአግባቡ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ወይም የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ከሊያወጡ ይችላሉ፡፡

<u>፲፫. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

<u>፲፬. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከወጣበት ከዛሬ ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስተካከል እና ለመከላከል የወጣ ደንብ ፺፭/፪ሺ፯

### አጭር መግለጫ

ማውጫ

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት

አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በተያዘ ይዞታ ላይ ስለሚወሰድ የማስተካከያ እርምጃ

፬. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ እስከ ሚያዝያ ፩፱፻፺፯ ዓ.ም ድረስ የተየዘና ቤት የተደነባበት ይዞታ

፭. የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለሚዘጋጅላቸው ይዞታዎች

፮. ከከተማ ፕላን ስለሚቃረኑ ይዞታዎች

፯. አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዙና ተቀባይነት ያገኙ ይዞታዎች መስተንግዶ አሰጣጥ

፰. ህጋዊ ባልሆነ የይዞታ መስፋፋት የተያዙና ተቀባይነት ያገኙ ይዞታዎች ውሳኔ አሰጣጥ

፱. ከቀድሞ መመሪያ ውጭ ስለሚስተናገዱ ይዞታዎች

ክፍል ሶስት

እርምጃ ስለሚወሰድባቸው ይዞታዎች እና ህገ-ወጥ ግንባታ ስለመከላከል

፲. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዘ እና በዚህ ደንብ እውቅና ስለማይሰጠው ይዞታ

፲፩. እርምጃ ስለሚወሰድባቸው ህገ-ወጥ ይዞታዎች

፲፪. መስተንግዶ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ

ክፍል አራት

ይህንን ደንብ በማስፈፀም ሂደት የአስተዳደሩ አካላት ያላቸው ተግባርና ኃላፊነት

፲፫. የአስተዳደሩ አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት በተመለከተ

፲፬. የአስተዳደሩንቤቶችእንዲያስተዳድርበህግስልጣንየተሰጠውየአስተዳደሩአካላት በተመለከተ

፲፭. የመሬትልማትናማኔጅመንትቢሮእናየተጠሪተቋማትን በተመለከተ

፲፮. የፍትህቢሮተግባርናኃላፊነት

፲፯. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት
፲፰. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት
፲፱. የወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳. ስለተጠያቂነት
፳፩. የመተባበር ግዴታ
፳፪. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ህጎች
፳፫. መመሪያ ስለማውጣት
፳፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስተካከል እና ለመከላከል ሲባል የወጣ ደንብ ነው፡፡ ደንቡ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በተያዘ ይዞታ ላይ ስለሚወሰድ የማስተካከያ እርምጃ እና እርምጃ ስለሚወሰድባቸው ይዞታዎች እና ህገ-ወጥ ግንባታ ስለመከላከል ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ይህንን ደንብ በማስፈፀም ሂደት ውስጥ የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ያላቸውን ተግባርና ኃላፊነት ይዘረዝራል፡፡

# <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስተካከል እና ለመከላከል የወጣ ደንብ ፳፱/፪ሺ፬</u>

በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የመሬት ሀብት በአግባቡ ለይቶ ለመጠቀም እና በተገቢው ሁኔታ ለማስተዳደር የከተማ አስተዳደር አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዙ ይዞታዎች የከተማውን ፕላን እስካልተቃረኑ ድረስ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ ህገ-ወጥ ይዞታን ለማስተካከልና ለመከላከል ደንብ ቁጥር ፺፰/፪ሺ፫ አውጥቷል፡፡ከዚህ ደንብ መውጣት በኋላ ዝርዝር የአፈፃጸም መመሪያ ሲዘጋጅ በደንቡ ውስጥ በአዲስ መልክ ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮች በተለይም የከተማ መሬትን በአዲስ መልክ አረጋግጦ ከመመዝገብ ጋር ተያይዞ መብት ለተፈጠረላቸው ይዞታዎች መብት የመፍጠር ሂደቱ የከተማ መሬትን ለመመዝገብ ዋንኛው ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ፤

በደንቡ ውስጥ የተካተቱት አንዳንድ አንቀጾች በአጠቃላይ በከተማ አስተዳደሩ ህገ-ወጥ ይዞታን ለመከላከል ቀደም ሲል ሲወሰዱ ከነበሩ እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ ባለመሆናቸው ይህም በከተማው ነዋሪ መካከል የፍትሃዊነት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሸሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሸሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ /፩/ረ/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ የከተማ ቦታዎችን ለማስተካከልና ለመከላከል የወጣ ደንብ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. “አዋጅ” ማለት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፳፩/፪ሺ፬ ነው፡፡

፪. “ሊዝ” ማለት በጊዜ በተገደበ ውል መሰረት የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት የሚገኝበት የመሬት ይዞታ ስሪት ነው፡፡

፫. “የከተማ ቦታ” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስተዳደራዊ ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ነው፡፡

፬. “የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፭. “አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዘ ቦታ” ማለት በከተማው አስተዳደር መሬትን በይዞታነት እንዲፈቅድ ስልጣን በተሰጠው አካል ሳይፈቀድ የተያዘ የከተማ ቦታ ነው፡፡

፮. “ህጋዊ ያልሆነ የይዞታ መስፋፋት” ማት አግባብ ባለው አካል ከተፈቀደው ይዞታ በተጨማሪነት ዞታው ኩታ ገጠም ያለውን የከተማ ቦታ መያዝ ነው፡፡

፩. “ህጋዊ ይዞታ” ማለት በከተማው አስተዳደር መሬትን በይዞታነት እንዲፈቅድ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ያለው ይዞታ ነው፡፡

፪. “ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ” ማለት በከተማው አስተዳደር መሬትን በይዞታነት እንዲፈቅድ ስልጣን በተሰጠው አካል ለዚሁ በተደነገገው ህጋዊ አሰራር መሰረት የይዞታውን እና የባለመብቱን መረጃዎች የያዘ፣ ህጋዊ አሰራርን ተከትሎ የተዘጋጀ፣ በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ስልጣን ባለው ኃለፊ ተረጋግጦና ጸድቆ የተሰጠ የመሬት ባለይዞታነት መብት ማረጋገጫ ሰነድ ወይም ምስክር ወረቀት ነው፡፡

፫. “የከተማ ፕላን” ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፡፡

፲. “የማስተካከያ እርምጃ” ማለት ህጋዊ በሆነ ይዞታ ላይ የተገነባ ቤት ከከተማው መዋቅራዊ ፕላን የመሬት አጠቃቀም ጋር የማይቃረነውን ለይቶ በዚህ ደንብ መሰረት ህጋዊ ዕውቅና የመስጠትና የሚቃረነውን የማስነሳት እርምጃ ነው፡፡

፲፩. “የሽንሻኖ ማስተካከል” ማለት የአካባቢ ልማት ፕላን የተዘጋጀላቸው በከተማው አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ ነጠላ ይዞታዎችን ለማስተካከል የሚዘጋጅ የማስተግበሪያ ፕላን ነው፡፡

፲፪. “የመከላከል እርምጃ” ማለት ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የሚደረግ ግንባታ መንስሄውን ለይቶ ማስወገድን፣ ግንባታዎችን ከጅምሩ ተከታትሎ ማስቆምንና ማፍረስን፣ ገንቢዎችንም ሆነ አስገንቢዎችን ወደ ህግ ማቅረብን እና ማንኛውንም በከተማው ክልል በመሬት ላይ የሚደረግን ህገ ወጥ እንቅስቃሴንና ተግባርን መከላከል ነው፡፡

፲፫. “ራሱን ችሎ የማይለማ ቦታ” ማለት በከተማው ፕላን መሰረት ዝቅተኛውን የቦታ ስፋት የማያሟላ እና መዳረሻ መንገድ የሌላው ነው፡፡

፲፬.... “የቀድሞ መመሪያ” ማለት ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለሌላቸው የይዞታ ማረጋገጫ መስተንግዶ ለመስጠትና ህጋዊ በሆነ መንገድ የይዞታ መስፋፋት የተፈፀመባቸው ይዞታዎችን ለመወሰን የወጡ መመሪያ ቁጥር ፩/፩፱፻፺፪፤ መመሪያ ቁጥር ፪/፪ሸ፪ እንዲሁም እነዚህን መመሪያዎች ለማሻሻል የወጡ መመሪያዎችን ያካትታል::

፲፭..“የሊዝ መነሻ ዋጋ” ማለት ዋና ዋና የመሰረተ ልማት አውታሮች የመዘርጊያ ወጪን፣ ነባር ግንባታዎች ባሉበት አካባቢ የሚነሱ ግንባታዎች እና ንብረቶችን ለማንሳት የሚያስፈልገውን

ወጪ እና ለተነሺዎች የሚከፈል ካሳን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መስፈርቶችን ታሳቢ ያደረገ የመሬት የሊዝ ዋጋ ነው::

፲፮... "ወቅታዊ የሊዝ ጨረታ ዋጋ" ማለት በአካባቢው ለተመሳሳይ የቦታ ደረጃና አገልግሎት በጨረታ ለቀረቡት ቦታዎች ተወዳድረው ያሸነፉ ተጫራቾች በሙሉ የሰጡት ዋጋ አማካኝ ስሌት ነው፡፡

፲፯. "ኤጀንሲ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ የተቋቋመው የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ ነው::

፲፰ "ፕሮጀክት ጽኅፈት ቤት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሸ፬ የተቋቋመ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽኅፈት ቤት ነው::

፲፱. "ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽኅፈት ቤት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሸ፬ እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሸ፭ መሰረት የተቋቋመ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ነው::

፳. "ቤት" ማለት በከተማው አስተዳደር አስተዳደራዊ ወሰን ክልል ውስጥ ለመኖሪያ፣ ለንግድ፣ ለማህበራዊ ወይም ለማንኛውም ለሌላ አገልግሎት የተሰራ ሆኖ በ፩፱፺፯ ዓ.ም በተነሳው የመስመር ካርታ ላይ የሚታይ እና አሁንም ያለ ግንባታ ነው::

፳፩. "ተቀባይነት ያለው የቦታ ስፋት ልዩነት ወሰን" ማለት በልኬት ወቅት ከልኬት መሳሪያ አጠቃቀም፣ ከመሳሪያው ዓይነት፣ ከልኬት ባለሙያው የሙያ ደረጃና ብቃት እና በተመሳሳይ ምክንያቶች በመብለጥ ወይም በማነስ የሚከሰት ተቀባይነት ባለው የቦታ ስፋት ወሰን ውስጥ የሚወድቅ የቦታ ስፋት የልዩነት መጠን ነው::

፳፪. "ሰው" ማት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

፳፫. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩ ይህ ደንብ እስከ ሚያዚያ ወር ፩፱፻፺፯ዓ.ም ድረስ፡-

ሀ. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በተያዘ የከተማ ቦታ፤

ለ. ህጋዊ በሆነ መንገድ በተስፋፋ ይዞታ እና፤

ሐ. በአርሶ አደር ለመኖሪያ አገልግሎ በተያዘ የመሬት ይዞታዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪ ከሚያዚያ ወር ፩፱፻፺፯ ዓ.ም በኃላ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በተያዘ ወይም በተስፋፋ የከተማ ቦታ ላይ የማስተካከል እርምጃው ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በተያዘ ይዞታ ላይ ስለሚወሰድ የማስተካከያ እርምጃ

### ፬.አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ እስከ ሚያዝያ ፩፱፻፺፯ ዓ.ም ድረስ የተያዘና ቤት የተገነባበት ይዞታ

፩. በ፩፱፻፺፯ ዓ.ም ዓ.ም በተነሳው የመስመር ካርታ ላይ የሚታይ ቤት ያለውና አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

፪. ከከተማው ፕላን ጋር የማይቃረን እና በሽንሻኖ ማስተካከል የሚፈቀድ ከሆነ፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ላይ የተደነገገው ቢኖርም በተለያዩ ምክንያቶች በ፩፱፻፺፯የመስመር ካርታ ላይ የማይታይ ቢሆንም ስለቤቱ መንግስታዊ በሆነ ተቋም ከሚያዚያ ፩፱፻፺፯ዓ.ም በፊት የተሰጠ ሰነድ ማቅረብ እና ቤቱ በወቅቱ ተገንብቶ በእጃቸው የሚገኝ እንደነበረ በወረዳው አስተዳደር ተረጋግጦ ከቀረበ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

### ፭.የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለሚዘጋጅላቸው ይዞታዎች

፩. በአንቀጽ ፬ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ህጋዊ የሚደረጉ ይዞታዎች የቦታ ስፋታቸው የሚወሰነው በይዞታው ላይ የሰፈረውን ቤት መሰረት ተደርጎ በሚዘጋጀው ሽንሻኖ ተቀባይነት ሲኖረው፤

፪. የጸደቀ የአካባቢ ልማት ፕላን ሳይኖረው ቦታው ሲመደብ የተደረገ ሽንሻኖ ባላቸው የመኖሪያ ቤት የሕብረት ስራ ማኅበራት ላይ የተገለፁት ይዞታዎች ያሉባቸው አካባቢዎች ሲያጋጥሙ ቀድሞ ለማህበራት የተሰራው ሽንሻኖ ከከተማ ፕላን ጋር ተቃርኖ ከሌላው፤

፫. የፕላን ተቃርኖው ከቦታ ስፋት ስታንዳርድ ጋር የተያያዘ ሆኖ ነገር ግን ህገ-ወጥ ይዞታዎቹ በአንድ ግቢ ውስጥ ባይኖሩም በአካባቢው ሽንሻኖ መሰረት ለእያንዳንዱ ባለይዞታ አነስተኛውን የቦታ ስፋት ድርሻ በመያዝ በጋራ ለማልማት ከተሰማሙ እና፤

፬. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩እስከ ፫በተዘረዘረው መሰረት ለተረጋገጡ ይዞታዎች የቦታው ባለይዞታ ማን እንደሆነ ነዋሪውን በማሳተፍ በወረዳው አስተዳደር ይወሰናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

፭. በዚህ ደንብ የተደነገገው ቢኖርም ይዞታውና ቤቱ በነባር አርሶ አደሮች የተያዘ ከሆነ እስከ ፭፻ሜትር ካሬ እና በልጆቻቸው የተያዘ ከሆነ እስ ከ፩፻፶ሜትር ካሬ ድረስ ለመኖሪያ አገልግሎት ያለቅጣት በነባር/በኪራይ ስሪት ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጣቸዋ፤ ይዞታው ከፕላን ህግጋት ጋር ተቃርኖ ካለው በይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ላይ በማመልከት መስተንግዶ ይሰጣቸዋል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፮.ከከተማ ፕላን ስለሚቃረኑ ይዞታዎች

፩. በ፩፱፻፺፯ ዓ.ም በተነሳው የመስመር ካርታ ላይ ቤቱ የሚታይ ሆኖ ከከተማ ፕላን ጋር የሚቃረን ከሆነ በቦታው ላይ ያለውን ንብረት በራሱ ወጪ አንስቶ ቦታውን እንዲለቅ ይደረጋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩መሰረት የተለቀቀው ቦታ ለመኖሪያ አገልግሎት ተይዞ ከነበረ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ በከተማ ፕላን የተቀመጠውን አነስተኛ የቦታ ስፋት በምትክ ይሰጠዋል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩መሰረት የተለቀቀው ቦታ ከመኖሪያ ቤት አገልግሎት ውጪ ለትልልቅ ማህበራዊ ተቋማት መስጫ ማለትም ትምህርትና የጤና ተቋማት፣ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እና መሰል ትልልቅ ተቋማት ተይዞ ከነበረ በሚቀርበው የልማት እቅድ መሰረት በሸንሻኖው ማስተካከል በሚፈቀደው የቦታ ስፋት ልክ ምትክ ቦታ የሚሰጣቸው ሲሆን ከነዚህ ውጪ ያሉ ሌሎች የድርጅት ይዞታዎች የልማ እቅድ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው ፸፭ ሜትር ካሬ የቦታ ስፋት ምትክ ይሰጣቸዋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ፩መሰረት ቦታውን ለሚለቅ ሰው ምትክ ቦታ በተሰጠው በ ፺ቀናት ጊዜ ገደብ ውስጥ ቦታውን እንዲለቅ የማስለቀቂያ ማስጠንቀቂያ በጽሁፍ ይሰጠዋል፡፡

፯.<u>አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዙና ተቀባይነት ያገኙ ይዞታዎች መስተንግዶ አሰጣጥ</u>

፩. በማስተካከሉ ሂደት ተቀባይነት ያገኙ ይዞታዎች በሊዝ ስሪት ይተዳደራሉ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩የተጠቀሱ ይዞታዎች እስከ ፸፭ካሬ ሜትር ድረስ ለቦታው ደረጃ የተቀመጠውን ወቅታዊ የሊዝ መነሻ ዋጋ ከፍለው ይስተናገዳሉ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ ፸፭ካ.ሜ በላይ ለተፈቀደው የቦታ ስፋት ልዩነት በአካባቢው ወቅታዊ የሊዝ የጨረታ ዋጋ በመክፈል ይስተናገዳሉ፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱ የይዞታ ባለመብቶች ከመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት ጋር የሊዝ ውል ይዋዋላሉ፣ ክፍያም ይፈፅማሉ፡፡ በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ አማካኝነት የሊዝ ይዞታ ምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

፭. ተቀባይነት የሚኖራቸው ይዞታዎች አገልግሎት የሚወሰነው በከተማው ፕላን መሰረት ይሆናል፡፡

፰. <u>ህጋዊ ባልሆነ የይዞታ መስፋፋት የተያዙና ተቀባይነት ያገኙ ይዞታዎች ውሳኔ አሰጣጥ</u>

፩. በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ላይ የተገለጸውና በልኬት በሚገኘው የቦታ ስፋት መካከል ያለው ልዩነት ተቀባይነት ባለው የቦታ ስፋት ልዩነት ወሰን ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ ያለ ቅጣት በነበረው ስሪት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

፪. ተቀባይነት ያለው የቦታ ስፋት ልዩነት ወሰን፡-

ሀ. የልኬት ውጠየታቸው እስከ ፪፻፶ ሜትር ካሬ ድረስ ላሉት ይዞታዎች በካርታ ካለው እስከ ፲፬ በመቶ፣

ለ. የልኬት ውጤታቸው ከ፪፻፶፩ እስከ ፭፻ ሜትር ካሬ ድረስ ላት ይዞታዎች በካርታ ካው እስከ ፲ በመቶ፣

ሐ. የልኬት ውጤታቸው ከ፭፻፩ እስከ ፩ሺ፭፪ ሜትር ካሬ ድረስ ያሉት ይዞታዎች ካርታ ካለው እስከ ፯ በመቶ፣

መ. የልኬት ውጤታቸው ከ፩ሺ፭፻እስከ ፪ሺ፭፻ሜትር ካሬ ድረስ ላሉ ይዞታዎች ካርታ ካለው እስከ ፭በመቶ፤

ሠ. የልኬት ውጤታቸው ከ፪ሺ፭፻፩እስከ ፫ሺ፭፻ሜትር ካሬ እና በላይ ላት ይዞታዎች በካርታ ካለው እስከ ፫ በመቶ ያህል ልዩነቶች ተቀባይነት አላቸው፡፡

፫. የተያዘው ጠቅላላ የቦታ ስፋት ተቀባይነት ካለው የቦታ ስፋት ልዩነት ወሰን በልጦ ከተገኘ በአካባቢው የሊዝ መነሻ ዋጋ እና ለቦታው ደረጃ እንደ አገልግሎቱ የተቀመጠውን የቅጣት ተመን ተከፍሎ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡ የቅጣት ተመኑን በሚመለከት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫የተደነገገው ቢኖርም የተስፋፋው ይዞታ ራሱን ችሎ የሚለማና ቤት ያልሰፈረበት መሆኑ ሲረጋገጥ የተስፋፋው ይዞታ ተቆርጦ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

፱ . <u>ከቀድሞው መመሪያ ውጪ ስለተስተናገዱ ይዞታዎች</u>

፩. በማኛውም ጊዜ በወቅቱ የነበረን መመሪያ በመተላለፍ ከሚፈቀደው የቦታ ስፋት በላይ የይዞታ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ባለይዞታዎች በወቅቱ በነበረው መመሪያ መሰረት የሚፈቀደው የቦታ ስፋት ይጠበቅላቸዋል፡፡

፪. በወቅቱ ከነበረው መመሪያ ከሚፈቀደው የቦታስፋትበላይየይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቷቸዋል፤ ይዞታው በቀደመው ባለይዞታ እጅ የሚገኝ ከሆነ እስከ ፭፻ ካሬ ሜትር ድረስ እንዲስተናገዱ ይፈቀዳል፡፡

፫. በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ፪ላይየተጠቀሰውቢኖርም አጠቃላይ ይዞታው በ፩፱፻፹፰ዓ.ም በተነሳው የአየር ካርታ ላይ የሚታይ ሆኖ የይዞታው ስፋት ከ፭፻ካሬ ሜትር በላይ ከሆነ የሰነድ አልባ ይዞታዎች በሚስተናገዱበት አግባብ ይስተናገዳሉ፡፡

፬. ተከፍሎ ወደ ሶስተኛ ወገን የተላለፈ ከሆነና በተላለፈው ይዞታ ላይ በ፩፱፻፹፰ ዓ.ም በተነሳው የአየር ካርታ ላይ ተቀባይነት የሚኖረው ይሆናል፡፡

፭. ይዞታው ተከፍሎ ለሶስተኛ ወገን የተላለፈ ከሆነና በ፩፱፻፹፰ዓ.ም በተነሳው የአየር ካርታ ላይ የሚታይ ቤት ከሌለው የተያዘው ይዞታ የቦታ ስፋት ከ፭፻ካሬ ሜትር እስካልበለጠ ድረስ የሊዝ መነሻ ዋጋ እንዲከፍሉ በማድረግ መስተንግዶ ይሰጣቸዋል፡፡

፮. በማህበር በመደራጀት ወይም በተናጠል የተያዘ ይዞታ ሆኖ ከይዞታው አመጣጥ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ ጉዳያቸው ስልጣን ባለው አካል ውሳኔ ያገኙ ወይም በከተማው አስተዳደር በኩል ውሳኔ እንዲሰጥባቸው የተደረጉትና መሰል ይዞታዎች ቀደም ሲል በወጡ መመሪያዎች እየታዩና እየተረጋገጡ መስተንግዶ ይሰጣቸዋል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ የተደነገገው ቢኖርም ይዞታው ለከተማው አስተዳደር ተመላሽ እንዲደረግ በፍርድ ቤት የተወሰነ ከሆነ ይዞታው ግንባታ ቢኖረውም እንዲፈርስ በማድረግ ቦታው ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## እርምጃ ስለሚወሰድባቸው ይዞታዎች እና ህገ-ወጥ ግንባታ ስለመከላከል

፲. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዘ እና በዚህ ደንብ እውቅና ስለማይሰጠው ይዞታ

፩ በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ ከአንድ ይዞታ በላይ በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ የያዘ ባለይዞታ በሚመርጠው አንድ ይዞታ ብቻ መስተንግዶ የሚሰጠው ሲሆን ቀሪውን እንዲለቅ ይደረጋል፡፡

፪ በሽንሻኖ ማስተካከል ሂደት ይዞታው ከአንድ በላይ ሽንሻኖ የሚኖረው ከሆነ ባለይዞታው በሚመርጠው አንድ ሽንሻኖ ብቻ መስተንግዶ የሚሰጠው ሲሆን ቀሪውን እንዲለቅ ይደረጋል::

፫ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀዱ የተያዙ ይዞታዎችን ዝቅተኛው የቦታ ስፋት መጠን ከ፸፭ ካ.ሜ እንዲሁም ለመኖሪያ አገልግሎት ከፍተኛው የቦታ ስፋት ከ፭፻ ካ.ሜ መብለጥ የለበትም፡፡

፬ በሚያዝያ ወር ፩፱፻፺፯ዓ.ም በተነሳው የመስመር ካርታ ላይ የማይታዩና አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ግንባታዎች እና የይዞታ መስፋፋቶች ያለተጨማሪ ማስተካከያ የሚፈርሱ ይሆናሉ፡፡

፭. በከተማው ክልል ውስጥ ማንኛውም ሰው ሕጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እና የግንባታ ፈቃድ ሳይኖረው በየትኛውም ቦታ ማንኛውንም ግንባታ ማከናወንም ሆነ መሬትን አጥሮ መያዝ አይችልም፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭የተደነገገውን በመተላለፍ የሚፈፀም ተግባርና እንቅስቃሴን ከጅምሩ የማስቆም ድርጊቱን በፈጸመው አካልም ሆነ በግንባታው ላይ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት በየደረጃው ያለው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽኀፈት ቤት ይሆናል፡፡

፯. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽኀፈት ቤት ጅምር ህገ ወጥ ይዞታና ግንባታ የማካሄድ ተግባር ላይ ተሰማርቶ የተገኘን ሰው ከጅምሩ ተግባሩን የማስቆም፣ ድርጊቱን እየፈጸመ ያለውን አካል አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፯መሠረት የግንባታ ሂደቱ እንዲቆም የተደረገ ግንባታ ሕገ-ወጥነቱ አጠራጣሪ ካልሆነ በስተቀር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ግንባታውን ወዲያውኑ ያፈርሳል ወይም ያስፈርሳል፡፡ በህገ-ወጥ ተግባሩ ውስጥ የተሳተፈ ሲያጋጥም ለሚመለከተው ተቋም እና ለክፍለ ከተማው መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽህፈት ቤት ጉዳዩ እንዲጣራ ወዲያውኑ ያስተላልፋል፡፡

፱. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፰መሰረት የቀረበውን የማጣሪያ ጥያቄ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶችጥያቄው በደረሳቸው ቢበዛ በሚቀጥሉት ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢውን ማጣራት አድርገው ምላሽይሰጣሉ፤ ሕገ ወጥነቱ ከተረጋገጠ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ግንባታውን ወዲያውኑያፈርሳል ወይም ያስፈርሳል፡፡በዚህ ደንብ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ በህገወጥነት የተገነቡና የሚያዙ ይዞታዎችን በሚመለከት ህገ ወጥ ተግባሩን የፈፀመውም ሆነ በሂደቱ ተባባሪ ካለ በሊዝ አዋጁና በሌሎች አግባነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎች ላጠፋው ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፲፩. <u>እርምጃ ስለሚወሰድባቸው ሕገ-ወጥ ይዞታዎች</u>

፩. በዚህ ደንብና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣው መመሪያ መሰረት የሚለቀቅ መሬት ኤጀንሲው ሌሎችንም አግባብነት ያላቸውን የመሬት ማስለቀቂያ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በማስለቀቅና ከማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ነፃ በማድረግ መሬቱን ለመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ያስረክባል፡፡

፪. በዚህ ደንብ ወይም በቀድሞ መመሪያ እውቅና ተሰጥቷቸው ነገር ግን ባለይዞታዎቹ በራሳቸው ምክንያት ቀርበው ለመስተናገድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩ ባለይዞታዎችን ማስረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ለኤጀንሲው ያስተላልፋል፡፡

፫. ኤጀንሲውም ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በሚደርሰው ማስረጃ መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩በተደነገገው መሰረት ይፈጽማል፡፡

፬. ሕጋዊ ድንጋጌዎችን በመጣስ የተሰጡትም ሆኑ ወደፊት የሚሰጡት የይዞታ ማረጋገጫዎች እየተጣሩ የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ እና የማስወሰድ ኃላፊነት የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ይሆናል፡፡

፲፪. <u>መስተንግዶ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሰረት መስተንግዶ ሚሰጣቸው ባለይዞታዎች በአዋጁ በተደነገገው መሰረት በቀሪው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

፪. አግባብያለውአካልሳይፈቅድተይዘውበዚህ ደንብ መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጣቸው ውሳኔ ያገኙ ባለይዞታዎች ውሳኔው በተሰጠ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የተዘጋጀላቸውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መውሰድ አለባቸው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የሊዝ ውል ተፈራርሞ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታውን የማይወስድ ሰው ይዞታውን እንዳልፈለገው ተቆጥሮ መሬቱ ወደ መሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ገቢ ይደረጋል፡፡

፬. በካርታ ያላቸው የቦታ ስፋትና በልኬት የሚገኘው የቦታ ስፋት ልዩነት በመኖሩ አገልግሎት ሳያገኙ የቀሩ ባለይዞታዎች በዚህ ደንብ ተቀባይነት የሚያገኙ ከሆነ ለህዝብ ይፋ በሚደረገው የማስተናገጃ መርሀ-ግብር በወረዳ ፣ በክ/ከተማና በማዕከል ደረጃ በማስታወቂያ መግለጽ አለበት፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት ይፋ በሚደረገው መርሃ-ግብር ቀርበው ያልተስተናገዱ ባለይዞታዎች ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ያስፋፉትን ይዞታ እስኪስተካከል ድረስ ማንኛውም ይዞታ ነክ አገልግሎት አይሰጥም፡፡

፮. በቀድሞ መመሪያ ተቀባይነት አግኝተው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተዘጋጀላቸው ባለይዞታዎች በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር ፩ሺ፯፻፺በተገለጸው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማስታወቂያው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የተዘጋጀላቸውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መውሰድ አለባቸው፡፡

፯. በንዑስ አንቀጽ ፮ መሰረት ቀርቦ ያልተስተናገደ ባለይዞታ ከግንቦት ፲፱፻፺፰ዓ.ም በኋላ እንደተያዘ ይዞታ ተቆጥሮ በዚህ ደንብ በተደነገገው አግባብ መስተንግዶ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ይህንን ደንብ በማስፈጸም ሂደት የአስተዳደሩ አካላት ያላቸው ተግባርና ኃላፊነት

፲፫. የአስተዳደሩ አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት በተቋቋሙበት ህግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተሰጣቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህንን ደንብ ለማስፈጸምና በደንቡ አፈጻጸም ሂደት በየዕርከኑ ያላቸውን አደረጃጀቶች ጨምሮ በዚህ ክፍል ስር በጥቅልና በተናጠል የተደነገጉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራል፡፡

፲፬. በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው ወይም የአስተዳደሩን ቤቶች እንዲያስተዳድር በህግ ስልጣን የተሰጠው የአስተዳደሩ አካላት በስልጣን ክልላቸው ውስጥ ያለውን የአስተዳደሩን መሬትና ቤት ከየትኛውም ህገወጥ ተግባር የመከላከል፣ የመጠበቅ ወይም የማስጠበቅ ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፲፭. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ እናየ ተጠሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት፡-

፩. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. በስሩ ባሉ የሚመለከታቸው ተቋማት መካከል በሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ደንቡን ለማስፈጸም የሚያስችሉና የሚያግዙ ቅንጅታዊ አሰራሮች እንዲነደፉ ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

ለ. ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችል አፈፃፀም ስልት ይነድፋል ወይም እንዲነደፍ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ

እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወስድ ያደርጋል፣ በአጠቃላይ የደንቡን አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

ሐ. ይህንን ደንብና ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪዎችና የአሰራር፣ ማኑዋሎች ሳይጣሱ መተግበራቸውን የሚያረጋግጥበት ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ግድፈቶችን ሲያገኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወስድ ያደርጋል፤

መ. ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችሉ መመሪያዎችና የአሰራር ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ በዚህ ደንብ መሰረት እንዲፀድቁና ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርሱ ያደርጋል፣ መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣ በትግበራ ሂደት የሚታዩ የህግ ክፍተቶች ተለይተው ከውሳኔ ኃሳብ ጋር ሲቀርቡ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ማሻሻያ የሚያስፈልግ ከሆነ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ እንዲሻሻል ያደርጋል፤

ሠ. ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ አላማ እና ይዘት ላይ የከተማውን ህዝብ፣ ፈፃሚው አካልና ባለድርሻው አካላት በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልቶችን ይነድፋል፣ እንዲነድፍ ያደርጋል፤ ስልቶቹን ይተገብራል፣ እንዲተገብር ያደርጋል፣ በቂ ግንዛቤ መፍጠሩን ያረጋግጣል፡

፪. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. በዚህ ደንብ የተደነገገውን የማስተካከያ እርምጃ ለማስፈፀም የሚያስችል የአፈፃፀም ስልትና ዕቅድ ይነድፋል፣ ለቢሮው ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንደወሰድ ያደርጋል፤

ለ. ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችሉ መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣አግባብ ላለው አካል መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣ በትግበራ ሂደት የሚታዩ የህግ ክፍተቶችን ተከታትሎ በመለየት ለቢሮው ከውሣኔ ሃሳብ ጋር ያረቅባል፣ ተቀባይነት ሲያገኝ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሐ. ይህንን ደንብና ለማስፈፀም በሚወጡ የህግ ማዕቀፎችና አሠራሮች ላይ የከተማው ህዝብ፣ ፈፃሚው አካልና ባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተቀባይነት ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

መ. ይህንን ደንብና ደንቡን ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎችን የአሠራር ማኑዋሎች ሳይጣሉ መተግባራቸውን የሚያረጋግጥበት ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ግድፈቶችን ሲያገኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ሠ. በዚህ ደንብ መሠረት ተቀባይነት ለሚኖራቸው ህገወጥ የመሬት ይዞታዎችና ህገወጥ የይዞታ መስፋፋቶችን በሚመለከት የመስክ መረጃ ማሰባሰብና መረጃውን መሠረት አድርጎ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ውሣኔ በመስጠት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አዘጋጅቶ ይሰጣል፣ ወደ ሊዝ ሥርዓት የሚገቡትን ይዞታዎች ዝርዝር የሊዝ ውል እንዲያዋውል ለመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፤

ረ. በዚህ ደንብ መሠረት ምትክ ቦታ የሚገባቸውን ሰዎች በየደረጃው አግባብነት ካላቸው አካላት የሚሰበሰቡ ወይም የሚቀርቡ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ለይቶና አረጋግጦ ምትክ መሬት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያስተላልፋል፣ ከመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ቀድሞ የያዙትን መሬት መልቀቃቸውን በማረጋገጥ ምትክ በተሰጣቸው ቦታ ላይ የሊዝ ውል ተዋውለው ሲያቀርቡ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ያዘጋጃል፤

ሰ. ከህግ ውጭ የተሰጡ ካርታዎችን በመለየት በደንቡና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያና አሠራር መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ መረዳው ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ ያደርጋል

ሸ. መስተንግዶ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ካቀረቡት ውስጥ በደንቡ ተቀባይነት የማይኖራቸውን ይዞታዎች ተገቢነት ያለው የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንዲቻል መረጃውን ለይቶና አደራጅቶ ለሚመለታቸው አካላት ያስተላልፋል፣ መረጃውን አደራጅቶ ይይዛል::

፫. የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ለልማት ተዘጋጅተው ከኤጀንሲው የተላለፉለትን፣ የሊዝ ውል የተቋረጠባቸው ይዞታዎችን፣ በማስተካከያ፣ በማስተካከያ እርምጃ ለአስተዳደሩ ተመላሽ የሚደረጉትን ቦታዎች እና በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን ለይቶና ከልሎ መረጃዎቹ የሚደራጁበትና የሚያዙበትን ሥርዓት በመዘርጋት መረጃዎቻቸውን በዲጂታልና በወረቀት አደራጅቶ ይይዛል ወይም ባንክ ያደርጋል፣ የቦታዎቹንም አገልግሎት፣ ደረጃ እና አስፈላጊ መግላጫዎችን የያዘ የመለያ ሰሌዳ ይተክላል፤

ለ. በዚህ ንዑስ አንቅፅ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተጠቀሱትን ቦታዎች ለሕግወጥነት እንዳይጋለጡ ይከላከላል፣ ወይም እንዲጠበቁለት ለሚመለከተው በህጉ መሠረት ያስረክባል፣ መጠበቃቸውንም ተከታትሎ ያረጋግጣል፤

ሐ. በዚህ ደንብ መሠረት በማስተካከያ እርምጃ ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው ለተወሰነላቸው ባለይዞታዎች ምትክ ቦታ ያዘጋጃል፣ የሊዝ ውል አዋውሎና የቀድሞውን ይዞታ መልቀቃቸውን በማረጋገጥ ምትክ ቦታውን በፕላን ፎርማት ካርታ እንዲዘጋጅለት በሀርድና በሶፍት ኮፒ አዘጋጅቶ ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያስተላልፋል፣ ቦታዎቹ ተወርረው ቢገኙ በህግ

መሠረት ማስለቀቅና ኃላፊነቱን ባልተወጣ አካል ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

መ. በዚህ ደንብ መሠት ወደ ሊዝ ሥርዓት ከሚገቡ ባለይዞታዎች ጋር የሊዝ ውል ይዋዋላል፣ መረጃቸውን አደራጅቶ ይይዛል፣ የሊዝ ክፍያ በማስላት ያስከፍላል፣ ቀሪ የሊዝ ክፍያን ተከታትሎ በውሉና በህጉ መሠረት ይሰበስባል::

፬.የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. በዚህ ደንብ መሠት በማስተካከያ እርምጃ ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው ለተወሰነላቸው ባለይዞታዎች ምትክ ቦታ እንዲዘጋጅ ጥያቄ ሲቀርብለት ምትክ ቦታውን አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

ለ. በደንቡ መሠረት ሕጋዊ ለማይደረጉና እንዲለቀቁ የሚወሰኑ ቦታዎችን የማስለቀቂያ ትዕዛዝ በመስጠት ያስለቅቃል ቦታውንም ነፃ አድርጎ ለመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤተ ያስረክባል፡፡ ፫

፫. የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ የከተማው ፕላን መረጃዎችን አደራጅቶ ከተገቢው ዝርዝር የአጠቃቀም መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ጋር ለፕሮጀክት ጽ/ቤት ለአጠቃቀም በሚመች መልኩ ያቀርባል፤

ለ. በዚህ ደንብ መሠረት መስተንግዶ የሚሰጣቸው ይዞታዎች ያሉባቸው አካባቢዎች የአካባቢ ልማት ፕላን ከሌላቸው የሽንሻኖ ፕላንን አዘጋጅቶ አፀድቆ ያቀርባል፤

ሐ.የሽንሻኖ ፕላን ለሚጋጅላቸው አካባቢዎች የሽንሻኖ ፕላን ዝግጅት መመሪያዎችንና የአሠራር ማኑዋሎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ በማድረግ አፀድቆ ያቀርባል፣ በህግ ማዕቀፎች ላይ ለፈፃሚዎችና ለሚመለከታቸው ሁሉ የግንዛቤ ማፍጠሪያ ስልት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የሽንሻኖ ፕላን ለሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች አዘጋጅቶና አፀድቆ ለካርታ ዝግጅት ይሰጣል፤

መ.በፕላን ላይ የሚደረጉት ማሻሻያዎችና ማንኛውም ለውጥ ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ማሻሻያው ወይም ለውጡ ተግባራዊ ከሚደረግበት ቢያንስ አንድ ቀን አስቀድሞ እንዲደርስ ያደርጋል፤

ሠ.በደንቡ ትግበራ ወቅት የፕላን ህግጋት በተገቢው መጠበቃቸውን ይከታተላል፣ ተጥሶ ቢገኝ እርምጃ ይዋስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል::

፮.የመሬት መረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ለዚህ ደንብ ትግበራ የሚያግዙ እስከ ሚያዝያ ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ድረስ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን የስፓሻልና ስታስቲካል መረጃዎችን አዘጋጅቶ አደራጅቶ ከአጠቃቀምና አያያዝ መመሪያ ወይም ማኑወል ጋር አጠቃቀም በሚያመች መልኩ አዘጋጅቶና አረጋግጦ ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያቀርባል፣ በመረጀዎቹ አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ የስፓሻል መረጃው የይዞታ መለያ ቁጥር የያዘ/ ብሎክ እና ፓርሴል/ መረጃን አደራጅቶ ማቅረብን ይመለከታል፤

ለ. ይህንን ደንብና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ትግበራ ወቅት በህጉ መሠረት የሚደረጉ የመሬት ይዞታ መረጃ ለውጦችን ተከታትሎ ወቅታዊ ያደርጋል፣ መረጃዎቹን አደራጅቶ ለአጠቃቀም ምቹ በሆነ ሁኔታ ይይዛል፤

ሐ. ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የይዞታ መረጃን በተመለከተ የሚፈጠሩ ልዩነቶች እንዲስተካከል ሲቀርቡ ጥያቄዎችን ተቀብሎ በመመሪያው መሠረት ያስተካክላል፣ የታረመውን መረጃ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡

፯. የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. በከተማው ውስጥ ያለ ግንባታ ፈቃድ ወይም ከተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ውጭ ግንባታ የሚከናወኑ ሕገወጥ ግንባታዎችን ተከታትሎ በመለየት የግንባታ ማስቆሚያ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ በህግ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል::

ለ. የግንባታ ፈቃድ መረጃዎችን በአግባቡ በማደራጀትና በመያዝ የመረጃውን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ከሚመለከተው አካል ጥያቄ ሲቀርብለት ወቅታዊና ሕጋዊ ምላሽ ይሰጣል::

__፲፯. የፍትህ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት__

፩.በደንቡና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጡ ሕጎች ትግበራ ወቅት ከከተማው አስተዳደርና ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚነሱ የህግ ክርክሮችን፣ በመሬት ላይ ሕገ-ወጥ ተግባራት ተፈጽመው ሲገኙ አስተዳደሩን ወክሎ የህግ ክርክር ያደርጋል፣ ሕገ-ወጥ ተግባር ፈጽመው የተገኙትን አካላት ለሕግ አቅርቦ እንዲጠየቁ ያደርጋል፣ የሚሰጡ ውሣኔዎችን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያሣውቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ በአፈፃፀም ላይ ክፍተቶች ሲፈጠሩ የእርምት እርምጃ ይወስደል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፪. በዚህ ደንብ ትግበራ ሂደት የህግ አስተያየት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የህግ አስተያየት ለውሣኔ በሚመች ሁኔታ በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

__፲፯.የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት__

፩ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲ ሥር የተደነገጉት ትግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

፪ በዚህ ደንብና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተከለከሉ ወይም ተቀባይነት የሌላቸው በመሬት ላይ የሚፈፀሙ ሕገ-ወጥ ተግባራትን ይከላከላል፣ ተፈጽሞ ሲገኝም በህግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል::

፲፰. <u>የቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. የአስተዳደሩን ቤቶችና ይዞታዎችን መረጃ ለይቶ በማደራጀትና በመያዝ በአስትዳደሩ ስም እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣ ይህንን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል ስልት በንደፍ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል::

፪. የአስተዳደሩ ቤቶችና ይዞታዎች ከህግ ውጭ ለግለሰብ እንዲተላለፍ በሚያደረግ የማጣሪያ ሥራ፣ መረጃ ሲጠየቅ ትክክለኛና ግልፅ ምላሽና መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት በተለይም ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የመስጠት ኃላፊነትይኖርበታል::

፲፱. <u>የወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. ይህንን ደንብና ደንቡን ለማስፈፀም የሚወጣውን መመሪያና አሠራሮችን በተመለከተ ለወረዳው ሕዝብና ፈፃሚ አካላት የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ በማድረግ ለደንቡ አፈፃፀም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፤

፪. በወረዳው አስተዳደራዊ ክልል ውስጥ የሚገኘውና ለአልሚዎች ወይም ለተጠቃሚው በሕጋዊ መንገድ ባልተላለፈ የከተማ መሬት በዚህ ደንብ መሠረት ከማንኛውም ሕገ-ወጥ ተግባር መጠበቁን፣ በማንኛውም ሰው ይዞታ ሥር ባለ መሬት ላይ ማንኛውም ሕገ-ወጥ ተግባር እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ተፈጽሞ ቢገኝ በዚህ ደንብና በሌሎች ተገቢነት ባላቸው ሕጎች እርምጃ ይወሰዳል፣ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፫. በዚህ ደንብ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድባቸው ይዞታዎችን መረጃ የነዋሪውን ተሣትፎና የግልጽነት አሠራርን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት በደንቡና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች፣ የአፈፃፀም ማኑዋሎችና አሠራሮችን መሠረት በማድረግ እንዲጣራና ተረጋግጦ ለክፍለ ከተማው ፕሮጀክት ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ይደረጋል፤

፬. በዚህ ደንብ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድባቸው ወይም መስተንግዶ የሚሰጣቸው ይዞታዎች ለወረዳው በሚወጣው ፕሮግራም መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በደንቡና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጡ የህግ ማዕቀፎችና አሠራሮች መሠረት ባለይዞታዎቹ ሙሉ በሙሉ ቀርበው መስተንግዶ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፭. ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በመስከረም ሆነ በቢሮ ደረጃ ለሚከናወኑ ተግባራት እና በተግባሩ ለሚሣማሩ አካላት ለሥራው ስኬታማነት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ በወረዳው

ሥራውን ለማሣካት በቅርበት የሚመራና የሚከታተል ጠንካራ አመራርና ባለሙያ በወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊመደብ ይችላል፤

፯….በዚህ ደንብና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ላይ ተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብና ደንቡን ለማስፈፀም በሚወጡ የሕግ ማዕቀፎችና አሠራሮች መሠረት ህግ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው ለመስተናገድ ፈቃደኛ ባልሆኑት ወይም በደንቡ ትግበራ ሂደት ሥራውን ለማደናቀፍ ወይም ሂደቱን ለማጭበርበር በሚነቀሰቀሱ ወይም ለሥራው በማይተባበሩ ሰዎች ወይም የባለይዞታዎችንና ግንባታዎችን ተከታትሎ በመለየት በዚህ ደንብ የተደነገገው እርምጃ ተግባራዊ እንዲሆን ያስደርጋል፣ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

፰. በወረዳው አስተዳደራዊ ወሰን ክልል ውስጥ ሕገ-ወጥ ግንባታና የመሬት ወረራ ተፈፅሞ ከተገኘና በሶስት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ እርምጃ ካልተወሰደ የወረዳው አመራሮች አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳. ስለተጠያቂነት

፩. ይህንን ደንብና ደንቡን ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎችና የአፈፃፀም ማኑዋሎችን ለማስፈፀም ኃላፊነት የተሰጣቸው የአስተዳደሩ አካላት፣ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም የኮሚቴ አባላት ግዴታቸውን ካልተወጡ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

፪. ከአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም ከወጡት ወይም ከሚወጡት ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ድንጋጌ ውጭ የከተማውን መሬት አጥሮ የያዘ፣ ግንባታ የፈፀመ ወይም እንዲፈፀም ያደረገ፣ የተጭበረበረ መረጃ በማቅረብ ወይም ሌሎችን በጥቅማ ጥቅም በመደለል ሕጋዊ ባለይዞታ ለመሆን ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ያገኘ ወይም ለማግኘት የሞከረ፣ የዚህን ደንብ አፈፃፀም ያደናቀፈ፣ ለማደናቀፍ የሞከረ እና በጠቃላይ በከተማው መሬት ላይ ሕገ-ወጥ ተግባር የፈፀመ፣ እንዲፈፀም ያደረገና በህግ ያልተፈቀደን መብት በመሬት ላይ ለማግኘት የሞከረም ሆነ ያገኘ ማንኛውም ሰው ተገቢነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### ፳፩…የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፳፪. <u>የተሻሩና ተፋፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች</u>

፩.በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ ህገ-ወጥ ይዞታ ለማስተካከልና ለመከላከል የወጣ ደንብ ቁጥር ፶፰/፪ሺ፰ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡ ደንቡን መሰረት ተደርጎ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

፪. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፳፫. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

ይህን ደንብ ለማስፈፃም ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ በከተማው ካቢኔ ይወጣል፡፡

፳፬. <u>ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህደንብከፀደቀበት ከዛሬ ሚያዝያ ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፸/፪ሺ፰ አጭር መግለጫ

አጭር መግለጫ

የአዲስ አበባ ከተማን ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገትን ለማሳካት ቀልጣፋና ተደራሽ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለማቋቋም እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በማቋቋምና የተቋሙን አደረጃጀት በመወሰን ለከተማው ህብረተሰብ የተሻለና ውጤታማ የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ለማቅረብ የተዘጋጀ ህግ ነው፡፡

<u>ማውጫ</u>


፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. መቋቋም

፬. ዋና መስሪያ ቤት

፭.አደረጃጀት

፮. ካፒታል

፯. የድርጅቱ ስልጣንና ተግባራት

፰. የሥራ አመራር ቦርዱ ስልጣንና ተግባር

፲. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

፲፩. የምክትል ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባራት

፲፪. የዋናና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም

፲፫. ኃላፊነት

፲፬. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

፲፭. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች

፲፮. የመተባበር ግዴታ

፲፮. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፲፯. ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች

፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፸/፪ሺ፰

የአዲስ አበባ ከተማን ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገትን ለማሳካት ቀልጣፋና ተደራሽ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በማቋቋምና የተቋሙን አደረጃጀት በመወሰን ለከተማው ህብረተሰብ የተሻለና ውጤታማ የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩(ረ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር ፸/፪ሺ.፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቻርተር"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ነው፤

፬. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

፭. **"ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፤

፮. **"ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰንና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፩ ነው፤

፯. **"ቦርድ"** ማለት በቻርተሩ እና በዚህ ደንብ መሰረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የስልጣን አካል ነው፤

፰. **"የብዙሃን ትራንስፖርት"** ማለት አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል እንዲያገለግል የሚደራጅ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ነው፤

፱. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲. በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ድርጅቱ መቋቋም፣ ዓላማ እና ሥልጣንና ተግባር

**፫. መቋቋም**

፩. ሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የከተማ አስተዳደሩ የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

፪. ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰንና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፩ መሰረት ይተዳደራል፣

፫. የድርጅቱ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፣ ሆኖም የዕለት ተዕለት ተግባራትን በተመለከተ በባለሥልጣኑ ይመራል፣

፬. የቻርተሩ አንቀጽ ፳ በድርጅቱ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መስሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ማዕከል ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

**፭.አደረጃጀት**

ድርጅቱ የሚከተለዉ አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፣

፪. ዋና ሥራ አስኪያጅ፣

፫. ሁለት ምክትል ሥራ አስኪያጆች፣

፬. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች፡፡

**፮. ዓላማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፡-

፩. ለተማሪዎች ቀልጣፋና ተደራሽ መደበኛ የአዉ ቶብስ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፣

፪. ለከተማው ኅብረተሰብ የፈጣን አዉቶብስ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፣

፫. ከሌሎች የሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ የተቀናጀ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፡፡

**፯. ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፪ ቢሊየን ፮፻፵፪ ሚሊየን (ሁለት ቢሊየን ስድስት መቶ አርባ ሁለት ሚሊየን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፯፻፴፩ ሚሊየን ፫፻፵፩ ሺህ ፭፻፷፬ (ሰባት መቶ ሰላሳ አንድ ሚሊየን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አራት ብር) በአይነት ተከፍሏል፡፡

፰. <u>የድርጅቱ ስልጣንና ተግባራት</u>

ድርጅቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የብዙሀን ትራንስፖርት በህዝብ ዘንድ ተፈላጊና ተመራጭ እንዲሆን ይሰራል፤

፪. መደበኛ የከተማ አዉቶብሶችና የተማሪዎች አዉቶብሶች በመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ የፈጣን አዉቶብስና የመደበኛ አዉቶብስ የትራንስፖርት አገልግሎት ያቀርባል፤

፫. ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በተለይም ተማሪዎችን፣ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን ህጻናትን ንና ነፍሰጡሮችን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ምቹና አስተማማኝ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፤

፬. አገልግሎት አሰጣጡ በተገቢው የቴክኖሎጂ አውታሮች የታገዘ፣ ተመራጭ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና አስተማማኝ እንዲሆን ያደርጋል፤

፭. ከባለሥልጣኑ በሚሰጠዉ የአገልግሎት ክፍያ መጠን፣ የመስመር ድልድል እና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፤

፮. ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ አቅጣጫ መሠረት ለብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የትኬት ሽያጭ አሰራር ይዘረጋል፣ ትኬት ይሸጣል፣ ገቢ ይሰበስባል፤

፯. አውቶብሶቹ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሸከርካሪ ምርመራ፣ ቀላል ጥገና እና የእድሳት አገ ልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፰. የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሟላ መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤

፱. ለአውቶብሶቹ ምቹ መንገድ እና የተለየ የአውቶብስ የጉዞ መስመር እንዲኖር ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

፲. ለድርጅቱ የሚያስፈልጉ ዴፖ፣ የተርሚናል፣ የጥገና እና የመሳሰሉት መሰረተ ልማቶች እንዲ ሟሉ ከባለሥልጣኑ ጋር በጋራ ይሰራል፤

፲፩. በቦርዱ ውሳኔ መሰረት አውቶብሶችን ይገዛል፣ በሥራ ላይ ያዉላል ይሸጣል፤

፲፪. የትራንስፖርት ባለስልጣን በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት የትራንስፖርት አገልግሎቱ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፫. በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ከተሰማሩ እና ጠቃሚ ልምድ ካላቸው የብዙሃን ትራንስ ፖርት ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲፬. የተሰጠውን ተልዕኮ ሊያሳኩ የሚችሉ በስራ አስፈፃሚ ወይም በቦርዱ ተለይተው የሚሰጡ ትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤

፲፰. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፱. ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ይፈጽማል፡፡

**፱. <u>የሥራ አመራር ቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>**

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚመለከታቸውን የመን ግስት ከፍተኛ አመራሮችና ባለድርሻ አካላት ያካተተ ሆኖ የሚከተሉት ሰልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የሥራ አፈጻጸም ይቆጣጠራል፤

፪. ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ይወስናል፤

፫. የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና ውስጠ ደንቦችን ያፀድቃል፣ አፈጻፀማቸውንም ይከታተላል፤

፬. በዋና ሥራ አስኪያጅ ሪፖርት መነሻ የድርጅቱን የበጀትና የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፤

፭. ድርጅቱን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ የፖሊሲ ጥያቄዎችና ሌሎች የአሠራር ደንብና መመሪያ ዎችን በመርመር ለውሳኔ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤

፮. ለድርጅቱ የሚያስፈልገውን በጀትና የሥራ ማስኬጃ ያጸድቃል፤

፯. የድርጅትን የረዥም ጊዜ ብድሮችና ክሬዲቶች ያፀድቃል፤

፰. በከተማው ካቢኔ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የገንዘብ ወጪ ይፈቅዳል፣ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌለውን የቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፤

፱. የድርጅቱ ሂሣቦችና ንብረቶች በአግባቡ መያዛ ቸውን ያረጋግጣል፤

፲. የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፤ ለተሰየሙ ኦዲተሮች የድርጅቱ የሂሣብ መዝገቦች መቅረባ ቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩. የድርጅቱን የሂሳብ ሪፖርትና የውጪ ኦዲተር ሪፖርት ያፀድቃል፤

፲፪. የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨመር፣ ወይም እንዲ ቀንስ ለከተማው ካቢኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፲፫. በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው ደረጃ መሠረት የዋና ሥራ አስኪያጅን የደመወዝ ጣሪያ ተከትሎ የበታች ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን የደመወዝ እርከንና የድርጅቱን አደረጃጀት ይወስናል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤

፲፬. አፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፡፡

**፲. <u>የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር</u>**

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ሲሆን በቀን ተቀን ተግባሩ ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ባለስልጣን በመሆን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የድርጅቱን ሥራ በበላይነት ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፤

፪. ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸዉም ስምምነቶች ድርጅቱን በመወከል ይፈራረማል፣ ውሎቹና ስምምነቶቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤

፫. ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎች ለቦርዱ እያቀረበ ያጸድቃል፣ የስራ እንቅስቃሴያቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፬. ድርጅቱን ውጤታማ፣ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሊያደርጉ በሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

፭. ሌሎች ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ተግባራቸውን ይወስናል፤

፮. የድርጅቱን ፋይናንስ ያንቀሳቅሳል፣ ወጭዎችን ይፈቅዳል፣ ያጸድቃል፤

፯. የፋይናንስ እና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም በመመሪያው መሠረት መተግበሩን ያረጋግ ጣል፤

፰. የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲ ሁም ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

፱. ዉሳኔ የሚሹ ጉዳዩችን ለቦርዱ ያቀርባል፣ የቦርዱን ውሣኔዎች ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤

፲. በሥራው ሂደት ላይ የሚመክርና በዕቅዶችና ውሣኔዎች ላይ የሚወያይ የማኔጅመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባውን ይመራል፤ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፤

፲፩. ቦርዱ የሚሰጠውን ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናል፤

፲፪.የድርጅቱን ሥራ አፈጻጸም በተመለከተ ለቦርዱና ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣ በሚሠጠውም ግብረ-መል ስና አቅጣጫ መሠረት ተገቢውን ይፈጽማል፡፡

## ፲፩. <u>የምክትል ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባራት</u>

ምክትል ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩. የድርጅቱን የሥራና የበጀት ዕቅድ በማዘ ጋጀትና በመተግበር ዋና ሥራ አስኪያጁን ያግዛል፤

፪. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በሌለበት በእርሱ ተለይቶ የተወከለው ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ እሱን ተክቶ ይሰራል፤

፫. የተመደበበትን የሥራ ክፍል የመምራት ሥራ ይሠራል፤

፬. የድርጅቱን ግብና ዓላማ ለማሳካት በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከና ውናል፡፡

## ፲፪. <u>የዋናና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም</u>

የድርጅቱ ዋናና ምክትል ሥራ አስኪያጆች በከተማዉ ከንቲባው ይሾማሉ፡፡

፲፫. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፲፬. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፭. <u>ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች</u>

ድርጅቱ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ያከናወናቸው ተግባራት በዚህ ደንብ ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

፲፮. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ የማክበርና የማስ ከበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያ ዎችን ቢሮዉ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፰. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተካተቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

፲፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመስከረም ፩ ቀን ፩ሺ፰ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ ፮ ቀን ፩ሺ፯ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ በንቲ**

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አንበሳ የከተማ አዉቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፻፩/፪ሺ፲</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስሮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ አንበሣ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንዲተላለፍ በመወሰኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ዕድገትን ለማሳካት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመራና የሚተዳደር ተቋም ለማቋቋም በማስፈለጉ፤ በመገኘቱ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በማቋቋምና የተቋሙን አደረጃጀት በመወሰን ለከተማዉ ህብረተሰብ የተሻለና ዉጤታማ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አዉጥቷል::

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አንበሳ የከተማ አዉቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፩/፪ሺ፲›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. <u>መቋቋም</u>

፩) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አንበሳ የከተማ አዉቶቡስ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኃላ ድርጅት ተብሎ የሚጠራ) የራሱ የሕግ ሰዉነት ያለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪) ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፮ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

፬. <u>ዓላማዎች</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች፡-

፩) የከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በህዝብ ዘንድ ተፈላጊና ተመራጭ እንዲሆን መሥራት፤

፪) የመደበኛ፣ የፈጣን፣ ሌሎች አዉቶቡሶች በመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ የትራንስፖርት አገልግሎት ለህብረተሰቡ ማቅረብ፤

፫)ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በተለይም ተማሪዎችን፣ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ነፍሰጡሮችን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ምቹና አስተማማኝ የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፬) አገልግሎት አሰጣጡ በተገቢዉ የቴክኖሎጂ አዉታሮች የታገዘ ተመራጭ ቀልጣፋ ተደራሽና አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ፤

፭) አዉቶቡሶቹ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተሽከርካሪ ምርመራ፣ ጥገና እና የእድሳት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤

፮) የመንጃ ፈቃድ ስልጠና እንዲሁም የተሽከርካሪ ምርመራ ወይም የክላዉዶ አገልግሎት መስጠት

፯) ዓለማዉን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተመሣሣይ ሥራዎችን መሥራት፡፡

፭. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደዉ ካፒታል ብር ፫ ቢሊዮን ፭፻፳፬ ሚሊዮን ፬፻፭ ሺህ ፰፻፩ (ሶስት ቢሊዮን አምስት መቶ ሀያ አራት ሚሊዮን አራት መቶ አምስት ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፭፻፶፭ ሚሊዮን ፭፻፵፫ ሺህ ፰፻፶፯ ብር (አምስት መቶ ሀምሳ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ ሰባት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፮. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፯. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከ ነሃሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሃሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ (ኢ/ር)

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

# የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ፻፹/፪ሺ፲፩

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተረጋግጦ የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ባለመብት የሆነ ሰው የመሬት ይዞታ መብቱ ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

በተከናወኑ ምዝገባዎች መሠረት በሚሰጡ የምዝገባ ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች ላይ ዋስትና በመስጠት ሕብረተሰቡ በመሬት ይዞታ ምዝገባ ስርዓት ላይ እምነት እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

በተሰጡ የምዝገባ ማረጋገጫ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና በሚፈጽሙት ተግባር ምክንያት ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሣ ለመክፈል የሚያስችል የዋስትና ፈንድ ማቋቋም ስለአስፈለገ፤

በከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፰/፪ሺ፮ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፺፯ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ቁጥር ፻፹/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ ነው፤

፬. "ኤጀንሲ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ነው፤

፭. "አዋጅ" ማለት የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፮/፪ሺ፮ ነው፤

፮. "ደንብ" ማለት የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹፬/፪ሺ፮ ነው፤

፯. "መመሪያ" ማለት የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ እና ምዝገባ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር ፹፩/፪ሺ፲ ነው፤

፳. “የመሬት ይዞታ” ማለት የሊዝ ሥሪት በሚመራበት ህግ መሠረት በሊዝ የተያዘ ወይም በሊዝ ሕግ መሠረት ዕውቅና የተሰጠው የከተማ ነባር የመሬት ይዞታ ላይ የተገኘ የተጠቃሚነት መብት ነው፤

፱. “መዝጋቢ ሹም” ማለት በአዋጁ መሠረት የመሬት ይዞታ መብትን፣ ክልከላንና ኃላፊነትን እንዲመዘግብ እና ማረጋገጫዎችን እንዲሰጥ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

፲. “የማይንቀሳቀስ ንብረት” ማለት የከተማ መሬትንና በመሬቱ ላይ የሚገኘውን መሬት ነክ ንብረት፣ በመሬት ላይ በቋሚነት የተገነቡ ግንባታዎችን ወይም የተተከሉ ቋሚ ተክሎችን የሚያካትት ሲሆን ሌሎች ተነሺ ንብረቶች እንደ ሰይወክላል፣ ሣር እና ቋሚ ያልሆኑ ተክሎችን አይጨምርም፤

፲፩. “የዋስትና ፈንድ” ማለት ኤጀንሲው ላረጋገጣቸውና ለመዘገባቸው የከተማ መሬት ይዞታዎች በተቋሙ ስህተት በተፈጠሩ የመሬት ይዞታ መብት መዛባቶች ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ካሣ ክፍያ እንዲውል በየጊዜው ከሚደረግ የከተማ መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ዝውውር ከግብይቱ ዋጋ አንድ መቶኛ ሣይበልጥ የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፤

፲፪. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በኤጀንሲው በሚፈፀም የመሬት ይዞታ መብት የስም ዝውውር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የዋስትና ፈንድ መቋቋም</u>

፬. <u>የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የዋስትና ፈንድ ስለመቋቋሙ</u>

የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የዋስትና ፈንድ /ከዚህ በኋላ “ፈንዱ” እየተባለ የሚጠራ/ ቢሮው በኤጀንሲው ስም በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፭.<u>የፈንዱ ምንጮች</u>

የሚከተሉት ምዝገባዎች ለፈንዱ የሚውል ተጨማሪ ክፍያ ይከፈልባቸዋል፡-

፩. የመሬት ይዞታ መብት በሙሉ ወይም በከፊል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በዓይነት መዋጮ ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ በመተላለፉ፤

፪. የመሬት ይዞታ መብት በውርስ በመተላለፉ ምክንያት የስም ዝውውር ሲፈጸም፡፡

፮. <u>የፈንዱ ዓላማ</u>

የፈንዱ ዓላማ፡-

፩. በኤጀንሲው ተረጋግጦ የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ባለመብት የሆነ ሰው የመሬት ይዞታ መብቱ እና በይዞታው ላይ ያረፈ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ባለቤትነት መብቱ ዋስትና እንዲኖረው ለማድረግ፤

፪. በኤጀንሲው ተረጋግጠው ለተመዘገቡ ምዝገባዎች በተሰጡ የምዝገባ ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች ላይ ዋስትና በመስጠት ሕብረተሰቡ እምነት እንዲኖረው ለማድረግ፤

፫. ኤጀንሲው በሰጠው የምዝገባ ማረጋገጫ ማስረጃ ላይ በመደገፍ ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና በሚፈጽሙት ተግባር ምክንያት ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ ለመክፈል፣ ይሆናል፡፡

፯. ስለ ክፍያዎች

ከፈንዱ ሂሣብ ገንዘብ ወጭ ሆኖ የሚከፈለው በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር፣ በመዝጋቢ ሹም እና በኤጀንሲው የክፍያና ሂሣብ ኃላፊ ፊርማ ይሆናል፡፡

፰. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሥልጣን

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር፡-

፩. ፈንዱ የሚቀመጥበት ልዩ የባንክ ሂሣብ በቢሮው እንዲከፈት ያደርጋል፣

፪. በዚህ ደንብ መሠረት የተሰበሰበው ገንዘብ በፈንዱ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ገቢ እንዲደረግ ያደርጋል፣

፫. የፈንዱን ሂሣብ ይይዛል፣ በዚህ ደንብ መሠረት ፈንዱን ሥራ ላይ ያውላል፣ ያስተዳድራል፡፡

፱. የፈንዱ ክፍያ ተመን

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ሥር በተመለከተው በእያንዳንዱ ግብይት ወይም አገልግሎት ለፈንዱ እንዲውል የሚከፈለው ተጨማሪ ክፍያ ተመን የሚከተለው ይሆናል፣

፩. የከተማ መሬት ይዞታ መብት ከውርስ በስተቀር በማናቸውም ሕጋዊ መንገድ ለሌላ ሰው በመተላለፉ የስም ዝውውር ሲፈፀም ከግብይቱ ዋጋ ዜሮ ነጥብ ሦስት ከመቶ /0.፫%/፣

፪. የመሬት ይዞታ መብት በውርስ የስም ዝውውር ሲፈፀም በውርስ በተላለፈው ይዞታ ላይ ካለው የማይንቀሣቀስ ንብረት ዋጋ ግምት ዜሮ ነጥብ አንድ ከመቶ /0.፩%/ ወራሽ ከአንድ በላይ ከሆኑና ውርሱን ከተከፋፈሉ በሚደርሣቸው የውርስ ድርሻ አግባብ/፡፡

፲. የክፍያ ግዴታ

፩. የመሬት ይዞታ መብት በሙሉ ወይም በከፊል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በዓይነት መዋጮ ወይም በሌላ መንገድ ለሌላ ሰው የሚያስተላልፍ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተወሠነው የክፍያ ተመን መሠረት ለፈንዱ የሚውል ተጨማሪ ክፍያ መፈፀም አለበት፡፡

፪. የመሬት ይዞታ በውርስ የስም ዝውውር ሲፈፀም፣ እንደአግባብነቱ ወራሹ ወይም ወራሾቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፪/ በተወሠነው የክፍያ ተመን መሠረት ለፈንዱ የሚውል ተጨማሪ ክፍያ መፈፀም አለበት፡

፲፩. የፈንዱ ክፍያ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ለፈንዱ እንዲውሉ የሚከፈሉ ተጨማሪ ክፍያዎች በተናጠል እና አገልግሎቶቹ በተጠየቁ ጊዜ መከፈል አለባቸው፡፡

፪. ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ዓይነት የሚፈፀም ክፍያ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ለየብቻ የስም ዝውውሩ ከመፈፀሙ በፊት መከፈል አለበት፡፡

፫. ስለኤጀንሲው ተጠያቂነት፣ ስለኃላፊነት መጠን፣ ስለጉዳት ካሣ ስሌት፣ ስለ ጉዳት ካሣ አከፋፍል የአዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው ድንጋጌዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

፲፪. ስለ ፈንዱ የባንክ ሂሣብ

የቢሮው ኃላፊ ፈንዱ የሚቀመጥበትን ልዩ የባንክ ሂሣብ በኤጀንሲው ስም ይከፍታል፡፡

፲፫. ፈንዱን ለልማት ስለማዋልና ኢንቨስት ስለማድረግ

፩. ፈንዱ ለጊዜው ለክፍያ የማይፈለግ መሆኑን ኤጀንሲው ለቢሮው ሲያሳውቅና ቢሮው ሲያረጋግጥ፣ ፈንዱ ካቢኔው ተገቢ ናቸው ለሚላቸው የከተማ የልማት ሥራ ሊውል ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለከተማ ልማት ሥራ የሚውለው ገንዘብ ከጠቅላላ የፈንዱ ገንዘብ ከአሥር በመቶ /10%/ ሊበልጥ አይችልም፡፡

፫. ኤጀንሲው ፈንዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለክፍያ የማይፈለግ መሆኑን በቅድሚያ እያረጋገጠ ቢሮው ከፈንዱ ጠቅላላ ገንዘብ ከሃምሣ በመቶ /50%/ ሣይበልጥ ፈንዱን ካቢኔው ተገቢ ናቸው በሚላቸው በዋስትና ሰነዶች ላይ ኢንቨስት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፬. የመዝግብና ሂሳብ አያያዝ

የፈንዱ የመዝገብና የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን የሚከተል ይሆናል፡፡

፲፭. ኦዲት

የፈንዱ ሂሣብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይመረመራል፡፡

፲፮. የመተባበር ግዴታና ተጠያቂነት

፩. ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም አፈፃፀሙን ያሰናከለ ወይም የፈንዱን ገንዘብ ያባከነ ወይም ያጕደለ እንደሆነ በሀገሪቱ የወንጀል ሕግ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፲፯. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የከተማው ካቢኔ ደንብ ወይም መመሪያ፣ እንዲሁም ማንኛውም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

፲፰.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ኤጀንሲው ይህንን ደንብ በሚገባ ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፱.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሚያዝያ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 13/2001

**ማውጫ**

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

አጭር ርዕስ

ትርጓሜ

የአፈጻጸም ወሰን

ጾታ አገላለጽ

የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር መርሆች

አለም አቀፍ ግዴታዎች

የግዢ ንብረቶች ህዝብ እንዲያውቅ ስለማድረግ

የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ሀላፊ ሀላፊነት

የፋይናንስ የግዢ እና ንብረት አስተዳደር የስራ ሂደት ተግባርና ሃላፊነት

ተጠያቂነት

ምዕራፍ ሁለት

የቢሮው ስልጣን እና ሀላፊነት

የቢሮ አላማ

የቢሮው ተግባር

የቢሮው ስልጣን

ምዕራፍ ሶስት

መሰረታዊ የግዢ ድንጋጌዎች

የግዢ እቅድ

የግዢ ሰነዶች

አድሎ ያለማድረግ

ልዩ አስተያየት

ስለ ግንኙነት ስልት

ስለ ቋንቋ

ስለ እጩ ተወዳዳሪዎች ብቃት

የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

ጨረታን፣ የመወዳሪያ ሃሳብን እና የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ስለማድረግ

ስለ ኤልክትሮኒክስ ግዢ

የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ስነ- ምግባር

የግዢ ዘዴዎች

ስለ መንግስት እና የግል ሽርክና

ምዕራፍ አራት

ስለ የግልጽ ጨረታ አፈጻጸም

የጨረታ ማስታወቂያ

የጨረታ ጥሪ

ስለ የጨረታ ሰነድ

ስለ የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

ስለ ጨረታ ማስከበሪያ

የመጫረቻ ሰነድ ስለማቅረብ እና ስለመቀበል

ጨረታን ስለመክፈት

የመጫረቻ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም

በሚስጢር ስለሚያዙ አሰራሮች

ከአሸናፊ ተጫራቾ ጋር ድርድር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች

አሸናፊነትን ስለመግለጽ እና ውል ስለመፈራም

ስለ ውል ማስከበሪያ

ስለ ቅድሚያ ክፍያ

ምዕራፍ አምስት

ስለ ውስን ጨረታ

በውስን ጨረታ ለመጠቀም መሟላት ስላባቸው ጉዳዬች

ስለ የውስን ጨረታ አፈጻጸም

ምዕራፍ ስድስት

ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዢ
ከአንድ አቅራቢ ግዢ ለመፈጸም መሟላት ስላባቸው ሁኔታዎች
ከአንድ አቅራቢ የሚከናወን ግዢ አፈጻጸም
ምዕራፍ ሰባት
የመወዳሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈጸም ግዢ
የመወዳሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ግዢ ለመፈጸም መሟላት ስላባቸው ሁኔታዎች
የመወዳሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚከናወን ግዥ አፈጻጸም
ምእራፍ ስምንት
በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም ግዢ
በዋጋ ማቅረቢያ ስለሚፈጸም ግዢ መሟላት ስላባቸው ሁኔታዎች
በዋጋ ማቅረቢያ ስለሚካሄድ ግዥ አፈጻጸም
ምዕራፍ ዘጠኝ
በሁለተኛ ደረጃ ጨረታ ስለሚፈጸም ግዢ
በሁለተኛ ደረጃ ጨረታ ግዢ ለመፈጸም መሟላት ስላባቸው ሁኔታዎች
በሁለተኛ ደረጃ ጨረታ አፈጻጸም ስርአት
**ምእራፍ አስር**
በአለም አቀፍ ውድድር ስለሚፈጸም ግዢ
ስለ አለም አቀፍ ግዢ
ምዕራፍ አስራ አንድ
ልዩ ግዢ
ስለ ከፍተኛ ግዢዎች
ስለ ማእቀፍ  ስምምነት አፈጻጸም
ምዕራፍ አስራ ሁለት
ስለ መንግስት ንብረት አስተዳደር
አጠቃላይ
ንብረትን ስለመያዝ
ስለ አጠቃቀም እና ጥገና
ስለ መንግስት ንብረት አስተዳደር
ስለ መጠበቅ እና መንከባከብ
ስለ ማስወገድ

ስለ መሰረዝ

ስለ ማስተላፍ

ምዕራፍ አስራ ሶስት

በመንግስት ግዢ አፈጻጸም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት ስለሚቀርብ አቤቱታ

ጠቅላላ

ለመንግስት መስሪያ ቤት ለበላይ ሃላፊዎች ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

ለቢሮው የሚቀርቡ አቤቱታዎች

ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ለቢሮ ስለሚቀርቡ አቤቱታ

ምዕራፍ አስራ አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

ስለ ጥፋች እና ቅጣቶች

ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ስለ ተሽሩ እና ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ህጎች

አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 13/2001 ሲሆን አዋጁ የከተማ አስተዳደሩ የግዢ ስርአትን በተመለከተ በማንኛውም በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ የግዢና ንብረት አስተዳደር ላይ ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን ይህም የመንግስት የግዢ ስርአት ይበልጥ ግልጽ፣ቀልጣፋ እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ እንዳይባክን እና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያደርግ ሲሆን ። የመንግስት መስሪያ ቤቶች እቃዎችን የግንባታ ዘርፍ ስርአቶችን የምክር ና ልሎች አገልግሎት ወጪ በመሸፈን ከልሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለማግኘት የሚደረግ ውል ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንደማይሆን አስቀምጧል። ከዚህም በተጨማሪ የግዢ ንብረት አስተዳደር ስር የተመደቡ ሰራተኞች ወይም የተሾሙ ሃላፊዎች በዚህ አዋጅ እና የቢሮ ሃላፊ በሚያወጡዋቸው መመሪያ መሰረት ስለሚወስዱት እርምጃ ተጠያቂ እንደሚሆኑ የሚደነግጉ አንቀጾን ይዟል።

## የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ ደንብ 14/1991ዓ/ም

**አጭር መግለጫ**

**የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች ሀገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸውና ወዲያውም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ባለቤትነት የሚገለጽበት መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ እንዲሁም የሚመሩበትን ዝርዝር ሁኔታ ለማመላከት የተዘጋጀ ህግ ነው።**

1. መቋቋምና ካፒታል
2. ዋና ጽ/ቤት
3. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ሲኒማ ቤቶች ድርጅት ዓላማዎች
4. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የኤግዚቢሽን ማዕከል እና የገበያ ድርጅት ዓላማዎች
5. የድርጅት አካላት
6. የቦርድ ሥልጣንና ተግባር
7. የቦርድ ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት
8. ስለመጠባበቂያ ሂሳቦችና አጠቃቀም
9. የባለገንዘቦችን መብት ስለመጠበቅ
10. የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫ እና የመፍረስ ማስታወቂያ ስለማውጣት
11. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች
12. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች
13. ስለሌሎች ህጎች ተፈፃሚነት
14. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

## የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር 14/1991ዓ/ም

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች ሀገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸውና ወዲያውም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ባለቤትነት የሚገለጽበት መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ እንዲሁም የሚመሩበትን ዝርዝር ሁኔታ በሕግ መወሰን በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 83/1989 አንቀጽ 3(1) እና (4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰንና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ደንብ ቁጥር 14/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡"

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ

1. "ድርጅት" ማለት የመስተዳድሩ ሙሉ ወይም በከፊል ባለቤትነት የማምረት፣ የማከፋፈል፣ አገልግሎት የመስጠት፣ ወይም ሌሎች የኢኮኖሚ ተግባሮችንና ከእነዚሁ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በንግድ መልክ ለማካሄድ በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ ወይም በሌላ ደንብ የሚቋቋም የመስተዳድሩ ድርጅት ነው፡፡
2. "ጠቅላላ ንብረት" ማለት የድርጅት የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ ድርጅቱ ገና ያልተቀበላቸው ገቢዎች፣ ጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሲሆን፣ ግዙፍ ያልሆኑ ንብረቶችን፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችንና ሌሎች ገቢ መሆን ያለባቸው ሂሳቦችን ይጨምራል፡፡
3. "የተጣራ ጠቅላላ ንብረት" ማለት ከጠቅላላ ንብረት ላይ በተያዘው የበጀት ዓመት ውስጥ የሚከፈሉ እዳዎች፣ በረዥም ጊዜ የሚከፈሉ እዳዎች፣ በቅድሚያ የተከፈሉ እዳዎችና ሌሎች እዳዎች ተቀንሰው የሚቀረው ንብረት ነው፡፡
4. "ካፒታል" ማለት አንድ ድርጅት በዚህ ደንብ፣ እንደተመለከተውና በመስተዳድሩ በማናቸውም ጊዜ የሚመደበው የተጣራ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፡፡
5. "የተጣራ ትርፍ" ማለት ከገቢዎችና ከሌሎች ክፍያዎች ከተገኘው ገንዘብ ላይ ወጪዎችና በበጀት ዓመት ውስጥ ለሥራ ማስኬጃና ደመወዝ፣ በአግባቡ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ወለድና ልዩ ልዩ ታክሶች ተቀንሰው የሚቀረው ሂሳብ ነው፡፡

6. "የመስተዳድሩ የትርፍ ድርሻ" ማለት ከተጣራ ትርፍ ላይ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳብ ገቢ የሚሆነው ገንዘብ ተቀንሶ የሚቀረው ሂሳብ ነው፡፡
7. "መስተዳድር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ነው፡፡
8. "ኦዲተር" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፩፯ በተመለከተው መሠረት የማናቸውንም ድርጅት ሂሳብ የሚመረምር የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡
9. "ምክር ቤት" ማለት የመስተዳድሩ ምክር ቤት ነው፡፡
10. "ሥራ አስፈፃሚ" ማለት የመስተዳድሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው፡፡

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>መቋቋምና ዋና ጽ/ቤት</u>

3. <u>መቋቋምና ካፒታል</u>
1. እንደየአግባቡ ድርጅት እየተባለ በጥቅል የሚጠቀስና ሕጋዊ ሰውነት ያለው
ሀ)የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ቄራዎች ድርጅት፡-
1. ጠቅላላ የተፈቀደ ሃያ አምስት ሚሊዮን አርባ አምስት ሺህ ሃምሣ ብር፣
2. በዓይነት የተከፈለ ብር አስራ ሁለት ሚሊዮን አርባ አምስት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም፣
3. በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ብር ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከስልሳ ዘጠኝ ሣንቲም

ለ) የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ሲኒማ ቤቶች ድርጅት
1. ጠቅላላ የተፈቀደ ብር አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከሰላሳ ሣንቲም፣
2. በዓይነት የተከፈለ ብር ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር ከአርባ ሣንቲም
3. የጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ብር አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አስር ብር ከአስራ ሰባት ሣንቲም

ሐ) የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ኤግዚቢሽን ማዕከል፣ እና የገበያ ድርጅት
1) ጠቅላላ የተፈቀደ ብር አስራ ሶስት ሚሊዮን ዘጠና ሰባት ሺህ አንድ መቶ አስር ብር
2) በዓይነት የተከፈለ ብር ሃያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ስድስት ብር፣
3) በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ብር ሦስት ሚሊዮን ሥልሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሠላሣ አራት ብር ያካተተ ካፒታል ኖሮት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. የእያንዳንዱ ድርጅት ዕድሜ ላልተወሰነ ጊዜ ይሆናል፡፡
3. እያንዳንዱ ድርጅት በዋና ሥራ አስኪያጁና በዚህ ደንብ መሠረት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች ወኪሎች አማካኝነት ሥራውን ይፈጽማል፣ መብት ያገኛል፣ ግዴታ ይገባል፡፡

4. የአንድ ድርጅት ዕጻዎች ሊሸፈኑ የሚችሉት ድርጅቱ ባለው ጠቅላላ ንብረት ብቻ ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተቋቋመው ወይም በሌላ ደንብ የሚቋቋም እያንዳንዱ ድርጅት የሚኖረው የተከፈለ ካፒታል መጠን ከተፈቀደው ጠቅላላ የካፒታል መጠን ፪፭ በመቶ ሊያንስ አይችልም፡፡
6. የእያንዳንዱ ድርጅት የተፈቀደ ካፒታል መጠን ድርጅቱ በተቋቋመ በአምስት ዓመት ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ ያልቃል፡፡
7. የተፈቀደው ካፒታል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ በተወሰነው ጊዜ በሙሉ ተከፍሎ ካላለቀ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሦስተኛ ወገኖችን መብት ሳይነካ የድርጅቱን ካፒታል ወደ ተከፈለው የካፒታል መጠን ዝቅ ያደርገዋል፡፡
8. የእያንዳንዱ ድርጅት ካፒታል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተወሰነው ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

   ሀ) የድርጅቱ ካፒታል እንዲቀንስ ኦዲተሮች ሃሣብ ሲያቀርቡ፣ ወይም

ለ) የድርጅቱ ቦርድ በሚያቀርበው ሃሳብ መሠረት ካፒታሉ እንዲቀንስ ሊወስን፣ ወይም

ሐ) የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ ካላለቀ ነው፡፡

4. <u>**ዋና ጽ/ቤት**</u>

የእያንዳንዱ ድርጅት ዋና ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሆኖ፣ እንደየአስፈላጊነቱ በከተማ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የእያንዳንዱ ድርጅት ዓላማዎች</u>

5. <u>**አዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ቄራዎች ድርጅት ዓላማዎች**</u>

ድርጅቱ፡-

1. ንጽሕናው በሚገባ የተጠበቀና ጤናማነቱ ተመርምሮ የተረጋገጠ የእንስሳት እርድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
2. የሥጋ ውጤቶችን አደራጅቶ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባል፡፡
3. ከተረፈ ሥጋ የሚገኙ መሠረታዊ ተፈላጊነት ያላቸው ምርቶችን በብዛትና በጥራት በማዘጋጀትና በማምረት ለሃገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል፡፡
4. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል፣ ያስከፍላል፡፡

6. <u>**የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ሲኒማ ቤቶች ድርጅት ዓላማዎች**</u>

ድርጅቱ

1. በከተማው ውስጥ ለህብረተሰቡ አዝናኝና አስተማሪ የሆኑ የፊልም ትርዒቶችን ያቀርባል፡፡
2. በከተማው ውስጥ ሲኒማ ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፡፡
3. ለትርዒት የሚውሉ ፊልሞችን ከውጭ ሃገር ያስመጣል፣ ያከፋፍላል፡፡

4. ከፊልም ስራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ስራዎችን ይሰራል፡፡
5. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል፣

7. <u>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የኤግዚቢሽን ማዕከል እና የገበያ ድርጅት ዓላማዎች</u> ድርጅቱ፡-

1. የመስተዳድሩን፣ ብሎም የሀገሪቱን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማጎልበትና ለማስፋፋት የሚረዱ ኤግዚቢሽኖችንና ባዛሮችን ያዘጋጃል ያስተናግዳል፡፡
2. የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ግኝቶችንና ሞዴሎችን፣ የምርት ናሙናዎችን፣ የታሪክ መረጃዎችን፣ የወግና የባህል ውጤቶችን ያስጎበኛል፣ ያስተዋውቃል፡፡
3. የሚመለከተውን የመስተዳድሩን አካል እያስፈቀደ የስፖርትና የመዝናኛ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡
4. ለሲምፖዚየምና ለልዩ ልዩ ስብሰባዎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡
5. በንግድና ቱሪዝም መረጃ ማዕከልነት ያገለግላል፡፡
6. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል ያስከፍላል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የወል ድንጋጌዎች</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>የድርጅት አቋምና አሠራር</u>

8. <u>የድርጅት አካላት</u>

1. እያንዳንዱ ድርጅት

   ሀ) የሥራ አመራር ቦርድ፣

   ለ) ዋና ሥራ አስኪያጅ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ እና

   ሐ) ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
2. የስራ አመራር ቦርድ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪ ይሆናል

9. <u>የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ ፩0(፩) (ለ) እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርድ አባላትን ይመድባል፣ ያነሳል፡፡
2. ከሚመድባቸው አባላት መካከል የቦርዱን ሊቀመንበር ይሾማል፡፡
3. ለቦርድ አባላት የሚከፈል አበልና ማበረታቻ በመመሪያ ይወስናል፡፡ እንዲሁም የእያንዳንዱን ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የደሞዝ ጣሪያ የሚያመለክት ደረጃ በመመሪያ ይወስናል፡፡
4. የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል
5. የድርጅቱን መነሻ ካፒታል በምክር ቤት ያስመድባል፡፡
6. የየድርጅቱ ካፒታል እንዲቀንስ ወይም ከመስተዳድሩ ገንዘብ በማስመደብ ወይም የድርጅቱን ገቢ በማሳደግ የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ይወስናል፡፡

7. የእያንዳንዱ ድርጅት የተፈቀደ ካፒታል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫(፮) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ እንዲያልቅና የመጠባበቂያ ሂሳቦች እንዲያዙ፣ ወይም ከመስተዳድሩ ገንዘብ እንዲመደብ ያደርጋል፡፡
8. በቦርድ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ከተጣራው ትርፍ ውስጥ በየዓመቱ ለመስተዳድሩ ፈሰስ ሊደረግ የሚገባውን መጠን ይወስናል፡፡
9. የየድርጅቱን ሂሳብ ሪፖርትና የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ያፀድቃል፡፡
10. በቦርድ የሚቀርብለትን የድርጅት የኢንቨስትመንት ዕቅድ ያፀድቃል፡፡
11. አስፈላጊ ሲሆን ድርጅት እንዲፈርስ፣ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ፣ ወይም እንዲከፋፈል፣ ወይም እንዲሸጥ ለምክር ቤቱ ሃሳብ እያቀረበ ያስወስናል፡፡
12. ከቦርድ ኃላፊ ጋር በመመካከር የድርጅት ዓመታዊና አጠቃላይ ግቦችን ያፀድቃል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፡፡
13. ለቦርድ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመስተዳድሩን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡
14. የሦስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ፣

ሀ) ማናቸውም ድርጅት በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ማህበር ሆኖ እንዲቋቋም ይወሰናል፡፡

ለ) ማናቸውም ድርጅት እንዲሸጥ፣ወይም በሌላ አኳኋን ድርጅቱ ወይም ማኔጅመንቱ እንዲተላለፍ ይወሰናል፡፡ በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ውሳኔ መስተዳድሩ በድርጅቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት የሚያሳጣ በሚሆንበት ጊዜ ለምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ በሚወጣ ደንብ መሠረትም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

15. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፬(ሀ) መሠረት በሚቋቋም የንግድ ማህበር በመንግስት የተያዘ አክስዮን እንዲሸጥ ይወስናል፡፡
16. በእያንዳንዱ ድርጅት ገንዘብ ወጪ የሚደረግበትንና ሽያጭም ሆነ ግዢ የሚፈፀምበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፡፡
17. የድርጅቶች ሥራ ክትትል እና ማስተባበር በተለየ ክፍል እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ የክፍሉን ዝርዝር ኃላፊነትና ተግባር በመመሪያ ይወስናል፡፡
18. ይህን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

10. <u>የሥራ አመራር ቦርድ</u>

1. <u>አመሰራረት</u>

ሀ) የቦርዱ አባላት ቁጥር ቢያንስ አምስት፣ ቢበዛ ሰባት ይሆናል፡፡

ለ) ከቦርድ አባላት መካከል ከአንድ ሦስተኛው የማይበልጡት በሠራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ፡፡

ሐ) የቦርድ አባላት፣ ሊቀመንበሩን ጨምሮ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመደባሉ፡፡

መ) የቦርድ አባላት ምርጫና ምደባ በሙያ፣ በሥራ ልምድና በብቃት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

ሠ) ማንኛውም የቦርድ አባል ተወዳዳሪ ያልሆነ የሌላ ድርጅት ቦርድ አባል ሆኖ እንዲሠራ ሊመደብ ይችላል፡፡

ረ) የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ከ፫ ዓመት የማያንስ፣ ከ፭ዓመት የማይበልጥ ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሲሆን አንድ የቦርድ አባል የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ እንደገና ሊመደብ ወይም ሊመረጥ ይችላል፡፡

ሰ) የቦርድ የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣነት ይኖረው ዘንድ፣ የአባላቱ፣ የሥራ ዘመን ማብቂያ በአንድ ወቅት አይሆንም፡፡

ሸ) ማንኛውም የቦርድ አባል የቦርድ አባልነቱን የለቀቀ እንደሆነ፣ ቦርዱ አባልነቱን የለቀቀው አባል በተመደበው አኳኋን ተተኪ አባል እንዲመድብ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማሳሰቢያ ያቀርባል፡፡

ቀ) ለሥራው ተገቢ ላለመሆኑ በቂ ምክንያት ሲኖር፣ አንድን የቦርድ አባል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማንኛውም ጊዜ ሊያነሳው ይችላል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሠራተኛ በሚመረጥ የቦርድ አባል ላይም ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የሠራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ መረጃ እንዲደርሰው ተደርጎ ተተኪ አባል ሊመርጥ ይችላል

2. <u>የቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>

<u>ቦርዱ</u>

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ መሠረት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መቅረብ ከሚገባቸው በስተቀር የድርጅቱን የፖሊሲ ጉዳዮችን ይወስናል፡፡

ለ) የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፣ ያሰናብታል፡፡

ሐ) ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት እንዲሁም ደመወዝና አበል ይወስናል፡፡

መ) የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና ውስጠ ደንቦችን ያፀድቃል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፡፡

ሠ) የድርጅቱን የረዥም ጊዜ ብድሮችና ክሬዲቶች ያፀድቃል፡፡

ረ) በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የገንዘብ ወጪ ይፈቅዳል፣ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን የቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፡፡

ሰ) የድርጅቱ ሂሳቦች ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፡፡

ሸ) ለተመደቡ ኦዲተሮች የድርጅቱ የሂሳብ መዝገቦች መቅረባቸውን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስለድርጅቱ ሥራ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎችን ያቀርባል፡፡

ቀ) የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

በ) በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወሰነው ደረጃ መሠረት የዋና ሥራ አስኪያጅን የደመወዝ ጣሪያ ተከትሎ የበታች ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን የደመወዝ እርከን የድርጅቱን አደረጃጀት ይወስናል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡

ተ) የቦርድ አባላት ተግባራቸውን በጥንቃቄ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ውሳኔው ትክክል አይደለም ተብሎ በድምጽ የተለየ የቦርድ አባል ውሳኔው ለሚያስከትለው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

3. <u>**የቦርድ ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**</u>

ቦርድ

ሀ) ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

ለ) አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከቦርድ አባላት መካከል ቢያንስ ሁለት አባላት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ቦርዱን ሊቀመንበሩ ይሰበስባል፡፡

ሐ) የስብሰባው አጀንዳ በቅድሚያ ለአባላቱ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

መ) ከአባላቱ አብዛኞቹ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

ሠ) ውሳኔ በድምጽ ይወክላልጫ ይተላለፋል፡፡ ድምጹ እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

ረ) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በቦርድ ስብሰባ ላይ ሊገኝ ይችላል፡፡

ሰ) በየስብሰባው በተገኙት አባላት የሚፈረም ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፡፡ ለዚህም ዓላማ ከድርጅቱ ሠራተኞች መካከል ቃለ-ጉባኤ የሚይዝ ፀሐፊ ይመደባል፡፡

ሸ) የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. <u>**የድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**</u>

የእያንዳንዱ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ለድርጅቱ ቦርድ ተጠሪ ሆኖ

1. የድርጅቱን ሥራ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
2. ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነትና ድርጅቱ በሚያቀርባቸው ክሶች ድርጅቱን ወክሎ ይሰራል፡፡
3. በቦርድ በሚወሰነው መሠረት ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ተግባራቸውን ይወስናል፡፡
4. በድርጅቱ ውስጠ ደንብና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሌሎች ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዝና አበላቸውን ይወስናል፡፡
5. የድርጅቱን ሂሳቦች በአግባቡ ይይዛል፣ ለድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፡፡

6. ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ የሚውል የአጭር ጊዜ ብድር ውል ይዋዋላል፣ ቦርዱን በማስፈቀድ የረዥም ጊዜ ብድር ይበደራል ለእነዚህ አላማዎች ቦርዱን እያስፈቀደ የድርጅቱን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ሊሰጥ ይችላል፡፡
7. የድርጅቱን ሥራ ፕሮግራምና በጀት፣ እንዲሁም ውስጠ ደንብ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
8. በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወጣ መመሪያ መሠረት በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን የድርጅቱን ቋሚ ንብረቶች ይሸጣል፣ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፡፡
9. የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፡፡
10. ቦርዱ በሚወስነው ሁኔታ ሪፖርት ያቀርብለታል፡፡
11. አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መጠን ስልጣንና ተግባሩን ለድርጅቱ ሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል፡፡
12. በሥራው የሚመክርና በሥራ ግምገማዎች፣ በእቅዶችና ውሳኔዎች ላይ የሚወያይ የማኔጅመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባውንም ይመራል፡፡
13. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ይፈፅማል፡፡
14. ተግባሩንም በሚፈጽምበት ጊዜ በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለድርጅቱ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና ምርመራ

12. **የድርጅት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት**

ማናቸውም ድርጅት በንግድ አሠራር ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

13. **የሂሳብ ዓመት፣ ሂሳብ መዝጋትና ዓመታዊ ሪፖርት**

1. የአንድ ድርጅት የሂሳብ ዓመት በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወስናል፡፡
2. ማናቸውም ድርጅት ቢያንስ በዓመት ሂሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መዘጋት አለበት፡፡
3. ማናቸውም ድርጅት ስላለፈው ዓመት የድርጅቱ ሥራዎችና አቋሞች ሁኔታ፣ ስለተከናወኑ ተግባሮችና በቅርብ ሥራ ላይ ሊውሉ ስለታሰቡ ዋና ዋና እቅዶችና ፕሮግራሞች ጭምር ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የድርጅትን ሂሳብ በወቅቱ አለመዝጋት የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

5. የሂሳብ ዓመት ከተዘጋ በኋላ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ፕሮራም መሠረት የተዘጋው ሂሳብ በዓመቱ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰየም የውጭ ኦዲተር ይመረመራል፡፡

14. <u>ስለመጠባበቂያ ሂሳቦችና አጠቃቀም</u>

1. እያንዳንዱ ድርጅት ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ይኖረዋል፡፡
2. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ የተወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እያንዳንዱ ድርጅት ከተጣራ ትርፉ ላይ ፭% (አምስት በመቶ) በየአመቱ እያነሳ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ የድርጅቱ ካፒታል ፪0% (ሃያ በመቶ) እስኪያህል ድረስ ወደ መጠባበቂያ ሂሳብ ይሰበሰባል፡፡
3. ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ

   ሀ) ኪሳራን ለመሸፈን፣

   ለ) ያልታሰቡ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን ሊውል ይችላል፡፡
4. የእያንዳንዱ ድርጅት ቦርድ ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴን እያስፈቀደ ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች እንዲያዙ ለማድረግ አቋማቸውን ለመወሰን ይችላል፡፡

15. <u>ስለግብርና ቀረጥ ክፍያ</u>

1. የግብርና ቀረጥ ክፍያን በተመለከተ አግባብ ያላቸው ህጎች በድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. እያንዳንዱ ድርጅት በሌላ ሕግ መሠረት ከግብርና ከቀረጥ ነፃ ለሚሆን ያለውን መብትና ሌላም ይህ ደንብ አያስቀርበትም፡፡

16. <u>የመስተዳድሩ የትርፍ ድርሻ ክፍያ</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ድርጅት የሂሳብ ዓመቱ ከተፈጸመበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት (፯) ወራት ውስጥ የመስተዳድሩን የትርፍ ድርሻ ለመስተዳድሩ ፈሰስ ያደርጋል፡፡

17. <u>የኦዲተሮች አመዳደብ</u>

1. በሕግ ለመስተዳድሩ ኦዲትና ቁጥጥር መስሪያ ቤት የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የየድርጅቱ ሂሳብ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡
2. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በፌደራል ዋና ኦዲተርና በመስተዳድሩ ኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት የወጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉና ከማንኛውም ዓይነት ተጽዕኖ ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

18. <u>ሂሳብ የማስመርመር ግዴታ</u>

የተመርማሪውን ድርጅት ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም የሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠይቅ ሂሳቡን የማስመርመር አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

19. <u>የኦዲተሮች ሥልጣን፣ ተግባርና ተጠያቂነት</u>

በልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፪፭/፩፰፰፬ አንቀጽ ፫፬ በተደነገገው መሠረት የንግድ ሕግ ቁጥር ፫፯፫፣፫፯፬፣፫፯፭፣፫፯፮፣፫፯፯፣፫፰0 አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎባቸው የኦዲተሮችን ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለድርጅት መዋሐድና መከፋፈል

### 20. መሠረቱ

1. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ድርጅቶች እንደየአግባቡ አንዱ ሌላውን በመጠቅለልም ሆነ አንድ ሌላ አዲስ ድርጅት በመፍጠር እንዲዋሐዱ ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ ሊደነገግ ይችላል፡፡
2. አንድ ድርጅት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አዲስ ድርጅቶች እንዲሆን በምክር ቤቱ በሚወጣ ደንብ መሠረት ሊከፋፈል ይችላል፡፡

### 21. የወል ድንጋጌዎች

1. ከአበዳሪ ድርጅት ጋር የብድር ስምምነት አድርጎ እዳው ገና ያልተከፈለ ድርጅት ከመዋሀዱ ወይም ከመከፋፈሉ በፊት የአበዳሪውና የዋስትና ሰጪውን ስምምነት መጠየቅ አለበት፡፡
2. አንድ ለማዋሀድ ወይም ለመከፋፈል የታሰበ ድርጅት እዳ ያለበት ከሆነና በገንዘብ ጠያቂዎች በኩል የሚፈለግበትን ግዴታ ለመፈጸም የማይችል ከሆነ መዋሀዱም ሆነ መከፋፈሉ አይፈቀድም፡፡
3. የሚዋሀዱት ድርጅቶች ወይም የሚከፋፈለው ድርጅት ካለፈው የሂሳብ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ መዋሀዱ ወይም መከፋፈሉ እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሂሳብ ይዘጋል፣ በኦዲተርም ይመረመራል፡፡

### 22. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

1. በመዋሀድ ምክንያት ሕልውናውን የሚያጣው ድርጅት መብትና ግዴታ ወደሚጠቀልለው ወይም በመዋሀድ ወደሚፈጠረው አዲስ ድርጅት ይተላለፋል፣
2. የሚከፋፈል ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪፫ በተመለከተው የመብትና ግዴታ ምደባ መሠረት በመከፋፈሉ ወደሚፈጠሩት አዲስ ድርጅቶች ይተላለፋሉ፡፡

### 23. የሚከፋፈል ድርጅት መብትና ግዴታ አመዳደብ

1. በመከፋፈል ላይ ያለ ድርጅት

ሀ) መብትና ግዴታው በመከፋፈል ወደሚፈጠሩ ድርጅቶች የሚመደበው በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

ለ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የድርጅቱን መከፋፈል ውሳኔ የያዘና መብትና ግዴታው በመከፋፈል በተፈጠሩት ድርጅቶች መካከል እንዴት እንደተመደበ የሚያሳይ የተሟላ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

ሐ) የሪፖርቱ አንድ ቅጂ በመከፋፈል የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት በሚቋቋምበት ጊዜ ለምክር ቤት ይቀርባል፣ በመከፋፈሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅትም አንድ ቅጂ ይሰጠዋል፡፡

መ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሪፖርቱን ዋና ዋና ነጥቦች የያዘ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ በመከፋፈል የተፈጠሩት ድርጅቶች ሁሉ የተከፋፈለው ድርጅት ለሦስተኛ ወገኖች የገባውን ግዴታ በሚመለከት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ስለ ድርጅት መፍረስና ሂሳብ ስለማጣራት

### 24. ድርጅት የሚፈርስባቸው ምክንያቶች

ማናቸውም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡፡

1. ድርጅቱ የተቋቋመበት ሥራ ሲያልቅ፣
2. ድርጅቱ የተቋቋመበት አላማ ሲከሽፍ ወይም ሊፈፀም የማይችል ሲሆን፣
3. ከመቶ ሰባ አምስት (፸፭%) የሚሆነው የተከፈለው የድርጅቱ ካፒታል ሲጠፋ፣
4. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የድርጅቱን ሕልውና የሚነካ ውሳኔ ሲሰጥና በም/ቤት ሲጸድቅ ወይም
5. የድርጅቱ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን፡፡

### 25. በኪሳራ ጊዜ ስለሚደረግ ሂሳብ ማጣራት

1. የመክሰር ስርዓትን በሚመለከት በልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፪፭/፩፱፰፬ አንቀጽ ፬0 በተደነገገው መሠረት የንግድ ሕግ ፭ኛ መጽሐፍ ድንጋጌዎች አስፈላጊ ለውጥ ተደርጎባቸው በእያንዳንዱ ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. በንግድ ሕግ ቁጥር ፩፩፺፺(፩ እና ፪) የተደነገገው ቢኖርም ፍርድ ቤት የድርጅት መክሰር የሚጣራበት ሁኔታ በንግድ ሕግ መሠረት በአጭር ሥነ-ሥርዓት እንዲመራ ሊወስን ይችላል፡፡

### 26. ስለሂሳብ አጣሪዎች ሹመት፣ ተግባርና ሥልጣን

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪፺(፩) እስከ (፬) የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በመስተዳድሩ ኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት የወጣውን መመዘኛ የሚያሟላ እና የድርጅቱ ሠራተኛ ያልሆነ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሂሳብ አጣሪዎች ይሾማል፡፡ በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አጣሪዎችን ይሽርና በምትካቸው ሌሎችን ይሾማል፡፡
2. ሂሳብ አጣሪዎች በመፍረስ ላይ ያለውን ድርጅት መዝገቦችና ሂሳቦች ይረከባሉ፡፡
3. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሂሳብ አጣሪዎች የድርጅቱን ንብረት በኃላፊነት ይይዛሉ፣ በሥራ አፈፃፀማቸው በዚህ ደንብ ለቦርዱና ለዋናው ሥራ አስኪያጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፣ ሆኖም ግዴታቸው ያላለቀ ውሎችን ለመፈፀም ወይም የሂሳብ ማጣራቱን ተግባር ለማሳካት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር አዲስ ሥራ መጀመር አይችሉም፡፡

4. ቦርዱ ካለፈው የሂሳብ ምርመራ መጨረሻ ጀምሮ የሂሳብ ማጣራት ተግባር እስከተጀመረበት ቀን ያለውን ጊዜ የሚሸፍንና ስለድርጅቱ አቋም የሚገልፅ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሂሳብ አጣሪዎች ይሰጣል፡፡
5. ሂሳብ አጣሪዎችና ቦርዱ የድርጅቱን መብቶችና ግዴታዎች ባጭሩ የያዘ መግለጫ በጋራ አዘጋጅተው ይፈርሙበታል፡፡
6. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በቀር ቦርዱና ዋናው ሥራ አስኪያጅ ሂሳብ አጣሪዎቹን በሥራቸው ይረዷቸዋል፡፡

27. <u>ባለገንዘቦችን ስለመጥራት</u>

1. ሂሳብ አጣሪዎች ድርጅቱ የሚፈርስ መሆኑንና ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ በማስረጃ በማስደገፍ እንዲቀርቡ ለባለገንዘቦች ያስታውቃሉ፡፡
2. ስማቸው በድርጅቱ መዝገብ ተይዞ ለሚገኙት በሌላ ሁኔታ ለታወቁ ባለገንዘቦች ማስታወቂያ በሪኮማንዴ ይሰጣቸዋል፡፡ ሌሎች ባለገንዘቦች  በአዲስ ልሳን ጋዜጣ በየሳምንቱ በሚወጡ ሦስት ተከታታይ ማስታወቂያዎች እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ ባለገንዘቦቹ እንደነገሩ ሁኔታ ደብዳቤ ከደረሳቸው ወይም የመጨረሻ የጋዜጣ ማስታወቂ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዘጠና (፱0) ቀን ውስጥ የገንዘብ ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ ይጠበቃሉ፡፡
3. ሂሳብ አጣሪዎች ስለድርጅቱ የሂሳብ አቋም መግለጫ አዘጋጅተው ስለእዳው አከፋፈል ያላቸውን ሂሳብ፣ የባለገንዘቦችን ዝርዝርና የአከፋፈሉን ቅደም ተከተል (የሚኖር ከሆነ) በመጨረሻ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባሉ፡፡
4. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሂሳብ አጣሪዎች ያዘጋጁትን ሂሳብ አቋም መግለጫ መሰረት በማድረግና ስለእዳው አከፋፈል ያቀረቡትን ሀሳብ በማመዘን፣

ሀ) የገንዘብ ጥያቄዎችን በማስረጃ በማስደገፍ ላቀረቡ ባለገንዘቦች ክፍያ እንዲፈፀም ይፈቅዳል፡፡

ለ) የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ ለባለገንዘቦች መከፈል ያለበትን እዳ የማይሸፍን ሆኖ ሲገኝ የሦስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ በሚያፀድቀው የሽያጭ ዘዴ አማካይነት የድርጅቱን ንብረቶች ሂሳብ አጣሪዎች እንዲሸጡ ይፈቅዳል፡፡

5. የድርጅቱ ጠቅላላ ንብረት እዳውን ለመክፈል በቂ በማይሆንበት ጊዜና የተፈቀደው ካፒታል በሙሉ ሳይከፈል ከቀረ ሂሳብ አጣሪዎች ቀሪ ሂሳብ እንዲከፈል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ይጠይቃሉ፡፡

28. <u>የባለገንዘቦችን መብት ስለመጠበቅ</u>

1. የታወቁ ባለገንዘቦች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄያቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ፣ ሊከፈላቸው የሚገባ ገንዘብ በሕግ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እስኪያበቃ ድረስ በባለገንዘቦቹ ስም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል፡፡

2. ባልተጠናቀቁ የድርጅቱ ሥራዎች መነሻነት የሚቀርቡ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ፣ ወይም ባለገንዘቦች ዋስትና ያልተሰጣቸው ከሆነ ክርክር ያስነሱ ዕቃዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ክርክሩ እስከሚወሰን ድረስ ለብቻ ተቀማጭ ሆኖ ይያዛል፡፡
3. በድርጅት መዝገብ ያልታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች የገንዘብ ጥያቄያቸውን በአንቀጽ ፪፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተወሰነው ጊዜ ያላቀረቡት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ በትርፍነት ለመስተዳድሩ ከገባው ሀብት ላይ እንዲከፈላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በሂሳብ አጣሪዎች ቸልተኝነት ምክንያት ያልተከፈላቸው ባለገንዘቦች ሂሳብ አጣሪዎችን በኃላፊነት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## 29. <u>የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫ እና የመፍረስ ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

1. ባለገንዘቦች ከተከፈላቸውና ሊቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪፰ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት ተቀማጭ ከሆነ በኋላ ሂሳብ አጣሪዎች ድርጅቱ ትርፍ ሀብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና የዕዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባሉ፡፡ እንዲሁም ለመስተዳድሩ ፋይናንስ ቢሮና ለመስተዳድሩ ኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት ግልባጭ ያደርጋሉ፡፡
2. የኦዲትና ቁጥጥር መ/ቤት የሚሰጠው አስያየት ካለው ወዲያውኑ ለመስተዳድሩ ፋይናንስ ቢሮና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የፋይናንስ ቢሮን ስምምነት በማግኘት የመጨረሻውን የሀብትና የዕዳ መግለጫ ሲያፀድቀው ወዲያውኑ ድርጅቱ እንዲፈርስ መወሰኑን በመግለጽ ለምክር ቤት የደንብ ረቂቅ ያቀርባል፡፡
3. በሚወጣ ደንብም ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ ተሽሮ የድርጅቱ ሕልውና ያበቃል፡፡
4. የፈረሰ ድርጅት የሂሳብ ተዛማጅ መዝገቦች በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ጽ/ቤት ተቀምጠው ለ፩0 ዓመት ይቆያሉ፡፡ እነዚህን መዝገቦች ለማየት የሚፈልጉ ሰዎችም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል መመርመር ይችላሉ፡፡

## 30. <u>ለመስተዳድሩ ገቢ ስለሚሆን ሀብት</u>

ፈርሶ ሂሳብ የተጣራ ድርጅት ትርፍ ሀብት ለፋይናንስ ቢሮ ገቢ ይሆናል፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## 31. <u>ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተደረጉ እንቅስቃሴዎች</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከ (ሀ)-(ሐ) የተቋቋሙት ድርጅቶች ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ያከናወኗቸው ተግባሮች በዚህ ደንብ ሕጋዊ ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

## 32. <u>ስለሌሎች ህጎች ተፈፃሚነት</u>

በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕግና የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 33. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከዛሬ ከመጋቢት ፳ ቀን ፩፱፱፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## ደንብ ቁጥር ፳፬/፲፱፻፺ ዓ.ም

## የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሕዝብ ት/ቤቶችን አመራር አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ

<u>ማውጫ</u>


ጠቅላላ

፪. አጭር ርዕስ

፫. የአፈፃፀም ወሰን

፬ የሕግ ሰውነት

፭ ስለ ሕዝብ ት/ቤት ኮሚቴ መቋቋም

፮ የሕዝብ ት/ቤት ኮሚቴ አባሎች

፯ የተማሪዎችና የሠራተኛው ተወካይ ምርጫ አፈፃፀም

፰. የኮሚቴው የሥራ ዘመንና አመራር ኮሚቴው፤

፱. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

፲. የመሰብሰቢያ ጊዜና ምልዓተ ጉባዔ

፲፩. የኮሚቴው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

፲፪. የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

፲፫. የኮሚቴው ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

፲፬. የኮሚቴው ሂሳብና ንብረት ተቆጣጣሪ ስልጣንና ተግባር

፲፭. የሕዝብ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ስልጣንና ተግባር

፲፮. የትምህርት ቢሮው ስልጣንና ተግባር

፲፯. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ


አጭር መግለጫ

የግል ትምህርት ቤቶችን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፷፲ መሰረት የሕዝብ ሀብት የተደረጉትን ት/ቤቶች እና በቀጣይ በሕዝብ የተቋቋመ ት/ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር አወቃቀር ጋር ለማጣጣምና የሕዝብ ት/ቤቶችን አደረጃጀት እንደገና ለመወሰን የወጣ ደንብ ነው፡፡፤

# <u>ደንብ ቁጥር ፳፬/፲፱፻፺፫ ዓ.ም</u>

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሕዝብ ት/ቤቶችን አመራር አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ</u>

የግል ትምህርት ቤቶችን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፷፯ መሰረት የሕዝብ ሀብት የተደረጉትን ት/ቤቶች እንዲሁም ከዚህ ወዲህ በሕዝብ የተቋቋመ ት/ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር አወቃቀር ጋር እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉ፣

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሚገኙ የሕዝብ ት/ቤቶች አደረጃጀት እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የት/ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ለማጠናከር በአዋጁ ቁጥር ፪፻፲፯/፲፱፻፺፪አንቀጽ ፫ ለከተማ መስተዳድር ምክር ቤቶች በሰጠው ሥልጣን መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

<u>ጠቅላላ</u>

<u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሕዝብ ት/ቤቶችን አመራርና አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፳፬/፲፱፻፺፫ ዓ/ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.<u>ትርጓሜ</u>

፩ “የሕዝብ ት/ቤት” ማለት የግል ት/ቤቶችን የህዝብ ሀብት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፷፯ ዓ/ም አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የሕዝብ ሀብት የሆነ ወይም ከዚያ ወዲህ በሕዝብ የተቋቋመ ት/ቤት ነው፡፡

፪ “ወላጅ” ማለት በሕዝብ ት/ቤት የሚማር የራሱ፣ በሞግዚትነት፣ በአስተዳዳሪነት ወይም በኃላፊነቱ እያሳደገ የሚያስተምረው ልጅ ያለው ነው፡፡

፫ “የውስጥ ገቢ” ማለት ከቀን ተማሪ፣ ከማታ ትምህርት፣ ከምርት ሽያጭ፣ ከኪነጥበባትና ከመሳሰሉት የሚገኝ ገቢ ነው፡፡

፬ “ትምህርት ቢሮ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

፭ “መስተዳድር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ነው፡፡

፮ “መምህር” ማለት በሕዝብ ት/ቤት በመምህርነት ተቀጥሮ የሚሰራ ነው፡፡

፯ “የወላጅ ኮሚቴ” ማለት ሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች ስብሰባ የአመራር አካል ነው፡፡

፰ “ሠራተኛ” ማለት በሕዝብ ት/ቤት ከመምህርነት ውጭ በሌሎች የሥራ ምድቦች ለመሥራት ተቀጥሮ የሚሰራ ነው፡፡

፱ "ኮሚቴ" ማለት የሕዝብ ት/ቤት የአስተዳደርና አመራር ኮሚቴ ነው፡፡

፲ "የወረዳ ትምህርትና የሥልጠና አመራር ቦርድ" ማለት በመስተዳድሩ በየወረዳው አስተዳደር ሥር የተቋቋመ የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ነው፡፡

<u>፫. የአፈፃፀም ወሰን</u>

ይህ ደንብ ተፈፃሚነት የሚኖረው በሕዝብ ት/ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡

<u>፬ የሕግ ሰውነት</u>

. እያንዳንዱ የሕዝብ ት/ቤት የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

<u>፭ ስለ ሕዝብ ት/ቤት ኮሚቴ መቋቋም</u>

፩ እያንዳንዱ የሕዝብ ት/ቤት የሕዝብ ት/ቤት ኮሚቴ እየተባለ የሚጠራ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

፪ የሕዝብ ት/ቤት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው የትምህርት ሥልጠና አመራር ቦርድ ይሆናል፡፡

<u>፮ የሕዝብ ት/ቤት ኮሚቴ አባሎች</u>

የኮሚቴው አባላት በተደጋጋሚ የመምረጥ መብት ያላቸው ሆኖ፣

፩ ት/ቤቱ የሚገኝበት የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ከአባላቱ መካከል ወይም ከወረዳው ነዋሪ የሚወክለው ሰብሳቢ፣

፪ ከወላጆች ኮሚቴ የሚወከሉ ፩ ም/ሰብሳቢና ፪ አባላት

፫ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ፀሐፊ፣

፬ የት/ቤቱ ም/ርዕሰ መምህር አባል፣

፭ ከተማሪዎቹ መካከል የሚመረጥ በችሎታውና በጠባዩ እንዲሁም በዕድሜው ብስለት ያለው ፩ ተወካይ ተማሪ አባል፣

፮ ከመሰረታዊ የመምህራን ማህበር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚወከሉ ፩ የሂሳብና ፩ ንብረት ተቆጣጣሪ አባል፣፯ የሠራተኞች ተወካይ ፩ አባል፣

፰ ት/ቤቱ የሚገኝበት የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል ወይም ከቀበሌ ነዋሪ የሚወክለው ፩ አባል ናቸው፡፡

<u>፯ የተማሪዎችና የሠራተኛው ተወካይ ምርጫ አፈፃፀም</u>

ምርጫው የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው በሚገኝበት የሚከናወን ሆኖ የምርጫው አፈፃፀም እንደሚከተለው ይሆናል፣

፩. በትምህርታቸው፣ በጠባያቸው፣ በአስተሳሰባቸው፣ በዕድሜያቸውና በብስለታቸው ከየሴክሽኑ አንዳንድ ተማሪዎች ይመረጣሉ፡፡ ከተመረጡት ተማሪዎች መካከል በድምጽ ይወክላልጫ የሚመረጠው ፩ ተማሪ ይወክላል፣

፪. የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ከመካከላቸው በድምጽ ይወከላል፣ አንድ ሰው ይወክላሉ፡፡ ሆኖም ተወካዩ ኃላፊነቱን በአግባቡ ካልተወጣ ሰራተኞች እርሱን በሌላ መተካት ይቻላል፡፡

<u>፰. የኮሚቴው የሥራ ዘመንና አመራር</u>

<u>ኮሚቴው፤</u>

፩. የአገልግሎት ዘመኑ ፪ ዓመት ይሆናል፤

፪. ማናቸውንም ውሳኔ የሚያስተላልፈው በጹምጽ ይወክላል፣ ይሆናል፡፡ አባሎች የሚሰጡት ድምጽ እኩል ለእኩል ለሁለት የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፫. የእራሱን የውስጥ የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤

፬. የኮሚቴው የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ የአባላቱ የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት በማንኛውም ጊዜ ለትምህርት ሥራ ሲባል የወረዳው የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ የኮሚቴው አባላት ለተወከሉባቸው ክፍሎች በማሳወቅ በምትካቸው ሌሎች እንዲተኩ ያደርጋል፡፡

፱. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው፤

፩.ት/ቤቱ በሥነ ሥርዓትና በሚገባ ሥራውን ማከናወኑን ይቆጣጠራል፤

፪. ርዕሰ መምህሩ በሚያወጣው ፕሮግራም መሰረት በት/ቤቱ ውስጥ የሚካሄደውን የተጓዳኝ ትምህርት ሥራ ያማክራል፣ ይረዳል

፫. ከወረዳ ት/ቤቶች ጽ/ቤትና ከወረዳው የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ጋር ተወያይቶ የትምህርት ክፍያ በወላጆች ስብሰባ ያስወስናል፤

፬. የትምህርት ቤቱ ንብረት በሚገባ እንዲጠበቅ ከመንግሥት የሚሰጠው ድጋፍ በሚገባ በሥራ ላይ እንዲውል እና ልዩ ልዩ ገቢዎችም ለት/ቤቱ ሥራ ጠቀሜታ ላለው ተግባር ብቻ መዋላቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤

፭ የት/ቤቱ አጠቃላይ ዓመታዊ እቅድና በጀት በመምህራንና ሠራተኞች ጠቅላላ ጉባኤ ተገምግሞ በር/መምህሩ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፡፡ የፀደቀውን ዕቅድና በጀት የወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤትና የወረዳው የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ እንዲያውቁት ያደርጋል

፮ ት/ቤቱ የሚያወጣውን ፕሮግራም ለማስፈፀም ሕብረተሰቡ ሁለገብ ድጋፍ እንዲያደርግ የአካባቢውን ሕዝብና ባለሙያዎች ያስተባብራል፤

፯. ት/ቤቱ የሚያድግበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡

በወረዳው የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ እውቅና መሰረት እርዳታ ወይም ስጦታ ይቀበላል፤

፰. የት/ቤቱ ንብረት መሸጥ፣ መለወጥ፣ ማከራየት ወይም በስጦታ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት የሚችለው የትምህርት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ብቻ ይሆናል፡፡

፱. ለት/ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች የእቅድ አፈፃፀምና ክትትል ሪፖርት አቅርቦ ያስገመግማል፤ ውጤቱንም በየሴሚስተሩና በዓመቱ የትምህርት ካሌንደር መጨረሻ ለወላጆች ለወረዳው የትምህርትና የሥልጠና አመራር ቦርድ እንዲሁም ለወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤት ያስተላልፋል፤

፲. በትምህርት ቢሮው መመሪያ መሰረት በት/ቤቱ የሥርዓተ ትምህርት ኮሚቴ እንዲሁም የሥነ ሥርዓት ትምህርት ኮሚቴ እንዲሁም የሥነ ሥርዓትና ዲስፕሊን ኮሚቴና እንዲሁም የመምህራን የደረጃ ዕድገት ኮሚቴ መቋቋማቸውን ይከታተላል፡፡

፲፩. በት/ቤቱ ውስጥ ዴሞክራዊያዊ አስተዳደር፣ አመራርና አሰራር፣ እንዲሁም የመስተዳድሩ መርሐ ግብር በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤በተግባር መተርጎሙንም፤ የከታተላል ይቆጣጠራል ፤፤

፲፪. ከወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤት ጋር በመሆን ከት/ቤቱ ቋሚ የሕዝብ ቅጥር መምህራን መካከል ተፈላጊውን የሙያ መስፈርት የሚያሟሉትን ለርዕሰ መምህርነትና ለም/ርዕሰ መምህርነት መርጦ ይመደባል፡፡ ከት/ቤቱ መምህራን መካከል ለቦታው የሚመጥን ካልተገኘ ከወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር ያስመድባል፡፡

፲፫. የመምህራንና ሠራተኞች ደመወዝና ደረጃ ዕድገት ትምህርት ቢሮ የሕዝብ ት/ቤቶችን የገቢ ልዩነት እና የትምህርት ጥራትን የመጠበቅ መርሆን ተከትሎ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሰጣል፡፡

፲፬. በወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤት በኩል የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤ የት/ቤቱ የገንዘብ አወጣጥና ዝውውር የት/ቢሮው የያወጣውን መመሪያ የተከተለ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፲፭. ለሠራተኛውና ለመምርሩ በት/ቤቱ በኩል የሠራተኛውን የመምህሩ ደመወዝ በመቶ ፯ እንዲሁም ከሠራተኛው ከመምህሩ ደመወዝ በመቶ ፬ በማዋጣት የመጠባበቂያ ሂሳብ /ፕሮ ቬደንት ፈንድ/ ባንክ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

፲፮.በትምህርት ቢሮ መመሪያ መሰረት መምህራንና ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ እንዲሁም የት/ቤቱ የሥነ ሥርዓትና የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚሰጠውን የውሳኔ ሃሳብ ያፀድቃል፤ ይሽራል፣ ያሻሽላል፡፡

፲. <u>የመሰብሰቢያ ጊዜና ምልዓተ ጉባዔ</u>

፩. ኮሚቴው ቢያንስ በወር ፩ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡

፪. የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ወይም ከኮሜቴው አባሎች ከግማሽ በላይ ኮሚቴው እንዲሰበሰብ ከጠተየቁ በማናቸውም ጊዜ ጥሪ ይደረጋል፡፡

፫. ኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ሲገኙ ይሆናል፣

፬. የመምህራን ወይም የሠራተኞች ቢያንስ አንድ ተወካይ ባልተገኘበት የሚወሰን ውሳኔ ተግባራዊ አይሆንም፡፡

፲፩. <u>የኮሚቴው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

የኮሚቴው ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለኮሚቴው ሆኖ፤

፩. የኮሚቴውን ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራል፤ ውሳኔዎችም በተግባር እንዲተረጎም ያደርጋል፡፡

፪. ኮሚቴውን በመወከል ት/ቤቱን የመቆጣር ስልጣን አለው፡፡

፫. አስቸኳይ ስብሰባ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ለአባላት ጥሪ ያስተላልፋል፤

፬. ኮሚቴውን በመወከል የሚቀርቡትን ሃሳቦች፤ አቤቱታዎችና አስተያየቶች ይቀበላል፣ በኮሚቴው የሚወሰን ጉዳይ ቢሆንም እስከ የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜ ድረስ ሊቆዩ በማይችሉ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭. ስለ ትምህርት ቤቱ በሚወጡ የጽሁፍ መግለጫዎች፣ ውሎች፣ ውሳኔዎችና ደብዳቤዎች ላይ ኮሚቴውን በመወከል ይፈርማል፤

፮. የኮሚቴው ስብሰባ ሊጠብቁ በማይችሉ አስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፯. በት/ቤቱ የሚያጋጥመው ችግሮች ከኮሚቴው አቅም በላይ ሆነው ሲገኙ ጉዳዩን በየደረጃው ለበላይ አካላት በማቅረብ በሚያስፈልግበት ጊዜ ኮሚቴውን በመወከል ተከታትሎ ያስፈጽማል፤

፰. የት/ቤቱን ሂሳብ ከኮሚቴው ፀሐፊና ከት/ቤቱ ገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል፡፡

፲፪. <u>የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

በኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ተጠሪነቱ ለሰብሳቢው ወይም ሰብሳቢው በሌላ ጊዜ ለኮሚቴው ሆኖ፤

፩. ስብሰባው ባለበት ጊዜ ሰብሳቢው የሚሰጠውን ተግባር ያከናውናከል፡፡

፪. ሰብሳቢው በሌለበት ጊዜ ሁሉ በቦታው ተተክቶ የሰብሳቢውን ስልጣንና ተግባር ያከናውናል፡፡

፫. ሰብሳቢው ስራውን ማከናወን የማይችልበት ሁኔታ ሲኖር በምትኩ ሌላ እንዲወክል ለሚመለከተው አካል ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ያሳውቃል፡፡

፲፫. <u>የኮሚቴው ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር</u>

በኮሚቴው ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ሆኖ

፩. አጀንዳዎች ቀደም ብለው እንዲዘጋጁና ለአባላት እንዲደርሱ እንዲሁም የስብሰባ ቀጠሮ እንዲያዝ ሰብሳቢውንና አባሎቹን ያስታውሳል፤

፪. ኮሚቴው ስብሰባ በሚያደርግበት ጊዜ የስብሰባውን ቃለ ጉባዔ በትክክል ይይዛል፤

፫. ኮሚቴው በሚወስነው መሰረት የኮሚቴውን መዛግብት በአግባቡ ያስቀምጣል፤

፬. የት/ቤቱን ሂሳብ ከኮሚቴው ሰብሳቢና ከት/ቤቱ ገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል፤

፭. ሌሎች በኮሚቴው የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፤

፮. ት/ቤቱ ሲከስም ሆነ ሲከሰስ ት/ቤቱን ይወክላል፤ ከት/ቢሮ የሕግ ባለሙያ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፲፩. <u>የኮሚቴው ሂሳብና ንብረት ተቆጣጣሪ ስልጣንና ተግባር</u>

የኮሚቴው የሂሳብና ንብረት ተቆጣጣሪ ተጠሪነቱ ለኮሚቴው ሆኖ፤

፩. ማናቸውም የት/ቤቱ ገንዘብና ንብረት በሕግ መሰረት መጠበቁንና መስራቱን ያረጋግጣል፤

፪. ማናቸውም ክፍያ በሕጋዊ መንገድ መፈፀሙንና በተገቢው መረጃ መደገፉን ያረጋግጣል፤

፫. ት/ቢሮው የሚያወጣቸውን መመሪያዎች በመከተል የት/ቤቱን የገንዘብ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም እንዲሁም የንብረት አያያዝ፣ አዘጋገብ አጠባበቅና አጠቃቀም ይቆጣጠራል፤

፬. በየሦስት ወሩ መጨረሻ ለኮሚቴውና ለወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤት የተሟላና የተብራራ የገቢና ወጪ ሪፖርት ያቀርባል፣ በቁጥጥር ወቅት ከመመሪያ ውጪ የሆነ አሰራር ተፈጽሞ ካገኘ ጊዜ ሳይወስድ ሪፖርቱን በአስቸኳይ ለኮሚቴው አቅርቦ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፡፡

፲፭. <u>የሕዝብ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ስልጣንና ተግባር</u>

ርዕሰ ተጠሪነቱ መምህሩ ለወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤትና ለኮሚቴው ሆኖ፤

፩. ለወረዳው ት/ቤቶች ጽ/ቤት ባለው ተጠሪነት

ሀ/ በት/ቤቱ የሚካሄደውን የመማር ማስተማሩን ሂደት ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ/ የት/ቤቱን የትምህርት ሥራ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ/ የመማር ማስተማሩን ሥራ በማመልከት ትምህርት ቢሮ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪. ለኮሚቴው ባለው ተጠሪነት

ሀ/ ትምህርት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የት/ቤቱን መምህራንና ሠራተኞች ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የሥራ ብቃታቸውን ይገመግማል፤

ለ/ መምህር ወይም ሠራተኛ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ፈጽሞ ሲያገኘው ጉዳዩን ለሥነ-ሥርዓትና ዲስፕሊን ኮሚቴ ይመራል፣

ሐ/ መምህሩ ወይም ሠራተኛው ከሥራ ከሚያሳግድ ጥፋት ፈጽሞ ሲያገኘው ስለ ሥራ መታገድ እንዲወሰን ጉዳዩን ለኮሚቴው ያቀርባል፤

መ/ የመምህራንና የሠራተኛ ጠቅላላ ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራል፤

ሠ/ በሰብሰባ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ሌላ ሰው ይተካል፡፡

፲፮. <u>የትምህርት ቢሮው ስልጣንና ተግባር</u>

፩. በእራሱ፣ በት/ቤቱ ኮሚቴ ወይም በት/ቤቱ መምህራንና ሠራተኞች ጥያቄ የት/ቤቱ ሂሳብና ንብረት እንዲመረመር ያደርጋል፡

፪. የት/መሣሪያዎች፣ የመምህራን፣ የሕግ የኦዲትና ሌሎች ቴክኒክ ነክ አገልግሎቶች ድጋፍ ይሰጣል፡፡

፫. መምህራንና ሠራተኞች የሙያ ሥልጣንና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፬. ቅጥር፣ ደመወዝ ጭማሪ ደረጃ ዕድገትና ሌሎች ይህን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፡፡

፭. ተግባሩን በሥሩ በተዋቀሩት የቢሮ እርከኖች ማስፈፀም ይችላል፡፡

፲፭. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከዛሬ ከታህሳስ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

## ደንብ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፯

# የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ሥያሜና የአድራሻ ሥርዓት ደንብ

ማውጫ


ክፍል አንድ ፲፪. የረዥም መንገድ
ስያሜ ስለሚለወጥበት ሁኔታ
ጠቅላላ ክፍል አራት ስለ
አድራሻ አሰጣጥ
፩. አጭር ርዕስ ፲፫. የአድራሻ አሰጣጥ መርህ
፪. ትርጓሜ ፲፬. የቁጥሮች አሰጣጥ
አፈጻጸም
ክፍል ሁለት ፲፭.በንብረት ላይ የሚደረግ
ቁጥር
የመንገድ ስያሜ መርሆዎች ፲፮. ከመንገዶች ስያሜ
አንፃር ስለሚሰጥ አድራሻ
፫. ስያሜ ስለሚሰጣቸው መንገዶች ክፍል አምስትልዩ ልዩ
ድንጋጌዎች
፬. የመንገድ ስያሜ ግምት ውስጥ የሚያስገባቸው ነጥቦች ፲፯. የአድራሻ ቁጥሮችን
ስለመለጠፍ በሚመለከት
፭. አዲስ መንገድ ስያሜ ስለሚሰጥበት ሥነ ሥርዓት ፲፰. የአድራሻ ቁጥሮችን
ለውጥ ማሳወቅ
፮. ተደራራቢ የመንገድ ስያሜ ስለማስወገድ ፲፱. ቁጥሮችን ስለማሳደስ
ክፍል ሦስት ስለመንገድ አሰያየም ሥነ ሥርዓት ፳. የመንገድ ምልክቶችን
ስለመትከል
፯. የመንገድ ስያሜ ስለሚይዛቸው ነጥቦች ፳፩. የመተባበር ግዴታ
፰. ቀደም ሲል ስለተሰጡ የመንገድ ስሞች ፳፪. መመሪያ የማውጣት
ሥልጣን
፱. የመንገድ ስያሜ ስለሚሰጠው አካል ፳፫.ተፈጻሚነት የሌላቸው
ሕጎች
፲.የመንገድ ስያሜ የሚይዘው የሆሄያት ብዛት ፳፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ
፲፩. አጭር መንገዶች ስያሜ


አጭር መግለጫ

የመንገድ መርበብ ካርታውን ተከትሎ የመንገድ ስያሜ መስጠትና የአድራሻ ሥርዓት በከተማው በሥራ ላይ የሚውልበትንና የመንገድ አጠቃቀምን ለማቀላጠፍ የወጣ ሕግ ነው፡፡

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ሥያሜና የአድራሻ ሥርዓት ደንብ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፯</u>

የአዲስ አበባ ከተማ መዋቅራዊ ኘላን ማጽደቂያና የአፈጻጸም ደንብ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፯ ህጋዊ ጥበቃ ከሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የመንገድ መርበብ ካርታ በመሆኑ፤

በሌሎች ዘመናዊ ከተሞች እንደተለመደው የመንገድ መርበብ ካርታውን ተከትሎ የመንገድ ስያሜ መስጠትና በዚያው ላይ ተመስርቶ የአድራሻ ሥርዓት በአዲስ አበባ ከተማ በሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንገድ ስያሜና የአድራሻ ሥርዓት ለከተማው ነዋሪ ከሚያስገኘው ጥቅም ውስጥ የአምቡላንስ፣ የእሳት አደጋ መቆጣጠር፣ የፖስታ አገልግሎትና የመሳሰሉትን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል በመሆኑ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፷፯/፪/ እና ፵፫ (፩) (ረ) እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መሪ ኘላን አዘገጃጀት፣ አወጣጥና አፈጻጸም አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፵፱ (ሸ) መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ስያሜና የአድራሻ ሥርዓት ደንብ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፺፯ ዓ/ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩. "መንገድ" ማለት በፀደቀው መዋቅራዊ ኘላንና ተያያዥ ዝርዝር ኘላኖች ላይ የተገለጹት መንገዶች ናቸው፡፡

፪. የአድራሻ ሥርዓት" ማለት በመንገዱ ሥያሜ ላይ ተመስርቶ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለበት ቦታ የማመልከቻ ሥርዓት ነው፡፡

፫. "አደባባይ" ማለት የተለያዩ መንገዶች የሚገናኙበት አማካይ ቦታ ነው፣

፬. "የማይንቀሳቀስ ንብረት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ቤቶችና የቦታ ይዞታዎችን ይመለከታል፡፡

፭. "የመንገዶች መገናኛ" ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መንገዶች የሚጋጠሙበት ወይም የሚቋረጡበት ማዕከላዊ ነጥብ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመንገድ ስያሜ መርሆዎች

**፫. ስያሜ ስለሚሰጣቸው መንገዶች**

በአዲስ አበባ ከተማ መዋቅራዊ ኘላን ማጽደቂያና የአፈጻጸም ደንብ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፯ የተመለከቱት መንገዶች በዚህ ደንብ መሠረት ስያሜ ይሰጣቸዋል፡፡

**፬. የመንገድ ስያሜ ግምት ውስጥ የሚያስገባቸው ነጥቦች**

መንገድ በሚሰየምበት ጊዜ የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ይሰጣቸዋል፣

፩. የመንገዱ ስያሜ ቀላልና ለንባብ የማያስቸግር ማድረግ፣

፪. በሚቻልበት ጊዜ ታሪካዊ የመንገድ ስሞች እንዲቀጥሉ ማድረግ፣

፫. የሚያሳስቱ ወይም ከሌላ የመንገድ ስያሜ ጋር የሚያምታቱ ስሞች ያለመጠቀም፣ እና

፬. መደበኛ የአቅጣጫ ማመልከቻ የሆኑትን/ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ/ለመንገድ ስያሜ ያለመጠቀም፣

**፭. አዲስ መንገድ ስያሜ ስለሚሰጥበት ሥነ ሥርዓት**

፩. የመንገድ ወይም የአደባባይ ስያሜ በከተማው ውስጥ በሚሰጥበት ጊዜ በከተማው ደረጃ የሚሰየሙ ይሆናል፡፡

፪. የመንገዶችና የአደባባዮች ስያሜ ላይ መንገዱ ወይም አደባባዩ የሚገኝበት የክፍለ ከተማ አስተዳደሮች ስለመንገዱ ወይም አደባባዩ አሰያየም የበኩላቸውን አስተያየት ለከተማው አስተዳደር ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**፮. ተደራራቢ የመንገድ ስያሜ ስለማስወገድ**

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት መንገዶች ወይም አደባባዮች አንድ ስያሜ ይዘው በሚገኙበት ጊዜ በሚከተሉት መርሆች ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ ይፈታል፣

፩. ቀደም ብሎ ስያሜ ለተሰጠው መንገድ በማጽናት፣

፪. ከበርካታ አድራሻዎች ጋር አስቀድሞ ለተያዘው በመፍቀድ፣

፫. በከተማው መዋቅራዊ ኘላን መሠረት መንገዶች ደረጃ ተዋረድ ከፍ ባለ ደረጃ ላይ ለሚገኘው መንገድ በመፍቀድ፣ እና

፬.ለስያሜያቸው ታሪካዊ ምክንያት ያላቸው ሲሆን በያዘው እንዲቀጥል በማድረግ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለመንገድ አሰያየም ሥነ ሥርዓት

**፯. የመንገድ ስያሜ ስለሚይዛቸው ነጥቦች**

፩. የመንገድ ወይም የአደባባይ ስያሜ በሚደረግበት ጊዜ የመንገዱ ወይም የአደባባዩ መለያ ስም መያዝ አለበት፡፡

፪. የመንገዱን ስያሜ የሚያመላክቱ ምልክቶች ቢያንስ መንገዱ በሚጀምርበት እና የመንገዱ ስያሜ በሚያበቃበት ቦታ ላይ ይመለከታሉ፡፡

፰. ቀደም ሲል ስለተሰጡ የመንገድ ስሞች

ቀደም ሲል በከተማው ውስጥ የሚገኙ የመንገዶች ስያሜ የተሰጣቸው ሲሆን በዚህ ደንብ ውስጥ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር እንዲታዩ ተደርጐ ስያሜው እንዲለወጥ ወይም እንዲፀና ይደረጋል፡፡

፱. የመንገድ ስያሜ ስለሚሰጠው አካል

፩. የከተማውን አስተዳደር መንገዶች ስያሜ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ለከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም ስራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈጻሚ የሚሆነው የመንገድ ስያሜን በሚመለከት የመሠረተ ልማትና የግንባታ ሥራዎች ባለሥልጣን የሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መነሻ ነው፡፡

፲.የመንገድ ስያሜ የሚይዘው የሆሂያት ብዛት

የመንገድ ስያሜ ደረጃን ከግምት ውስጥ በማስገባት በከተማው ውስጥ ያሉ መንገዶች የሚኖራቸው ስያሜ ከሃያ ሆሂያት መብለጥ የለበትም፡፡

፲፩. አጭር መንገዶች ስያሜ

፩. የመንገዱ ርዝመት ከአደባባይ ወይም ከመንገዶች መሐል ሲለካ ከአርባ ሜትር በታች ከሆነ አዲስ የመንገድ ስያሜም ሆነ የመንገድ ስያሜ ምልክት ማቆም አያስፈልግም፡፡

፪. አዲስ መንገድ ከነባር መንገድ ቀጥሎ በሚሰራበት ጊዜ ለአዲሱ መንገድ አዲስ ስያሜ መስጠት ሳያስፈልግ የቀድሞው መንገድ ስያሜ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

፲፪. የረዥም መንገድ ስያሜ ስለሚለወጥበት ሁኔታ

፩.ረዥም መንገድ የተሰጠው ስያሜ መንገዱ የምሥራቅ ምዕራብ ወይም የሰሜን ደቡብ አቅጣጫን በመከተል የሚያደርገውን ለውጥ ምክንያት በማድረግ ወይም የመንገድ አዘረጋግን በመከተል ለመንገዱ ከፊል ክፍል ሌላ የመንገድ ስም መስጠት ይበልጥ ትክክለኛ ሆኖ ሲገኝ ሊለወጥ ይችላል፡፡ ይህም ከመንገድ መገናኛ አንጻር ታይቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪. የረዥም መንገድ ስያሜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /፩/ በተመለከተው ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ የመንገድ ስያሜ ምልክት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ አድራሻ አሰጣጥ

፲፫. የአድራሻ አሰጣጥ መርህ

፩.የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በሚመለከት ቁጥር የሚሰጠው ንብረቱ ከሚመለከተው መንገድ አንፃር ያለበትን ቦታ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

፪. በአንድ ይዞታ ላይ የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ከመንገዱ አንፃር የሚሠጣቸው አንድ የአድራሻ ቁጥር ይሆናል፡፡

፫. ከመንገዱ በስተቀኝ ያሉት ከመጀመሪያው ጀምሮ ሙሉ ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡

፬. ከመንገዱ በስተግራ ያሉት ከመጀመሪያው ጀምሮ ጐደሎ ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡ የመጀመሪያ ነጥብ ተብሎ የሚወሰደው ለከተማው ማዕከል ይበልጥ ቅርብ የሆነው የመንገዱ ማብቂያ ነው፡፡ የከተማው ማዕከል የሚባለው የመስቀል አደባባይ ነው፡፡

## ፲፬. የቁጥሮች አሰጣጥ አፈጻጸም

፩. ወደ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይዞታው መግቢያ የሆነውንና ለማይንቀሳቀስ ንብረቱመለያ የሆነውን መንገድ በመለየት ቁጥር ይሰጣል፡፡ እያንዳንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይዞታ የሚሰጠው ቁጥር ከአጠገቡ ካለው ቁጥር ቀጥሎ ያለውን ይሆናል፡፡

፪. ለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በሚሰጠው ቁጥር ውስጥ በተከታታይነቱ የሚታለፍ ቁጥር አይኖርም፡፡ ሆኖም ሰፊ ይዞታ ንብረት ያልሰፈረበት በሚሆንበት ጊዜ የተወሰኑ ቁጥሮች በመጠባበቂያነት ለመያዝ ይቻላል፡፡

## ፲፭.በንብረት ላይ የሚደረግ ቁጥር

በአንድ ህንጻ ወይም ቤት ላይ የሚደረግ ቁጥር መሠረት የሚያደርገው ወደ ንብረቱ የሚያደርሰውን የመንገድ ስያሜ ይሆናል፡፡

## ፲፮. ከመንገዶች ስያሜ አንፃር ስለሚሰጥ አድራሻ

ከመንገዶች ስያሜ አንፃር የሚከተለው የአድራሻ አሰጣጥ ተግባራዊ ይሆናል፣

፩. ተቀጥለው የሚሰሩ መንገዶች በሚመለከት የሚሰጠው አድራሻ ተቀጥለው በተሰሩበት መንገድ ስያሜ ይሆናል፡፡ ለሚጠማዘዙ መንገዶች ኩርባ ፺$^0$±፲፭$^0$ ሲሆን እና ርዝመቱ ከሁለት መቶ ሜትር ካልበለጠ የቀድሞውን የመንገድ ስያሜ ይይዛል፡፡

፪. የ "L" ቅርጽ ያላቸው መንገዶች ከሁለት መቶ ሜትር በላይ ርዝመት ያላቸው ሆነው ፷$^0$ በላይ በሆነ ኩርባ የሚለያዩ ሲሆን ሁለቱም የተለያዩ የመንገድ ስያሜ ይኖራቸዋል፡፡

፫. የ "S" ቅርጽ ያላቸው መንገዶች ርዝመቱ ከ፪፻ ሜትር በታች ሲሆን መንገዱ በአጠቃላይ አንድ ስያሜ ይኖረዋል፡፡

፬.የ "U" ቅርጽ ያለው መንገድ ርዝመቱ ከ፬፻ ሜትር በታች ሲሆን መንገዱ በአጠቃላይ አንድ ስያሜ ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን አንዱ ክፍል ፺$^0$±፲፭$^0$ የሚሆንበት መታጠፊያ ሲኖረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ /፩/ የተገለጸው ተፈጻሚነት ይሆናል፡፡

፮.አፖርታማዎች፣ የጋራ ህንጻና የግል ቤቶች ከመንገድ ስያሜ ጋር የተገናዘበ አድራሻ ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፯. የአድራሻ ቁጥሮችን ስለመለጠፍ በሚመለከት

፩. ማናቸውም የመኖሪያ፣ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ድርጅት ባለቤት፣ ተከራይ፣ ወኪል ወይም ባለይዞታ በዚህ ደንብ መሠረት የሚዘጋጅለትን ተፈላጊውን የአድራሻ ቁጥሮች የመግዛት፣ በግልጽ ቦታ መለጠፍና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. የአድራሻ ቁጥሮችን በሚመለከት ወጥነት እንዲኖረው ሲባል የከተማው አስተዳደርየአገልግሎት ክፍያ በመጠየቅ ሊያቀርብ ወይምየሚዘጋጁበትን ደረጃ በመወሰን ተግባራዊ እንዲሆንያደርጋል፡፡

፫.ለተለያየ አገልግሎት የአድራሻ ቁጥሮች የሚኖራቸው መጠን እንዲሁም የመንገድ ምልክቶችና የአድራሻ ቁጥሮች ስለሚለጠፉበት ዝርዝር ሁኔታ በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፰.የአድራሻ ቁጥሮችን ለውጥ ማሳወቅ

፩.የአድራሻ ቁጥሮች ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ የህንጻው ባለቤት ተገቢውን ለውጥ እንዲያደርግ በከተማው አስተዳደር በኩል ይገለጽለታል፡፡

፪.የህንጻው ባለቤትም የተደረገውን የአድራሻ ለውጥ የሚመለከታቸው ተቋማት እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፲፱. ቁጥሮችን ስለማሳደስ

የማይንቀሳቀስ ንብረት መለያ የአድራሻ ቁጥሮችን የማደስና በአግባቡ መጠበቅ የንብረቱ ባለይዞታ ግዴታ ነው፡፡

፳.የመንገድ ምልክቶችን ስለመትከል

፩.የመንገድ ምልክቶችን የመትከልና የማደስ ኃላፊነት የከተማው አስተዳደር ነው፡፡

፪. የመንገድ ምልክቶች የሚኖራቸው ደረጃ፣ ቅርጽ እና ይዘት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፩.የመተባበር ግዴታ

፩. በከተማው ውስጥ የሚገኙ መንግሥታዊ፣ የግል እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶችና ግለሰቦች ለዚህ ደንብ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

፪. የከተማው አስተዳደር አካላት የሥነድ አያያዛቸውና የአገልግሎት አሰጣጣቸው በዚህ ደንብ የተደነገገውን የመንገድ ስያሜና የአድራሻ ሥርዓት የተከተለ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

፳፪. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የመሠረተ ልማትና የግንባታ ሥራዎች ባለሥልጣን ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

፳፫. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ሕግና የተለመደ ከሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፳፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር ከጸደቀበት ከግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፣ ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

የእንስሳት ሀብት በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት፣ ጤናማ እንስሳትን ለእርድ ማቅረብና የስጋ ምግብ ዉጤቶች በጠቅላላዉ ለሰዉ ምግብነት ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ተመጋቢዎችን ጤንነት ለመጠበቅ እንዲቻልና ጤንነቱ ያልተረጋገጠ እንስሳት እርድንና የስጋ ዝውውርን ለመግታት በሚል የወጣ ህግ ነው፡፡

፩. አጭር ርዕስ

፪.ትርጓሜ

፫. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

፬. ዓላማ

፭. የእንስሳት ዕርድ ስለ ማስኬድ

፮. ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ስለመከልከሉ

፯. ስጋና የስጋ ዉጤቶች ስለማጓጓዝ

፰. የቢሮው ስልጣንና ተግባር

፱. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

፲.የምግብ መድሃኒትና የጤና ክብካ  አስተዳደር ቁጥጥርና ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር

፲፩.የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣን ተግባር

፲፪. ቅጣት

፲፫. የመተባበር ግዴታ

፲፬. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፲፭. ስለተሸሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖቸው ህጎች

፲፮. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የስጋ ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር ፶፮/፪ሺ፲ ዓ.ም

የአዲስ አባበ ከተማ ዕድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና ከተማዋ ቀድሞ ከነበረችበት ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለወጠች ትገኛለች፣ የነዋሪው ሕዝብ ቁጥር እንዲሁ በፍጥነት እያደገና

በማንኛዉም መልኩ ዘመናዊነትን እየተላበሰ  ከተማዋ ለነዋሪዎቿና በተለያዩ ጉዳይ ወደ ከተማዋ የሚመጡትን እንግዶች ጤንነት መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የእንስሳት ሀብት በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማልማት፤ ጤናማ እንስሳትን ለእርድ ማቅረብና የስጋ ምግብ ዉጤቶች በጠቅላላዉ ለሰዉ ምግብነት ተስማሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ተመጋቢዎችን ጤንነት ለመጠበቅ እንዲቻልና ጤንነቱ ያልተረጋገጠ እንስሳት እርድንና የስጋ ዝውውርን መግታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሸለዉ የአዲስ አበባከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፩፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫ ንኡስ አንቀጽ (፩) ረ መሰረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጊዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድንና የስጋ ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር ፺፯/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ዉስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "**የከተማ አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "**ቢሮ**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ነው፤

፬. "**የእርድ እንስሳት**" ማለት ለምግብነት የሚዉሉ እንስሳት ዳልጋ ከብት፣ በሬ፣ ላም፣  መሲና ጊደር፣ ወይፈን፣ ጥጃ፣ በግ፣ ፍየል፣ አሳማና ግመልን ያጠቃልላል፤

፭. "**የስጋ ላይ ማህተም**" ማለት የእንስሳት ዕርድ አገልግሎት እንዲሰጡ በተፈቀደላቸዉ የቄራ ድርጅቶች ዉስጥ የታረደ ከብት ወይም የዕርድ እንስሳት ስጋ ጤነኛነት ወይም ለሰው ምግብነት ተሰማሚ መሆኑ በቢሮ በተመደበ ስጋ መርማሪ ሐኪም አማካኝነት በተመረመረ ስጋ ላይ የሚደረግ የጤንነት ማረጋገጫ ምልክት ነው፤

፮. "**ቄራ**" ማለት በሌላ ሕግ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት፣ በግል፣ የተቋቋመ ጤናማ ስጋ፣ የስጋ ዉጤት፣  የታረደ /ካርካስ/ ወይም ተረፈ ስጋ የሚዘጋጅበት፣ የሚታሸግበት፣ ምልክት በቁጥር የሚለጠፍበት ወይም ማህተም የሚደረግበት ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ባለፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው፤

፯. "**ህገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ**" ማለት ከቄራ ውጪ የእንስሳት ዕርድ በማካሄድ ለተመጋቢዎች፣ ለምግብ ቤቶች፣ ለግሮሰሪዎች፣ ለሆቴሎች፣ ወይም ለሱፐር ማርኬቶች ለልኳንዳ ቤት፣

ለንግድ ማሰራጨትና መሸጥ ሲሆን ለራስና ቤተሰብ ፍጆታ የሚውለውን ዕርድ አያጠቃልልም፤

፰."**የታረደ ካርካስ**" ማለት ማንኛዉም የታረደ እንስሳ ለሰዉ ምግብነት የሚውል የእንስሳትን ቆዳ፣ ሾኮና፣ የሆድ ዕቃን፣ ጭንቅላትን፣ ደምና ፈርስን ሳይጨምር ያለዉ ስጋ ማለት ነው፤

፱."**ስጋና የስጋ ውጤቶች**" ማለት ከእርድ እንስሳት የሚገኝ ለማንኛውም ሰዉ ለምግብነት የሚዉል የእንስሳት ስጋና መንኛውም ክፍል ወይም ከዚሁ የተዘገጀ ዉጤት ነው፤

፲. "**የስጋ ማጓጓዣ**" ማለት ለስጋ ማጓጓዣነት የተዘገጀ እና ተፈቀደ ከአሉሚንም የተሰራ ነጭ ቀለም የተቀባ ወይም ንጽህናውን የጠበቀ የስጋና ስጋ ዉጤቶች ማጓጓዣ ወይም የሙቀት መጠን መቆጣጠሪያ ተርሞ ኪንግ የተገጠመለት መኪና ማለት ነው፤

፲፩."**ተቆጣጠሪ**" ማለት ይህን ደንብ ለማስፈጸም ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድና የስጋ ዉጤቶች ዝውውር ለመቆጣጠር በቢሮ የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

፲፪. "**ሰው**" ማለት የተፈጥር ሰው ወይም የሕግ ሰዉነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**፫. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር ለራስና ለቤተሰብ ፍጆታ ከሚዉል የእንስሳት ዕርድ ውጭ ከስጋና ስጋ ውጤቶች ጋር ሚገናኝ ስራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፬. ዓላማ**

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የህብረተሰቡን ጤና በህገወጥ የእንስሳት እርድ ከሚተላለፉ በሽታዎች ለመከላከል፤

፪. በሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ምክንያት ሊከሰት የሚችላዉን ፍትሀዊ ያልሆነ የንግድ ዉድድር ለማስቀረት፤

፫. የስጋና ስጋ ውጤቶችን እንዲሁም ተረፈ ምርቶች ያለ አግባብ እንዳይባክን ለመከላከል እና የቆዳና ሌጦ ምርት እንዳይባክን ለመቆጣጠርና ደረጃዉን እንዲጠብቅ ለማስቻል፤

፬. በሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ምክንያት የሚያስከትለዉን የአከባቢ ብክለትና የጽዳት ጉድለት ለመቆጣጠር፡፡

## ክፍል ሁለት

## ህገ-ወጥ የእንስሳ እርድና የስጋ ዝውውር ስለመከልከሉ

**፭. የእንስሳት ዕርድ ስለ ማስኬድ**

በመኖሪያ ቤት ውስጥ ለራስ ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ የሚውል ስጋና የስጋ ውጤቶች ለማግኘት ከሚደረግ ዕርድ ውጪ እርድ የሚካሄደው በቄራ ብቻ ነው፡፡

፮. **ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ስለመከልከሉ**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ላይ ከተገለጸው በስተቀር ማንኛውም ሰው የእንስሳት ዕርድ ማካሄድ አይችልም፡፡

፯. **ስጋና የስጋ ዉጤቶች ስለማጓጓዝ**

ማንኛውም ሰው ካርካስ ወይም ስጋና የስጋ ዉጤቶችን በስጋ ማጓጓዣ መኪና ብቻ ማጓጓዝ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የቢሮውና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ስልጣንና ተግባር

፰. **የቢሮው ስልጣንና ተግባር**

፩. ህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ እና የታረደ ሥጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ሥራውን በባለቤትነት እና በበላይነት ይመራ፤

፪. ይህን ሥራ ከሚሰሩ ከባለድርሻ ጋር
በትሥሥር መሥራት፤

፫. ህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ የሚፈፀምባቸውን ቦታዎች በጥናት ይለያል፤

፬. ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንና ለደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፤

፭.በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ ቁጥጥር ወቅት የተያዘውን የሥጋ ምርት፣ቆዳና ሌጦ ወደ ሚወገድበት ክፍል ወደ አዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት በተገቢው መንገድ እና አግባብ ሥራውን ማስወገድ አለበት፣

፮. በዚህ ደንብ መሠረት ባለድርሻ አካላት ተግባራቸውን እንዲወጡ ያስተባራል አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፱. **የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር**

፩. በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ የተገኘን መረጃ ወዲያውኑ ለንግድ ቢሮ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

፪. በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ የተገኘን መረጃ ወዲያውኑ በንግድ ስር ለሚገኘው ለከተማ ግብርና የሥራ ዘርፍ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

፫. በህገወጥ የእንስሳት ዕርድ ጥቆማ ሲደርሰው ፈጥኖ በቦታው በመገኘት ዝርዝር ጉዳዩን ለንግድ ቢሮ ያሳውቅልን፡፡ ከንግድ ቢሮ ጋር በመቀናጀት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፬. በቁጥጥር ሂደት የያዘውን የሥራ ምርት፣ ቆዳና ሌጦ ለንግድ ቢሮ ያስረክባል፡፡

፭. ህገ-ወጥ የእንስሳት ዕርድ ሊከናወንባቸው ይችላል ተብሎ በተለያ ወይም በተጠረጠሩ ቦታዎ ህገ-ወጥ እርድ እንዳይከናወን ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡

፮. ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ መከላከልና መቆጣጠርን በተመለከተ የሠራቸውን ሥራዎች በጽኁፍ በየ፫ ወሩ ሪፖርት ለንግድ ቢሮ ያቀርባል፡፡

፲.<u>የምግብ መድሃኒትና የጤና ክብካ  አስተዳደር ቁጥጥርና ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. በህገ-ወጥ እንስሳት ዕርድ ቁጥጥር ወቅት ያገኘውን መረጃ ወዲያውኑ ለንግድ ቢሮ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪. ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ስለ ስጋና ሥጋ ውጤቶች ምርት አያያዝ በተገቢው መንገድ መሆኑን ይከታተላል

፫. በሥጋ ሥጋ ውጤቶች ለሚሠማሩ ነጋዴዎች የጤና ሰርተፊኬት ማውጣት እና ሰርተፊኬቱ በየስድስት ወሩ መታደስ እንዳለበት የማሳወቅ ሥራ መሥራት አለበት፣

፬. ልኳንዳ ቤቶች ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን በተገቢው መንገድ መያዛቸውን መከታተል፡፡

፲፩.<u>የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ሥልጣን ተግባር</u>

፩.ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና የሥጋ ዝውውር ጥቆማ ሲደርሰው ፈጥኖ በቦታው በመገኘት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡ ድርጊቱን ለንግድ ቢሮ ያሳውቃል የተያዘውን የሥጋ ምርት፣ቆዳና ሌጦ ለንግድ ቢሮ ያስረክባል፡፡

፪.ህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ ይከናወንባቸዋል ተብሎ የተለያየ ወይም የተጠረጠሩ ቦታዎች መረጃ ሲደርሰው ሕገ-ወጥ እርድ እንዳይከናወን ይከላከላል፡፡

፫.ይህ ደንብ የጣሱ ሰዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፣

፬.ይህ ደንብ ለማስፈፀም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### ፲፪. <u>ቅጣት</u>

ቢሮው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ የሚወስዳቸዉ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቀ ሆነው ድርጊቱ አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ይህንን ደንብ መተላለፉ እንደሚከተለው ያስቀጣል፡-

፩. የዚህን ደንብ አንቀጽ ፮ የተላለፈ ማንኛም ሰው ከብር ፲፭ሺ  እስከ ብር ፳ሺ በሚደርስ ገንዘብ መቀጫ ወይንም ከ፪ ወር እስከ ፫ ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል፤

፪. የዚህን ደንብ አንቀጽ ፯ የተላለፈ ማንኛም ሰው ከብር ፯ሺ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ ገንዘብ መቀጫ ወይም ከ፩ ወር እስከ ፫ ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል፤

፫. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ፤ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ቢሮው የሚያወጣውን  መመሪያ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ከብር ፭ሺ እስከ ብር ፯ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከ፲፭ ቀን እስከ ፫ ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ይቀጣል፤

፬. ድርጊቱ ሲደጋገም የገንዘብ ቅጣቱ እጥፍ ያሆናል፤

፭. ተቆጣጣሪው ቅጣቱ እንዲፈጸም የአንድ ጊዜ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ሲሆን፤ ካልተፈጸመ በወረዳ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**፲፫. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛዉም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፬. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፭. <u>ስለተሸሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖቸው ህጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉት ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፮. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፲፪ ቀን ፪ሺ.፲ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፪ ቀን ፪ሺ.፲ ዓ.ም.

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ፤አስተዳደርና አመራር ማሻሻያአዋጅ ቁጥር ፷/፪ሺ.ህ፩ ዓ.ምአጭር መግለጫ

ክፍል አንድ

አጭር ርዕስ
ማሻሻያ
ትርጉም
ስለ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መርህ
ፍቃድ ስለማግኘት
መድሀኒት
ክፍል ሁለት
የጤና አገልግሎት አስተዳደር
የጤና አገልግሎት አስተዳደር  የስልጣን አካላት
የጤና ቢሮሃላፊ ስልጣን
የመማክርት ጉባኤ
ስለ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያ አቋም
የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ስለማቋቋም
የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ስልጣን እና ተግባር
የሆስፒታል / የጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ ስልጣን እና ተግባር
የቦርድ ወይም የከፍተኛ አመራሩ ተጠያቂነት
ክፍል  ሶስት
የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አኳኃን
ስለየጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት
የሙያ ስነ ምግባር
ስለ ህሙማን አላላክ እና አቀባበል ስርአት
ክፍል  አራት
የከተማው አስተዳደር ሆስፒታሎች / ጤና ጣቢያዎች ፍይናንስ
ሆስፒታሎች / ጤና ጣቢያዎች ፍይናንስ ምንጭ
በገቢ ስለመጠቀም
ስለ ጤና አገልግሎት ክፍያ
ስለ እቃ እና አገልግሎት ግዢ
ስለ ጤና መድህን ዋስትና
ክፍል  አምስት
የማህበረሰብ ተሳትፎ
የተሳትፎ አላማ
በእቅድ ዝግጅት ስለ መሳተፍ
**ክፍል  ስድስት**
የመንግሥት ፣ የግል ዘርፍ ትብብር እና አስቸኳይ ጊዜ ጤና አገልግሎት
የስራ ካባን ስለ ማሻሻል
ስለ ምክክር መድረክ
ድጋፍ ስለማድረግ

መረጃን ስለማጠናከር
ስለ አስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት
የመተባበር ግደድት
ክፍል ሰባት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን
ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች
አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

*አጭር መግለጫ*

*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የነዋሪውን የጤና ሁኔታ ለማሻሻል በሚያደርገው ጥረት ውስጥ የህግ ማዕቀፎች በበቂ ሁኔታ አጋዥ ሚናቸውን ለመወጣት በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት እነንዳለባቸው እሙን ነው፡፡ በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አመራር አዋጅ የተሸሻለበት ዋናው ምክንያትም ከወቅቱ ጋር እና ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እየተስማማ የሚሄድ የጤና ስርአትና አስተዳደርን ለመፍጠር የሚያስችል አዋጅ በዚህም የፋይናነስ አስተዳደር እና የህብረተሰብ ተሳትፎን ጨምሮ የተዘጋጀ አዋጅ ነው፡፡*

## ***<u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ፤አስተዳደርና አመራር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺህ፩ ዓ.ም.</u>***

*የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደር አመራር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ማሻሻል በማስፈለጉ፣*

*በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፰ /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ፲፬/፩፩/ሀ/ እና /ረ/ በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡*

*<u>፩. አጭር ርዕስ</u>*

ይህ አዋጅ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና አመራር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፰/፪ሺ.ህ፩›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፰/፲፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፫. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩. ‹‹ከተማ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. ‹‹የጤና አገልግሎት›› ማለት የበሽታ መከላከልን፣ ቁጥጥርን፣ የተላላፊ በሽታዎች ቅኝትን፣ የአካል፣ የላብራቶሪ፣ የራጅና ልሎች ጤና ነክ ምርመራዎችን፣ የፈውስ ሕክምናን የጤና አጠባበቅ ትምህርቶችን ማሰራጨትና የሕብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ መፈተሽና መገምገምን ያጠቃልላል፣

፫. ‹‹የነፃ ሕክምና›› ማለት ወደፊት በከተማ መስተዳድሩ ካቢኔ በሚወሰነው ደንብ መሠረት ወጪው አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ወይም ለልላ ሦስተኛ ወገን ተሸፍኖ የመክፈል አቅም ለለልላቸው ዜጎች በነፃ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፣

፬. ‹‹ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት›› ማለት የሕብረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ልምድ ከማሳደግ እንዲሁም በሕዝብ ጤና አጠባበቅ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የሕብረተሰቡ ክፍል ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፣

፭. ‹‹የጤና ተቋም›› ማለት በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደር ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ጤና ኬላና የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ማሰራጫ ዩኒት ነው፤

፮.‹‹ካቢኔ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤

፯. ‹‹ገቢ›› ማለት የጤና ድርጅቶች ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶች፣ የመድኃኒት ሽያጭ እና ከልሎች አገልግሎቶች እና ዕቃዎች ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ እንዲሁም በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበሉት ዕርዳታ ነው፤

፰. ‹‹ሦስተኛ ወገን›› ማለት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን የወጪ /በኤንሹራንስ ወይንም በሌላ መልክ/ የሚሸፈን የግል ወይም የመንግሥት ድርጅት ማለት ነው፤

፱. ‹‹የግል የጤና ድርጅት›› ማለት በመንግሥት የሚወጡ ሕጋዊ መሥፈርቶችን በማሟላት በግል ባለሃብቶች ኤንቨስትመንት የሚቋቋም የጤና ድርጅት ማለት ነው፤

፲. ‹‹ቢሮ›› እና ‹‹የቢሮ ኃላፊ›› ማለት እንደቅደም ተከተል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮእና የጤና ቢሮኃላፊ ነው፤

፩. ‹‹የግል ሕክምና መስጫ ክፍል›› ማለት ከሆስፒታሎች የመደበኛ የሕክምና መስጫ ክፍል ውጪ የሆስፒታል አንድ ክፍል ሆኖ የሚቋቋም ለተመላላሽ ወይም ተኝተው ለሚታከሙ የታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ነው፣

፪. ‹‹የቤተሰብ ገቢ›› ማለት ቤተሰቡ ከማንኛውም እንቅስቃሴው በዓመት ወይም በወር የሚያገኘው በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚገኝ ገቢ ማለት ነው፣

፫. ‹‹የሚገኝ ወጪን የሚሸፍን አካል›› ማለት የመክፈል አቅም ለለልላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና ወጪ በጀት ይዞ የሚሸፍን አካል ማለት ነው፣

፬. ‹‹የግል ሴክተር›› ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግስት መዋቅር ውጭ በግልና በመንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደራጁና የሚተዳደሩትን የሚያጠቃልል ነው፣

፭.‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

፬. <u>የጤና አገልግሎት አሠጣጥ መርህ</u>

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የጤና አገልግሎት የሚሰጡት በካቢኔው የሚወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

፪. ከዚህ በላይ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም፡፡

፫. በካቢኔው በሚወጣው ደንብ መሠረት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚሰጡት የነፃ የሕክምና ማስረጃ በቂ ሆኖ ማንኛውም ሰው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

፬. ፈቃድ ስለማግኘት

ማንኛውም የጤና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚሰማራ ሰው ከቢሮው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ ሥራ መጀመር አይችልም፡፡

፭. መድኃኒት

ማንኛውም ከመድኃኒት ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማስመጣት፣ ማምረት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ እና ለታካሚዎች ማዘዝ በመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጤና አገልግሎት አስተዳደር</u>

፭. የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣን አካላት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣን አካላት፣

፩. የጤና ቢሮ

፪. የመማክርት ጉባዔ፣

፫. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ፣

፬. የሆስፒታሎች አመራር፣ እና

፭. የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት አመራር ናቸው፡፡

፯. የጤና ቢሮኃላፊ ሥልጣን

በዚህ አዋጅ በልሎች አንቀጾች ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ የጤና ቢሮ ኃላፊው የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፩. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ሲኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር፣ የሕንፃ፣ የሕክምና መሣሪያዎች እና የመገልገያዎች ደረጃ ይወስናል፣

፪. ለግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ፈቃድ ማረጋገጫ ይሰጣል፣

፫. የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋሞች በሚያቀርቡት ሃሳብ መሠረት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ለሳከፈል የሚገባውን ክፍያ የተቋሞቹን ወጪ እና የሕዝቡን የመክፈል አቅም ከግምት ማስገባቱን በማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነም በማሻሻል ከአስተያየት ጋር ለካቢኔው አቅርቦ ያስወስናል፣

፬. የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋሞች የሰው ኃይል ብቃት፣ የአሠራር ሥርዓት እና ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣

፭. የጤና ድርጅቶችን ደረጃ መለየት የሚያስችል የመመዘኛ መመሪያ ያወጣል፣ በዚህም መሠረት ለጤና አገልግሎት መስጫተቋሞች ደረጃ ይሰጣል፣

፮. በከተማው ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት፣ የግብረ ሰናይና አትራፊ የሆነ የግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ ይቆጣጠራል፣

፯. የጤና አገልግሎት ለማስፋፋትና ጥራቱንም ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ መሥፈርቶች መመሪያዎችና ደንቦች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፰. ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ያወጣል፣

፯. የመማክርት ጉባዔ

፩. በከተማው የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የጤና አገልግሎቱ ሽፋንና ጥራት በሚሻሻልበት የጤና ዕቅዶች ላይና በአመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ በመምከር አስተያየት የሚሰጥ የመማክርት ጉባኤ ተቋቁሟል፡፡

፪. የምክር ቤቱ አባላት ብዛትና ስብጥር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር ጤና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. የመማክርት ጉባዔው አካላት በቢሮው ኃላፊ ይሰየማል፣

፬. የቢሮው ኃላፊ የመማክርት ጉባዔው ሥራ የሚመራበትን ሁኔታ የሚወሰን መመሪያ ያወጣል፡፡

፰. የሆስፒታሎችና የጤና ጣቢያዎች አቋም

፩/ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ እያንዳንዱ ሆስፒታል

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ በተደነገገው መሠረት ከሚቋቋም የሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ሆኖ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

ለ) የንብረት ባለቤት መሆን መከሰስና፣ በስሙ ውል መዋዋል፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት እና ሀብቱን በልማት ላይ ማዋል ይችላል፡፡

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩-፲፫ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ቦርድ እና የሥራ አስኪያጅ ተጨማሪ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነት በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፪/ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ እያንዳንዱ ጤና ጣቢያ

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲በተደነገገው መሠረት በሚቋቋም በጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር የሚመራ ሆኖ የህግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

ለ) የንብረት ባለቤት መሆን መክሰስና መከሰስ፣ በስሙ ውል መፈጸም፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት እና ሀብቱን በልማት ላይ ማዋል ይችላል፡፡

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲-፲፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከፍተኛ አመራሩ እና የሥራ አስኪያጅ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነትና ተዛማጅ ጉዳዮች በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፱. የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር መቋቋም

፩/ በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ

ሀ/ እያንዳንዱ ሆስፒታል በላይነት የሚያስተዳድር ተጠሪነቱ ለጤና ቢሮው የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ በካቢኔው በሚወጣ ደንብ ይቋቋማል፡፡

ለ/ እያንዳንዱን ጤና ጣቢያ በበላይነት የሚያስተዳድር ተጠሪነቱ ለሚገኝበት ክፍለ ከተማ የጤና ጽ/ቤት ተጠሪ የሆነ ከፍተኛ አመራር በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይቋቋማል፡፡

፪/ የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ እንደሁኔታው ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት አባላት ይኖሩታል እንዲሁም የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ቢያንስ ፯ ቢበዛ ፱ አባላት ይኖሩታል፡፡ የሁለቱም አሰያየም የጾታ ተዋጽኦን ባገናዘበ መልኩ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርድ ሰብሳቢና አባላት በከተማው ከንቲባ ይሰየማል፣ የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ሰብሳቢና አባላት ደግሞ በክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሰየማል፡፡

፬/ የሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ አባል ፀሐፊ የሠራተኞች ተወካይ ደግሞ የቦርዱ አባል ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ፣ የጤና ጣቢያ ስራ አስኪያጅ የከፍተኛ አመራሩ ፀሐፊ፣ የጤና ጣቢያው ሠራተኞች ተወካይ ደግሞ የጤና ጣቢያው ከፍተኛ አመራር አባል ይሆናል፡፡

፭/ የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት በከተማው ካቢኔ በሚወስነው መሠረት አበል ይከፈላቸዋል፡፡

፲. የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድና የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር ስልጣንና ተግባር

የእያንዳንዱ የሆስፒታል የስራ አመራር ቦርድ ወይም የእያንዳንዱ የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተል የሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን

፩/ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣

፪/ የሆስፒታልን ዓመታዊ የሥራ እቅድ ያፀድቃል፣ የበጀት ረቂቅ መርምሮ ለቢሮው ወይም ለሚገኝበት ክ/ከተማ ጤና ጽ/ቤት ያቀርባል፣

፫/ የሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን ወርሃዊ፣ የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

፬/ የሆስፒታል/የጤና ጣቢያው የገቢ ምንጮች የሚተገበሩበትን ስልት ይቀይሳል፣ በተግባር ላይ መዋልንና ገቢ መደረጋቸ-ውንም ይቆጣጠራል፣

፭/ የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ የሥራ እንቅስቃሴን የሚያሻሽል የውስጥ ደንብ ያፀድቃል፣

፲፩. የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

፩/ የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ የሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከቦርዱ ወይም ከከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተል በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት የሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ፣

ሀ) የከተማውን አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ለ) የሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ወይም ለከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሐ) የሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን የሥራ ክንውንና የሒሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ወይም ለከፍተኛ አመራር እንደቅደም ተከተል ያቀርባል፣

መ) ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን የሆስፒታላን ወይም የጤና ጣቢያው ኃላፊዎች በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ መሠረት አወዳድሮ በመምረጥ አቅርቦ ያፀድቃል፣

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ሆስፒታልን ወይም የጤና ጣቢያውን ይወክላል፡፡

፫/ ዋና ስራ አስኪያጁ ለሆስፒታል ወይም የጤና ጣቢያው የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታል ወይም ለጤና ጣቢያው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ለላያስተላልፍ ይችላል፡፡

፲፪. የቦርድ ወይም የከፍተኛ አመራር ተጠያቂነት

፩/ የቦርዱ ወይም የከፍተኛ አመራር ሰብሳቢ እና አባላት ከዚህ በላይ በአንቀጽ አስር /፲/ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር በጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፡፡

፪/ ሰብሳቢውና አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በሆስፒታል ወይም በጤና ጣቢያው ላይ ለሚደርሰው ጉዳይ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፫/ በአብላጫ ድምጽ በሚሰጠው ውሳኔ ለሚደርሰው ጉዳት የተለየ ድምጽ ያለው አባል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አኳኋን

፲፫. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት

፩/ የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሦስት ደረጃዎች የሚከፈል ሲሆኑ፣

እነዚህም፡-

ሀ/ ሆስፒታል፣

ለ/ የጤና ጣቢያ እና

ሐ/ የጤና ኬላ ናቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተዘረዘሩት ደረጃዎች በሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ የሚያገለግለው የሰው ኃይል መገልገያዎች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በቢሮው ይወሰናል፡፡

፲፬. የሙያ ሥነ ምግባር

ቢሮው የመንግሥትና የግል ዘርፍ የጤና ተቋማት እና በእነዚህ የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ሊከተሉት የሚገባውን የሙያ ሥነ-ምግባር የሚመራ ደንብ አዘጋጅቶ በካቢኔው አፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፭. የሕሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓት

ሕሙማን አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ለአንድ የጤና ተቋም ወደሌላ የሚላኩበት ሥርዓት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

፯. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ስለማቋቋም

፩/ የጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ከመደበኛ አገልግሎታቸው ጎን ለጎን የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሊያቋቁሙ ይችላል፡፡

፪/ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች አሠራር፣ አመራር አስተዳደርን የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ይወጣል፡፡

ክፍል አራት

የነፃ ሕክምና አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው

የጤና አገልግሎቶች

፲፯. ስለ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች

፩/ የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ የነፃ ሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡ ዜጎች በከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

፪/ የነፃ ሕክምና የሚሰጥበት ሥርዓት ማለትም ተጠቃሚዎች የሚለዩበት ማስረጃ በማን እና እንዴት እንደሚሰጥ፣ ወጪውም በማንና እንዴት እንደሚሸፈን በአዲስ አበባ ካቢኔ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲፰. ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

፩. የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የጤና አገልግሎቶች ያለክፍያ ይሰጣል፣

ሀ) የሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ አክታ ምርመራ፣ ክትትልና የመድኃኒት አቅርቦት፣

ለ) የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

ሐ) የቅድመ እና ድኅረ የወለላድ አገልግሎት፣

መ) በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የማዋለድ አገልግሎት፣

ሠ) ፀረ-ስድስት የሕፃናት በሽታዎች ክትባት፣

ረ) ከእናት ወደ ጽንስ HIV/AIDS እንዳይተላለፍ መከላከል፣

ሰ) ሥጋ ደዌ

ሸ) ወረርሽኝ እና

ቀ) ወጪያቸው በመንግሥት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለ ክፍያ እንዲሰጡ የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች፣

፪/ ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥ የጤና ተቋም በዚህ ዓይነቶቹን አገልግሎቶች የሚያሳይ መረጃ ለይቶ በመያዝ ለቢሮው ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

ክፍል አምስት

የከተማው አስተዳደር ሆስፒታሎች/ጤና

ጣቢያዎች ፋይናንስ

፲፱. የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የፋይናንስ ምንጭ

፩/ በከተማው አስተዳደር በጥቅል የሚመደብ በጀት፣

፪/ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ እና

፫/ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ከሚቀበለው ዕርዳታ ይሆናል፡፡

፳. በገቢ ስለመጠቀም

፩/ ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የሚያገኙት ገቢ በጤና ተቋሙ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፡፡

፪/ ማናቸውም የአስተዳደሩ ሆስፒታል/ጤና ጣቢያ የሚያገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ የበጀቱ አካል ሆኖ፣ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ የበጀት አዋጅ በሚፈቀደው መሠረት ለሥራው ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

፫/ የሆስፒታሎች/የጤና ጣቢያዎች ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ኦዲት ይደረጋል፡፡

፬/ የሆስፒታሎች/የጤና ጣቢያዎች የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዝርዝር አፈጻጸም የሚያሳይ መመሪያ ቢሮው ከፋይናንስ ቢሮው ጋር በቅንጅት ያወጣል፡፡

፳፩. የጤና አገልግሎት ክፍያ

፩/ ለከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት ለላፈፀም የሚገባው ክፍያ ልክ በካቢኔው እየተወሰነ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪/ የጤና ቢሮው የጤና አገልግሎት ክፍያ ልክን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንደአስፈላጊነቱ እንዲከናወን በማድረግ የውሣኔ ሃሣብ ለከተማው ካቢኔ ያቀርባል፡፡

፫/ የጤና ቢሮው ከሆስፒታሎች ወይም ከክፍለ ከተማው ጤና ዴስክ ከአስተያየት ጋር የሚቀርብለትን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ለከተማው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

፳፪. የዕቃና አገልግሎት ግዢ

፩/ ጤና ተቋሞች የዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈጽሙት የከተማው አስተዳደር የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያን በመከተል ይሆናል፡፡

፪/ ማናቸውም የአስተዳደሩ ሆስፒታል/ጤና ጣቢያ በራሱ ሀብት፣ አመራር አስተዳደር ለሆስፒታል/ለጤና ጣቢያው ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ለሚችል ማናቸውም ህጋዊ ባለሀብት ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን በውል መስጠት ይችላል፡፡

፫/ ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በውል በሦስተኛ ወገን የሚሰጡበት ሁኔታ በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፫. የጤና መድን ዋስትና

፩/ የከተማው አስተዳደር የጤና መድን ዋስትና ለማቋቋምና ለማስፋፋት የሚረዱ ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

፪/ የጤና መድን ዋስትና የሚከተሉትን የአደረጃጀት ዓይነቶች መሠረት በማድረግ ይቋቋማል፣

ሀ/ የግል ድርጅቶች በሚያቋቁሙት የጤና መድን ዋስትና ፖሊሲ፣

ለ/ የተለያዩ የማህበረሰብ ተቋማት የጤና መድን ሥርዓት እንዲዘረጉ በማድረግ፣

ሐ/ አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የጤና መድን ፖሊሲዎችን በመግዛት ወይም በራሳቸው የመድን ሽፋን እንዲያቋቁሙ በማድረግ፣

መ/ መንግሥት ለሠራተኞች ማኅበራዊ የጤና መድን በማቋቋም፡፡

## ክፍል ስድስት
## የማሕበረሰብ ተሳትፎ

### ፳፩. የተሳትፎው ዓላማ

የማኅበረሰብ ተሳትፎ ዋነኛ ዓላማ ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የመከላከል አገልግሎቶችን ለማጠናከርና በጤና ተቋሞች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል ይሆናል፡፡

### ፳፪. በዕቅድ ዝግጅት መሳተፍ

የመከላከል ፕሮግራም ነዳፊዎችና የጤና ተቋሞች በዕቅድ ዝግጅት ሂደት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ አመቺ በሆነ መንገድ የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች አስተያየት ማግኘት አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት
## የመንግሥት፣ የግል ዘርፍ ትብብርና አስቸኳይ ጊዜ ጤና አገልግሎት

### ፳፫. የሥራ ከባቢን ስለማሻሻል

፩/ ቢሮው የግል ዘርፍ በጤናው ሴክተር የበለጠ ተሳታፊ የሚያደርገውን ወሳኝ የማትጊያ ስልቶች በመለየት ሃሣብ ያቀርባል፣ በተጨማሪም የአቻ ተጽዕኖን በመጠቀም የተሻለ ከባቢ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

፪/ ቢሮው የሙያ ሥነ ምግባርን በማስፈን ረገድ ከግል ዘርፍ ጋር በቅንጅት የሚሠራበትን ስልት ይነድፋል፡፡

### ፳፬. የምክክር መድረክ

ቢሮው ከግል ዘርፍ ጋር በፖሊሲ፣ በቴክኒካዊ፣ በአሠራርና በቅንጅት ላይ ለመምከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የምክክር ጉባዔዎች ያካሂዳል፡፡

### ፳፭. ድጋፍ ስለማድረግ

፩/ ቢሮው የግል ዘርፍ የጤና ተቋማት እንዲስፋፉ እና የአገልግሎታቸው ጥራት እንዲሻሻል የቴክኒክ ዕገዛ ያደርጋል፡፡

፪/ ቢሮው በመንግሥት የሚደረጉ የሥልጠናና የአሠራር መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የግል ዘርፍ እንዲሳተፍ ያደርጋል፡፡

### ፳፮. መረጃን ስለማጠናከር

፩/ የግል ዘርፍ የሚያደርገውን ተሳትፎና የሚያጋጥመውን ችግር በአግባቡ ማወቅና እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ቢሮው በግል ዘርፍ ላይ ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ጥናቶችንም በቋሚነት ያካሂዳል፡፡

፪/ የመንግሥትና የግል ዘርፍ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ስለበሽታዎች ዓይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፡፡

፴/ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት

፩/ ቢሮው በአገር አቀፍና በተለይም በከተማው ውስጥ በወረርሽኝ መልክ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን በመለየት ተገቢውን መረጃ ወቅታዊና ቀጣይ በሆነ መልኩ ያሰባስባል ያሠራጫል፡፡

፪/ ቢሮው በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ድርጅቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመረጃና የሎጂስትክስ አቅም እንዲገነቡ እንዲሁም የመጠባበቂያ ግብዓቶችን እንዲመቻች ያደርጋል፡፡

፫/ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ የሚደርሰውን የሕዝብ ጤናና ሕይወት አደጋ ለመቀነስ እንዲቻል ቢሮው የሁሉን ተሳትፎና አስተዋጽኦ በተለይም የኅብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎና በማስተባበር የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ ካቢኔው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያግዝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቢሮው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፴፪. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፫. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም.

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፭

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፬

አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

ማውጫ


ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የጤና አገልግሎት አሠጣጥ መርህ

፬. ፈቃድ ስለማግኘት

፭. መድኃኒት

ክፍል ሁለት

የጤና አገልግሎት አስተዳደር
፮. የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣን አካላት
፯. የጤና ቢሮ ኃላፊ ሥልጣን
፰. የመማክርት ጉባኤ
፱. የሆስፒታሎች አቋም
፲. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም
፲፩. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት
፲፪. የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር
፲፫. የቦርዱ ተጠያቂነት
ክፍል ሦስት
የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አኳኋን
፲፬. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት
፲፭. የሙያ ስነ ምግባር
፲፮. የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓት
፲፯. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ስለማቋቋም
ክፍል አራት
የነፃ ሕክምና አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች
፲፰. ስለ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች
፲፱. ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች
ክፍል አምስት
የከተማው አስተዳደር ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ፋይናንስ
፳. የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የፋይናንስ ምንጭ
፳፩. በገቢ ስለመጠቀም
፳፪. የጤና አገልግሎት ክፍያ
፳፫. የዕቃና አገልግሎት ክፍያ
፳፬. የጤና መድህን ዋስትና
ክፍል ስድስት
የማህበረሰብ ተሳትፎ
፳፭. የተሳትፎው ዓላማ
፳፮. በዕቅድ ዝግጅት መሳተፍ
ክፍል ሰባት
የመንግሥት፣ የግል ዘርፍ ትብብርና የአስቸኳይ ጊዜ ጤና አገልግሎት
፳፯. የሥራ ከባቢን ስለማሻሻል
፳፰. የምክክር መድረክ
፳፱. ድጋፍ ስለማድረግ
፴. መረጃን ስለማጠናከር
፴፩. የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት
ክፍል ስምንት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፪. ደንብና መመሪያ የማውጣትሥልጣን

፴፫. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፴፬. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

አጭር መግለጫ

ይህ አዋጅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፲፬ (፩) (ረ) እና አንቀጽ ፹፮ (፪) መሰረት የከተማውን ነዋሪ ጤንነት ለመጠበቅ መከላከልን ማዕከል ያደረገው ፖሊሲ በጤና ስልጠናዎችና በሕክምና አገልግሎት የታገዘ ለማድረግና የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገቢውን መስፈርት ያሟል እንዲሆኑ በማድረግ ወጥነት ባለው መልኩ የተቀናጀ አሰራር ለመዘርጋት ያወጣው አዋጅ ነው

# <u>የአዲስ አበባ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ዓ.ም</u>

በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና ተቋሞች አንድ ወጥ በሆነ የአሠራር፣ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

የአዲስ አበባ ከተማ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀ እና በሥርዓት የሚመራ እንስሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመከላከል ላይ የተመሠረተውን የጤና አገልግሎት በሥልጠናና በሕክምና አገልግሎት እንስደገፍ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማ ውስጥ የጤና ተቋሞች ስለነባርና አዲስ ስለሚከሰቱ በሽታዎች እና የእነዚህም ሥርጭት ስላስከተለው ውጤት ከተማ አቀፍ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ በመታመኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞችን አደረጃጀትና የሥራ አመራር ማሻሻል፣ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ የጤና ተቋሞች ጋር ያላቸው ግንኙነት የሠመረ እንስሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬ (፩) (ረ) እና ፳፮ (፪) መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና አመራር አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፰ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው ፣

፪ "የጤና አገልግሎት" ማለት የበሽታ መከላከል, ቁጥጥርን፣ የተላለፊ በሽታዎች ቅኝትን፣ የአካል የላብራቶሪ ፣ የራጅና ልሎች ጤና ነክ ምርመራዎች የፈውስ ሕክምና የጤና አጠባበቅ ትምህርቶች ማሰራጨትና የኅብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ መፈተሽና መገምገምና ያጠቃልላል፤

፫. "የነፃ ሕክምና" ማለት ወደፊት በከተማ መስተዳደሩ ካብኔ አካል በሚወሰነው ደንብ መሠረት ወጪው አግባብ ባለው ለሌላቸው የመንግሥት ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ተሸፍኖ የመክፈል አቅም ዜጎች በነፃ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፤

፬. "ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት" ማለት የኅበረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎት ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የኅበረተሰብ ክፍል ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

፭. "የጤና ተቋም" ማለት በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደር ሆስፒታል ፣ ጤና ጣቢያ ጤና ኬላና የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ማሰራጫ ዩኒት ነው፤

፮. "ካቢኔ ማለት" የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤

፯. "ገቢ"ማለት የጤና ድርጅቶች ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶች የመድኃኒት፣ ሽያጭ እና ከልሎች አገልግሎቶች እና ዕቃዎች ሽያጭ የሚያገኙት ገቢ እንዲሁም በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚቀበልት ዕርዳታ ነው፤

፰. "ሶስተኛ ወገን" ማለት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ወጪ / በኤንሹራንስ ወይንም በሌላ መልክ የሚሸፍን የግል ወይም የመንግሥት ድርጅት ማለት ነው፤

፱. "የግል የጤና ድርጅት" ማለት በመንግሥት የሚወጡ ሕጋዊ መሥፈርቶችን በሚሟላት በግል ባለሃብቶች ኤንቨስትመንት የሚቋቋም የጤና ድርጅት ማለት ነው፣

፲. "ቢሮ" እና "የቢሮ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮእና የጤና ቢሮ ኃላፊ ነው፤

፲፩. "የግል ሕክምና መስጫ ክፍል" ማለት ከሆስፒታሎች የመደበኛ የሕክምና መስጫ ክፍል ውጪ የሆስፒታል አንድ ክፍል ሆኖ የሚቋቋም ለተመላላሽ ወይም ተኝተው ለሚታሙ ታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ነው፤

፲፪. "የቤተሰብ ገቢ" ማለት ቤተሰቡ ከማንኛውም እንቅስቃሴው በዓመት ወይም በወር የሚያገኘው በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚገኝ ገቢ ማለት ነው፤

፲፫."ወጪን የሚሸፍን አካል" ማለት የመክፈል አቅም ለሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና ወጪ በጀት ይዞ የሚሸፍን አካል ማለት ነው፤

፲፬."የግል ሴክተር" ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ በግልና በመንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደራጁና የሚተዳደሩትን የሚያጠቃልል ነው፤

፲፭. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

<u>፫. የጤና አገልግሎት አሠጣጥ መርህ</u>

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የጤና አገልግሎት የሚሰጡት በካቢኔው የሚወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል ፡፡

፪. ከዚህ በላይ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም፡፡

፫. በካቢኔው በሚወጣው ደንብ መሠት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚሰጡት የነፃ የሕክምና ማስረጃ በቂ ሆኖ ማንኛውም ሰው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

፬.ፈቃድ ስለማግኘት

ማንኛውም የጤና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚሰራ ሰው ከቢሮው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ ሥራ መጀመር አይችልም፡፡

፭. መድኃኒት

ማንኛውም ከመድኃኒት ጋር የተያያዙ ሥራዎች ማስመጣት ማምረት ማከፋፈል መሸጥ እና ለታካሚዎች ማዘዝ በመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፮/፲፱፻፺፩ ዓ.ም በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጤና አገልግሎት አስተዳደር

፮. የጤና አልግሎት አስተዳደር የስልጣን አካላት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አስተዳደር የሥልጣንና አካላት

፩. የጤና ቢሮ፤

፪. የመማክርት ጉባዔ፤

፫. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ፤

፬. የሆስፒታሎች አመራር፣ እና

፭. የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተቋማት አመራር ናቸው፡፡

፯. የጤና ቢሮ ኃላፊ ስልጣን

በዚህ አዋጅ በልሎች አንቀጾች ከተሰጠው ስልጣን በተጨማሪ የጤና ቢሮ ኃላፊው የሚከተለው ስልጣን ይኖረዋል፣

፩. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ሊኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር፣ የሕንፃ የሕክምና መሣሪያዎች እና የመገልገያዎች ደረጃ ይወስናል፤

፪. ለግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ፈቃድ ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፫. የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋቀሞች በሚያቀርቡት ሃሣብ መሠረት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ለላከፈል የሚገባውን ክፍያ የተቋሞቹን ወጪ እና የሕዝቡን የመክፈል አቅም ከግምት ማስገባቱን በማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነ በማሻሻል ከአስተያየት ጋር ለካቢኔው አቅርቦ ያስወስናል፤

፬. የከተማው አስተዳደር የጤና ተቋሞች የሰው ኃይል ብቃት የአሠራር ሥርዓት እና ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፤

፭. የጤና ድርጅቶችን ደረጃ መለየት የሚያስችል የመመዘኛ መመሪያ ያወጣል፣ በዚህም መሠት ለጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ደረጃ ይሰጣል፤

፮. በከተማው ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት የግብረሰናይና አትራፊ የሆኑ የግል ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ደረጃውን የጠበቀ አልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ ይቆጣጠራል፤

፯. የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋትና ጥራቱንም ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ መሥፈርቶች መመሪያዎችና ደንቦች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

፰. የመማክርት ጉባዔ

፩. በከተማው የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የጤና አገልግሎቱ ሽፋንና ጥራት በሚሻሻልበት የጤና ዕቅዶች ላይና በዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ በመምከር አስተያየት የሚሰጥ የመማክርት ጉባኤ ተቋቁሟል ፡፡

፪. የምክር ቤቱ አባላት ብዛትና ስብጥር እንዲሁም ስልጣንና ተግባር ጤና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. የመማከርት ጉባዔው አባላት በቢሮው ኃላፊ ይሰየማል

፬. የቢሮው ኃላፊ የመማክርት ጉባዔው ሥራ      የሚመራበት ን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

፱ የሆስፒታሎች አቋም

፩. በከተማው አስተዳደር ሥር ያለ እያንዳንዱ ሆስፒታል በሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ሆኖ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

፪. እያንዳንዱ ሆስፒታል የንብረት ባለቤት መሆን መክሰስና መከሰስ በስሙ ውል የመፈፀም ፣ የባንክ ሂሣብ መክፈት እና ሀብቱን በልማት ላይ ማዋል ይችላል ፡፡

፫. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ እና የሆስፒታሎች ሥራ አስኪያጅ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነት ወደፊት በካቢኔው በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም

፩. በከተማው አስተዳደር ሥር ባለ በማንኛውም ሆስፒታል በበላይነት የሚያስተዳድር ተጠሪነቱ ለጤና ቢሮው የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ ይቋቋማል፡፡

፪. የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ እንስሁኔታው ቢያንስ አምስት ቢበዛ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡፡ አሰያየሙም የጾታ ተዋጽኦን ባገናዘበ መልኩ ይሆናል፡፡

፫. የቦርድ ሰብሳቢ በከተማው ከንቲባ ይሰየማል፡፡

፬. የሆስፒታል ዋና ሥራ አስክያጅ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ የሠራተኞች ተወካይ ደግሞ የቦርዱ አባል ይሆናል፡፡

፭. የቦርዱ አባላት ለሚሰጡት አልገልግሎት አግባብ ያለውን የመንግሥት መመሪያ በመከተል በከተማው ምክር ቤት የሚወሰን አበል ይከፈላቸዋል፡፡

፲፩ <u>የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የሥራ አመራር ቦርዱ

፩. የሆስፒታልን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

፪. የሆስፒታልን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፤

፫. የሆስፒታል ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ያፀድቃል፣ የበጀት ረቂቅ መርምሮ ለቢሮው ኃላፊ ያቀርባል፤

፬. የሆስፒታልን ወርሃዊ ፣ የሩብ ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ሪፓርት መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤

፭. የሆስፒታል የገቢ ምንጮች የሚዳብሩበትን መንገድ ይቀይሳል.በተግባር ላይ መዋላቸውን እና ገቢ መደረጋቸውንም ይቆጣጠራል፤

፮. የሆስፒታልን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያሻሽል የውስጥ ደንብ ያጸድቃል፡

፯. የሆስፒታል ዋና ስራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ የመምሪያ አገልግሎት ኃላፊዎችን ቅጥርና እድገት ያፀድቃል፤

፰. የጤናው ቢሮበሚያወጣው መመሪያ መሰረት በውል ለሶስተኛ ወገኖች ለላሰጡ የሚችሎትን ከሕክምና ውጪ ያል አገልግሎቶች ይወስናል፤

፱. በኃላፊነት መደብ ለሚመደቡ የወንበር  አበል ይወስና፤

፲. የሆስፒታል የስራ እንቅስቃሴዎችን ግልጽነት፣ የሙያ ሥነ-ምግባር እና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ እንስከናወኑ ያደርጋል፤

፲፩. ቢሮው የሚያወጣቸው መመሪያዎች በሆስፒታል ውስጥ በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፲፪. በሆስፒታል ዋና ስራ አስኪያጅ የሚቀርቡለትን ሌሎች ጉዳዮች   መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፲፪ <u>የሆስፒታል ሥራ-አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩ የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የሆስፒታል ዋና ስራ አስፈጻሚ ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የሆስፒታልን ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ስራ አስኪያጁ፣

ሀ) የክልልን ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ ጊዚያዊ አስተዳደሩ በሚያጸድቀው መመሪያ መሰረት የሆስፒታሎችን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

ለ) የሆስፒታልን የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የሆስፒታልን የሥራ ክንውን የሂሣብ ሪፓርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

መ) ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት የሆስፒታል ኃላፊዎች በሠራተኞች አስተዳደርና ደንብ መሠረት አወዳድሮ በመምረጥ ለቦርድ አቅርቦ ያስጸድቃል እና

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ሆስፒታል ይወክላል፡፡

፫. ዋና ሥራ አስኪያጁ ለሆስፒታል የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሆስፒታል የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ለላያስተላልፍ ይችላል፡፡

፲፫. የቦርዱ ተጠያቂነት

፩. የቦርዱ ሰብሳቢ እና አባላት ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፲ የተሰጣቸውን ተግባር በጥንቃቄ መፈጸም አለባቸው፡፡

፪. ሰብሳቢውን አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ባለመፈጸማቸው ምክንያት በሆስፒታል ላይ ለሚደርሰው ጉዳይ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፫. በአብላጫ ድምጽ በሚሰጠው ውሣኔ ለሚደርሰው ጉዳይ የተለየ ድምጽ ያለው አባል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሶስት

## የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥበት አኳኋን

፲፬. የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት

፩. የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሶስት ደረጃዎች የሚከፈል ሲሆኑ እነዚህም ፣

ሀ) ሆስፒታል፤

ለ) የጤና ጣቢያ እና

ሐ) የጤና ኬላ ናቸው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተዘረዘሩት ደረጃዎች በሚገኙ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ውስጥ የሚያገለግለው የሰው ኃይል፣ መገልገያዎች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በቢሮው ይወሰናል፡፡

፲፭ የሙያ ሥነ ምግባር

ቢሮው የመንግሥትና የግል ዘርፍ የጤና ተቋማት እና በእነዚህ የጤና ተቅማት ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለላከተልት የሚገባውን የሙያ ሥነ ምግባር የሚመራ ደንብ አዘጋጅቶ በካቢኔው አፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፮ <u>የሕሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓት</u>

ሕሙማን አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ከአንድ የጤና ተቋም ወደሌላ የሚላኩበት ሥርዓት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፯. <u>የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ስለማቋቋም</u>

፩. ሆስፒታሎች የሆስፒታል አንድ ክፍል ሆኖ የሚሠራ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል ሊያቋቁሙ ይችላል፡፡

፪. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች አሠራር ፣ አመራርና አስተዳደርን የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በቢሮው ይወጣል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የነፃ ሕክምና አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች</u>

፲፰. <u>ስለ ነፃ የሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች</u>

፩. የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ የነፃ ሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡ ዜጎች በከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

፪. የነፃ ሕክምና የሚሰጥበት ሥርዓት ማለትም ተጠቃሚዎች የሚለዩበት ማስረጃ በማን እና እንደድት እንደሚሰጥ፡ ወጪውም በማንና እንደድት እንደሚሸፈን ወደፊት በአዲስአበባ አስተዳደር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፲፱. <u>በክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች</u>

፩. የከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጤና አገልግሎቶች ያለክፍያ ይሰጣል፡

ሀ) የሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ አክታ ምርመራ፣ ክትትልና የመድኃኒት አቅርቦት፡

ለ) የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፡

ሐ) የቅድመ እና ድኅረ የወለላድ አገልግሎት፤

መ) በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የማዋለድ አገልግሎት

ሠ) ፀረ ስድስት የሕፃናት በሽታ ክትባት፤

ረ) ከእናት ወደ ጽንሱ HIV/AIDS እንዳይተላለፍ መከላከል፤

ሰ) ሥጋ ደዌ፡

ሸ) ወረርሽን፡ እና

ቀ) ወጪያቸው በመንግሥት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለ ክፍያ እንስሰጡ የሚወሰኑ ልሎች የጤና አገልግሎቶች፡፡

፪.ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥ የጤና ተቋም የዚህ ዓይነቶቹን አገልግሎቶች የሚያሳይ መረጃ ለይቶ በመያዝ ለቢሮው ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የከተማው አስተዳደር ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ፋይናንስ

፳. የሆስፒታሎች /ጤና ጣቢያዎች የፋይናንስ ምንጭ

፩. በከተማው አስተዳደር በጥቅል የሚመደብ በጀት፣

፪. ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ እና

፫. ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በዓይነት በጥሬ ገንዘብ ከሚቀበለው ዕርዳታ ይሆናል፡፡

፳፩. በገቢ ስለመጠቀም

፩. ሆስፒታሎች /ጤና ጣቢያዎች የሚያገኙት ገቢ በጤና ተቋሙ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፡፡

፪. ሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ከሚሰጡት አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ ሙል በሙል ከበጀታቸው ተጨማሪ ሆኖ ለሥራዎቻቸው ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

፫. የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ኦስት ይደረጋል ፡፡

፬. የሆስፒታሎች/ጤና ጣቢያዎች የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳይ መመሪያ ቢሮው ከፋይናንስ ቢሮው ጋር በቅንጅት ያወጣል ፡፡

፳፪. የጤና አገልግሎት ክፍያ

፩. ለከተማው አስተዳደር የጤና አገልግሎት ለላፈጸም የሚገባው ክፍያ ልክ በካቢኔው እየተወሰነ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፪. የጤና ቢሮው የጤና አገልግሎት ክፍያ ልክን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንደአስፈላጊነቱ እንስከናወን በማድረግ የውሣኔ ሃሣብ ለከተማው ካቢኔ ያቀርባል ፡፡

፫. የጤና ቢሮው ከሆስፒታሎች ወይም ከክፍለ ከተማው ጤና ዴስክ ከአስተያየት ጋር የሚቀርብለት የአገልግሎት ክፍያ ተመን ለከተማው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

፳፫. የዕቃና አገልግሎት ግዢ

፩. ጤና ተቋሞች የዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈጽሙት የከተማው አስተዳደር የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያን በመከተል ይሆናል፡፡

፪. በራሳቸው ሀብት አመራርና አስተዳደር ለሆስፒታል ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት ለሚችል ባለሀብቶች ሆስፒታሎች ሕክምና ነክ ያልሆነ አገልግሎቶች በውል መስጠት ይችላል፡፡

፫. ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በውል ለሶስተኛ ወገን የሚሰጡበት ሁኔታ በቢሮበሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፬. የጤና መድን ዋስትና

፩. የከተማው አስተዳደር የጤና መድን ዋስትና ለማቋቋምና ለማስፋፋት የሚረዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

፪. የጤና መድን ዋስትና የሚከተልትን የአደረጃጀት ዓይነት መሠረት በማድረግ ያቋቁማል፤

ሀ) የግል ድርጅቶች በሚያቋቁሙት የጤና መድን ዋስትና ፓሊሲ

ለ) የተለያዩ የማኅበረሰብ ተቋማት የጤና መድን ሥርዓት እንስዘረጉ በማድረግ፤

ሐ) አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የጤና መድን ፓለሳሲዎች በመግዛት ወይም በራሳቸው የመድን ሽፋን እንስቋቁሙ በማድረግ፤

መ) መንግሥት ለሠራተኞች ማኅበራዊ የጤና መድን በማቋቋም፡፡

## ክፍል ስድስት

## የማኅበረሰብ ተሳትፎ

፳፩. <u>የተሳትፎው ዓላማ</u>

የማኅበረሰብ ተሳትፎ ዋንኛ ዓላማ ኀበረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የመከላከል አገልግሎቶች ለማጠናከርና በጤና ተቋሞች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል ይሆናል፡፡

፳፪. <u>በዕቅድ ዝግጅት መሳተፍ</u>

የመከላከል ኘሮግራም ነዳፊዎችና የጤና ተቋሞች በዕቅድ ዝግጅት ሂደት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በሚካሄድበት ጊዜ ሁል አመቺ በሆነ መንገድ የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች አስተያየት ማግኘት አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት

## የመንግሥት የግል ዘርፍ ትብብርና የአስቸኳይ ጊዜ ጤና አገልግሎት

፳፫ . <u>የሥራ ከባቢን ስለማሻሻል</u>

፩. ቢሮው የግል ዘርፉ በጤናው ሴክተር የበለጠ ተሳታፊ የሚያደርገውን ወሳኝ የማትጊያ ስልቶች በመለየት ሃሣብ ያቀርባል፣ በተጨማሪም የአቻ ተጽዕኖን በመጠቀም የተሻለ ከባቢ እንስፈጠር ያደርጋል፡፡

፪. ቢሮው የሙያ ሥነ ምግባርን በማስፈን ረገድ ከግል ዘርፍ ጋር የቅንጅት የሚሠራበትን ስልት ይነድፋል ፡፡

፳፬. <u>የምክክር መድረክ</u>

ቢሮው ከግል ዘርፍ ጋር በፖሊሲ ፣ በቴክኒካዊ፣ በአሠራርና በቅንጅት ላይ ለመምከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የምክክር ጉባዔዎችን ያካሂዳል፡፡

፳፱. ድጋፍ ስለማድረግ

፩. ቢሮው የግል ዘርፍ የጤና ተቋማት እንስስፋፋ እና የአገልግሎታቸው ጥራት እንስሻሻል የቴክኒክ ዕገዛ ያደርጋል፡፡

፪. ቢሮው በመንግሥት የሚደረጉ የሥልጠናና የአሠራር መመሪያዎች ዝግጅት ላይ የግል ዘርፍ እንስሳተፍ ያደርጋል፡፡

፴. መረጃን ስለማጠናከር

፩. የግል ዘርፍ የሚያደርገውን ተሳትፎና የሚያጋጥመውን ችግር በአግባቡ ማውቅና እርምጃ መውሰድ እንስቻል ቢሮው በግል ዘርፍ ላይ ውቅታዊ የመረጃ ልውውጥ የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ጥናቶች በቋሚነት ያካሂዳል፡፡

፪. የመንግሥትና የግል ዘርፍ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ስለበሽታዎች ዓይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፡፡

፴፩ የአስቸኮይ ጊዜ የጤና አገልግሎት

፩ ቢሮው በአገር አቀፍ በተለይም በከተማው ውስጥ በወረርሽኝ መልክ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን በመለየት፣ ተገቢውን መረጃ ወቅታዊና ቀጣይ በሆነ መልኩ ያሰባስባል ያሰራጫል፡፡

፪ ቢሮው በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ድርጅቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመረጃና የሎጂስቲክስ አቅም እንስገነቡ እንዲሁም የመጠባበቂያ ግብዓችን እንስመቻ ያደርጋል፡፡

፫ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ የሚያደርሰውን የሕዝብ ጤናና ሕይወት አደጋ ለመቀነስ እንስቻ ቢሮው የበኩልን ተሳትፎና አስተዋጽኦ በተለይም የኅብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ በማስተባበር የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩. ካቢኔው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያግዝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪. ቢሮው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፴፫. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፬. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በአዲስነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርየኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፩/፲፱፻፺፰

ማውጫ
ክፍል አንድ
ጠቅላላ
፩. አጭር ርእስ
፪. ትርጓሜ ርእስ
ክፍል ሁለት
መቋቋም አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ምዕራፍ አንድ መቋቋም፣ አደረጃጀትና ዓላማ
፫. መቋቋም
ምዕራፍ ሁለት
የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር
፮. ሥልጣንና ተግባር
ምዕራፍ ሦሥት
የኤች አይቪ/ኤድስ ምክር ቤት
መቋቋም፣
ስብሰባ፤
ሥልጣንና ተግባር
፲. ስለምክር ቤቱ መቋቋም
ምዕራፍ አራት
የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር
፲፩. አመሠራረትና ስብሰባ
ክፍል ሦስት
፲፪. የጽሕፈት ቤቱ የክፍለ ከተማ አካላት ሥልጣን ተግባርና አሠራር
ምዕራፍ አንድ
፲፫. የዴስኩና የኃላፊው ሥልጣንና ተግባር
፲፬. የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ
ምዕራፍ ሁለት
፲፭. የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባር፣ አመሠራረትና ስብሰባዎች
፲፮. የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር
፲፮. የጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት
፲፰. የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች
ምዕራፍ ሦስት
የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣ አመሠራረትና ስብሰባ
፲፱. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር ኮሚቴው፤
፳. ስለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

፳፩. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ

ክፍል አራት

የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ የሥልጣን አካላት

ምዕራፍ አንድ

የቀበሌው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የዴስኩና የኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

፳፪. የዴስኩ ሥልጣንና ተግባር

፳፫. የዴስክ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

ምዕራፍ ሁለት

የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር፣ አመሠራረትና ስብሰባ

፳፬. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር፡-

፳፭. የጉባዔው አመሠራረት

፳፮. የጉባኤው ስብሰባዎች

፳፯. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር ኮሚቴው፤

፳፰. ስለ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ኮሚቴው፤

፳፱. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴. የጽሕፈት ቤቱ በጀትና አስተዳደሩ

<u>አጭር መግለጫ</u>

የኤች አይቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመግታት የተለያዩ የከተማውን አስተዳደር አካላትና የሕዝብ ተሳትፎን በማጎልበት ላይ የተመሠረተ የመከላከልና የቁጥጥር ሥራ ከሀገር አቀፍ አተገባበር ስልት በመከተል ስራውን የሚመራ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ጽህፈት ቤት ለማቋቋም የወጣ ሕግ ነው፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፩/፲፱፻፺፰

ኤች አይ ቪ ኤድስ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ጤናና የልማት አቅም ላይ ከፍተኛ አደጋ እያስከተለ ያለ በመሆኑ፤

ኤች አይ/ ቪ/ኤድስ ቅንጅት ያለውና በሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የመከላከልና የቁጥጥር ዘመቻ ተደርጎበት ስርጭቱ ካልተገታ በስተቀር ሊያስከትል የሚችለው የጤና፤ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ቀውስ እጅግ የሚያስፈራ በመሆኑ፤

የኤች አይቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመግታት የተለያዩ የከተማውን አስተዳደር አካላትና በከተማው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በማካተትና በስፋት በማሳተፍ የሀገሪቱን የኤች አይቪ/ኤድስ ፖሊሲና ሀገር አቀፍ የአተገባበር ስልቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ድርጅታዊ አቋም ያለው እራሱን የቻለ የከተማው አስተዳደር መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፫ (፩) (ሀ) እና አንቀጽ ፷፮ (፪) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፰ ዓ.ም.›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩. ‹‹ከተማ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. ‹‹ክፍለ ከተማ›› ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎችና ቀበሌዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፬ የተመለከተ ማንኛውም ክፍለ ከተማ ነው፤

፫. ‹‹ጽሕፈት ቤት›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተቋቋመው ነው፤

፬. ‹‹መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት›› ማለት በከተማው ደረጃ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሕጋዊ አቋም ያለውና ኤች አይቪ/ኤድስ በመከላከልና በመቆጣጠር ተግባር ተሳትፎ ያለው ማሕበር፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የሃይማኖት ተቋም ነው፡፡

፭. ‹‹የከተማ አስተዳደር›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

## ምዕራፍ አንድ

## መቋቋም፣ አደረጃጀትና ዓላማ

፫. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪. ጽሕፈት ቤቱ ለከተማው ከንቲባ ተጠሪ ይሆናል፡፡

፬. የጽሕፈት ቤቱ ድርጅታዊ አቋም

ጽሕፈት ቤቱ፤

፩. በከተማ ደረጃ፤

ሀ) የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች፤

ለ) የሥራ አመራር ቦርድ እና

ሐ) የኤች አይቪ/ኤድስ ምክር ቤት፡፡

፪. በክፍለ ከተማ፤

ሀ) ኤች አይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ፤

ለ) ሥራ አመራር ኮሚቴ እና

ሐ) ጠቅላላ ጉባኤ፤

፫. በቀበሌ፤

ሀ) ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ፤

ለ) ሥራ አመራር ኮሚቴ እና

ሐ) ጉባኤ ይኖሩታል፡፡

፭. ዓላማዎች

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩. በፌደራል ኤች/አይቪ/ ኤድስ ምክር ቤት የተቀየሰውን ስልት ግምት ውስጥ በማስገባት ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በከተማው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አግባብ ያላቸው አካላት ለችግሩ ይበልጥ ትኩረት ሰጥተው እንዲያንቀሳቀሱ በማድረግና የሕብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲያጐለብቱ እንዲሁም ስለኤች አይቪ/ኤድስ ጥናትና ምርምር እንዲያካሂዱ በማበረታታት ጤናማ አመለካከትና ባሕሪ የሚዳብርበትን ሁኔታ መቀየስ፤

፪. በከተማው ደረጃ የሚደረጉት ኤች አይቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ጥረቶች በተቀናጀ መልክ እንዲካሄድና ወጣቶችንና ሴቶችን ጨምሮ ለበሽታው ይበልጥ የተጋለጡ የከተማው

ሕብረተሰብ ክፍሎች እራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል የመወሰን መብታቸውን እንዲጠቀሙና ለመከላከል እንዲችል አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፫. በከተማው ውስጥ ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች የጤና፣ የሥነ ልቦናና የምክር አገልግሎትና አስፈላጊውን የማቴሪያል ድጋፍ የሚያገኙበትን እንዲሁም ሰብአዊ መብታቸው የሚከበርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፬. ከሚቀይሰው አጠቃላይ ስልት ጋር በሚጣጣም መልኩ በከተማው ውስጥ ተግባር ላይ የሚውልበትን መንገድ ለመቀየስ፣ የበሽታውን ስርጭት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል እቅድና ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚረዱ ሀሳቦችን ማመንጨትና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የጥናትና የምርምር ተግባረሬችን ማበረታታት፤

፭. በተጠናከረና በተቀናጀ መልክ የኤች አይቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም እርዳታ የሚሰባሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

፮. ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፮ የተደነገጉት የውል ሥልጣንና ተግባራት ከማከናወን በተጨማሪ፤

፩. የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

፪. የምክር ቤቱን አስተያየት አካቶ ከተማ አቀፍ የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

፫. ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ የከተማው ማእከልና የክፍለ ከተማ መንግሥታዊ አካላትንና መንግታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል፤ የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፬. በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም በብሔራዊ ኤች አይቪ/ኤድስ የሥራ ፕሮግራም መሠረት ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከለከልና ለመቆጣጠር እቅድ መካተቱን ይከታተላል፤

፭. ኤች አይ/ ቪ/ኤድስ የመከላከልንና የመቆጣጠሩን ሥራ በቀጥታ ለሚፈጽሙ ግለሰቦች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተቀላጠፈና የተሟላ የሥራ፣ የሙያ፣ የሞራልና ሌላም ድጋፍ በጊዜው በመስጠት ሕብረተሰቡን ለማዳን የሚደረገውን ጥረት ይደግፋል፤

፮. ኤች አይቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚሠሩ አካላት ግንዛቤን ለማዳበርና የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት የሚያከናውናቸው ተግባራት እድሜን፣ ጾታን፣ አካል ጉዳትን፣ ባሕልን፣ የትምህርት ደረጃን ባገናዘበ መልኩ መታቀዱና መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ ለዚህም የሚረዱ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፤

፯. ሕብረተሰቡ ስለኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች የኤድስ ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው የሕክምና የሥነ ልቦና፣ ማኅበራዊና ሕጋዊ ድጋፍ ለማግኘት እንዲችል ለሚመለከታቸው አካላትና ለሕብረተሰቡ ያሳውቃል፤

፰. ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ ክልላዊና ብሔራዊ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤

፱. በከተማው ውስጥ ያለውን የኤች አይቪ/ኤድስ ገጽታ የሚያሳይ መረጃ ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፣

፲ ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፤

፲፩. በልገሳ የተገኘው ገንዘብና በከተማው አስተዳደር የሚመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋልን ያረጋግጣል፤

፲፪. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፫. ዓላማውን ከግቡ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

፯. የጽሕፈት ቤቱ ኀላፊ ሥልጣንና ተግባር

፩. የጽሕፈት ቤቱ ኀላፊ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የጽሕፈት ቤቱ ኀላፊ፤

ሀ) በቦርዱ ስብሰባዎች በአባልነት ይሳተፋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባረሬች በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) በከተማው አስተዳደር ሰራተኞች ሕግ መሠረት  የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለስራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፤

ሰ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሸ) የቦርዱ ውሳኔ ያረፈበትን የሥራ ፕሮግራም በጀትና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፡፡

## ምዕራፍ ሦሥት

## የኤች አይቪ/ኤድስ ምክር ቤት መቋቋም፣ ስብሰባ፤ ሥልጣንና ተግባር

### ፲. ስለምክር ቤቱ መቋቋም

ኤች አይቪ/ኤድስ ነክ በሆኑ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚመክር በከተማው ከንቲባ ሰብሳቢነት የሚመራ የሚከተልት አባላት የሚኖሩት ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፩. የከተማው አስተዳደር ቢሮኃላፊዎች፤

፪. የከተማው ምክር ቤት አፈጉባዔ፤

፫. የክፍለ ከተማዎች ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤

፬. የከተማው አስተዳደር የሴቶች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፤

፭. የከተማው አስተዳደር የማህበራዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፤

፮. የከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽነር፤

፯. የከተማው አስተዳደር የፖሊሲ ጥናትና ፕላን ኮሚሽነር፤

፰. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፤

፱. የከተማው አስተዳደር የመገናኛ ብዙሀን ኤጀንሲ ኃላፊና በከተማው ውስጥ ስርጭት ያላቸው ልሎች የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ኃላፊዎች፤

፲. ከሚከተልት ሃይማኖት ድርጅቶች መካከል በምክር ቤቱ ውስጥ ተወካይ የሚኖራቸው፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት፤

ለ) የአዲስ አበባ እስልምና ጉባዔ ጽሕፈት ቤት፤

ሐ) የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የአዲስ አበባ ሴክሪታሪያት፤

መ) በኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነየሱስ ቤተክርስቲያን የአዲስ አበባ ጽሕፈት ቤት፤

ሠ) በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ናቸው፡፡

፲፩.የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ተወካይ፤

፲፪. የአዲስ አበባ ቀይ መስቀል ማሕበር፤

፲፫. የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

፲፬. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኀበር ኮንፌደድሬሽን ሕብረት የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

፲፭. የኢትዮጵያ አሠሪዎች ማኀበር አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤

፲፮. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት፤

፲፯. በአዲስአበባ መምህራን ማኀበር ፕሬዝዳንት፤

፲፰. በአዲስአበባ ተወስነው የሚንቀሳቀስና ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ዜጐች ማኅበራት መረዎች፤

፲፱. የአዲስ አበባ ሴቶች ስሞክራሲያዊ ማኅበር፤

፳. የአዲስ አበባ ወጣቶች ዲሞክራሲያዊ ማኅበር፤

፳፩. በኤድስ ወላጅ አልባ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማኅበር፤

፳፪. የአዲስ አበባ ሠራተኞች ማኅበር፤

፳፫. የአዲስ አበባ ነርሶች ማኅበር፤

፳፬. የአዲስ አበባ ሆቴሎችና ቡና ቤቶች ባለቤቶች ማኅበር፤

፳፭. የአዲስ አበባ ታክሲ ባለንብረቶች ማኅበር፤

፳፮. በአዲስ አበባ ውስጥ የሚሠሩ የግል ክሊኒኮች ባለቤቶች፤

፳፯. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀፅ ፬ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች፤

፳፰. በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ታዋቂ የአዲስ አበባ ግለሰብ ነዋሪዎች፤

<u>፱. የከተማው አስተዳደር ኤች አይቪ/ኤድስ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ፤

፩. የፌደራል ኤች አይቪ/ኤድስ ምክር ቤት በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት በከተማው ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን በተመለከተ አቅጣጫዎችንና ስልቶችን ይቀይሳል፣ ለተፈጻሚነታቸው አመቺ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ይከታተላል፡፡

፪. የኤች አይቪ/ኤድስ ፕሮግራሞች አፈጻጸምና በዚሁ ዙሪያ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ ይገመግማል፣ የማሻሻያና የማጠናከሪያ ሀሳቦችን ያቀርባል፡፡ በኤች አይቪ/ኤድስ ፕሮግራሞች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ የከተማው ነዋሪዎች ሕሙማን፣ በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ሕጻናትና ቤተሰቦቻቸው የጤና እንክብካቤ፣ የሥነ ልቦና ምክርና እንደሁኔታው ማሕበራዊ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱንና ሰብአዊ መብታቸው መከበሩን መከታተል፡፡

፫. የፌደራል ኤች አይቪ/ኤድስ ምክር ቤት በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት ከአገር ውስጥና ከውጭ የሚገኝ እርዳታ እንዲሰበስብና በከተማው ውስጥ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ከተማ አቀፍ አመራር ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

፬. በኤች አይቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር፣ እንዲሁም ጥናትና ምርምር አመርቂ ውጤት ላስገኙ ተቋማትና ግለሰቦች ሽልማት ይሰጣል፡፡

፭. የራሱን አርማ ቅርጽና ይዘት ይወስናል፡፡

፯. ዓላማውን ለማስፈጸም በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሀሳብ ያመነጫል፡፡ ሀሳቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎችንም ያቋቁማል፡፡

፲. የምክር ቤቱ ስብሳዎች

፩. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል፣ ሆኖም በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ለላያደረግ ይችላል፤

፪. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫. የምክር ቤቱ ውሣኔ በድምጽ ይወክላል ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

አመሠራረትና ስብሰባ

፲፩. የጽሕፈት ቤቱ ሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ፤

፩. ጽሕፈት ቤቱ የሚከታተላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ መልክ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. ከፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር ተያይዘው በሚነሱና አመራር በሚሹ ጉዳዮች ላይ እንደ አግባቡ ውሣኔ ይሰጣል ወይም ከአስተያየቱ ጋር ለከንቲባው እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፫. የጽሕፈት ቤቱን መዋቅርና የሰው ኃይል ፕላን መርምሮ፣ ለከንቲባው እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፬. ለከንቲባው የሚቀርበውን የጽሕፈት ቤቱን የሥራ ፕሮግራም በጀትና ሪፖርት ያፀድቃል፣

፭. በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፡፡

፲፪. ስለቦርድ አባላት

፩. የሥራ አመራር ቦርዱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲን በማስፈፀም ረገድ ጉልህ ሚና ካላቸው የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እና የከተማው አስተዳደር ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምክር ቤት አባላት ከሆኑ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ በከንቲባው የሚሰየም አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

፪. የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በከንቲባው ይመደባል፡፡

፲፫. ስለሥራ አመራር ቦርድ አባላት ስብሰባ

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰባሰብ ይችላል፡፡

፪. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫. ቦርዱ ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ይወክላል ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሣብ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጽሕፈት ቤቱ የክፍለ ከተማ አካላት ሥልጣን ተግባርና አሠራር

## ምዕራፍ አንድ

## የዴስኩና የኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

### ፲፬. የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ

የዴስክ ሥልጣንና ተግባር

፩. የክፍለ ከተማውን ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ የሥራ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፪. በቀበሌ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ኮሚቴዎች የሚሠሩ ሥራዎች ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ እንዲታቀዱ በክፍለ ከተማው ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲገመገምና እንዲፀድቁ ለማድረግ በሥሩ ያሉትን ቀበሌዎች የሥራ ፕሮግራሞች በማጠናቀር ያቀርባል፤

፫. ክፍለ ከተማው ውስጥ የተለያዩ ማኅበራትና ዕድሮች እንዲሁም የክፍለ ከተማ አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት በተለያየ መልክ እንዲቀናጁና ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሠሩ ያበረታታል፤ ያስተባብራል፡፡ ሥራዎቻቸውን በሚመለከት መረጃ ያጠናቅራል፤ ለጽህፈት ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

፬. በክፍለ ከተማው ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስ ወረርሺኝ ሊያስፋፉ የሚችል ሁኔታዎችን በመለየት ችግሮች እንዲፈቱ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሠራል፣ በክፍለ ከተማው ውስጥ የፈቃደኝነት ደም ምርመራና የምክር አገልግሎቶች የሚያስፋፉበትን ሁኔታ ያቅዳል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ኅብረተሰቡም እንዲጠቀምባቸው ይቀሰቅሳል፤

፭. የክፍለ ከተማው ኅብረተሰብ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖረው ስለቫይረሱ መተላለፊያ መንገዶችና በኅብረተሰቡ ላይ ስለሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ቀውስ ያወያያል፤ የክፍለ ከተማው ህዝብ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ሥልቶች በክፍለ ከተማው ውስጥ እንዲተገበሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ያስተባብራል፤

፯. በክፍለ ከተማው ውስጥ የኮንዶም አቅርቦት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፯. በክፍለ ከተማው ውስጥ ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናትና ጧሪ ያጡ አረጋውያንን በተመለከተ መረጃ ያጠናቅራል፣ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትንም ሁኔታ ያመቻቻል፤

፰. የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር የፕሮጀክት ፈፃሚ አካላት የአፈፃፀም ብቃት እንስኖራቸው ለማድረግ ከጽሕፈት ቤቱ መምሪያዎች ጋር በቅርበት ይሠራል፤

፱. በክፍለ ከተማው ውስጥ በሚካሄዱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ጥናቶችና ምርምረሬች ይሳተፋል፤ ለተፈፃሚነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

<u>፲፰. የዴስክ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የሚመደብ ሆኖ የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊ ለክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተጠሪ ሆኖ፤

፩. በዴስኩ አስፈፃሚነት በክፍለ ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት የዴስኩን ሥራዎች ይመራል ያስተዳድራል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፤

ሀ) የዴስኩ ኃላፊ በክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባዎች በአባልነት ይሳተፋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ የተመለከቱትን የዴስኩን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ለይ ያውላል፤

ሐ) የዴስኩን ሠራተኞች በከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት ያስተዳድራል፤

መ) የዴስኩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ለይ ያውላል፤

ሠ) ለዴስኩ በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ዴስኩን ይወክላል፤

ሰ) የዴስኩን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለክፍለ ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤

ሸ) የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሣኔ ያረፈበትን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

፫. የዴስኩ ኃላፊ ለዴስኩ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለዴስኩ ልሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ለላያስተላልፍ ይችላል፡፡ ሆኖም እርሱ በማይኖርበት ጊዜ የሚወክለው ሰው ከ" ቀናት በላይ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ቀርቦ መፈቀድ አለበት፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ተግባር፣ አመሠራረትና ስብሰባዎች</u>

፲፮. <u>የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር</u>

የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል ለመቆጣጠር በክፍለ ከተማ ውስጥ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች የከተማው አስተዳደር የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በቀየሰው ስልት መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

፪. በክፍለ ከተማው ውስጥ በክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶችና መምሪያዎች፤ እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚካሄዱ የኤች አይቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ ይገመግማል፣ የማሻሻያና የማጠናከሪያ ሃሣቦችን ያቀርባል፤

፫. በክፍለ ከተማው ውስጥ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች ሕሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናትና ቤተሰቦቻቸው የጤና እንክብካቤ፣ የሥነ ልቦና ምክርና እንደሁኔታው ማኅበራዊ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱንና ሰብአዊ መብታቸው መከበሩን ይከታተላል፤

፬. ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚሰበሰብ እርዳታ የከተማው አስተዳደር ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት በክፍለ ከተማው ውስጥ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፭. ዓላማውን ለማስፈጸም በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሃሣብ ያመነጫል፣ ሃሣቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎችንም ያቋቁማል፤

፲፯. <u>የጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት</u>

የክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ ጉባኤ በክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩. የክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎች፤

፪. የክፍለ ከተማው ምክር ቤት አፈጉባዔ፤

፫. የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፣

፬. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፬-፯) የተመለከቱት መሥሪያ ቤቶች የክፍል ከተማ መምሪያዎች፣

፭. የክፍል ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊና የክፍል ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣

፮. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፲-፲፭) የተመለከቱት አካላት የክፍል ከተማ ተወካዮች፣

፯. በክፍል ከተማው ውስጥ የሚገኙ የግል ክሊኒኮች ባለቤቶች፣

፰. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪/፬ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ በክፍል ከተማው ውስጥ ኤች አይ ቪ/ኤድስ በመከላከልና በመቆጣጠር ተግባር የተሰማሩ ልሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች እና

፱. በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰየሙ የክፍል ከተማው ታዋቂ ነዋሪዎች፡፡

፲፰. <u>የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች</u>

የክፍል ከተማውን አች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ በተደነገገው የስብሰባ ሥነ ስርዓት ይመራል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የክፍል ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣ አመሠራረትና ስብሰባ</u>

፲፱. <u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

<u>ኮሚቴው፣</u>

፩. ዴስኩ የሚከታተላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ መልክ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. በክፍል ከተማው ውስጥ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር ተያይዘው በሚነሱና አመራር በሚሹ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ውሣኔ ይሰጣል ወይም ከአስተያየቱ ጋር ለክፍል ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚና ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

፫. ለክፍል ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የሚቀርበውን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና ሪፖርት ያፀድቃል፣

፬. በዴስኩ ኃላፊ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፡፡

፳. <u>ስለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት</u>

ኮሚቴው፣

፩. ከክፍለ ከተማው አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት፣ የክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ከሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል በከንቲባው በሚሰጥ አጠቃላይ አመራር መሠረት በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤

፪. የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይመደባል፡፡

፳፩. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ

ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ በተመለከቱት የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ሥነ ሥርዓቶች ይመራል፡፡

## ክፍል አራት

## የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ የሥልጣን አካላት

### ምዕራፍ አንድ

### የቀበሌው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የዴስኩና የኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

፳፪. የዴስኩ ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ፣

፩. የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጉባኤ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

፪. የጉባኤውን አስተያየት አካትቶ የተዘጋጀ ቀበሌ አቀፍ ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ለቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለክፍለ ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

፫. የቀበሌው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲሁም በቀበሌው ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ፕሮግራም የሚያካሂዱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ያስተባብራል፤ የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፬. በክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ቀበሌውን በሚመለከት የሚሰጡትን ኤች አይቪ/ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፳፫. የዴስክ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

በክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊ የሚመደብ የቀበሌው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊ ለቀበሌ ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለክፍለ ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊ ተጠሪ ሆኖ፤

፩. በዴስኩ አስፈፃሚነት በቀበሌ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በክፍለ ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊ በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት የዴስኩን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዴስኩ ኃላፊ፤

ሀ) የዴስክ ኃላፊ በቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች በአባልነት ይሳተፋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ የተመለከቱትን የዴስኩን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) በክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ኃላፊ በሚሰጠው ውክልና መሠረት የዴስኩን ሠራተኞች በከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፤

መ) የዴስኩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ለዴስኩ በተቀፈደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ዴስኩን ይወክላል፤

ሰ) የዴስኩን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሸ) የቀበሌውው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሣኔ ያረፈበትን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለክፍለ ከተማ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ ያቀርባል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር፣ አመሠራረትና ስብሰባ

፳፬. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር፡-

የቀበሌው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጉባዔ፤

፩. ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለመከላከያና ለመቆጣጠሪያ በቀበሌው ውስጥ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች የከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በቀየሰው ስልት መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤

፪. በቀበሌው ውስጥ በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት የሥራ ክፍሎች፣ እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚካሄዱ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠር ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ ይገመግማል፣ የማሻሻያና የማጠናከሪያ ሃሣቦችን ያቀርባል፡፡

፫. በቀበሌው ውስጥ ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ሕሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናትና ቤተሰቦቻቸው የጤና እንክብካቤ፣ የሥነ ልቦና ምክርና እንደሁኔታው ማኀበራዊ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱንና ሰብአዊ መብታቸው መከበሩን ይከታተላል፤

፬. ዓላማውን ለማስፈፀም በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ሃሣብ ያመነጫል፣ ሃሣቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎችንም ያቋቁማል፡፡

<u>፳፫. የጉባዔው አመሠራረት</u>

የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ጉባኤ በቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚመራ ሆኖ፣ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩. በቀበሌው ደረጃ የተዋቀሩ የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ኃላፊዎች፤

፪. የቀበሌው ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፤

፫. በቀበሌው የሚገኙ እድሮች ሰብሳቢዎች እና

፬. በጉባዔው የሚሰየሙ ታዋቂ የቀበሌው ነዋሪዎች፡፡

<u>፳፬. የጉባኤው ስብሰባዎች</u>

የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጉባኤ በዚህ አዋጅ በተደነገገው የከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ይመራል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር አመሠራረትና ስብሰባዎች</u>

<u>፳፭. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው፤

፩. ዴስኩ የሚከታተላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ መልክ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. በቀበሌው ውስጥ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር ተያይዘው በሚነሱና አመራር በሚሹ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ውሣኔ ይሰጣል፤ ወይም ከአስተያየቱ ጋር ለቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለክፍለ ከተማው ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፫. ለቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለክፍለ ከተማው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዴስክ የሚቀርበውን የሥራ ፕሮግራም በጀትና ሪፖርት ያፀድቃል፤

፬. በዴስኩ ኃላፊ በሚቀርቡለት ልሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፤

፭. ሰብሳቢው ከአባላቱ መካከል በቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይመደባል፡፡

፳፰. ስለ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

ኮሚቴው፤

፩. ከቀበሌው አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እና የቀበሌውው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጠቅላላ አባላት ከሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሚሰጠው አጠቃላይ አመራር መሠረት በቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፤

፪. የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይመደባል፡፡

፳፱. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ

የቀበሌው ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ በተደነገገው የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ይመራል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴. የጽሕፈት ቤቱ በጀትና አስተዳደሩ

፩. የጽሕፈት ቤቱ መደበኛ በጀት በከተማው አስተዳደር ይመደባል፡፡

፪. ጽሕፈት ቤቱ ለሚያስፈጽማቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገው በጀት ከከተማው አስተዳደር፣ በለጋሽ ድርጅቶችና በኅብረተሰቡ ከሚደረግ የገንዘብ መዋጮና ከውጭ ከሚገኝ የከተማው አስተዳደር ብድር የተውጣጣ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው በጀት የገንዘብ መዋጮዎች ከተደረጉበት የብድርና የእርዳታ ስምምነቶች ጋር በተጣጠመ መልኩና በሥራ አመራር ቦርዱ በፀደቀ የጽሕፈት ቤቱ የግዥና የወጪ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት በጥቅም ላይ ይውላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ገንዘብ በጽሕፈት ቤቱ ስም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ና (፪) ለተመለከቱት የገንዘብ ምንጮች የተለያዩ የሂሣብ መዝገቦች ይይዛል፡፡

፮. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና አስተዳደር ወይም የከተማው ዋና አስተዳደር በሚሰይመው አስተዳደር ይመረመራል፡፡

፴፩. የመተባበር ግዴታ

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲ አፈፃፀምን በማስተባበርና በመምራት ረገድ ጽሕፈት ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በከተማው ውስጥ የሚኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

፴፪. የተሻሩ ሕጎች

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፳፩/፪ሺህ ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፴፫. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ተላልፈዋል፡፡

፴፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ፶፯ /፪ሺ፮

ክፍል አንድ_ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩.አጭር ርዕስ

፪.ትርጓሜ

፫ . የተፈፃሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት የውሻ መዝገብ ስለማቋቋምና ስለመመዝገብ

፬. የውሻ መዝገብ ስለማቋቋም

፭. በውሻ መመዝገቢያ መዝገብ ስለማስመዝገብ

፮. ስለ ምዝገባ ማመልከቻ

፯. የምዝገባ መረጃዎቹንና ሰነዶችን ስለማስተላለፍ

፰. ከመዝገብ ስለመሰረዝ

፱.ምትክ የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፲.የውሻ እብደት በሽታ መኖርን ወይም ጥርጣሬ ስለማሳወቅ

፲፩.የውሻ እብደት  በሽታ መኖሩን ለማረጋገጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት

፲፪.የውሻ ዕብደት በሽታ የተከሰተበትን አካባቢ ይፋ ስለማድረግ

፲፫.የውሻ ዕብድር በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የውሾቹን እንቅስቃሴ ስለመቆጣጠር

፲፬.በውሻ  ዕብደት በሽታ የተጋለጠ ውሻን በቁጥጥር ሥር ስለማዋል ወይም ስለማስወገድ

፲፭.የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የእንስሳት ውሻን በቁጥጥር ስር ስለ ማዋልና ስለማስወገድ

ክፍል ሶስት ስለ ውሻ ክትባትና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

፲፮. ስለ ውሻ ባለቤትነት፣ ስለ ውሻ ክትባት የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ውሻን ስለማምከን

፲፯.የውሻ  ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ ለውሾች የሚሰጥ መከላከያ ክትባት

፲፰. ተልከስካሽ ውሾችን ስለ መያዝና ማስወገድ

፲፱. የውሻ ባለቤት መብትና ግዴታ

ክፍል አራት የአስፈፃሚ አካላት ስልጠንና ተግባር

፳.የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

፳፩. የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ማስወገድ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት

፳፪. የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን

፳፫. የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ

፳፬. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት

ክፍል አምስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፭.ቅጣት

፳፮.የመተባበር ግዴታ

፳፯.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፳፰. ተፈፃሚነት ስለሚይኖራቸው ሕጎች

፳፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

የሰውንና የእንስሳትን ሕይወት ከዚህ አደገኛ በሽታ ለመታደግና የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የውሻ እብደት በሽታ መከላከያ ክትባት ለመደንገግ እና ምዝገባ ያካተተ ነው፡፡ ይህን ግዴታ ተላልፈው የተገኙ እንደሆነ አግባብነት ያላቸው የፖሊስ እና ደንብ ማስከበር ተቋማት እርምጃ ስለሚወስዱበት ሁኔታ እና የቅጣት አወሳሰን ያካተተ ደንብ ነው፡፡

## <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ፶፯/፪ሺ፮</u>

በአዲስ አበበ ከተማ የውሻ ዕብደት በሽታ ክስተትና ስርጭት ከምንጊዜም የበለጠ እየተሰፋፋ በመምጣቱ ሰውንና የተለያዩ እንስሳትን በመጉዳት ለሞት በመዳረግ ላይ በመገኘቱ፤

የሰውንና የእንስሳትን ሕይወት ከዚህ አደገኛ በሽታ ለመታደግና የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የውሻ እብደት በሽታ መከላከያ ክትባት መስጠት፣ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ በአንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሻ ዕብደት በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ቁጥር ፶፯/፪ሺ፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.<u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩.“ቢሮ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

፪.“አግባብ ያለው ባለስልጣን” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ወይም በቢሮው የተወከለ አካል ነው፤

፫.“ክፍለ ከተማ” ማለት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፪(፭) የተመለከተው የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፬.“ወረዳ” ማለት የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፭.“እንስሳ” ማለት ለዚህ ደንብ ዓላማ ሲባል የቤትና የዱር እንስሳትን ያጠቃልላል፤

፮.“ለውሻ ዕብደት በሽታ የተጋለጠ” ማለት በበሽታው መለከፋ የተረጋገጠ ወይም በተጠረጠረ ውሻ የተነከሰ፣ ወይም ሌላ ቀጥታ ግንኙነትና ንክኪ የነበረው ሰው ወይም እንስሳት ነው፤

፯."በሽታው የተከሰተበት አካባቢ" ማለት የውሻ እብደት በሽታ የተገኘበት ወይም መኖሩ የተጠረጠረበት አካባቢ ነው፤

፰."የውሻ ምዝረባ ሠርቲፊኬት" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈቀድና አግባብ ባለው ባለስልጣን ለውሻው ባለቤት የሚሰጥ የምዝገባ ሰርቲፊኬት ነው፤

፱."የውሻ ባለቤት" ማለት በግል ወይም በጋራ የውሻ ባለቤትነት ማስረጃ ሠርተፊኬት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲."ተልከስካሽ ውሻ" ማለት ባለቤት የሌለው ወይም ከውሻው ባለቤት ቅጥር ግቢ ውጪ በመንገድ ላይ በሌላ ሰው ይዞታ ወይም ለውሻ ባልተፈቀደ ሥፍራ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ እና በመሳሰሉት ቦታዎች ሲዘዋወር የተገኘ ነው፤

፲፩."የመከላከያ ክትባት" ማለት የተዳከመ ወይም ሕይመት የሌለው የበሽታ መንስኤ ተህዋሲያን ውጤት ሆኖ ለጤነኛ እንስሳት በመርፌ የሚሰጥና እንስሳትን ከበሽታ የሚከላከል ነው፤

፲፪."የእንስሳት ጤና ባለሙያ" ማለት በየደረጃው የሚሰጠውን እንስሳት ሕክምና ትምህርት ተከታትሎ በሠርተፊኬት፣ በዲፕሎማ፣ በዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ደረጃ ያለውና ሙያውን ለመተግበር የተፈቀደለት ሰው ነው፤

፲፫."የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሠራተኛ" ማለት በየደረጃው የሚሠጠውን አነስተኛ የቤት እንስሳትን እንደ ውሻ፣ ድመት እና የመሳሰሉትን ተከታትሎ ለመያዝና ለማስወገድ በቢሮው የተመደበ ሥራውን ለመተግበር የተፈቀደለት ሰው ነው፤

፲፬."ማምከን" ማለት ውሾች በቀዶ ጥገና እንዳይወልዱ ማድረግ ነው፤

፲፭."የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ" ማለት ደረጃውን ጠብቆ የተሰራ ለማንኛውም እንስሳት ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ነው፤

፲፮."ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፯.በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀርበ በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫ . <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ የውሻ ባለቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የውሻ መዝገብ ስለማቋቋምና ስለመመዝገብ</u>

፬. <u>የውሻ መዝገብ ስለማቋቋም</u>

የሚከተሉት የውሻ መመዝገቢያ መዛግብት ተቋቁመዋል፡-

፩.በቢሮው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት የሚተዳደር ከተማ አቀፍ የውሻ መመዝገቢያ መዝገብ፤

፪.በየወረዳው የንግድና እንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ወይም በወረዳ የከተማ ግብርና አስተባባሪ የሚተዳደር የውሻ መመዝገቢያ መዝገብ፡፡

፫. <u>በውሻ መመዝገቢያ መዝገብ ስለማስመዝገብ</u>

፩. ማንኛውም ሰው ውሻውን ሳያስመዘግብ የውሻ ባለቤት መሆን አይችልም፤

፪. ማንኛውም ሰው ውሻውን የሚያስመዘግበው በሚኖርበት ወረዳ ይሆናል፤

፫. ማንኛውም ሰው ውሻውን የሚያስመዘግበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤

፬. የውሻ ባለቤት የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ ቀድሞ ላስመዘገበበት የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት በማሳወቅ ወደ አዲሱ አድራሻ ደብዳቤ በመውሰድ እና በማሳወቅ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፬. <u>ስለ ምዝገባ ማመልከቻ</u>

፩. ማንኛውም ሰው የውሻ ባለቤት መሆን ከፈለገ ወይም ቀደም ሲል የውሻ ባለቤት ከሆነ በቢሮው የሚዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና አስፈላጊውን ማስረጃ በማያያዝ ለወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

፪. የውሻው ባለቤት የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ በቢሮው ሚዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፫. ለመዝገብ የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት በቢሮው ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ የውሻ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት የቀረበለት የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ሲያረጋግጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፭. <u>የምዝገባ መረጃዎቹንና ሰነዶችን ስለማስተላለፍ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የውሻ ባለቤትነት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዝገባ መረጃዎቹን ወዲያውኑ ለክፍለ ከተማው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ያስተላልፋል፤ ክፍለ ከተማውም ወዲያውኑ ለቢሮው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

፪. የቢሮው ከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የተላለፉትን የምዝገባ መረጃዎች በከተማ የውሻ ባለቤት መዝገብ መዝግቦ ይይዛል፡፡

፮. <u>ከመዝገብ ስለመሰረዝ</u>

፩. የውሻው ባለቤት ሲሞት የሚች ወራሾች በሚች ባለቤትነት የተመዘገበው መዝገብ እንዲሰረዝላቸው ለመዘገበው ወረዳ ማመልከቻ ሲያቀርቡ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ወራሾቹ የውሻው ባለቤት መሆን ከፈለጉ የተስማማበትን የስምምነት ውል ለወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ካቀረቡ በውሉ መሠረት የውሻው ባለቤትነት ምዝገባ ይካሄዳል፡፡

፫. ለመዝገብ የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት በቢሮው ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ የውሻ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት የቀረበለት የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ሲያረጋግጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፯. <u>የምዝገባ መረጃዎቹንና ሰነዶችን ስለማስተላለፍ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የውሻ ባለቤትነት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዝገባ መረጃዎቹን ወዲያውኑ ለክፍለ ከተማው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ያስተላልፋል፤ ክፍለ ከተማውም ወዲያውኑ ለቢሮው የከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

፪. የቢሮው ከተማ ግብርና ዋና የስራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የተላለፉትን የምዝገባ መረጃዎች በከተማ የውሻ ባለቤት መዝገብ መዝግቦ ይይዛል፡፡

፱. <u>ከመዝገብ ስለመሰረዝ</u>

፩. የውሻው ባለቤት ሲሞት የሚች ወራሾች በሚች ባለቤትነት የተመዘገበው መዝገብ እንዲሰረዝላቸው ለመዘገበው ወረዳ ማመልከቻ ሲያቀርቡ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውራሾቹ የውሻው ባለቤት መሆን ከፈለጉ የተስማማበትን የስምምነት ውል ለወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ካቀረቡ በውሉ መሠረት የውሻው ባለቤትነት ምዝገባ ይካሄዳል፡፡

፫. የውሻው ባለቤት ውሻውን አልፈልግም በማለት በጽሁፍ ለወረዳው ሲያመለክት፡፡

፬. ውሻው በመሞቱ ምክንያት የወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ከመዘገብ ሲሰርዘው፡፡

፱.<u>ምትክ የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

የውሻ ባለቤትነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል ምዝገባ ላከናወነበት ወረዳ በጽሁፍ በማመልከትና አስፈላጊውን ክፍያ በመፈጸም ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፲.<u>የውሻ እብደት በሽታ መኖርን ወይም ጥርጣሬ ስለማሳወቅ</u>

፩.ማንኛውም ሰው በማንኛውም እንስሳት ላይ የውሻ ዕብደት በሽታ መኖሩን እንዳወቀ ወይም ሲጠረጥር ወይም በበሽታው ምክንያት ሞት መከሰቱን እንዳወቀ በአቅራቢያው ለሚገኘው እንስሳት ጤና ክሊኒክ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ወይም ለፖሊስ ወይም ለህዝብ ጤና ተቋም በፍጥነት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም በውሻ እብደት በሽታ የታመመ ወይም የተጠረጠረ ወይም የሞተ እንስሳ ከሰውም ሆነ ከእንስሳት ተለይቶ በርቀት ለብቻው መጠበቅ ወይም መያዝ አለበት፡፡

<u>፲፩.የውሻ እብደት በሽታ መኖሩን ለማረጋገጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት</u>

፩. የእንስሳት ጤና ባለሙያ በደረሱት መረጃዎች መሠረት አንድ ውሻ የውሻ እብደት በሽታ የተያዘ ስለመሆኑ መረጃ ከደረሰው በውሻው ላይ ተጨማሪ የማረጋገጫ ምርመራ ሊያካሂድ ወደሚችል አካል ይልካል፡፡

፪. በውሻ ዕብደት በሽታ ተጠርቅሮ ክትትል እየተደረገበት ያለ ውሻ ወይም ሲልከሰከስ የተገኘ ውሻ ቢወገድ የካሳ ክፍያ አይጠየቅበትም፡፡

<u>፲፪.የውሻ ዕብደት በሽታ የተከሰተበትን አካባቢ ይፋ ስለማድረግ</u>

ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውሻ ዕብደት በሽታ የተከሰተበትን አካባቢ ይፋ በማድረግ በሽታውን ለመቆጣጠር እንዲቻልና እንዳይዛመት ለማረግ በዚህ ደንብየተዘረዘሩት ተግባራት እንዲፈጸሙ ያደርጋል፡፡

<u>፲፫.የውሻ ዕብድር በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የውሾቹን እንቅስቃሴ ስለመቆጣጠር</u>

፩.የውሻ ዕብደት በሽታ የቁጥጥርና የመከላከል ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ ማንም ሰው አግባብ ካለው ባለስልጣን ህጋዊ የማዘዋወሪያ ፈቃድ ሳያገኝ የውሻ ዕብደት በሽታ ከተከሰተበት አካባቢ ውሻን ወደ ሌላ አካባቢ መውሰድ፣ ማዘዋወር ወይም ከሌላ አካባቢ የውሻ ዕብደት በሽታ ወደ ተከሰተበት ቦታ ማምጣት አይችልም፡፡

፪.የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የሚኖር ማንኛውም የውሻ ባለቤት የሆነ ሰው ውሻውን ለብቻው ለይቶ በማሰር መጠበቅ አለበት፡፡

፫.ከውሻው ባለቤት ይዞታ ውጪ ከባለቤቱ ተለይቶ ሲዘዋወር የተገኘ ማንኛውም ውሻ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ባለሙያ ይወገዳል፡፡

<u>፲፬.በውሻ ዕብደት በሽታ የተጋለጠ ውሻን በቁጥጥር ሥር ስለማዋል ወይም ስለማስወገድ</u>

፩.የእንስሳት ጤና ባለሙያ የመከላከያ ክትባት መውሰዱን የሚያረጋግጥ መረጃ ያለው ውሻ ከሌላ የውሻ ዕብደት በሽታ ከያዘው ወይም መያዙ ከሚጠረጠር ውሻ ጋር ከተገናኘ እንደገና እንዲከተብና በቁጥጥር ስር ሆኖ ለ ፲ ቀናት ለብቻው እንዲጠበቅና በባለሙያ ክትትል እንዲደረግበት ይወስናል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ዓይነት ጉዳይ ሲያጋጥም የእንስሳት ጤና ባለሙያ ውሻው ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ በአቅራቢያው በሚገኘው የእንስሳት ጤና ክሊኒክ እየቀረበ እንዲታይና ክትትል እንዲደረግበት ይመስናል፡፡

፲፭.<u>የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ የእንስሳት ውሻን በቁጥጥር ስር ስለ ማዋልና ስለማስወገድ</u>

፩.አንድ ሰው በተከተበም ሆነ ባልተከተበ ውሻ ቢነከስ የውሻው ባለቤትና የተነከሰው ሰው በአስቸኳይ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የህክምና ተቋም ቀርበው ሪፖርት ማድረግና የመጀመሪያ እርዳታ እንዲያገኝ ማድረግ አለባቸው፤ ሪፖርት የቀረበላቸው የአካባቢ አስተዳደርና ፖሊስ አካላት ሁኔታውን የመከታተል ግዴታ አለባቸው፤ በውሻ የተነከሰ ሰው የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ካገኘ በኋላ በአካባቢው ወደ ሚገኘው ጤና ማዕከል በፍጥነት መወሰድ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም ውሻ የመንከስ ጉዳት ሲያደርስ ባለቤቱ ውሻውን የማስመርመር ግዴታ አለበት፡፡

፫.ውሻው የውሻ ዕብደት በሽታ ምልክቶች የሚያሳይ ከሆነ ባለቤቱ እንዲያወቀው በማድረግ በእንስሳት ጤና ሠራተኛ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፬.ውሻው ጤናማ መስሎ ከታየ ወይም ባለቤቱ እንዲወገድ ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲካሄድበት ካልተስማማ ቢሮው ወይም አግባብነት ያለው ባለስልጣን በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ለብቻው አቆይቶ የጤናው ሁኔታ ክትትል ይደረግበታል፡፡

፭.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ክትትል የተደረገለት ውሻ ጤናማ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለቤቱ ውሻውን አስከትቦ እንዲወስድ ይደረጋል፡፡

፮.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ክትትል ተደርጎለት ጤናማ ያልሆነ ውሻ በባለሙያ ይወገዳል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለ ውሻ ክትባትና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

፲፮. <u>ስለ ውሻ ባለቤትነት፣ ስለ ውሻ ክትባት የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ውሻን ስለማምከን</u>

፩.ማንኛውም የውሻ ባለቤት የሆነ ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ መሠረት የውሻው ዕድሜ ሶስት ወር ሲሞላው በሚኖርበት የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት እየቀረበ የማስመዝገብ ፣ የውሻ ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የማግኘትና ሰርተፊኬቱን በየዓመቱ የማሳደስ ግዴታ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም የውሻ ባለቤት ለውሻው ማስመዝገቢያና የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ወይም ድጋሚ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፫.ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ውሻውን ለክትባት ሲያቀርብ ውሻው በሶስት ወር ዕድሜውና ከዚያም በኋላ በተሰጠው የክትባት ቆይታ ጊዜ መሠረት የውሻ ዕብደት በሽታ መከላከያ ክትባት ወቅቱን ጠብቆ መከተቡን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፬.ለእያንዳንዱ የተመዘገበ ውሻ አግባብ ያለው አካል ክትባት ይሰጣል፤ ለዚህም ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፭.በእያንዳንዱ ውሻ አንገት ላይ የሚንጠለጠል መለያ ምልክት ወይም ታግ ወይም ኮላር በመጀመሪያው የክትባት ወቅት ይደረጋል፡፡

፮.የውሻ ባለቤት የሆነ አንድ የከተማዋ ነዋሪ ውሻውን ለማምከን ወይም ለማኮላሸት ፈቃደኛ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል፡፡

<u>፲፮.የውሻ ዕብደት በሽታ በተከሰተበት አካባቢ ለውሾች የሚሰጥ መከላከያ ክትባት</u>

፩.በአንድ የከተማዋ አካባቢ የውሻ ዕብደት በሽታ ሲከሰት ወይም ሲጠረጠር በእንስሳት ጤና አገልግሎት ሠራተኛ የመከላከያ ክትባት ዘመቻ ያዘጋጃል፡፡

፪.ሁሉም ዕድሜያቸው ከሶስት ወር በላይ የሆናቸው ውሾች ቢሮው ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያወጣው ማስታወቂያ መሠረት የውሻ ዕብደት በሽታ መከላከያ ክትባት መከተብና በተወሰነ ጊዜም ተከታታይ ማጠናከሪያ ክትባት ማግኘት አለባቸው፡፡

፫.የመከላከያ ክትባቱ የሚሰጥበትን ጊዜና ቦታ በሚመለከተው አካል ይወስናል፡፡

፬.የውሻ ባለቤቶች ውሾቻቸውን በተባለው ጊዜና ቦታ እያቀረቡ ማስከተብ አለባቸው፡፡

፭.ውሾች መከላከያ ክትባት ሲከተቡ መከተባቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ይሰጣቸዋል፣ በአንገታቸውም ላይ ልዩ መለያ ምልክት ይደረጋል ወይም ይንጠለጠላል፡፡

<u>፲፰. ተልከስካሽ ውሾችን ስለ መያዝና ማስወገድ</u>

፩.ቢሮው ከፖሊስና ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር በቅድሚያ አስፈላጊውን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለህብረተሰቡ ከሰጠ በኋላ ማንኛውም ሲዘዋወር የተገኘ ተልከስካሽ ውሻ እንዲገደልና እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፪.ማንኛውም ለመያዝ አስቸጋሪ የሆነ ተልከስካሽ ውሻ በተገኘበት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፫.ተልከስካሽ ውሻ ለመያዝና ለማስወገድ ስልጣን የተሰጠው አካል በማናቸውም ሁኔታ ተልከስካሽ ውሻን መያዝና ማስወገድ ይችላል፡፡

፬.የተገደሉ ተልከስካሽ ውሾችን ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ፣ በአግባቡ ለመቅበት ወይም ለማቃጠል ቢሮው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡

፭.ሲልከሰከስ ለተወገደ ውሻ ባለቤት ካሳ አይከፈልም፡፡

<u>፲፱. የውሻ ባለቤት መብትና ግዴታ</u>

፩. መብት

ሀ.ማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ውሻን በባለቤትነት የመያዝና የማሳደግ መብት አለው፤

ለ.አንድ የውሻ ባለቤት ውሻውን ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት አሳልፎ የመስጠት፣ ውሻውን በሚፈለግበት ጊዜ በማመለከተው አካል እንዲወገድለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

፪.ግዴታ

ማንኛውም የውሻ ባለቤት፡-

ሀ) የውሻ ባለቤት ለመሆን ባለውሻው ውሻው በሚገኝበት ወረዳ የንግድና ኢንዱስትሪ ከልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ውሻውን ይዞ በመቅረብ አስመዝግቦ የባለቤትነት ማስረጃ መያዝ አለበት፤

ለ) ውሻውን በየአመቱ ማስከተብ አለበት፤

ሐ) ውሻውን በይዞታው ስር አድርጎ ጤናውን፣ አመጋገቡን እና አያያዙን መንከባከብና መከታተል አለበት፣ በተጨማሪም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በአግባቡ አስሮ መያዝና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፤

መ) ውሻውን ከተመዘገበበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ሲያዛውር ቀድሞ በተመዘገበበት ወረዳ የንግደና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት መልቀቂያ በመውሰድ በተመዘገበበት ወረዳ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ማስመዝገብ አለበት ፤

ሠ) ውሻውን በውሻ ዕብደት በሽታ ከተለከፈ ባለቤቱ ኃላፊነት ስላለበት በአካባቢው ለሚገኘው የወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት ወይም ለፖሊስ ወይም ለጤና ባለሙያ ማሳወቅና ቀጣይ እርምጃ ማስወሰድ አለበት፤

ረ) ውሻው ሲሞት እንዲቀበር በማድረግ ለማዘገበው ወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት የከተማ ግብርና የስራ ሂደት በማሳወቅ ከመዝገብ ማሰረዝ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር</u>

፳.<u>የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ</u>

፩.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭፣ ፮፣ ፯(፩)፣ ፰፣ ፱ የተቀመጡትን ተግባራት ያከናወናል፡፡

፪.ያልተከተቡ ውሾች ሲገኙ እንዲወገዱ ለክፍለ ከተማ ወይም ለወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፡፡

፫.ባለቤት ያላቸው ውሾች በወቅቱ እንዲከተቡና እንዲመዘገቡ ያደርጋል፡፡

፬.ውሾቻቸውን ያላስከተቡ ባለቤቶች እንዲያስከትቡ ያደርጋል፡፡

፭.በመከላከያ ክትባት ዘመቻ ወቅት ሕብረተሰቡ ውሾችን እንዲያስከትብ ቅስቀሳ ያደርጋል፡፡

፤.በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ውሾች መመዝገባቸውንና መከተባቸውን፣ መለያ ቁጥራቸውንና ሰርቲፊኬት በማየት አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

፳፩. <u>የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ማስወገድ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት</u>

፩.ለተወገዱት ውሾች የማንሻና ማቆያ ቦታ ያዘጋጃል፤

፪.ለተወገዱ ውሾች ማጓጓዝ የተዘጋጁ ገንዳዎችን በየዕለቱ በማንሳትና ወደ ማዕከላዊ የቆሻሻ መጣያ ቦታ በማጓጓዝ እንዲቀበሩ ወይም እንዲያጠሉ ያደርጋል፡፡

፳፪. <u>የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን</u>

፩.ተልከስካሽ ውሾች በሚወገዱበት ወቅት በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋል፡፡

፪.ለማስወገድ አስቸጋሪ የሆኑ ውሾችና ሌሎች በበሽታው የተጠቁ እንስሳት ሲገኙ በአስወጋጅ ባለሙያዎች የእገዛ ጥያቄ መሠረት በጋራ በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

፫.ውሾቻቸውን ለማስከተብ ወይም ለማስመርመር ወይም ለማስወገድ ፈቃደኛ ያልሆኑ ወይም ለማስወገድ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያቀርበው መሠረት ለመቅረብ እምቢተኛ የሆኑ የውሻ ባለቤቶች በማስገደድ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

፳፫. <u>የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ</u>

፩.ሰውንም ሆነ ማንኛውም የቤት እንስሳት በነከሱ ውሾች ላይ ምርመራ ያስደርጋል፣ የጤንነት ማረጋገጫ ይሠጣል፡፡

፪.በውሻ የተነከሱ ሰዎች በወቅቱ በአቅራቢያቸው ህክምና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፫.በውሻና ድመት ሕክምና ላይ ለተሠማሩ ባለሙያዎች የቅድመ መከላከያ ክትባት ይሰጣል፡፡

፳፬. <u>የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት</u>

ያልተከተቡ ውሾች ቁጥጥር፣ እና እርምጃ አወሳሰድ ላይ ከቢሮው ጋር ተባብሮ ይሰራል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳፭.<u>ቅጣት</u>

አግባብ ባለው ሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ የተዘረዘሩትን የተላለፈ ማንኛውም ሰው እንደሆነ ከብር ፩ሺ እስከ ፪ሺ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፳፮.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፳፯.<u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቢሮው ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፰. <u>ተፈፃሚነት ስለሚይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህንደንብየሚቃረንማንኛውምደንብ፣መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፳፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፤ ዓ.ምጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፤

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፰/፪ሺ፮

<u>ማውጫ</u>


ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫.የተፈፃሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት የምግብ ደህንነትና ጥራት አስተዳደርና ቁጥጥር

፬. መርህ

፭.ምግብን ስለማምረት

፮.ምግብን ስለመከለስ

፯. ምግብን ስለማከማቸት፣ ለዕይታ ማቅረብና ማጓጓዝ

፰.ንጥረ ምግብ

፱.ስለተጨማሪ ምግቦች

፲.የጨቅላና ህጻናት ምግቦችና ማሟያ ምግቦች

፲፩.ምግብን ስለማበልጸግ

ክፍል ሦስት የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር

፲፰.ስለ መድሀኒት አያያዝ

፲፱÷ስለ መድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ

፳.ስለመድኃኒት ማሸጊያዎችና ገላጭ ጽሑፍ

፳፩.ስለህክምና ሙከራ

፳፪÷ስለ ህገ-ወጥ የመድኃኒት ዝውውር

፳፫.ስለ መርዞችና ጨረር አፍላቂ  መድሀኒቶች

፳፬.ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት

፳፭.ስለድኅረ ገበያ ቅኝት

፳፮. ስለናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሣይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮችና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ልዩ ፈቃድ ስለማስፈለጉ

፳፯. መድኃኒትን ስለመያዝና ማስወገድ

ክፍል አራት የትምባሆ ዝግጅት ቁጥጥር

፳፰.ስለትምባሆ ቁጥጥር

፳፱.ስለ ትንባሆ ዝግጅት ማሸጊያና ገላጭ ፅሁፍ

፴.የትንባሆ ዝግጅትን ማስተዋወቅ፣ መረጃና ድጋፍ አሰጣጥ

፴፩.ማጨስ የሚከለከልባቸው ቦታዎች

ክፍል አምስት የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ  አሰጣጥና ቁጥጥር

፴፪.ስለሙያ ስራ ፈቃድ አስፈላጊነት

፴፫.የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት

፴፬.ስለ ሙያ ስራ ወሰን

፴፭.የሙያ ስራ ፈቃድ ስለማሳደስ

፴፮.የተሰጠ የሙያ ስራ ፍቃድ የማይሰራበት ጊዜ

፴፯.ስለጤና ባለሙያዎች መዝገብ

፴፰.የሙያ ስራ ፍቃድን ስለመመለስ

፴፱.ስለ ባህላዊ ሕክምና ባለሙያ

፵.የጤና ባለሙያዎች የስነምግባር ኮሚቴ ስለማቋቋም

፵፩.የጤና ባለሙያዎች የስነምግባር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

፵፪.የስነምግባር ኮሚቴው የስብሰባ ስነስርዓት

፵፫.የስነ-ምግባር ኮሚቴ አባላት

ክፍል ስድስት የጤና ባለሙያ ሥነ-ምግባር

፵፬.መርሆዎች

፵፭.የጤና ባለሙያ ዋና ዋና ኃላፊቶች

፵፮.የድንገተኛ ሕክምናና ሪፈራል

፵፯.መድኃኒት ስለማዘዝና ማደል

፵፰.የአገልግሎት ክፍያና ኮሚሽን

፵፱.ፍቃድ ካለው ባለሙያ ጋር አብሮ መስራት

፶.የሙያ ሚስጥር ስለመጠበቅ

፶፩.የአገልግሎት መድልዎና ታካሚዎችን ስለመላክ

፶፪.ምስጢራዊ ህክምና ስለመከልከሉ

፶፫.ስለ ማስተዋወቅ

፶፬.መድኃኒትንና የህክምና መሳሪያን ስለማስተዋወቅ

፶፭.በምርምር ስለመሳተፍ

፶፮.የሙያ ድጋፍ ወይም ምክር ስለመጠየቅና ስለመስጠት

፶፯.የግል እምነትና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ

፶፰.ሕጋዊ መረጃዎችን ስለመስጠት

፶፱.ስለቆሻሻ አወጋገድና የበሽታን መከላከል

፷.በሽታ ስለሚያስከትለው ሁኔታ ስለመግለጽ

፷፩. የሰውነት አካላትን ስለማስቀረት

፷፪.ስለ ሞትና አስከሬን ምርመራ

፷፫.የታካሚዎች የግል መረጃ አያያዝ

፷፬.ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

ክፍል ሰባት የሃይጂን፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅና የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር

፷፭.የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

፷፮.የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት የሃይጂንና አካባቢ ጤና

፷፯.የድምጽና የአየር ብክለት

፷፰. የመጸዳጃ ቤት እንዲኖር ስለማድረግ

፷፱. ኳራንታይን ስለማድረግና ለይቶ ስለማቆየት

፸.ስለ አደገኛ ኬሚካል

፸፩.ስለ አስከሬን አያያዝ እና ዝውውር

፸፪.ስለተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

፸፫.ስለመታጠቢያ ሥፍራዎችና የመዋኛ ገንዳዎች

፸፬.ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች

፸፭. ስለሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት

ክፍል ስምንት ስለተቋማት

፸፮.ስለ ምግብ ተቋም ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

፸፯.ስለ ጤና ተቋም ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

፸፰.ስለ መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅት

፸፱.ስለ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም

፹.ባህላዊ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ

፹፩.የጤና ምርመራ

፹፪.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለመመለስ

፹፫.የጤና አገለግሎት ተቋም ደረጃ

፹፬.ሥራ ስለማቋረጥ

፹፭.ስለተቋም መስፈርቶች

፹፮.ስለቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪዎች

ክፍል ዘጠኝ ስለ ቦርድና ተቆጣጣሪዎች

፹፯.ስለሥራ አመሪር ቦርድ

፹፰.ስለ ተቆጣጣሪዎች

ክፍል አስር አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና የቅሬታ አቀራረብ

፹፱.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፺.ስለቅሬታ አቀራረብ

ክፍል አስራ አንድ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፺፩.ስለንግድ ማስታወቂያዎች

፺፪.መረጃ ስለመስጠት

፺፫.የመተባበር ግዴታ

፺፬.መረጃ ስለማቅረብ

፺፭.ስለ አገልግሎት ክፍያ

፺፮.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፺፯.ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

፺፰. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ ደንብ በአጠቃላይ ከጤና አጠባበቅ እና መድሃኔት ቁጥጥር ጋር ተያይዞ አስተዳደራዊ የሆኑ ድንጋጌዎችን የያዘ የማሕበረሰቡን ጤንነት ለመጠበቅ ከመድሃኔት አያያዝ፤ የተላላፊ በሽታዎች በተመለከተ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፤ ስለ ንጽህና እና ይህን ደንብ መተላለፍ ስለሚያስከትለው ቅጣት በወናነት በይዘቱ ላይ ተካተዋል።

# <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፷/፪ሺ፮</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና የአዲስ አበባ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር፴/፪ሺ፬ ዓ.ምአንቀጽ ፳፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥር ደንብ ቁጥር ፷/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩."የፌደራል አዋጅ" ማለት የፌደራል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፪ሺ፪ ነው፤

፪."አዋጅ" ማለት የአዲስ አበባ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴/፪ሺ፬ ነው፤

፫."የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት" ማለት ፈቃድ ባለው የሕክምና ባለሙያ ተጽፎ ለሕሙማን የሚሰጥ ደረጃዉን የጠበቀ የመድኃኒት ዕደላ ትዕዛዝ ነው፤

፬."ምግብ" ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ውኃ ወይም ሌላ መጠጥ፣ የሚታኘክ ማስቲካ፣ ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከምና ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትንባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉንጥረ ነገሮችን አይጨምርም፤

፭."ተጨማሪ ምግብ" ማለት ማንኛውም የመደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ የንጥረ ምግብ ወይም ፊዚዮሎጂካል ጥቅም ያላቸው የቫይታሚን ወይም የማዕድን ወይም የሌሎች ንጥረ ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበት በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ በካፕሱል፣ በእንክ ይወክላል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በጠብታ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ነው፤

፮.“የምግብ ጭማሪዎች” ማለት እንደ ምግብ አካል ተቆጥሮ ምግብን ለማጣፈጥ፣ ለማቅለም፣ ሳይበላሽ ለማቆየት ወይም ለማሳመር የሚረዳ በምግብ ላይ የሚጨመር ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

፯.“የምግብ ንግድ” ማለት ምግብንና የምግብ ጥሬ ዕቃዎችን ለንግድ ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ማጭረር፣ ማሸግ፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ ጅምላና በችርቻሮ መሸጥንና የምግብ ጥራት ላቦራቶሪ ሥራን ይጨምራል፤

፰.“የምግብ ተቋም” ማለት ምግብን ለንግድና ለንግድ ላልሆነ ተግባር የሚያውል ድርጅት ነው፤

፱.“የምግብ አምራች” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በባለስልጣኑ ፈቃድ ተሰጥቶት ምግብን የሚያመርትና በከተማው ውስጥ ብቻ የሚያከፋፍልና የሚሸጥ ማለት ነው፤

፲.“ምግብ አዘጋጅ” ማለት ማንኛውም በምግብ ንግድ ስራ ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከምግቡ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ነው፤

፲፩.“የምግብ ደህንነት” ማለት ምግብን በተገቢው መንገድ በማምረት፣ በማዘጋጀት፣ በመያዝ፣ በማከማቸትና በማጓጓዝ ለተጠቃሚ በማቅረብ ሂደት የምግብ ወለድ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር ነው፤

፲፪.“ለብክለት ተጋላጭ ምግብ” ማለት ለበሽታ አምጪ ጥቃቅን ሕዋሳት ዕድገት ወይም ለመርዞች መመረት የተመቻቸ ወይም የተጋለጠ ምግብ ነው፤

፲፫.“የመልካም አመራረት አሰራር” ማለት ማንኛውም የምግብ ወይም የመድሀኒት አምራች ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ ምግብ ወይም ደህንነቱ ፈዋሽነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ መድሀኒት ማምረት እንዲቻል በማምረት ሂደት ወጥነት ባለው ሁኔታ ሊከተለው የሚገባው መሰረታዊ አሰራር ነው፤

፲፬.“መከለስ” ማለት ለንግድ ወይንም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት በሚቀርብ ምግብ ወይንም መድሃኒት ይዘት ላይ ያልተፈቀደ ነገር በመጨመር ወይንም ይዘቱን በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ በሌላ ነገር በመተካት ወይንም በተገቢው መንገድ በንፅህና ባለመመረቱና ባለመያዙ ከባዕድ ነገር ጋር እንዲነካካ ማድረግ ነው፤

፲፭.“የአልኮል መጠጥ” ማለት በማንኛውም መጠን የአልኮል ይዘት ያለው መጠጥ ነው፤

፲፮.“ገላጭ ጽሁፍ” ማለት ስለ አንድ ምግብ ወይም መድኃኒት አስፈላጊውን መረጃ የሚገልጽ በማሸጊያው ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ጽሁፍ ሲሆን በማሸጊያው ውስጥ በአባሪነት የሚከተተውን ጽሁፍ ይጨምራል፤

፲፯.“መድኃኒት” ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የናርኮቲክናሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን፣ ፕሪከርሰር ኬሚካሎች፣ የባህል መድኃኒቶች፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒቶች፣ መርዞች፣ ደምና የደም ተዋጽኦዎች፣ ቫክሲኖች፣

ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶች፣ ኮስሞቲኮች፣ የሳኒተሪ ዝግጅቶች እና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤

፲፰."የመድሃኒት ንግድ" ማለት መድሃኒቶችን ለትርፍ አላማ ማምረት፣ እንደገና ማሸግ፣ በጅምላ ማከፋፈል ወይም በችርቻሮ ከበቂ መረጃ ጋር መሸጥ ወይም ማደል ማለት ነው፤

፲፱."መርዝ" ማለት በአነስተኛ መጠንም ሲወሰድ በሰው፣ በእንስሳት፣ በዕጽዋት ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

፳."የሳኒተሪ ዝግጅት" ማለት የሰው ወይም የቤት ውስጥ ንጽህናን ለመጠበቂያ የሚያገለግል ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን ፓዶችን፣ ታምፖችን፣ የጥርስ ንጽሕና መጠበቂያ ዝግጅቶችን፣ የላብ መምጠጫዎችን እና ዲተርጀንቶችን ይጨምራል፤

፳፩."ፀረ-ተባይ" ማለት ለሰው፣ ለእንሰሳት ወይም ለእጽዋት ጤና አጠባበቅ ሲባል ተባይን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር ወይም ለማጥፋት የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገር ውህድ ነው፤

፳፪."ባህላዊ መድኃኒት" ማለት የእጽዋት፣ የእንስሳት ወይም የማዕድን ተዋጽኦ ሆኖ በነጠላም ሆነ በመቀላቀል ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት የሚውል ዝግጅት ነው፤

፳፫."የሕክምና መሣሪያ" ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር ወይም ለማከም በውስጥ ወይም በውጭ አካል ላይ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላቦራቶሪ፣ የቀዶ ህክምና፣ የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎች እና የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ ሲሪንጆችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻ፣ ጉዝ፣ ጥጥና መሰል ዝግጅቶችን፣ ሰው ሰራሽ ጥርሶችን፣ ኬሚካሎችን፣ የጨረራ ፊልሞችንና ሌሎች መሰል መሳሪያዎችና መገልገያዎችን ይጨምራል፤

፳፬. "ኮስሞቲክ" ማለት ሰውነትን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደም ግባት ለመጨመር ወይም የአካልን ቅርጽና አሠራሩን ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር በገላ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን የቆዳ ቅባቶችን፣ ሎሽኖችን፣ ሽቶዎችን፣ የከንፈር ቀለሞችን፣ የጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ፣ የዓይንና የፊት ማስዋቢያ፣ የጸጉር ማቅለሚያዎችን፣ የጠረን መቀየሪያ ዝግጅቶችን፣ ሜዲኬትድ ሳሙናዎችን እና ለእነዚህ ዝግጅቶች መሥሪያ የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤

፳፭. "የትምባሆ ዝግጅት" ማለት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ከትምባሆ ቅጠል የተዘጋጀ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ ወይም በማሽተት የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው፤

፳፮. "የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት" ማለት በወጣው የጤና ቁጥጥር ደረጃ መሰረት በምግብና በመድሃኒት ወይም በጤናና ጤና ነክ አገልግሎት ወይም በንግድ ስራ የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፤

፳፯. "የሙያ ሥራ ፈቃድ" ማለት የጤና አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥየ ምስክር ወረቀት ነው፤

፳፰. “የሕክምና ባለሙያ” ማለት ሕመምተኛውን በመመርመር የበሽታውን ዓይነት የሚለይና በመድኃኒት ወይም አካልን በመቅደድ የሚያክም የሰው ሐኪም ወይም እነዚህኑ ተግባራት እንዲያከናውን የተመዘገበና የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ነው፤

፳፱. “የጤና ባለሙያ” ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት በባለስልጣኑ ወይም በፌደራል የምግብ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የተመዘገበ ወይም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፴. “የመድኃኒት ባለሙያ” ማለት አግባብ ባለው አካል የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ፋርማሲስት፣ ድራጊስት ወይም ፋርማሲቴክኒሻን ነው፤

፴፩.“ባህላዊ ሕክምና” ማለት አገር በቀል የሆነና በልምድ የካበተ እንዲሁም በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያገኘ ዕውቀት ሆኖ የዕጽዋትን ወይም የእንስሳትን ተዋጽኦ፣ የማዕድናት ወይም የእጅ ጥበብ በመጠቀም የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ነው፤

፴፪.“የባህላዊ ሕክምና አዋቂ” ማለት ባህላዊ ሕክምና ለመስጠት በባለሥልጣኑ የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፴፫.“አስመስሎ ማቅረብ” ማለት የምግብ ወይም የመድኃኒት ማሸጊያ፣ መለያ፣ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም ወይም ማንኛውንም ዓይነት ልዩ ምልክት በመጠቀም ምግቡ ወይም መድኃኒቱ በእውነተኛው አምራች እንደ ተመረተ በማስመሰል ወይም የምግብነት ወይም የመድኃኒትነት ይዘትና ባህርይ ለውጦ በማቅረብና በሰው ጤና ላይ ጉዳት ማስከተል ነው፤

፴፬.“አደገኛ ኬሚካል” ማለት በጥንቃቄ ካልተያዘ ወይም አገልግሎት ላይ ካልዋለ በሰው ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የፌደራል ባለሥልጣንአደገኛ በሚል በዝርዝር የሚለየው ኬሚካል ነው፤

፴፭.“ሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ” ማለት በሥራ አካባቢ የሚከሰቱ ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነትያላቸው ኬሚካላዊ፣ ፊዚካላዊና ሥነ ሕይወታዊ ጎጂ ንጥረ ነገሮች በመከላከልና በመቆጣጠር ሠራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ ሳይንሳዊ፣ ቴክኖሎጂያዊና አስተዳደራዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የሠራተኞችን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሳይንስ ነው፤

፴፮.“መርዛማ ቆሻሻ” ማለት ማንኛውም ታክሞ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ለሰው ልጅ ጤና ጎጂ የሆነ ቆሻሻ ነው፤

፴፯.“ቆሻሻ” ማለት ከኢንዱስትሪዎች፣ ከእርሻ ቦታዎች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከመኖሪያ ቤቶች፣ ከንግድ ስፍራዎች፣ ከጤናና ምርምር ተቋማት፣ ከመጸዳጃ ቤት ወይም ከሌሎች መሰል ተቋሞች የሚወጣና በሰው ወይም በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ፈሳሽ፣ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ሌላ ቆሻሻ ነው፤

፴፰. “የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለት” ማለት ሰው በሚኖርበት አካባቢ የሚገኝ በአካላዊ እድገት፣ በጤና ወይም በአኗኗር ዘይቤ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ሁኔታ ነው፤

፴፱. “እንደገና ጥቅም ላይ የሚውል ቆሻሻ” ማለት በተለያየ ሂደት ውስጥ በማለፍ የሰውን ጤና እንዳይጎዳ ታክሞ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ፈሳሽ ቆሻሻ ወይም ወደ ሌላ ጠቃሚ ነገር ሊለወጥ የሚችል ቆሻሻ ነው፤

፵. “የተጠረጠረ ሰው” ማለት አግባብ ባለው አካል ተገምግሞ ለተላላፊ በሽታ እንደተጋለጠ የሚቆጠርና ያለበትን በሽታ ማስተላለፍ የሚችል ሰው ነው፤

፵፩. “ተላላፊ በሽታ” ማለት በተለያዩ መንገዶች በፍጥነት በመዛመት አደገኛ ወረርሽኝ የሚያስከትል የነበረ ወይም በአዲስ መልክ የሚከሰት በሽታ ነው፤

፵፪. “ኳራንታይን” ማለት ለድንገተኛ ተላላፊ በሽታ ተጋልጠዋል ወይም በበሽታው ተይዘዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎችን እስኪረጋገጥ ድረስ በተለየ ቦታ እንዲቆዩ ማድረግ ነው፤

፵፫. “ለይቶ ማቆየት” ማለት በተላላፊ በሽታ የተያዙ ሰዎች በሽታውን ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፉ ለተወሰነ ጊዜ ለብቻቸው ተለይተው እንዲቆዩ ማድረግ ነው፤

፵፬. “የጤና አገልግሎት”ማለት የጤና ባለሙያው በተፈቀደለት የጤና ሙያ ተግባር አይነትና ወሰን መሰረት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

፵፭. “በበቂ መጠን በገበያ ላይ የማይገኙ የጤና ባለሙያዎች” ማለት ሀገራዊ ፍላጎትን ማሟላት ሳይቻል ሲቀር አግባብ ባላቸው አካላት እጥረት እንዳለባቸው የሚቆጠሩ የጤና ባለሙያዎች ናቸው፤

፵፮. “ሙያዊ ያልሆነ ሥነ ምግባር” ማለት በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎችና ደረጃዎች የተደነገጉ የጤና ባለሙያ ሙያዊ ግዴታን ወይም ሥነ ምግባርን የሚቃረን ተግባር ነው፤

፵፯. “ተገልጋይ” ማለት ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን የጤና አገልግሎት ለማግኘት ሲል በውል ወይም በሌላ መልኩ ከጤና ባለሙያ ጋር ግንኙነት የሚፈጥር ታካሚ ወይም ደንበኛ ነው፤

፵፰. “ተቋም” ማለት የጤና ተቋም ወይም ጤናነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ወይም የምግብ ተቋም ነው፤

፵፱. “የጤና ተቋም” ማለት የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ወይም የመድኃኒት ንግድ ሥራን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ሆኖ ዲያግኖስቲክ ማእከላትንም ይጨምራል፤

፶. “ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም” ማለት ማንኛውም የኅብረተሰብ መገልገያ ተቋም ሲሆን፣ ትምህርት ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማዕከላት፣ የአሳዳጊ አልባ ህፃናት ማዕከላት፣ መዋዕለ ህፃናት፣ የህፃናት ማቆያ የገበያ ቦታዎች፣ የስፖርት ቦታዎች፣ የመታሻ ማዕከላት፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የጸጉር ቤቶችና የውበት ሳሎኖችን ይጨምራል፤

፶፩. “ስረዛ” ማለት የሙያ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን መሰረዝና በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት እንዳይሰራ መከልከል ነው፤

፶፪. “ዕገዳ” ማለት በዚህ ደንብ ድንጋጌ መሠረት ዕገዳን የሚያስከትል ተግባር በሚፈጽም የጤና ባለሙያ ላይ የሚወሰድ ማንኛዉም አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

፶፫. “የፌደራል ባለሥልጣን” ማለት የፌደራል የምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነዉ፤

፶፬. “ባለሥልጣን” ማለትየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነዉ፤

፶፭. “ከተማ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፶፮. “አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፶፯. “ተቆጣጣሪ” ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን በባለሥልጣኑ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ባለሙያ ነው፤

፶፰. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፶፱. በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

በፌዴራል አዋጁ አንቀፅ ፫ (፪) ላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ይህ ደንብ በምግብ፣ በመድኃኒት፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ በጤና ባለሙያዎች እና በጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ላይ በከተማው በሚካሄዱ የቁጥጥር ተግባሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የምግብ ደህንነትና ጥራት አስተዳደርና ቁጥጥር</u>

፬. <u>መርህ</u>

ተገቢውን የደህንነትና ጥራት ደረጃ ያልጠበቀ ምግብ ማምረት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ወይም ለህብረተሰቡ ጥቅም ማዋል የተከለከለ ነው፡፡

፭.<u>ምግብን ስለማምረት</u>

፩. ማንኛውም የምግብ አምራች በባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውንም የምግብ ዓይነት ማምረት፣ ለሽያጭ ማቅረብ ወይም የዓይነትና የማምረት ሂደት ለውጥ ማድረግ የተከለከለ ነው፤

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት ፈቃድ የሚሰጠው የመልካም የአመራረት አሰራር፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት ላብራቶሪ ምርመራ እና ሌሎችም አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

፮.<u>ምግብን ስለመከለስ</u>

፩.በማንኛውም ምግብ ላይ ከነበረው የሚዛን ክብደት ወይም መጠን ለመጨመር፣ መልክ ለማሳመር፣ ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ሲባል ባዕድ ነገር መቀላቀል የተከለከለ ነው፤

፪.ማንኛውንም ምግብ ከማንኛውም መርዛማ፣ በንጽህና ካልተያዘ፣ አደገኛ ንጥረ ነገር ወይም ሌላ ማናቸውም ጠቃሚነት ከሌለው ንጥረ ምግብ መደባለቅ፣ የምግብ ንጥረ ነገሮች መጠን አለመጠበቅ የተከለከለ ነው፡፡

፯. <u>ምግብን ስለማከማቸት፣ ለዕይታ ማቅረብና ማጓጓዝ</u>

፩. ማንኛውም ምግብ ወይም ለብክለት ተጋላጭ ሊሆን የሚችል ምግብ በሚከማችበት፣ ለዕይታ በሚቀርብበት፣ በሚታሸግበት ወይም በሚጓጓዝበት ጊዜ ሁሉ በተገቢው የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን ውስጥ የተጠበቀ መሆን አለበት፤

፪. ምግብን ማጓጓዝ፣ መያዝ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ የሚቻለው ከምግቡ ጋር ንክኪ የሚኖረው የማጓጓዣው ክፍል ወይም እቃ ንፁህ እና ከኬሚካላዊ፣ አካላዊ ወይም ማይክሮ ባይዮሎጂካል ብክለት ምግቡን የማያጋልጥ መሆን አለበት፤

፫. ማንኛውንም ምግብ ከተበከለ ምግብ፣ ከምግብ ትርፍራፊ፣ ከመርዛማ ነገሮች፣ ጎጂ ከሆኑ ነገሮች፣ ከእንስሳት ወይም ከሌሎች በካይ ነገሮች ጋር ማከማቸት እና መጫን ወይም ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

፰.<u>ንጥረ ምግብ</u>

፩. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የወጣውን ደረጃ ካላሟላ በስተቀር በንጥረ ምግብ ምርት ስራ ላይ መሰማራት አይችልም፤

፪. ማንኛውም ሰው በፌደራል ባለስልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር የሚያመርታቸው የምግብ ምርቶች በንጥረ ምግብ የዳበሩ እንደሆኑ አድርጎ መግለጽ አይችልም፤

፫. ማንኛውንም በንጥረ ምግብ የዳበሩ የምግብ ምርት ማሸጊያ ላይ የንጥረ ምግቡ ዓይነትና ይዘት፣ የአጠቃቀም መመሪያና የአገልግሎት ጊዜ ማብቂያ በቀላሉ በማይለቅና በግልጽ መገለጽ ይኖርበታል፤

፬. ማንኛውም ሰው በሚያመርተው ወይም በሚያከፋፍለው ምግብ ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ የአዮዲን ጨው ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፱.<u>ስለተጨማሪ ምግቦች</u>

፩.ማንኛውም ሰው ተጨማሪ ምግቦችን ለሽያጭ ማቅረብ የሚችለው ተጨማሪ ምግቡ በፌደራል ባለሥልጣኑ ተመዝግቦ ሲፈቀድ መሆን አለበት፤

፪.ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የታሸገ እና “ተጨማሪ ምግብ” የሚል ገላጭ ጽሁፍ ሳይኖረው ማንኛውንም ተጨማሪ ምግብ መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፫.ማንኛውም የተጨማሪ ምግብ ገላጭ ጽሁፍ፣ አቀራረብ ወይም ማስታወቂያ የተመጣጠነና የተለያየ አመጋገብ፣ ተገቢውን የንጥረ ምግብ መጠን እንደማያስገኝ ወይም ተጨማሪ ምግቡ የሰውን በሽታ እንደሚከላከል ወይም እንደሚያድን የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡

፫. ማንኛውንም ምግብ ከተበከለ ምግብ፣ ከምግብ ትርፍራፊ፣ ከመርዛማ ነገሮች፣ ጉጂ ከሆኑ ነገሮች፣ ከእንስሳት ወይም ከሌሎች በካይ ነገሮች ጋር ማከማቸት እና መጫን ወይም ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

፰.<u>ንጥረ ምግብ</u>

፩. ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል የወጣውን ደረጃ ካላሟላ በስተቀር በንጥረ ምግብ ምርት ስራ ላይ መሰማራ ትአይችልም፤

፪. ማንኛውም ሰው በፌደራል ባለስልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር የሚያመርታቸው የምግብ ምርቶች በንጥረ ምግብ የዳበሩ እንደሆኑ አድርጎ መግለጽ አይችልም፤

፫. ማንኛውንም በንጥረ ምግብ የዳበሩ የምግብ ምርት ማሸጊያ ላይ የንጥረ ምግቡ ዓይነትና ይዘት፣ የአጠቃቀም መመሪያና የአገልግሎት ጊዜ ማብቅያ በቀላሉ በማይለቅና በግለጽ መገለጽ ይኖርበታል፤

፬. ማንኛውም ሰው በሚያመርተው ወይም በሚያከፋፍለው ምግብ ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ የአዮዲን ጨው ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፱.<u>ስለተጨማሪ ምግቦች</u>

፩.ማንኛውም ሰው ተጨማሪ ምግቦችን ለሽያጭ ማቅረብ የሚችለው ተጨማሪ ምግቡ በፌደራል ባለሥልጣኑ ተመዝግቦ ሲፈቀድ መሆን አለበት፤

፪.ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የታሸገ እና "ተጨማሪ ምግብ" የሚል ገላጭ ጽሁፍ ሳይኖረው ማንኛውንም ተጨማሪ ምግብ መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፫.ማንኛውም የተጨማሪ ምግብ ገላጭ ጽሁፍ፣ አቀራረብ ወይም ማስታወቂያ የተመጣጠነና የተለያየ አመጋገብ፣ ተገቢውን የንጥረ ምግብ መጠን እንደማያስገኝ ወይም ተጨማሪ ምግቡ የሰውን በሽታ እንደሚከላከል ወይም እንደሚያድን የሚገልጽ መሆን የለበትም፡፡

፲.<u>የጨቅላና ህጻናት ምግቦችና ማሚያ ምግቦች</u>

፩. ማንኛውንም ሰው በከተማው ተመርተው እና በከተማው ውስጥ ብቻ ለሽያጭ የሚቀርቡ የጨቅላና ህጻናት ምግቦችን ወይም ማሚያ ምግቦች ለማምረት፣ ለማከፋፈል ወይም ለሽያጭ ለማቅረብ ከባለሥልጣኑልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-

ሀ. "የጨቅላ ሕጻን ምግብ" ማለት ከአትክልት ወይም እንስሳ የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ በኮዴክስ አሊመንተሪየስ የጨቅላ ሕጻን ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ

የተዘጋጀና ከውልደት እስከ መጀመሪያዎቹ ስድስት ወር እድሜ ውስጥ ላለ የጨቅላ ሕጻን የንጥረ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት የተዘጋጀ ምግብ ነው፤

ለ. “የሕጻን ምግብ” ማለት ከአትክልት ወይም ከእንስሳ የሚገኝ ወተትና የወተት ተዋጽኦ ወይም ሌላ ግብአት ሆኖ በኮዴክስ አሊመንተሪየስ የሕጻን ምግብ ደረጃ በፋብሪካ ወይም በሀገር ውስጥ ተመርተው በሀገር አቀፍ ደረጃ በወጣው መስፈርት መሰረት የተዘጋጁ ከስድስት ወር እድሜ በላይ የሆነን ሕጻን ለመመገብ ተስማሚ እንደሆነ የተገለፀ ወይም በሌላ መልኩ ገበያ ላይ የዋለ ምግብ ነው፤

ሐ. “ማሚያ ምግብ” ማለት የእናት ጡት ወተት፣ የጨቅላ ሕጻን ወይም የሕጻን ምግብ ለሕጻኑ የምግብ ፍላጎት በቂ ሳይሆን ሲቀር ለምግቦቹ ማሚያነት ተስማሚ ሆኖ የሚመረት ወይም የሚዘጋጅ ምግብ ነው፡፡

፫.ባለስልጣኑ የጨቅላና ህጻናት ምግቦችና ማሚያምግቦች ገበያ ላይ ከመዋላቸው በፊት በፌደራሉ ባለስልጣን መመዝገባቸውን ማረጋገጥና ግብይትን የሚመለከት ዝርዝር መስፈርቶችን ያስፈጽማል፡፡

፲፩.<u>ምግብን ስለማበልጸግ</u>

፩.ምግብ ማበልጸግ ማለት በማህበረሰቡ ወይም በማህበረሰቡ የተወሰነ ክፍል የሚታይን የአንድ ወይም የብዙ ንጥረ ምግቦች እጥረትን ለመከላከል ወይም ለመተካት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ንጥረ ነገሮችን በምግብ ውስጥ መጨመር ነው፤

፪.የፌደራል ባለሥልጣን ለህዝብ ጤናና ደህንነት ሲባል ምግብ እንዲበለጽግ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት መከናወኑን ባለስልጣኑ ይቆጣጠራል፤

፫.ማንኛውም የምግብ ተቋም እንዲበለጽግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት በባለሥልጣኑ የተለየ ምግብን ማምረት፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ የሚችለው በመስፈርቱ መሰረት የበለጸገ ሲሆን ብቻ ነው፤

፬.የምግብ ጭማሪ ገላጭ ጽሁፍ “የበለጸገ"” የሚል ሀረግ ሊኖርበት ይገባል፡፡

፲፪.<u>ስለ ምግብ ማሸጊያዎችና ገላጭ ጽሑፍ</u>

ማንኛውም የታሸገ ምግብ አምራች ወይም ቸርቻሪ ምግቡ በአግባቡ ካልታሸገና ገላጭ ጽሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ካልተደረገበት በስተቀር ለገበያ ሊያቀርበው ወይም በማናቸውም አኳኋን ሊያሰራጨው አይችልም፡፡

፲፫.<u>ምግብን ማጭረር</u>

፩.ምግብ የሚያጨር ተቋም ተገቢውን የደህንነትና የሀይጂን መስፈርቶችን በሚያሟላ መልኩ ዲዛይን መደረግ ይኖርበታል፤

፪.በማንኛውም ምግብ የሚኖር የራዲዮ ኒውኩላይ ቅሪት ተቀባይነት ካለው መጠን መብለጥ የለበትም፡፡

፲፬.ስለ ውሃ አቅርቦት

፩.አግባብ ባለው አካል ጥራቱ ካልተረጋገጠ በስተቀር የምንጭ፣ የጉድጓድ ወይንም የቧንቧ ውኃ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መስጠት የተከለከለ ነው፤

፪.ማንኛውም ሰው ከአስፈጻሚ አካሉ ፈቃድ ሳያገኝ የማዕድን ውኃም ሆነ የታሸገ ውኃ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ወይም በአገር ውስጥ በማምረት ለሕብረተሰቡ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

፲፭.ስለአልኮል መጠጥ ሽያጭ

፩. ማንኛውም ሰው አግባብ ያለው አካል ያወጣውን ደረጃ እና ንፅህናው ባልተጠበቀ ሁኔታ የአልኮል መጠጥ ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፪.ማንኛውም የታሸጉ አልኮል መጠጦችን የሚያመርት ድርጅት አግባብ ባለው አካል የወጣውን የንፅህና ሁኔታና ደረጃ በማያሟላ መልኩ ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፫.ማንኛውንም የአልኮል መጠጥ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ሰው መሸጥ ክልክል ነው፡፡

፲፮.ስለድኅረ ገበያ ቅኝት

፩.ባለስልጣኑ የምግቦችን ደህንነት፣ ጥራት ገበያ ላይ ከዋሉ በኋላ ለማረጋገጥ የድህረ ገበያ ቅኝት በማካሄድ ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ ያካሂዳል አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፤ ዝርዝሩም በመመሪያ ይወሰናል፤

፪.ማንኛውም የምግብ ተቋም፡-

ሀ.በምግብ ደህንነትና ጥራት ላይ ያልተጠበቀ ችግር ሲኖር ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ፤

ለ. ለሰው ምግብነት የማይስማማ ማንኛውንም ምግብ ከማሰራጨት የመቆጠብ፤ እና

ሐ. ለሽያጭ የቀረበው ማንኛውም ምግብ ለሰው ምግብነት የማይስማማ ከሆነ አግባብ ባለው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የመሰብሰብ፣ የማስወገድና ግዴታ አለበት፡፡

፲፯.ምግብን ስለመያዝና ማስወገድ

፩.ባለስልጣኑ ምግብን ላይዝ ወይም እንዲወገድ  ሊያደርግ የሚችለው፡-

ሀ. ገበያ ላይ እንዲውል ያልተፈቀደ፣

ለ. አስመስሎ የቀረበ፣

ሐ. የአገልግሎት ጊዜው ካለፈ ወይም የጥራት ደረጃውን የማያሟላ፣

መ. የመልካም አመራረት አሰራርን ሳይጠብቅ የተመረተ፣

ሠ. የምግብ ንግድ ሥራን ለማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሌለው ሰው የተመረተ፣ የተከማቸ፣ የተከፋፈለ፣ ለዕደላ የተዘጋጀ ወይም የታደለ ከሆነ ነው፡፡

፪.ባለስልጣኑ ምግቡ ጥቅም ላይ የሚውል እስከሆነ ድረስ ተገቢውን አወጋገድ ስርዓት ተከትሎ ስለመወገዱ ማረጋገጥ አለበት፤

፫.ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ለተወገደው ምግብ ማስረጃ ሲጠየቅ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለምግቡ ባለቤት ወይም ባለይዞታ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር

፲፰.ስለ መድሀኒት አያያዝ

፩. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ አግባብ ባለው ህግ መሰረት መድሀኒቶችን እንደ ባህሪያቸው በተገቢው ቦታ፣ የሙቀት መጠን፣ ጊዜ፣ የጸሀይ ጨረር እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ጥንቃቄዎችን በማሟላት መቀመጡን ማረጋገጥ አለበት፤

፪. ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን እና በልዩ ልዩ ምክንያት አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መድሀኒቶችን፣ አገልግሎት ከሚሰጡ መድኒቶች ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፤

፫.ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ ተቀጣጣይነት ያላቸውን ወይም ሌሎች መድኃኒቶችን ሊበክሉ የሚችሉ ኬሚካሎችን፣ ቅመሞችን፣ ከሌሎች መድኃኒቶች ለይቶ ማስቀመጥ አለበት፤

፬.ማንኛውም የመድኃኒት ባለሙያ የሚይዛቸውን መድኃኒቶች በጠቀሜታ ጊዜያቸው ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ ቀድሞ ጊዜ የሚያልፍባቸውን ቀድሞ ማውጣት ወይም ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፤

፭.ማንኛውም የመድኒት ባለሙያ ከአቅም በላይ የተከሰተ ችግር ሲያጋጥመውና ለመድኃኒቶች አያያዝ አስጊ ሁኔታ ሲፈጠር ለባለስልጣኑ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፤

፮.ማንኛውም ጤና ተቋም የመድኃኒትን ግብይት፣ ክምችት፣ ስርጭት እና ሽያጭ ግልጽ መረጃ መስጠት ደረሰኝ የማቅረብ እና ኦዲት ሊደረግ በሚችል ስርዓት የማደራጀት ግዴታ አለበት፡፡

፲፱.ስለ መድሀኒት አገልግሎት አሰጣጥ

፩. ማንኛውም የጤና ተቋም አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም መቆጣጠርያ ዘዴን በመጠቀም የመድኃኒት አገልግሎቱን በየጊዜው መከታተል አለበት፤

፪. ማንኛውም የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋሙ የመጣ ተጠቃሚ ከመድሃኒት ጋር በተያያዘ ጉዳት እንዳይደርስበት፣ ተገቢውን ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤ ከመድሃኒቱ ጋር በተያያዘ የሚደርሱ ጉዳቶችንም ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፤

፫.ማንኛዉም የጤና ተቋም የመድኃኒቶችን ስም፣ አወሳሰዳቸውንና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በግልጽ ተጽፎ፣ አግባብነት ባለው ማሸጊያ ታሽጎ ከተሟላ መረጃና የምክር አገልግሎት ጋር መሰጠቱን መከታተል አለበት፤

፬.ማንኛውም የጤና ተቋም በክምችት የሚገኙ መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት ጥቅም ላይ ውለው የሚያልቁ መሆናቸውን መከታተል አለበት፤

፭.ማንኛውም የጤና ተቋም የመድሀኒት አገልግሎቱን ለማካሄድ የሚያበቁትን የሰው ሀይል፣ መሳሪያዎች እና መድኃኒት ማከማቻ፣ ቅመም ፣ ለእደላ ሂደት እና ለመድኃኒት አጠቃቀም የምክር አገልግሎት መስጫ የሚውሉ ክፍሎች ለተጠቃሚው አመቺ በሆነ መልክ ማደራጀት አለበት፤

፮.መድኃኒት ለታካሚዎች የሚታደለው በመድሃኒት ባለሙያ መሆን አለበት፡፡

፳.<u>ስለመድኃኒት ማሸጊያዎችና ገላጭ ጽሑፍ</u>

፩.ማንኛውም የመድኃኒት ቸርቻሪ ወይም የጤና ተቋም መድኃኒቱ በአግባቡ ካልታሸገና ገላጭ ጽሑፍ ካልደተረገበት በስተቀር ለገቢያ ሊያቀርበው ወይም በማናቸውም አኳኋን ማሰራጨት የተከለከለ ነው፤

፪.የማንኛውም መድኃኒት ገላጭ ጽሑፍ በአማርኛወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ ሊሆን ይገባል፡፡

፳፩.<u>ስለህክምና ሙከራ</u>

ከፌደራል ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ በከተማ ውስጥ በሚገኙ የጤና ተቀማት ውስጥ ወይም በማንኛውም ቦታ የህክምና ሙከራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፳፪.<u>ስለ ህገ-ወጥ የመድኃኒት ዝውውር</u>

፩.በፌዴራሉ ባለስልጣን ባልተመዘገቡና ፍቃድ ባልተሰጣቸው የመድኃኒት አስመጪዎችና አምራቾች የቀረቡ መድኃኒቶችን መግዛት፣ ማከማቸት፣ ማሰራጨት፣ መሸጥ ወይንም ማደል የተከለከለ ነው፤

፪.ከባለስልጣኑ ፍቃድ ያልተሰጠው ሰው መድኃኒትን መያዝ፣ መሸጥ ወይንም ማደል የተከለከለ ነው፤

፫.ማንኛውም መድኃኒት እንዲያድል ወይም እንዲሸጥ የተፈቀደለት ሰው መድኃኒት ማደል ወይም መሸጥ የሚችለው በህጋዊ ደረሰኝ ብቻ ነው፡፡ ደረሰኙ በፋይናንስ ቢሮ የሚታወቅ ሆኖ ቢያንስ የመድኃኒቱን ስም፣ ጥንካሬ፣ መለኪያና መጠን፣ ይዘት፣ የውስጥ መለያ ኮድ፣ መድኃኒቱ ዋጋ፣ የህሙማኑ ስም፣ ጾታ፣ እድሜ፣ የታደለበት ቀን፣ የተቋሙ ስም፣ የአዳዩ ባለሙያ ስምና ፊርማ ሊኖረው ይገባል፤

፬.ማንኛውም ሰው ህገወጥ የመድሃኒት ዝውውርን ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፳፫.<u>ስለ መርዞችና ጨረር አፍላቂ መድሀኒቶች</u>

ማንኛውም ሰው ከፌደራል ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ መርዞችን ወይም ጨረር አፍላቂ መዳኒቶችን መያዝ ማከማቸት ወይም ማከፋፈል የተከለከለ ነው፡፡

፳፬.<u>ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት</u>

ማንኛውም በአገር ውስጥ የሚመረት ባህላዊ፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒት በፌደራል ባለሥልጣኑ ተገምግሞ ሳይመዘገብ አገልግሎት ላይ ሊውል የተከለከለ ነው፡

፳፰.ስለ ድኅረ ገበያ ቅኝት

፩.ባለስልጣኑባካሄደው የድህረ ገበያ ቅኝት ወይም ፌደራል ባለሥልጣኑ በመድኃኒት ላይ በሚያወጣው የድህረ ገበያ ቅኝት ሪፖርት መሰረት በማድረግ ባለስልጣኑ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣

፪.ማንኛውም የጤና ተቋም፡-

ሀ.በመድሀኒት ጥራት' ፈዋሽነትና ደህንነት ረገድ የሚያጋጥመውን ማንኛውም የቀድሞው የማይታወቅ ችግር ¨ÃU ከተገልጋይ የሚቀርብ ቅሬታ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፣

ለ.የፌደራል ባለሥልጣኑ መድኃኒቱ የደህንነት፣ የፈዋሽነት ወይም የጥራት ችግር አለሙ ብሎ ሲያሳውቅ ወይም ከሚመለከተው አካል ሲገለጽለት የመድሀኒቱን ስርጭት የማቆም፣

ሐ.ባለስልጣኑ መድኃኒቱ የደህንነት፣የፈዋሽነት ወይም የጥራት ‹Ó` አለው ብሎ ሲያሳውቅ መድሀኒቱን በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ የመተባበር፣

መ.የፌደራል ባለሥልጣን በተለያየ ደረጃ ለሚገኑ ጤና ተቋማት ያወጣውን የመድሃኒት አገልግሎት ስታንዳርድ ተከትሎ የመስራትግዴታ አለበት።

፫.ማንኛውም ከመድሃኒት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የጤና ባለሙያ የደህንነት' ፈዋሽነትና ጥራትን አስመልክቶ የሚያጋጥመውን ችግር ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፳፺.ስለናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሣይኮትሮፒክን ጥረ ነገሮችና ፐሪከርሰር ኬሚካሎች ልዩ ፈቃድ ስለማስፈለጉ

፩.ማንኛውም ሰው ናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ለመያዝ ከፌደራል ባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ማውጣት አለበት፣

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ልዩ ፈቃድ የሚሰጠው መድኃኒት መያዝንና የጤና አገልግሎት መስጠትን በሚመለከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላለው ሰው ብቻ ይሆናል፡፡

፴.መድኃኒትን ስለመያዝና ማስወገድ

፩.ባለስልጣኑ መድኃኒትን ላይዝና እንዲወገድ ሊያደርግ የሚችለው፡-

ሀ. ገበያ ላይ እንዲውል ያልተፈቀደ ወይም ልዩ የመድኃኒት ማስገቢያ ፍቃድ ያለው፣

ለ. አስመስሎ የቀረበ፣

ሐ. ጊዜው ካለፈ ወይምየጥራት ደረጃውንየማያሟላ፣

መ.የመድኃኒት ንግድ ሥራን ለማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሌለው ሰው የተከማቸ፣ የተከፋፈለ፣ ለዕደላ የቀረበ ወይም የታደለ፣

ሰ.መድኃኒቱ ላልተፈቀደ የህክምና ሙከራ የዋለ ከሆነ ፡፡

፪.የባለስልጣኑ መድኃኒቱ ጥቅም ላይ የማይውል እስከሆነ ድረስ መወገዱን ማረጋገጥ አለበት፤

፫.ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ለተወገደው መድኃኒት ማስረጃ ሲጠየቅ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመድኃኒቱ ባለቤት ወይም ባለይዞታ ይሰጣል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የትምባሆ ዝግጅት ቁጥጥር</u>

፳፫.<u>ስለ ትምባሆ ቁጥጥር</u>

፩.ማንኛውንም የትንባሆ ዝግጅት መሸጥ ወይም መቸርቸር የሚቻለው የትንባሆ ዝግጅቱ ከፌዴራል ባለስልጣኑ ፈቃድ ካገኘ አከፋፋይ ድርጅት የተገዛ መሆን አለበት፤

፪.ማንኛውም የትንባሆ ዝግጅት መሸጥ ወይም መቸርቸር የሚቻለው የትምባሆ ዝግጅት እንዲሸጥ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ያገኘ የንግድ ድርጅት ውስጥ መሆን አለበት፤

፫.ማንኛውም የንግድ ድርጅት የትንባሆ ዝግጅት መሸጥ ወይም መቸርቸር የሚቻለው በህጋዊ መንገድ በአገር ውስጥ የተመረተ ወይም ወደ አገር ውስጥ የገባ መሆን አለበት፡፡

፳፬.<u>ስለ ትንባሆ ዝግጅት ማሸጊያና ገላጭ ፅሁፍ</u>

፩.ማንኛውም የትንባሆ ዝግጅት ችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማራ ሰው አንድ የትንባሆ ዝግጅት ባህሪውን፣ የጤና ችግር ማስከተሉን፣ አደገኝነቱን የሚገልጽ ፅሁፍ ከሌለው በስተቀር ለችርቻሮ ንግድ ማቅረብ የለበትም እንዲሁም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የአንዱ የትንባሆ ዝግጅት ጉዳት ከሌላ የትንባሆ ዝግጅት ጉዳት ያነሰ መሆኑን የሚያስመስል መሆን የለበትም፤

፪.ማንኛውም የትንሆ ዝግጅት ችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማራ ሰው የትንባሆ ዝግጅት ነጠላ ፓኬት፣ ጥቅል ማሸጊያና የውጭ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ፡-

ሀ.ስለ ትንባሆ የጤና አስከፊነት የጤና ማስጠንቀቂያ የያዘና ይህም የማሸጊያውን ገጽ ከ፴ በመቶ በማያንስ የሚሸፍን፤

ለ. የጤና ማስጠንቀቂያው በቃላት ወይም በስዕል ማጨስ ካንሰር ወይም የልብ ህመም ወይም ብሮንካይትስ ያመጣል እና ያለ እድሜ ይገድላልየሚል፤

ሐ.በትልቁና፣ ግልጽ ሆኖ የሚታይና የሚነበብ  ሆኖ በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ የተጻፈ፤ እና

መ. ትንባሆ የያዘውን ንጥረ ነገርና በጪሱ ውስጥ የሚገኘውን ንጥረ ነገር የሚገልጽ፤ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፴.<u>የትንባሆ ዝግጅትን ማስተዋወቅ፣ መረጃና ድጋፍ አሰጣጥ</u>

ማንኛውም ሰው የትንባሆ ዝግጅትን ግዢ ለማበረታታት ወይም ለማስፋፋት በሬድዮ በቴሌቪዥንና፣ በጋዜጣ በሌሎች ማናቸውም ስልቶች ማስተዋወቅ፣ መረጃ መስጠት ወይም ስፖንሰር ማድረግ ወይም ማንኛውንም ድጋፍ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

፴፩.ማጨስ የሚከለከልባቸው ቦታዎች

፩.ትምባሆን በማንኛውም ሕዝብ በሚሰበሰብበት ወይም በሚገለገልበት ቦታ ማጨስ ክልክል ነው፤

፪.ሕዝብ የሚሰበሰብበት ወይም የሚገለገልበት ቦታ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) ማንኛውም የሥራ ቦታን፣

ለ) ሲኒማ፣ ቴያትር፣ ቪዲዮ ቤቶችና ሌሎች ተመሳሳይ ቦታዎችን፣

ሐ) ጤና ተቋማትን፣

መ) ካፍቴሪያዎች፣ ሻይ ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች፣ ሆቴሎች፣ ቡና ቤት፣ የምሽት ክበብ እና ሌሎች መዝናኛ ቦታዎች፣

ሠ) ሕጻናትና ነፍሰ ጡሮች የሚገኙበት ቦታን፣

ረ) የህዝብ ማጓጓዣን፣

ሰ) የትምህርት ተቋማትን፣

ሸ) ስታዲየም፣ የስፖርት መዝናኛ ስፍራዎችን፣ እና

ቀ) ሌሎች የፌደራል ባለሥልጣን እንዳይጨስባቸው የሚወስናቸው ቦታዎችን፡፡

፫.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም በፌደራል ባለሥልጣኑ የሚለዩ ሕዝብ የሚሰበሰብባቸው ወይም የሚገለገልባቸው ተቋማት ውስጥ ትምባሆን ማጨስ የሚቻለው ለዚሁ ዓላማ በተለየ የማጨሻ ቦታ ብቻ ይሆናል፡፡

፬.ማንኛውም ማጨስ የማይፈቀድባቸው ቦታዎች ባለቤት ወይም ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ወይም የድርጅቱ ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ እንዳይጨስ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር

፴፪.ስለሙያ ስራ ፈቃድ አስፈላጊነት

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከባለስልጣኑ የሙያ ስራ ፈቃድ ሳያገኝ የጤና አገልግሎት በከተማው ውስጥ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡ ሆኖም በፌደራል ባለስልጣን የሙያ ስራ ፈቃድ የሚሰጣቸውን የጤና ባለሙያዎችን አይጨምርም፡፡

፴፫.የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፍቃድ የሚሰጠው ፌዴራል ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው መስፈርቶችን ሲያሟላ ይሆናል፤

፪.ባለስልጣኑ አንድ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራውን እንዳያከናውን ብቃቱን ወይም ሚዛናዊነቱን የሚያዛባ የአዕምሮ ወይም አካላዊ ሁኔታ ሲገጠመው እንደ አግባብነቱ ውስን የሙያ ሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

፫.ከአንድ በላይ የጤና ሙያ ያለው ሰው አስፈላጊውን መስፈርት እስካሟላ ድረስ ባሉት ሙያዎች መስራት የሚያስችለው የሙያ ሥራ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፤

፬.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያየ ሙያ በተመሳሳይ ሰአት አገልግሎት መሥጠት የተከለከለ ነው፤

፭.ማንኛውም የጤና ባለሙያ በማንኛውም መልኩ የሙያ ስራ ፈቃዱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ወይም ማከራየት የተከለከለ ነው፡፡

<u>፴፬.ስለ ሙያ ስራ ወሰን</u>

፩.ማንኛውም የሙያ ሥራ ፍቃድ የተሰጠውን ባለሙያ ከሙያው የስራ ወሰን ውጭ የሆነ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፤

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ባለሙያው ከሙያው የስራ ወሰን ውጭ የሆነ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፤

፫.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የጤና ባለሙያ በአደጋ ጊዜ መሰረታዊ የሆነ የህክምና ዕርዳታ መስጠት ይችላል፡፡

<u>፴፭.የሙያ ስራ ፈቃድ ስለማሳደስ</u>

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠው የሙያ ሥራ ፈቃድ በየአምስት ዓመቱ የሙያ ሥነ-ምግባርና ሙያዊ ብቃቱ ተገምግሞ ማሳደስ አለበት፤

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሙያ ፈቃዱ የሚታደሰው፡-

ሀ.በሙያ ዘርፉ አስፈላጊውን ተከታታይ የጤና የትምህርት መውሰዱን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ሲቀርብ፤

ለ.ሙያውን ለማከናወን የሚያስችል የጤና ሁኔታ እንዳለው የሚያረጋግጥ የህክምና ምስክር ወረቀት ሲቀርብ፤

ሐ.ባለሙያው በስራ ላይ እንደነበረ የሚገልጽ የስራ ልምድ ማስረጃ ሲሰራበት ከነበረው ተቋም ሲቀርብ ነው፡፡

፫.ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ተከታታይ የጤና ትምህርት" ማለት የፌደራሉ ባለሥልጣን በሚወስነውና በሚዘረጋው አሰራር መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሙያ በስራ ላይ እያለ በሙያው ያገኘውን እውቀትና ክህሎት ጠብቆ እንዲቆይ እና የሙያ ብቃቱን ለማጎልበት በየጊዜው የሚወስደው ሥልጠና ነው፡፡

<u>፴፮.የተሰጠ የሙያ ስራ ፍቃድ የማይሰራበት ጊዜ</u>

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሁለት ዓመት በላይ በማንኛውም ምክንያት በሙያው ሳይሰራ ከቆየ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፤

፪.ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከሙያው ተለይቶ ለቆየ ባለሙያ እንደ አግባብነቱ ተከታታይ የጤና ትምህርት መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ስልጠና እንዲወስድ በማድረግ በሙያው እንዲሰራ ሊፈቅድለት ይችላል፤

፫.ባለሙያው ከሁለት ዓመት በላይ በሙያው ሳይሰራ ቆይቶ ለባለሥልጣኑ ሳያሳውቅ ድጋሚ በሙያው ሲሰራ ቢገኝ ያለሙያ ስራ ፍቃድ እንደሰራ ይቆጠራል።

<u>፴፮.ስለጤና ባለሙያዎች መዝገብ</u>

፩.ባለሥልጣኑ በከተማው ውስጥ ስራ ላይ የሚገኝ ማንኛውንም የጤና ባለሙያ ስም፣ ዜግነት፣ መደበኛ የመኖሪያ፣ የሥራ አድራሻ እና ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎችን የሚይዝ መዝገብ ይኖረዋል፤

፪.ባለሥልጣኑ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም እና ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም በጤና ሙያ ዘርፍ በየጊዜው የሚመረቁ ምሩቃን ዝርዝር ከሚመለከተው አካል ማግኘት አለበት፤

፫.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሚያዘው መዝገብ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ለህዝብ ክፍት ሊደረግ ይችላል።

<u>፴፯.የሙያ ስራ ፍቃድን ስለመመለስ</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠው የሙያ ስራ ፍቃድ ሲታገድ፣ሲሰረዝ፣ወይም በራሱ ፈቃድ የሙያ ስራውን ሲተው ወይም የተሰጠውን አላማ ሲያሳካ ፈቃዱን ለባለሥልጣኑ የመመለስ ግዴታ አለበት።

<u>፴፱.ስለ ባህላዊ ሕክምና ባለሙያ</u>

፩.ማንኛውም ሰው ከፌደራል ባለስልጣኑ የሙያ ሥራ ፈቃድ ሳያገኝ በባህላዊ ሕክምና ሊሰማራ የተከለከለ ነው፤

፪.የባህላዊ ሕክምና የሙያ ፈቃድ በየአምስትዓመቱ የባለፈቃዱ የሙያ ሥነ ምግባርና ብቃት እየተገመገመ መታደስ አለበት፤

፫.ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበትየባህላዊሕክምና ባለሙያ አገልግሎት ሊሰጥየተከለከለ ነው።

<u>፵.የጤና ባለሙያዎች የስነ ምግባር ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

የባለሥልጣኑ የጤና ባለሙያዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን የሚያግዝ የጤና ባለሙያዎች የሥነ ምግባር ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

<u>፵፩.የጤና ባለሙያዎች የስነ ምግባር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

የጤና ባለሙያዎች የሥነ-ምግባር ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩.የጤና ባለሙያን የሥነ-ምግባር ግድፈትን የሚመለከት አቤቱታ ተቀብሎ ያጣራል፤

፪.በጤና ባለሙያው ላይ የቀረበውን አቤቱታ ለማየት የሚያበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ መልሱን እንዲያቀርብ በመጥሪያው ላይ በመግለጽ አቤቱታውን ለጤና ባለሙያው ይልካል፤

፫.በጤና ባለሙያው ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በጤና ባለሙያው በኩል የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፤

፬.የተለያዩ የጤና ባለሙያ ቦርድ እንዲቋቋም የውሳኔ አስተያየት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቅርቦ የጤና ባለሙያ ቦርዱ እንዲቋቋም ያደርጋል፤ የሚቋቋመው የጤና ባለሙያ ቦርድ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ የጤና ሙያዎችን ያካተተ ሊሆን ይችላል፤

፭.የስነ-ምግባር ኮሚቴው በዚህ ደንብ መሰረት ለሚቋቋም የጤና ባለሙያ ቦርድ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤እና

፮.የጤና ባለሙያዎች የስነምግባር ኮሚቴ ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፯.ይህን አንቀጽ ለማስፈጸም ባለስልጣኑ መመሪያ ያወጣል፡፡

<u>፴፪.የስነምግባር ኮሚቴው የስብሰባ ስነስርዓት</u>

፩.የስነ ምግባር ኮሚቴ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪.ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፫.ኮሚቴው ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ይወክላልጫ ይሆናል፡ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የኮሚቴዉ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤

፬.የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

<u>፴፫.የስነ-ምግባር ኮሚቴ አባላት</u>

የስነ-ምግባር ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩.በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየም……………….ሰብሳቢ፣

፪.የባለስልጣኑ ተወካይ………………………….ፀኃፊ፣

፫.በህግ መሠረት ከተቋቋሙት የጤና ባለሙያ ማህበር ከእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ተወካይ…...አባል፣

፬.ከህብረተሰብ ሁለት ተወካይ………………….አባል፣

፭.ከባለስልጣኑ አንድ የህግ ባለሙያ……………..አባል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የጤና ባለሙያ ሥነ-ምግባር</u>

<u>፴፬.መርሆዎች</u>

፩. ማኝኛውም የጤና ባለሙያ አዋጁን፣ ይህን ደንብ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎችን በሚሰጥ መልኩ ስራውን ማከናወን የተከለከለ ነው፤

፪. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ያለምንም አድልዎ የጤና አገልግሎትን ለተገልጋይ መስጠት አለበት፤

፫.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ለተገልጋይ ጤንነትና ምርጫ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

፵፫.የጤና ባለሙያ ዋና ዋና ኃላፊቶች

ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-

፩.እንደ ስራ ድርሻው በሚሰጠው የጤና አገልግሎትና በሚወስነው ውሳኔ ተጠያቂነት አለበት፤

፪.አግባብ ባለው ህግ መሰረት የጤና አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የተገልጋዩን ሙሉ ፍቃድ ማግኘት አለበት፤

፫.ከሙያ አጋሩ ሆነ ከተገልጋይ ጋር በሚያደርገው ሙያዊ ግንኙነት እውነተኛና በቂ መረጃ መስጠት አለበት፤

፬.የተገልጋዩን ሚስጢር፣ የግል ሕይወት፣ ምርጫና ክብር መጠበቅ አለበት፤

፭.ዘላቂ ስነ ምግባርና ስብዕና ሊኖረው ይገባል፤

፮.በቡድን ስራ ውስጥ የሌላውን ባለሙያ አስዋጽኦ በማክበር የሚጠበቅበትን ሙያዊ ኃላፊነት መወጣት አለበት፤

፯.ተገቢውን የምክር አገልግሎት ለተገልጋዩ መስጠት አለበት፤

፰.በየጊዜው የሚወጡ አዳዲስ ህክምና ቴክኖሎጂዎች እናግኝቶች ሙያዊ እውቀቱንና ክህሎቱን ማሳደግ ይኖርበታል፤

፱.ከታካሚውና ከሌሎች የጤና ባለሙያዎች ጋር አግባቢያዊና ፍሬያማ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፤

፲.የታካሚውን ትክክለኛ የህክምና መረጃ መዝግቦ ማስቀመጥ፤

፲፩.በተመደበበት ቦታና የስራ ሰዓት በስራ ገበታው ላይ በመገኘት ሙያዊ አገልግሎት መስጠት አለበት፤

፲፪.የህብረተሰብ ጤና ፕሮግራሞችን በሚቀርጽበትና በሚተገበርበት ጊዜ የህብረተሰቡን ተሳታፊነትና ፈቃደኝት ማረጋገጥ አለበት፤

፲፫.ሙያውን በሚመለከት ጉዳይ አግባብ ያለው አካል የሚሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም የሚያወጣው የአሰራር ስርአት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፵፬.የድንገተኛ ሕክምናና ሪፈራል

፩. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ደረጃው በሚፈቅደው መሠረት የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለበት፤

፪. የጤና ባለሙያው በሚሰራበት የጤና ተቋም ደረጃ መሠረት ተገቢውን የድንገተኛ ሕክምና አገል ግሎት መስጠት ያልቻለ እንደሆነ ታካሚውን ተፈላጊውን አገልግሎት ሊያገኝ ወደሚችልበት አግባብ ያለው የጤና ተቋም ሪፈራል ስርአቱን በመከተል ወዲያውኑ ሪፈር ማድረግ አለበት፡፡

፵፭.መድኃኒት ስለማዘዝና ማደል

፩. መድኃኒቶችን ማዘዝ የሚችለው አግባብ ባለው አካል የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው የሕክምና ባለሙያ ብቻ ይሆናል፤

፪.ማንኛውም የሕክምና ባለሙያ መድኃኒት የሚያዘው የመድኃኒት አስተዛዘዝ ሥርዓትን በመከተልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ላይ ይሆናል፤

፫.መድኃኒቶች የሚታደሉት በመድኃኒት ባለሙያ ይሆናል፤

፬.በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአስገዳጅ ሁኔታዎች በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና በሌሎች የጤና ባለሙየዎች መድሀኒት ማደል ይቻላል፤

፭.ማንኛውም መድኃኒት ለማደል ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ የመድኃኒት እደላ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ በቂ መረጃና ግንዛቤ በመስጠት በጥንቃቄ ማደል አለበት፤

፮.በመድኃኒት አስተዛዘዝ ስርዓት መሠረት ያለሀኪም ትዕዛዘዝ ከሚሰጡ መድኃኒቶች በስተቀር ማንኛውም በመድኃኒት ማደል ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ያለመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት መድኃኒቶችን ማደል (መሸጥ) የለበትም፤

፯.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ስለይዘቱ እና በሰው አካል ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት የማያውቀውን መድኃኒት ወይም የተቀመመ የመድኃኒት ዝግጅቶችን ማዘዝ ወይም ማደል የለበትም፤

፰.ማንኛውም የጤና ባለሙያ መድኃኒትን የሚያዝ በት የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት በተቋሙ ደረጃና በሙያው አይነት የተዘጋጀ፣ ህጋዊና ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት፤

፱.ማንኛውም የጤና ባለሙያ አስገዳጅ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሚያዝዘው መድኃኒት የብሔራዊ የመድኃኒት መዘርዝር ውስጥ የተመዘገበ መሆን አለበት፤

፲.ማንኛውም መድኃኒት ለማደል ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ማንኛውንም በሕጋዊ መንገድ ያልተገኘ መድኃኒትን ማደል ወይም መያዝ የለበትም፤

፲፩.ማንኛውም መድኃኒት ለማደል ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ስለሚያድለው መድሀኒት ስለአወሳሰዱ፣ መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ እና ሌሎች አግባብነት ያለውን መረጃ ተገልጋዩ በሚገባው አግባብ አብሮ መስጠት አለበት፡፡

<u>፵፰.የአገልግሎት ክፍያና ኮሚሽን</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-

፩.ለሰጠው አገልግሎት ከሚጠይቀው ህጋዊ የአገልግሎት ክፍያ ውጪ የገንዘብ ወይም በገንዘብ የሚተመን ንብረት ወይም ኮሚሽን ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለው ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ከማንኛውም ሰው ወይም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም፤

፪.ተገልጋይ እንዲላክለት ሲል የኮሚሽን፣ የገንዘብ ወይም ሌላ ዋጋ ሊያስገኝ የሚችል ነገር መክፈል ወይም መስጠት የለበትም፤

፫.ሙያው ከሚፈቅደው አገልግሎት በላይ ወይም በታች እንዲያከናውን ወይም እንዳያከናውን ተፅዕኖ ለማሳደር ወይም ታካሚው መክፈል ከሚገባው በላይ ክፍያ እንዲከፈል ለማድረግ ምንም ዓይነት ክፍያ ወይም ሌላ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ንብረት መስጠትም ሆነም መቀበል የለበትም፤

፬.በራሱ ወይም በአጋርነት በቀጠረው ወይም አብሮት በሚሰራው ወይም በምትክነት በመደበው ባለሙያ ለተሰጠ የጤና አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር ክፍያ ማስከፈልም ወይም መቀበል የለበትም፤

፭.ተገልጋይን ለህክምና ወይም ለህክምና ሙከራ ወይም ለምርመራ ወደ ሌላ ጤና ባለሙያ በማስተላለፉ ለዚሁ አገልግሎቱ ክፍያ ማስከፈል ወይም የገንዘብ ወይም ሌላ በዋጋ ሊተመን የሚችል ጥቅም መቀበል ወይም መጠየቅ የለበትም፤

፮.ለጥቅም ሲል የታካሚውን የጤና ችግር የማይፈታ ወይም የማያቃልል የጤና አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡

<u>፵፱.ፍቃድ ካለው ባለሙያ ጋር አብሮ መስራት</u>

ለትምህርትና ስልጠና ካልሆነ በስተቀር አንድ የጤና ባለሙያ ከሌላ አገባብ ባለው አካል የሙያ ፈቃድ ካልተሰጠው ባለሙያ ጋር አብሮ መስራት ወይም ለዚሁ ባለሙያ ማንኛውንም አይነት ሙያዊ ድጋፍ መስጠት የለበትም፡፡

<u>፶.የሙያ ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

፩.አግባብ ባለው አካል ለህብረተሰቡ ጤና ጎጂነቱ የታመነበት ጉዳይ ካልሆነ፣ በፍርድ ቤት ካልተጠየቀ፣ የተገልጋዩን ስምምነት ካላገኘ ወይም በሕግ የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የጤና ባለሙያ ታካሚውን የሚመለከት ማንኛ ውንም መረጃ በቃል ወይም በጽሁፍ መግለጽ ወይም መስጠት የተከለከለ ነው፤

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ታካሚውን የሚመለከት መረጃን ለሳይንሳዊ ምርምር ወይም ጥናት አላማ መግለጽ ወይም ማስተላለፍ የሚችለው የታካሚውን ማንነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማያሳውቅ ሁኔታ መሆን አለበት፤

፫.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ተላላፊ በሽታ ያለበት ታካሚን በሽታው ሊተላለፍባቸው ለሚችሉ ሰዎች ህመሙን እንዲያሳውቅ ማበረታታት አለበት፡፡

<u>፶፩.የአገልግሎት መድልዎና ታካሚዎችን ስለመላክ</u>

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ በመደበኛና በትርፍ ጊዜ ስራ ለተገልጋይ የሚሰጠው ክብካቤ ተመሳሳይ መሆን አለበት፤

፪.አገልግሎቱ በጤና ተቋሙ የማይገኝ እስካልሆነና ያለውን የጥቅምና የስራ ግንኙነት ግልጽ አድርጎ ለታካሚው እስካልገለፀ ድረስ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከአንድ ከሚሰራበት የጤና ተቋም ወደ ሌላ ወደሚሰራበት የጤና ተቋም ታካሚውን መላክ የተከለከለ ነው፡፡

<u>፶፪.ምስጢራዊ ህክምና ስለመከልከሉ</u>

<u>፩.ማንኛውም የህክምና ባለሙያ ምስጢራዊ ህክምና መስጠት የለበትም፤</u>

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የጤና አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሚገለገልበት መሳሪያ፣ ቴክኖሎጂ ወይም ህክምና መፍትሄ ሊሰጥ እንደሚችል በጥናትና በምርምር የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

፫.ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል “ምስጢራዊ ህክምና” ማለት ሆን ተብሎ ከሌሎች ሰዎች የሚደበቅና በጥቂት ሰዎች ብቻ የሚታወቅ በሽታን ለማዳን ወይም የጤና ችግርን ለመቅረፍ ወይም ህመምን ለማስታገስ የሚውል መድሀኒት ወይም ህክምና ነው፡፡

፶፫.ስለ ማስተዋወቅ

፩.ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “ማስታወቂያ” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በፅሁፍ፣ በድምጽ፣ በምስል ወይም በማናቸውም መንገድ የጤና አገልግሎት እንዲታወቅ፣ እንዲታዘዝ ወይም ጠቅም ላይ እንዲውል የሚተላለፍ መልዕክት ነው፤

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ አገልግሎቱን የሚመ ለከት ሙያዊ ያልሆነ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች የሆነ የማስተዋወቅ ተግባር መፈጸም የለበትም፤

፫.ማንኛውም የጤና ባለሙያ አግባብ ባለው የመንግስት አካል የማስተዋወቅ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር የሚሰጠውን አገልግሎት ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፤

፬.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ አገልግሎቱን ሲያስተዋውቅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አላስፈላጊ የሆነ የተገልጋይነት ተነሳሽነትን ሁኔታ በሚፈጥር መሆን የለበትም፤

፭.ማንኛውም የጤና ባለሙያ አገልግሎቱን ሲያስተዋውቅ ሌሎች የጤና ባለሙያዎችን በሚጎዳ ወይም አገልግሎታቸውን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ መሆን የለበትም፤

፮.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሚያደርገው የሙያ ማስተዋወቅ ተግባር በራሱ የተሻለ የሙያ ብቃትና የዕውቀት የበላይነት ላይ ልዩ ትኩረት የሚያሰጥ መሆን የለበትም፤

፯.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ስለሚሰጠው አገልግሎት የሚያደርገው የማስተዋወቅ ተግባር ለተገልጋዩ ስጦታ፣ የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌላ ማበረታቻ የሚያስገኝ መሆኑን በመግለጽ መሆን የለበትም፤

፰.ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስሙ የወጣ የጤና ባለሙያ ጤና ተቋሙ የሚያስተላልፈው ማስታወቂያ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ማክበሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፶፬.መድኃኒትንና የህክምና መሳሪያን ስለማስተዋወቅ

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከአምራቹ ወይም ከአከፋፋዩ ጋር የቅጥር ግንኙነትና የማስተዋወቂያ ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም መድኃኒትና መሳሪያን ሊያስተዋውቅ አይችልም፤

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሊያገኘው የሚችለውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ለታካሚው በዋጋ ወይም በፈዋሽነት አግባብነት የሌለውን መድኃኒት ወይም የህክምና መሳሪያ የበለጠ ጠቀሜታ አጉልቶ ማሳየት የለበትም፤

፫.የመድኃኒት ወይም የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በማናቸውም መንገድ የሚተላለፍበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፤

፬.ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን ወይም ማስታወቂያ አስተላላፊ አካል አስፈጻሚ አካሉ ያወጣውን መመሪያ አክብሮ የመሥራት ግዴታ አለበት፤

፫.አስፈጻሚ አካሉ የመድኃኒት ወይም የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያ አስመልክቶ የሚወጣው መመሪያ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡

__፶፫.በምርምር ስለመሳተፍ__

ማንኛውም የጤና ባለሙያ በሰው ላይ በሚደረግ ጥናታዊ ስራ ውስጥ ሊሳተፍ የሚችለው ጥናቱ ተገቢውን የስነ ምግባር ግምገማ በማለፍ ነው ከፌደራል ባለስልጣኑ በጽሁፍ ፈቃድ ያገኘና አሰራሩም ተቀባይነት ያገኘውን የጥናት ፕሮቶኮል የጠበቀ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

__፶፬.የሙያ ድጋፍ ወይም ምክር ስለመጠየቅና ስለመስጠት__

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ለተገልጋዩ ጥቅም ሲል አጠራጣሪ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥመው ወይም ተጨማሪ ወይም ከፍተኛ እርዳታ ሲያስፈልገው ከማንኛውም አግባብ ካለው የሙያ ባልደረባው ምክር ወይም ድጋፍ መጠየቅ አለበት፤

፪.በስራ ባልደረባው ምክር የተጠየቀ ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተጠየቀውን ሙያዊ ምክርና አገልግሎት የሙያው ደረጃ በሚፈቅደው መሰረት መስጠት አለበት፡፡

__፶፭.የግል እምነትና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ__

ማንኛውም የሙያ ደረጃው የሚፈቅድ የጤና ባለሙያ እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያ፣ ሕጋዊ ውርጃ ወይም ደም ማስተላለፍ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የህክምና አገልግሎት በድንገተኛ ሲጠየቅ የግል እምነቱን መሰረት በማድረግ የህክምና አገልግሎቱን አልሰጥም ማለት አይችልም፡፡

__፶፮.ሕጋዊ መረጃዎችን ስለመስጠት__

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ተገልጋዩን የሚመለከቱ የላብራቶሪና የሌላ ምርመራ ማዘዣና ውጤት፣ የመድኃኒት ማዘዣ፣ የምስክር ወረቀት፣የደንበኛው ማህደር፣ የሆስፒታል ወይም ሌላ ሪፖርቶችን ሲሰጥ  ሊነበብ በሚችል ጽሁፍ ሙሉ ስሙንና ፊርማውን ማስፈር አለበት፤

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሟላና እውነተኛ የህመም ፈቃድ ወይም የህክምና ምስክር ወረቀት እንደአግባቡ መስጠት አለበት፡፡

__፶፱.ስለ ቆሻሻ አወጋገድና የበሽታን መከላከል__

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ለራሱ፣ ለተገልጋዩ ሆነ ለህብረተሰቡ ጎጂ ባልሆነ መልኩ የቆሸሹና የተጠቀመባቸውን ቁሳቁስ ማስወገድ አለበት፤

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከራሱ ወደ ተገልጋይ፣ ከተገልጋይ ወደ ተገልጋይ፣ ከተገልጋይ ወደ ጤና ባለሙያ ወይም ከጤና ተቋሙ ወደ ተገልጋይ ወይም ባለሙያ በሽታ እንዳይተላለፍ የሚቀመጡ የደህንነት ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት፡፡

__፷.በሽታ ስለሚያስከትለው ሁኔታ ስለመግለጽ__

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የታካሚን የህመም ሁኔታና በሽታው የሚያስከተለውን ውጤት ለታካሚው ወይም ታካሚው ላአካለመጠን ያልደረሰ ወይም የዓእምሮ ህመምተኛ ወይም ራሱን የሳተ ሰው ከሆነ ለቅርብ ቤተሰቡ ወይም ለሞግዚቱ ወይም ላሳዳሪው መግለጽ አለበት፤

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)ድንጋጌ ቢኖርም የጤና ባለሙያው በሞት አፋፍ ላይ ያለና ሊድን በማይችል ወይም ከባድ በሽታን የተያዘን ሰው የበሽታ ሁኔታና በሽታው የሚያስከተለውን ውጤት ለታካሚው መንገር በመንፈስ አለመረጋጋት ታካሚው እራሱን ይጎዳል ብሎ ካመነ ይህንን መረጃ ለታካሚው ቅርብ ቤተሰብ ብቻ ሊናገር ይችለል፤

፫.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የቅድሚያ ምክር የሚያስፈልገው የህመም ሁኔታ ላለበት ህመምተኛ ይህንኑ ምክር ሳይሰጥ የህመሙን ሁኔታና በሽታው የሚያስከትለውን ውጤት መናገር የለበትም።

<u>፷፩.የሰውነት አካላትን ስለማስቀረት</u>

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሰውነት አካልን መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ድጋፍ መስጠት የለበትም፤

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የጤና ባለሙያ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ የሰውነት አካላትን ሊወስድ ወይም እንዲወሰድ ድጋፍ መስጠት ይችላል፦

ሀ.በሕይወት ካለ ሰው ለንቅለ ተከላ ዓላማ፤ ወይም

ለ.ከሞተ ሰው ወይም እንዲወሰድ በህይወት እያለ ፍቃዱን ከሰጠ ሰው ለምርምር፣ ለትምህርት ወይም ለንቅለ ተከላ ዓላማ።

<u>፷፪.ስለሞትና አስከሬን ምርመራ</u>

፩.ሞትን ሊያረጋግጥ የሚችለው ሞትን ሊያረጋግጥ የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ብቻ ሲሆን ባለሙያው በሟች ቤተሰብ ወይም በፖሊስ ወይም በፍርድ ቤት ሲጠየቅ የሞት ምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፤

፪. ሞትን ሊያረጋግጥ የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ማንኛውንም በሞት ምስክር ወረቀቱ የተመለከተውን መረጃ እውነተኝነትና ትክክለኝነት እንዲያዛባ ወይም እንዲለውጥ የሚቀርብ ጥያቄን መቀበል የለበትም፤

፫. ከሟች ቤተሰብ ፈቃድ ካልተገኘ ወይም በሟች ቤተሰብ፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት ካልተጠየቀ በስተቀር ማንኛውም ሞትን ሊያረጋግጥ የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ የአስከሬን ምርመራን ሊያከናውን አይችልም፤

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም የአስከሬን ምርመራ ለትምህርት ወይም ለምርምራ ወይም ለምርምር ዓላማ ማድረግ የሚቻለው ሟች በሕይወት እያለ ፈቃዱን በጽሁፍ ከሰጠ ወይም ሟች በህይወት ዘመኑ ክልከላ ካላደረገና የሟች ቤተሰብ ፈቃድ ከተገኘ ብቻ ይሆናል።

<u>፷፫.የታካሚዎች የግል መረጃ አያያዝ</u>

ማንኛውም የጤና ባለሙያ በጤና ተቋም ውስጥ ከታካሚ ጋር በተደረገ በእያንዳንዱ ግንኙነት የተገኙ የግል ጤና መረጃዎችን አሟልቶ መመዝገብ አለበት።

፷፬.ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ፡-

ሀ)እክል ገጥሞታል ብሎ ያመነበትን የሌላ የጤና ባለሙያን እክል፤ወይም

ለ)የራሱን እክል ሲያውቅ ወይም በይፋ እንዲያውቅ የተደረገ ከሆነ ወይም በተጠረጠረው ወይም በተረጋገጠው እክሉ ምክንያት በሥራ ባልደረቦቹ ተገቢውን ድጋፍ እንዲጠይቅ ምክር ከተለገሰው የራሱን እክል፤ ወይም

ሐ)የሙያ ፈቃድ የሌለው ወይም የሙያ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው የጤና አገልግሎት መስጠቱን ወይም እየሰጠ መሆኑን፤ ወይም

መ)ሙያዊ ስህተት መፈጸሙን፤ወይም

ሠ)የሌላ ባለሙያን ማንኛውም ሙያዊ ያልሆነ ሥነ ምግባርን፤ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፪.ማንኛውም የጤና ባለሙያ ሪፖርት መደረግ አለባቸው ተብለው በህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል የተለዩ ተላላፊ በሽታዎች መኖራቸውን ባወቀ ወይም በጠረጠረ ጊዜ ባፋጣኝ ለህብረተሰብ ድንገተኛ አደጋ ቁጥጥር አካል ማሳወቅ አለበት፤

፫.ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል “እክል” ማለት አንድ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራውን እንዳያከናውን ብቃቱንና ሚዛናዊነቱን የሚያዛባ የአዕምሮ ወይም አካላዊ ሁኔታ የገጠመው ከሆነ ነው፤

፬.ማንኛውም ሰው አንድ ባለሙያ የጤና ሁኔታው ብቁ የሚያደርገው አለመሆኑን ወይም ሙያዊ ያልሆነ ሥነ ምግባር መፈጸሙን ካመነበት ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤

፭.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፬) መሰረት ለባለ ስልጣኑ በቅን ልቦና መረጃ የሰጠ ሰው በሕግ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሰባት

## የሃይጂን፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅና የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር

፷፭.የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

፩.ማንኛውም ሰው ደረቅ፣ ፍሳሽ ወይም ሌሎች ቆሻሻዎችን አካባቢን በሚበክልና በጤንነት ላይ ጉዳት በሚያደርስ ሁኔታ ማጓጓዝ ወይም ማከማቸት ወይም ማስወገድ የለበትም፤

፪.ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች፣ ከማስረጊያዎችና ከኢንዱስትሪ የሚወጣውን ጤና የሚበክል ያልታከመ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ አካባቢ፣ ወደ ውኃ አካላት ወይም ወደ ውኃ አካላት መገናኛዎች መልቀቅ የተከለከለ ነው፤

፫.ማንኛውም ሰው ቆሻሻን ለጤንነት ጎጂ ባልሆነ ሁኔታና አግባብነት ባለው አካል ተለየቶ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ስፍራ ማከማቸት አለበት፤

፬.ማንኛውም የቆሻሻ መሰብሰብ፤ ማጓጓዝ፤ ማከማቸት፤  ማስወገድ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ተግባር ላይ የሚሰማራ ሰው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፫.ማንኛውም ፈሳሽ ቆሻሻ ወደአካበቢ ሊለቀቅ የሚችለው አግባብ ያለው አካል ያወጣውን ደረጃ ሲያሟላ ይሆናል፤

፯.የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖከጤና ወይም ምርምር ተቋም የሚወጣ ደረቅ፣ ፍሳሽ ወይም ሌላ ቆሻሻ በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ አለበት፣ አወጋገዱም የፌደራል ባለሥልጣኑ ያወጣውን ደረጃ ማሟላት አለበት፡፡

፹፯.የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት የሃይጂንና አካባቢ ጤና

ባለሥልጣኑ በከተማው ውስጥ ጤናና ጤናነክ ተቋማት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚያወጣውን የሃይጂንና አካባቢ ጤና መሥፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ እንዳስፈላጊነቱ እርምጃ ይወስዳል፡፡

<u>፹፯.የድምጽና የአየር ብክለት</u>

፩.ማንኛውም ሰው  የህብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅ የድምጽና የአየር ብክለትን ለመከላከል በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን መስፈርቶች ማክበር አለበት፤

፪.ማንም ሰው አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ውጭ ከባቢ አየርን ሊበክል የሚችል ቁፋሮዎችን፤ የቆሻሻ ማቃጠል ሥራ፣ ከባድ ጥቁር ጭስ አውጭ መሣሪያዎች ወይም ሞተሮችን መጠቀም የተከለከለ ነው፤

፫.ከኢንዱስትሪ ወይም ከሌላ የሥራ ቦታ የሚወጣ ማንኛውም ዓይነት ጋዝ፣ ኬሚካላዊ ትነት፣ ጭስ፣ አቧራ፣ ወይም ሌላ አየር በካይ ንጥረ ነገሮችን ለሠራተኛውም ሆነ ለአካባቢው ነዋሪ የጤና አደጋ ወይም ሁከት በማይፈጥርበት ሁኔታ መወገድ አለበት፤

፬.ማንም ሰው የአካባቢውን አየር ሊበክል የሚችል ከባድና ጥቁር ጭስ አውጭ ሞተሮችን ወይም መኪናዎችን መጠቀምም ሆነ መንዳት የተከለከለ ነው፤

፫.ማንኛውም ማሽነሪ በሰው ጤና ላይ ጉዳት ማስከተል በማይችል የድምጽ መጠን ብቻ  መስራት አለበት፤

፯.ማንም ሰው በህዝብ  መገልገያ አካባቢዎች ሆስፒታሎች፣ትምህርት ቤቶች፣ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እና መኖሪያ አካባቢዎችን ጨምሮ የድምጽ ሁከት የሚያስከትል ሞተር፣ ጡሩንባ፣ ድምጽ ማጉያ ወይም በሚጮሁ መሣሪያዎች ከተፈቀደው መጠን በላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፤ ዝርዝሩ ይህንን ደንብ  ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

<u>፹፹.የመጸዳጃ ቤት እንዲኖር ስለማድረግ</u>

፩.ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ንፅህናው የተጠበቀ እና በቂ የመጸዳጃ ቤት ሊኖረው ይገባል፤

፪.ማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ንጽህናው የተጠበቀ በቂ የመጸዳጃ ቤት የማዘጋጀትና ለደንበኞች ክፍት የማድረግ ግዴታ አለበት፤

፫.ማንኛውም የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች አስተዳደሪ አካል በከተማ ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች ንጽህናቸው ሁል ጊዜ የተጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፳፱. ኳራንታይን ስለማድረግና ለይቶ ስለማቆየት

፩.ማንኛውም በተላላፊ በሽታ መያዙ የተጠረጠረ ሰው ወዲያውኑ ኳራንታይን መደረግ አለበት። ባለሥልጣኑ የተጠረጠረ ሰው መኖሩን ሲያውቅ ኳራንታይን እንዲያደርገው ለሚመለከተው አካል ወዲያውን ያስተላልፋል /ያስታውቃል፤

፪.ባለሥልጣኑ ማንኛውም ኳራንታይን የተደረገ ሰውን በተላላፊ በሽታ መያዙን ሲረጋገጥ ወደ ጤና ተቋም ለይቶ ማቆያ ክፍል መዛወሩንና አስፈላጊውን ህክምና መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

፫.ማንኛውም ተለይቶ እንዲቆይ የተደረገ ሰው ተለይቶ እንዲቆይ ሲደረግ ተለይቶ አንዲቆይ ያደረገው ተቋም ሰብአዊ መብቱ መጠበቅ አለበት።

፴.ስለ አደገኛ ኬሚካል

፩.ማንኛውም አደገኛ ኬሚካል ከተማው ውስጥ ሲጓጓዝ፣ ሲከማች፣ ሲከፋፈል፣ ለሽያጭ ሲቀርብ ወይም አገልግሎት ላይ ሲውል በህብተሰብ ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የፌዴራል ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን መስፈርት መሰረት በማድረግ ይቆጣጠራል፤

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ተጥሶ ሲገኝ ባለሥልጣኑ አደገኛ ኬሚካሉን የመያዝ ወይም ከገበያ እንዲሰበሰብ እና እንደአስፈላጊነቱ እንዲወገድ ያደርጋል ወይም ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን ከሚመለከተዉ አካል ጋር ይወስዳል፣ ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፴፩.ስለ አስከሬን አያያዝ እና ዝውውር

፩.አስከሬን ለመቅበር ወይም ለማቃጠል ከተፈቀደው ቦታ በስተቀር ማንኛውንም የሰው አስከሬን ወይንም አፅም መቅበር ወይም ማቃጠል የተከለከለ ነው፤

፪.በባህል፣ በሃይማኖታዊ ወይም በማህበራዊ ስርዓት ምክንያት በ፳፬ ሰዓት ውስጥ አስከሬኑ መቀበር ካልቻለ አስከሬኑ በፈሳሽ ፌኖል ወይም ፎርማሊን ተዘጋጅቶ መቆየት አለበት፤

፫.አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የመቃብሩ ቦታ ለሕዝብ ጥቅም ሲፈለግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ወይም አስከሬን ከተቀበረበት ቦታ ሰባት አመት ካልሞላው በስተቀር ማውጣት የተከለከለ ነው፤

፬.ከሰባት አመት በላይ የቆየ አስከሬን ከተቀበረበት ቦታ መውጣት የሚቻለው ከሚመለከተው አካል የማውጠት ፈቃድ ሲያገኝና ባለስልጣኑ ተገቢውን የጤናና አካባቢ ክትትልና ቁጥጥር ሲያደርግ ይሆናል፤

፭.ማንኛውም አስከሬን ለቤተሰብ የሚሰጠው ወይም የሚጓጓዘው በተገቢው የጤና ባለሙያ አስፈላጊው ክብካቤ ከተደረገለትና አስፈላጊው ምክር፣ ትእዛዝ እና ማስረጃ ከተሰጠ ብቻ ነው።

፴፪.ስለተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

፩. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በአቅራቢያው የተላላፊ በሽታን መኖር ባወቀ ጊዜ ይህንኑ ወዲያውኑ በቅርቡ ላለው የጤና አገልግሎት ተቋም የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ የጤና ተቋሙም አስፈላጊውን እርምጃ እየወሰደ አግባብ ላለው አካል ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤

፪. አግባብ ያለው የጤና ባለሙያ በወረርሽኝ ተላላፊ በሽታ የተያዘን ወይም የተጠረጠረን ማንኛውም ሰው ለተወሰነ ጊዜ ተገልሎ እንዲታከም ወይም እንዲቆይ ማድረግ አለበት፤

፫. በወረርሽኝ ተላላፊ በሽታ የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ለምርመራ፣ ለሕክምና ወይም ለክትባት ፈቃደኛ መሆን አለበት፤

፬. ቤተሰቦች ወይም አሳዳጊዎች ህጻናትን ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል የማስከተብ ግዴታ አለባቸው፤

፭. ባለሥልጣኑ ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር በከተማው ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ፡-

ሀ) ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ሕዝብ የሚሰበሰብባቸው ተቋማት ለተወሰነ ጊዜ ሊዘጋ፤

ለ)ጊዜያዊ የቁጥጥር ጣቢያዎችን በየትኛውም የከተማው ክፍል ሊያቋቁም፤

ሐ)የተላላፊ በሽታ መዛመት ያለበትን የከተማውን የተወሰነ ክፍል እንደ አደጋ ቀጠና ሊሰይም፤ እና

መ)ሌሎች በሽታውን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡

<u>፸፫.ስለመታጠቢያ ሥፍራዎችና የመዋኛ ገንዳዎች</u>

፩.ለጤና አደገኛ በሆነ ቆሻሻ መበከሉ በታወቀ የውሀ ምንጭ በመጠቀም የመታጠቢያ ሥፍራ ማዘጋጀት የተከለከለ ነው፤

፪.የህዝብ መታጠቢያ ወይም የመዋኛ ቦታ አዘጋጅቶ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው አገልግሎቱን ግልጽ የሆነ የቆዳ ህመም ወይም ቁስል ላለባቸው ሰዎች መፍቀድ የለበትም፤

፫.የህዝብ መዋኛ ስፍራ ላይ በመዋኘት ሊተላለፍ የሚችል በሽታ ወይም የቆዳ በሽታ ያለበት፣ የሚታይ ቁስል፣ የቁስል ፕላስተር ወይም ማሸጊያ ያደረገ ሰው ህዝብ በሚዋኝበት ቦታ መጠቀም አይፈቀድለትም፤

፬.የመዋኛ ገንዳዎች ውሃ በየጊዜው መለወጥና እንዳይበከል ክሎሪን በመጨመር መታከም አለበት፤

፭.ማንኛውም የመዋኛ ገንዳ ቦታ በቂ የሆነ መታጠቢያ ሊኖረው ይገባል፤ የመታጠቢያና የመዋኛ ቦታዎች በቂ የሆነ የወንድና የሴት መጸዳጃ ቤቶች ሊኖራቸው ይገባል፤

፮.ባለሥልጣኑ በየወቅቱ የመዋኛ ገንዳዎችን ጥራት ለማረጋገጥ ናሙና በመውሰድ ሊመረምር ይችላል፣ በውጤቱም መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

፯.ማንኛውም መታጠቢያ ስፍራና የመዋኛ ገንዳዎች አግባብ ያለው አካል የሚያወጣቸውን ሌሎች የደህንነትና የኃይጂን ደረጃዎችን ማሟላት አለባቸው፤

፰.አግባብ ባለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ስው የተፈጥሮ እንፋሎት መታጠቢያ ወይም የፍልውሀ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም፤

፱.የሕዝብ መታጠቢያ ስፍራ፣ መዋኛ ገንዳ፣ የተፈጥሮ እንፋሎት ወይም የፍል ውኃ መታጠቢያ አዘጋጅቶ ለከተማው ለሕዝብ አገልግሎት የሚያቀርብ ማንኛውም ድርጅት የፌደራሉ ባለሥልጣን ያወጣውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

<u>፸፱.ከእንስሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ በሽታዎች</u>

፩. ማንኛውም የቤት እንስሳ ባለቤት የሆነ ሰው እንስሳውን የማስከተብ፣ ጤንነቱን የመጠበቅ እና የመከታተል ግዴታ አለበት፤

፪. ባለቤት አልባ የሆኑ የቤት እንስሳን በተመለከተ አግባብ ያለው አካል አስፈላጊውን ክትትልና እርምጃ ስለመውሰዱ ባለስልጣኑ ይቆጣጠራል፤

፫.ማንኛውም ሰው በወረርሽኝ መልኩ ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች የተጠቃ ከሆነ ወይም በዚሁ በሽታ መያዙ ከተጠረጠረ ወይም በሽታው ከተከሰተበት አካባቢ ከመጣ በሽታውን ለመከላከል ሲባል ለሚደረግ ቁጥጥር የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፬. ማንኛውም የጤና አገልግሎት ተቋም ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች በደረጃው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠትና ከአቅሙ በላይ ከሆነ ህክምና ማግኘት ወደሚችልበት ጤና ተቋም በወቅቱ የመላክ ግዴታ አለበት፤

፭. ማንኛውም የጤና አገልግሎት ተቋም ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን አስመልክቶ በየጊዜው የሚወጡ የመከላከልና የመቆጣጠሪያ መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፤

፮. ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታ ያለበት ወይም የህመሙ ምልክት የሚታይበት እንስሳ ሲኖር ባለቤቱ ይህንኑ ባወቀ ጊዜ በሚመለከተው አካል ወዲያውኑ እንስሳውን ወይም የእንሳሳውን ተዋጽኦ ማስመርመር፣ ማሳከም ወይም ማስወገድ አለበት፡፡

<u>፹.ስለ ሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት</u>

፩.ማንኛውም አሰሪ የሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች ለሰራተኞቹ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለበት፤

፪.ባለስልጣኑ ስለ ሥራ ነክ ጤና አጠባበቅና ስለመሳሪያ አጠቃቀም ተገቢውንመመሪያ ያወጣል፡፡

<u>ክፍል ስምንት</u>

<u>ስለተቋማት</u>

<u>፹፩.ስለ ምግብ ተቋምብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>

፩. የምግብ ተቋምን ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፤

፫. ማንኛውም የምግብ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በወሰደበት መስፈርት መሰረት ስራውን ማከናወን ይኖርበታል፤

፬. ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚሰጥበት ወይም በሚያድስበት ጊዜ የአገልግሎቱን ዓይነት፣ አዘገጃጀት፣ ክምችት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ከአገልግሎቱ ጥራትና ደህንነት ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ዓይነት ግዴታ ሊያስቀምጥ ይችላል፤

፭. ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጪ በማንኛውም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

<u>፸፯.ስለ ጤና ተቋምብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት</u>

፩.የጤና ተቋምን ለማቋቋም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፤

፫. ማንኛውም የጤና ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በወሰደበት መስፈርት መሰረት ስራውን ማከናወን ይኖርበታል፤

፬.ማንኛውም የጤና ተቋም ቀጥሮማሰራት የሚችለው ተቀጣሪውየጤና ባለሙያ አግባብ ባለው አካልየተመዘገበ ፍቃድየተሰጠው ሲሆን ነው፤

፭. ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሚሰጥበት ወይም በሚያድስበት ጊዜ የአገልግሎቱን ዓይነት፣ አዘገጃጀት፣ ክምችት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ከአገልግሎቱ ጥራትና ደህንነት ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ዓይነት ግዴታ ሊያስቀምጥ ይችላል፤

፮. ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጪ በማንኛውም መልኩ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

<u>፸፰.ስለ መድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅት</u>

፩.ማንኛውም ሰው የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

፪. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት ደረጃ፣ ባለሙያና ቦታ ውጭ የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፤

፫. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፬. ማንኛውም የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ያልተመዘገበ ወይም ያልተፈቀደ መድኃኒትን ለሽያጭ ማቅረብ ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

<u>፸፱.ስለ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም</u>

፩.ማንኛውም ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም በፌደራል ባለሥለጣኑ የወጡ የጤና አጠባበቅ ደረጃዎችን ማሟላት አለበት፤

፪.የፌደራል ባለስልጣኑ በሚያወጣው ደረጃ መሰረት ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ በየአመቱ ያድሳል፣ መታደሱን ይቆጣጠራል፣ በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ መሰረት መሰራታቸውን ያረጋግጣል።

<u>፹.ባህላዊ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ</u>

፩. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት ባለሙያ፤ ቦታ ውጭ የባህላዊ ሕክምና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

፪. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ባህላዊ መድኃኒት ማምረት፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት።

<u>፹፩.የጤና ምርመራ</u>

፩.ማንኛውም ከተገልጋይ ጋር ግንኙነት ያለው ባለሙያ ወይም ምግብ አዘጋጅ በተቋም ውስጥ ከመቀጠሩ በፊት እና በየዓመቱ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በስተቀር የጤና ምርመራ በተቋሙ ወጪ ማድረግ አለበት፤

፪.ማንኛውም ምግብ አዘጋጅ በምግብ በሚተላለፍ በሽታ በሚያዝበት ጊዜ ለተቋሙ ማሳወቅ ይኖርበታል፤ ማንኛውም የምግብ ተቋም በምግብ በሚተላለፍ በሽታ የተያዘን የምግብ አዘጋጅ መለየት አለበት፤

፫.በምግብ በሚተላለፍ በሽታ የተያዘ መሆኑ የታወቀን የምግብ አዘጋጅ በሽታው የማይተላለፍበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ከምግብ ጋር ንክኪ ካላቸው ስራዎች መገለል አለበት።

<u>፹፪.የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለመመለስ</u>

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት፣ የተሰረዘበት፣ ስራውን ያቋረጠ ወይም እድሳት የተከለከለ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለባለስልጣኑ መመለስ አለበት።

<u>፹፫.የጤና አገለግሎት ተቋም ደረጃ</u>

ባለሥልጣኑ የጤና ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት ዓይነትና ደረጃ በፌደራል ባለሥልጣኑ በሚወሰነው መስረት መፈጸሙን ያረጋግጣል።

<u>፹፬.ሥራ ስለማቋረጥ</u>

ማንኛውም የጤና ተቋም ወይም የመድኃኒት ንግድ ድርጅት ሥራውን ሲያቋርጥ በይዞታው ስለሚገኙ መድኃኒቶችና ስለእነዚሁ ኢንቮይሶች፣ መዝገቦችና ማዘዣ ወረቀቶች ባለሥለጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መፈጸ አለበት።

፹፫.ስለተቋም መስፈርቶች

፩. ማንኛውም ተቋም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በፌዴራል ባለስልጣኑ የተቀመጠውን መስፈርት ስለሚሟላቱ ከባለስልጣኑ አስተያየት ሳያገኝ ማንኛውንም ግንባታ ማከናወን ክልክል ነው፤

፪. በሥራ ላይ የሚገኝ ማንኛውም የጤና ተቋም ማሻሻያ አድርጎ እንደገና ለመመዝገብ ሲያመለክት እየሰራበት የሚገኘውን የህንጻ ፕላን በማቅረብ ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን መመሪያ መተግበር ይኖርበታል፤

፫. ማንኛውም ተቋም ለሚለቀው ጉጂ ንጥረ ነገሮችና ቆሻሻዎች ለመቆጣጠር ውስጣዊ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

፹፬.ስለ ቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪዎች

፩. ማንኛውም የጤና ተቋም የቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በተግባር እንዲለማመዱ ሲፈቀድ የጤና ተቋሙና ትምህርት ቤቱ ልምምዳቸውን የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የቅድመ ወይም ድህረ ምረቃ ተማሪ በታካሚ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ቦርድና ተቆጣጣሪዎች

፹፮.ስለሥራ አመራር ቦርድ

፩.የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር ከ ፭ እስከ ፱ ይሆናል፤

፪.ሰብሳቢዉን ጨምሮ የቦርዱ አባላት በከተማዉ ከንቲባ ይሰየማሉ፤

፫.ያለ ድምጽ የሚሳተፍ የቦርዱ ጸሐፊ ሊሰየም ይችላል፡፡

፹፯.ስለ ተቆጣጣሪዎች

፩. የከተማው አስፈጻሚ አካል የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ለማስፈጸም የወጡ ሌሎች ህጎችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፤

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ መሰረት የተመደበ ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራትይኖሩታል፡-

ሀ) በከተማው የሚገኙ የጤናና ጤና ነክ ተቋማትና የምርት ማጓጓዣዎች በሥራ ሰዓትና እንዳአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሰአት ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ እርምጃም ይወስዳል፤

ለ)ጤናን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖረው በማንኛውም ሰዓት ወደ ማንኛውም ግቢ ወይም ሕንፃ ይገባል፣ ፍተሻም ያካሂዳል፣ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

ሐ) ከምግቦች ወይም ከመድሐኒቶች ወይም እንደአስፈላጊነቱ ቁጥጥር ከተደረገባቸው ላይ ለማስረጃነት የሚያገለግሉ ናሙናዎችን ይወስዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምርመራ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ልኮችን ይወስዳል፣ ፎቶግራፎችን ያነሳል፣ ቪዲዮ ይቀርፃል፣ መረጃዎችን ፎቶ ኮፒ ያደርጋል፤

መ) የተከለሱ፣ የተበላሹ፣ የተጭበረበሩ፣ የተበከሉ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በተጠረጠሩ ምግቦችና መድሀኒቶች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲካሄድ ለማድረግና ውጤቱ እስከሚታወቅ ድረስ በአገልግሎቱ ላይ እንዳይውሉ ታሽገው እንዲቆዩ ያደርጋል፤

ሠ) በተጠረጠረ ግለሰብ ወይም ተቋም ግቢ ወይም በሕንጻው የሚያገኘውን ማንኛውም መሳሪያ፣ ቁሳቀስ ወይም ዕቃ በጤና ላይ ጉዳት እንዲሁም የተለያዩ አደጋዎች የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል ነው የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖረው ዕቃው ተለይቶ እንዲቀመጥ ለማድረግና ጤናን ሊበክሉ የሚችሉ አላስፈላጊ ቁሳቁሶችንም እንዲወገዱ ለማድረግ ይችላል፡፡ ሆኖም ዕቃውን የመለያየት እርምጃ በዕቃው ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆን የለበትም፤

ረ) ምግቦችና መድሀኒቶች የአገልግሎት ዘመናቸው ሲያበቃ ወይም በዚህ ደንብ መሰረት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሲወሰን በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ ለማድረግና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪(ሠ) መሰረት የታሸጉትን በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

<u>ክፍል አስር</u>

<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና የቅሬታ አቀራረብ</u>

<u>፹፬.አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

፩. ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ወይም ለደንቡ አፈጻጸም የወጣን መመሪያ በመተላለፍ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ የተሰጠው የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ሊታገድ፣ ሊሰረዝ ወይም እንደ አግባቡ ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላል፤

፪. ባለሥልጣኑ ማንኛውም መድኃኒት ወይም ምግብ ለአገልግሎት ብቁ አለመሆኑን ሲያረጋግጥ መድኃኒቱን ወይም ምግቡን ለመያዝና በባለቤቱ ወይም በባለ ይዞታው ወጪ እንዲወገድ ሊያደርግ ይችላል፤

፫. ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው በምግብ ወይም በመድኃኒት ንግድሥራ ወይም  በጤና አገልግሎት ተሰማርቶ ከተገኘ ባለስልጣኑ ተቋሙን ያሽጋል እንዲሁም ሌሎች ተገቢ እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

<u>፺.ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

፩. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ የተከለከለ፣ የምስክር ወረቀቱ ወይም ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ወይም ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች

የተወሰደበት ሰው ቅሬታውን እርምጃው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ ፴ ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ ላቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፤

፪. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት አካል ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

## ክፍል አስራ አንድ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፺፩.ስለንግድ ማስታወቂያዎች

፩.በከተማው ውስጥ የሚተላለፉ የምግብ፣ የመድኃኒት ወይም የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በማናቸውም መንገድ የሚተላለፍበት ሁኔታ የፌደራሉ ባለሥልጣኑ የሚያወጣው መመሪያ ይሆናል፤

፪. ማንኛውም የመገናኛ ብዙኃን ወይም ማስታወቂያ አስተላላፊ አካል የፌደራሉ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መመሪያ አክብሮ የመሥራት ግዴታ አለበት፤

፫. ባለሥልጣኑ የምግብ፣ የመድኃኒት ወይም የጤና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያ አስመልክቶ በፌደራል ባለሥልጣኑ የሚወጣው መመሪያ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

### ፺፪.መረጃ ስለመስጠት

፩. የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ስለሥራቸው መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፤

፪. ባለሥልጣኑ ስለሰጠው፣ ስላገደው ወይም ስለሰረዘው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ ለህብረተሰቡ ወይም ለሚመለከተው አካል እንደ አግባቡ ያሳውቃል።

### ፺፫.የመተባበር ግዴታ

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

### ፺፬.መረጃ ስለማቅረብ

፩.ማንኛውም የጤና ባለሙያ በባለሥልጣኑ በማናቸውም ጊዜ የሙያ ስራ ፈቃዱን እንዲያሳይ ወይም የራሱን ወይም የሌላ ባለሙያ ሙያዊ እንቅስቃሴ የሚያሳይ መረጃ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት ያገኘውን መረጃ በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር በምስጢር መጠበቅ አለበት።

### ፺፭.ስለ አገልግሎት ክፍያ

ማንኛውም ሰው የሙያ ስራ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ለማሳደስ፣ ሌሎች ምስክር ወረቀቶችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ አግባብ ባለው አካል በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

### ፺፮.ቅጣት

በኢትዮጵያ ወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ይህን ደንብ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው በፌደራል አዋጁ ፯፻፴፩/፪ሺ፪ መሰረት ይቀጣል፡፡

<u>፺፰.ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

የሚከተሉት ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡-

፩. የክልል ፲፬ መስተዳድር ደንብ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯ ዓ.ም የወጣው የሃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ደንብ በዚህ ደንብ ተሽሯል፤

፪. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

<u>፺፱. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከግንቦት ፴ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## ደንብ ቁጥር ፻/፪ሺ፲

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ

ማውጫ


ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ
፪. ትርጓሜ
፫. የፆታ አገላለፅ
፬. የተፈፃሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት
ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በአይነት መለየት፣ አጓጓዝ፣ መልሶ መጠቀም፣ ዑደትና ማስወገድ

፭. የደረቅ ቆሻሻን በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶች
፮. የደረቅ ቆሻሻን በተመለከተ የተጣሉ ግዴታዎች
፯. ደረቅ ቆሻሻን መሰብሰብና ማጓጓዝን በተመለከተ የተጣሉ ግዴታዎች
፰. ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም፣ ዑደትና ማስወገድ በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶችና የተጣለ ግዴታ

ክፍል ሶስት
ደረቅ ቆሻሻ ስለመጣል

፱. የተከለከሉ ድርጊቶች
፲. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል አራት
የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ደስት ቢን አጠቃቀምና አያያዝ

፲፩. የተከለከሉ ድርጊቶች
፲፪. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል አምስት
የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ማህበራት/ድርጅቶች የቆሻሻ አያያዝ

፲፫. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል ስድስት
ከተለያዩ ቦታዎች ስለሚመነጩ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ

፲፬. የተከለከሉ ድርጊቶች
፲፭. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል ሰባት
የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

፲፮. የተከለከሉ ድርጊቶች
፲፯. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል ስምንት
የተለያዩ አካባቢዎች ጽዳትና ቋሚ የጽዳት ቀን ስለመወሰን

፲፰. የተጣሉ ግዴታዎችን የተከለከለ ድርጊት

ክፍል ዘጠኝ
የደህንነት መጠበቂያ ስለመጠቀም፣ ግንዛቤ ስለመስጠት

፲፱. የተከለከሉ ድርጊቶች
፳. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል አስር
በደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ላይ ስለሚሰሩ ድርጅቶች ግዴታዎ

፳፩. የተጣሉ ግዴታዎች

ክፍል አስራ አንድ
የኤጀንሲውና የሌሎች ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

፳፪. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት
፳፫. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት
፳፬. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት
፳፭. የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት
፳፮. የሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባር

ክፍል አስራ ሁለት
ስለአገልግሎት ክፍያና ማበረታቻ

፳፯. ስለጽዳት አገልግሎት ክፍያ
፳፰. ስለማበረታቻ

ክፍል አስራ ሶስት
ስለአስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ

፳፱. አስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ
፴ . ቅጣትን ስለማስፈፀም
፴፩. ስለአቤቱታ አቀራረብ

ክፍል አስራ አራት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
፴፪. የመተባበር ግዴታ
፴፫. መመሪያ የማውጣት ስልጣን
፴፬. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች
፴፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ደንብ ቁጥር፲፫/፲፱፻፺፯ ለማሻሻል የወጣ ደንብ ነው፡፡ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፯ የደረቅ ቆሻሻ፣ የፍሳሽ ቆሻሻና የውበትና ፓርክ ተግባራት በአንድ ላይ ተቀላቅለው ለአንድ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን ነገር-ግንበ አሁን ወቅት እነዚህንተግባራት የተለያዩ ተቋማት የሚያስተዳድሩት በመሆኑ ይህን ደንብ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የተደነገገ ደንብ ነው፡፡በተጨማሪም ደንቡ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በአይነት መለየት፣ አጓጓዝ፣ መልሶ መጠቀም፣ ውደትና ማስወገድ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ክልከላዎችን እና ግዴታዎችን ያስቀምጣል፡፡ በተያያዘም ይህንን ደንብ በማስፈፀም ሂደት ውስጥ ኤጀንሲው እና የከተማው አስተዳደር ሌሎች አስፈፃሚ አካላት ያላቸውን ተግባርና ኃላፊነትም ይዘረዝራል፡፡

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፶/፪ሺ፲</u>

በከተማዋ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘርፉ የሚታየውን የመልካም አስተዳደር ችግር በመቅረፍ የከተማዋ ጽዳት አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ ወደ ተሻለ እርከን ለማሸጋገር በማስፈለጉ ፤

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፮የደረቅ ቆሻሻ፣ የፍሳሽ ቆሻሻና የውበትና ፓርክ ተግባራት ተቀላቅለው ለአንድ ኤጀንሲ የተሰተጠ ሲሆን ነገር ግን በአሁን ወቅት እነዚህን ተግባራት የተለያዩ ተቋማት የሚያስተዳድሩት ተግባር በመሆኑ ይህን ደንብ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፰ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፰/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት  ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ <<የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፶/፪ሺ፲>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. <<ከተማ>> ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. <<ኤጀንሲ>>ማለት የአዲስ አበባከተማ አስተዳደርየደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፫. <<ክፍለ ከተማ>>ማለት የከተማው ሁለተኛ የሆነ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

፬. <<ወረዳ>>ማለት የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳዳር እርከን የሆነ የክፍለ ከተማ አካል ነው፡፡

፭. <<ጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ>> ማለት በየቦታው በግልፅ የሚታዩና በሰዎች እንቅስቃሴ ምክንያት ተጠቃሚዎች የሚጥሏቸው የሲጋራ ቁርጥራጭ፣ የሶፍት ወረቀት፣ ፌስታል፣ የጫት ገለባ፣ የፍራፍሬ ተረፈ-ምርቶች፣ የትራንስፖርት ቲኬት፣ የሞባይል ካርዶችን፣ የማስቲካና ከረሜላ ሽፋኖች፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

፱. <<የኤሌክትሮኒክስ ነክ ቆሻሻዎች>> ማለት እንደገና አገልግሎት ሊሰጡ ወይም ላይሰጡ የሚችሉ ኮምፒዩተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ማንኛውም የስልክ ቀፎ፣ ቴሌቪዥኖች፣ የማቀዝቀዣ መሳሪያዎች፣ ወዘተ እና የእነዚህ ዕቃዎች የውስጥና የውጭ ስብርባሪና የወላለቁ አካላት ማለት ነው፡፡

፲. <<አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ>> ማለት የሚፈነዱ፤ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ፤ መርዛማ ነገሮች፤ ራዲዮአክቲቭ ቁሶች፤ ልዩ ልዩ ኬሚካሎች፤ የደም ንኪኪ ያላቸው ሆነው ከኢንዱስትሪ፤ ከማምረቻ ተቋማት፤ ከጤና ተቋማት ወይም ከቤተ ሙከራ የሚወጡና በሰው፤ በእንስሳ፤ በእጽዋትና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ማንኛውም ቆሻሻ ነው፡፡

፲፩. <<የመንገድ ጽዳት>> ማለት የአንድን መንገድ ግራና ቀኝ ጠርዞች፣ የእግረኛ መንገድና አካፋይ መንገድ ማጽዳት፣ ጥቃቅን ቆሻሻዎች የሚጣሉበት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችን ማራገፍ፣ መንገድ በሚያልፍባቸው ድልድዮች አካባቢ በሕገ-ወጥ ተግባር የሚጣለውን ደረቅ ቆሻሻ መከላከልና ማጽዳትን ያካትታል፡፡

፲፪. <<ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ መለየት>>ማለትኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻን የሚያመነጨው አካል በግቢው ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን እንደ ተፈጥሮአዊ ባህሪው ለይቶ ለየብቻ ማከማቸት ነው፡፡

፲፫. <<ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ>> ማለት ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳረርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ በዓይነት ለይቶ ወደ ጊዜያዊ ማቆያ ማዕከላት፤ ኡደት ማዕከላት፤ ማቃጠያና ማስወገጃ ቦታ ማጓጓዝ ነው፡፡

፲፬. <<መልሶ መጠቀም>> ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት በቀጥታ ወይም የተወሰነ ለውጥ አድርጎ ለተመሳሳይ ወይም ለተለየ አገልግሎት መጠቀም ማለት ነው፡፡

፲፭. <<መልሶ ኡደት ማድረግ>> ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም ከመጀመሪያው ዕቃ ጋር የሚመሳሰል ወይም የማይመሳሰል ጠቃሚ ዕቃ ማምረት ነው፡፡

፲፮. <<ቅብብሎሽ ጣቢያ>> ማለት ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ በተሽከርካሪዎች እየተሰበሰበ ለጊዜው የሚቆይበት፣ እንደሁኔታውም በዓይነት የሚለይበትና ጥቅም የማይሰጠው፣ ወደ ማስወገጃ ቦታ በተሽከርካሪዎች ለማጓጓዝ የሚያስችል የመቀባበያ ጣቢያ ነው፡፡

፲፯. <<ቆሻሻን በከፍተኛ ሙቀት ማቃጠል>>ማለት ከሸክላ ጡብ፤ ከወፍራም ብረት፤ ከድንጋይ ወይም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተሰራ መሳሪያ በመጠቀም ሊቃጠሉ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በከፍተኛ ሙቀት (በኦክሲጅን ወይም ያለ ኦክሲጅን) ሁከትና ብክለት በማይፈጥር ሁኔታ በማቃጠል ለጤና ጎጂ ወዳልሆነ ዝቃጭ ወይም አመድ መለወጥ ነው፡፡

፲፰. <<ማስወገጃ ቦታ>> ማለት ምንም ጥቅም የማይሰጠውን ደረቅ ቆሻሻ በመሬት ላይ ወይም በመሬት ውስጥ ለጤናና ለአካባቢ ጠንቅ በማይሆንበት መንገድ የሚደፋበት፣ የሚከማቸበት፣ የሚቀበርበት ወይም የሚወገድበት ስፍራ ነው፡፡

፲፱. <<የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት>> ማለት ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመሰበስብ፣ የማጓጓዝ፣ የማስወገድና የመንገድ ጽዳትና  አገልግሎት የሚሰጡ በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን፣ ወዘተ የሚሰሩና የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው፡፡

፳. <<የመልሶ መጠቀምና ኡደት ድርጅት>> ማለት በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን፣ ወዘተ የሚሰሩና ደረቅ ቆሻሻን ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚያውሉ ድርጅቶች ወይም ፋብሪካዎች ናቸው፡፡

፳፩.<<ሰው>> ማለት በተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፳፪. <<የደንብ ማስከበር ደንብ>>ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ደንብ ቁጥር ፶፬/፪ሺ፫ ነው፡፡

፫. <u>የፆታ አገላለፅ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

፬. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

### <u>ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በዓይነት መለየት፣ አጓጓዝ፣ መልሶ መጠቀም፣ ኡደትና ማስወገድ</u>

<u>፭. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶች</u>

፩. ማንኛውን መኖሪያ ቤት ወይም ድርጅት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በሰው፣ በእንስሳት፣ በአካባቢና በሌሎች ሰዎች ድርጅት፣ ጤናና የከተማዋን ጽዳት ገጽታ ሊያበላሽ በሚችል መልኩ መያዝ ወይም ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፪. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ከደንበኛው ሲረከብ አካባቢው ላይ ማዝረክረክና ማንጠባጠብ የተከለከለ ነው፡፡

፮. <u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ የተጣሉ ግዴታዎች</u>

፩. ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ ተሰብስቦ እስከ ሚወገድ ድረስ ቆሻሻውን ያመነጨው አካል ኤጀንሲው ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት በዓይነት ለይቶ የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡፡

፪. ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት ኤጀንሲው ባወጣው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት በማጠራቀም ለጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ በቆይታ ምክንያት የጤና ችግር ወይም የአካባቢ ብክለት በማያስከትል ሁኔታ መያዝና ማጠራቀም ይገባዋል፡፡

፬. ማንኛውም የመኖሪያ ቤት አከራይ በግቢው ውስጥ ያለው ተከራይ ደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ እንዲይዝና እንዲለይ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፯. ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝን በተመለከተ የተጣሉ ግዴታዎች

፩. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ከመኖሪ ቤትና ከድርጅት የሚሰበስብ የጽዳት ድርጅት ከኤጀንሲው እውቅናና ውል ሊኖረው ይገባል፡፡

፪. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻን ከመኖሪ ቤት ወይም ከድርጅት የሚሰበስብ የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ኤጀንሲው ባወጣው ወይም በሚያወጣው የተሽከርካሪ ስታንዳርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻውን መሰብሰብና ማጓጓዝ ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ኤጀንሲው ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት ለደንበኞቹ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ ወደ ቅብብሎሽ ጣቢያ፣ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ማስወገጃ ቦታ ሲያጓጉዝ በጉዞ ላይ ቆሻሻ በንፋስ እንዳይበተን በሸፍን ተሽከርካሪ ወይም ሙሉ በሙሉ በመረብ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

፭. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ እስከ ማስወገጃ ቦታ እንዲያጓጉዝ ፈቃድ የተሰጠው የጽዳት ሽርክና ማህበር ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማጓጓዝ ግዴታ አለበት፡፡

፰. ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም፣ ኡደትና ማስወገድ በተመለከተ የተከለከሉ ድርጊቶችና የተጣለ ግዴታ

፩. የተለያዩ እቃዎች ተጠቅልሎባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡት ውጭ ውፍረታቸው 0.0፫ ሚ.ሜና በታች የሆኑ የእቃ መያዣ ፕላስቲክ ፌስታል በከተማው ውስጥ ማምረት፣ መሸጥ፡ ለእቃ መያዣነት መጠቀም፣ ከቦታ ቦታ ማዘዋወር፣ ወደ ከተማው ማስገባት፣ በመጋዘንና በንግድ መደብር ማስቀመጥና መሸጥ፣ በምርት ማሸጊያነት መጠቀም፣ በታሸጉ ምርቶች ላይ ለማስታወቂያነት መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

፪. ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ወደ ማስወገጃ ቦታ ማጓጓዝና ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፫. ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ህጋዊ ፈቃድ ወይም ህጋዊ ውክልና ሳይኖረው ከየትኛውም ቦታ መሰብሰብም ይሁን ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፬. ማንኛውም ሰው በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ውስጥ ከኤጀንሲው ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን መልቀም፣ ማከማቸትና መጫን የተከለከለ ነው፡፡

፭. ማንኛውም የመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ሰብስቦ አገልግሎት ላይ የሚያውል ድርጅት ከኤጀንሲው ፈቃድ ወይም የድጋፍ ደብዳቤ ሊኖረው ይገባል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ደረቅ ቆሻሻ ስለመጣል

፱. የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

፩. ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ መንገድ፣ በባቡር ሀዲድ፣ አውቶብስ መነኸሪያዎችና ፌርማታዎች፣ በእግረኛ መንገድ፣ በአደባባይ፣ በማንኛውም ክፍት ቦታ፣ በውሀ አካላት፣ በአረንጓዴ ቦታዎች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች ውስጥ፣ አጥር ጥግ፣ የመንገድ አካፋዬች ወዘተ መጣል ወይም እንዲጣል ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፪. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት/ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃነት ከፈቀደው ቦታ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ማስቀመጥ፣መጣል፣ማቃጠል ወይም መቅበር የተከለከለ ነው፡፡

፫. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ጊዚያዊ ማቆያ ከፈቀደው ቦታ ውጭ ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጥ ወይም ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡

፬. ማንኛውም አሽከርካሪ ሆነ ተሳፋሪ ከመኪና ውስጥ ሆኖ በመስኮትም ይሁን በበር በኩል ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ መወርወር ወይም መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፭. ከንግድ ድርጅት/መኖሪያ ቤት የመነጨ ደረቅ ቆሻሻን ጠርጎ ወደ መንገድ ዳር ማስቀመጥ ወይም መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፲. የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩. ማንኛውም ሰው ከቤት ውጭ በእንቅስቃቀሴ ምክንያት የሚመነጩ ጥቃቅን ቆሻሻዎች (የሶፍትና የወረቀት ቁርጥራጮች፣ የተለያዩ የምግብ፣ የመጠጥና ትናንሽ እቃዎች ማሸጊያዎች፣ የማስቲካና የከረሜላ ልጣጭ ወዘተ) በመንገድ ዳር በተቀመጡ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

፪. በንፋስ የሚበተን እቃ ጭኖ በመንገድ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የጭነት ተሽከርካሪ ሙሉ በሙሉና በአግባቡ ሸፍኖ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

### የጥቃቀን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ደስት ቢን አጠቃቀምና አያያዝ

፩. የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

፩. በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች ላይ ከቤት፣ ከድርጅትና ከገበያ ማዕከላት የመነጨ ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡

፪. የሞቱ እንስሳትን በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች ላይ መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፫. በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎች ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ ተደግፎ ንግድ ማከናዎን፣ በላያቸው ላይ እቃ ማስቀመጥና ማስደገፍ የተከለከለ ነው፡፡

፬. በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫዎች ላይ ከወረዳው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት እውቅና ውጭ ከአካባቢው ማስወገድ፣ መንቀል፣ ቦታቸውን መቀየር፣ ለሌላ አገልግሎት ማዋል የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

### የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ማህበራት /ድርጅቶች የቆሻሻ አያያዝ

፫. የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ማህበር/ድርጅት የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ እስከሚጓጓዝ ድረስ ሸፍኖ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ የጽዳት ማህበር/ድርጅት የሰበሰበውን ደረቅ ቆሻሻ ጽዳት ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት የማጓጓዝ ወይም እንዲጓጓዝ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ማህበር/ድርጅት መጥፎ ሽታ ሊፈጥሩ የሚችሉና ለጤና ስጋት የሆኑ ደረቅ ቆሻሻዎችን በልዩ ሁኔታ በፍጥነት ከአካባቢው ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዲጓጓዙ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፬. በህግ በተፈቀዱ ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማሰቀመጫ ቦታዎች የሚሰሩ የጽዳት ማህበራት/ድርጅቶች የማቆያ ቦታውን ከውስጥና ከግቢው ውጭ እስከ ፭ ሜትር ዙሪ ድረስ ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ቆሻሻው እንዳይበተንየማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት የጽዳት ኤጀንሲ በሚያወጣው የአሰራር ስታንዳርድና መመሪያ መሰረት ለደንበኞች አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ከተለያዩ ቦታዎች ስለሚመነጩ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ

፩. የተከለከሉ ድርጊቶች

፩. የሞቱ እንስሳትን በየትኛውም ቦታ መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፪. ማንኛውም በከተማው የሚገኝ ስጋ ቤት የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርቱን ባልተፈቀደ ቦታ መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፫. የተበላሹ የአትክልትና የፍራፍሬ ተረፈ ምርቶችን ከንግድ ማዕከሉ ግቢ ውጭ ወይንም መንገድ ዳር ማከማቸት፣ ማስቀመጥ ወይም መጣል የተከለከለ ነው፡፡

፪.የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩. ማንኛውም የቤት እንስሳትን የሚያረባ ሰው/ድርጅት ከእንስሳቱ የሚወጡ እዳሪዎችንና የእንስሳቱ የምግብ ተረፈ ምርቶችን በአግባቡ የመያዝና በተፈቀደ ቦታ ብቻ የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

፪. የቤት እንስሳትን በመንገድ ይዞ የሚንቀሳቀስ ሰው/ድርጅት ከእንስሳቱ የሚወጡ እዳሪዎች በመንገድ ላይ ለሚፈጥሩት የጽዳት ችግር ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. በከተማው በእንስሳት ጀርባ ተጭነው የሚጓጓዙ ሳር፣ ጭድና ቅጠላ ቅጠል አካባቢን በማያቆሽሽ መልኩ በአግባቡ ተሸፍኖ መሆን ይገባዋል፡፡

፬. በከተማው የሚገኙ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው የእንስሳት የግብይት ማዕከላትን የሚያስተዳድሩ ድርጅቶች የገበያ ማዕከሉን ውስጥና የግቢውን ውጭ እስከ ፳ ሜትር ዙሪያ በቋሚነት በማጽዳት ቆሻሻውን በተፈቀደላቸው ቦታ ብቻ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማስወገድ ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. በከተማው ለሰው ልጅ ጤንነት ችግር የሚፈጥሩ የቤት እንስሳትን የሚገድል ድርጅት/ተቋም እንስሳቱን ከመግደሉ በፊት ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እቅዱን ለኤጀንሲው በማቅረብ ዝግጅት እንዲደረግ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፮. የቤት እንስሳት የሞተበት ሰው/ድርጅት የሞቱ እንስሳትን አንስቶ ለሚያስወግዱ ድርጅት ወይም ለወረዳው ጽዳት ጽሕፈት ቤት በስልክ ወይም በአካል እንዲነሳለት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፯. ማንኛውም የሞቱ የቤት እንስሳትን አንስቶ የሚያስወግዱ ድርጅት/የመንግስት ተቋም ጽዳት ኤጀንሲ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ጤናንና አካባቢንና በማይጎዳ ሁኔታ የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

፰. በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ የተሰማራ ሰው/ድርጅት ተረፈ ምርቶቹን ለጤና ወይም ለአካባቢ ጎጂ ባልሆነ ሁኔታ በንግድ ማዕከሉ ግቢ ውስጥ በራሳቸው ወጭ ለዚሁ ተብሎ ባዘጋጁትና

ክዳን ባለው ፍሳሽን ሊያስወጣ በማይችል ደረጃውን በጠበቀ ማጠራቀሚያ እቃ ውስጥ የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡፡

፱. ማንኛውም አትክልትና ፍራፍሬ የሚነግድ የገበያ ማዕከል ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡ ማንኛውም የአትክልትና የፍራፍሬ የሚነግድ ሰው/ድርጅት ከተሽከርካሪ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ ሲጭንና ሲያወርድ የሚወዳድቁ ቆሻሻዎችን ወዲውኑ የማጽዳት ግዴታ አለበት፡፡

፩. ከግንባታ ቦታ ላይ በንፋስ በቀላሉ የሚበተን ወይም አካባቢን ሊያቆሽሽ የሚችል አሸዋ፣ ፍርስራሽ፣ ጠጠር፣ ጭቃ ጭኖ በመንገድ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የጭነት ተሽከርካሪ ሙሉ በሙሉ ከግንባታ ቦታው ሳይወጣ ሸፍኖ ወይም ጭቃውን አጥቦ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፡፡

፪. በግንባታ ወቅት ከግንባታ ማዕከሉ በተሽከርካሪው ጎማ አማካኝነትና ከጭነት መንጠባጠብ ምክንያት ከግንባታ ማዕከሉ ውጭ ለሚፈጠር የአፈር፣ የጭቃ፣ የአሸዋና የጠጠርና የፍርስራሽ መበተን አካባቢውን እንዳይቆሽሽ ግንባታው እስኪያልቅ ድረስ የግንባታው ባለቤት ቋሚ የጽዳት ባለሙያ ቀጥሮ አካባቢውን የማጽዳትና ንጹህ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም በከተማው የሚገኝ ስጋ ቤት የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርቱን በአግባቡ የመያዝ፣ መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ወይም የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ</u>

፤. <u>የተከለከሉ ድርጊቶች</u>

፩. ማንኛውንም ዓይነት አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ የማዘጋጃቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፪. አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ጋር ቀላቅሎ ማጓጓዝም ይሁን ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፫. ከጤና ተቋማት የሚመነጫ ደረቅ ቆሻሻን ከማዘጋጃ ቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ጋር ቀላቅሎ ማጠራቀም፣ ማጓጓዝ ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፬. የኤሌክትሮኒክስ ደረቅ ቆሻሻዎችን ሕጻናት በሚውሉባቸውና በሚጫወቱባቸው አካባቢዎች፣ በየመንገዱና በተገኙ ክፍት ቦታዎች መወርወርና እንዲወገዱ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፤.<u>የተጣሉ ግዴታዎች፡-</u>

፩. አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጭ ሰው/ድርጅት ያመነጨውን አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ከማዘጋጃ ቤታዊ ደረቅ ቆሻሻ ለይቶ ማከማቸት ወይም ማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

፪. የኤሌክትሮኒክስ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ኤጀንሲ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሰውንና የአካባቢን ጤንነትና ደህንነት በማይጎዳ ሁኔታ መወገድ ይገባዋል፡፡

፫. ማንኛውም ግለሰብ ወይም የከተማ ነዋሪ የደረቅ ቆሻሻን በሚያስወግድበት ወቅት ደረቅ ቆሻሻን በዓይነት መለየት የሚጠበቅበት ቢሆንም የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን በተለየ መልኩ በመለየት በደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብና በማስወገድ ሥራ ለተሰማሩ ሠራተኞች ማስረከብ አለበት፡፡

፬. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የተሰማሩ የጽዳት ሠራተኞች የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻዎችን በሚሰበስቡበትና በሚያጓጉዙበት ወቅት ከሌሎች የደረቅ ቆሻሻ ዓይነቶች ለይተው ለመልሶ መጠቀም በሚውልበት መልኩ መሆን አለበት፡፡

፭. የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁስ አምራቾች፣ አስመጪ ድርጅቶች፣ ተጠቃሚ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያረጁና አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶችን በአግባቡና አካባቢን በማይበክል መንገድ እንዲወገዱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፮. ማንኛውም የጤና ተቋም በተቋሙ የሚመነጨውን የሜዲካል ደረቅ ቆሻሻ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ወይም የምግብና መድሃኒትና መጠጥ ቁጥጥር ባለስልጣን በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በሚገነባ ማቃጠያ ውስጥ ደረቅ ቆሻሻው እንዲቃጠልና እንዲወገድ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## የተለያዩ አካባቢዎች ጽዳትና ቋሚ የጽዳት ቀን ስለመወሰን

፹. የተጣሉ ግዴታዎችና የተከለከለ ድርጊት

፩. ማንኛውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የንግድ ተቋም፣ ኢምባሲ፣ ከመስሪያ ቤቱ አጥር አጠገብ በ፭ ሜትር ክልል ውስጥ የሚገኘውን አካባቢ በቋሚነት ጽዱ የማድረግ፣የመንከባከብና በአካባቢው ለተጣለ ደረቅ ቆሻሻ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. ማንኛውም ነዋሪ ከመኖሪ ቤቱ አጥር አጠገብ በ፭ ሜትር ዙሪያ ክልል ውስጥ የሚገኘውን አካባቢ በቋሚነት ጽዱ የማድረግ፣ የመንከባከብና በአካባቢው ለተጣለ ደረቅ ቆሻሻ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. ወቅታዊና ልዩ ዝግጅቶች ማለት ፌስቲቫል፣ ባዛር፣ ኤግዚብሽን፣ የመንገድ ላይ ሩጫ፣ የተለያዩ ሰልፎች፣ ወዘተ የሚያዘጋጁ ድርጅቶች/ግለሰቦች የአካባቢውን ጽዳት ዝግጅቱ እስኪ ጠናቀቅ ድረስ በኃላፊነት የመጠበቅና የማጽዳት ግዴታ አለባቸው፡፡

፬. ዓመታዊ፣ ወርሃዊና ሳምንታዊ የእምነት በዓላት የሚያከናውኑ የእምነት ተቋማት ለምዕመኑ በአካባቢው ቆሻሻ እንዳይጣል የማስገንዘብና በዓሉ ሲጠናቀቅ በእለቱ አካባቢውን የማጽዳት ግዴታ አለባቸው፡፡

፭. የታክሲና ሚኒባስ ተራ አስከባሪዎች፣ የፓርኪንግ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፣ በጫማ ጥገናና ጽዳት (ሊስትሮ) የተሰማሩ፣ በእረፍት ቀን (ቅዳሜና እሁድ) መንገድ ላይ እንዲነግዱ ህጋዊ ፈቃድ የተሰጣቸው ነጋዴዎች ወዘተ የሚሰሩበትን አካባቢ እስከ ፭ ሜትር ዙሪያ በቋሚነት የማጽዳት፣ የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

፮. ማንኛውም በገበያ ማዕከል ውስጥ የሚነግድ ግለሰብ/ድርጅት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው የማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በግቢው ውስጥ ማከማቸት ይገባዋል፡፡

፯. ማንኛውም በገበያ ማዕከል ውስጥ የሚነግድ ግለሰብ/ድርጅት ከሱቁ ወይም ከመደብሩ ፊት ለፊት የወደቁ ደረቅ ቆሻሻዎችን ወዲያውኑ የማንሳትና ንጹህ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፰. አጠቃላይ በገበያ ማዕከሉ ጽዳት ለማስጠበቅ የገበያ ማዕከሉ አስተዳደሪ በራሱ ወጭ ቋሚ የጽዳት ባለሙያዎችን ቀጥሮ አካባቢውን በቋሚነት ማጸዳት ይጠበቅበታል፡፡

፱. ማንኛውም የገበያ ማእከል ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት በዓይነት ለይቶ ማጠራቀም ይገባዋል፡፡ ማንኛውም የገበያ ማእከል ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡

፩.የመንገድ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች/ግለሰቦች መንገድ ግራና ቀኝ ጠርዞች፣ የእግረኛ መንገድና አካፋይ መንገድ ማጸዳት፣ ጥቃቅን ቆሻሻዎች የሚጣሉበት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችን ማራገፍ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም በግል ድርጅት ወይም በማህበር ተደራጅቶ መንገድን የሚያፀዳ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፫. በከተማው የሚንቀሳቀሱ የከተማ አውቶብሶችና ቀላል የከተማ ባቡሮች በትኬት ምክንያት ለሚፈጠር የአካባቢየጽዳት ችግር ድርጅቶች ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፬. የከተማ ባቡሩን የሚያስተዳድረው ድርጅት የባቡር ሀዲድ የተዘረጋባቸውን መስመሮችና የባቡር ፌርማታዎችን ሙሉ በሙሉ በቋሚነት ጽዳቱን የመጠበቅና የማጽደት ግዴታ አለበት፡፡

፭. በአዲስ አበባ ከተማ የወሩ የመጨረሻ አርብ ለትምህርት ቤቶችና ለመንግስትና ለግል መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ቅዳሜ ለነዋሪውና በስራ ቦታቸው ላሉ ማንኛውም ተቋማት አጠቃላይ የጽዳት ቀን ይሆናል፡፡

፮. ሁሌም በወሩ የመጨረሻው ዓርብ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሁሉም የመንግስት መስሪ ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ኢምባሲዎች ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞችና ኃላፊዎች በጋራ የስራ ቦታቸውን ግቢ እና ከግቢ ውጭ እስከ ፭ ሜትር እንዲያፀዱ ይገደዳሉ፡፡

፯. ሁሌም በወሩ የመጨረሻው ቅዳሜ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሁሉም የከተማው ነዋሪ የመኖሪያ አካባቢውን በጋራ ወጥቶ እንዲያጸዳ ይገደዳል፡፡

፲፰. ክፍት ቦታዎችን የአካባቢው ነዋሪ በጋራ የማጽዳትና የመንከባከብ ግዴታ አለበት

## ክፍል ዘጠኝ

## የደህንነት መጠበቂያ ስለመጠቀም፣ ግንዛቤ ስለመስጠት

%፱. የተከለከሉ ድርጊቶች፡-

ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅትና የኤጀንሲው ባለሙያ ኤጀንሲው በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ዩኒፎርምና የደህንነት መጠበቂያ ግብዓቶችን ሳይጠቀም አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

&. የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩. ሁሉም የመንግሥትና የግል ትምህርት ተቋማት ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የአካባቢ ጥበቃና ጸዳት ክበብ የማቋቋም፣ ስለአካባቢ ጽዳት ለተማሪዎቹ ግንዛቤ የመፍጠርና የማስተማር እና ተማሪዎች የትምህርት ቤት አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ለተለያዩ አገልግሎቶች በራሪ ወረቀቶችን የሚያሠራጭ ማንኛውም ድርጅት /ግለሰብ/ ተቋም በበራሪ ወረቀቱ ምክንያት ለሚከሰት የከተማ ጽዳት መጓደል ኃላፊነት አለበት፣

## ክፍል አስር

## በደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ላይ ስለሚሰማሩ ደርጅቶች ግዴታዎች

፩. የተጣሉ ግዴታዎች፡-

፩.. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በተሰጠው የመሥሪያ ክልል ውስጥ የተረከበውን የመስሪያ አካባቢ ለጤናና ለአካባቢ ችግር መንስኤ በማይሆን ሁኔታ ተገቢውን ጥንቃቄ በመውሰድ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፪. ከተለመደው የዕለት ተዕለት ስራዎች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ ቆሻሻ በሚመነጭባቸው የበዓልና የልዩ ዝግጅቶች ወቅት የጽዳት አገልግሎት ሰጭው ድርጅት በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ፈጣን አገልግሎት የመስጠጥ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ድርጅት ከደንበኛው ጋር ውል በገባው መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## የኤጀንሲውና የሌሎች ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

፩. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት፡-

በሌሎች ህጎች ለኤጀንሲው የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ለመስጠት ለተሰማሩ ድርጅቶች የስራና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፪. በመንግስት ተሸከርካሪ የሚጓጓዘውን ደረቅ ቆሻሻ አዲስ መመሪያ በማዘጋጀት በጽዳት የሽርክና ማህበራት እንዲጓጓዝ ያደርጋል፡፡

፫. የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን አገልግሎት አሰጣጥ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፬. የጽዳት አገልግሎቱን ለማሻሻል እንዲቻል ልዩ ልዩ የማበረታቻና የቁጥጥር ስርዓት ይፈጥራል፡፡

፭. ይህንን ደንብ ለማስፈፀምና አገልግሎቱን ለማሻሻል አግባብ ካለው አካል ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

፮, ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የቆሻሻ አያያዝ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብና ደንቡን ለማስፈጸም የሚወጡ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ጥሶ ሲገኝ የተሰጠው ፈቃድ ይሠረዛል ወይም ከስራውም ያግዳል ::

፯. የከተማውን የመንገድ ጽዳት ለማዘመንና ለማሻሽል ኤጀንሲው የመንገድ ጽዳትን በሽርክና ለተደራጁ ማህበራት በውክልና ያሰራል፡፡

፰. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ድርጅቶችን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡ እንዲሁም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ሊያዘምኑ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት ለይቶ ይተገብራል፡፡

፫, የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት፡-

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት በከተማው አስተዳደር ክልል የሚፈፀም የአካባቢ ጽዳት መጓደልን፣ ማንኛውንም ህገወጥ ቆሻሻ መጣልንና ዝውውርን፣ በመንገድ ዳር የተተከሉ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎችን ጉዳትና ስርቆትን ከፖሊስ ጋራ በመሆን፣ ይከላከላል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ሥልጣን ላለው አካል ያስተላልፋል፡፡

፬. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፡-

፩. የክፍለ ከተማው ህብረተሰብ በቋሚነት አካባቢውን እንዲያፀዳ በንቅናቄው እንዲሳተፍ ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

፪. በክፍለ ከተማው ለሚገኙ ወረዳዎች የጽዳት የስራ እቅድ ያቅዳል፣ ያከፋፍላል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ቆጣጠራል፡፡

፫. በክፍለ ከተማው የሚሰሩ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይመራል፡፡

፬. በክፍለ ከተማው ለሚከሰት የጽዳት መጓደል ኃላፊነት አለበት፡፡

&፮. የወረዳ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት፡-

የወረዳ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት፡-

፩. የወረዳው ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ጽዳት እንዲጠብቁ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. ህገ-ወጥ ደረቅ ቆሻሻ የሚጥሉትን፣ ከተማ የሚያቆሽሹትን፣ ንብረት የሚያበላሹና የሚሰርቁትን፣ አጠቃላይ ይህንን ደንብ የሚተላለፉትን ድርጅቶች/ግለሰቦች ይቆጣጠራል በደንቡ መሰረምት እዲቀጡ ያደርጋል፡፡

፫. በወረዳው የሚንቀሳቀሱ የደረቅ ቆሻሻ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን ቆጣጠራል፣ ይደግፋል፡፡

፬. በወረዳው የሚገኙ ጊዚያዊ ደረቅ ቆሻሻ ማቆያ ቦታዎችን በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት መስጠጣቸውን ይከታተላል፣ ችግር ሲኖር በደንቡና መመሪያው መሰረት ዕርምት ዕርምጃ ይወስዳል፡፡

፭. በወረዳው የሚኖረው ነዋሪ ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ሳያዝረከርክ እንዲያዝ፣ በዓይነት እንዲለይ ይከታተላል፣ ግንዛቤ ፈጥራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፮. በወረዳው የሚገኙ ነዋሪዎች በስታንዳርዱ መሰረት የጽዳት አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፯. በወረዳው ለሚከናዎነውን መንገድ ጽደት ይቆጣጠራል፣እንዲሁም በወረዳው ለሚከሰት የጽዳት ችግር ኃላፊት አለበት፡፡

፰. በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎቱን በአግባቡ የማይሰጡ የጽዳት ድርጅቶች በደንቡ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፱. በወረዳው ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ እንዲሁም የተለያዩ የእምነት ተቋማት ለምዕመኑ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ ይከታተላል፡፡

&፯, የሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባር፡-

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሌሎች የተጠቀሱ አካላት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፣

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በሁሉም የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአካባቢ ጥበቃና የጽዳት ክበብ እንዲቋቋምና ስለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ግንዛቤ እንዲፈጠር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪. የአውቶብስና የባቡር አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በትኬት ምክንያት ለሚከሰት የጽዳት ችግር መፍተሄ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፫. የተለያዩ የእምነት ተቋማት ለምዕመኑን ስለ አካባቢ ጽዳት ግንዛቤ መፍጠርና የእምነት ተቋሙን አካባቢ ጽዱና አረንጓዴ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፬. ወቅታዊና ልዩ ዝግጅቶች ማለት ፌስቲቫል፣ ባዛር፣ ኤግዚቢሽን፣ የመንገድ ላይ ሩጫ፣ ልዩ በዓላት ለምሳሌ መስቀል፣ የጥምቀት አረፋና መውሊድ ፕሮግራሞች የሚያዘጋጁ አካላት ኃላፊነት ወስደው አካባቢውን የማጸዳትና ጽዳቱን የሚያስጠብቅ ኮሚቴ በተለየ መንገድ ከክፍለ ከተማው ጽዳት ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት የማቋቋም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፭. የትራፊክ ፖሊስ በዚህ ደንብ ውስጥ ከተሽከርካሪ ጋር ተያይዞ ለሚደርሱ የጽዳት መጓደል የደንብ ጥሰትና በመንገድ ዳር የተቀመጡ የጥቃቅን የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ግብዓቶች በመኪና ግጭት ሲደርስባቸው ተከታትሎ ይይዛል፤ ይቆጣጠራል፤ ለህግም ያቀርባል፤ ደንብን ለማስፈፀም ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የመተባበርና ፈጣን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

፮. በሌሊት ክፍለ ጊዜ ተረኛ ሆነው የሚሰማሩ መደበኛ ፖሊሶች ጨለማን ተገን እድርገው ባልተፈቀደ ቦታ በህገወጥ መንገድ ደረቅ ቆሻሻ የሚጥሉትንና ከተማ የሚያቆሽሹትን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የመቆጣጠርና ለህግ እዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፯. የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ማለትም ትምህርት ቢሮ፤ ንግድ ቢሮ፣ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ ውበት መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ፣ ጤና ቢሮ፣ ባህልና ቱሪዝም፣ የመገናኛ ብዙሃን፤ ፖሊስ፤ ደንብ ማስከበር፤ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን፤ መንገዶች ባለስልጣን፤ ቤቶችና ኮንስትራክሽን፣ የከተማ ባቡርና አውቶብስ ድርጅት ወዘተ ለከተማዋ ጽዳት መሻሻል ከኤጀንሲው ጋር በቅንጅት መስራት አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አስራ ሁለት</u>

## <u>ስለ አገልግሎት ክፍያና ማበረታቻ</u>

፯. <u>ስለጽዳት አገልግሎት ክፍያ፡-</u>

፩. ማንኛውም ሰው ለሚያገኘው የጽዳት አገልግሎት አግባብ ባለው ህግ የተወሰነውን የጽዳት አገልግሎት ክፍያ የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

፪. የጽዳት አገልግሎት ማስፈጸሚያ እንዲሆን ከማንኛውም ቆሻሻን ከሚያመነጨው ህብረተሰብ ክፍልም ሆነ ከአገልግሎት ሰጭ ወይም ከአምራች ድርጅቶች ገቢ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

፫. አካባቢን በመበከል ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸውን ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች፤ የመጠጥና የምግብ አምራች ድርጅቶች፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ቴሌ፣ የትራንስፖርት ሰጪ ድርጅቶች ወዘተ) እና የተለያዩ የንግዱ ማህበረሰብ ፣ በበከሉት ልክ እንዲከፍሉ በጥናት ላይ የተመሰረተ የፋይንስ ደንብ በማዘጋጀት በደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ የባንክ አካውንት ገቢ በመሰብሰብ ለደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አጓጓዝና ፤ መልሶ መጠቀምና ኡደት፤ ማስወገድና ለአዳዲስ ቴክኖሎጂ ፈጠራና ማበረታቻ አገልግሎት እንዲውል ይደረጋል፡፡

&፰,. <u>ስለማበረታቻ</u>

፩. በጽዳት አገልግሎትና በመልሶ መጠቀምና ኡደት ሥራ ላይ ለሚሠማሩ የግልና የጽዳት ህብረት ሽርክና ድርጅቶች አግባብ ባለው ሕግና የሚመለከተው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለተወሰኑ ዓመታት የከተማው አስተዳደር ከሚሰበስባቸው የተለያዩ ታክሶች ምህረት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

፪, በጽዳት አገልግሎት የተሰማሩ ህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበር ኤጀንሲው በሚያወጣው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት በመንግሥት ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች በቅናሽ ወይም በተመጣጣኝ ክፍያ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋሉ፡፡

፫, በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና መቀነስ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦና ልዩ የፈጠራ ፕሮጀክቶች፣ ቴክኖሎጂዎች ወይም ልዩ ልዩ ተግባራትን ላከናወኑ ሰዎች ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማበረታቻ ሽልማትና እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

፬, ኤጀንሲው በተለይም በጽዳት አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ሥራቸውን ለማስፋፋትና አገልግሎታቸውን ለማጠናከር የሚያስችል በረጅም ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ ብድር እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው የአበዳሪ ድርጅቶችና ተቋማት ጋራ በመነጋገር ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡

፭. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሠብና ማጓጓዝ ሥራውን ለማገዝ ተደራጅተውና አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልተው ለተገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡ የጽዳት ተሽከርካሪዎች በረጅም ጊዜ ክፍያ እንዲሸጡላቸው ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

## <u>ክፍል አስራ ሶስት</u>

## <u>ስለአስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ</u>

፱, <u>አስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ፡-</u>

አግባብ ባለው የወንጀል ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ይዋሰኑበታል /እርምጃዎች ይወሰዱበታል፡-

፩. የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፡-

ሀ. በደንብ ማስከበር ደንብ መሠረት እንደጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ የማስነሳት እርምጃ ይወስዳል፤

ለ. በደንብ ማስከበር ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

፪. ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ የጽዳት አገልግሎት ሰጭ ድርጅት የቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ፣ መመሪያና ስታንዳርድ ከጣሰ ፈቃዱ ይሠረዛል፣ ወይም ይታገዳል፡፡

፫. ቆሻሻ ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ማንኛውም ሰው/ድርጅት የሚቀጣው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ያለአግባብ የጣለውን ደረቅ ቆሻሻ በራሱ ወጭ አንስቶ በህጋዊ ማስወገጃ ቦታ እንዲያስወግድ ይደረጋል፡፡

፴. ቅጣትን ስለማስፈፀም

ቅጣቱ የሚፈፀመው በደንብ ማስከበር ደንብ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

፴. ስለአቤቱታ አቀራረብ፡-

የአቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን በደንብ ማስከበር ደንብ በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡

## ክፍል አስራ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴. የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈፀም ረገድ በዚህ ደንብ ከተጠቀሱት አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፴፫. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈፀም ኤጀንሲው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፴፬. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ አያያዝ፤ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፮ ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

፪. ማንኛውም የአስተዳደሩ ደንብ፣ መመሪያ፣ የተለመደ አሠራር ወይም ሥነ-ሥርዓት የተፃፈም ቢሆን ሣይፃፍ በልማድ የሚሠራበት ሁሉ ይህን ደንብ የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

’፷. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከግንቦት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፺፬/፪ሺ፬ አጭር መግለጫ

**አጭር መግለጫ**

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸውና ድህነትን ከመቅረፍ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆናቸው ብድር ለመበደር የሚጋጥማቸውን የዋስትና ችግር መቅረፍ ለማስቻል በሚል የወጣ ህግ ነው፡፡

፩፥ አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፬. የተፈፃሚነት ወሰን

፭. መርሆዎች

፮. የፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ

፯.የፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

፰.የፈንዱ ምንጭ

፱.የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች

፲.መመልመያ መስፈርቶች

፲፩. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስልጣንና ተግባር

፲፪.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

፲፫.የአበዳሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

፲፬.የዋስትና ሽፋን አፈፃፀም

፲፭.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፲፭.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፲፮.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፲፯.የመተባበር ግዴታ

፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

# <u>የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፬</u>

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸውና ድህነትን ከመቅረፍ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆናቸው ብድር ለመበደር የሚጋጥማቸውን የዋስትና ችግር መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

**፩÷ <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፵፬/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ከንቲባ"** ማለት የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ነው፤

፬. **"የብድር ዋስትና ፈንድ"** ማለት በጥቃቅን ወይም አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ የተወሰደ ብድር ባይከፈል ለአበዳሪ ሊከፈል የሚችል የተያዘ ወይም ተቀማጭ ገንዘብ ነው፤

፭. **"የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ባለቤቱን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ሀብቱ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር ፶ሺ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር ፻ሺ ያልበለጠ ኢንተርኘራይዝ ነው፤

፮. **"አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ"** ማለት ባለቤቱን ጨምሮ እስ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ሀብቱ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ ከብር ፶ሺ፩ እስከ ፭፻ሺ ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር ፻ሺ፩ እስከ ፩ሚሊዮን፭፻ሺ ያልበለጠ ኢንተርኘራይዝ ነው፤

፯. **"የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋም"** ማለት አዲስ የብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማህበርን ጨምሮ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በዘርፉ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በፋይናንስ አገልግሎት ለመደገፍ ከብሄራዊ ባንክ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ አበዳሪ ተቋም ነው፡፡

**፫.ዓላማ**

፩. የብድር ዋስትና የሚሆን ንብረት ለሌላቸው ነገር ግን ብድር ቢያገኙ ሠርተው ብድራቸውን ከመመለስ አልፈው ራሳቸውን ማሳደግና ትርፋማ መሆን የሚችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብድር እንዲያገኙ ዋስትና ለመስጠት፤

፪. በኤክስፖርት ምርት ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች ለመተካትና በሌሎች ትኩረት በሚሰጣቸው የስራ ዘርፎች የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለመበደር የሚጋጥማቸውን የዋስትና ችግር በመቅረፍ በዚህ ዘርፍ የሚሰማሩትን ለማበረታታት፤

፫. የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማገዝ ፡፡

፬. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስራዎች ላይ ተሰማርተው የብድር ዋስትና ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፭. **መርሆዎች**

፩.የብድር ዋስትና ፈንድ የብድር ዋስትናን ለማጠናከር በድጋፍ ማዕቀፍ ውስጥ የተካተተና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ፣ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና ከተማው አስተዳደር የሚቋቋምና የሚተዳደር ፈንድ ነው፤

፪.የዋስትና ፈንድ አጠቃቀም በብድር ስርዓቱ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የስራ ዘርፎች ብቻ ይሆናል፤

፫.የዋስትና ፈንዱ ዋስትና ማቅረብ ለማይችሉና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት መደብር ወይም በሌሎች የዋስትና አማራጮች መስተናገድ ያልቻሉት ብቻ የሚስተናገዱበት የድጋፍ ስርዓት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## አወቃቀር፣ ኃላፊነትና ተግባር

፮. **የፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ**

፩.የከተማ አስተዳደሩ የብድር ዋስትና ፈንድ ከአስተዳደሩ አካላት ተውጣጥቶ በተደራጀ የአስተዳደር ኮሚቴ የሚመራ ይሆናል፤

፪.የአስተዳደር ኮሚቴ ተጠሪነት ለከንቲባው ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ……..…..…ሰብሳቢ፣

ለ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ኃላፊ ……አባል፣

ሐ) የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ…………………..…….አባል፣

መ) የአዲስ ብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማህበር ተቋም ማኔጂንግ ዳይሬክተር…....………...አባል፣

ሠ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ዳይሬክተር…………...…..አባል፣

ረ) ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚመደብ የዋስትና ፈንድ አስተባባሪ...አባልና ፀሐፊ፡፡

**፯.የፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

የአስተዳደር ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የብድር ዋስትና ፈንድ ምንጮችን በማፈላለግ የዋስትና ፈንዱን ያቋቁማል፣ ፈንዱን ከልዩ ልዩ ምንጮች በሚያገኘው ገቢ ያጠናክራል፤

፪. የዋስትና ፈንዱን በሚመለከት ሪፖርቶችን ያዳምጣል፤

፫. በዋስትና ፈንዱ አፈፃፀም ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፰.የፈንዱ ምንጭ**

ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች ይሰበሰባል፡-

፩. ፸ በመቶ ከከተማው አስተዳደር ከሚመደብ በጀት፣

፪. ፳ በመቶ በዘርፉ ከተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚደረግ ቁጠባ፣

፫. ፲ በመቶ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ከሚደረግ መዋጮ ፣ እና

፬. ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች ይሆናል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ስለዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎችና መመልመያ መስፈርት**

**፱.የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች**

የሚከተሉት የዋስትና ፈንድ ተጠቃሚዎች ናቸው፡-

፩. ለኤክስፖርትና ለገበያ የሚያመርቱ ኢንተርፕራይዞች፤

፪. ከውጭ ሀገር የሚገቡትን በሚተኩ ምርቶችና በኮንስትራክሽን ስራ ለተሰማሩ፤

፫. በክላስተር ማዕከላት በመሰባሰብ በሞዴልነት ተመርጠው የሚያመርቱና አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ፤

፬. የራሳቸው ቁጠባና የመልካም ተበዳሪነት ታሪክ ያላቸው ሆነው በማምረትና በኤክስፖርት ምርት ላይ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሲሆን እንደተጠቃሚው ብዛት በሌሎች የተመረጡ የስራ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችም የዋስትና ፈንዱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

**፲.መመልመያ መስፈርቶች**

፩.ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለማግኘትና ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ፳ በመቶ ቢያንስ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በየወሩ እኩል ክፍያ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

ለ) የኤክስፖርት ምርት ከሚያመርቱና በእድገት ተኮር የስራ ዘርፍ ከተሰማሩ ውጭ ያሉ ጀማሪ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ለመበደር ያቀዱትን ፳፭ በመቶ ቢያንስ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በየወሩ እኩል ክፍያ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡

**፪.ታዳጊ ኢንተርፕራይዞች**

ሀ) ኤክስፖርት ምርት የሚያመርቱና በእድገት ተኮር ዘርፍ የሚሰማሩ ታዳጊ ኢንተርፕራይዞች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ለመበደር ያቀዱትን ፲፭ በመቶ ቢያንስ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በየወሩ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

ለ) በስትራቴጂው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የሥራ ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ኢንተርፕራዞች ብድር ለማግኘትና ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ፭ በመቶ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

ሐ) የዕድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት በማስፈፀሚያ መመሪያው መሠረት የያዙ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**፫.የበቃ ኢንተርፕራዝ**

ሀ) ኤክስፖርት ምርት የሚያመርቱና በእድገት ተኮር ዘርፍ የሚሰማሩ የበቁ ኢንተርፕራይዞች ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ለመበደር ያቀዱትን ፲፭ በመቶ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

ለ) በስትራቴጂው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የሥራ ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለማግኘትና ለብድር ዋስትና ሽፋን ብቁ ለመሆን ከሚበደሩት የብድር መጠን ፭ በመቶ አስቀድመው መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

ሐ) የዕድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት በማስፈፀሚያ መመሪያው መሠረት የያዙ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት
## ስልጣንና ተግባር

**፲፩. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስልጣንና ተግባር**

ሀ) ለዋስትና ፈንድ የሚሆን የገንዘብ ምንጭ ያፈላልጋል፤ በከተማው የሚንቀሳቀሱ ግብረሰናይ ድርጅቶች እንዲሳተፉ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

ለ) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ቢሮ በሚቀርበው የዋስትና ፈንድ የበጀት ጥያቄ መሠረት በጀት ይመድባል፣ በዋስትና ፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ውሳኔ ሲሰጥም አግባብነት ወዳለው አነስተኛ ፋይናንስ ተቋሙ የባንክ ሂሳብ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

ሐ) የዋስትና ፈንድ አስተዳደር መረጃ ያደራጃል፤ ወቅታዊ ሪፖርት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ያዘጋጃል ሪፖርት ያደርጋል፤

መ) የዋስትና ፈንድን አፈፃፀም ኦዲት ያደርጋል፤ የውጤት ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤

ሠ) ሌሎች ከፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፪.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት**

፩.ለኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጣል፤

፪.የዋስትና ፈንድ የሚያስፈልጋቸውን ኢንተርፕራይዞች ይለያል፤ ለአበዳሪ ተቋሙ ያስተላልፋል፤

፫.ብድር ሳይመልሱ በመቅረታቸው ዋስትና ፈንዱ የሚተካላቸውን ኢንተርፕራይዞች ከአበዳሪ ተቋሙ ጋር በመቀናጀት ይለያል፤ ለፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

**፲፫.የአበዳሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት**

፩. የተበዳሪዎችን የንግድ እቅድ በመገምገም አዋጭነቱን ያረጋግጣል፤

፪. የተበዳሪዎችን የብድር አጠቃቀምና የፕሮጀክት አፈፃፀም ይከታተላል፤

፫. በስድስት ወር አንድ ጊዜ ስለፈንዱ አጠቃቀምና አፈፃፀም ለፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፤

፬. የሚጠየቀው የዋስትና ክፍያ ጥያቄ ወቅቱን የጠበቀና በስምምነቱ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፤

፭. ከዋስትና ፈንድ በቀጥታ ላልተመለሰ የብድር ገንዘብ እንዲተካ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት በሚቻለው መንገድ ሁሉ አበዳሪው ብድሩን እንዲመልስ ጥረት ያደርጋል፡፡ ይህንንም የሚያረጋግጥ የማስረጃ ሪፖርት ለፈንድ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

፮.ከብድር ጋር በተያያዘ ዋስትና ሰጭው ወይም የፈንድ አስፈፃሚ ኮሚቴ በየጊዜው የሚሰጣቸውን መመሪያዎች ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፡፡

**፲፬.የዋስትና ሽፋን አፈፃፀም**

፩. ከዋስትና መያዣ ወይም ከብድር ዋስትና ፈንድ የሚተካ ብድር የመጨረሻው አማራጭ ሆኖ ከብድር ዋስትና ፈንድ እንዲተካ የሚደረገው ብድር በየስድስት ወሩ የሚከናወን ይሆናል፤

፪. በንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዋስትና ፈንድ የተሸፈነ የብድር ገንዘብ ክትትልና የማስመለሱ ተግባር በአበዳሪ ተቋማቱም ሆነ በሚመለከታቸው አካላት የሚቀጥል ይሆናል፤

፫. የሚመለሰው ገንዘብ በቀጣይነት በተዘዋዋሪ ፈንድነት የሚያገለግል ወይም የሀብት ማጠናከሪያ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**፲፭.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረም፡፡

**፲፮.መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

በዚህ ደንብ ዋስትና የፈንዱ አስተዳደር ኮሚቴ ለዚህ ደንብ አፈፃጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፯.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ የካቲት ፳፪ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ፵፮/፪ሺ፬ አጭር መግለጫ

የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በአሁኑ ሰአት በግብይት ስርአቱ ላይ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ የተሻለ ተደራሽነት ያላቸው በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ሱቆችን ወደ ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ሀብትና ንብረት ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡፡

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. ተፈፃሚነት ወሰን

፬.ንብረትን ስለማስተላለፍ

፪. ስለ ንብረት ርክክብ

፭. የሠራተኛ ሁኔታ

፮. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

፯. የባለአደራ ቦርድ ግዴታዎች

፰. የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

፱. ስለ ቁጥጥርና ሂሣብ አያያዝ

፲. ስለ ቅጣት

፲፩. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

፲፪. ከባለ አደራ ቦርድ ጋር ስለተደረጉ ውሎች

፲፫. የመተባበር ግዴታ

፲፬. ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጐች

፲፭. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

# <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ፵፮/፪ሺ፬</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ከቆሙለት አላማ አንፃር ተገቢውን ህዝባዊ አገልግሎት ያልሰጡ በመሆኑ፤

እነዚህ ተቋማት በከተማው ውስጥ የታየውን የዋጋ መናር በማረጋጋት ህዝቡን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ የነበራቸው ሚና ውስን በመሆኑ እና የከተማው የልማት እቅድ ማሳካት ባለመቻላቸው በዚህም ምክንያት ህዝቡም በነዚህ ተቋማት ላይ የባለቤትነት ስሜት ያጣና ተደጋጋሚ ጥያቄ ለከተማዉ አስተዳደር ያቀረበ በመሆኑ፤

እነዚህ ተቋማት ህዝቡን የሚጠቅሙ የልማት ተቋማት ከመሆን ይልቅ የግለሰቦች መጠቀሚያ በመሆናቸው ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ቢተላለፉ የተሻለ በመሆኑ፤

የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በአሁኑ ሰአት በግብይት ስርአቱ ላይ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ የተሻለ ተደራሽነት ያላቸው በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ሱቆችን ወደ ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ሀብትና ንብረት ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭፫/፩(ረ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ቁጥር ፵፮/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቢሮ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

፬. **"የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበር"** ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ነው፤

፰. **"የሕዝብ ሱቅ እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት"** ማለት በከተማው ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች በተለምዶ የቀበሌ ሱቅና መዝናኛ ማዕከል በመባል የሚታወቁ ለህዝቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ያሉና የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችና ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን፣ የሕዝብ ሱቆችን፣ ወፍጮ ቤቶችን፣ ሥጋ ቤቶችን፣ መጋዘኖች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የተለያዩ የመገልገያ መሣሪያዎች፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የሚከራዩ ቤቶች እና ሌሎችም ገቢ የሚያስገኙና የመዝናኛ ተቋማት ንብረቶችን የያዘ ወይንም ባለቤት የሆነ ተቋም ማለት ነው፤

፱. **"ባለአደራ ቦርድ"** ማለት የሕዝብ ሱቅና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋምን ለማስተዳደርና ለመምራት በህዝብ የተመረጠ ወይም የተወከለ አካል ነው፤

፲. **"ንብረት"** ማለት የሕዝብ ሱቅ እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ ገና ያልተቀበሉዋቸው ገቢዎች፣ በጥሬና በባንክ ሂሳብ ያለ ገንዘብ፣ ግዙፍነት የሌላቸው ንብረቶችን፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎች እና ሌሎች ገቢ መሆን ያለባቸው ሂሳቦችን ይጨምራል፤

፲፩. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **<u>ተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ውስጥ በሚገኙ ሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ንብረት፣ሰራተኛና የተለያዩ አካላት ግዴታ</u>

፬.<u>ንብረትን ስለማስተላለፍ</u>

፩. በከተማው አስተዳደር ውስጥ በየወረዳው የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ማንኛውም ንብረት የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት መነሻ ካፒታል ሆነው በዚህ ደንብ ተላልፈዋል፡፡

፭. <u>ስለ ንብረት ርክክብ</u>

ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተመለከተው መሠረት የንብረት ባለቤትነት እንዲተ ላለፍና ርክክብ እንዲፈፀም ተገቢዉን ድጋፍ ያደርጋል፤ ለዚህ አላማም፡-

ሀ. ሀብትና ዕዳን በተመለከተ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት የሂሣብ አጣሪና የንብረት ቆጣሪ ይወከላል ወይም ይመደባል፤

ለ. የንብረት ማስተላለፉን ሽግግር ለማገዝ ከ፯ እስከ ፱ አባላት ያሉት ኮሚቴ በማእከልና በወረዳ ደረጃ ያቋቁማል፤

ሐ. የሕዝብ ሱቅና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋሙ ንብረት ለጉዳት የተጋለጠ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተቋሙን በከፊል ወይንም በሙሉ ሊያሽግ እና ቀጣይ የርክክብ ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፤

፫. በዚህ ደንብ መሠረት የሕዝብ ሱቅ እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋምን ያስተዳደር የነበረ ማንኛውም ሰው ወይም ባለአደራ ቦርድ ተረካቢ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበር ሲጠይቅ የተቋማቱን ማንኛውም ንብረትና ሠነዶች የማስረከብ ግዴታ አለበት፤

፬. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ንብረት እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ወይም ባለአደራ ቦርድ ሲኖር ቢሮው የወረዳው ህዝብ ተወካዮች ባሉበት የንብረት ቆጠራ በማካሄድ ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር አመራር ያስረክባል፤

፭. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፫ መሰረት ግዴታውን እንዲፈፅም የተጠየቀ ሰው ወይም ባለአደራ ቦርድ በተጠየቀበት ሰአት ባለማስረከቡ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፤

፮. የመሬት ይዞታን አስመልክቶ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፬ እና ማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ይሆናሉ፤

፯. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ መሰረት ወረዳዎች ሲዋቀሩ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋሞች ከሚገኙበት ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ የተቀላቀሉ ነዋሪዎች እነዚህ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋሞች በዚህ ደንብ ከተላለፉበት የሸማች የህብረት ስራ ማህበር አገልግሎትና የአባልነት መብት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## ፭. <u>የሠራተኛ ሁኔታ</u>

የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ሰራተኛ ጉዳይን አስመልክቶ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## ፮. <u>የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ መሰረት የተደነገጉ ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ወደ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የመተላለፉን የሽግግር ሂደት ብቻ ለማስፈጸም ሲባል፡-

፩. በየወረዳው የሚገኙ ሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ማንኛውም ንብረት ይመዘግባል፤

፪. ይህን ደንብ በተሟላ መልኩ ለማስፈፀም ጥናት ያካሂዳል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት ማንኛውም ንብረት የተላለፈለት የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበር የተላለፈለትን ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚሰጥ መንገድ ማስተዳደሩን ያረጋግጣል፣ የእርምት እርማጃም ይወስዳል፤

፬. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሰረት ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት የባለአደራ ቦርዱ በማንኛውም ባንክ ወይም የገንዘብ ተቋም የተቀመጠ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ገንዘብ ከገቢ በስተቀር ወጪ እንዳይደረግ ሊያዝ ይችላል፤

፭. ሥራውን ለማቀላጠፍ ለሌሎች የባለ ድርሻ አካላት ውክልና መስጠት ወይም የመግባቢያ ሰነድ ሊፈርም ይችላል፤

፮. ህብረተሰቡ ከሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት ተጠቃሚ እንዲሆን የሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶችን ድጋፎችን ያስተባብራል፤

፯. በአንድ ወረዳ ውስጥ ከአንድ በላይ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በሚኖሩበት ጊዜ የህዝቡን ፍላጎትና የአባላት ቁጥርን ማእከል በማድረግ የህዝብ ሱቆችንና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ንብረት የሚረከበውን የሸማች ማህበር ይወስናል፤

፰. የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ኅብረተሰቡ ስለሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸውን ግንዛቤ ያሳድጋል፡፡

## ፯. የባለአደራ ቦርድ ግዴታዎች

ማንኛዉም የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት የባለአደራ ቦርድ፡-

፩. የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ዕዳና ብድር ካለባቸው ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ ለቢሮው ወይንም ቢሮው ለሚወከወለው አካል አረካካቢነት ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር ያስረክባል፤

፪. በሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ውስጥ የተቀጠሩ ቅጥር ሠራተኞች ማስረጃን ቢሮው በሚያዘጋጀው የመመዝገቢያ ዝርዝር መሠረት መዝግቦ ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ያስረክባል፤

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሰረት የንብረት ማስተላለፍ ከመፈፀሙ በፊት የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋሙን ንብረትን አስመልክቶ ቢሮው በሚወክለው አካል ኦዲት ያስደርጋል፡፡

## ፰. የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የተላለፈላቸውን ንብረት ይረከባሉ ያስተዳድራሉ፤

፪. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት ከመተላለፉ በፊት ስለነባር ንብረታቸው አስፈላጊውን ኦዲት ያደርጋሉ፤

፫. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረቶች ሳይባክኑና ሳይበላሹ የሚተላለፉበትን መንገድ ይቀይሳሉ፤

፬. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረትና ሀብት ለወረዳዉ ነዋሪ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ አገልግሎት ላይ ያዉላሉ፤

፭. ተቋማቱ የሚገኑባቸዉ ወረዳዎች ነዋሪ በሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

**፱. ስለ ቁጥጥርና ሂሣብ አያያዝ**

የኅብረት ሥራ ማህበራትና ሌላ የህግ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት፡-

፩.ለህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረት መተላለፍ ቢሮው የሚያዘጋጀውን የሂሳብ አሰራር ስነ ስርአት ይከተላሉ፤

፪.ከቀድሞ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ወደ ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት የተላለፈ ካፒታል፣ ለአባላት ከሚሸጥ ዕጣ የሚገኝ የመንቀሳቀሻ ካፒታልና ማህበሩ ከሚያገኘው ገቢ እየተቀነሰ የሚቀመጥ ልዩ የመጠባበቂያ ካፒታል ይይዛል፤

፫.ከተቋማት የሚተላለፍ ንብረትና የሰው ኃይል አስተዳዳርን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሰራር ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲. ስለ ቅጣት**

፩. ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ በሚከናወኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ እንቅፋት የሚፈጥር ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለዉ የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛዉ የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ከሆነ በአዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ ድንጋጌ መሠረት ከአባልነት እስከ ማሰናበት ሊወስንበት ይችላል፡፡

**፲፩. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ንብረት ለተላለፉላቸው የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ተላልፈዋል፡፡

**፲፪. ከባለ አደራ ቦርድ ጋር ስለተደረጉ ውሎች**

የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን አስመልክቶ ከባለ አደራ ቦርድ ጋር ውል የተዋዋለ ሰው ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ የተቋሙ ንብረት ወደተላለፈለት የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር ዘንድ በመቅረብ ውሉን ማደስ አለበት፤ ለዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

**፲፫. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፬. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጐች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ፡፡

**፲፭. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ጀምሮ ባሉ ስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ብቻ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው  የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ፶፮/፪ሺ፬ አጭር መግለጫ

አጭር መግለጫ

እነዚህ ተቋማት ህዝቡን የሚጠቅሙ የልማት ተቋማት ከመሆን ይልቅ የግለሰቦች መጠቀሚያ በመሆናቸው ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ለማስተላለፍ እና የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በአሁኑ ሰአት በግብይት ስርአቱ ላይ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ የተሻለ ተደራሽነት ያላቸው በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ውስጥ የሚገኙ  የህዝብ ሱቆችን ወደ ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ሀብትና ንብረት ማስተላለፍ የወጣ ህግ ነው፡፡

<u>**ማውጫ**</u>

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. ተፈፃሚነት ወሰን

፬.ንብረትን ስለማስተላለፍ

፭.  የሠራተኛ ሁኔታ

፮. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

፯. የባለአደራ ቦርድ ግዴታዎች

፱. ስለ ቁጥጥርና ሂሣብ አያያዝ

፲. ስለ ቅጣት

፲፩. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

፲፪. ከባለ አደራ ቦርድ ጋር ስለተደረጉ ውሎች

፲፫. የመተባበር ግዴታ

፲፬. ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች

፲፭. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

## <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ፵፮/፪ሺ፬</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ከቀሙለት አላማ አንፃር ተገቢውን ህዝባዊ አገልግሎት ያልሰጡ በመሆኑ፤

እነዚህ ተቋማት በከተማው ውስጥ የታየውን የዋጋ መናር በማረጋጋት ህዝቡን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ የነበራቸው ሚና ውስን በመሆኑ እና የከተማው የልማት እቅድ ማሳካት ባለመቻላቸው በዚህም ምክንያት ህዝቡም በነዚህ ተቋማት ላይ የባለቤትነት ስሜት ያጣና ተደጋጋሚ ጥያቄ ለከተማዉ አስተዳደር ያቀረበ በመሆኑ፤

እነዚህ ተቋማት ህዝቡን የሚጠቅሙ የልማት ተቋማት ከመሆን ይልቅ የግለሰቦች መጠቀሚያ በመሆናቸው ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ቢተላለፉ የተሻለ በመሆኑ፤

የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በአሁኑ ሰአት በግብይት ስርአቱ ላይ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ የተሻለ ተደራሽነት ያላቸው በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ሱቆችን ወደ ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ሀብትና ንብረት ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩(ረ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚገኙ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ወደ ሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ለማስተላለፍ የወጣ ደንብ ቁጥር ፵፮/፪ሺ.፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቢሮ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

፬. **"የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበር"** ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ማህበር ነው፤

፭. **"የሕዝብ ሱቅ እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት"** ማለት በከተማው ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች በተለምዶ የቀበሌ ሱቅና መዝናኛ ማዕከል በመባል የሚታወቁ ለህዝቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ያሉና የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችና ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን፣ የሕዝብ ሱቆችን፣ ወፍጮ ቤቶችን፣ ሥጋ ቤቶችን፣ መጋዘኖች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የተለያዩ የመገልገያ መሣሪያዎች፣ የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የሚከራዩ ቤቶች እና ሌሎችም ገቢ የሚያስገኙና የመዝናኛ ተቋማት ንብረቶችን የያዘ ወይንም ባለቤት የሆነ ተቋም ማለት ነው፤

፮. **"ባለአደራ ቦርድ"** ማለት የሕዝብ ሱቅና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋምን ለማስተዳደርና ለመምራት በህዝብ የተመረጠ ወይም የተወከለ አካል ነው፤

፯.**"ንብረት"** ማለት የሕዝብ ሱቅ እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ ገና ያልተቀበሉዋቸው ገቢዎች፣ በጥሬና በባንክ ሂሳብ ያለ ገንዘብ፣ ግዙፍነት የሌላቸው ንብረቶችን፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎች እና ሌሎች ገቢ መሆን ያለባቸው ሂሳቦችን ይጨምራል፤

፰. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ውስጥ በሚገኙ ሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ንብረት፣ሰራተኛና የተለያዩ አካላት ግዴታ

፬.**ንብረትን ስለማስተላለፍ**

፩. በከተማው አስተዳደር ውስጥ በየወረዳው የሚገኙ የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ማንኛውም ንብረት የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት መነሻ ካፒታል ሆነው በዚህ ደንብ ተላልፈዋል፡፡

፪. ስለ ንብረት ርክክብ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተመለከተው መሠረት የንብረት ባለቤትነት እንዲተ ላለፍና ርክክብ እንዲፈፀም ተገቢዉን ድጋፍ ያደርጋል፤ ለዚህ አላማም፡-

፭. **የሠራተኛ ሁኔታ**

የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ሰራተኛ ጉዳይን አስመልክቶ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

፮. **የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፩ መሰረት የተደነገጉ ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ የህዝብ ሱቆችና

ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ወደ ሸማቾች ኅብረት ሥራ ማህበራት የመተላለፉን የሽግግር ሂደት ብቻ ለማስፈጸም ሲባል፡-

፩. በየወረዳው የሚገኙ ሕዝብ ሱቆችንና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ማንኛውም ንብረት ይመዘግባል፤

፪. ይህን ደንብ በተሟላ መልኩ ለማስፈፀም ጥናት ያካሂዳል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት ማንኛውም ንብረት የተላለፈለት የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበር የተላለፈለትን ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚሰጥ መንገድ ማስተዳደሩን ያረጋግጣል፣ የእርምት እርማጃም ይወስዳል፤

፬. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሰረት ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት የባለአደራ ቦርዱ በማንኛውም ባንክ ወይም የገንዘብ ተቋም የተቀመጠ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ገንዘብ ከገቢ በስተቀር ወጪ እንዳይደረግ ሊያዝ ይችላል፤

፭. ሥራውን ለማቀላጠፍ ለሌሎች የባለ ድርሻ አካላት ውክልና መስጠት ወይም የመግባቢያ ሰነድ ሊፈርም ይችላል፤

፮. ህብረተሰቡ ከሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት ተጠቃሚ እንዲሆን የሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶችን ድጋፎችን ያስተባብራል፤

፯. በአንድ ወረዳ ውስጥ ከአንድ በላይ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በሚኖሩበት ጊዜ የህዝቡን ፍላጎትና የአባላት ቁጥርን ማእከል በማድረግ የህዝብ ሱቆችንና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ንብረት የሚረከበውን የሸማች ማህበር ይወስናል፤

፰. የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ኅብረተሰቡ ስለሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸውን ግንዛቤ ያሳድጋል፡፡

## ፯. <u>የባለአደራ ቦርድ ግዴታዎች</u>

ማንኛዉም የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት የባለአደራ ቦርድ፡-

፩. የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ዕዳና ብድር ካለባቸው ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ ለቢሮው ወይንም ቢሮው ለሚወከወለው አካል አረካካቢነት ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር ያስረክባል፤

፪. በሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ውስጥ የተቀጠሩ ቅጥር ሠራተኞች ማስረጃን ቢሮው በሚያዘጋጀው የመመዝገቢያ ዝርዝር መሠረት መዝግቦ ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት ያስረክባል፤

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሰረት የንብረት ማስተላለፍ ከመፈፀሙ በፊት የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋሙን ንብረትን አስመልክቶ ቢሮው በሚወክለው አካል ኦዲት ያስደርጋል፡፡

## ፰. <u>የሸማቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የተላለፈላቸውን ንብረት ይረከባሉ ያስተዳድራሉ፤

፪. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት ከመተላለፉ በፊት ስለነባር ንብረታቸው አስፈላጊውን ኦዲት ያደርጋሉ፤

፫. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረቶች ሳይባክኑና ሳይበላሹ የሚተላለፉበትን መንገድ ይቀይሳሉ፤

፬. የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረትና ሀብት ለወረዳዉ ነዋሪ ጥቅም በሚሰጥ መልኩ አገልግሎት ላይ ያዉላሉ፤

፭. ተቋማቱ የሚገኑባቸዉ ወረዳዎች ነዋሪ በሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

## ፱. <u>ስለ ቁጥጥርና ሂሣብ አያያዝ</u>

የኀብረት ሥራ ማህበራትና ሌላ የህግ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት፡-

፩.ለህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ንብረት መተላለፍ ቢሮው የሚያዘጋጀውን የሂሳብ አሰራር ስነ ስርአት ይከተላሉ፤

፪.ከቀድሞ የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት ወደ ሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት የተላለፈ ካፒታል፣ ለአባላት ከሚሸጥ ዕጣ የሚገኝ የመንቀሳቀሻ ካፒታልና ማህበሩ ከሚያገኘው ገቢ እየተቀነሰ የሚቀመጥ ልዩ የመጠባበቂያ ካፒታል ይይዛል፤

፫.ከተቋማት የሚተላለፍ ንብረትና የሰው ኃይል አስተዳዳርን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሰራር ይኖራቸዋል፡፡

# <u>ክፍል ሶስት</u>

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## ፲. <u>ስለ ቅጣት</u>

፩. ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ በሚከናወኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ እንቅፋት የሚፈጥር ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለዉ የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛዉ የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ከሆነ በአዋጅ ቁጥር <u>፩፻፵፯/፲፱፻፺፩</u> ድንጋጌ መሠረት ከአባልነት እስከ ማሰናበት ሊወስንበት ይችላል፡፡

## ፲፩. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

የሕዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ንብረት ለተላለፉላቸው የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ተላልፈዋል፡፡

## ፲፪. <u>ከባለ አደራ ቦርድ ጋር ስለተደረጉ ውሎች</u>

የህዝብ ሱቆችና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተቋማትን አስመልክቶ ከባለ አደራ ቦርድ ጋር ውል የተዋዋለ ሰው ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ወር ድረስ የተቋሙ ንብረት ወደተላለፈለት የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበር ዘንድ በመቅረብ ውሉን ማደስ አለበት፤ ለዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፲፫. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፬. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች</u>

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ፡፡

## ፲፭. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፩ ጀምሮ ባሉ ስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ብቻ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮርያ ዘማቾች መታሰቢያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞች የልህቀት ማዕከል ለማቋቋም፤ አደረጃጀትና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፻፩/፪ሺ፲

የኮርያ ዘማቾች ልጆችና የልጅ ልጆች መለስተኛ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ተብሎ ሲጠራ የነበረው ተቋም ሙሉ ለሙሉ ተልዕኮውን ጨርሶ ለከተማ አስተዳደሩ በመተላለፉ የስልጠና ማዕከሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞችና ባለሞያዎችን ብቁና ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ በየጊዜው ለሚኖሩ የቴክኖሎጂ ለውጦች ቅርበት እንዲኖራቸው፣ የኢንዱስትሪው ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ አዋጭና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች ለመስራትና ለማሸጋገር የሚያስችል የልህቀት ማዕከል ማቋቋምና አደረጃጀቱንና አሰራሩን በሕግ መወሰን በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንኡስ አንቀጽ (፩) (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮና የማሰልጠኛ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፱/፪ሺ፱ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮርያ ዘማቾች መታሰቢያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞች የልህቀት ማዕከል ለማቋቋም፤ አደረጃጀትና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ ደንብቁጥር ፻፩ /፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "አዋጅ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፱/፪ሺ፱ ነው፡፡

፪."ቢሮ" ማለት የከተማ አስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ነው፡፡

፫. "ከተማ "ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው

፬.“የልህቀት ማዕከል” ማለት  በማንኛውም የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኝ የቴክኒክና ሙ.ያ አስልጣኝ ያለበትን የክህሎትና የቴክኖሎጂ አቅም  ክፍተት የሚሞላበትና የአሰልጣኞች ማረጋገጫ የሚሰጥበት ማዕከል ነው፡፡

፭. “አሰልጣኝ” ማለት በቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት  በማሰልጠን ስራ ላይ የተሰማራ ባለሙ.ያ ማለት ነው፡፡

፮.“ሰልጣኝ”“ ማለት ሙ.ያ ለመቅሰም፣ ዕውቀቱንና አመለካከቱን ለማጎልበት በማዕከሉ በሚሰጠው መርሃ ግብር ተመዝግቦ የሚሰለጥን ማንኛውም ሰው ማለት ነው፡፡

፯. “የኮርያ ዘማቾች” ማለት የኮርያ ሕዝብና መንግስት ለነፃነት ያደረገውን ተጋድሎ ለማገዝ በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ወደ ኮርያ የተላኩ ኢትዮጵያውያን ነው፡፡

፰. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ደንቡ በከተማ አሰተዳደሩ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር</u>

፬. <u>መቋቋም</u>

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮርያ ዘማቾች መታሰቢ.ያ  የቴክኒክና ሙ.ያ ትምርህርትና ስለጠና አሠልጣኞች የልህቀት ማዕከል (ከዚህ በኋላ «የልህቀት ማዕከል» እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የልህቀት ማዕከሉ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፡፡

፭.<u>ዓላማ</u>

የልህቀት ማዕከሉ  የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩.የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና አሠልጣኞች እና ቴክኒሺ.ያኖችን የክህሎት ክፍተት በመለየት የክህሎትና የቴክኖሎጂ  ብቃት በአጫጭር ስልጠና  ማሳደግ፤

፪.የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞችን የአሰልጣኝነት ብቃት ማረጋገጥ፤

፫. ውጤታማ የምርምር ስራዎችን በማካሄድ ውጤት ተኮር የስልጠና ሥርዓትን መደገፍ፤

፬. በከተማ አስተዳደሩ በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ምርታማነት ተወዳዳሪነት የሚያጎለብትበት  የቴክኖሎጂ ሽግግር መደገፍ፤

፭. ከኢንዱስትሪዎችና የምርምር ተቋማት ጋር በመተሳሰር ብቁ የሆነ የሰው ሃብትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችንማሳለጥ

፮. <u>አደረጃጀት</u>

የልህቀት ማዕከሉ፡-

፩. ተጠሪነቱ ለቢሮው የሆነ በቢሮው የሚሰየም  አንድ ዋና ዳይሬክተር እና፡ አንድ ምክትል ዳይሬክተር፤

፪. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል

፯. <u>የማዕከሉ ስልጣንና ተግባር</u>

የልህቀት ማዕከሉ  የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት በማደረግ የአሰለጣኞች ክፍተት   በየጊዜው በመለየት የስልጠና ካሪኩልም እና የስልጠና መሳሪያዎች በማዘጋጀት የክህሎት ስልጠና መስጠት፤

፪. አዳዲስ የሚቀጠሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞች ደረጃውን የጠበቀ በተግባር ላይ ያተኮረ የክህሎት  ስልጠና መስጠት፤

፫. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለተሰማሩ ቴክኒሺያኖች የንድፈ  ሐሳብና የተግባር ስልጠና መስጠት፤

፬. አዳዲሰ የክህሎትና የቴክኖሎጂ አሰራሮች መሰረት በማድረግ ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የሚያግዙ ስረዓተ ስልጠናዎች፡ የስልጠና ሰነዶችና ትክኖሎጂዎች በማዘጋጀት ለአሰልጣኞች እንዲሸጋገሩ ማድረግ፤

፭. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ከተሰማሩ የውጪ አገርና የአገር ውስጥ ተቋማት ጋር የትብብር ግኑኙነት በመመስረት አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ ማስፋት፤

፮. አግባብ የሆኑ የከተማ አስተዳደሩን ተቋማት በቴክኒክ ምክር ተገቢውን እገዛ ማድረግ፤

፯. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሠልጣኞች የአሰልጣኝነት የምስክር ወረቀት መስጠት፤

፰. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተለያዩ የዓውደ ጥናት  መድረኮችን ማመቻቸት፤

፱. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተካሄዱ ምርምሮችን አጠቃሎ ለተጠቃሚ ማሰራጨት፤

፲. አለማቀፍ የክህሎትና የቴክኖሎጂ ተሞክሮዎች በመለየት በተደራጀ መልኩ ለአሰልጣኞች ማስተላልፍ፤

፲፩.በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰሩ ቴክኖሎጂዎች የጥራት ግምገማ በማካሃድ ያላቸውን ክፍትቶች በመለየት ከፈተቶች የሚሞላ የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ስልጠና ፕሮግራም በመቅረጽ ስልጠና መስጠት፤

፲፪.በአገር አቀፍና ከተማ አቀፍ የሚሰጡ የክህሎትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ስልጥናዎች በተደራጅና ተቋማዊ በሆነ መልኩ ማሸጋገር፤

፲፫. የስራ ገበያውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ አዳዲስ የስራ ክፍሎችንና የስልጠና ዘርፎችን በማስጠናት ተጨማሪ ማስፋት፤

፲፬. የንብረት ባለቤት መሆን በማዕከሉ ስም የመከሰስና  የመክሰስ መብት ይኖረዋል፤

፲፭. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፤

፰. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጠንና ተግባር</u>

ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለቢሮ ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣን ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ለማዕከሉ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ጨምሮ በቢሮው የሚሰጡትን አጠቃላይ መመሪያ መሰረት በማድረግ የልህቀት ማዕከሉን ስራ በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል ይቆጣጠራል፣

፪. የቢሮውን ውሳኔዎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

፫.የማዕከሉን የአስተዳደር ሰራተኞች በሕግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ያሰናብታል

፬. የልህቀት ማዕከሉ ገቢ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፭. የልህቀት ማዕከሉን አመታዊ የስራ እቅድና በጀት በማዘጋጀት ለቢሮው ያቀርባል፣

፮. የልህቀት ማዕከሉን በመወከል ውሎችን ይፈርማል፣

፯. ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የልህቀት ማዕከሉን ይወክላል፣

፰. የማዕከሉን አስተዳደርና ፋይናንስ ተግባሮች በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ይመራል፣

፱. የልህቀት ማዕከሉን የስራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ ለቢሮው ያቀርባል፣

፲. በተጨማሪ በቢሮው የሚሰጡ ተግባራትን ይፈጽማል፣

፲፩. ዳይሬክተሩ ለልህቀት ማዕከሉ የስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከስልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ዳይሬክተሩ ወይም ለዘርፍ መሬዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፱. <u>የምክትል ዳይሬክተሩ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ምክትል ዳሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ኃላፊነቶች ይኖሩታል

፩. የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር በማይኖርበት ወቅት ተክቶ ይሰራል፣

፪. ከዋና ዳሬክተሩ ጋር በመመካከር የቢሮውን ውሳኖዎችን ያስፈጽማል፣

፫. የዓመታዊና ወርሃዊ የማዕከሉ ሪፖርቶች በአግባቡ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት መተላለፉን ያረጋግጣል፣

፬. የማዕከሉን የማስፋፊያና የግንባታ ፍላጎት በማጥናት የግንባታ ዕቅድ የዘጋጃል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፭. የሚጠገኑ ህንፃዎችን ዝርዝር በመለየት ተገቢው ጥገና እንዲደረግላቸው ያደርጋል፣

፮. ቋሚና አላቂ እቃዎችና መሳሪያዎች በአግባቡ ተመዝግበው እንዲያዙ ስርዓት ይዘረጋል፣

፯. በልህቀት ማዕከሉ የሚሰጥ ስልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ የክትትልና ድጋፍ ቡድን ያዋቅራል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

፰.በልህቀት ማዕከሉ የሚሰጠው ስልጠና የከተማ አስተዳደሩን ስትራቴጂና ውጤት ተኮር ስረዓቱን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፱. የማዕከሉ አሰልጣኞችን ቅጥር የደረጃ እድገትና የትምህርት እድል አፈፃፀም ይከታተላል፣

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲. የልህቀት ማዕከሉ የፋይናንስ አጠቃቀም**

ማዕከሉ የአዲሰ አበባ ከተማ አስትዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የሚያወጣወን የገንዘብ አጠቃቅም መመሪያን ተከትሎ ይሰራል።

**፲፩. በጀት**

የማዕከሉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

ሀ) ከከተማ አስተዳደሩ የሚመደብ ዓመታዊ በጀትና ድጎማ፤

ለ) ከልህቀት ማዕከሉ የሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ፤

ሐ) ከሚያገኘው ህጋዊ ስጦታና ድጋፍ የመሳሰሉት ይሆናል፡፡

**፲፪.ገቢ የማመንጨትና የመጠቀም መብት**

የልህቀት ማዕከሉ፡-

ሀ) የገቢ ማስገኛ ስልቶችን በመጠቀም የሚገኘውን ገቢ የከተማ አስተዳደሩን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በማስፈቀድ ሊጠቀም ይችላል፤

ለ) የሚገኘውን ገቢ በፋይናንስ ሕግና ደንብ መሰረት ሥራ ላይ ማዋል ይኖርበታል

**፲፫. የሒሳብ መዝገብ አያያዝ**

ሀ) በሕግና በአሰራር የተፈቀዱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

ለ) የማዕከሉ የሂሳብ መዝገብ እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፤

ሐ) የልህቀት ማዕከሉ የበጀት ዓመት የከተማ አስተዳደሩን የበጀት አመት የተከተለ ይሆናል፡፡

**፲፬. መመሪያ ስለማውጣት**

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ግዜ**

ይህ ደንብ ከግንቦት ፴ ቀን ፪ሺ፲ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ትረስት ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ፶፮/፪ሺ፲፩</u>

መላውን ህብረተሰብ፣ ሲቪክ ማህበራት፣ የንግድ ዘርፉን እና በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበርና በማሳተፍ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡና ውሎ አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ሰዎችን፣ ጧሪና ደጋፊ ያጡ አረጋውያንን፣ የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህጻናትን፣ የአልጋ ቁራኛ ሆነው ረዳት ያጡ ህመምተኞችን፣ እንዲሁም ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን በዘላቂነት መርዳትና ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በከተማው ውስጥ የነዋሪውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በዘላቂነት ለማቃለል ለተቀረጹና ለሚቀረጹ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ፣ የማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከል፣ ተጎጂዎችን ለማቋቋም እና የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ደሀ ሴቶችና ወጣቶችን ለመደገፍ እና በጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲሆን ለማበረታታት የማህበራዊ ትረስት ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፶፫ እና በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፺፫ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ትረስት ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፶፮/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ካቢኔ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቤኔ ነው፤

፬. "የማህበራዊ ትረስት ፈንድ"ማለት ከህብረተሰቡ፣ ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከግለሰቦች፣ ከሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከሐይማኖት ተቋማት፣ ከመንግስት ልማት ድርጅቶች፣ ከከተማ አስተዳደር እና ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች የሚገኝ የህብት ድጋፍ ነው፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬. <u>የፆታ አገላለጽ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ ዓላማ፣ አደረጃጀት እና ተግባርና ኃላፊነት

፭.የማህበራዊ ትረስት ፈንድ ስለመቋቋሙ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናስ ቢሮ በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ የሚሆን የማህበራዊ ትረስት ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንድ ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፮. የፈንዱ ምንጮች

፩. ከከተማው አስተዳደር የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ፣

፪. ከህብረተሰቡ የሚሰበሰብ ድጋፍና ስጦታ፣

፫. ከንግዱ ማህበረሰብና ከተለያዩ ግለሰቦች የሚሰጥ ልዩ ልዩ ድጋፍ፣

፬. ከሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታና ድጋፍ፣

፭. ከሐይማኖት ተቋማት የሚገኝ ድጋፍና ስጦታ፣

፮. ከመንግስት ልማት ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍና ስጦታ፣

፯. ከእድር ወይም ከሚዲያ ተቋም የሚሰጥ ድጋፍና ስጦታ፣

፰. ከሲቪክ ማህበራት የሚደረግ ድጋፍና ስጦታ፣

፱. ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች፡፡

፯. የፈንዱ ዓላማ

የማህበራዊ ትረስት ፈንዱ፡-

፩. ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ ውሎ አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ሰዎችን፣ የአካልና የአምሮ ጉዳተኞችን፣ ጧሪና ደጋፊ ያጡ አረጋውያንን፣ ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህጻናትን፣ የአልጋ ቁራኛ ሆነው ረዳት የሌላቸው ህመምተኞችን እንዲሁም ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭና ተጎጂ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን በዘላቂነት ለማቋቋም፣

፪. ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭነትን ለመከላከል፣

፫.የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ደሀ ሴቶችና ወጣቶችን ለመደገፍ፣ እና

፬.በጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲሆን ለማበረታታት፣ የሚውል ይሆናል፡፡

፰.ስለቦርድ መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የቦርዱ መቋቋምና አደረጃጀት

ሀ) ፈንዱን በበላይነት የሚያስተዳድር እና የሚመራ የዳይሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

ለ) የቦርዱ አባላት በከንቲባው ይሰየማሉ፣ ብዛታቸውም ከ ፱ እስከ ፲፩ አባላት ይሆናል፣

ሐ) ከቦርዱ አባላት መካከል የቦርዱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ በከንቲባው ይሰየማሉ፤

መ) የቦርዱ አባላት ከመንግስት፣ ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከሀይማኖት ተቋማት፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ከሙያ ማህበራት፣ ከሚዲያ ተቋማት እና ከታዋቂ ግለሰቦች የተውጣጡ ይሆናሉ፤

ሠ) በዚህ ንዑስ-አንቀፅ በፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከንቲባው እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች አካላት በቦርድ አባልነት እንዲካተቱ ሊያደርግ ይችላል፤

ረ) ቦርዱ የቦርዱን የዕለት ተዕለት ስራዎች የሚፈጽም የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

፪. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት፡-

ቦርዱ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ) ፈንዱን በበላይነት ያስተዳድራል፣ ይመራል፤

ለ) የፈንዱን ፕሮግራም፣ ስትራቴጂና ማዕቀፎችን ይቀርጻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) ቦርዱ የፈንዱን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚያስችለው ተግባርና ኃላፊነት ሁሉ ይኖረዋል፤

መ)የፈንድና ሀብት አሰባሰብ ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) ለፈንዱ ዓላማ የሚውል ገንዘብ ከፈንዱ ወጪ እንዲደረግ ይወስናል፤

ረ) ምክር ቤቱን ያስተባብራል፤

ሰ) ከፈንዱ ወጪ የተደረጉ ሀብቶች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ሸ) በየዓመቱ ስለ ፈንዱ አስተዳደር እና አጠቃቀም በውጭ ኦዲተር ኦዲት እንዲደረግ ያደርጋል፤

ቀ) በኦዲተር የተመረመረ የፈንዱ ዓመታዊ ሂሳብ እንዲጠናከርና ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

በ) ከምክር ቤቱ ምክረ-ሀሳቦችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ ገንቢ ሀሳቦችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ተ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዘርፉ የተሻለ ብቃትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መመደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምክር ቤቱ አባል እንዲሆኑ የውሳኔ ሀሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፤

ቸ) ስለፈንዱ ጠቀሜታ ለህብረተሰቡ ያስተዋውቃል፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤

ኀ) ስለፈንድና ሀብት አሰባሰብ ከፈንዱ ገንዘብ ወጪ እና ተከፋይ ስለሚሆንበት ስርዓት መመሪያ ያወጣል፤

ነ) የቦርዱን ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፤

ኘ) እንደአግባብነቱ ከበላይ ጠባቂው ወይም ከከንቲባው ለፈንዱ ዓለማ ስኬታማነት የሚያግዙ ሀሳቦችን ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፱. <u>የቦርዱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ቦርዱን ይመራል፤ በዚህ ደንብ ለቦርዱ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት በበላይነት ያስተባብራል፤

፪. የቦርዱን የበጀትና የስራ ዕቅድ ያቅዳል፤ በቦርዱ ሲጸድቅ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤ ይከታተላል፤

፫. ስለፈንድና ሀብት አስተዳደርና አጠቃቀም ወቅታዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለከተማ ነዋሪ ይፋ ያደርጋል፤

፬. የቦርዱ ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ ለጽሕፈት ቤቱ ይመራል፤ ይከታተላል፤

፭. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ቦርዱን ይወክላል፤

፮. የቦርዱ ስብሰባዎች ወቅታቸውን ጠብቀው መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ሲያስፈልግ ጥሪው ለቦርድ አባላት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

፯.የቦርዱ ቃለ-ጉባዔዎች እና ሌሎች ሰነዶች በቃለ-ጉባኤ ፀሀፊ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

፰. የምክር ቤቱን ምክረ-ሀሳቦች በአግባቡ በማጤን ለቦርዱ ለውሳኔ ያቀርባል፤

፱. ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲. <u>የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. የቦርዱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ወቅት ተክቶት ይሰራል፤

፪. በቦርድ ሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፩. <u>የቦርዱ ፀሀፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. የቦርዱ ውሳኔዎች፣ ቃለ-ጉባኤዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች በትክክል መያዛቸውን ይከታተላል፤

፪. ቦርዱ ገንዘብ ከፈንዱ ወጪ እንዲደረግ ሲፈቅድ ከጽሕፈት ቤት ኃላፊው እና ከሚመለከተው የፋይናንስ ኃላፊ ጋር በጣምራ ፊርማ ገንዘብ ከፈንዱ ወጪ ያደርጋል፤

፫. በቦርድ ሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፪. <u>የአማካሪ ምክር ቤት አደረጃጀትና ተግባር</u>

፩. በከንቲባው የሚሰየሙ ፲፮ አባላት የሚገኙበት የአማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ይደራጃል፤ ከንቲባው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምክር ቤቱን አባላት ብዛት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፤

፪.የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለከንቲባው ሆኖ የሚከሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) በዘርፉ ላይ በተጠኑ ጥናቶች ላይ በመመስረት ስለ ስትራቴጂ ዝግጅት፣ ስለሀብትና ፈንድ አሰባሰብና አመዳደብ ምክረ-ሀሳብ ለከንቲባውና ለቦርዱ ያቀርባል፤

ለ) ለቦርዱ አሰራር ውጤታማነት፣ ጥራት እና ቅልጥፍና የሚረዳ ምክረ-ሀሳብ ያቀራይወክላል፤

ሐ) በዓመት ሁለት ጊዜ በመደበኛ የቦርድ ስብሰባ ላይ በመገኘት ስለአሰራር፣ አፈጻጸም እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ያለውን ልምድ ያካፍላል፤

መ) ከአጠቃላይ የቦርዱ አሰራር፣ አተገባበርና ሪፖርት ግምገማ ተነስቶ መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ለከንቲባው ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፤

ሠ) ሌሎች ፈንዱን ሊያሳድጉ የሚችሉ አዳዲስ አሰራሮች እና ስልቶችን በመቀየስ ለከንቲባው እና ለቦርዱ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤

ረ) የግንኙነት ጊዜውን እና አሰራሩን ራሱ በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወስናል፡፡

፲፫.ስለቦርዱ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት

የቦርዱ ጽህፈት ቤት በከንቲባ ጽህፈት ቤት ሥር የሚደራጅ ሆኖ፡-

፩. በከንቲባው የሚሾም ኃላፊ፣ እና

፪. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፲፬. የጽህፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የቦርዱ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

፪. የፈንዱን ሂሳብና ልዩ ልዩ ሰነዶች ይይዛል፤

፫.የቦርዱን ስብሳባዎች ሪኮርዶች ይይዛል፤

፬. የድጋፍ ጥያቄዎችን እና ሌሎች ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችን ለቦርዱ ለውሳኔ ያቀርባል፤

፭. ረቂቅ መመሪያ፣ እቅድ እና ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፮. የፈንዱን የሂሳብ መግለጫዎች እያዘጋጀ በየወቅቱ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፯. ለጽሕፈት ቤቱ ለአስተዳደራዊ ስራ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም እንዲሁም በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

፰.ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

፱. የጽሕፈት ቤቱን ወቅታዊ እና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ የስራ ክንውን ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፲. ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

፲፭. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

፩. በዚህ ደንብ ለጽሕፈት ቤቱ የተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነት መተግበራቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፪. የጽሕፈት ቤቱን ስራ ያቅዳል፤ ይፈጽማል፤ ይከታተላል፤ ይመራል፤ ሀብት ያስተዳድራል፤

፫. ስለ ጽሕፈት ቤቱ ስራ፣ በጀት፣ ሀብት አስተዳደር እና አጠቃቀም ወቅታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፬. የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

፭. ቦርዱ ገንዘብ ከፈንዱ ወጪ እንዲደረግ ሲፈቅድ ከቦርዱ ፀሐፊ እና ከሚመለከተው የፋይናንስ ኃላፊ ጋር በጣምራ ፊርማ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ የፋይናንስ አሠራሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፤

፮. ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት ወጪ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

፯. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

፰. ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፮. <u>የበላይ ጠባቂ</u>

የፈንዱ የበላይ ጠባቂ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ወይም ኘሬዝዳንቱ የሚሰይመው ሰው ይሆናል፡፡

፲፯. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

፩. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይደረጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ሲጠራ ቦርዱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፬. የቦርዱ ውሳኔ በህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ በውሳኔው ላይ የተገኙ አባላት በተናጠልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም በውሳኔው ላይ ልዩነቱን ያሰፈረ የቦርድ አባል ከተጠያቂነት ነፃ ይሆናል፡፡

፭. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የውስጥ የስብሰባ እና አሰራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፰. <u>የቦርድና የምክር ቤት አባላት የስራ ዘመን</u>

፩. የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ለሶስት ዓመታት ይሆናል፡፡

፪. የምክር ቤት አባላት የስራ ዘመን ለአምስት ዓመታት ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ለአንድ ዓመት ያህል ከንቲባው ለሁለቱም አካላት የስራ ዘመኑን ሊያራዝም ይችላል፡፡

፲፱.<u>የፈንዱ ገንዘብና ሀብት አሰባሰብ</u>

፩.ለፈንዱ የሚደረጉ የተለያዩ የገንዘብ ድጋፎችና ልገሳዎች አሰባሰብ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የገንዘብ ድጋፍና ልገሳዎች በፈንዱ የሂሳብ ቋት ውስጥ ገቢ ሲደረግ ገቢ ያደረገውን አካልና የገንዘብ መጠን በየወሩ ጽሕፈት ቤቱ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፫. በተለያየ መልኩ በዓይነትና በቁሳቁስ የሚገኙ ድጋፎችንና ስጦታዎችን ጽሕፈት ቤቱ ይረከባል፤ የተገኙትን ፈንድና ሀብት ለቦርዱ ያሳውቃል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳.<u>ስለሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች</u>

፩. ጽህፈት ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የፈንዱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ቦርዱ በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፤

፫. ሂሳቡ የሚመረመረው በህግ በተፈቀደለት የሂሣብ መርማሪ ሆኖ የኦዲት ሪፖርቱ በቦርዱ እና በከንቲባው አስተያየት እንዲሰጥበት ይቀርብላቸዋል፤

፬. በተመረጡ ተግባራት ላይ የቴክኒክ ምርመራ በየዓመቱ ይከናወናል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳፩. <u>የመተባበር ግዴታ እና ተጠያቂነት</u>

፩. ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም አፈጻጸሙን ያሰናከለ ወይም የፈንዱን ገንዘብም ሆነ ንብረት ያባከነ ወይም ያጎደለ እንደሆነ በሀገሪቱ የወንጀል ህግ እና ሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፳፪.<u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የከተማው ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብበተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

፳፫. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ቦርዱ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥር ፲ ቀን ፪ሺ.፲፩ ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፪ሺ.፲፩ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ፻፲/፪ሺ፲፪

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚከናወኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶች የሚታዩባቸውን የአፈጻጸም ችግሮች በማስወገድ ለፕሮጀከቶቹ የሚውለውን ሀብት ውጤታማ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የነዋሪውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ እንዲሆኑ ለማድረግ ፕሮጀክቶቹን በበላይነት የሚመራ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩አንቀጽ ፺፭ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክት ግንባታ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር፻፲/፪ሺ፲፪"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. “ከተማ”፡ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዉ፤

፪. “ከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፤

፫. “ከንቲባ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነዉ፤

፬. “ካቢኔ” ማለት የከተማው ካቢኔ ነዉ፤

፭. “ዋና ሥራ አስኪያጅ ” ማለት ጽህፈት ቤቱን እንዲመራ በከንቲባው የሚሾም ኃላፊ ነው፤

፮. “ትላልቅ ፕሮጀክት” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገነቡ ከመንገድ፣ ውሃና ቤቶች ግንባታ ውጭ ያሉና የፕሮጀክት ዋጋቸው ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ ግንባታ ወይም የሚመለከተው አካል የሚወስነው ፕሮጀክት ነው፤

፯.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው

**፫.የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**፬.ዓላማ**

፩.ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገድብ፣ ወጪ እና ጥራት እንዲጠናቀቁ ማድረግ፤

፪.በተቀናጀና በተደራጀ መንገድ ፕሮጀክቶችን መምራት፤

፫.በፕሮጀክቶቹ የግንባታ ሂደት የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር ማድረግ፤

፬.በፕሮጀክቶቹ አማካኝነት የስራ ዕድል እንዲፈጠር ማመቻቸት፤

፭.በለጋሽ አካላት ወይም በዕርዳታ የሚገኝ ሀብት ለሚመለከተው ስራ እንዲውል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

፭.የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደሩ በሚገነቡ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፤ተጠሪነት፤አደረጃጀት፤ስልጣንና ተግባር

፮.መቋቋም እና ተጠሪነት

፩.በዚህ ደንብ የተመለከቱት ዓላማዎች፣ ተግባሮችና ሥልጣኖች ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት (ከዚህ በኃላ "ጽህፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪.የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡፡

፯.አደረጃጀት

ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩.ዋና ሥራ አስኪያጅ፤

፪.እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፤ እና

፫.ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

፰.የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የጽህፈት ቤቱን የአጭርና የመካከለኛ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪.ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ፣ የወጪ እና የጥራት ደረጃ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፫.ፕሮጅክቶቹን በተሟላ መልኩ ለመምራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፤

፬.በከተማ አስተዳደሩ እና ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ጋር በሽርክና የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን ከተማ አስተዳደሩን በመወከል ውል ይዋዋላል፤ይከታተላል፤

፭.ለፕሮጀክት ስራዎች የተለዩ ቦታዎችን መረጃ ይሰበስባል፤ ይለያል፤ ያደራጃል፤ የተለዩ ቦታዎች እንዲፈቀድና የወሰን ማስከበር ስራ እንዲሰራ የሚመለከተውን አካል ይጠይቃል፣ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

፯.የፕሮጀክቶችን የአዋጭነት ጥናት ያጠናል ወይም ያስጠናል፣ የጥናቱንም ውጤት ለከንቲባው አቅርቦ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፯. ከከተማ አስተዳደሩ ቢሮዎች ወይም ኤጀንሲዎች ወይም ባለስልጣን ወይም ኮሚሽን በዘርፋቸው ከህዝብ ለሚነሱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፰. ስለፕሮጀክቱ ዓላማና አተገባበር ከህብረተሰቡ ጋር በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ውይይት ያደርጋል በውይይቱም ላይ የሚቀርቡ ሃሳቦችን በመቀመር የዕቅዱ አካል ያደርጋል፣

፱. ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፕሮጀክት ዲዛይን ያሰራል፣ በዲዛይኑ መሰረት ግንባታው መከናወኑን አማካሪ ድርጅት በመቅጠር ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲. በተዘጋጀው ዲዛይን መሰረት የግንባታ ስራ ለሚሰሩ ስራ ተቋራጮች አግባብ ባለው ህግ መሰረት ጨረታ ያወጣል፣ ውል ይገባል፣ውሉንም ያስተዳድራል፣

፲፩.ከግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት የሚመጣለትን የክፍያ ሰነድ በማረጋገጥ ክፍያ ይፈፅማል፣

፲፪. ከፕሮጀክቶች አስተዳደር ጋር የተያያዙ ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ይቀምራል፣ ይተገብራል፣

፲፫.ስለ ፕሮጀክቶቹ የስራ ሁኔታ በየወሩ ለከንቲባው የስራ ሪፖርት ያቀርባል፣

፲፬. የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አስተዳደር በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በማስመርመር ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፣

፲፭. የተጠናቀቁትን ፕሮጀክቶች በመጨረሻ የማስተዳደር ስልጣን ለተሰጠው አካል በሰነድ ያስረክባል፣

፲፯.ሌሎች ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን ያከናውናል፡፡

<u>፱.የዋና ሥራ አስኪያጁ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ዋና ሥራ አስኪያጁ በከንቲባው የሚሾምና ተጠሪነቱም ለከንቲባው ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ሰራተኞችን በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች ሕግ መሰረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

፪. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የስራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለከንቲባው ያቀርባል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፫. በፀቀደው አመታዊ የስራ ፕሮግራም መሰረት ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ጥራትና በጀት መሰረት መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል እንዲወሰድም ያደርጋል፣

፬. በፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት የጽህፈት ቤቱን የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ የጽህፈት ቤቱን ሃብትና ንብረት ያስተዳድራል፣

፭. ወቅታዊና ዓመታዊ የስራ ሪፖርት ለከንቲባው እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣

፮. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፣

፯. የጽሕፈት ቤቱን ዓላማና ግብ ለማሳካት የሚያስችሉ በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## በጀት፣ የሂሳብ መዛግብት አያያዝ፣ ንብረት እና የሰው ኃይል አስተዳደር

### ፲.ስለ በጀትና የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፩. የበጀት ምንጭ ከከተማ አስተዳደሩ የሚመደብ በጀትና ከልዩ ልዩ ሕጋዊ ምንጮችከሚገኝ ፈንድ ይሆናል፡፡

፪. የተሟላና የተረጋገጡ የሒሳብ መዛግብት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት ይይዛል፡፡

፫. የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እሱ በሚወክለው አካል ይመረመራል፡፡

### ፲፩.ስለ ንብረት አስተዳደር

፩.ጽህፈት ቤቱ የራሱ ንብረቶች ይኖሩታል፡፡

፪.ንብረቶችን በንብረት አስተዳደር ህግ መሰረት በኃላፊነት ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

### ፲፪.ስለሰው ኃይል

በሚመለከተው አካል የሰው ኃይል መዋቅሩ ሲፈቀድለት ለፕሮጀክቱ ውጤታማት አመቺ ሆኖ በተገኘው መንገድ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፫.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት::

### ፲፬.ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ

ይህን ደንብ የሚቃረን የካቢኔው ደንብ፣ መመሪያ ወይም የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ያወጧቸው መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

### ፲፭.ደንቡን ስለማሻሻልና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩. ካቢኔው እንደአስፈላጊነቱ ይህን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

፪. ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም ጽህፈት ቤቱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

### ፲፮.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከ ታህሳሥ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፪ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳሥ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ፪፲፩/፪ሺ፲፩</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ እና የአስተዳደር ኃላፊዎች አሰያየምንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፺፯ መሠረት ይህንን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፹፪/፪ሺ፱ /ማሻሻያ/ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ቁጥር ፪፲፩/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.<u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩."ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፡፡

፪."ፕሬዚዳንት" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ነው፡፡

፫. <u>ማሻሻያ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር ፹፪/፪ሺ፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩.ከደንቡ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተራ ፊደል /ሸ/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል /ቀ/ ተጨምሯል፣ የዚሁ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል "ቀ" የነበረው ተራ ፊደል "በ" በመሆን ተሸጋሽጓል፤

" ቀ/ የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ፣"፡፡

፪. የደንቡ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተተክቷል፤

"፫. አግባብነት ባላቸው የአዋጁ አንቀጽ ፹፰ ድንጋጌዎች ለሚኒስቴሩ እንዲሁም የአንቀጽ ፺፬ ድንጋጌዎች ለቦርዱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፡ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እንደተደነገገው ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነቱ ለከንቲባው ይሆናል፡፡"፡፡

፫. የደንቡ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ፣ /፪/ እና /፫/ ተሰርዘው በሚከተለው ተተክቷል፤

"በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭/እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ /፪/ /ኘ/ መሠረት የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት በከንቲባው ይሠየማሉ፣ ቦርዱ ሰባት ድምፅ መስጠት የሚችሉ አባላት ይኖሩታል፤ ፕሬዜዳንቱ ድምጽ የማይሰጥ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡"፡፡

፬.ከደንቡ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተጨምሯል፤

"፬. ለቦርድ አባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች ከንቲባው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡"፡፡

፭.የደንቡ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተራ ፊደል /ሠ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል /ሠ/ ተተክቷል፤" ሠ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዩኒቨርሲቲው ማቋቋሚያ ደንብ ላይ የማሻሻያ ሃሣብ ለከንቲባው ያቀርባል፣"፡፡

፮.ከደንቡ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተራ ፊደል /ተ/ ቀጥሎ አዲስ ተራ ፊደል /ቸ/ ተጨምሯል፤ "ቸ. ለዩኒቨርሲቲው አግልግሎት መስጠት የሚችሉና የከተማ አስተዳደሩ የሚያስተዳድራቸው ንብረቶችን፣ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ህንፃዎችን እና ተያያዥነት ያላቸውን ንብረቶች በመለየት ወደ ዩንቨርሲቲው እንዲተላለፉ የውሳኔ ሀሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፡፡"፡፡

፯.የደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተራ ፊደል /ሰ/ ተሰርዟል፡፡

፰.የደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ተተክቷል፤"፭. የዩኒቨርሲቲው ሬጂስትራር የሴኔቱ ፀሐፊ ይሆናል፡፡"

፱.የደንቡ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ /፰/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፰/ ተተክቷል፤"፰. ፕሬዚዳንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዓመት ቢያንስ ሦስት /፫/ ጊዜ ይሰበሰባል፣"፡፡

፲.የደንቡ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ /፯/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፯/ ተተክቷል፤"፯. በአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት ፕሬዚዳንቱ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራው ላይ በማይገኝበት ጊዜ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንቱ እሱን ተክቶ እንዲሠራ ይወከላል፤ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንቱ የማይገኝ ቢሆን ግን ሌላ ምክትል ፕሬዚዳንት ሊወከል ይችላል፣"፡፡

፲፩. የደንቡ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/፣ /፪/ እና /፫/ ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ ተተክተዋል፤"፩. የፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ሹመት በአዋጁና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ሐ/ መሠረት ይፈፀማል፤፪. የእጩ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት መልማይና መራጭ ኮሚቴ አሰያየም፣ የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት፣ ለፕሬዚ-ዳንትነት እና ለምክትል ፕሬዚዳንትነት የሚያበቁ መመዘኛዎችና ዝርዝር አፈፃፀም በከንቲባው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡"፡፡

፲፪. የደንቡ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተራ ፊደል /ሐ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል /ሐ/ ተተክቷል" ሐ. ሁሉም የአካዳሚክ አስተባባሪዎች፣"፡፡

፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ዓ/ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ፰፰/፪ሺ፲፪ አጭር መግለጫ

ማውጫ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የፆታ አገላለጽ

፬. የተፈጻሚነት ወሰን

፭. መቋቋም

፮. ዋና መሥሪያ ቤት

፯. ዓላማ

፰. ሥልጣንና ተግባራት

፱. የኢጀንሲው አቋም

፲. የቦርዱ አባላት

፲፩. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

፲፪. የቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

፲፫. የቦርዱ ስብሰባ

፲፯.የሒሳብ መዛግብት

፲፰. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፲፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፳. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

አጭር መግለጫ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለቤትነት በሚተዳደሩ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተጀመረውን የተማሪዎች ምገባ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት ሥርዓት ወጥ በሆነና በተቀናጀ መንገድ ለመምራት አስፈጻሚ አካል ለማቋቋም የወጣ ሕግ ነው

## <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፪ሺ፲፪</u>

በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ባለቤትነት በሚተዳደሩ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተጀመረውን የተማሪዎች ምገባ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት ሥርዓት ወጥ በሆነና በተቀናጀ መንገድ መምራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተማሪዎች ምገባ መርሀ ግብር የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል፣ የምግብ እጥረትና የጤና ችግር የሚያጋጥማቸውን ተማሪዎች ቁጥር በመቀነስ የተማሪዎች ተሳትፎ ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

የባለድርሻ አካላትና ማኅበረሰቡ በትምህርት ዘርፍ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በማጎልበት በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎችና የትምህርት ዕድል ያላገኙ ህጻናትን ወደ ትምህርት ገበታ እንስመጡ ለማስቻል፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሸሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ (ሀ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "የከተማ አስተዳደር " ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ቻርተር አዋጅ" ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፬. "ክንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነዉ፤

፭. "ቦርድ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲን በበላይነት የሚመራ የስራ አመራር ቦርድ ነው፤

፮. "ትምህርት ቤት" ማለት በከተማ አስተዳደሩ ባለቤትነት በሚተዳደሩ ቅድመ መደበኛ፣ መጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፤

፯. "የተማሪዎች ምገባ" ማለት ለተማሪዎች ምግብ የሚውልና በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ ንጥረ ምግቦችን ያካተተ በጥራትና በበቂ መጠን ተዘጋጅቶ በትምህርት ቤት የሚቀርብ ምግብ ሆኖ ለቀን ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ባልበት ወቅት ከሰኞ እስከ አርብ የሚቀርብላቸው ቁርስና ምሳ ነው፤

፰. “ግብዓት ወይም ቁሳቁስ ” ማለት ለመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምህርት ጊዜ የሚሰጥ የተማሪዎች ዩኒፎርም፣ ቦርሳ፣ ደብተር፣ እስኪሪብቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ፣ የሴት ተማሪዎች የሴት ሱሪ እና የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ነው፤

፱. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፫. <u>የፆታ አገላለጽ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፬. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በከተማ አስተዳደሩ ባለቤትነት በሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭. <u>መቋቋም</u>

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡፡

፮. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

፩. የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በከተማ ደረጃ ይሆናል፤

፪. ኤጀንሲው እንደአስፈላጊነቱ በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ጽህፈት ቤት ለላኖረው ይችላል፡፡

፯. <u>ዓላማ</u>

ኤጀንሲው የሚከተልት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩. በከተማዋ የሚገኙ ህጻናትና ወጣት ተማሪዎች በምግብ እና በትምህርት ግብዓት አቅርቦት ችግር ምክንያት ከትምህርት ገበታ ውጪ እንዳይሆኑ ማስቻል፤

፪. ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እና ብቁ ዜጋ ሆነው ሀገራቸውን እንዲረከቡ ለሚደረገው የሰው ሀብት ልማት ፕሮግራም መሳካት አስተዳደሩና ህብረተሰቡ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበት አሰራር መዘርጋት፣

፫. የተጀመረውን የምገባ እና የትምህርት ግብዓት አቅርቦት አሰራር ቀጣይነት ያለው እና ተቋማዊ እንስሆን ማድረግ፤

፬. የተማሪዎች ምገባ እና መሠረታዊ የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት አሳታፊ፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ሥርዓት በማስፈለጉ፤

፭. በተማሪዎች ምገባና ግብዓት አቅርቦት በሚፈጠር የስራ ዕድል ላይ የተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል

፮. የተማሪዎች ምገባ እና መሰረታዊ የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦት አሳታፊ ግልጸኝነት ተጠያቂነት ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ፡፡

፰. <u>ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኤጀንሲው የሚከተልት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩. የተማሪዎች ምገባ፣ የተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ እና የትምህርት መርጃ መሳሪያ ድጋፍ ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ይዘረጋል፤ ይተገብራል፤ እንስተገበር ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፤

፪. በቅድመ መደበኛ፣ በመጀመሪያ ደረጃ እና እንደአስፈላጊነቱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች የምገባ ተግባር ያከናውናል፤ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. ለምገባ፣ ለመማሪያ ቁሳቁስ፣ ለትምህርት መርጃ መሳሪያ እና የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም ደንብ ልብስ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶችና የተማሪዎችን መረጃ ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ልብስ

፬. ለመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ እና የተማሪ ዩኒፎርም ወይም ደንብ ልብስ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፭. ለተማሪ ወላጆች፣ ለሴቶችና ለወጣቶች በምገባ ኘረሬግራሙ የስራ ዕድል እንስፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በቅንጅት ይፈጽማል፤

፮. በተማሪዎች ምገባ፣ በተማሪዎች መማሪያ ቁሳቁስ፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያ እና በተማሪ ዩኒፎርም ደንብ ልብስ ድጋፍ በሚመለከት ከተማሪ ወላጆች፣ ከመንግስታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል፤

፯. የትምህርት ምገባ ፕሮግራም በተማሪዎች ጤንነት፣ ንጽህና ጥበቃና የስርዓተ ምግብ መሻሻል ላይ ያተኮረ መሆኑን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤

፰ የተማሪዎች ምግብ ማዘጋጃ እና መመገቢያ ህንጻ ያስገነባል፤ ተገቢውን ግልጋሎት እየሰጠ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእርምት እርምጃ እንስወሰድ ያደርጋል፤ የተማሪዎች መማሪያና መፀዳጃ ቤት ለተማሪዎች ምቹ እስሆን ድጋፍ ያደርጋል፤

፱. የሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ግብዓት ያቀርባል፣ ያሰራጫል፤

፲. ከኤጀንሲው ተልእኮ አኳያ ጥናትና ምርምር ያደርል፣ ጥናቱ በጥቅም ላይ እንዲውል ይከታተላል ከዚህ ቀጥሎ ያልት ተከታታይነታቸውን ጠብቀው እንዲቀመጡ ይደረጋል፤

፲፩. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤

፲፪. ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ልሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናወናል፡፡

፱. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፡-

፩. የተማሪዎች ምገባ የስራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፣

፪. በከንቲባው የሚሾም ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተረሬች፣ እና

፫. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች፣ ይኖሩታል፡፡

፲. የቦርዱ አባላት

የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት በከንቲባው አቅራቢነት በምክር ቤት የሚሾሙ ሲሆን የአባላቱ ቁጥር ከዘጠኝ እስከ አስራ አንድ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቁጥሩ በከንቲባው በኩል ለላጨምር ይችላል፡፡

፲፩. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ፡-

፩. በተማሪዎች ምገባ፣ የተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ እና የትምህርት መርጃ መሳሪያ አቅርቦትና ስርጭት ዙሪያ በሚቀርቡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እና የኤጀንሲውን ዓላማ ለማሳካት በሚረዱ ልሎች ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለከንቲባው የውሳኔ ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል፣

፪. የኤጀንሲው የአሰራር መመሪያ እና ማኑዋል ተጠንተው ሲቀርቡለት መርምሮ ያጸድቃል፣

፫. በኤጀንሲው ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ውሳኔም ይሰጣል፣

፬. የኤጀንሲው ተቋማዊ ብቃትና አገልግሎት አሰጣጥ በየጊዜው የሚሻሻልበትንና የሚጠነክርበትን አቅጣጫዎች ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

፭. ኤጀንሲው የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነትና በአግባቡ መወጣቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

፮. ልሎች በከንቲባው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::

፲፪. የቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

፩. የቦርዱን ስብሰባ ይመራል፣ የስብሰባ ጥሪ እንስተላለፍ ያደርጋል፣ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ቦርዱን ይወክላል፣

፪. የቦርዱ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ እንስካሄድ ያደርጋል፣ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለቦርድ አባላት ጥሪ እንስተላለፍ ያደርጋል፣

፫. የቦርድ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፬. የቦርድ ውሳኔዎችና ሰነዶች በቦርድ ፀሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

፲፫. የቦርዱ ስብሰባ

፩. ቦርዱ በወር አንዴ ይሰበሰባል፣ አስፈላጊ ሲሆን አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፪. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫. የቦርዱ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፣ እኩል ድምፅ በሚኖርበት ወቅት ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፬. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር</u>

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተልት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፰) የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ሠራተኞች በከተማው የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለከንቲባው እና ለቦርዱ ያቀርባል፤ በአስተዳደሩ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጅንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለከንቲባው እና ለቦርዱ እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከተው አስፈጻሚ አካል ያቀርባል፡፡

፫. ለኤጀንሲው ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ልሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ለላሰጥ ይችላል፡፡

፲፭. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተረሬች ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተረሬች የሚከተልት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፦

፩. የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ልሎች ስራዎችን ያከናውናል፤

፫. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጠው ውክልና መሠረት ዋና ዳይሬክተሩን ተክቶት ይሠራል፡፡

፲፮.<u>በጀት</u>

የኤንጀንሲው የበጀት ምንጭ፡-

፩. ከከተማው አስተዳደር ከሚመደብ በጀት፣ እና

፪. ከሌላ ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ይሆናል፡፡

፲፯.<u>የሒሳብ መዛግብት</u>

፩. ኤጀንሲው የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪. የኤጀንሲው የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦስት መሥሪያ ቤት እና በውስጥ ኦስት በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

፲፰. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩. የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

፪. ቦርዱ አዋጁና ደንቡን ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፳. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ  የአሰራር ደንብ ፻፲፪/፪ሺ፲፪

በከተማዋ የሚገኙ ህጻናትና ወጣት ተማሪዎች በምግብ እና በትምህርት ግብዓት አቅርቦት ችግር ምክንያት ከትምህርት ገበታ ውጪ እንዳይሆኑ የተጀመረውን የተማሪዎች ምገባ እና የትምህርት ግብዓት አቅርቦት አሰራር ቀጣይነት ያለው እና ተቋማዊ  እንዲሆን ለማድረግ የከተማው ምክር ቤት የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ እንዲቋቋም በመደረጉ፤

ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በመዘርጋት ኤጀንሲው ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚያስችለውን የአሰራር  ሥርዐት በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፲፰ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ የአሰራር ደንብ ቁጥር ፻፲፪/፪ሺ፲፪” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡፤-

፩. “ከተማ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. “ከተማ አስተዳደር” ማለት  የአዲስ  አበባ  ከተማ  አስተዳደር  ነዉ፤

፫. “ከንቲባ” ማለት  የአዲስ  አበባ  ከተማ  ከንቲባ  ነዉ፤

፬. “ካቢኔ” ማለት የከተማው ካቢኔ  ነዉ፤

፭. “አዋጅ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፪ሺ፲፪ነው፤

፮. “ቦርድ” ማለትየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲን በበላይነት የሚመራ የስራ አመራር ቦርድ ነው ፤

፯. “ኤጀንሲ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ ነው፤

፰. “ትምህርት ቤት” ማለት በከተማ አስተዳደሩ ባለቤትነት የሚተዳደሩ ቅድመ መደበኛ፣ መጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፤

፱. “የተማሪዎች ምገባ“ ማለት ለተማሪዎች ምግብ የሚውልና በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ ንጥረ ምግቦችን ያካተተ በጥራትና በበቂ መጠን ተዘጋጅቶ በትምህርት ቤት የሚቀርብ  ምግብ ሆኖ

ለቀን ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ባሉበት ወቅት ከሰኞ እስከ አርብ የሚቀርብላቸው ቁርስና ምሳ ነው፤

፲. "ግብዓት ወይም ቁሳቁስ" ማለት ለመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምህርት ጊዜ የሚሰጥ የተማሪዎች ዩኒፎርም፣ ቦርሳ፣ ደብተር፣ እስኪሪብቶ፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ፣ የሴት ተማሪዎች የውስጥ ሱሪ እና የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ነው፤

፲፩."የምግብ ዝግጅት" ማለት በኤጀንሲውና በሚመለከታቸው አካላት ቁጥጥር እየተደረገበት የሚከናወን ምግብ የማዘጋጀት ሂደት ነው፤

፲፪. "የትምህርት መርጃ " ማለት በኤጀንሲው ለተማሪዎች የሚቀርብ የትምህርት ቁሳቁስ ነው፤

፲፫."ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠው ሰው ነው።

፫. የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፬.የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአዋጁና በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለፕሮግራም ዝግጅትና አቀራረብ

፭. ስለ ፕሮግራም ዝግጅት

፩. የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ዝግጅት በበጀት ዓመቱ ዕቅድ በኤጀንሲው ይዘጋጃል፤

፪. የተማሪዎች የምገባ በጀት በምገባ ፕሮግራም በጀት መያዝ አለበት፤

፫. የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ዝግጅትና አቅርቦት አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት ይመራል፤

፬. የምገባ መርሐ ግብር ተጠቃሚ የሚሆኑ የትምህርት ዘመኑ ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች መሆን አለባቸው፤

፭. የተማሪዎች የምገባ የጊዜ ሰሌዳ በትምህርት ቢሮ የትምህርት ጊዜ ሰሌዳን መሰረት በማድረግ ይወስናል::

፮. ስለምግብ ዝግጅትና አቀራረብ

፩. የምገባ መርሐ-ግብር ተጠቃሚ ተማሪዎች ዝርዝር መረጃዎች ተጠናቅረው መያዝና ወቅታዊ መደረግ አለባቸው፤

፪. ለተማሪዎች የሚዘጋጅ ምግብ ይዘት ለአካላዊና አዕምሮዊ ዕድገት ጠቃሚ ንጥረ ነገር ያላቸው ገንቢ፣ ኃይል ሰጪ እና በሽታ ተከላካይ መሆን አለባቸው፤

፫.ኤጀንሲው የተማሪዎቹን አመጋገብ ስርዓት ለማሻሻል ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፤ይተነትናል፤ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፬. በምገባ ፕሮግራም ለአካል ጉዳተኞችና የጤና ችግር ላለባቸው ሕጻናትና ወጣቶች ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት፤

፭. በቀላሉ ሊበላሹና ሊበከሉ የሚችሉ ምግቦች ለምግብነት እንዳይውሉ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

፮. ለሕጻናት የሚቀርቡ ምግቦች መጠን ከዕድሜያቸው ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፣

፯. ለመጠጥ፣ ለምግብ ዝግጅትና አቀራረብ እንዲሁም ለተጓዳኝ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነ ንጹህ ውሃ መቅረብ ይኖርበታል፤

፰. የምግብ አቅርቦት አመጋገብ ምገባ በሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል ተመሳሳይነት እንዲኖርና ልዩነት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

፯. የምግብ ማከማቻ፣ ማብሰያና መመገቢያ ክፍሎች ዝግጅትና አጠቃቀም

፩.የምገባ ፕሮግራም የሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች ለምግብ ማዘጋጃና ማከማቻ ቦታ ማዘጋጀት አለባቸው፤

፪.የምግብ ሸቀጥ ማከማቻ ክፍሉ በሽታ አስተላላፊና ሌሎች ነፍሳት መራቢያ እንዳይሆን በየጊዜው ጽዳቱ የተጠበቀ መሆን አለበት፤

፫. የተማሪዎች መመገቢያ ክፍል በቂ ብርሃን፣ አየር ያለውና ንጽሕናው የተጠበቀ መሆን አለበት፤

፬. የተማሪዎች መመገቢያ ክፍል በቂ፣ ለሕጻናት ቁመት ተስማሚና ምቹ መቀመጫ እና የውሀ ማስቀመጫ ስፍራ ሊኖረው ይገባል፤

፭.የተማሪዎች መመገቢያ ክፍል በባለሙያ በሚወሰነው መሰረት ከመማሪያ ክፍሎችና ከመጸዳጃ ቤት መራቅ አለበት፤

፮. የምገባ ቦታ ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ምቹና ተስማሚ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤

፯.ማናቸውም የምግብ ግብአቶችና ምግቦች በባለሙያ በሚወሰነው መሰረት ከመሬት ከፍ ባለ ቦታ መቀመጥ አለባቸው፤

፰.የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያዎችና የጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፤

፱. መመገቢያና ምግብ ማብሰያ ክፍሎች ቢያንስ በግድግዳ መለየት አለባቸው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ምግብ አብሳዮች

## የምግብ አብሳዮችና የተማሪዎች ጤናና የንጽሕና አጠባበቅ

፰. የምግብ አብሳዮች የጤና ሁኔታና የንጽሕና አጠባበቅ

፩. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት ምግብ የሚያዘጋጅ ወይም የሚያቀርብ ሰው ተገቢ የሆነ የጤና ምርመራ ማድረግና ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

፪. ምግብ የሚያዘጋጁ ሰዎች በማንኛውም ሁኔታ አስፈላጊውን የንጽሕናና የጤና ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፤

፫. የመመገቢያና የማብሰያ ዕቃዎች ለምግባ አገልግሎት ከመዋላቸው በፊት እና በኋላ መታጠብና ንህጽናው እንዲጠበቅ ማድረግ አለባቸው፤

፬. የምግብ አብሳዮች የጤና ሁኔታ በየጊዜው ክትትልሊደረግበት ይገባል፤ በየሶስት ወሩ ደግሞ የጤና ምርመራ ሊደረግላቸው ይገባል፤

፭. ምግብ አብሳዮች ከታመሙ ታክመው መዳናቸው በህክምና ሳይረጋገጥ ምግብ ማዘጋጀት የለባቸውም፡፡

፱. <u>ስለሴቶች ንጽህና መጠበቂያ</u>

ምገባ በሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች ላሉ ሴት ተማሪዎች ኤጀንሲው የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ በነጻ ያቀርባል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለኃላፊነትና ተግባር</u>

፲. <u>የኤጀንሲው ኃላፊነትና ተግባር</u>

ኤጀንሲው በአዋጁ የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. የምገባ መርሐ ግብር ቀጣይነት ያለውና ተመሳሳይ የአመጋገብ ሥርዓት በከተማ ደረጃ እንዲኖር ያደርጋል፤

፪. ምገባ በሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚካሄደውን የተማሪዎች የምገባ መርሐ-ግብር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፫.ለተማሪዎች የምገባ መርሐ ግብር መስፈጸሚያ ድጋፍ በዓይነትና በገንዘብ ያሰባስባል፣ በፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል፤

፬. ከሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ፤ ከጤና ቢሮ፤ ከትምህርት ቢሮ ከምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ከንግድ ቢሮ፣ ከደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ከፋይናንስ ቢሮ እና ከውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፤

፭. መርሃ ግብሩ በሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ለምግብ ዝግጅትና ለመመገቢያ አመቺ ቦታዎች መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፤

፮. ለተማሪዎች ዕድገትና ጤና የሚመጥን የምግብ ዝርዝር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ ያዘጋጃል፤ በተዘጋጀው የምግብ ዝርዝር መሠረት መቅረቡን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፯. የተማሪዎች የምገባ መርሐ ግብር በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል፣ ባህሪ፣ አካላዊና አዕምሮዊ ዕድገት ላይ ያመጣውን ለውጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያጠናል ወይም እንዲጠና ያደርጋል፤

፰. በምግብ ዝግጅት ላይ ከሚሰማሩ ማህበራት ወይም ግለሰቦች ጋር ውል ይዋዋላል፤ በምግብ አቅርቦር፣ በጤና አጠባብቅ እና ተያያዥነት ባላቸው የተማሪዎች ምገባ ሂደት ላይ ጥፋት አጥፍተው ከተገኙ የስራ ውላቸው እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡

፲፩. <u>የትምህርት ቢሮ ተግባርና ሃላፊነት</u>

በሌሎች ሕጎች ለቢሮው የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. በምገባ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ ያደራጃል፣ ለኤጀንሲው ያሳውቃል፤

፪. በምገባ መርሐ-ግብር የሚሳተፉ ተማሪዎች በየዕለቱ ተገቢ አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፫. የትምህርት ቤቶችን አደረጃጀትና የሰው ኃይል በመጠቀም የምገባ ሂደቱን የዕለት ተዕለት ክትትል ያደርጋል፤

፬. የቁሳቁስ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያ እና የደንብ ልብስ ድልድል ያከናውናል፤

፭. አቅርቦቱ አካል ጉዳተኞችንም እንደየጉዳታቸው አይነትና ባህሪ ፍላጎታቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፮. በቂ የማብሰያና የመመገቢያ ቦታዎች በትምህርት ቤቶች እንዲዘጋጁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፡፡

፲፪. <u>የፋይናንስ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌሎች ሕጎች ለቢሮው የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. በተማሪዎች ምገባ፤ ቁሳቁስ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያ እና የደንብ ልብስ ግዢ የሚውል ተገቢ የሆነ መመሪያ ያወጣል፤ወይም ያሻሽላል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤

፪.የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፫.ኤጀንሲው ወቅታዊና አስተማማኝ የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖረው ያደርጋል፤

፬.ለቁሳቁስ ድጋፍ፣ መርጃ መሳሪያ እና የደንብ ልብስ የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፭. በተግባር አፈጻጸም ላይ አስቸኳይ ወይም ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በፋይናንስ ጉዳይ ላይ አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፡፡

፲፫. <u>የጤና ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌሎች ሕጎች ለቢሮው የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. ጤና ጣቢያዎች ለምግብ አብሳዮች የሚያደርጉት የጤና ምርመራ ደረጃውን የጠበቀና ታአማኒነት ያለው እንዲሆን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
፪. የምግብ አብሳይና መስተንግዶ ሠራተኞችን በየሶስት ወር የጤና ምርመራ በማድረግ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
፫. ምግብ አብሳዮችና በሂደቱ ውስጥ ለሚሳተፉ አካላት በምግብ አዘገጃጀት፣ አቀራረብና ጤና አጠባበቅ ግንዛቤ ይፈጥራል፤
፬. የምገባ ትግበራ ከክፍለ ከተማና ወረዳ ጤና ፅህፈት ቤት ጋር ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል፡፡

## ፲፬.የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

በሌሎች ሕጎች ለቢሮው የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. የምግብ አቅራቢዎችን በዋናነት ከተደራጁ የተማሪ ወላጆች እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤
፪. ለተለዩትን አቅራቢዎች የምግብ ዝግጅትና አቀራረብ ላይ ሙያዊ ስልጠናእንዲያገኙ ያደርጋል፤
፫. ለምግብ አቅራቢነት ተለይተው ስልጠና የወሰዱትን በማህበር እንዲደራጁና እውቅና እንዲኖራቸው ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሰራል፤

## ፲፭. የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ባለስልጣኑ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. የማብሰያና መመገቢያ ቦታዎችን ማከማቻ መጋዘኖችን የጥራት ደረጃ ይፈትሻል፤ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤
፪. ለምግብ ዝግጅት የቀረቡ ግብዓቶችን ጥራትና ደህንነት ይፈትሻል፤ የማስተካከያ እርምጃም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
፫. የምግብ አብሳዮች የጤና ምርመራ ምስክር ወረቀት ስለመኖሩ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤

፬. የምግብ አዘገጃጀት ደህንነትን ድንገተኛ ፍተሻ በማከናወን ማረጋገጫ ይሠጣል፤

፭. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ተግበራትን ያከናውናል፡፡

፲፮.የንግድ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ቢሮው የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩. የምግብ አቅራቢዎች የምግብ ግብዓቶች አቅርቦት እንዲያገኙ ከጅምላ አከፋፋይ የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፪. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ተግበራትን ያከናውናል፡፡

፲፯. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. ከምገባ ጣቢዎች የሚወገዱ የምግብ ትርፍራፊዎችና የተለያዩ ተረፈ ምርቶች የሚወገዱበት ስልት ይቀይሳል፤

፪. የተከማቸን ደረቅ ቆሻሻ በፍጥነት ከአካባቢው እንዲነሳ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፫. ስለ ደረቅ ቆሻሻ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ በምገባ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑ አካላት ግንዛቤ ያስጨብጣል፤

፬. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ተግበራትን ያከናውናል፡፡

፲፰.የውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ባለስልጣኑ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡-
የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩. የተማሪዎች የውሀ አቅርቦት ከምገባው ፕሮግራም ጋር በማጣመር ልዩ ክትትል ያደርጋል

፪. የምገባ ፕሮግራም በሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች የፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት ችግር ካለ በዘላቂነት እንዲፈታ ያደርጋል፤

፫. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ተግበራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፱. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ስኬታማነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፳. ተጠያቂነት

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በፍትሐብሔር ወይም በወንጀል ወይም በሁለቱም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### ፳፩. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ይህንን ደንብ ለማስፈጸም እንደአግባብነቱ ቦርዱ ወይም ኤጀንሲው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፳፪. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ካቢኔው ያወጣው ደንብ፣ ወይም ሌላ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### ፳፫. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከየካቲት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲፫ ቀን ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንደርን ማዕከል ያደረገ አሳታፊ አስተዳደር ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ፻፲፫/፪ሺ፲፪</u>

በከተማው ውስጥ በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎችና የመልከም አስተዳደር ማስፈን ስራዎች ማህበረሰቡ በተሟላ መልኩ የሚሳተፍበት እና ነዋሪው ሕዝብ የልማቱ ፍትሃዊ ተጠቃሚ የሚሆንበትን፤ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን አገልግሎት በግልጽነት፣በተጠያቂነት እና በፍትሃዊነት መርህ መሠረት እንዲያገኝ ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ በመሆኑ፤

ህብረተሰቡ በመንደሩ ወይም በሚኖርበት አካባቢ ያሉትን ችግሮች በመፍታት የመንግስት መዋቅሩን በመደገፍ እንዲሰራ፣ ችግሮችን በጋራ እንዲፈታ፣ ነጻና ግልጽ በሆነ መልኩ ማሳተፍ ለሁለንተናዊ ለውጥ ወሳኝ በመሆኑ እንዲሁም ዜጎች የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግስት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ፣ የህዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ እንዳለበት በመደንገጉና ይህን ተግባራዊ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፤

ነዋሪዎች ስለከተማው የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ ሀሳብና ጥያቄ የማቅረብ እና መልስ የማግኘት መብት እንዳላቸው በከተማው ቻርተር አዋጅ አንቀጽ ፺ የተደነገገ  በመሆኑ እነዚህ መብቶችና ተግባራት እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ኃላፊነት ወስዶ የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና የሚመራ አስፈጻሚ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፺፮ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

<u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርመንደርን ማዕከል ያደረገ አሳታፊ አስተዳደር ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፲፫/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

<u>፪. ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዉ፤

፪. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፤

፫. "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነዉ፤

፬. "ካቢኔ" ማለት የከተማው ካቢኔ  ነዉ፤

፫."መንደር" ማለት በአንድ በመንገድ በተከለለ ሰፈር በተከታታይ የሚኖሩ ነዋሪዎች ያሉበት አነስተኛው መዋቅር አካል ነው፤

፬. "አሳታፊ አስተዳደር" ማለት ነዋሪው በመንደሩ ያሉትን ችግሮች በመፍታት የመንግስት መዋቅሩን በመደገፍ እንዲሰራ ችግሮችን በጋራ እንዲፈታ ነጻና ግልጽ በሆነ መልኩ ማሳተፍ ነው፤

፭. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. የፆታ አገላለፅ

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፤ ዓላማ፤ ስልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት

፬. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንደርን ማዕከል ያደረገ አሳታፊ አስተዳደር ማስተባበሪያ ኤጀንሲ (ከዚህ በኃላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፡፡

፫. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ መንደርን ማዕከል ያደረገ አሳታፊ አስተዳደር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ሊደራጅ ይችላል፡፡

፫. ዓላማ

፩. መንደርን ማዕከል ያደረገ የህብረተሰብ ተሳትፎን በማጎልበት በህዝብና በከተማው አስተዳደር መካከል ያለውን ግንኙነት ማሳደግ፤

፪. ነዋሪዎችን በማሳታፍ የከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን አገልግሎት በእኩልነት፣ በግልጽነት እና ፍትሃዊነት መርህ መሠረት እንዲያገኙ ማድረግ፤

፫. በከተማው አስተዳደር የልማት ዕቅዶችና በአፈጻጸማቸው ሂደት ነዋሪው ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ እና የልማቱም ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል፤

፬. የነዋሪውን መስተጋብርና ትስስር በማጠናከር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በነዋሪው ንቁ ተሳትፎ እንዲቀረፉ ማድረግ፡፡

፭. የኤጅንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. መንደርን ማዕከል አድርጎ የተደራጀውን እና የሚደራጀውን ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ያጠናክራል፣ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤

፪. ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር ተቋማትና አካላት ጋር በመቀናጀት በመንደር የተደራጁ ማህበረሰብ አቀፍ ኮሚቴዎች ችግሮቻቸው የሚፈቱበት እና ጥያቄዎቻቸው ምላሽ የሚያገኙበት

ሁኔታ ያመቻቻል፤ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲያጋጥሙ በየደረጃው ላሉት አስተባባሪ ኮሚቴዎች ከመፍትሔ ሀሳብ ጋር ያቀርባል፤ ይከታተላል፤

፫.የመንደሩ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲቀረፉ ነዋሪው በባለቤትነት እና በፍላጎት እንዲደራጅ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ስለአደረጃጀቱም የህግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ በማድረግና በማፀደቅ ሥራዎችን ይመራል፤ ያስተባብራል፤

፬.በዚህ ደንብ መሠረት ለሚከናወነው የተለያዩ የልማት ስራዎች ከህብረተሰቡ የሚሰበሰብ ሀብት አሰባበሰብ፣ አጠባበቅ፣ አጠቃቀም፣ አስተዳደር፣ ኦዲት አደራረግና ተጓዳኝ ተግባራት የሚከናወኑበት የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭. አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በማፈላለግ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድ የአካባቢውን ህብረተሰብ የልማት ሥራ ያግዛል፤ ከህብረተሰቡ የሚሰበሰቡ የቁሳቁስ፤ የጉልበትና፤ የገንዘብ መዋጮዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፮. በመንደር በነዋሪው የተለዩ ፍላጎቶች የሚሟሉበትን እና የተለዩ ችግሮች የሚፈቱበትን ዕቅድ ከመንደር ኮሚቴ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፯. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመንደሮች መካከል በሚኖሩ ማናቸውም የማህበረሰብ ተሳትፎ ስራዎች እንዲቀናጁ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

፰. የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የአካባቢ ልማት ግንባታ ሥራዎች አጠናክሮ ነዋሪውን በማስተባበርና በማሳተፍ ማስቀጠል የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የጥናት ሥራዎች ያከናውናል፤ ሲፀድቁ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፱. በመንደር ውስጥ የተሰሩ ማንኛውም የልማት ስራዎች በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ከመንደር ኮሚቴው ጋር በመሆን ተገቢውን ሁሉ ይፈጽማል፤

፲. በመንደር በተምሳሌትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሁሉ-ገብ የህብረተሰብ ተሳትፎ ያደረጉ እና የልማት ስራዎችን ያከናወኑትን የመንደር ኮሚቴዎች በመለየት እውቅና እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ልምዳቸውን ይቀምራል፤ ወደሌሎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፲፩. ከከንቲባው የሚሰጡትን እና ሌሎች ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል።

፯. <u>ስለአደረጃጀት</u>

ኤጀንሲው፡-

፩. አስተባባሪ ኮሚቴዎች፣

፪. በከንቲባው የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤

፫.ሌሎች አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል።

፰.<u>ስለ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት</u>

፩. በየደረጃው ስራዎችን የሚያስተባብር መንደርን መሠረት ያደረገ አሳታፊ አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተደራጅቷል፤

፪. የከተማ ኮሚቴ

ሀ. የከተማው ከንቲባ ----------------ሰብሳቢ፣

ለ. ከህብረተሰብ የሚወከል-ምክትልሰብሳቢ፣

ሐ. የኤጀንሲው ኃላፊ ------------------ፀሀፊ፣

መ. እንደአስፈላጊነቱ በከንቲባው የሚሰየሙ ከስራው ጋር አግባብነት ያላቸው አስፈጻሚ አካላት፣ የሕዝብ አደረጃጀቶች እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች-------------------------------- አባል፤

<u>፫. የክፍለ ከተማ ኮሚቴ፡-</u>

ሀ. የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ-----ሰብሳቢ፣

ለ. ከህብረተሰብ የሚወከል---------ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ--------------------------ፀሐፊ፣

መ. እንደአስፈላጊነቱ በክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰየሙ ከስራው ጋር አግባብነት ያላቸው የሌሎች የክፍለ ከተማው አስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች ---------------------------አባል፤

<u>፬. የወረዳ ኮሚቴ፡-</u>

ሀ. የወረዳ ዋና ስራ አስፈጻሚ --------------ሰብሳቢ፣

ለ. ከህብረተሰብ የሚወከል-------ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ------------------------ፀሐፊ፣

መ. የመንደር ወይም የብሎክ ኮሚቴ አደረጃጀት ሰብሳቢዎች----------------------------------አባል፣

ሠ. እንደአስፈላጊነቱ በወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰየሙ ከስራው ጋር አግባብነት ያላቸው የወረዳው አስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች፣ የሕዝብ አደረጃጀቶች እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች---- ------አባል፤

፭. <u>የመንደር ኮሚቴ፡-</u>

በቀጥታ በነዋሪው የሚመረጥ የመንደር ወይም የብሎክ ኮሚቴ ሲሆን ብዛቱ ስራውን ለማስተባበር እንዲያመች ከ ፭-፯ ሆኖ ይደራጃል፡፡ ዝርዝር አደረጃጀትና አሰራር በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፱. <u>የኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

በየደረጃው ያለው ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. በተደራጁበት እርከን ያለውን የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤

፪. የኤጀንሲውን ዓላማ ለማስፈጸም የሚረዱ የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

፫. በየደረጃው ያለውን የኮሚቴ የሥራ ዕቅድ እና አፈጻጸም ይገመግማል፤

፬. በህብረተሰብ ተሳትፎ የሚሰሩ ተግባራትን ይለያል፤ ተግባራዊ እዲሆኑ ለኤጀንሲው ያስተላልፋል፤

፰. የህብረተሰብ ተሳትፎን የሚያጎለብቱ ሌሎች ስልቶችን ይቀይሳል፡፡

፲. <u>የኮሚቴዎች ስብሰባ</u>

፩. የከተማው ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፤

፪. የክፍለ ከተማው ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፤

፫. የወረዳው ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በሳምንት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተጠቀሱት ኮሚቴዎች የየራሳቸውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

፲፩. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ተባርና ኃላፊነት</u>

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ኤጀንሲውን ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት ሠራተኛ ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለከንቲባው ያቀርባል፣ በከተማው ምክር ቤት ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ.ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ የሥራ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ሠ. የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለከንቲባው ያቀርባል፤

ረ.የኤጀንሲውን የሂሳብ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል፤

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌ</u>

፲፪. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በከተማው አስተዳደር ይመደባል፡

፲፫. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩. ኤጀንሲው የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖሩታል፤

፪. የኤጀንሲውን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም እሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

፲፬. ተፈጻሚነት ስለማይኖረው ሕግ

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ካቢኔው ያወጣው ደንብ፤ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈነ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም

፲፭. መመሪያ የማውጣት ስልጣን፤

ኤጀንሲው ይህንደንብለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከየካቲት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓመተ ምህረት

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ